# የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔዎች



## ቅጽ -21

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት**

የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔዎች ቅጽ -21




የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
ድረ-ገጽ፡- www.fsc.gov.et
ስልክ፡- +251 111 55 34 00
ፋክስ፡- +251 111 56 55 83
የመ.ሣ.ቁ፡- 6166
ነፃ የስልክ ጥሪ፡- 992

# የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት

# ሰበር ችሎት ውሣኔዎች

**ቅጽ-21**

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍ/ቤት

የጥናትና ህግ ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

ጥር 2010 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

## የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎች ዝርዝር ማውጫ ሰንጠረዥ /ቅፅ 21/

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| **አሠሪና ሠራተኛ** | | | | | 1 |
| 1. | አንድ ሠራተኛ የሥራ መሪ ሆኖ ሥራውን ሲመራ በፈጸማቸው ማናቸውም ክንውኖች ምክንያት በተወሰደበት እርምጃ ሊያነሳቸው የሚችላቸው የመብት ጥያቄዎች የሥራ መሪው በሂደት ወደ ሠራተኛ የሥራ መደብ የተዛወረ ቢሆንም እንኳን በፍትሐብሔሩ ድንጋጌዎች የሚገዙ ስለመሆናቸው<br>*አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 3/1፣3/2/ሐ* | 130685 | ወጋገን ባንክ<br>እና<br>አቶ አናጋው ገበየሁ | ሕዳር 13 ቀን 2009 ዓ.ም | 2 |
| 2. | አንድ ሠራተኛ በራሱ ፈቃድ ስራ በሚለቅበት ጊዜ የሠላሳ ቀናት የማስጠንቀቂያ ጊዜ አለመስጠቱ የተረጋገጠ እንደሆነ ለሰራተኛው ከሚከፈለው ክፍያ ከሰላሳ ቀናት ክፍያ ያልበለጠ ካሳ ለአሰሪው ሊከፍል የሚገባ ስለመሆኑ፣<br>*አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 31፤አንቀጽ 45* | 119448 | አዲስ ጋዝና ፕላስቲክ ፋብሪካ ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>አቶ ሰለሞን ኃይሌ | ታህሳስ 06 ቀን 2009 ዓ.ም | 6 |
| 3. | በመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚፈጸም ጊዜያዊ ቅጥር ውል ሊከተላቸው ስለሚገባ መስፈርቶች | 132714 | ዶ/ር ደስአለኝ ተመስገን<br>እና | ታህሳስ 28 ቀን 2009 | 9 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | መንግስት መስሪያ ቤት የሚደረግ የጊዜያዊ ሰራተኛ ቅጥር ውል ለፕሮጀክት ስራ ካልሆነ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣<br>*አዋጅ ቁ. 515/99 አንቀጽ 22/3/፣93*<br>*የኢ.ፌ.ድ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ህዳር 18/2005 በቁጥር መ80-893/1/ የተጻፈ ደብዳቤ*<br>*የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በቁጥር ሲሰመ30/መ/18/22/459 በ16/04/2005 የተጻፈ ደብዳቤ* | | የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ | ዓ.ም | |
| 4. | ከቅጥር ውል በመነጨ ግንኙነት የሚጠየቅ ማንኛውም ክስ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ ፣<br>የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው በመብቱ ለመጠቀም ከሚችልበት ቀን ቀጥሎ ካለው ቀን ጀምሮ ስለመሆኑ፣<br>*አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162/1/፣163/1/* | 136981 | የሐረር ቢራ ፋብሪካ አ.ማህበር<br>እና<br>እነ አቶ አለሙ ነጋሽ<br>(ሰላሳ ዘጠኝ ሰዎች) | ሐምሌ 19 ቀን 2009 ዓ.ም | 17 |
| 5. | አንድ አሠሪ የቀጠረውን ሠራተኛ በሙከራ ጊዜ አጥጋቢ ውጤት አላሳየህም በማለት የሥራ ውሉን ያለምንም ማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ መብት የሚኖረው በህጉ አግባብ የተደረገ የሙከራ ጊዜ | 140781 | ታደሰ እንጆሪ ሆቴልና ጠቅላላ ንግድ ስራ ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና | ሐምሌ 18 ቀን 2009 ዓ.ም | 22 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስምምነት መኖሩ ሲረጋገጥ ብቻ ስለመሆኑ፣<br>*አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 11/1/ /2/ እና /3/* | | ወ/ሪት ሉላ ዘሪሁን | | |
| 6. | ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠረን ሠራተኛ የሥራ ውሉ የሚቋረጥበት ጊዜ ሲደርስ አሰሪው ማሰናበት የሚችል ሲሆን ስንብቱ ከህግ ውጪ ነው ሊያሰኝ የማይችል ሲሆን በዚህ አግባብ የተሰናበተን ሰራተኛ የሥራ ሥንብት ክፍያ ሊያገኝ ይገባል የማያስብል ስለመሆኑ፣<br>*አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 24/1/፣ አንቀጽ 30/1/* | 138054 | የላሊበላ ማር ሙዝየም<br>እና<br>ወ/ሮ ማሬ በዛ | ሐምሌ 28 ቀን 2009 ዓ.ም | 26 |
| 7. | ማንኛውም ወገን የይርጋው ጊዜ ካለፈ በኋላ የይርጋ ጊዜን እንደመቃወሚያ አድርጎ ለማንሳት ያለውን መብት ሊተው የሚችል ስለመሆኑ፣<br>ዳኞች በገዛ ስልጣናቸው የይርጋውንም ደንብ መከላከያ ለመጥቀስ የማይችሉ ስለመሆኑ፣<br>*አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 165/5/፤ የፍ/ሕ/ቁ. 1856/2/* | 142752 | በከልቻ ትራንስፖርት አ/ማህበር<br>እና<br>አቶ ወልደሰንበት ዳዲ | ሐምሌ 27 ቀን 2009 ዓ.ም | 30 |
| 8. | በኮንትራት /በጊዜያዊነት/ የተሰጠ አገልግሎት ለጡረታ ተግባር ስለሚያዝበት አግባብ | 130944 | አቶ ተሞገስ ወ/መላክ<br>እና | ሐምሌ 26 ቀን 2009 | 34 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | *አዋጅ ቁጥር 345/1995 ፤በአዋጅ ቁጥር 907/2007* | | የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ | ዓ.ም | |
| 9. | ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ቢያንስ 10 ዓመት ያገለገለ እና በራሱ ፈቃድ ወይም በአዋጅ ከተጠቀሱት ውጪ በሆነ ምክንያት አገልግሎት ካቋረጠ የጡረታ መውጫ እድሜው ሲደርስ የአገልግሎት ጡረታ አበል ለዘለቄታው ሊከፈለው የሚችል ስለመሆኑ<br>*የመንግስት ሰራተኞች ጡረታ(ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር907/2007 አንቀጽ 5/2/፤በአንቀጽ 18* | 132861 | እነ አቶ እርጋጤ መድበው<br>እና<br>የመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ- | ሐምሌ 28 ቀን 2009 ዓ.ም | 38 |
| 10. | በሥራ ላይ የደረሰ የአካል ጉዳት ወደ ዘላቂ የአካል ጉዳት ከተሸጋገረ የካሣ ጥያቄው የይርጋ ጊዜ መነሻ መቆጠር ያለበት ጉዳቱ ከደረሰበት ጊዜ ሳይሆን ዘላቂ የአካል ጉዳት መሆኑ ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ ስለመሆኑ<br>*አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162(1)* | 134188 | አቶ ዊንታ ቦርጄ<br>እና<br>ይርጋለም ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር | ሐምሌ 28 ቀን 2009 ዓ.ም | 42 |
| **የፍትሐ ብሔር ሥነ- ሥርዓት** | | | | | **46** |
| 11. | ክስን ከማሻሻል ጋር በተያያዘ ፤ፍ/ቤት ክስ እንዲሻሻል ከፈቀደ | 104621 | ወ/ሮ አዜብ ታምሩ | ህዳር 13 | 47 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | በኃላ የቀረበውን ክስ የሚሻሻልበትን ነጥብ ተገቢነት መመርመር ያለበት ከመፍቀዱ በፊት ስለመሆኑ እና ክሱ የተሻሻለበት ነጥብ ፍቃድ ከተሰጠበት ነጥብ ውጭ ከሆነም በውሳኔው ላይ መግለፅ ያለበት ስለመሆኑ ፤ *ፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 91 እና 216 (3)* | | እና አቶ ደጀኔ ዘውዴ | ቀን 2009 ዓ.ም | |
| 12. | ያለዋጋ ወይም በደመወዝ የሚሰጥ አደራ ሰጭና አደራ ተቀባይ ስምምነት ካላደረጉ በስተቀር በአደራ የሚቀመጥ ዕቃ ዋጋ የማይከፈልበት ስለመሆኑና አደራ ሰጭው አደራ ተቀባዩ ዕቃውን በመልካም አያያዝ ለማኖር ያወጣውን ወጭ ሁሉ ሊከፍለው የሚገባ ስለመሆኑ፣ *የፍ/ሕ/ቁ. 2788 እና 2793/2/* | 119571 | አቶ ባብሶ ቃልቦሬ እና ወ/ሮ ኩዘይማ ሁሴን | ህዳር 14 ቀን 2009 ዓ.ም | 50 |
| 13. | ከሳሽ ወገን ያለፍርድ ቤት ፈቃድ በተወው ወይም በሰረዘው ነገር ሌላ ክስ ለማቅረብ የማይችል ስለመሆኑ፣ *የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.፤278፤ 279/1/* | 116860 | ወ/ሮ አስቴር ሌንጂሳ እና እነ ወ/ሮ ሸታዬ ግርማ /ሁለት ሰዎች/ | ታህሳስ 26 ቀን 2009 ዓ.ም | 54 |
| 14. | በህግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ተቋማት በድሃ ደንብ ዳኝነት ሳይከፍሉ ለመስተናገድ በማስረጃ ሊያቀርቡት ስለሚገባቸው | 121938 | የድሬ እንጭኒ ወረዳ መንገዶች ባለስልጣን | ታህሳስ 27 ቀን 2009 | 58 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ጉዳዮች<br><br>*የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.467-479* | | እና<br>አንጭኒ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ | ዓ.ም | |
| 15. | በልዩ አዋቂነት ጉዳዩን የያዘው ፍርድ ቤት በሒሳብ አጣሪነት የሾመው ባለሙያ ለማጣራቱ ሥራ ይረዳው ዘንድ ሊቀርቡለት የሚገቡ ጠቃሚ ማስረጃዎች ከአንደኛው ተከራካሪ ወገን ወይም በሁለቱም ወገን ተከራካሪዎች ወይም በሌላ ሶስተኛ ሰው ሳያቀርቡለት ቢቀሩ ሊከተላቸው ስለሚገቡ እርምጃዎች<br>*በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 132፣136፣145(1)እና 250* | 97023 | የአ/አ ከተማ አስተዳደር መንገዶች ባለስልጣን<br>እና<br>አቶ አምባቸው ፈቀደነህ | ታህሳስ 28 ቀን 2009 ዓ.ም | 63 |
| 16. | አንድ ፍ/ቤት ክስ ቀርቦለት ጉዳዩን የማየት ሥረ ነገር ስልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን የዘጋው እንደሆነ ዋናውን ክርክር እንዳላየ የሚያስቆጥር ሲሆን በመዝገቡ ላይ የሰጣቸው ማናቸውም ትእዛዞች በማናቸውም ወገን ላይ ህጋዊ የሆነ አስገዳጅነት ውጤት የሌለውና በዚሁ ጉዳይ ለሚመለከተው ፍ/ቤት መዝገቡ ቢቀርብ ከዚህ ቀደም በፍርድ ያለቀ ነው ሊያስብል የማይችል ስለመሆኑ | 100295 | አቶ ደጓለ ገዳሙ<br>እና<br>ላይኩን ሙሉጌታ<br>(አራት ሰዎች) | ህዳር 26 ቀን 2009 ዓ.ም | 70 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | *የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.5፣9 እና 231* | | | | |
| 17. | ተከራካሪ ወገኖች ባላነሱት የመከራከሪያ ነጥብ ወይም የግራ ቀኙ ወገኖች ባልተለያዩበት ጉዳይ እንዲጣራ በማድረግ ውሳኔ መስጠት ተገቢ ስላለመሆኑ፣ *የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 241፣242* | 124669 | የሳስኮ ኢንዱስትሪያል ንግድና ት/ት ድርጅት እና የኢ.ፌ.ድ.ሪ ት/ትሚኒስቴር | ህዳር 30 ቀን 2009 ዓ.ም | 74 |
| 18. | አንድ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ከተከራካሪ ወገኖች አንዳቸው በስር ፍ/ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ አቤቱታ ሲያቀርቡለት በስር ፍ/ቤት የታዩ ሰነዶችን ወይም መታየት የነበረባቸውን ሰነዶች አስቀርቦ ሳይመረምር በይግባኙ ላይ ውሳኔ፣ ፍርድ ወይም ትእዛዝ መስጠት የሌለበት ስለመሆኑ፣ *የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 145/1/* | 99474 | እነ ወ/ሮ ሙሉነሽ ደሬሳ እና እነ ወ/ሮ ማሚቱ ጌታቸው | ህዳር 30 ቀን 2009 ዓ.ም | 78 |
| 19. | በክርክር ተሳታፊ ያልሆነ ወገን በስር ፍርድ ቤት በተሰጠ እግድ ትዕዛዝ የዕግድ ትዕዛዙን ለሰጠው ፍ/ቤት የዕግድ ይነሳ አቤቱታ ሳያቀርብ በቀጥታ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይግባኝ የሚያቀርብበት እና የዕግድ ትዕዛዙ ላይ ውሣኔ የሚያሰጥበት ስርዓት የሌለ ስለመሆኑ *በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 154፣158* | 123833 | አቶ ለሜሳ ደገፉ እና የአዳማ ከተማ ማዘጋጃ ቤት | መጋቢት 29 ቀን 2009 ዓ.ም. | 87 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 20. | በክስ አቀራረብ ሥርዓት ላይ ጉድለት ያለበት መሆኑ ተረጋግጦ የተዘጋ መዝገብ ምንም አይነት ክስ እንዳልቀረበ የሚያስቆጥርና የይርጋ ጊዜ የማቋረጥ ውጤት የሌለው ስለመሆኑ<br>*የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 278 (2) (ሀ) እና (3)* | 123123 | አቶ ተኽሊት አፈርቂ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን | ሚያዚያ 16 ቀን 2009 ዓ.ም | 92 |
| 21. | በአጭር ስነ ሥርዓት ክስ ሊቀርብ ስለሚችልበት አግባብ<br>*በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 284* | 124552 | አቶ ምትኩ አበበ<br>እና<br>የከሰረውሆላንድ ካር ኃ/የተ/የግ/ማሕበር | ሚያዝያ 16 ቀን 2009 ዓ.ም. | 95 |
| 22. | የሥር ፍ/ቤት በጭብጥነት ይዞ በአግባቡ ባጣራው ፍሬ ጉዳይ ላይ በይግባኝ ፍርዱን የሚመለከተው ፍ/ቤት ያለበቂና ህጋዊ ምክንያት የተጣራውን ፍሬ ነገር በድጋሚ እንዲጣራ ወደ ሥር ፍ/ቤት መመለስ ተገቢ ስላለመሆኑ<br>*የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.136(1)፣343(1)* | 127580 | የኢትዮጲያ መንገዶች ባለስልጣን<br>እና<br>ዲኖ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር | ሚያዚያ 26 ቀን 2009 ዓ.ም | 100 |
| 23. | የከሳሽ ተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ሊቀርብ የሚችለው በከሳሽ ወገን ላይ ብቻ ሥለመሆኑ<br>ተከሳሽ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ሲያቀርብ ሊከተለው ሥለሚገባ | 102668 | ማክሲመም ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>(ሁለት ሰዎች) | ሰኔ 12 ቀን 2009 ዓ.ም | 105 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ሥነ-ሥርዓት<br><br>*የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 30፣36፣224 እና 234(1)(ረ)* | | እና<br>የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/የሆሳህና ከተማ ቤቶች ልማት ፕሮጀክት ፅ/ቤት | | |
| 24. | በጠፋው ሰው መሞት ምክንያት መብት የሚያገኙ ሰዎች በመብታቸው መጠቀም የሚችሉት መጥፋቱን የሚወስነው ፍርድ የመጨረሻ ከሆነ በኃላ ስለመሆኑ<br>*የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 165(1)* | 132208 | ወ/ሮ ጸሀይ አጎናፍር<br>እና<br>አቶ ጌራ ላቀው | ሰኔ 28 ቀን 2009 ዓ.ም | 114 |
| 25. | • አንዱን የፍትሓብሔር ክስ ባንድ ወይም ካንድ በበለጡ ፍርድ ቤቶች ዘንድ ለማቅረብ የሚቻል ሲሆን የክሱ ማመልከቻ በቀደምትነት የቀረበለት ፍርድ ቤት ብቻ የዳኝነት ሥልጣን እንዳለው ተቆጥሮ ለክርክሩ ውሳኔ ሊሰጥ የሚችል ሥለመሆኑ<br>• አንድን ሰው በመወከል በፍርድ ቤት ቀርቦ ለመሟገት በህጉ የተቀመጠውን የዝምድና ደረጃ ወይም በህጉ የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟላ የውክልና ስልጣን | 131622 | ወ/ሮ አልማዝ እምሩ<br>እና<br>ወ/ሮ አይጠገብ ቀሬ | ሰኔ 20 ቀን 2009 ዓ/ም | 119 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የሚያስፈልግ ስለመሆኑ<br><br>*የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 7(2)፣32፣57፣58 እና 63* | | | | |
| 26. | ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ክሶች ወይም ይግባኞች መጣመር በነበረባቸው ሰዓት ሣይጣመሩ ቢቀሩና የግራ ቀኙን የተለያየ መብት በሚያጎናፅፍ ሁኔታ ቢወሰን እነዚህን ውሳኔዎች ተጣጥሞ እንዲፈፀሙ ማድረግ ተገቢ ሥለመሆኑ<br>*የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.11* | 113613 | በደቡብ ወሎ ዞን የለገሂዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ፅ/ቤት<br>እና<br>ሰለሞን አባይ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ | ግንቦት 30 ቀን 2009 ዓ.ም | 125 |
| 27. | በፍርድ ቤት የቀረበ ጉዳይ የክስ ምክንያት አለው ብሎ ለመወሰን የሚቻለው በክሱ ላይ የተገለፀው ነገር ቢረጋገጥ ከሳሹ የጠየቀውን ዳኝነት ለማግኘት ሕግ የሚፈቅድለት የሆነ እንደሆነ ስለመሆኑ፡-<br>ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብ እና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ፡-<br>*የኢፌድሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37(1)* | 136775 | ህዳሴ 1ኛ ደረጃ ከፍተኛ አገር አቋራጭ የህዝብ ባለንብረቶች ማህበር<br>እና<br>የፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን | ሐምሌ 19 ቀን 2009 ዓ.ም | 130 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| ንብረት | | | | | 134 |
| 28. | በኦሮሚያ ክልል የገጠር መሬት አጠቃቀም ህግ መሰረት ግጭትና አለመግባባትን በመጀመሪያ በአስታራቂ ሽማግሌዎች እንዲፈቱ የሚደነገጉት ድንጋጌዎች አርሶ አደር ከአርሶ አደር በሚያደርገው የሚፈጠርን አለመግባባትን ለመፍታት እንጂ በህግ ወለድ እና በአንድ አርሶ አደር ሰዎች መካከል የሚፈጠርን አለመግባባት ጭምር የሚያካትት ሥላለመሆኑ<br>*አዋጅ ቁጥር 130/99 አንቀፅ 16* | 102406 | የወንጂ ሸዋ ስኳር ፋብሪካ<br>እና<br>አቶ ባጫ አለሙ | ህዳር 9 ቀን 2009 ዓ/ም | 135 |
| 29. | የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ጋር በተያያዘ ሻጭ ንብረቱን ከ3ተኛ ወገን ይዞታና ቁጥጥር ነፃ በማድረግ የማስረከብ ግዴታ እና ገዥ ከተረከበ በኃላ ንብረቱ የእኔ ነው ባይ ቢመጣ ሻጩ በዋቢነት የመቆም ግዴታ የተለያየ ግዴታ ስለመሆኑ፤<br>*ፍ/ብ/ሕ/ቁ 2875 ፣ 2274 ፣ 2880 ፣ 2881 ፣ 2882 ፣2879፣ 2888 ፣1206 ፣ 1195 ፤ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 33(2) 36(4) እና 40 (2)* | 100395 | ወ/ሮ አማረች ማሬ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ሜሪ ታደሰ<br>( ሦስት ሰዎች) | ህዳር 29 ቀን 2009 ዓ.ም | 138 |
| 30. | የእርሻ መሬት ይዞታን ከማስለቀቅ ጋር በተገናኝ የሚቀርብ ክስ ከእርሻ መሬት ልዩ ባህሪ አንጻር ከንብረቱ የሚገኘውን አላባ | 120087 | አቶ አስራት ኩምሳ<br>እና | ታህሳስ 07 ቀን 2009 | 146 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ወይም ሌላ ጥቅም ጭምር ከዋናው ክስ ጋር አጣምሮ ይክሰስ ሊባል ስለማይችል፣<br>*የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216/3/፣218/ሀ/*<br>*አዋጅ ቁ. 452/1997 አንቀጽ 12*<br>*የአ/ክ የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ ቁ. 130/1999 አንቀጽ 16 ደንብ ቁ. 151/2005 አንቀጽ 18* | | እነ ጉደታ በዳዳ<br>(ሁለት ሰዎች) | ዓ.ም | |
| 31. | በትግራይ ክልል የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ መሰረት ወራሽ የሌለው መሬት በቀበሌው የገጠር መሬት አስተዳደር ኮሚቴ መሬት ለሌላቸው ከተሸጋሸገ በኂላ የሚቀርብ አቤቱታ ከመሬት ዳኝነትና ከፍርድ ቤት ውሳኔ ውጭ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣<br>*አዋጅ ቁ. 239/2006 አንቀጽ 14/8/*<br>*ደንብ ቁ. 85/2006 አንቀጽ 22/1//ሀ/፣21/8/* | 121663 | አቶ ሀጋዚ ዘውድ<br>እና<br>ወ/ሮ ረኸብ ቸኮል | ታህሳስ 25 ቀን 2009 ዓ.ም | 152 |
| 32. | በአማራ ክልል የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ መሰረት መሬት በኑዛዜ ተላልፎልኛል የሚል አካል ኑዛዜው ተቀባይነት እንዲያገኝ ሊያደርገው ስለሚገባ እርምጃ<br>*የአ/ክ/የመ/አጠቃቀም አዋጅ ቁ. 133/98* | 115399 | እነ አቶ ተስፋዬ ተሾመ<br>(ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>ሞላን ወልደ | ታህሳስ 24 ቀን 2009 ዓ.ም | 156 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | *ደንብ ቁ. 51/99ን ለማስፈጸም የወጣው መመሪያ አንቀፅ 13/1/2/* | | (ሁለት ሰዎች) | | |
| 33. | በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ መሰረት ስጦታው በተደረገበት የእርሻ መሬት ላይ በቤተሰብነት የተመዘገበ አባልን ያገለለ መሆኑ ከታወቀ ይኸው ሰነድ በህግ ተቀባይነት የማይኖረው ስለመሆኑ<br><br>ህጉን ያልጠበቀ የገጠር መሬት ይዞታ በኑዛዜ ወይም በስጦታ ተላልፏል የሚለው ወገን መብቱን ለማስጠበቅ በሁለት ዓመት መጠየቅ ነበረበት ሊባል የሚችል ስላለመሆኑ<br>*በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2441፣*<br>*አዋጅ ቁጥር 456/97*<br>*የአ/ብ/ክ/መ/የመ/አስ/አጠቃቀም አዋጅ ቁ. 133/98 አንቀጽ 16/3 ፣*<br>*ደንብ ቁጥር 51/99 አንቀጽ 11/2* | 125186 | ወ/ሮ አዛል አይናለም<br>እና<br>እነ አቶ ምህረት በላይ (ሁለት ሰዎች) | ሰኔ 26 ቀን 2009 ዓ.ም. | 160 |
| 34. | በደቡብ ክልል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ መሰረት በወረዳ በተጀመረ ክርክር በክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ከፀና ውሳኔው የፀናበት ወገን ለተጨማሪ ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ | 114670 | እነ አቶ ባንኩ ኢሩስ<br>(ሁለት ሰዎች)<br>እና | ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም | 163 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ይግባኝ ሰሚ ችሎት ማቅረብ የሚችል ስለመሆኑ፣<br>*የኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3//ሀ/*<br>*የደቡብ ክልል ህገ መንግስት አንቀጽ 75/2/ሐ/*<br>*የከ/ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁ. 43/1994 አንቀጽ 5/3/*<br>*የፌደራል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁ. 456/1997 አንቀጽ 12*<br>*የደ/ክ/የገጠር መሬት አጠቃቀም አዋጅ ቁ. 110/1999 አንቀጽ 12/4/* | | አቶ ሳምሶን ገ/ዮኃንስ | | |
| 35. | የገጠር መሬት ሕጋዊ በሆነ ሁኔታ አግባብ ባለው አካል በስጦታ የተላለፈለት ተጠቃሚ ለረጅም ጊዜ ተጠቃሚ የሆነበት መሬት መሆኑ ከተረጋገጠ መሬቱ በስጦታ ሰጪዉ ስም ተመዝግቦ መገኘቱ እና ግብር በስሙ መከፈሉ ብቻ ይዞታዉ በስጦታ ዉል አልተላለፈም የሚያሰኝ ወይም በመሬቱ ላይ ያለዉን የባለይዞታነቱን መብት የማያስቀር ስላለመሆኑ<br>*የኦሮሚያ ክልል ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀፅ 2/3፣9(5)* | 122740 | አቶ ጤና ጋርደዉ<br>እና<br>ወ/ሮ መደቅሴ ገርቢ | ሚያዚያ 30 ቀን 2009 ዓ.ም | 170 |
| 36. | የመንግስት ቤት ተከራይቶ የሚኖሩ ሰዎች የባለቤትነት መብት | 115387 | እነ አቶ መክብብ ተስፋ | ሚያዚያ 26 | 175 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | (የመፋለም ክስ) የመጠየቅ ክስ ማቅረብ የሚችሉበት ህጋዊ ምክንያት ስላለመኖሩ<br>*የፍ/ሕ/ቁ. 1205* | | (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ፀሐይ ለገሰ<br>(ሁለት ሰዎች) | ቀን 2009 ዓ.ም | |
| *የዳኝነት ስልጣን* | | | | | *180* |
| 37. | የአዲስ አበባ ከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ቀደም ብሎ በሰጠው ፍርድ ላይ የሚቀርብለትን የፍርድ መቃወሚያ ተቀብሎ የመዳኘት ስልጣን ያለው ስለመሆኑ፣<br>*የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358፣የኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37/1/ አዋጅ ቁ. 721/2004* | 121660 | አቶ ለገሰ ገለታ<br>እና<br>እነ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ<br>(ሁለት ሰዎች) | ህዳር 26 ቀን 2009 ዓ.ም | 181 |
| 38. | በህገወጥ መንገድ ተይዘው በተገኙ የቁም እንስሳት ላይ አግባብ ያለው አካል በሚወስደው እርምጃ ላይ በቀጥታ ክስ ስልጣን ላለው ፍ/ቤት ማቅረብ የሚቻል ስለመሆኑ፣<br>*የቁም እንስሳት ግብይት አዋጅ ቁጥር 819/2006 አንቀጽ 15/5/* | 129430 | የእነማይ ወረዳ ንግድ ትንስፖርት ጽ/ቤት<br>እና<br>አቶ ጉበዜ አሰፋ | ታህሳስ 26 ቀን 2009 ዓ.ም | 188 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | *እና 8 ደንብ ቁጥር 341/2007 አንቀጽ 19/4/ እና 5* | | | | |
| 39. | የተጨማሪ እሴት ታክስ የፌዴራል ታክስ በመሆኑና የክልል የገቢዎች ቢሮዎች ታክሱን የሚያስተዳድሩት በዉክልና ስልጣናቸዉ በመሆኑ ምንም እንኳ ታክሱ የተወሰነዉ በክልሉ የገቢዎች ቢሮ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እና የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ቢሆንም የሕግ ስህተት አለበት የሚል ወገን ይግባኝ ማቅረብ የሚገባዉ ስልጣን ላለዉ የፌዴራል ፍ/ቤት ወይም የዉክልና ስልጣን ላለዉ የክልል ፍ/ቤት ሥለመሆኑ<br><br>*አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 28(2) እና አንቀጽ 30፣አንቀጽ 43(3)፣ 112* | 123986 | አቶ መቻልደጉ ሰሙር<br>እና<br>የሚዛን አማን ከተማ ገቢዎች ባለስልጣን ቅ/ጽ/ቤት | ግንቦት 18 ቀን 2009 ዓ.ም | 192 |
| 40. | የአንድ ሃገር ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ብሔራዊ የዳኝነት(judicial jurisdiction) ስልጣን አለው ለማለት ሊወሰዱ ስለሚገባቸው ዝርዝር ነጥቦች | 183200 | እነ ማጂኮን ኮንስትራክሽን ሊ.ትድ(ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>አቶ ታትገኝ ፊጣሞ ወሌቦ (አራት ሰዎች) | ሰኔ 27 ቀን 2009 ዓ.ም | 197 |
| 41. | የሊዝ ውል እንዲሰረዝ የሚቀርብን የዳኝነት ጥያቄን በተመለከተ | 119435 | አቶ አብዱልቀኒ አብዱራህማን | ሰኔ 27 ቀን | 201 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | መደበኛ ፍርድ ቤቶች ሊያስተናግድ የሚገባ ስለመሆኑ | | እና<br>እነ አቶ ዳንኤል ወ/ጋዋሪያት(ሁለት ሰዎች) | 2009 ዓ.ም. | |
| ጉሙሩክ | | | | | 204 |
| 42. | የተሻረው ህግ ይሰራ በነበረበት ጊዜ የተፈጸመ ወንጀል ሲኖርና በአዲሱ ህግ ግን እንደወንጀል ያልተቆጠረ ሲሆን ድርጊቱ ሊያስከስስም ሆነ ሊያስቀጣ የማይችልና የተጀመረውን ክስም የማቋረጥ ህጋዊ ውጤት ያለው ስለመሆኑ<br>*የኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 21(2)፣ የኢ.ፌ.ድ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 5/3/*<br>*አዋጅ ቁ. 622/2001 አንቀጽ 99፣ አዋጅ ቁ. 859/2006* | 111960 | ወ/ሮ አባይነሽ ፈቀደ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>የሺ ኃይሌ | ሕዳር 06 ቀን 2009 ዓ.ም | 205 |
| 43. | አንድ ግብር ከፋይ የሂሳብ መዝገብ እና ሰነድ ካልያዘ ወይም በማናቸውም ምክንያት የሂሳብ መዝገቡን እና ሰነዱን የግብር አስገቢው ባለስልጣን ያልተቀበለው እንደሆነ ወይም ግብር ከፋዩ በሕጉ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ገቢውን ያላስታወቀ እንደሆነ ግብር አስገቢው ባለስልጣን የግብሩን ልክ በግምት ሊወስን የሚችል | 133773 | አቶ ተክሌ ፈረጃ ጋዲሳ<br>እና<br>የኢ/ያ ገ/ጉ/ ባለስልጣን የመርካቶ ቁ.1 | ሐምሌ 14 ቀን 2009 ዓ.ም | 209 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስለመሆኑ፡- *የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 69* | | | | |
| ውል | | | | | 213 |
| 44. | አንድ ዕቃ ለመሸጥ /በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ለማስረከብ/ የተዋዋለ ወገን ከዕርሱ አቅም በላይ በሆነ ችግር ምክንያት ውሉን መፈጸም ባልቻለ ጊዜ በቅድሚያ ለዚሁ ስራ የተቀበለውን ገንዘብ ከወሰደበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ከመመለስ ውጭ ውሉን ባለመፈጸሙ ምክንያት ለደረሰው ኪሳራ እንዲከፍል የማይገደድ ስለመሆኑ፣ *ፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2356/1/* | 117036 | ፀጉ ብርሃን ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና ኮሎኔል ይትባረክ አማረ | ህዳር 12 ቀን 2009 ዓ.ም | 214 |
| 45. | በጽሁፍ በተደረገ ውል አንደኛው ወገን ውሉን ለማሻሻል ሲፈለግ ዋናው ውል በፅሁፍ እስከተደረገ ድረስ ማሻሻያውም በዛው አግባብ መሆን ያለበት ሥለመሆኑ<br>በጽሁፍ በተደረገ ውል አንደኛው ወገን የውል ማሻሻያ ጽሁፍ ለሌላኛው ወገን ሲላክልት ሌላኛው ወገን ሊቀበለው እንደሚችል ሲደነግግ ውሉን ለመቀበሉ ግን የተለየ ስርዓት ካለማስቀመጡ በተጨማሪ በምክንያታዊ ጊዜ ውሉን ያለመቀበሉን ካላስታወቀ | 120150 | እሌ ኢንተርናሽናል ቢዝነስ ሀ/የተ/የግ/ማህበር እና ፋርም አፍሪካ የኢትዮ ፕሮግራም | ታህሳስ 5 ቀን 2009 ዓ.ም | 224 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ውሉን እንደተቀበለ የሚቆጠር ስለመሆኑ፣<br>*የፍ/ሕ/ቁ. 1722፣2625* | | | | |
| 46. | የሊዝ ውል ሊቋረጥ ወይም ሊፈርስ ስለሚችልባቸው መሰረታዊ ምክንያቶች<br>*የሊዝ አዋጅ ቁ. 272/94 አንቀጽ 15/1/* | 109194 | የጎንደር ከተማ አስተዳደር አገልግሎት ጽ/ቤት<br>እና<br>እስማኤል አህመድ ሃላፊነቱ የተ/የግ/ማህበር | ታህሳስ 25 ቀን 2009 ዓ.ም | 230 |
| 47. | በተዋዋይ ወገኖች መካከል የተደረገ ውል የፍቃድ ጉድለት ስለመኖሩ ማሳያ ሊሆኑ ከሚችሉ ጉዳዮች ውስጥ ከተዋዋይ ወገኖች በአንዱ ውልን ለማፍረስ የሚያስችል ጉዳይ መኖሩን ማሳየት ሲቻል ስለመሆኑ፣<br>*የፍ/ሕ/ቁ. 1696፣1710/2/* | 114398 | ወ/ሮ ደስታ ኪዳነ<br>እና<br>ወ/ሮ አመቴ ኤርታቦ | ታህሳስ 25 ቀን 2009 ዓ.ም | 235 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 48. | የዱቤ የቤት ሽያጭ ውል የወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል ህገ ወጥ ውል ነው በማለት በውሉ መሰረት ላለመፈፀም የሚቀርብ ክርክር ህጋዊ መሰረት የሌለው ስለመሆኑ<br>*የፍትሓ ብሔር ህግ ቁጥር 1792 ንዑስ አንቀጽ 1፣1793* | 119233 | አያት አክሲዮን ማህበር<br>እና<br>ወ/ሪት ክፍለሚካኤል ተክሌ | ሚያዚያ 17 ቀን 2009 ዓ/ም | 240 |
| 49. | የዕቃ አቅርቦት ውል በአቅራቢው ባለመፈፀሙና ለተወሰደ ቅድሚያ ክፍያ እንዲሆን የቅድሚያ ክፍያ የዋስትና ሰነድ የሰጠ አካል ውል አቅራቢው በውል የገባውን ግዴታ ባለመፈፀሙ ምክንያት በሰጠው የዋስትና ሰነድ መሠረት ከዋናው ባለዕዳ ጋር በአንድነትና በነጠላ ኃላፊነት ያለበት ስለመሆኑ | 106994 | ብሔራዊ የኢትዮጲያ ኢንሹራንስ /ኢ.ማ/<br>እና<br>እነ የአብክመ ዘላቂ ግብርና ተሃድሶ ኮሚሽን | ሚያዚያ 24 ቀን 2009 ዓ.ም | 248 |
| 50. | የህብረት ሥራ ማህበር ውስጥ ያለ የማህበር አባል ዕጣውን ወይም ጥቅሙን ሲያስተላልፍ ሊከተለው ስለሚገባ አካሄድ<br>*አዋጅ ቁ.147/91 አንቀፅ 19* | 113013 | ወ/ት ማህሌት እንዳለ<br>እና<br>እነ አቶ አህመድ አለም<br>(ሁለት ሰዎች) | ሚያዚያ 25 ቀን 2009 ዓ.ም | 254 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 51. | በህጉ አግባብ በሕግ ፊት የጸና የወለድ አገድ ዉል መደረጉ ባልተረጋገጠበት የወለድ አገድ ዉል ተቋቋሚል ማለት ስላለመቻሉ<br>*የፍትሐ ብሐር ሕግ ቁጥር 3052፣ 3053፣3117–3130* | 117953 | አቶ ሰብስቤ አበበ<br>እና<br>ወ/ሮ ፍቅርተ ካህሳይ | ሚያዚያ 30 ቀን 2009 ዓ.ም | 258 |
| ከውል ውጪ ኃላፊነት | | | | | 262 |
| 52. | በተሽከርካሪዎች ላይ የደረሰን ጉዳት በተመለከተ የገበያ ዋጋ አስልቶ ግምት ለማቅረብ በህግ ለትራፊክ ፖሊስ የተሰጠ ተግባር ስላለመሆኑ<br>የተሽከርካሪ ዋጋ ግምት የመተመን አገልግሎት መስጠት የትራንስፖርት ባለሥልጣን ስለመሆኑ<br>በአንድ ንብረት ላይ የደረሰው ጉዳት ጠቅላላ ጉዳት (total loss) በሚሆንበት ጊዜ በንብረቱ ላይ የደረሰውን አጠቃላይ ግምት ከመጠየቅ ውጪ ይገኛል ተብሎ የሚታሰበውን ገቢ መጠየቅ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ<br>*አዋጅ ቁ.681/2002 አንቀፅ 2(25)፣37(2(ሐ)*<br>*አዋጅ ቁ.468/97 አንቀፅ 7(1(ዘ)) የፍ/ሕ/ቁ.2090(1)፣2092 እና 2119(1)(2)* | 127587 | ፐርፌክት ትራንዚትና ትራንስፖረት ኃ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>አቶ አህመድ ዳውድ | ሚያዚያ 16 ቀን 2009 ዓ.ም | 263 |
| ***ቤተሰብ*** | | | | | ***269*** |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 53. | ባልና ሚስት የጋራ የሆነውን የንግድ ድርጅታቸውን መልካም ስም የማከራየት መብትና በቤቱ ውስጥ የሚገኘውን የንግድ ዕቃ የመከፋፈል መብት ያላቸው ስለመሆኑ፣ <br> *የን/ሕ/ቁ. 127* | 117164 | ወ/ሮ ተክአ ሐጎስ <br> እና <br> አቶ ፀጋዬ ገ/ጻዲቅ | ታህሳስ 25 ቀን 2009 ዓ.ም | 270 |
| 54. | ጋብቻ የተፈጸመው በአንድ ክልል ውስጥ እና በዚያው ክልል ሕግ መሰረት ሆኖ ክስ በቀረበበት ጊዜ ተጋቢዎቹ የሚኖሩት በተለያዩ ክልሎች ውስጥ መሆኑ ቢረጋገጥ እንኳ ከፍቺ እና መሰል ጥያቄዎች ጋር ተይይዘው የሚነሱ ጉዳዮችን የማስተናገድ የስረ ነገር ስልጣን በክልሉ ሕግ መሰረት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የተሰጠው የክልሉ ፍርድ ቤት እንጂ ተጋቢዎቹ መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች ውስጥ እንደሆነ ተቆጥሮ ጉዳዩ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር የሚወድቅ ስላለመሆኑ <br> *አዋጅ ቁጥር 25/1988 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 5 (2)* | 127714 | ወ/ሮ ቃልኪዳን ይኸነው <br> እና <br> አቶ ኢብሳ ያደታ | መጋቢት 26 ቀን 2009 ዓ.ም. | 275 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 55. | በሌላ አገር ህግ እና በኢትዮጵያ የቤተሰብ ህግ መካከል እንደባልና ሚስት አብረው በመኖር ግንኙነት ውስጥ የተፈራ ንብረት የጋራ እንዲሆን ለመወሰን በሁለቱም ህጎች መካከል ግጭት መኖር ያለመኖሩን የሌላኛው አገር ህግ እንዲቀርብ በማድረግ መወሰን የሚገባው ስለመሆኑ<br>በዓለም አቀፍ የግለሰብ ህግ /Private International law/ መሠረት በዘርፉ እውቀት ያለ ወይም ምሁር /Scholar/ የሰጠውን አስተያየት በማስረጃነት ሲቀርብ የቀረበውን አስተያየት እንደማንኛውም ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን አስተያየቱ የቀረበለት ፍርድ ቤት ስለመሆኑ<br>*የኢ.ፌ.ድ.ሪ ቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 5፣102 /1/* | 123132 | አቶ ከሳሁን ታደሰ<br>እና<br>ወ/ረ ፀዳለ ሀፍታይ | ሚያዝያ 30 ቀን 2009 ዓ/ም | 279 |
| 56. | ለህፃን ልጅ ማሳደጊያ ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለበት ወላጅ፣ የሚከፍለውን የገንዘብ መጠን በተመለከተ ለመወሰን ግምት ውስጥ ሊገቡ ስለሚገባቸው ሁኔታዎች<br>*የተሻሻለው ፌዴራል የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 197 (2) ፣202* | 130931 | አቶ በላይ ዘለቀ<br>እና<br>ወ/ሮ ትዕግስት ዳባ /የህፃን ሀሴት በላይ ሞግዚት/ | ሰኔ 19 ቀን 2009 ዓ.ም | 284 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 57. | በፌደራል የቤተሰብ ህግ መሰረት በአባት በኩል ያለን መወለድ የመካድ ክስ በማቅረብ መቃወም ስለሚችሉ ሰዎች<br>*የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 177/1-3* | 129933 | አቶ አየለ ወ/አለማው<br>እና<br>እነ ወ/ሮ እመቤት ማሞ<br>(ሁለት ሰዎች) | ሰኔ 28 ቀን 2009 ዓ/ም | 288 |
| ***ውርስ*** | | | | | ***292*** |
| 58. | የውርስ ንብረት የመከፋፈል ጥያቄ ንብረቱ በአይነት ተለይቶና ተገምቶ እስከቀረበ ድረስ በቀረበው ግምት መሰረት የፍርድ ቤቶችን የስረ ነገር ስልጣን ሊወሰንበት የሚገባ ስለመሆኑ<br>*የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 18፣23* | 124313 | እነ ወ/ሪት ቅድስት ዮሴፍ<br>(ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ምስራቅ አለማየሁ<br>(ሶስት ሰዎች) | ሚያዚያ 16 ቀን 2009 ዓ.ም | 293 |
| 59. | ፍ/ቤት የሚችን ኑዛዜ ፈራሽ መሆን አለመሆን ላይ ተመስርቶ በሚቀርብለት የዳኝነት ጥያቄ ላይ አግባብ ያለው ዳኝነት ከመስጠት አልፎ በኑዛዜ የሚደርሳቸውን ድርሻ በትክክል ለይተው ሳይጠይቁ የውርስ ንብረት መጠን ግምት በመቀመጡ ብቻ ይኼው ግምት መሰረት ተደርጎ ሊፈጸም የሚችል ዳኝነት ስላለመኖሩ<br>*ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 182(1)* | 135694 | እነ አቶ ይርዳው ሽፈራው<br>(አምስት ሰዎች)<br>እና<br>እነ አቶ መስፍን ሽፈራው<br>(አስር ሰዎች) | ሐምሌ 20 ቀን 2009 ዓ.ም | 298 |
| ***ንግድ*** | | | | | 302 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 60. | በአንድ የህብረት ስራ ማህበር ውስጥ አባል የሆነ ሰው በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ በአካል ተገኝቶ ድምፅ መስጠት ያለበት ስለመሆኑ እና ይህ ሁኔታ /አጠቃላይ መርህ/ ሊታለፍ የሚችለው መረጃ ሊቀርብበት የሚችል ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ሲያጋጥም ስለመሆኑ፣<br>*አዋጅ ቁጥር 147/91 /በአዋጅ ቁጥር 402/96 እንደተሻሻለ አንቀጽ 18/2/* | 110149 | ምድር ሎዛ የጋራ ሕንጻ መኖሪያ ቤት የህብረት ስራ<br>እና<br>አቶ ይህደጎ ኪዳኔ | ታህሳስ 27 ቀን 2009 ዓ.ም | 303 |
| 61. | ቼክ የብድር ዉልን ተክቶ ብድር መኖሩን ለማስረዳት አግባብነት ያለዉ ሰነድ ነዉ ለማለት የሚያስችል የሕግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ<br>በብድር የተሰጠዉ ገንዘብ 500 /አምስት መቶ/ የኢትዮጵያ ብር በላይ ሲሆን የብድሩ ዉል በጽሑፍ ወይም በፍ/ቤት በተደረገ የእምነት ቃል ወይም መሐላ ካልሆነ በቀር ለማስረዳት የማይቻል ሥለመሆኑ<br>*ንግድ ሕጉ ቁጥር 827 /ሀ/ እና 854*<br>*የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2472(1)* | 123984 | አቶ ጌታቸዉ መሸሻ<br>እና<br>አቶ ተሾመ ወልዴ | ሚያዚያ 25 ቀን 2009 ዓ.ም | 308 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 62. | አንድ የውጪ ዜግነት ያለው ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ በሚካሄደው ኢንቨስትመንት ውስጥ አክሲዮንን በመግዛት ለንግድ ስራ ምቹ የሆነ ህንፃ በማሰራት የሥራ መስክ ሊሳተፍ የሚችል ስለመሆኑ<br>አንድ የባለአክሲዮኖቹ ጉባኤ ሕግን፣ መመስረቻ ፅሑፍንና መተዳደሪያ ደንብን በመከተል የተደረገ እስከሆነ ድረስ በሕጉ ጥበቃ የሚያገኝ ስለመሆኑ<br>*አዋጅ ቁጥር 769/2004 አንቀጽ 12(1ሀ))፣ 2(6) እና 38*<br>*ደንብ ቁጥር 270/2005 አንቀጽ 3*<br>*የን/ሕ/ቁጥር 416(1)* | 118246 | የሲዳሞ ተራ ህንጻ ስራ አክሲዮን ማህበር<br>እና<br>ወ/ሮ አብረኸት ሀብተእዝጊ ተማኑ ወራሾች<br>(ዘጠኝ ሰዎች) | ሰኔ 23 ቀን 2009 ዓ.ም | 312 |
| 63. | ቼክ አምጪው በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ባንክ ሣያቀርብ ይህንኑ ጊዜ አሳልፎ አንድ ዓመት ሣያልፍ ባንክ አቅርቦ በቼክ አውጪው ስም በቂ ስንቅ የሌለው መሆኑን ያረጋገጠ ቼክ አምጪ ቼኩን መሰረት አድርጎ የሚያቀርበው ክስ አንድ ዓመት አላለፈም በሚል የሚያቀርበው ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ፣<br>በንግድ ህግ ቁጥር 881/1/ ስር በተመለከተው የአንድ ዓመት የጊዜ ገደብ ክስ የማቅረብ መብታቸው በህግ ፊት ተቀባይነት | 139932 | አስማማው በየነ<br>እና<br>አሰፋ ነጋሽ | ሐምሌ 20 ቀን 2009 ዓ.ም | 327 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ሊኖር የሚችለው በን/ሕ/ቁ. 855 ስር ቼኩን በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ለባንክ የማቅረብ ቅድመ ሁኔታ ሲያሟላ ስለመሆኑ፣<br>*የን/ሕ/ቁ. 855፣881/1* | | | | |
| ***ወንጀል*** | | | | | ***331*** |
| 64. | ወንጀል አድራጊው የመጀመሪያውን የጥፋት ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ሲል መሰረታዊ ከሆነው ወንጀል በኂላ አከታትሎ ያደረገው ድርጊት ከቀድሞ ሃሳቡና ሊደርስበት ካቀደው ግብ ጋር የተያያዘ ሆኖ ሲገኝ በዋናው ወንጀል ስር መጠቃለል የሚገባው ስለመሆኑ ፣<br>የወ/ሕ/ቁ. 61/3/ | 104637 | የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ<br>እና<br>ሙዑዝ ደስታ ገ/እግዚአብሔር | ታህሳስ 24 ቀን 2009 ዓ.ም | 332 |
| 65. | ሰውን ለአደጋ ማጋለጥ ወይም መተው ወንጀል ተፈጽሟል ለማለት ስለሚገባቸው ሁኔታዎች<br>*የወ/ሕ/ቁ. 57* | 132266 | ወ/ሮ አልማዝ አስፋው<br>እና<br>የኢትዮ ሱማሌ ክልል ዐ/ህግ | ታህሳስ 26 ቀን 2009 ዓ.ም | 338 |
| 66. | አንድ አሽከርካሪ በአንድ ቸልተኝነት ተግባር በተለያዩ ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት ሲያደርስ የወንጀል ሕግ ቅጣቱን ከፍ ከሚያደርግበት በስተቀር በቸልተኝነት ተደሪራቢ አካል ማጉደል ወንጀል እንደፈፀመ ተቆጥሮ ተደራራቢ ወንጀል ክስ ሊቀርብበትና | 123046 | አቶ አዲሱ ገመቹ<br>እና<br>የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ዓ/ሕግ | የካቲት 29 ቀን 2009ዓ.ም | 345 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | በተደራራቢ ወንጀል በመፈፀም ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ የሚገባ ስላለመሆኑ<br>*የወንጀል ሕግ አንቀፅ 60(ሐ)፣61፣ 543(3)፣559(2)* | | | | |
| 67. | አንድ ተከሳሽ በወንጀል ተጠርጥሮ የጣት አሻራ ሰጥቷል በመባሉ ብቻ እንደጥፋተኛ ተቆጥሮ የወንጀል ጥፋት ሪከርድ እንዳለበት ተደርጎ ግምት በመውሰድና እንደ ቅጣት ማቅለያ ሳይያዝ የሚሰጥ ውሳኔ መሰረታዊ የህገ መንግስት መርህን የሚጣረስ ስለመሆኑ<br>*የወንጀል ህግ አንቀጽ 82* | 131705 | እነ አብርሃም ሰለሞን (ሦስት ሰዎች)<br>እና<br>የፌዴራል ዓ/ህግ | ሚያዚያ 16 ቀን 2009 ዓ.ም | 354 |
| 68. | በወንጀል ጉዳይ በኤግዚቪትነት የተያዘ ንብረት በፍርድ ውሳኔ የሚያገኘው በወንጀሉ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ሲሰጥ ለባለንብረቱ ይመለስ ወይም ለመንግስት ገቢ ይሁን ተብሎ ሲወሰን ወይም ተገቢውን የህግ ስርዓት ተከትሎ ሥልጣን ባለው አካል ትዕዛዝ ሲተላለፍ ስለመሆኑ | 126017 | የአርሲ ነገሌ ከተማ ፖሊስ ጽ/ቤት<br>እና<br>አቶ ተስፋአለም ገ/ሚካኤል | ሚያዚያ 26 ቀን 2009 ዓ.ም. | 358 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| 69. | ተከሳሽ በሚያቀርበው ይግባኝ መነሻነት ቅጣትን በማክበድ መወሰን መሰረታዊ የህግ ስህተት ስለመሆኑ<br>*የወንጀል መ/ስ/ስ/ሕ/ቁጥር 196(2* | 131088 | አቶ ኀይትኦም ግደይ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን | ሚያዝያ 30 ቀን 2009 ዓ.ም. | 362 |
| 70. | ዓቃቤ ህግ በቅድሚያ ያቀረበው ክስ ላይ ማስረጃዎቹን ካሰማና እንዲከላከሉ ታዞ የክሱ መሰማት በቀጠለበት ሂደት ላይ ያቀረበው ክስ ማሻሻል አቤቱታ ተቀባይነት ሲያጣ ይህንን በህጉ አግባብ በይግባኝ ከማሳረም በቀር ክሱን በማንሳት በሌላ መዝገብ አዲስ ክስ ማቅረብ ሥነ-ሥርዓታዊ ሥላለመሆኑ<br>*የወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 118/፣119፣38፣40/1/ እና 41፣* | 127312 | የአ/ብ/ክ/መ/ፍ/ቢሮ ዐቃቤ ህግ<br>እና<br>እነ አቶ እሸቱ ሉሌ ንጉሴ<br>(አራት ሰዎች) | ግንቦት 23 ቀን 2009 ዓ.ም | 367 |
| 71. | በአንድነት ተጣምረው መታየት የነበረባቸው የወንጀል ክሶች በተለያዩ ፍርድ ቤቶች ወይም ችሎቶች በተናጠል ታይተው የተለያዩ ቅጣቶች በተወሰኑ ጊዜ እንደገና በአዲስ መልክ እያንዳንዱ ቅጣት ተሰልቶና የቅጣት ማቅለያዎች ሁሉ ታይተው የሚወሰን ሳይሆን ሕጉ ጥፋተኛው በፈፀማቸው ተደራራቢ ወንጀሎች በአንድ ጊዜ ቢፈረድበት ኖሮ ሊወሰንበት ይችል ከነበረው ከፍተኛ ቅጣት ሳያልፍ መወሰን ያለበት ሥለመሆኑ | 110736 | አብዲ ኡመር ሰዒድ<br>እና<br>የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ | ሰኔ 23 ቀን 2009 ዓ.ም | 372 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | *የወንጀል ሕግ አንቀጽ 186(3)* | | | | |
| 72. | በወንጀል ጉዳይ ፍርድ ከተሰጠ በኋላ ይግባኝ የሚጠይቅ አካል ሊከተላቸው ስለሚገቡ ቅድመ ሁኔታዎች<br>*የወንጀል ሥነ- ሥርዓት ሕግ ቁጥር 187/1* | 134834 | የፌደራል ጠቅላይ ዓቃቢ ሕግ<br>እና<br>እነ ሽዋነሽ መንግስቱ (ሁለት ሰዎች) | ሰኔ 29 ቀን 2009 ዓ.ም | 375 |
| 73. | ፍርድ ቤቶች በተከሳሽ ላይ የሚጣለው ቅጣት ከወንጀል አፈጻጸሙ ሆነ ባህሪዉ እንዲሁም ከተፈፀመው ወንጀል ክብደት አንፃር ፍትሃዊ ውሳኔ ለመስጠት በቅጣት አወሳሰን መመሪያዉ መሠረት ለመወሰን የማያስችል ሆኖ በተገኘ ጊዜ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሰረት ምክንያቱን በማስቀመጥ በመመሪያው ከተቀመጠው በተለየ መልኩ ቅጣት ሊወስኑ የሚችሉ ሥለመሆኑ<br>*የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 አንቀፅ 21(1)*<br>*የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 88(2)* | 122766 | አቶ ሄኖክ ብሩክ አረጋ<br>እና<br>ፌዴራል ዓ/ህግ | ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም. | 379 |
| ***አፈፃፀም*** | | | | | 393 |
| 74. | በፍርድ አፈጻጸም ምክንያት ተይዞ የሚሸጠው የማይንቀሳቀስ | 124618 | እነ ወ/ሮ ደብካ መሰለ | ህዳር 22 | 394 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ንብረት ሁለት /ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች በህብረት የያዙት እና ያልተከፋፈሉት በሆነ ጊዜ ከተከፋዮቹ አንዱ ንብረቱን ለመግዛት በጨረታ ተወዳዳሪ ሆኖ የቀረበ እንደሆነ የፍርድ ባለእዳው እንደቀረበ ተቆጥሮ የቀዳሚነት መብት የሚሰጠው ስለመሆኑ፣ *የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 443፣ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 126/1/፣ 1386-1409* | | እና<br>ሣጅን ሀይሉ ሞገስ | ቀን 2009 ዓ.ም | |
| 75. | የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ነው የተባለ ንብረትን አፈፃፀምን በተመለከተ የንብረቱ ሕጋዊነት ላይ የሚመለከተው አስተዳደር አካል አግባብ ያለው ውሣኔ እስኪሰጥ ድረስ መሸጥ መለወጥ ባይቻልም ባለበት ሁኔታ የግራ ቀኙን እኩል ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ አግባብ በጋራ የሚያስተዳድሩበት ወይም ተከፋፍለው የሚጠቀሙበት ወይም አከራይተው ጥቅሙን እኩል የሚከፋፈሉበት ሁኔታ መመቻቸት ያለበት ስለመሆኑ *የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ 386/2/* | 121565 | ወ/ሮ ፍረወይኔ አብርሃ<br>እና<br>አቶ ገ/ጊዮርግስ ፀጋይ | ሚያዚያ 20 ቀን 2009 ዓ.ም | 399 |
| 76. | ሁለት ባለዕዳዎች በአንድነትና በነጠላ አንድን ዕዳ እንዲከፍሉ ከተፈረደባቸዉ ባለገንዘቡ ገንዘቡ እንዲከፈለዉ ሁለቱን ባለዕዳዎች በአንድነት ወይም አንደኛዉን ባለዕዳ ሙሉ ገንዘቡን እንዲከፍል | 118808 | አቶ ደስታ ንጉሴ<br>እና<br>አቶ ሐየሎም በላይ | ሚያዚያ 30 ቀን 2009ዓ.ም | 402 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ሊጠይቅ የሚችል ሥለመሆኑ<br>በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ ከሆኑት የፍርድ ባለእዳዎች አንዱ የፍርድ ባለዕዳ በዋናዉ ፍርድ ይግባኝ ጠይቆ የራሱን ኃላፊነት አስመልክቶ ፍርዱን አሸሮት ከሆነ ሙሉ እዳዉን ለመክፈል ኃላፊነት የሚኖርበት ይግባኝ ሳይጠይቅ በመቅረቱ ዋናዉን ፍርድ ባልተሻረለት ወይም ይግባኝ ጠይቆ ፍርዱ በጸናበት ሰዉ ላይ የሚሆን ስለመሆኑ<br>*ክፍ/ብ/ሕ/ቁ 1896፣ 1897* | | | | |
| 77. | በፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ ማናቸውም ንብረት በሐራጅ እንዲሸጥ በሚወሰንበት ጊዜ የሚሸጠው ንብረት ከትክክለኛው የዋጋ ግምት አላግባብ ከፍ ወይም ዝቅ ተደርጎል ብሎ የሚያስበው ወገን የጨረታው ቀን ከመድረሱ በፊት የጨረታውን ትዕዛዝ ለሰጠው ፍ/ቤት ግምቱ ተጋኗል በማለት መቃወሚያ ማቅረብ የሚጠበቅበት ሥለመሆኑ<br>በሁለተኛው የጨረታ ማስታወቂያ በተወሰነው ቀን ተጫራች ያልቀረበ እንደሆነ ለጨረታ የቀረበውን ንብረት የፍርድ ባለገንዘቡ ተረክቦ እንዲይዝ ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችለው የፍርድ ባለገንዘቡ | 128776 | አቶ ገ/ኢየሱስ ሃይሉ<br>እና<br>ዳዊት ልዑል | ግንቦት 16 ቀን 2009 ዓ.ም | 407 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | ንብረቱን ለመረከብ ፈቃደኛ ከሆነ ብቻ ስለመሆኑ<br>*የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 423/(1)(2)፣የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 428/2* | | | | |
| **አእምሯዊ ንብረት** | | | | | 412 |
| 78. | በንግድ ምልክት መመሳሰል በአንድ ምርት ወይም አገልግሎት ጋር በተገናኘ ሁኔታ የሕዝብ ግንዛቤ ያዛባ ወይም ሊያዛባ የሚችል፤ በሁለት ድርጅቶች መካከል መሳከርን የሚፈጥር ከሆነ ሕብረተሰቡ ሊያገኝ የሚገባው ሕጋዊ ጥበቃና ዋስትና በተሟላ ሁኔታ ተፈፃሚ ለማድረግ የሚያስችል በመሆኑ በተመሳሳይ የንግድ ምልክት ላይ ምዝገባ እንዲደረግ የሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>*አዋጅ ቁጥር 501/1998 አንቀፅ 7*<br>አዋጅ ቁጥር 320/1995 | 104755 | ዱራታ ባትሪ ካምፓኒ<br>እና<br>የኢትዩጵያ አዕምሯዊ ንብረት ፅ/ቤት | ህዳር 16 ቀን 2009 ዓ.ም | 413 |
| **ልዩ ልዩ** | | | | | 417 |
| 79. | ፍርድ ቤቶች የሥም ይቀየርልኝ ጥያቄ በሚቀርብላቸው ጊዜ የአመልካችን ስም መለወጥ አስፈላጊ የሚያደርጉ ሁኔታዎች መኖር አለመኖራቸውን በማስረጃ አጣርተውና የሶስተኛ ወገን ጥቅም የማይጎዳ ለመሆኑ ጭምር ካረጋገጠ በኋላ ተገቢውን | 120355 | ወ/ሪት ሐናን እስማኤል አብዱልዋሂድ<br>እና<br>የለም | ህዳር 6 ቀን 2009 ዓ.ም | 418 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | መወሰን ያለባቸው ስለመሆኑ<br>*አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41/1/ /1/* | | | | |
| 80. | በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ውስጥ አንድ ጠበቃ የጥቅም ግጭት ሊፈጥር በሚችልበት ሁኔታ የተለያዩ ተከራካሪዎችን በመወከል መከራከር የማይችልና ይሄንኑ ተግባር ፈፅሞ ሲገኝ እንደ ከባድ የሥነ -ምግባር ጥሰት ሊቆጠር የሚችል ስለመሆኑ<br>*የኦሮሚያ ክልል የጠበቆች እና ሕግ ጉዳይ ፀሃፊዎች እና ፍቃድ አሰጣጥ አዋጅ ቁ. 182/2005 አንቀፅ 36(3)*<br>*ደንብ ቁጥር 57/92 አንቀፅ 10፣11፣12 እና 13* | 110507 | አቶ ጉታ ጫካ<br>እና<br>የኦሮሚያ ፍትህ ቢሮ<br>(ሁለት ሰዎች) | ሕዳር 30 ቀን 2009 ዓ.ም | 422 |
| 81. | አንድ ዳኛ ተግባሩን በሚያከናውንበት ወቅት የፍርድ ስራ ስህተት ተፈጽሟል ከተባለ በይግባኝ ፣ በሰበር ወይም በሌላ በህግ በተዘረጋ ስርዓት ከማሳረም በቀር ስልጣንን አላግባብ ተጠቅሟል በሚል ሊቀጣ የማይችል ስለመሆኑ፣ | 108692 | የትግራይ ክልል ዓቃቤ ህግ<br>እና<br>አቶ ገብረሃርያ አሰፋ | ታህሳስ 4 ቀን 2009 ዓ.ም | 428 |
| 82. | አንድ ጠበቃ ከጅምሩ የሕግ መሠረት የሌለዉና አዋጭ አለመሆኑ የተረጋገጠን ወይም ተከራክሮ የመርታት ዕድል የሌለዉ መሆኑን | 128466 | አቶ እንዳልካቸዉ ይላቅ<br>እና | ሰኔ 29 ቀን 2009 ዓ.ም | 431 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | እያወቀ ደንበኛዉን አላስፈላጊ ለሆነ ክርክርና ወጪ መጋበዝ የሌለበት ስለመሆኑ<br>አንድ ጠበቃ የጥብቅና አገልግሎት ዉል ከመዋዋሉ በፊት ማስረጃ ሰብስቦ ማጠናቀቅ ወይም ምስክሮችን አስቀርቦ መጠየቅና የሚያዉቁትን አስቀድሞ ማወቅ የሚጠበቅበት ሥላለመሆኑ<br>*የደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 4* | | የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር ዐ/ሕግ | | |
| 83. | አንድን ጉዳይ በግልግል እንዲያይ የተቀመጠን የግልግል ዳኛ ከተከራካሪ ወገኖች በአንዱ እንዲነሳ ጥያቄ ሲቀርብ ዳኛው ገለልተኛ ወይም ነፃ ላይሆን የሚችልበት ግምት ለመውሰድ የሚያስችል ወይም ጥርጣሬን የሚፈጥር አከባቢያዊ ምክንያት መኖሩ ብቻ በቂ ሥለመሆኑ<br>*የፍ/ሕ/ቁ. 3340(2)፣3342* | 135094 | አቶ ዳዊት በላይ<br>እና<br>እነ አቶ ደነቀ አበበ<br>(ሁለት ሰዎች) | ግንቦት 21 ቀን 2009 ዓ.ም | 436 |
| 84. | በጡረታ አበል ተጠቃሚ ሆኖ በወንጀል ጥፋት ምክንያት ከሦስት ዓመት ያላነሰ ጽኑ እስራት የተፈረደበት የዘለቄታ የጡረታ አበል መብቱን ያጣ ባለመብት የተሻሻለው የጡረታ አዋጅ ከፀናበት ጊዜ ጀምሮ ውዝፍ አበል ሳይጨምር የጡረታ አበል የማግኘት መብት | 117151 | የመንግስት ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ<br>እና<br>ወ/ሮ ቸኮለ ሙሉጌታ | ህዳር 21 ቀን 2009 ዓ.ም | 440 |

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | የሚኖረው ስለመሆኑ፣<br>*አዋጅ ቁ. 907/2007 አንቀጽ 11/9* | | | | |
| 85. | በዕዳ አከፋፈል ሂደት የቀደምትነት መብትን ለመወሰን መታየት ያለበት ህጎች ከወጡበት ጊዜ አንፃር ሳይሆን በክርክሩ ለተያዘው ጉዳይ በልዩ ህግ /special law/ የተቋቋመው የቀደምትነት መብት ስለመሆኑ<br>*የአዋጅ ቁጥር 715/2003 አንቀጽ 11/12/ ፣ 57/(1)፤*<br>*አዋጁ ቁጥር 97/1990* | 122258 | አቢሲንያ ባንክ አክሲዮን ማህበር<br>እና<br>የኤ.ፌ.ድ.ሪ የግል ድርጅት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የደቡብ ሪጅን ፅ/ቤት | ሚያዚያ 30 ቀን 2009 ዓ.ም | 444 |

# አሠሪና ሠራተኛ

የሰ/መ/ቁ. 130685

ሕዳር 13 ቀን 2009 ዓ/ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

አብዩ ካሣሁን

እትመት አሰፋ

**አመልካች፡-** ወጋገን ባንክ -ነ/ፊጅ ቢንያም ትእግስቴ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ አናጋው ገበየሁ -ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

የጉዳዩ መነሻ የአሁን አመልካች በአሁን ተጠሪ ላይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡የተጠሪ ክስ ይዘት በአጭሩ ከጥቅምት 02 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ በተጠሪ ድርጅት ሥራ አሥኪያጅ ሆነው ሲሰሩ የነበረ እና መጋቢት 28 ቀን 2007 ዓ.ም በክሬዲት ቁጥጥር የሥራ ዘርፍ ተመድበው ሲሰሩ የነበረ መሆኑን፤አመልካች የተለያዩ ምክንያቶችን በመጥቀስ ከሥራ ያሰናበታቸው ቢሆንም የጠቀሳቸው ምክንያቶች ተቀባይነት የሌላቸው መሆኑን በመጥቀስ ስንብቱ ሕገወጥ ነው ተብሎ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት ሊከፈላቸው የሚገባ ክፍያ እንዲከፈላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አመልካች በሰጠው መልስ ተጠሪው የተሰናበቱት የብድር መያዣ የሆነውን የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ በሚመለከተው አካል ሳይመረመር እና ሳይፈቀድ በመቀየራቸው፤ ከተቀመጠላቸው የብድር ወሰን በላይ በመበደራቸው፤እራሳቸው ተበዳሪ እንዲሁም ባንኩን በመወከል አበዳሪ በመሆን ውል በመዋዋላቸው ምክንያት መሆኑን በመጥቀስ ጥፋታቸው ያለማስጠንቀቂያ የሚያሰናብታቸው በመሆኑ ስንብቱ ሕጋዊ ነው፤ሊከፈላቸው የሚገባ ክፍያም የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤት ተጠሪው ንብረት አጥፍተዋል በማለት አመልካች የተከራከረ ቢሆንም ተጠሪ አመልካቹ የጠቀሰውን የታግ ቁጥሩ WB/BU/CA/10-02-002 የሆነ ሠርቨር ሞኒተር አልተረከቡም በመሆኑም አመልካች ይህን አስመልክቶ የሰጠው ምክንያት ተቀባይነት የለውም፤በሌላ በኩል አመልካች የጠቀሳቸውን ሌሎች ጥፋቶች በተመለከተ አመልካች እነዚህ ጥፋቶች መፈጸማቸውን ያወቀው መጋቢት 17 ቀን 2007 ዓ.ም ሆኖ ተጠሪን ከሥራ ያሰናበተው ከ41 የሥራ ቀናት በኋላ ነው፤በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/3 መሠረት አሠሪው ጥፋት መፈጸሙን ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በ30 የሥራ ቀናት ውስጥ በመብቱ ካልተጠቀመ ይርጋ የሚያግደው በመሆኑ ስንብቱ ሕገወጥ ነው፤ተጠሪው በሥልጣን አለአግባብ መጠቀም ድርጊት የፈጸሙት በተለያየ ጊዜ በመሆኑ እና በድርጅቱ የሰው ሀይል መመሪያ ቁጥር 3.2.2.2 መሠረት ሥልጣንን አለአግባብ መጠቀም ለሁለተኛ ጊዜ ሲፈጸም ከሥራ የሚያሰናብት በመሆኑ የተጠሪ የሥራ ውል ያለማስጠንቀቂያ መቋረጡ ተገቢ ነው በመሆኑም የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ሊከፈል አይገባም በማለት አመልካች ለተጠሪው የካሣ ክፍያ ብር 82,572 / ሠማንያ ሁለት ሺህ አምሥት መቶ ሠባ ሁለት ብር /፤የሥራ ስንብት ክፍያ ብር 55,048 / ሀምሳ አምሥት ሺህ አርባ ሥምንት ብር / በድምሩ ብር 137,620 /አንድ መቶ ሠላሳ ሰባት ሺህ ሥድስት መቶ ሀያ ብር / እንዲከፍል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት አቤቱታው ውድቅ ተደርጓል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡-ተጠሪው የፈጸሟቸው ጥፋቶች የተፈጸሙት የሥራ መሪ በነበሩበት ወቅት ነው፤ይህንኑ በመጥቀስ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የለውም በማለት መቃወሚያ ያቀረብን ቢሆንም ግምት ውስጥ መግባት ያለበት ተጠሪ ከሥራ ሲሰናበት ሲሰራበት የነበረው የስራ መደብ ነው በማለት መቃወሚያችን ውድቅ መደረጉ ተገቢ አይደለም፤የተጠሪን ጥፋት በተመለከተ የኢንስፔክሽን ሥራ የተሰራው መጋቢት 17 ቀን 2007 ዓ.ም ቢሆንም ጉዳዩ ወደ ዲስፐሊን ኮሚቴ ተመርቶ የዲስፐሊን ኮሚቴው የውሳኔ ሐሳብ ያቀረበው ሚያዝያ 21 ቀን 2007 ዓ.ም በመሆኑ ተጠሪን የማሰናበቻ ጊዜ ሊቆጠር የሚገባው ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡የበታች ፍ/ቤቶች ጉዳዩን በዚህ አግባብ ተመልክተው መወሰን ሲገባቸው ይህን በመተላለፍ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ችሎት መታየት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ ለተጠሪው ጥሪ ተደርጎ ተጠሪ መልሳቸውን በጽሑፍ ሰጥተዋል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት በአጭሩ ለስራ ውሉ መቋረጥ መንስኤ የሆነው ምክንያት የተፈጸመው ተጠሪ የሥራ መሪ በነበርኩበት ጊዜ ቢሆንም መፍትሔ ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ተጠሪ ጥፋቱን የፈጸምኩ መሆን አለመሆኑ እና ጥፋቶቹ ከሥራ ለማሰናበት በቂ ናቸው? ወይስ

አይደሉም? የሚለው ነው፤አመልካቹ ተጠሪን ከሥራ የማሰናበት መብቱም በይርጋ ቀሪ የሆነ በመሆኑ የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ተገቢ ነው የሚል ነው፡፡አመልካቹም የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ይህ ችሎትም ወደዋናው ጉዳይ ከመግባቱ በፊት ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት የተጠሪን አቤቱታ አይቶ የማስተናገድ ሥልጣን አለው ወይስ የለውም የሚለው ነጥብ መታየት ያለበት ሆኖ ስላገኘነው ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

አመልካች ለስንብቱ ምክንያት ያደረጋቸውን በተጠሪው ተፈጽመዋል የተባሉት ጥፋቶች የተፈጸሙት ተጠሪ የሥራ መሪ በነበሩበት ጊዜ መሆኑን ተጠሪ አልካዱም፤ተጠሪው ለዚህ ችሎት በሰጡት መልስም ይህንኑ አረጋግጠዋል፡፡ አከራካሪው ጉዳይ ለተጠሪ ስንብት ምክንያት የሆኑት ጥፋቶች ተጠሪ የሥራ መሪ በነበሩበት ወቅት የተፈጸሙ ሆኖ የተጠሪ የሥራ ውል ሲቋረጥ ተጠሪ በሠራተኛ የሥራ መደብ ላይ የነበሩ መሆናቸው ጉዳዩን በሥራ ክርክር ችሎት እንዲታይ ያደርገዋል? ወይስ አያደርገውም? የሚለው ነው

የአዋጅ ቁጥር 377/96 ተፈጻሚነት በአሠሪ እና ሠራተኛ መካከል በሚደረግ በቅጥር ላይ በተመሠረተ የሥራ ግንኙነት ላይ መሆኑን ከአዋጁ አንቀጽ 3/1 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 3/2/ሐ በቅጥር ላይ በተመሠረተ ግንኙነትም ቢሆን አዋጁ በሥራ መሪ ላይ ተፈጻሚ እንደማይሆን ይደነግጋል፡፡ ከድንጋጌው ይዘት እና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው የሥራ መሪው የሥራ መሪ ሆኖ ሥራውን ሲመራ በፈጸማቸው ማናቸውም ክንውኖች ምክንያት በተወሰደበት እርምጃ ሊያነሳቸው የሚችላቸው የመብት ጥያቄዎች የሥራ መሪው በሂደት ወደ ሠራተኛ የሥራ መደብ የተዛወረ ቢሆንም አዋጁ ተፈጻሚ ሊሆን እንደማይችል ነው፡፡ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ ውሳኔ ለመስጠት የቻለው ተጠሪ ከሥራ የተሰናበቱት በሠራተኛ የሥራ መደብ ላይ በነበሩበት ወቅት ነው በማለት እንደሆነ ግራቀኙ ካቀረቡት ክርክር መገንዘብ ችለናል፡፡ለተጠሪ የሥራ ስንብት ምክንያት የሆነው ጥፋት የተፈጸመው ተጠሪ የሥራ መሪ በነበሩበት ጊዜ በመሆኑ ተጠሪ የሥራ መሪ በነበሩበት ጊዜ በፈጸሟቸው ጥፋቶች ምክንያት የተወሰደባቸው እርምጃ ተገቢ አይደለም በማለት የሚያቀርቡት ማንኛውም የመብት ጥያቄ ሊስተናገድ የሚችለው በፍትሐብሔር ሕጉ ድንጋጌዎች እንጂ በአሠሪ እና ሠራተኛ ሕጉ መሠረት አይደለም፡፡ በአጠቃላይ ጉዳዩ በቀጥታ የቀረበለት ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን የሚያስችል የሥረ ነገር ሥልጣን ሳይኖረው ውሳኔ መስጠቱ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ይህንኑ ሳያርም ማለፉ መሠረታዊ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 23020 መጋቢት 21 ቀን 2008 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ173531 ሐምሌ 14 ቀን 2008 ዓ.ም በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ለተጠሪው የሥራ ስንብት ምክንያት የሆኑት ጥፋቶች የተፈጸሙት ተጠሪው የሥራ መሪ በነበሩበት ጊዜ በመሆኑ የአሠሪ እና ሠራተኛ ሕጉን መሠረት በማድረግ በሥራ ክርክር ችሎት ክስ ለማቅረብ አይችሉም፤ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የስራ ክርክር ችሎትም የተጠሪን አቤቱታ ተቀብሎ የማየት የሥረነገር ሥልጣን የለውም ብለናል፡፡
3. ተጠሪው ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ክስ የማቅረብ መብታቸውን ይህ ውሳኔ አያግዳቸውም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

የሰ/መ/ቁ.119448

ታህሳስ 06 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

አብዬ ካሳሁን

እትመት አሰፋ

**አመልካች፡-**አዲስ ጋዝና ፕላስቲክ ፋብሪካ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር

ነ/ፈጅ ዘገየች ግደይ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ሰለሞን ኃይሌ የቀረበ የለም … ከተባለ በኋላ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታው መቅረብ ምክንያት የሆነው በተጠሪ ክስ አቅራቢነት የተጀመረውን ክርክር ሲመለከት የቆየው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ከአሁን ተጠሪ ዕዳ አለብህ በማለት የቀነሱትን ብር 2,000/ሁለት ሺህ ብር/ ስርዓቱን ተከትለው የተቀነሰ ባለመሆኑ ለተጠሪ እንዲመልሱላቸው የሰጠውን ውሳኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ ተመልክቶ ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በፌዴራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ታይቶ ሊታረምልኝ ይገባል በማለት አመልካች ጥቅምት 25 ቀን 2008 ዓ.ም የተፃፈ 02 ገጽ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

አቤቱታቸው ከሥር ፍርድ ቤቶች የመዝገብ ግልባጭ ጋር ተገናዝቦ ከተመረመረ በኋላ ተጠሪው ሥራቸውን በራሳቸው ፈቃድ ሲለቁ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 31 መሠረት የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ ሳይሰጡ ሥራ በመልቀቃቸው በፈቃዳቸው አንድ ወር ደመወዝ ከከፈሉ በኋላ ከሌሎች ክፍያዎች ጋር ቀላቅለው የአንድ ወር የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያን ጭምር በመጠየቃቸው ገንዘቡ እንዲመለስላቸው የተወሰነበት አግባብ ተጠሪ ባሉበት ሊጣራ የሚገባው

ሆኖ በመገኘቱ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ታዝዘው መልስ ያቀረቡ ሲሆን አመልካችም የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ክርክሩ በዚህ አግባብ ተጠናቋል እኛም ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀርብ ከተወሰነበት ነጥብ አንፃር ጉዳዩን በመመልከት አመልካች ከተጠሪ የቀነሱት ብር 2,000/ሁለት ሺህ ብር/ እንዲመልሱለት የተወሰነበት አግባብ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን መርምረናል፡፡ እንደመረመረነውም ለሰበር አቤቱታው መቅረብ ምክንያት የሆነው ብር 2,000/ሁለት ሺህ ብር/ የተጠሪ የወር ደመወዝ ሲሆን አመልካች የሚከራከሩት ተጠሪው በራሳቸው ፈቃድ ሥራ ሲለቁ የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ መስጠት ከህግ የመነጨ ግዴታ እያለባቸው ይህንኑ ሳይፈፅሙ ሥራ በመልቀቃቸው የአንድ ወር ደመወዝ ያስከፈሏቸው መሆኑን ጠቅሰው አከፋፈሉም ተጠሪው አምነውበት በፈቃዳቸው ገቢ ያደረጉት ስለመሆኑ ይከራከራሉ፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው በአመልካች ፋብሪካ ሲሰሩት የነበረው ሥራ በፈቃዳቸው የለቀቁት የአንድ ወር ማስጠንቀቂያ በመስጠት ከመሆኑም በላይ ገንዘቡን ገቢ ያደረጉት ተገደው በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ዳኝነት መሠረታዊ የህግ ስህተት አልተፈፀመበትም ተብሎ እንዲፀናላቸው ይከራከራሉ፡፡ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክርክር ወቅት ይህንኑ ገንዘብ ተጠሪ የአንድ ወር የማስጠንቀቂቂያ ጊዜ ሳይሰጡ ሥራ ስለለቀቁ አመልካች ቀንሰው ያስቀሩ ለመሆናቸው አስመዝግበዋል፡፡

በመሠረቱ አንድ ሠራተኛ በራሱ ፈቃድ ሥራ በሚለቅበት ጊዜ ለአሰሪው የሰላሳ ቀናት የማስጠንቀቂያ ጊዜ ሊሰጥ እንደሚገባ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 31 ሥር የተደነገገ ሲሆን ሰራተኛው ይህንን ማስጠንቀቂያ ጊዜ ለአለመስጠቱ የተረጋገጠ እንደሆነ ለሰራተኛው ከሚከፈለው ክፍያ ከሰላሳ ቀናት ክፍያ ያልበለጠ ካሳ ለአሰሪው ሊከፍል እንደሚገባም በአዋጁ አንቀፅ 45 ሥር ተደንግጓል፡፡ የዚህ ካሳ አከፋፈል ሰራተኛው ለአሰሪው የማስጠንቀቂያ ጊዜ ያለመስጠቱ ሥልጣን ባለው አካል ተረጋግጦ ካሳው ሲወሰን የሚከፈል መሆኑን መረዳት ተገቢ ነው፡፡ ከሥር መዝገቡ መገንዘብ የሚቻለው አመልካች በተጠሪው በኩል በህግ የተቀመጠው የማስጠንቀቂያ ጊዜ እንዳልተሰጣቸው ያላረጋገጡ ከመሆኑም በላይ ገንዘቡን ቀንሰው ያስቀሩት ራሳቸው ለመሆናቸው አምነዋል፡፡ አመልካች ከክፍያዎቹ እንዲቀንስባቸው ያቀረቡት ፈቃድ ስለመኖሩም በጽሑፍ በተጠሪው ተፈርሞ የተረጋገጠ ማስረጃ በዚህ ረገድ ሥልጣን ለተሰጣቸው የሥር ፍርድ ቤቶች አልቀረበም፡፡ ይልቁን አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ያስመዘገቡት ተጠሪው የአንድ ወር ጊዜ ማስጠንቀቂያ ባለመስጠታቸው ብር 2,000/ሁለት ሺህ ብር/ ቀንሰን አስቀርተናል የሚል ነው፡፡ አሰሪው ከሰራተኛው ክፍያ ውስጥ የራሱን ጉዳይ ራሱ በመዳኘት ገንዘብ ቀንሶ ለማስቀረት የሚፈቅድ ግልፅ ህግ በሌለበት ሁኔታ አመልካች ለተጠሪው የሚከፈል ክፍያን ቀንሰው ማስቀረታቸው ተገቢነት የሌለው ከመሆኑም በላይ ተጠሪው ከሚከፈላቸው ገንዘብ ውስጥ

አከራካሪ የሆነው ገንዘብ እንዲቀነስ መስማማታቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ተጠሪ በፊርማቸው ያረጋገጡበት ሰነድ ሳይቀርብ ቀንሰው ያስቀሩትን ገንዘብ ለተጠሪው እንዲመልሱ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ውሳኔ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 13531 ሐምሌ 15 ቀን 2006 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተሰጠውና በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 155830 መስከረም 20 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት የፀናው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔው መፅናቱን አውቆ እንደ ፍርዱ እንዲያስፈፅም የዚህ ችሎት ውሳኔ ይተላለፍለት ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት የወጣ ወጭና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሰ/መ/ቁ.132714

ታህሳስ 28 ቀን 2009 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** ፀጋይ አስማማው

አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

ሀትመት አሰፋ

**አመልካች፡-** ዶ/ር ደስአለኝ ተመስገን ቀረቡ

**ተጠሪ** ፡- አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ የቻለው በኢፌዴሪ ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስተር አስተዳደር ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 041/2008 ቀን የካቲት 15 ቀን 2008 ዓ/ም በዋለው ችሎት አስተዳደር ፍርድ ቤቱ የመንግስት ሰራተኞችን የስራ ክርክር በይግባኝ አይቶ ሊያስተናግድ የሚችለው በፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/99 በተሰጠው ስልጣን በአንቀጽ 2/1/ እና /3/ መሰረት አዋጅ ተፈፃሚ በሚሆንላቸው በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች በቋሚነት ተቀጥረው ለሚያገለግሉ የመንግስት ሰራተኞች ብቻ በመሆኑ የአሁኑ አመልካች ከአሁኑ ተጠሪ ጋር የፈጸሙት የስራ ውል በፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አ/ቁ/ 515/99 አንቀጽ 22/3/ መሰረት ህዳር 09 ቀን 2000 ዓ/ም በወጣው የፌዴራል መንግስት ሰራተኞች /ጊዜያዊ/ ኮንትራት ቅጥር አፈፃጸም መመሪያ አንቀጽ 10 መሰረት በመሆኑ የአመልካች ቅጥር ቋሚ ሳይሆን ኮንትራት ቅጥር ስለሆነ ጊዜያዊ ሰራተኛ ጉዳይ የማየት ስልጣን የለውም በማለት በብይን መዝገቡን ዘግይቶ ይህ ብይን በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 125278 በ22/10/2008 ዓ/ም በዋለው ችሎት በመፅናቱ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካች የሠበር አቤቱታቸውን በማቅረባቸው ይህንኑ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡

ይህ ጉዳይ ከሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር አስተዳደር ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የተጀመረ ሲሆን የአሁን አመልካች ይግባኝ ባይ፣ ተጠሪ ደግሞ መልስ ሰጪ ሁኖ ተከራክረዋል፡፡ የአሁኑ አመልካች በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር አስተዳደር ፍርድ ቤት ያቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ ይዘቱ ሲታይም፡- ከተጠሪ መስሪያ ቤት በቁጥር ገወ 3.9/3/53/08 በቀን ጥቅምት 08 ቀን 2008 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ የተላለፈባቸውን የሥራ ስንብት ውሳኔ ያላግባብ የተሰጠ መሆኑን የሚዘርዝር ሁኖ ተጠሪ መስሪያ ቤት የሰጠው ውሳኔ በአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ተሽሮ ወደ መደበኛ ስራቸው እንዲመለሱ፣ ከየካቲት 01 ቀን 2007 ዓ/ም እስከ ጥቅምት 23 ቀን 2008 ዓ/ም ያልተከፈላቸው የወር ደመወዝ ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ቀርቦ መልስ እንዲሰጥበት ተደርጎም አመልካች በዩኒቨርሲቲው ሴኔት "ሊጂስሌሽን" እንደ ስነ ምግባር ጉድለት የተጠቀሱትንና የፈጸሟቸውን ግድፈቶች ያመኑ በመሆናቸውና ከስነ ምግባር ግድፈት ጋር በተገናኘ ጉዳዩ በተጠሪ አጠቃላይ ቦርድ በጉባኤ ተመርምሮ በአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 44(ጎ) መሰረት በቦርዱ የተሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ውሳኔ በመሆኑ በፍርድ ቤት ሊታይ የማይችል መሆኑን፣ አመልካች በተጠሪው መስሪያ ቤት ሰራተኛ ቢሆኑም በመስሪያ ቤቱ ቋሚ ሰራተኛ ለመሆን በአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 33(1) እና ይህንኑ አዋጅ ለማስፈፀም በወጣው ደንብ ቁጥር 210/2003 አንቀፅ 6 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ተጠሪው መስሪያ ቤት ታህሳስ 16 ቀን 2005 ዓ/ም ባወጣው የቋሚ ቅጥር አፈፃፀም መስፈርቶችን አሟልተው ያልተገኙ መሆናቸውንና በተጨማሪም በየሁለት አመት በሚታደስ የኮንትራት ውል መሰረት የተቀጠሩ ሰራተኛ መሆናቸውን በመዘርዝር ፍርድ ቤቱ ስልጣን የለውም በማለት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ነገሩ ላይም ተገቢ ነው ያለውን ክርክር አቅርቧል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የሲቪል ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤትም በተጠሪ በኩል የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክርክር መርምሮ አስተዳደር ፍርድ ቤቱ የመንግስት ሠራተኞችን የስራ ክርክር በይግባኝ አይቶ ሊያስተናግድ የሚችለው በፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/99 በተሰጠው ስልጣን በአንቀጽ 2/1/ እና /3/ መሰረት አዋጅ ተፈፃሚ በሚሆንባቸው በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች በቋሚነት ተቀጥረው ለሚያገለግሉ የመንግስት ሰራተኞች ብቻ በመሆኑ የአሁኑ አመልካች ከአሁኑ ተጠሪ ጋር የፈጸሙት የስራ ውል በፌዴራል መንግስት ሰራተኞች አ/ቁ/ 515/99 አንቀጽ 22/3/ መሰረት ህዳር 09 ቀን 2000 ዓ/ም በወጣው የፌዴራል መንግስት ሰራተኞች /ጊዜያዊ/ ኮንትራት ቅጥር አፈፃጸም መመሪያ አንቀጽ 10 መሰረት በመሆኑ የአመልካች ቅጥር ቋሚ ሳይሆን ኮንትራት ቅጥር ስለሆነ ጊዜያዊ ሰራተኛ ጉዳይ የማየት ስልጣን የለውም በማለት በብይን መዝገቡን ዘግቷል፡፡ በዚህ ብይን አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸው ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት

ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የአስተዳደር ፍርድ ቤቱ የሠጠውን ብይን ሙሉ በሙሉ አጽንቶታል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡-በተጠሪ መ/ቤት በሚቀጠሩበት ጊዜ ከላይ ርዕሱ ኮንትራት ቅጥር ይባል እንጂ ለብዙ ጊዜ ለተለያዩ መ/ቤቶች ተጠሪው በፃፋቸው ደብዳቤዎች አመልካች ቋሚ የመንግስት ሰራተኛ መሆናቸውን በመግለጽ ተጠሪው ለተለያዩ መስሪያ ቤት ደብዳቤ ሲፃፍ የቆየ መሆኑን፣ በአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 33(1) ድንጋጌም የዩኒቨርሲቲ መምህራን ቅጥር በኮንትራት የሚፈፀም መሆኑን የሚያስገንዝብ ይዘትና መንፈስ የሌለው መሆኑን፣ በአዋጅ ቁጥር 515/99 አግባብ ወጣ የተባለው የመንግስት ሰራተኞች የኮንትራት ቅጥር አፈፃፀም መመሪያም በጠቅላይ ሚኒስትሩ በቁጥር መ80-839/1 በተላለፈው መመሪያ መሰረት ቀሪ የሆነ እና በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ታህሳስ 16 ቀን 2005 ዓ/ም በቁጥር ሲሰሚ.30/ጠ18/22/459 ባሰራጨው ደብዳቤ መሰረት በመንግስት መስሪያ ቤቶች የጊዚያዊ ቅጥር/ኮንትራት/ ለፕሮጀክቶች ብቻ የሚፈፀም እንጂ አመልካች ለተቀጠሩበት ስራ አይነት ተፈጻሚነት የሌለው መሆኑን፣ አመልካች የተቀጠሩበት የሥራ ውል በጊዜ የተገደበ ቢሆንም በጠቅላይ ሚኒስትሩ ከተላለፈው መመሪያና ከስራው ባህርይ የተነሳ ህጋዊ ሊሆን የሚችልበት አግባብ የሌለ መሆኑን፣ ተጠሪ የአመልካችን የቋሚነት ቅጥር በመቀበል የጡረታ መዋጮ እየቆረጠ እንዲጠራቀምላቸው ሲያደርግ የቆየ መሆኑንና ሌሎች ነጥቦችን በመዘርዝር ቅጥሩ ቋሚ ቅጥር በመሆኑ አስተዳደር ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለው ተብሎ እንዲወሰን ዳኝነት መጠየቃቸው የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች ቋሚ ሰራተኛ አይደሉም ተብሎ የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ሚኒስቴር አስተዳደር ፍርድ ቤት በይግባኝ የቀረበውን ጉዳይ የማየት ስልጣን የለውም ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርቦም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች በተጠሪ ተቋም የተቀጠሩት ከጥቅምት 12 ቀን 2005 ዓ/ም ጀምሮ በየ2/ሁለት/ አመት በሚታደስ ኮንትራት በባዮጂካል ኬሚካል ሳይንስና ቴክኖሎጂ ት/ቤት ውስጥ በረዳት ፕሮፌሰር የስራ ማዕረግ በወር ብር 5443.00 እየተከፈላቸው እንዲሰሩ የተቀጠሩ በቁጥር ሰሌዳ 25/6-1/05 ቀን ህዳር 19/2005 ዓ/ም ለአመልካቹ የተፃፈው ደብዳቤ ይዘቱ የሚያስረዳ መሆኑን፣ በአመልካችና በተጠሪ መካከል በ12/02/2005 ዓ/ም

በተደረገው የቅጥር ውል በአንቀጽ 4 የውሉ ጊዜ ከጥቅምት 12 ቀን 2005 ዓ/ም ጀምሮ ለሁለት ዓመታት ጊዜ ፀንቶ የሚቆይ መሆኑን፣ በአንቀጽ 8 ውሉ የውሉን ጊዜ ማብቂያ ተከትሎ በጽሁፍ የሚታደስ መሆኑን፣ በአንቀጽ 9/1/ ዩኒቨርስቲው ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እና ማስጠንቀቂያ ውሉን በማንኛውም በቂ ምክንያት የመሰረዝ መብት ያለው መሆኑን፣ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 4/መ/ የውሉ ጊዜ ሲያበቃ ውሉ የሚቋረጥ መሆኑን፣ ለውሉ ተፈፃሚነት ያላቸው ህጎችና የስልጣን ወሰን በኢትዮጲያ ህግ መሰረት የሚስተናገድ መሆኑን በመካከላቸው አለመግባባት በሚፈጠሩበት ጊዜ የኢትዮጲያ ፍርድ ቤት ስልጣን ያለው ስለመሆኑ በአንቀጽ 11 ስር በግልጽ መደንገጉን ነው፡፡ የአስተደዳር ፍርድ ቤት አመልካች ቋሚ አይደሉም በማለት ይግባኛቸውን ሳይቀበል የቀረውም ሆነ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይህንኑ የአስተዳደር ፍርድ ቤትን ብይን ያጸናው የቅጥር ውሉ በአመልካችና በተጠሪ መካከል በተስማሙት መሰረት አስገዳጅነት እንዳለው፣ በዚህም ምክንያት ውሉ ከመነሻውም ቢሆን በተጠሪ መ/ቤት በተሰጠው ውሳኔ ቅሬታውን መቅረብ ያለበት ለአስተዳደር ፍ/ቤት ሳይሆን ለመደበኛ ፍ/ቤት መሆኑን እንደሚያስረዳ፣ አመልካች ቅጥሩ ጊዜያዊ ሳይሆን ቋሚ ቅጥር ነው ሲሉ ለሚያነሱት ክርክር በማስረጃነት የሚጠቅሷቸውና ተጠሪ መ/ቤት ለተለያዩ ተቋማት የጻፏቸው ደብዳቤዎችም በራሪ ደብዳቤዎች ከመሆናቸው ውጪ በ12/02/2005 ዓ/ም የተፈጸመ ውል ወደ ቋሚነት የተሸጋገረ መሆኑን የሚያስረዳ ውል አመልካች አላቀረቡም የሚሉ ምክንያቶችን በማስፈር መሆኑን እንዲሁም የተጠሪ መስሪያ ቤት አመልካችን ሲያሰናብት በቦርዱ ውሳኔ መሰረት የሆኑት ምክንያቶች ከስነ ምግባር ግድፈቶች ጋር የተያያዙ እንጂ ቅጥሩ በሁለት አመት የጊዜ ገደብ በመወሰኑ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት የማያሳይ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በመሰረቱ የቅጥር ውል አለ ወይስ የለም? ከሚለው ነጥብ ጋር በተያያዘ የቅጥር ውል አፈፃፀምንና የቅጥር ውል አሰራረዝን አስመልክቶ ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት የቅጥር ዓይነት በሁለት ዓመት ጊዜ የተገደበ ስለመሆኑ ግራ ቀኙን ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ ይህ ክርክር ያስነሳው የቅጥር ዓይነት በጊዜ የተገደበ እንደመሆኑ መጠን የአዋጅ ቁጥር 515/99 የተፈፃሚነት ወሰንን ለመለየት እንዲረዳ በአንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር "የመንግስት ሠራተኛ" ማለት በፌደራል መንግስት መ/ቤት ውስጥ በቋሚነት ተቀጥሮ የሚሠራን ሠራተኛ ብቻ የሚመለከት በመሆኑና የአዋጁም ተፈፃሚነት ይኸው ቋሚ የመንግስት ሠራተኛ በዚሁ አንቀጽ 2(3) ሥር ከተመለከተው የመንግስት መ/ቤት ጋር በሚያደርጉት ክርክር ላይ የተወሰነ ነው በሚል የተቀመጠውን የአዋጅ ትርጓሜ መነሻ በማድረግ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ትርጉም በዚህ ደረጃ የሚነቀፍ አይደለም፡፡ ሆኖም የሚያከራክራቸውን የቅጥር ሁኔታ በጊዜ መገደቡን ተመልክቶ የአሁን አመልካች የኮንትራት ሠራተኛ ነው ከሚል መደምደሚያ ላይ ከደረሰ በአዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 2(2) "ጊዚያዊ ሠራተኛ" ማለት በመንግስት መ/ቤት ውስጥ የዘላቂነት ባህሪ

በሌለው ሥራ ወይም ሁኔታዎች ሲያስገድዱ በቋሚ የሥራ መደብ ላይ በጊዜያዊነት ተቀጥሮ የሚሠራ ሰው ነው የሚል ትርጓሜ በማስቀመጥ አዋጁ በእነዚህ ጊዜያዊ ሠራተኞች ላይ ተፈፃሚ ሊሆን እንደማይችል በአንቀጽ 2(1) የተመለከተውን የአዋጁን የተፈፃሚነት ወሰን በሚያጠናክር ሁኔታ ከተደነገገና ይህንኑም ይበልጥ ግልፅ በማድረግ በአንቀጽ 3 ላይ የአዋጁ የተፈፃሚነት ወሰንን በመንግስት መ/ቤት ውስጥ በቋሚነት ተቀጥሮ በሚሠራ የመንግስት ሠራተኛ ላይ ብቻ እንደሆነ ካስቀመጠ በኋላ ጊዚያዊ ሠራተኞች በዚህ አዋጅ ሊካተቱ የማይችሉ መሆኑን በመደንገግ ሳይገደብ በአዋጁ አንቀጽ 22 ሥር በአዋጅ የሚገዛ የመንግስት መ/ቤት ከቋሚ የመንግስት ሠራተኛ ባሻገር ጊዜያዊ ሠራተኛን መቅጠር የሚችልበትን ሁኔታ በንዑስ ቁጥር 1 ለይቶ ከደነገገ በኋላ በዚህ አኳኋን በመንግስት መ/ቤት የሚቀጠሩ ጊዜያዊ ሠራተኞች አቀጣጠር ስለሚኖራቸው መብቶችና ግዴታዎች እንዲሁም ስለሚጠበቅላቸው የሥራ ሁኔታዎች ዝርዝር መመሪያ ሊወጣ የሚችል መሆኑንም ሁሉ አካቷል፡፡ እንደዚሁም ይህን አዋጁን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን በሚኒስትሮች ም/ቤት እነዚህን ደንቦች ለማስፈፀም የሚረዱ መመሪያዎች በኤጀንሲው አማካኝነት ሊወጡ እንደሚችሉም በአዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 93 የተመለከተ በመሆኑ በአንቀጽ 22 እና በአንቀጽ 93 መሠረት ጊዜያዊ ሠራተኞችን የሚመለከት ዝርዝር ደንብና መመሪያ እንደሚወጣ ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሠረት በአንቀጽ 2(2) ስለ ጊዜያዊ ሠራተኛ የተሰጠውን ትርጓሜ መነሻ በማድረግ፣ በአንቀጽ 22 እንደ ተመለከተው የመንግስት መ/ቤት ጊዚያዊ ሠራተኛን መቅጠር የሚችልበትን አግባብ አስመልክቶ በአዋጁ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 22 (3) እና አንቀጽ 93 መሠረት በሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ በህዳር ወር 2000 የወጣውን የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የጊዜያዊ /ኮንትራት/ ሠራተኞች ቅጥር አፈፃፀም መመሪያ መውጣቱ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ መመሪያ በመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚፈጸመውን የጊዜያዊ ቅጥር ስርዓቱን ዘርግቶ የነበረ ሲሆን በመመሪያው በጊዜያዊ ቅጥር የተቀጠሩ ሰራተኞች ወደ ቋሚነት እንዲሸጋገሩና ጊዜያዊ ቅጥር ለ"ፕሮጀክት" ስራዎች ብቻ እንዲሆንና በዚሁ አግባብ አፈጻጸሙ እንዲቀጥል የኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ህዳር 18 ቀን 2005 ዓ/ም በቁጥር መ80-839/1 ለሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የፃፈ መሆኑን፣ የሲቪል ሲርቪስ ሚኒስቴርም ይህንኑ ከጠቅላይ ሚኒስቴር ፅ/ቤት የተላከውን መመሪያ መነሻ በማድረግ በቁጥር ሲሰሚ30/መ/18/22/459 በ16/04/2005 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ በመስሪያ ቤት በጊዜያዊነት የተቀጠሩት ሰራተኞች ወደ ቋሚ ሰራተኛነት የሚመደቡበትን አግባብ በመመዘርዘር ከደብዳቤው በኋላ በማንኛውም የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤት እጅግ አስፈላጊ ለሆኑና ለአጭር ጊዜ ብቻ የኮንትራት/ጊዚያዊ ቅጥር መፈጸም አስገዳጅ ሁኔታ ከተፈጠረ ጥያቄው በቅድሚያ ለሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር እየቀረበ ተቀባይነት ማግኘቱ መረጋገጥ ያለበት መሆኑን በመግለጽና ከዚህ ውጪ በማንኛውም መልኩ የኮንትራት/ጊዜያዊ ቅጥር መፈፀም ተጠያቂነት የሚያስከትል መሆኑን የሚያሳይ መመሪያ አስተላልፏል፡፡ በመሆኑም የፐብሊክ ሰርቪስ አስተዳደር ፍርድ ቤትም ሆነ

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በዚህ ረገድ ያስቀመጡት ምክንያት የለም፡፡ ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው በሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ በህዳር ወር 2000 የወጣውን የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የጊዜያዊ /ኮንትራት/ ሠራተኞች ቅጥር አፈፃፀም መመሪያ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ሲሆን በመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚፈፀም የጊዜያዊ ቅጥር ውል በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት በሲሰሚ30/መ/18/22/459 በ16/04/2005 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ አግባብ መፈጸሙ ካልተረጋገጠ ሕጋዊ ነው ተብሎ የሚወሰድ አይደለም፡፡

የአሁን ተጠሪ ዩኒቨርሲቲ አጥብቆ የሚከራከረው በአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 33(1) እና በደንብ ቁጥር 210/2003 አንቀጽ 6 አግባብ በዩኒቨርስቲው ሰኔት በወጣው ሌጂስሌሽን መሰረት ቅጥሩ በየሁለት አመት የሚታደስ መሆኑ ሕጋዊ ነው፣ ስንብቱም ጊዜውን ጠብቆ የተደረገ ነው በማለት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ይሁን እንጂ በተጠሪው ቦርድ ለአመልካች ስንብት ምክንያት የሆነው የቅጥር ጊዜ ማብቃቱ ሳይሆን በአመልካች በኩል ተፈጸሙ የተባሉ የስነ ምግባር ግድፈቶች ከመሆናቸው በላይ የአዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀፅ 33 (1) አግባብ ቋሚ ቅጥር የሚፈፀመበት አግባብ በዩኒቨርሲተው እና አመልካችን ከመሰሉ መምህራን ጋር የሚፈጸመው ቅጥር ጊዚያዊ ቅጥር ነው ብሎ ለመደምደም የሚያስችል ሁኖ አልተገኘም፡፡ የአሁን ተጠሪ ዩንቨርሲቲ በማስተማር ሙያ ጊዜን ወስኖ ከመምህራን ጋር የቅጥር ውል የሚፈጸመው የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥና በዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት የታነፁ ምሩቃንን ለማፍራት የሚያስችል አቅም ያለውን መምህር መሆኑንና አለመሆኑን ለመፈተሽ እንዲረዳው ሲባል ስለመሆኑ ከራሱ ከዩኒቨርስቲው ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 216/2003፣ ለዩኒቨርስቲው በደንብ ቁጥር 210/2003 አንቀጽ 6 በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር በወጣው የዩኒቨርሲቲው "ሌጂስሌሽን"ም ሆነ ከከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 በአዋጅ ቁጥር 861/2006 እንደተሻሻለው፤ የተመለከተውን ግብና አላማ በማገናዘብ መረዳት የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ የአሁን ተጠሪም ቢሆን በሥር ፍ/ቤት የቅጥሩ ሁኔታ በዩኒቨርሲቲው ሌጂስሌሽን አንቀጽ 61 መሰረት ቋሚ አይደለም፤ ቅጥር በዚሁ ደንብ መሰረት የተፈፀመ አለመሆኑ እስከ ተረጋገጠ ድረስ ሊሰረዝ የሚችል ነው በሚል አዋጁን፣ደንቡንና የዩኒቪርሲቲውን "ሌጂስሌሽ"ን ጠቅሶ መከራከሩና ቅጥሩ በጊዜ ተገድቦ እንዲፈፀም መደረጉ በእራሱ ብቻውን ይህ አመልካች ጊዚያዊ /የኮንትራት/ ሠራተኛ ነው በሚለው አቋም ሥር ሊወድቅ የሚችል መሆኑን የሚያመለክት ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም በዚህ በተያዘው ጉዳይ በግራ ቀኙ መካከል ተደርጓል የተባለው የቅጥር ውል በሁለት ዓመት ጊዜ ተገድቦ የመደረጉ እውነታ ለትምህርት ጥራት ስኬት ሲባል ቅጥሩ ሊቋረጥ የሚችልበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ታስቦ የተደረገ ነው ካልተባለ በስተቀር የተቆረጠው ጊዜ በእራሱ የቅጥሩ ሁኔታ ጊዜያዊ መሆኑን ጠቋሚ ሆኖ ጊዜያዊ /ኮንትራት/ ሠራተኞች በሚል

ትርጓሜ ሥር የሚሸፈን ባለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 515/ 1999 በወጣው የጊያዚያዊ ቅጥር አፈጻጸም መመሪያና ይህንኑ መመሪያ በተመለከተ ቀጥሎ በተዘረጋው ስርዓት አግባብ ሊገዛ የሚችልበት ሁኔታ የሌለ ሁኖ አግኝተናል፡፡

በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የቅጥር ውል ስለጊዜያዊ /ኮንትራት/ ሠራተኞች ቅጥር አፈፃፀም በወጣው መመሪያ መሠረት ሊሆን ይገባል ብሎ ለመደምደም እንደማያበቃ በአዋጅ ቁጥር 515/99 አግባብ ህዳር 2000 ዓ/ም በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ወጥቶ የነበረውና በኋላም በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚስቴር ጽ/ቤት በቁጥር መ80-839/1 በተላለፈው መመሪያ መነሻ ቀሪ የሆነ እና በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ታህሳስ 16 ቀን 2005 ዓ/ም በቁጥር ሲሰሚ.30/ጠ18/22/459 ባሰራጨው ደብዳቤ መሰረት በመንግስት መስሪያ ቤቶች የጊዚያዊ ቅጥር/ኮንትራት/ ለፕሮጀክቶች ብቻ የሚፈፀም እንጂ አመልካች ለተቀጠሩበት ስራ አይነት ተፈጻሚነት የሌለው ስለመሆኑ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች የተረጋገጠ ሲሆን አመልካች ለአስተዳደር ፍርድ ቤቱ ያቀረቡት ይግባኝ ይህ ችሎት በመ/ቁጥር 98435 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2(1) በየትኛውም ፍርድ ቤት የሚገኝ የዳኝነት አካል የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም ከመስጠቱና በህገ መንግስቱ አንቀጽ 37 ከተመለከተው ፍትህ የማግኘት መብት አንፃር ሁሉ ሲታይ ጉዳዩ በፌደራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ አዋጅ ቁጥር 515/99 አግባብ በተዘረጋው የይግባኝ ስርዓት ታይቶ ሊወሰን የሚገባው ሆኖ እያለ የሥር ፍርድ ቤቶች ቅጥሩ በጊዜ መገደቡን ብቻ በማየት የአመልካችን ይግባኝ ውድቅ ማድረጋቸው ሕጋዊ ሁኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም የውሉን ቆይታ ጊዜ በተመለከተ ቅጥሩ ሕጋዊ ስለመሆኑ ሳይረጋገጥ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ተፈጻሚነት አለው ተብሎ የተያዘው የበታች ፍርድ ቤቶች ድምዳሜ ከላይ የተዘረዘሩትን ሕጋዊ ምክንያቶችን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1731 የተቀመጠው በሕግ አግባብ የተቋቋሙ ውሎች በተዋዋይ ወገኖች የአስገዳጅነት ኃይል አላቸው የሚለው ድንጋጌ በቅድሚያ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1678(ለ)፣1711 እና 1716 ስር ስለህጋዊ ውል አመሰራረት የተቀመጡትን ታሳቢ ያደረገ መሆኑን ያላገናዘበ ሁኖ አግኝተናል፡፡

ሲጠቃለልም በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የቅጥር ውል ጊዚያዊ/ኮንትራት ነው ሊባል የሚችልበት አግባብ የሌለ መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 650/2001 በአዋጅ ቁጥር 861/2006 እንደተሻሻለው ከአንቀፅ 30 እና 33 ጣምራ ንባብና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና በመምህራን መካከል የሚደረጉ ውሎች በየሁለት አመት እንዲታደሱ ከሚደረጉበት መሰረታዊ ዓላማ፣ በአዋጅ ቁጥር 515/99 አግባብ ሕዳር 09 ቀን 2000 ዓ/ም ወጥቶ የነበረው የጊዚያዊ ቅጥር ውል አፈጻጸም መመሪያ በኢ.ፌ.ዲ.ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚስቴር ጽ/ቤት በቁጥር መ80-839/1 በተላለፈው መመሪያ መነሻ በከፊል ቀሪ ከመሆኑና በሕግ ጥበቃ ሊሰጣቸው የሚገባቸው ውሎች በህጉ አግባብ የተቋቋሙ ናቸው ከሚለው የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1731 ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘት የተገነዘብን በመሆኑ

በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር አስተዳደር ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 041/2008 ቀን የካቲት 15 ቀን 2008 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 125278 በቀን 22/10/2008 ዓ.ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ግራ ቀኙ የተከራከሩበትን የቅጥር ውል አፈፃፀም ሆነ የቅጥር ውል አሰራረዝ በሚመለከት በየፊናቸው ያቀረቡትን ክርክር ማስረጃ ለጉዳዩ ተፈፃሚ መሆን ከሚገባው ህግና ደንብ አንፃር በማየት ተገቢውን ዳኝነት መስጠት ይቻል ዘንድ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341 መሠረት ለፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር አስተዳደር ፍ/ቤት መልሰናል ፡፡
3. በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተደረገው ክርክር ላስከተለው ውጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ.136981

ሐምሌ 19 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፦ አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ አርሺሶ

ሠናይት አድነው

አመልካች ፡- የሀረር ቢራ ፋብሪካ አክሲዮን ማህበር………………አልቀረበም

ተጠሪዎች ፡- 1.አቶ ዓለሙ ነጋሽ

2. አቶ ሙሉቀን ከበደ

3. አቶ ተስፋዬ ማኮ

4. አቶ መለሰ ሽምታጋ

5. ወ/ሮ ጽጌ አክሊሉ

6. አቶ እሸቴ በየነ

7. አቶ አገሳ ዋቅጅራ

8. አቶ ተስፋዬ ደስታ

9. አቶ ፀጋዬ ሚደቅሳ

10. አቶ አበበ አያሌው

11. አቶ አብዲሳ ታደ

12. አቶ ገ/ሥላሴ ገሠሠ

13. አቶ ብርሃኑ ዘፈሩ

14. አቶ መኮንን ጌታሁን

15. አቶ ጌታቸው ለማ

16. አቶ ተሰማ ተማም

17. አቶ ይታገሱ ሳህሌ

18. አቶ ገ/ማርያም በርሄ

19. አቶ ኤልያስ ይሌ

20. አቶ በዜ አባትሁን

21. አቶ አስናቀ ታደሰ

22. ወ/ሮ የሹምነሽ አድነው

23. አቶ መላኩ መር

24. ወ/ሮ አልማዝ ገ/ማርያም

25. አቶ ሰንበቶ ባይሳ

26. አቶ ቡልቱማ ጉታ

27. ወ/ሮ አልማዝ ዘውዴ　　28. አቶ አሰፋ መርጊያ

29. አቶ አለነ አሞኘ　　30. አቶ ማስረሻ ገ/አምላክ

31. አቶ መስፍን ግርማ　　32. አቶ ገበየሁ አዛለ

33. አቶ አስማማው አንተነህ　　34. አቶ ገመቹ ዓለሙ

35.አቶ ባቱ ቶሎሳ　　36 አቶ መንግስቱ ግርማ

37. አቶ ፍቃዱ ደበሌ　　38. አቶ ዘነበ ፍኔ

39. አቶ አበበ መዘምር　　40. አቶ ኃይሌ አክሊሉ

41. አቶ ዘውዴ ፍንታዬ　　42. አቶ አብደላ ቃሲም

43. አቶ ፍቃደ ኃይሌ　　44.አቶ ሲሣይ መኮንን

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ ::

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ፡- ከስራ ውል መቋረጥ ጋር ተያይዞ የደመወዝ ጭማሪን መሰረት ያደረገ ክርክር ነው ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው የአሁን ተጠሪዎች የነበሩት የስር ከሳሾች 1ኛ. በአሁን አመልካች፣ 2ኛ. በሀረር ቢራ አክሲዮን ማህበር መሰረታዊ ሰራተኛ ማህበር እና 3ኛ.በሀረር ቢራ አክሲዮን ማህበር ብድር እና ቁጠባ ላይ ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በሀረሪ ክልል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ፍርድ ቤቱም የከሳሾችን ክስ እና የቀረበውን መቃወሚያ መርምሮ ከሳሾች በ1ኛ ተከሳሽ ላይ ያቀረቡትን ከስራ ውል መቋረጥ ጋር ተያይዞ 40 ፐርሰንት ደመወዝ ጭማሪ ተጨማሪ ክፍያ እና የኢንሹራንስ ክፍያ ክሱ የቀረበው የስራ ውላቸው ከተቋረጠ ከ6 ወር በኃላ ስለሆነ ክሱ በይርጋ ይቋረጣል፡፡ ሲል በ2ኛ እና በ3ኛ ተከሳሾች ላይ የቀረበውን ክስ አስመልክቶ በግራ ቀኙ መካከል የስራ ውል ግንኙነት የሌለ ስለሆነ ጉዳዩ በግልጽ የፍትሀብሄር ክርክር በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁን ተጠሪዎች በውሳኔው ቅር ተሰኝተው ለከፍተኛው ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡ ሲሆን ከፍተኛው ፍ/ቤትም ቅሬታው መልስ ሰጪን ያስቀርባል በማለት አስቀርቦ ካከራከረ በኃላ በ2ኛ እና 3ኛ ተከሳሾች ላይ የቀረበው ክስ ላይ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት እና በ1ኛ ተከሳሽ ላይ የቀረበውን ክስ በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር ክሱ በይርጋ አይታገድም በማለት በፍሬ ነገር አከራክሮ እንዲወስን ለስር መጀመሪያ ደረጃ

ፍርድ ቤት መልሶ ልኮታል፡፡ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁን አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በክልሉ ህግ አግባብ የተቋቋመ የሰበር ስርአት ስለሌለ ችሎቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም በማለት አቤቱታውን ውድቅ በማድረግ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

አመልካች ለዚህ ለፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታን ያቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ድርጅት ነ/ፈጅ ጥር 3 ቀን 2009 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ በአጭሩ ክሱ በይርጋ ይታገድ ይገባው እንደነበር እና የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይርጋ ክርክሩን ውድቅ ለማድረግ የሰጠው ምክንያት መሠረታዊ የሕግ ትርጉም ስሕተት የተፈፀመበት ስለመሆኑ በማብራራት የሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲታረም አመልክተዋል፡፡ የሰበር አጣሪው አቤቱታውን ከመረመረ በኂላ የአመልካች ድርጅት ያቀረበው የይርጋ መቃወሚያ የታለፈበትን አግባብ ለመመርመር ተጠሪን አስቀርቧል፡፡ የተጠሪዎች ወኪል ሚያዝያ 16 ቀን 2009 ዓ.ም የጽሑፍ መልስ ያቀረቡ ሲሆን አመልካች የመልስ መልስ ለመስጠት ያለመፈለጉን በመግለጽ ያላቀረበ ስለሆነ የመልስ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር እና የጉዳዩ አመጣጥ ከፍ ሲል የተመለከተው ሲሆን እኛም የተያዘውን ጭብጥ ከሕጉ አንፃር አገናዝበን መርምረናል፡፡ ከፍ ሲል በዝርዝር እንደተመለከተው በአመልካች እና ተጠሪዎች መካከል የነበረው የሥራ ውል የተቋረጠው ግንቦት 3 ቀን 2005 ዓ.ም መሆኑ እና ክስ የቀረበው መጋቢት 17 ቀን 2006 ዓ.ም መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡በተጠሪዎች በኩል የቀረበው ክስ የሥራ ውላችን ሲቋረጥ በስምምነት ከስራ ለሚለቅ ሰራተኛ ከተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች ጋር የደመወዙን 100 ፐርሰንት ለመክፈል አሰሪው ስምምነት አድርጎ የተከፈለን ቢሆንም የስራ ውላችን ከተቋረጠ በኃላ ታህሳስ ወር 2006 ዓ.ም ጀምሮ በስምምነት ከስራ ለሚለቅ ሰራተኛ ከተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች ጋር የደመወዙን 140ፐርሰንት ለመክፈል አሰሪው ስምምነት ላይ መድረሱን በመግለጽ ሊከፈለን የሚገባ የደመወዝ ጭማሪ 40 ፐርሰንት እና የኢንሹራንስ ክፍያ እንዲከፈለን ይወሰንልን የሚል ነው፡፡

በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162 ልዩ ልዩ የመብት ጥያቄዎችን አስመልክቶ ክሱ መቅረብ ያለበትን የጊዜ ገደብ ወስኗል፡፡

የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካችን የይርጋ ክርክር ውድቅ ለማድረግ የሰጠው ምክንያት የሥራ ውል ከተቋረጠበት ከግንቦት 3 ቀን 2005 ዓ.ም ክስ እስከቀረበበት መጋቢት 17 ቀን 2006 ዓ.ም ድረስ ያለው ጊዜ ሲሰላ ስድስት ወር ያለፈው መሆኑን በመግለጽ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 162(4)ን በመጥቀስ ሲሆን የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር ክርክሩ በይርጋ አይታገድም በማለት ውሳኔ የሰጠው የደመወዝ 40 ፐርሰንት ጭማሪ እና የኢንሹራንስ ክፍያ የይርጋ ጊዜ በአዋጁ አንቀጽ

162(1) መሰረት በ1 አመት ይርጋ የሚቋረጥ መሆኑን እና የተጠሪዎች ክስም የቀረበው የስራ ውሉ ከተቋረጠ አንድ አመት ሳይሞላው ነው በማለት መሆኑን ከስር መዝገብ መረዳት ተችሏል። የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 162(4)ን ስንመለከት የስራ ውል በመቋረጡ ምክንያት በሰራተኛውም ሆነ በአሰሪው የሚቀርብ ማንኛውም የክፍያ ጥያቄ የስራ ውሉ በተቋረጠ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ እንደሚታገድ ተደንግጎ ይገኛል። የተጠሪዎችን የክስ ይዘት ስንመለከት ደግሞ የስራ ውላችን ግንቦት 3/2005 ከተቋረጠ በኃላ ታህሳስ ወር 2006 ዓ.ም ጀምሮ ለሚወጡ ሰራተኞች አመልካች ለመክፈል የተስማማው የደመወዝ ጭማሪ ለኛም ሊከፈለን ይገባል የሚል ነው። ተጠሪዎች ክስ ያቀረቡበት መብት ተቋቁሚል የሚሉት የስራ ውላቸው ከተቋረጠ ከ7ወር በኃላ አመልካች ከስራ ለሚለቁ ሰራተኞች የደመወዝ ጭማሪ አድርጓል በሚል መሆኑ ከግራ ቀኙ ክርክር የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ነው። ይህ መሆኑ ከተረጋገጠ የተጠሪዎች የዳኝነት ጥያቄ የስራ ውል በመቋረጡ ምክንያት የተቋቋመ የመብት ጥያቄ ሊሆን የሚችልበት ምክንያት የለም። ስለሆነም የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተጠሪዎች መብት ከስራ ውል መቋረጥ የመነጨ ነው በማለት ድምዳሜ ላይ ደርሶ የአዋጁን አንቀፅ 162(4)ን በመጥቀስ ክርክሩ በ6 ወር ይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጠው ውሳኔ ሕጋዊና ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም።

ይልቁንም የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በአዋጁ አንቀጽ 162(1) መሰረት ከቅጥር ውል በመነጨ ግንኙነት የሚጠየቅ ማንኛውም ክስ በ1 አመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን በመጥቀስ እና የተጠሪዎች የስራ ውል ከተቋረጠበት ክስ እስከቀረበበት ድረስ ያለው ጊዜ ሲታሰብ 1አመት የማይሞላው መሆኑን በመግለጽ የተጠሪዎች ክስ በይርጋ አይታገድም በማለት ድምዳሜ ላይ ደርሶ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር የሰጠው ውሳኔ አዋጁ ለይርጋ አቆጣጠር በምክንያትነት የደነገገውን መስፈርት መሰረት ያደረገ በመሆኑ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል።

ነገር ግን አዋጅ ቁጥር 377/1996 "ን" መሰረት አድርገው የሚቀርቡ ክሶችን የይርጋ ጊዜ አቆጣጠር በተመለከተ በአዋጁ በተለየ አኳኃን ካልተገለጸ በቀር የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው መብትን ለመጠቀም ከሚቻልበት ቀን ቀጥሎ ካለው ቀን ጀምሮ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 163(1) ስር የተደነገገ ከመሆኑ በተጨማሪ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 51912 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል።

የስር ሁለቱም ፍርድ ቤቶች ማለትም መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱ ክርክሩ በይርጋ የሚታገደው ክሱ በ6ወር ጊዜ ውስጥ ባለመቅረቡ ነው በማለት እና የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ክሱ በይርጋ የማይታገደው በ1 አመት ጊዜ ውስጥ የቀረበ ስለሆነ ነው በማለት የይርጋ ጊዜውን በማስላት መደምደሚያ ላይ የደረሱት የስንበት ደብዳቤው ለተጠሪዎች ተሰጥቷል ከተባለበት ከ03/09/2005 ዓ.ም ጀምሮ በመቁጠር ስለመሆኑ የውሳኔው ይዘት ያመለክታል።ይሁን እንጂ ለተጠሪዎች የስንብት ደብዳቤው በ03/09/2005ዓ.ም የተሰጣቸው ቢሆንም ተጠሪዎች ለክሳቸው መሰረት

ያደረጉት ታህሳስ ወር 2006ዓ.ም ጀምሮ በስምምነት ከስራ ለሚለቅ ሰራተኛ ከተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች ጋር የደመወዙን 140 ፐርሰንት ለመክፈል  አሰሪው ስምምነት ላይ መድረሱን እና በዚህ መሰረት ክፍያ መፈጸሙን በመግለጽ መሆኑን ተጠሪዎች በስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ካቀረቡት ክስ ይዘትም ሆነ ከግራ ቀኙ ክርክር መረዳት የተቻለ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች የስንብት ደብዳቤው ለተጠሪዎች ተሰጥቷል ተብሎ በተጠሪዎች የተገለጸውን ግንቦት 03 ቀን 2005 ዓ.ም ለይርጋ ጊዜው አቆጣጠር የመነሻ ቀን አድርገው መውሰዳቸው ይልቁንም ተጠሪዎች ከስራ የተሰናበቱት በ3/9/2005 ጀምሮ ቢሆንም ተጠሪዎች ሊከፈለን ይገባል በማለት ክስ ያቀረቡት ታህሳስ 6 ቀን 2006 ዓ.ም የተደረገ የደመወዝ ጭማሪን መሰረት ያደረገ መሆኑን ከግራ ቀኙ ክርክር መገንዘብ የተቻለ በመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 163(1) በተመለከተው መሰረት ለይርጋ ጊዜው አቆጣጠር የመነሻ ቀን ተደርጎ መወሰድ የሚገባው በስምምነት ከስራ ለሚለቁ ሰራተኞች ደመወዝ ጭማሪው ክፍያ 140 ፐርሰንት እንዲሆን ከተወሰነበት ከታህሳስ 6 ቀን 2006 መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ክሱ እስከቀረበበት መጋቢት 17 ቀን 2006 ዓ.ም ድረስ ያለው ጊዜ ሲቆጠር ደግሞ አንድ(1)አመት የማይሞላው በመሆኑ ተጠሪዎች ያቀረቡት የክፍያ ጥያቄ በአዋጁ አንቀጽ 162(1) መሰረት በይርጋ የሚታገድ አይደለም፡፡

ሲጠቃለል የሀረሪ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ ክርክር በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጠውን ውሳኔ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሻር ክርክሩ በይርጋ አይታገድም በማለት እና የፍሬ ነገር ክርክሩን አከራክሮ እና አጣርቶ እንዲወስን ለስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንዲመለስ የሰጠው ውሳኔ በውጤት ደረጃ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የሚከተለውን ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የሀረሪ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 40519 በ9/12/2006ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የሀረሪ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 12532 በ18/8/2008ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348(1)መሠረት ጸንቷል፡፡
2. የተጠሪዎች የክፍያ ጥያቄ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162(4) መሠረት በይርጋ የሚታገድ አይደለም ብለናል፡፡
3. የዚህን ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. የውሳኔው ግልብጭ በየደረጃው ለሚገኙ የስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷልወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

የሰ/መ/ቁ 140781

ሐምሌ 18 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጸውሎስ ኦርሺዮ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- ታደሰ እንጆሪ ሆቴልና ጠቅላላ ንግድ ስራ ኃ.የተ.የግል ማህበር -ነ/ፈጅ ይሁንልኝ ቡሎ- ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሪት ሉላ ዘሪሁን - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የሥራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ተጠሪ በሐዋሳ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ተከሳሽ ለሪቬኒ ሂሳብ ስራ መደብ በቋሚነት ተቀጥረው ከአርባ አምስት ቀናት በላይ በስራ ላይ ከቆዩ በኋላ አመልካች ድርጅት ከህግ ውጪ የሥራ ውላቸውን ያቋረጠባቸው መሆኑን ገልጸው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈሏቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስም ተጠሪን የሙከራ ጊዜ ሲጠናቀቅ ያሰናበታቸው በመሆኑ እርምጃው ሕጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለትም የሐዋሳ ከተማ መ/ደ/ፍ/ቤትም በአመልካችና በተጠሪ መካከል ተደረገ በተባለው የስራ ቅጥር ውል ላይ ያለው የተጠሪ ፊርማ የተባለው በተጠሪ በመካዱ ምክንያት በባለሙያ እንዲመረመር አድርጎ ውጤቱ እንዲቀርብ በማድረግና የግራ ቀኙን ምስክሮችን በመስማት ፍሬ ነገሩን ከአጣራ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች ከተጠሪ ጋር ያለውን የቅጥር ውል ያቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ ለተጠሪ የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፍል በማለት የክፍያዎችን አይነትና መጠናቸውን ለይቶ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ፍርድ

ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ የተቀጠሩት ለሙከራ ጊዜ ሁኖ የሙከራ ጊዜ ሲጠናቀቅ እንዲሰናበቱ መደረጉ ከሕግ ውጪ አይደለም በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ሽሮታል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኗ ተጠሪ ቅር በመሰኘት የሠበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ችሎቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ በአመልካችና በተጠሪ መካከል በ26/09/2008 ዓ/ም የተደረገው የቅጥር ውል ተጠሪ ለሙከራ ጊዜ የተቀጠሩ ስለመሆኑ የሚያሳይ አለመሆኑ ተረጋግጦ እያለ ተጠሪ ለሙከራ እንደተቀጠሩ ተቆጥሮ የአርባ አምስት ቀን ጊዜ ሲያልፍ የሥራ ውሉ መቋረጡ ተገቢ ነው ተብሎ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት መወሰኑ ያላግባብ ነው በማለትና በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 11(3) ድንጋጌን በዋቢነት ጠቅሶ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ አፅንቶታል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- ተጠሪ የአርባ አምስት ቀን ጊዜ ከአለፋቸው በኋላ መሰናበታቸው በሕጉ አግባብ ሁኖ እያለ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ መወሰኑ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበውም ግራ ቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን በበኩላችንም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ በዚህም መሰረት በጉዳዩ ላይ ምላሽ የሚያሻውም የጉዳዩ መሰረታዊ ጭብጥ አመልካች ተጠሪን ከሥራ ማሰናበቱ በሕጉ አግባብ ነው? ወይንስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የቅጥር ውል የተደረገው ግንቦት 26 ቀን 2008 ዓ/ም ስለመሆኑና በዚህ የቅጥር ስምምነት ላይ ቅጥሩ የሙከራ ጊዜ ያለው ስለመሆኑ የተስማሙበት አግባብ የሌለ መሆኑን ተጠሪ ጠቅሰው የሚከራከሩ ሲሆን አመልካች በበኩሉ ቅጥሩ በ01/10/2008 ዓ/ም ተደርጎ ስንብቱ በአርባ ሶስተኛው ቀን በ13/11/2008 ዓ/ም የተደረገ ስለመሆኑና በዚህ ጊዜ ደግሞ አሰሪው ሰራተኛውን በማናቸውም ምክንያት ማሰናበት እንደሚችል ሕጉ መብት የሰጠው መሆኑን ገልጾ ተከራክሮ የሥር ፍርድ ቤት በግራ ቀኙ መካከል የቅጥር ውሉ የተደረገበትን ጊዜና በ01/10/2008 ዓ/ም ተደረገ በተባለው ሰነድ ላይ ያለው ፊርማ የተጠሪ መሆን ያለመሆኑ ላይ ክርክር በመነሳቱ ምክንያት ፊርማው እንዲመረመር አድርጎ በሰነዱ ላይ ያለው ፊርማ ከተጠሪ ፊርማ ጋር የማይመሳሰል መሆኑን በባለሙያ ተረጋግጦ ያቀረበለት ከመሆኑም በላይ የግራ ቀኙን ምስክሮችን ሰምቶ የተጠሪ ማስረጃዎች ክብደት ሊሰጣቸው የሚገባ መሆኑን በመግለጽ የአመልካች የሥራ ስንብት እርምጃ ሕገ ወጥ ነው በማለት መወሰኑን፣ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ደግሞ ስንብቱ በሕጉ በተመለከተው የሙከራ ጊዜ ውስጥ የተከናወነ በመሆኑ ህጋዊ ነው

በማለት የወሰነ ቢሆንም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በግራ ቀኙ መካከል የሙከራ ጊዜ እንዲኖር የተደረገ ስምምነት በሌለበት ሁኔታ አመልካች ተጠሪን ከአርባ አምስተኛው ቀን በፊት አሰናብቼአለሁ በማለት የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት ሊያገኝ የሚችልበት አግባብ የለም በማለት የወሰነ መሆኑን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡

አንድ ሠራተኛ ሊመደብበት ለታቀደው ቦታ ተስማሚ መሆኑና አለመሆኑን ለመመዘን ለሙከራ ጊዜ ሊቀጥር እንደሚችል፤ይህ የግራ ቀኙ ስምምነትም በጽሑፍ መደረግ እንዳለበት፤ የሙከራ ጊዜውም ከ45 ተከታታይ ቀናት መብለጥ እንደሌለበት ከአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 11(1) ፣(2) እና (3) አጠቃላይ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ነው፡፡ የሙከራ ጊዜ ቅጥር ሲፈፀም ሰራተኛው በግልጽ ሊያውቀው የሚገባው ጉዳይ ሲሆን የሙከራ ጊዜ እንዲኖር ስምምነት ከተደረሰም ስምምነቱ በጽሑፍ ሁኖ በሁለት ምስክሮች መረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ ሕጉ ያሳያል፡፡ በዚህ አግባብ የተደረገ የሙከራ ጊዜ ስምምነት መኖሩ ከተረጋገጠ አሰሪው ሰራተኛውን ለተቀጠረበት የሥራ መደብ ተስማሚ አለመሆኑን ካመነበት የቅጥር ውሉን ያለምንም ማስጠንቀቂያ የማቋረጥ መብት ሕጉ የሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አሰሪው ይህንኑ በሕጉ የተቀመጠውን መብቱን ሊጠቀም የሚችለው አሰሪው ሰራተኛውን ለሙከራ ጊዜ ለመቅጠር ወስኖ ሰራተኛውም ይህንኑ በግልጽ አውቆትና ተገንዝቦት በፅሑፍ ያሰፈሩት ስምምነት መኖሩ ከተረጋገጠ ብቻ ነው፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመጣ አመልካች ተጠሪን በ43ኛው ቀን ያሰናበታቸው ስለመሆኑ ቢረጋገጥም ለሙከራ ጊዜ የቀጠራቸው ስለመሆኑና በዚህ ረገድም ተጠሪ የሚያውቁት ውል መኖሩን ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች አላረጋገጡም፡፡ ይልቁንም አመልካች አለኝ የሚለውና የተጠሪ ፊርማ ተቀምጦበታል በተባለው ሰነድ ላይ ያለው ፊርማ በባለሙያ እንዲመረመር ተደርጎ ፊርማው የተጠሪ ያለመሆኑና አመልካች ያቀረበው ይኼው ሰነድ ከሌሎች የተጠሪ ማስረጃዎች ጋር ሲመዘን የማስረጃነት ክብደት ሊሰጠው የማይገባ መሆኑ መረጋገጡን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ ስለሆነም አመልካች ተጠሪ ለሙከራ የተቀጠሩ በመሆኑ ያለምንም ማስጠንቀቂያ የማቋረጥ መብት አለኝ በማለት የሚያቀርበው ክርክር በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 11(3) ስር የተቀመጠውን ድንጋጌ ሙሉ ይዘትና መንፈስ ያላገናዘበ ሁኖ አግኝተናል፡፡ ተጠሪ ያለማስጠንቀቂያ ሊያሰናብት የሚያስችል ጥፋት የፈፀሙ ስለመሆኑ አመልካች ገልጾ የሚያቀርበው ክርክርም ስንብቱ የሙከራ ጊዜ ውስጥ የተከናወነ ነው በማለት ከሚያቀርበውና ሕጋዊ ካልሆነው ክርክሩ ጋር አብሮ የማይሄድና በተገቢው ማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን ፍሬ ነገሩን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያለው የወረዳው ፍርድ ቤት ያረጋገጠው ጉዳይ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በአጠቃላይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስንብቱ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 11(3) ድንጋጌን

ያላገናዘበ መሆኑን በመጥቀስ የሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የሐዋሳ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ማፅናቱ የሚነቀፍበትን የሕግ አግባብ ስለሌለ በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አልተፈጸመም በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በሐዋሳ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 06177 በ29/02/2009 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 09913 በ03/08/2009 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበረውን የሥራ ውል ያቋረጠው ከሕግ አግባብ ውጪ ነው ተብሎ ብር 16,522.00 (አስራ ስድስት ሺህ አምስት መቶ ሃያ ሁለት ብር) አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ተብሎ በተወሰነው ውሳኔ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህትት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

<u>ት ዕ ዛ ዝ</u>

በ19/08/2009 ዓ/ም የተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው አካላት ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

ቅ/ሀ

የሰ/መ/ቁ. 138054

ሐምሌ 28 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ፀጋይ አስማማው

አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- የላሊበላ ማር ሙዝየም - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ማሬ በዛ - የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በአማራ ብ/ክ/መ/ የሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር ላስታ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በወረዳ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች ተከሳሽ የነበረ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ ነበረች፡፡ የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ ያቀረቡት ክስ መሰረታዊ ይዘት በአመልካች ድርጅት ከመስከረም 2004 ዓ.ም ጀምሮ በቀን ብር 45.00 /አርባ አምስት / እየተከፈላት እየሰራች እያለ መጋቢት 30 ቀን 2008 ዓ.ም ያለአግባብ ከስራ ስላሰናበተኝ የስንብት ክፍያ፤ የካሳ ክፍያ፤ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፤ የህዝብ በዓላት፤ የዓመት ዕረፍት፤ የትርፍ ሰዓት ክፍያዎች በጠቅላላ ብር 24,020.60 /ሃያ አራት ሺህ ሃያ ብር ከስልሳ ሳንቲም/ እንዲከፍለኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የአሁን አመልካችም በተከሳሽነት ቀርቦ በሰጠው መልስ ተጠሪ የቀን ሰራተኛ ስለሆነች በአሰሪና ሰራተኛ ህግ ልትዳኝ አይገባም፤ የህዝብ በዓላትና የትርፍ ሰዓት ክፍያ ክስ ከከሰሰችበት ወደኋላ እስከ ስድስት ወር ድረስ ያለውን ብቻ እንጂ መጠየቅ የምትችለው ካዛ በፊት ያለው በይርጋ ቀሪ ስለሚሆን ልትጠይቅ አይገባም፤የዓመት ዕረፍት ከ2 ዓመት በላይ ያለው በይርጋ ይታገዳል

በማለት የመጀመሪያ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ጉዳዩ አስመልክቶ የሰጠው መልስ ደግሞ ተጠሪ ከስራ የተሰናበተችው ስራው እየቀነሰ ስለሆነ ተቀንሳ ነው፤ የኮንስትራክሽን ድርጅት የሆነ አሰሪ ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 30 እና በሰበር መዝገብ ቁጥር 42075 እና 39042 መሰረት  የስራ መጠን በቀነሰ ጊዜ ሰራተኞች ለማሰናበት የማስጠንቀቂያና ሌሎች የቅነሳ ስርዓቶችን እንዲከተል የማይጠበቅበት በመሆኑ ተጠሪ የካሳ ክፍያ፤ ያለማስጠንቀቂያና የአገልግሎት ክፍያ ልታገኝ አይገባም፤የአመት እረፍት ይከፈላታል ከተባለ የሁለት ዓመት ብቻ ነው ሊከፈላት የሚገባው ሲል የመከላከያ መልሱን አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማና ማስረጃ ከመዘነ በኋላ ተጠሪ ከስራ የተሰናበተችው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 29 እና 30 በተደነገገው መሰረት በመሆኑ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፤ የካሳ ክፍያ አመልካች ሊከፍል አይገባም፤ የሁለት ዓመት እረፍት ክፍያ ብር 1,485.00 /አንድ ሺህ አራት መቶ ሰማንያ አምስት ብር/፤ የህዝብ በዓል የአንድ ቀን ብር 90.00 /ዘጠና ብር/ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል፤ ስራው ሙሉ በሙሉ ሳያልቅ ስራው እየቀነሰ በመምጣቱ ምክንያት ከስራ የተቀነሰ ሰራተኛ በአዋጁ አንቀጽ 39/1/ሐ/ መሰረት የስራ ስንብት ክፍያ ማግኘት ያለበት ስለሆነ አመልካች ለተጠሪ የስራ ስንብት ክፍያ ብር 3,000.00 /ሶስት ሺህ ብር/ እንዲከፍል ሲል ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለሰሜን ወሎ ዞን መስተዳድር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ፍርድ ቤቱም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.337 መሰረት ይግባኙ በትእዛዝ ሰርዞታል፡፡ በመቀጠል አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታውን ያቀረበ ቢሆንም በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም በማለት አቤቱታው በትእዛዝ ሰርዞታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች የካቲት 17 ቀን 2009 ዓ.ም በፃፈው አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝሮ አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ግንቦት 14 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር

መርምረናል፡፡ እንደመረመርነው የስራ ስንብት ክፍያ ይከፈል ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከመዝገቡ መገንዘብ የተቻለው የአሁን ተጠሪ ከስራ እንዲሰናበት የተደረገው በአመልካች ድርጅት የተያዘው የህንፃ ስራ ፕሮጀክት ስራው እየተጠናቀቀ በመሄዱ ነው፡፡ የስራ ውል ሊቋረጥ የሚችልባቸው መንገዶች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 23 ስር ተመልክቷል፡፡ አንደኛው መንገድ በአሰሪው አነሳሽነት የሚደረግ የስራ ውል መቋረጥ እንደሁኔታው በማስጠንቀቂያ ወይም ያለማስጠንቀቂያ ሊደረግ የሚችል ሆኖ የምክንያቶቹ ዝርዝር እና አፈፃፀሙ ከአንቀፅ 26 እስከ 30 ተደንግገው ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በሕብረት ስምምነት ያለማስጠንቀቂያ ውሉን ለማቋረጥ የሚያበቃ ምክንያት ተደርጎ የተወሰደ ጉዳይም በአሰሪው አነሳሽነት ያለማስጠንቀቂያ ውሉን ሊያቋረጥ የሚችል መሆኑ በአንቀጽ 27/1/ተ/ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ስለዚህ በአዋጁ በተደነገጉ ምክንያቶችና ሁኔታዎች የሚፈፀም የስራ ውል ማቋረጥ ህጋዊ የስራ ማቋረጥ ሲሆን ከነዚህ ውጭ የሚደረጉ የስራ ውል ማቋረጥ ህገወጥ መሆኑን ከአንቀጽ 42 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ለአንድ ኮንስትራክሽን ስራ የተቀጠረ ሰራተኛ የኮንስትራክሽኑ ስራ ሲያልቅ ወይ ሲጠናቀቅ በወሳኝ ደረጃ የሚገኝ ሆኖ እያለ አሰሪ የስራ ውሉ ማቋረጥ እንደሚችል እርምጃው ከህግ ውጭ ነው የሚያሰኝ ህጋዊ ምክንያት የለውም፡፡ በኮንስትራክሽን የሚሰሩ ስራዎች በባህሪያቸው በተወሰነ ጊዜ የሚያልቅ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ተጠሪ የተሰማራችው የግንባታ ፕሮጀክት መሆኑ በግራ ቀኙ ተከራካሪ ወገኖች የሚያከራክር አይደለም፡፡ በፕሮጀክት የተያዘው ስራ ሲጠናቀቅ አሰሪው ሰራተኞች ይዞ የሚቆይበት ሁኔታ ሊኖር አይችልም፡፡ በመሆኑም የግንባታ ስራው በሂደት እየተጠናቀቀ ሲሄድ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 30 መሰረት ስንብቱ መፈጸሙ በአጠቃላይ የፕሮጀክት ስራ እንደመሆኑ መጠን ተጠሪ የምትሰራው ስራ እየተጠናቀቀ በመሄዱ አመልካች የወሰደው እርምጃ በህጋዊ መንገድ መሆኑን የስር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡ የአመልካች ጥያቄ በዚህ ሁኔታ ከስራ የተሰናበት ሰራተኛ የስራ ስንብት ክፍያ ሊከፈለው አይገባም የሚል ነው፡፡ የግንባታ ስራው ባለበት ጊዜ የሚሰሩ ስራው ሲገባደድ ወይም ሲጠናቀቅ የስራ ውላቸው የሚቋረጥ ሰራተኞች ናቸው፡፡ ለእንደዚህ አይነት የስራ ውል የተቀጠሩ ሰራተኞች በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 24 ንዑስ 1 መሠረት ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሰራተኞች እንደሆኑ የሰበር ችሎቱ ከዚህ በፊት በመዝገብ ቁጥር 22956 አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠረ ሰራተኛ የስራ ውሉ የሚቋረጥበት ጊዜ ሲደርስ ከስራ ማሰናበት እንደሚቻል ከአዋጁ አንቀፅ 24 ንዑስ አንቀፅ 1 ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም አመልካች ተጠሪን ያሰናበተው በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 24 ንዑስ አንቀፅ 1 እና አንቀፅ 30 ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት መሆኑ ከተረጋገጠ ለተጠሪ የስራ ስንብት ክፍያ የሚከፍልበት ምክንያት የለም፡፡ በተመሳሳይ ጉዳይ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት

በሰ/መ/ቁ 42229፤ 42368 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀፅ 2(1) መሰረት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ስለሆነም የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ተጠሪን ከስራ ያሰናበተው በአግባቡ ነው ካሉ በኋላ አመልካች ለተጠሪ የስራ ስንብት ክፍያ እንዲከፍል የሰጡት ውሣኔ ክፍል መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በላስታ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 0107289 ጥቅምት 27 ቀን 2009 ዓ/ም ተሰጥቶ በሰሜን ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 18806 ህዳር 8 ቀን 2009 ዓ/ም እና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 0316070 በትእዛዝ ያፀኑት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረትተሻሽለዋል፡፡
2. የስራ ስንብት ክፍያ ብር 3,000.00 /ሶስት ሺህ ብር /አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል የተሰጠ ውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
3. የሁለት ዓመት እረፍት ክፍያ ብር 1,485.00/ አንድ ሺህ አራት መቶ ሰማንያ አምስት ብር/ እና የህዝብ በዓል የአንድ ቀን ብር 90.00/ዘጠና ብር/ አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል የተሰጠ ውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሰ/መ/ቁ. 142752

ሐምሌ 27 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡-ፀጋይ አስማማው

አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- በከልቻ ትራንስፖርት አክሲዮን ማህበር -የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ ወልደሰንበት ዳዲ -ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 "ን" መሰረት አድርጎ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 102019 በ15/07/2009 ዓ.ም ተሰጥቶ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 26172 በ16/09/2009 ዓ.ም የተሻሻለው እና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 268330 በ28/09/2009 ዓ.ም በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ ወረዳ ፍርድ ቤት ተከሳሽ በነበረው የአሁኑ አመልካች ላይ በ28/02/2009 ዓ.ም አዘጋጅተው ባቀረቡት ክስ በተከሳሽ ድርጅት ውስጥ ከ01/02/1974 ዓ.ም ጀምሮ በመካኒክነት የስራ መደብ ላይ በመጨረሻ ብር 5,198 (አምስት ሺህ አንድ መቶ ዘጠና ስምንት) ወርኃዊ ደመወዝ እያገኙ ሲሰሩ ቆይተው ስራቸውን በ09/03/2008 ዓ.ም በራሳቸው ፈቃድ የለቀቁ መሆኑን፣አመልካች የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲፈጽም እና የመልቀቂያ /የመሸኛ/ ደብዳቤ እንዲሰጣቸው ተጠሪው በ09/03/2008 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ የጠየቁ ቢሆንም አመልካች ዛሬ ነገ እያለ አቆይቶ በ25/08/2008 ዓ.ም የሰጣቸው መሆኑን የሚገልፅ ሆኖ፡-

1. የአዋጅ ቁጥር 377/1996 ማሻሻያ በሆነው አዋጅ ቁጥር 494/1998 አንቀጽ 39 እና 40 ድንጋጌዎች መሰረት የ34 ዓመት የአገልግሎት ክፍያ ብር 62,376፣
2. በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 77 (5) መሰረት የ2005፣2007 እና 2008 ዓ.ም. የ63 ቀናት የዓመት ዕረፍት ክፍያ ብር 10,915.80፣
3. በ2007 ዓ.ም. ለሰራተኞች የተከፈለ ቦነስ የአንድ ወር ተኩል ደመወዝ ብር 7,797 እና
4. በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 38 መሰረት ክፍያ የዘገየበት የሶስት ወር ደመወዝ ብር 15,594

በድምሩ ብር 96,682.80 (ዘጠና ስድስት ሺህ ስድስት መቶ ሰማንያ ሁለት ከሰማንያ ሳንቲም) አመልካች ድርጅት ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍላቸው እንዲሁም አስፈላጊውን ፎርማሊቲ በማሟላት የስራ ልምዳቸውን እና የክሊራንስ ደብዳቤ ለጡረታና ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እንዲያስተላልፍላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን አመልካች በበኩሉ በ22/03/2009 ዓ.ም በሰጠው መልስ ክሱ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 162 (4) መሰረት በስድስት ወር ይርጋ የሚታገድ ነው የሚል የመጀመሪያ መቃወሚያ ካስቀደመ በኃላ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ ክሱ ግልጽነት የጎደለው መሆኑን፣የጡረታ መብት ተጠቃሚ የሆነ ሰራተኛ በተደራቢነት የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት የሌለው መሆኑን፣የአመልካቹ ንብረት በዕዳ የሚፈለግባቸው መሆኑን፣ዕዳ ካለባቸው ደግሞ የስራ ልምድ ማስረጃ ከመስጠት ውጪ አመልካቹ የመልቀቂያ ደብዳቤ ለመስጠት የማይገደድ መሆኑን፣የዓመት ዕረፍታቸውን በወቅቱ መጠቀም ሲገባቸው ያልተጠቀሙ መሆኑን፣ዕዳ እያለባቸው እና የሚከፈላቸው ክፍያ በሌለበት ሁኔታ ክፍያ የዘገየበት መቀጫ መጠየቃቸው ተገቢ አለመሆኑን ገልጾ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም የይርጋ መቃወሚያውን በ17/04/2009 ዓ.ም በብይን ካለፈ እና በፍሬ ጉዳዩ ረገድ ክሱን እና የተጠሪውን ምስክሮች ከሰማ በኃላ የግራ ቀኙን አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ፡-

1. ተጠሪው ስራቸውን እንደለቀቁ የጡረታ ተጠቃሚ መሆናቸውን አመልካች ያላስረዳ በመሆኑ የ34 ዓመት የአገልግሎት ክፍያ ብር 62,376፣
2. የ2008 ዓ.ም. የዓመት ዕረፍት ክፍያ ብር 3,811 እና
3. የ2007 ዓ.ም. ቦነስ ብር 7,797

በድምሩ ብር 73,984.86 ከ10% የጠበቃ አበል ጋር አመልካች ለተጠሪው እንዲከፍል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይህንን ውሳኔ ያሻሻለው የቦነስ ክፍያው ከስራ ውል መቋረጥ ጋር ግንኙነት የሌለው በመሆኑ በይርጋ የሚታገድ ነው በሚል ምክንያት በዚህ ረገድ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል ብቻ በመሻር ሲሆን አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ

ተጠሪው የስራ ውላቸውን በፈቃዳቸው ያቋረጡት በ09/03/2008 ዓ.ም. ሆኖ ክስ ያቀረቡት ደግሞ በ28/02/2009 ዓ.ም መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ አመልካች ያቀረበው የይርጋ መቃወሚያ በስር ፍርድ ቤቶች ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 162 እና 164 ድንጋጌዎች አንጻር ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት እንዲቻል ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ነጥብ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት የስር ፍርድ ቤቶች አመልካቹ ያቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ ያደረጉት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 162 (4) የተመለከተው የስድስት ወር የይርጋ ጊዜ መቆጠር መጀመር የሚገባው አመልካች እንደሚከራከረው ተጠሪው ስራቸውን በፈቃዳቸው ከለቀቁበት 09/03/2008 ዓ.ም ጀምሮ ሳይሆን አመልካች የመሸኛ ደብዳቤ ለተጠሪ ከሰጠበት ከ25/08/2008 ዓ.ም ጀምሮ ነው፣ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ሲቆጠር ደግሞ ክሱ እስከቀረበበት 28/02/2009 ዓ.ም ድረስ ስድስት ወር አላለፈውም በማለት መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡በይርጋ ረገድ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ይህ ብይን ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ወይስ አይደለም? ወደሚለው ጥያቄ ከመገባቱ በፊት በስር ፍርድ ቤቶች በተሰጠው የይርጋ ብይን ረገድ አመልካቹ በሰበር አቤቱታው ላይ ያቀረበው የቅሬታ ነጥብ መኖር አለመኖሩን በቅድሚያ ማጤኑ ተገቢ ሆኖ ተገኝቶአል፡፡አመልካች በ01/10/2009 ዓ.ም አዘጋጅቶ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ ላይ የይርጋ መቃወሚያ አቅርቦ እንደነበረ እና ነገር ግን ውድቅ እንደተደረገበት የክርክሩን ሂደት እና የጉዳዩን አመጣጥ ለማሳየት ያህል ከመጥቀሱ ውጪ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ቅሬታውን በገለጸበት እና የዚህን ሰበር ችሎት ዳኝነት በጠየቀበት የሰበር አቤቱታው ክፍል ላይ በስር ፍርድ ቤቶች በይርጋ ረገድ የተሰጠው ብይን እና ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለመሆኑ የገለጸው ነገር አለመኖሩን እና የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በይርጋ ምክንያት እንዲሻርለት ያቀረበው የዳኝነት ጥያቄ አለመኖሩን የሰበር አቤቱታው በግልጽ ያመለክታል፡፡ተጠሪው በሰበር መልሳቸው ላይ በዚህ ረገድ ባቀረቡት የክርክር ነጥብ ረገድም አመልካቹ በመልስ መልሱ ላይ የሰጠው ማስተባበያ የለም፡፡ማንኛውም ወገን የይርጋው ጊዜ ካለፈ በኃላ የይርጋ ጊዜን እንደመቃወሚያ አድርጎ ለማንሳት ያለውን መብት ሊተው የሚችል ስለመሆኑ በአዋጁ በአንቀጽ 165 የመጀመሪያ ዐረፍተ ነገር ላይ የተመለከተ ሲሆን ዳኞች በገዛ ስልጣናቸው የይርጋውን ደንብ መከላከያ ለመጥቀስ የማይችሉ ስለመሆኑም ከአዋጁ አንቀጽ 162/5/ እና ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1856 (2) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካቹ በሰበር አቤቱታው ላይ የቅሬታ ነጥብ አድርጎ ባላቀረበበት ሁኔታ የይርጋ ጉዳይ በክርክር ጭብጥነት መያዙ ሕጋዊ መሰረት ያለው ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

አመልካቹ የሰበር አቤቱታ ያቀረበበት ዓቢይ ነጥብ ተጠሪው የጡረታ መብት ተጠቃሚ ሆነው ሳለ የስራ ስንብት ክፍያ በተደራቢነት የተወሰነላቸው አላግባብ ነው የሚል ሲሆን ተጠሪው ስራቸውን እንደለቀቁ ወዲያውኑ የጡረታ አበል ተጠቃሚ አለመሆናቸው በስር ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ የሚያመለክት በመሆኑ በዚህ ረገድ በአመልካቹ የቀረበው ክርክርም የመዝገቡን ግልባጭ መሰረት ያደረገ አይደለም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 102019 በ15/07/2009 ዓ.ም. ተሰጥቶ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 26172 በ16/09/2009 ዓ.ም. የተሻሻለው እና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 268330 በ28/09/2009 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት በውጤት ደረጃ ፀንቷል፡፡
2. በአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 103396 የተያዘው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ01/10/2009 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡
3. የውሳኔው ቅጂ ለስር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፡
4. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ አመልካች የራሱን ይቻል፡፡
5. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ.130944

ሐምሌ 26 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ዳኜ መላኩ

አሰግድ ጋሻው

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች ፡- አቶ ሞገስ ወ/መላክ - አልቀረበም

ተጠሪ ፡- የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ - አልቀረቡም

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በመ/ቁ ጡ/ይ/1/1/155/2008 በቀን 28/07/2008 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 126913 በቀን 15/09/2008 ዓ.ም በማጽናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው ፡፡

ጉዳዩ የኮንትራት ሥራ አገልግሎት ጊዜ ለጡረታ መብት አያያዝን የሚመለከት ነው ፡፡ አመልካች ለመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አዲስ አበባ ሪጅን /በተጠሪ/ ባቀረቡት አቤቱታ ከ11/06/68 እስከ 25/03/73 በቀድሞ ግብርና ሚኒስቴር ፣ከ12/01/84 እስከ 30/01/92 በአዲስ አበባ መስተዳደር የፕሮጀክት ፅ/ቤት ከ02/02/92 እስከ 07/11/2000 አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የህብረት ሥራ ማህበራት ማደራጀትና ማስፋፊያ ቢሮ ለ21 ዓመት ከ8 ወር ከ9 ቀን ያገለገሉ በመሆኑ የጡረታ አበል ይወሰንልኝ በማለት ያቀረበውን ከ02/02/92 እስከ 30/10/92 ያለውን አገልግሎት ውድቅ በማድረግ እንዲሁም ከሰኔ 01/1995 ዓ.ም በፊት ያለው የኮንትራት አገልግሎት ጊዜ አግባብ ባለው አካል ያልተፈቀደ በመሆኑ ለጡረታ አይታሰብም በማለት በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ያቀረቡትን ይግባኝ የተመለከተው የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የአመልካች አገልግሎት ከ21 ዓመት በላይ ቢሆንም በኮንትራት ተቀጥሮ በሰሩባቸው ጊዜያት

የጡረታ መዋጮ ተቀንሶ ገቢ ያለመሆኑ በጡረታ አዋጅ ቁጥር 345/1995 መሠረት በኮንትራት የተፈፀሙት አገልግሎት እንዲያዝ ከሚመለከተው ክፍል የተፈቀደበት ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ የመንግስት ሰራተኞች ማህበራዊ ኤጀንሲ የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው በማለት አጽንቷል ፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ያቀረቡትን ይግባኝ የተመለከተው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም መልስ ሰጪን ሳይጠራ የአመልካችን የይግባኝ ቅሬታ ባለመቀበል በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት አሰናብቶታል ፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታም የቀረበው ይህንን በመቃወም ሲሆን ይዘቱም የመንግስት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀጽ 11/4/መ በቋሚነት በተቀጠረበት የመንግስት መ/ቤት በጊዜያዊነት በተከታታይ አገልግሎት የሰጠበት ጊዜ ለጡረታ አገልግሎት የሚቆጠር መሆኑን የሚደነግግ በመሆኑና በሌላ አግባብ ባለው አካል ማስወሰን የሚጠይቅ አይደለም ፣ ከሆነም የጡረታ ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ነው፣ በኮንትራት ተቀጥሮ በስራሁበት ጊዜ የሚከፈለው የጡረታ መዋጮን በተመለከተ በአዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀጽ 11/6/መ/ ሆነ በአዋጅ ቁጥር714/2003 አንቀጽ 17/5/ መሰረት የኮንትራት ወይም ጊዜያዊ አገልግሎት ለመያዝ እንደቅድመ ሁኔታ ሠራተኛው የራሱንና የአሰሪውን የጡረታ መዋጮ ድርሻ ጨምሮ ራሱ ባቀረበ ጊዜ የሚከፍለው እንጂ በአገልግሎት ጊዜ አይደለም ፣በዚህ መሠረት ለመክፈል አመልክቻለሁ ፡፡ ስለሆነም የተፈፀመው ስህተት ታርሞ የኮንስትራት ጊዜው ታስቦ አበል ይወሰንልኝ የሚል ነው ፡፡የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች በቋሚነት ከመቀጠራቸው በፊት በመንግስት መ/ቤት በኮንትራት የሰሩበት ጊዜ አገልግሎት ለጡረታ አይታሰብም መባሉን በአዋጅ 714/2003 አንቀፅ 17/3 /ሠ/ መሰረት ለመመርመር ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዞ በሰጠው መልስ አመልካች ለጡረታ አገልግሎት ሊያዝልኝ ይገባል ያሉት ከ12/01/1984- 30/01/1992 በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፕሮጀክት ጽ/ቤት በጊዜያዊነት የፈፀሙት ሲሆን ይህም በአዋጅ 345/05 እና 714/03 ከመውጣታቸው በፊት በመሆኑ የአመልካች ጥያቄ ተፈጻሚነት የለውም ፣ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የነበረውም 209/55 ሲሆን የኮንትራት አገልግሎት ለጡረታ አይታሰብም፣ አመልካች ተጠሪ በኮንትራት በሰራሁበት ጊዜ የጡረታ መዋጮ ተቀንሶ ገቢ አልተደረገም ያሉትም የጡረታ መዋጮ የሚሰበሰበውም ሆነ የጡረታ ተጠቃሚነት ባለመብት የሚረጋገጠው ቋሚ ለሆነ የመንግስት ሰራተኛ ነው ፡፡ ስለሆነም በስር ፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመ ባለመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ይደረግልን ብሏል ፡፡ የአመልካች የመልስ መልስም ቀርቧል ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተለገፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን ለሰበር ችሎት መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር ጉዳዩ ለሰበር ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምረነዋል ፡፡ እንደመረመርነው አመልካች በኮንትራት የፈፀሙት አገልግሎት ለጡረታ አይታሰብም የተባለው ነጥብ ከህጉ ጋር በማገናዘብ በቅድሚያ መታየት ያለበት ነው ፡፡

አዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀጽ 11/4/ /ሠ/ ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ አዋጁ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ በቋሚነት በተቀጠረበት መ/ቤት በጊዜያዊነት /በኮንትራት/ በተከታታይ አገልግሎት የሰጠበት ጊዜ ለጡረታ ተግባር ይታሰብለታል ሲል በተመሳሳይ መልኩ አዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 17/3/ /ሠ/ ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ በቋሚነት በተቀጠረበት መ/ቤት በጊዜያዊነት ሳያቋርጥ በተከታታይ አገልግሎት የሰጠበት ጊዜ ለጡረታ ተግባር እንደሚያዝለት ይደነግጋል ፡፡

አመልካች በኮንትራት አገልግሎት ከሰኔ 1 ቀን 1995 ዓ.ም በፊት የሰጠባቸው ደግሞ ከ12/01/84 እስከ 30/01/92 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፕሮጀክት ጽ/ቤት እና ከ02/02/92 እስከ 30/10/92 ድረስ ያሉት ጊዜያት መሆኑን ከክርክሩ መገንዘብ ይቻላል፡፡ አመልካች እነዚህንየኮንትራት /ጊዜያዊ/ ሥራ አገልግሎት የሰጠው በዚያው በቋሚነት ተቀጥሮ በሚሠራበት መ/ቤት አይደለም፣ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር345/1995 አንቀጽ 11/6 /መ/ ሆነ በአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 17/5/ መሠረት የኮንትራት ወይም ጊዜያዊ አገልግሎት ለመያዝ እንደቅድመ ሁኔታ ሠራተኛው የራሱንና የአሰሪውን የጡረታ መዋጮ ድርሻ ጨምሮ ራሱ ቀርቦ ስለመክፈሉ አልተረጋገጠም፡፡ በሌላ በኩልም የአመልካች የኮንትራት /ጊዜያዊ/ የስራ አገልግሎት ጊዜ የተፈፀሙት አዋጅ ቁጥር 345/1995 ሆነ አዋጅ ቁጥር 714/2003 በስራ ላይ በነበሩበት ጊዜ አይደለም ፡፡ እንደዚህ በሚሆን ጊዜ ደግሞ ተፈጻሚነት የሚኖረውን አዋጅ በተመለከተ በሰበር መ/ቁ 50590፣50591 እና 80323 በተሰጠው ትርጉም መሠረት አዋጅ ቁጥር 345/1995 ከመውጣቱ በፊት የተፈጠሩ ህጋዊ ሁኔታዎች ተፈጻሚ የሚሆነው አዋጅ ቁጥር 209/55 ነው ፡፡ በዚህ አዋጅ መሠረት ደግሞ የኮንትራት አገልግሎት ለጡረታ አይታሰብም ፡፡

በሌላ በኩልም በአዋጅ ቁጥር 345/1995 አንቀጽ 17/5/ በኮንትራት /በጊዜያዊነት/ የተሰጠ አገልግሎት ለጡረታ ተግባር የሚያዘው በአዋጅ ቁጥር 345/1995 በሥራ ላይ ከዋለ በኂላ ቋሚ ሠራተኛ ለሆነና በአዋጅ ቁጥር 907/2007 በፀደቀ ቀን ሥራ ላይ ለሚገኝ ሠራተኛ መሆኑን ያስገነዝባሉ ፡፡

በአጠቃላይ የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ አመልካች በጡረታ አዋጅ ቁጥር 345/1995 መሠረት ቀደም ሲል በኮንትራት የፈፀሙት አገልግሎት ለጡረታ ሊያዝ አይገባም በማለት የሠራተኛና ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ውሳኔ ያፀናው መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህ መሰረት ተከታዩን ውሳኔ ሠጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባዔ በቁጥር ጡ/ይ/1/1/155/2008 በቀን 28/07/2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 126913 በ15/09/2008 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ፀንቷል ፡፡
2. አመልካችና ተጠሪ በዚህ ችሎት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/አ

የሰ/መ/ቁ. 132861

ሐምሌ 28 ቀን 2009 ዓ/ም

ዳኞች፡-ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

ጳውሎስ አርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካቾች፡- 1. አቶ እርጋጤ መድበው 2. ወ/ሮ አበበች ከተማ

3 አቶ ጋዲሳ ረጋሳ 4. አቶ መኮንን ገ/ማርያም

5 አቶ ኃይሌሚካኤል ሰናይ 6. አቶ ዘውዱ ገ/ጻድቅ

7. አቶ እንዳለ ጎሣዬ 8 . አቶ መኩሪያ ወ/ሥላሤ

9 አቶ አለምሰገድ ወ/አማኔኤል 10. የ፲ አለቃጥላሁን ከበደ

11 አቶ መስፍን በቀለ 12. አቶ አብርሃም ለማ

13. አቶ በረሁን ማሞ 14. አቶ ተምትሜ ዓለሙ

15 ም/መ/አለቃ አባተ መድበው 16. አቶ ደምሴ ንጉሴ

17. አቶ ሽመልስ ዓለሙ 18. አቶ ፍጹም ካህሳይ

19 አቶ ግርማ ተሰማ 20. አቶ አያሌው ፋንታዬ

21 አቶ ወንድሙ ገብሬ 22. አቶ ኃይሉ ቡራዩ

ተጠሪ፡- የመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ- ነ/ፈጅ ሄኖክ መሳይ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ ያለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የጉዳዩ አመጣጥ የዘለቄታ ጡረታ አበል እንዲከፈል እንዲወሰን ነው፡፡ የአሁኑ አመልካቾች ለመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና አጀንሲ የዘለቄታ የጡረታ አበል እንዲወሰንላቸው ጥያቄ አቅርበው ኮሚቴው ጉዳዩን ከመረመረ በኃላ በመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 907 አንቀጽ 27 እና በመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 1/2008 አንቀጽ 63 ተራ ቁጥር 3 መሠረት አገልግሎታቸው ከ20 ዓመት በታች ስለሆነ የሚወሰንላቸው የአንድ ጊዜ የዳረጎት አበል ወይም የጡረታ መዋጮ ተመላሽ ወይም የዘለቄታ ጡረታ አበል የለም ሲል ወስኗል፡፡፡

ይህን ውሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁኖቹ አመልካቾች ይግባኝ ለማኅበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አቅርበው የመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ኮሚቴ ውሳኔ ፀንቶባቸዋል፡፡

የአሁኑ አመልካቾች ውሳኔውን ለማስለወጥ ይግባኝ ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ተቀባይነትን ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

አመልካቾች የመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ፣ የማኅበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሰጡት ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት የሚሉባቸውን ምክንያቶች መስከረም 18 ቀን 2009 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ፡- በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 907 አንቀጽ 19 /2/ ላይ ማንኛውም መንግሥት ሠራተኛ ቢያንስ 10 ዓመት ያገለገለ የጡረታ መውጫ እድሜው ሲደርስ ጡረታ ያገኛል ሲል በግልጽ ደንግጎ እያለ የአመልካቾች አገልግሎት ከ20 ዓመት በታች ነው በማለት የዘለቄታ የጡረታ አበል አይገባቸውም ተብሎ መወሰኑ ግልጽ የሆነ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪው አቤቱታውን መርምሮ የአመልካቾች የጡረታ መብት ጥያቄ ከአዋጅ ቁጥር 907/2007 አንጻር የአገልግሎት ዘመናቸው ከ20 ዓመት በታች ስለሆነ የዳረጎት አበልም ሆነ የዘለቄታ የጡረታ አበል ሊወሰንላቸው አይገባም ተብሎ በሥር የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል አቤቱታው ለሰበር ችሎት ይቅረብ ሲል አዟል፡፡

ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ በቀን 6//6/2009 ዓ.ም የተጻፈ መቃወሚያ እና መልስ አቅርቦ የተከራከረ ሲሆን አመልካቾቹም መጋቢት 14 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን ጉዳዩን አጣሪው ከያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም አመልካቾች በመንግሥት ሥራ እያገለገሉ ቆይተው ከ1983 ዓ.ም ወዲህ በጽኑ እስራት ምክንያት አገልግሎት ያቋረጡ መሆናቸውን፣ የጽኑ እስራት ጊዜያቸውን ጨርሰው የወጡ መሆናቸውን፣ አስቀድመው በመንግሥት ሥራ ያገለገሉበት ዝቅተኛው 10 ዓመት ሲሆን ከፍተኛው 18 ዓመት መሆኑን አመልካቾች ያቀረቡት ዝርዝር እንዲሁም ተያይዞ የቀረበልን የውሳኔ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ የሥር መንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና አጄንሲ ኮሚቴ እንዲሁም የማኅበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ለውሳኔያቸው መሰረት ያደረጉት ዋናውና መሠረታዊው ነጥብ የአመልካቾች አገልግሎት ከ20 ዓመት በታች ስለሆነ የዘለቄታ የጡረታ አበል አይገባቸውም የሚል ነው፡፡ ይህ ውሳኔ ከተሻሻለው የመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና አዋጅ ቁጥር 907 አንቀጽ 5 /2/ አንጻር ሲታይ ተገቢ ነው ወይ? የሚለውን መመልከት ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት የሚያስችል ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሠረቱ ተጠሪ ለዚህ ችሎት ባቀረበው መልስ ላይ በአዋጅ ቁጥር 209/55፣በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 5/67 እና አዋጅ ቁጥር 714/2003 ላይ የተደነገገውን ከ20 ዓመት በላይ አገልግሎት እያነሳ የተከራከረ ሲሆን በእነዚህ አዋጆች ላይ የተደነገገው እና የአሁኑ ተጠሪዎች ስለመብታቸው የሚከራከሩበት የአገልግሎት ዘመን በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 907 ተተክቷል፡፡ በተሻሻለው አዋጅቁጥር 907 አንቀጽ 5/2/ ላይ ቢያንስ 10 ዓመት ያገለገለ የመንግሥት ሠራተኛ ይህ ማሻሻያ አዋጅ ከፀናበት ቀን አንስቶ በራሱ ፈቃድ ወይም በዚህ አዋጅ ከተጠቀሱት ውጪ በሆነ ምክንያት አገልግሎት ካቋረጠ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 18 1/ በተደነገገው መሠረት የጡረታ መውጫ እድሜው ሲደርስ የአገልግሎት ጡረታ አበል እስከ እድሜ ልክ ይከፈለዋል ሲል ይደነግጋል፡፡ በዚህ ንዑስ አንቀጽ ድንጋጌ መሠረት የዘለቄታ ጡረታ አበል ለማግኘት ቢያንስ አስር ዓመት ማገልገል ሲሆን በአዋጁ አንቀጽ 18/1/ መሠረት የጡረታ እድሜ መድረስ ነው፡፡ የአመልካቾች የጡረታ እድሜ ከ60 ዓመት በላይ ሲሆን በተያዘው ጉዳይ አከራካሪ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ተጠሪ ሲከራከር የነበረ አገልግሎታቸው ከ20 ዓመት በታች ስለሆነ የዘለቄታ ጡረታ አበል አይገባቸውም በማለት ነው፡፡ ይህ ክርክር ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 714/2003 አንቀጽ 19/2/ ላይ የተደነገገውን ድንጋጌ መሠረት ያደረገ ሲሆን ይህ ደግሞ በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 907 አንቀጽ 5/2/ የተተካ በመሆኑ የተጠሪ የ20 ዓመት አገልግሎት ክርክር ህጋዊ መሠረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 1/2008 አንቀጽ 63/3/ ድንጋጌም ቢሆን አዋጁን ሊጻረር አይችልም፡፡

ምክንያቱም መመሪያው አዋጁን ማስፈጸሚያ ነው እንጂ በአዋጁ የተደነገገውን ድንጋጌን ሊቃረን የሚችልበት የህግ አግባብ ባለመኖሩ ምክንያት ነው፡፡

ሌላው የተጠሪ ክርክር የተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 907 አንቀጽ 5/2/ አዋጁ በሚወጣበት ጊዜ በሥራ ላይ ያሉትንና ከአዋጁ በኋላ የጡረታ እድሜያቸው ሲደርስ ጡረታ የሚወጡትን የመንግሥት ሠራተኞችን የሚመለከት ነው የሚል ነው፡፡ ይህ ክርክር የማሻሻያ አዋጁን አንቀጽ 5/2/ 'ን' መሠረት ያደረገ አይደለም፡፡ የአሁኑ አመልካቾች የዘለቄታ የጡረታ አበል እየጠየቁ ያሉት በገዛ ፈቃዳቸው ሥራ ለቀው ሳይሆን ታስረው በመቆየታቸውና እድሜያቸው ለጡረታ የደረሰ በመሆኑ ነው፡፡ ይህም ከተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 907 አንቀጽ 11/9/ አንጻር ሲታይ የአመልካቾች አቤቱታ ተቀባይነት ያለው መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

በአጠቃላይ የማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲም ሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ከላይ የተመለከቱትን መሠረታዊና ህጋዊ ሁኔታዎችን በአግባቡ ሳያጤኑ የሰጡት ውሳኔም ሆነ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ኮሚቴ በቀን 9/6/2008 ዓ/ም ፣ የማኅበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ በቁጥር ይ/1/1/154/2008 በቀን 28/7/2008 የሰጡት ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 126747 ሰኔ 14 ቀን 2008 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348 /1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ የጡረታ አበል ክፍያ የመንግስት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅን ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 907/2007 ከፀናበት ከሐምሌ 1 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ለአመልካቾች እንዲከፍላቸው ተወስኗል፡፡
3. የዚህ ችሎት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. የውሳኔው ግልባጭ ለመንግሥት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ይድረሳቸው፡፡ መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

የሰ/መ/ቁ 134188

ሐምሌ 28 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ፀጋይ አስማማው

አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች ፡- አቶ ዊንታ ቦርጂ -የቀረበ የለም

ተጠሪ ፡- ይርጋለም ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግል ማህበር ……….የቀረበ የለም

መዝገቡ መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል ፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች በሐዋሳ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 31163 በ19/09/08 ዓ/ም ተሰጥቶ በሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 20112 በ24/12/08 ዓ/ም፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት በመ/ቁጥር 68973 በ09/02/2009 ዓ/ም የጸናው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡

ጉዳዩ በሥራ ላይ በሚደርስ የአካል ጉዳት የሚከፈል የካሣ ገንዘብ ጥያቄ የይርጋ ጊዜ ገደብን የሚመለከት ሲሆን አመልካች በ20/08/08 ባቀረቡት ከተጠሪ ድርጅት ጋር በፈፀሙት የቅጥር ውል መሰረት ስራ ላይ እያሉ በ17/06/2006 ዓ/ም በደረሰባቸው ከፊል አካል ጉዳት ምክንያት ህክምና ሲከታተሉ የቆዩ ቢሆንም በጥር ወር 2008 ዓ/ም ከፍተኛ የሆነ የጤና መታወክ ያጋጠማቸው መሆኑን ጠቅሰው በአዋጁ መሰረት ዘላቂ የአካል ጉዳት ካሳ እንዲከፈላቸውና ተጠሪ ድርጅት ለአመልካች ያላግባብ ደመወዝ እየቀነሰ ሲከፍል የነበረ በመሆኑ ይኼው የተቀነሰው ደመወዝም እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ድርጅትም አመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 162 ንዑስ አንቀፅ 4 የተደነገገው የስድስት ወር የይርጋ ጊዜ ገደብ አልፏል በማለት መቃወሚያ አቅርቧል ፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤትም ተጠሪ ያቀረበውን መቃወሚያ በመቀበል የአካል ጉዳት ካሳ ክስ በአንድ ዓመት፣የደመወዝ ክፍያ በስድስት ወር ይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ብይን ሰጥቷል ፡፡

አመልካች ይግባኝ ለሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ተቀባይነት ያጡ ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎትም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ብይን የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- በ17/06/2006 ዓ/ም አመልካች ስራ ላይ እያሉ የደረሰባቸው የአካል ጉዳት በህክምና ሲከታታሉ ቆይተውና ተጠሪ ድርጅትም ይህንኑ አውቆ ሲያሳክማቸው ቆይቶ ጉዳቱ ተባብሶ በአመልካች አካል ላይ የደረሰው ጉዳት ዘላቂ ጉዳት መሆኑ አመልካች ያወቁት ክስ ከመቅረቡ ከሶስት ወር በፊት ሆኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳቱ የደረሰበትን የካቲት 17 ቀን 2006 ዓ/ም ለይርጋው መቆጠር መነሻ አድርገው መያዛቸው ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርቦ በ ሰጠው መልስም ከአመልካች ጋር መጀመሪያ የተመሰረተው የስራ ውል በሕጉ አግባብ የተቋረጠ መሆኑን፣ አመልካች ጉዳት ደረሰብኝ የሚሉት በስራ ቦታ ላይ ስለመሆኑ በተጠሪ በሕጉ አግባብ ያላሳወቁ መሆኑን፣ ተጠሪ አመልካችን በስራ ላይ ጉዳት መድረሱን አምኖ ሲያሳክማቸው የነበረበት አግባብ የሌለ መሆኑንና ሌሎች ነጥቦችን በሰፊው ዘርዝሮ የአመልካች ክስ በይርጋ ውድቅ ነው ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ የአሁኑ አመልካችም የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ብይንና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ በይርጋ የታገደ ነው በማለት የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 162 ንዑስ አንቀፅ /1/ ድንጋጌ መሠረት በማድረግ የሰጡት ዳኝነት ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል ፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው ለጉዳዩ አግባብነት ያለው የይርጋ ጊዜ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 162 ንዑስ አንቀፅ 1 ስር የተደነገገው የአንድ አመት የይርጋ ጊዜ ገደብ ነው፡፡አሁን አከራካሪ የሆነው ይህ የጊዜ ገደብ መቆጠር የሚጀምረው መቼ ነው? የሚለው ነው፡፡ ይህንኑ ለመመለስ አመልካች በክሳቸው ላይ የጠቀሷቸውን መሰረታዊ ፍሬ ነገሮችንና ተጠሪም ለእነዚህ ፍሬ ነገሮች ያቀረባቸውን የክርክር ነጥቦችን መመልከቱ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ አመልካች በክሳቸው ላይ የጠቀሱት መሰረታዊ ነጥብ ከተጠሪ ጋር በመሰረቱት የስራ ውል አግባብ በስራ ላይ እያሉ የአካል ጉዳት የካቲት 17 ቀን 2006 ዓ.ም ደርሶባቸው ሕክምና

ሲከታታሉ ቆይተው ጉዳቱ ዘላቂ መሆኑን ጥር ወር 2008 ዓ.ም አካባቢ አውቀው ተጠሪ ላይ ለዚሁ ለዘላቂ የአካል ሚያዚያ 20 ቀን 2008 ዓ.ም ክስ የመሰረቱ መሆኑን ሲሆን ተጠሪ ጉዳት ካሳ እንዲከፍል አጥብቆ የሚከራከረው ደግሞ በ2006 ዓ.ም ከአመልካች ጋር የነበረው የስራ ውል በሕግ አግባብ የተቋረጠ መሆኑ በፍርድ ቤቶች ውሳኔ የተረጋገጠ መሆኑን፣ በዚህ ጊዜ ደረሰ የተባለው ጉዳትም በተጠሪ በሕጉ አግባብ ያልታወቀና በስራ ላይ የደረሰ ጉዳት ነው ሊባል የማይችል መሆኑንና አመልካች ህክምና እንዲያገኙ ሲያደርግ የቆየውም ድርጅቱ በአመልካች ላይ የደረሰውን የአካል ጉዳት በስራ ላይ የደረሰ መሆኑን በማመን ሳይሆን የድርጅቱ ባለቤት በግላቸው በሰብአዊነት ያደረጉት ተግባር መሆኑን በመዘርዘር ነው፡፡ይሁን እንጂ በ2006 ዓ/ም በአመልካች ላይ ደረሰ የተባለው የአካል ጉዳት በሕጉ አግባብ በስራ ላይ የደረሰ መሆን ያለመሆኑ፣ ተጠሪ ለህክምናው ሲያወጣው የነበረ ወጪ መኖርያ ለመኖሩና ጥር 2008 ዓ.ም በአመልካች የታወቀው የዘላቂ አካል ጉዳት በ2006 ዓ.ም በደረሰባቸው አደጋ የመጣ መሆን ያለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ በግራ ቀኙ ማስረጃ የሚታዩ ነጥቦች ከመሆናቸው ውጪ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ሊነሱ የሚችሉ ነጥቦች አይደሉም፡፡ ስለሆነም የአመልካች ክስ አመሰራረት ከተጠሪ ጋር የፀና የስራ ውል እያለ በ2006 ዓ.ም በደረሰባቸው አደጋ ምክንያት የመጣው ዘላቂ ያልሆነ የአካል ጉዳት በሕክምና ቢከታተሉም ለውጥ ሳያሳይ ቀርቶ ወደ ዘላቂ የአካል ጉዳት መሸጋገሩን የሚገልጽና ይህ ስለመሆኑ የታወቀው ደግሞ በጥር ወር 2008 ዓ/ም ጀምሮ መሆኑን የሚያሳይ እና ተጠሪም በዚህ ረገድ ግልጽ ማስተባበያ ክርክር ባለቀረበበት ሁኔታ የበታች ፍርድ ቤቶች የይርጋ ጊዜው መቆጠር ያለበት ከ17/06/2006 ዓ.ም ጀምሮ ነው በማለት የያዙት መነሻ የአመልካችን ክስ ይዘት ያላገናዘበ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ለይርጋው ጊዜ መነሻ መሆን ያለበት ጥር ወር 2006 ዓ/ም ነው ከተባለ ደግሞ አመልካቹ ክስ ያቀረቡት በ20/08/2008 ዓ.ም በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 162(1) ስር ያለው የአንድ አመት ጊዜ አላለፈም፡፡ በዚህም ምክንያት አመልካች ያቀረቡት የአካል ጉዳት ካሳ በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በሐዋሳ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 31163 በ19/09/08 ዓ.ም ተሰጥቶ በሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 20112 በ24/12/08 ዓ.ም፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር አጣሪ ችሎት በመ/ቁጥር 68973 በ09/02/2009 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2. አመልካች የአካል ጉዳት ካሳን በተመለከተ ያቀረቡት ክስ በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡ አመልካች በደመወዝ ላይ ያቀረቡት ክስ በይርጋ ውድቅ መደረጉ አልተነካም፡፡
3. በአመልካች የአካል ጉዳት ካሳ ላይ የቀረበውን የግራ ቀኙን ክርክር የሐዋሳ ከተማ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 31163 በመቀጠል ጉዳዩን በሚገባ አጣርቶ ተገቢውን ዳኝነት እንዲሰጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1) መልሰን ልከንለታል፡፡ይጻፍ፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጭ ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

ቅ/ሀ

# ፍትሐ ብሔር

# ሥነ-ሥርዓት ሕግ

የሰ/መ/ቁ. 104621

ህዳር 13 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

አብዬ ካሣሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- ወ/ሮ አዜብ ታምሩ - የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ ደጀኔ ዘውዴ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍቺ ውሳኔን ተከትሎ የተነሳ የንብረት ክፍያ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት በኮፈሌ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 10991 በ27/06/2006 ዓ.ም ተሰጥቶ በምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበርችሎት እንደቅደም ተከተሉ በመዝገብ ቁጥር 20374 በ23/07/2006 ዓ.ም. እና በመዝገብ ቁጥር 184251 በ05/10/2006ዓ.ም በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ ግራ ቀኙ በንብረት ክርክር ላይ እያሉ አመልካቿ ክሳቸውን ለማሻሻል እንዲፈቀድላቸው ጠይቀው በተፈቀደላቸው መሰረት በ07/04/2006 ዓ.ም የተሻሻለ ክስ ማቅረባቸውን፣የተሻሻለው ክስ ይዘትም ቀደም ሲል በቀረበው የንብረት ዝርዝር ውስጥ ግራ ቀኙ በጋብቻቸው ውስጥ ያፈሩት ሆኖ ነገር ግን በህጻን ረድኤት ደጀኔ ስም የሚታወቀው 200 ካ.ሜ ይዞታ ያለው ቤት ያልተካተተ መሆኑን የሚገልጽ ሆኖ ክፍፍሉ በዚህ ቤት ላይ ጭምር እንዲካሄድ የሚጠይቅ መሆኑን፣ተጠሪው የተሻሻለው ክስ ቅጂ ደርሶአቸው በ10/04/2006 ዓ.ም. በሰጡት አስተያየት የተሻሻለው የንብረት ዝርዝር ክርክሩን ወደኃላ የሚመልሰው በመሆኑ ውድቅ ተደርጎ በቀድሞው ክስ መሰረት ክፍፍሉ እንዲፈጸም መጠየቃቸውን፣ፍርድ ቤቱም የተጠሪውን

ክርክር ተገቢ አድርጎ በመቀበል አመልካች አሁን የክፍፍል ጥያቄ ያቀረቡበትን ቤት በመጀመሪያው ክሳቸው አካተው ማቅረብ ሲችሉ ሌላ ንብረት አካተው ማቅረባቸው የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 216 (3) ድንጋጌን የሚቃረን መሆኑን ገልጾ ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ ክፍፍሉ በቀደመው የንብረት ዝርዝር መሰረት እንዲቀጥል ትዕዛዝ መስጠቱን እና በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶችም ተቀባይነት ያገኘው ይኸው ውሳኔ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

የአመልካቿ የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች በፍርድ ቤቱ ፈቃድ ክሱን ካሻሻሉ በኃላ አዲስ ጥያቄን ያካተተ ስለሆነ ጉዳዩን ወደኃላ የሚመልስ ነው በማለት ማሻሻያው ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ነጥብ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በማናቸውም ጊዜ ወይም ፍርድ ቤቱ ተገቢ ሆኖ ካገኘው ተከራካሪ ወገኖች ክሳቸውን እንዲያሻሽሉና ክርክራቸውን እንዲለውጡ ሊፈቅድላቸው እንደሚችል በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕገ ቁጥር 91(1) ስር ተመልክቶአል፡፡ፍርድ ቤቱ የዚህ ዓይነቱን ፈቃድ የሚሰጠውም የክሱን መሻሻል ተገቢ እና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ስለመሆኑም ከዚሁ ድንጋጌው አጠቃላይ ይዘትና መንፈስ መገንዘብ ይቻላል፡፡በዚህ ሁኔታ ክሱ እንዲሻሻል ከተፈቀደ በኃላ ተሻሽሎ የቀረበው ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ከሰጠበት አግባብ ውጪ መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር ክሱ ውድቅ ሊደረግ የሚችልበት አግባብ የለም፡፡በተያዘው ጉዳይ አመልካች ክሱን አሻሽለው ያቀረቡት በፍርድ ቤቱ በተፈቀደላቸው መሰረት መሆኑ አላከራከረም፡፡የክሱ መሻሻል ጉዳይ ክርክሩን ወደ ኂላ የሚመልሰው ነው የሚል ከሆነ ፍርድ ቤቱ መጀመሪያውኑ የማሻሻያ ትዕዛዝ መስጠት አልነበረበትም፡፡ክሱ የሚሻሻልባቸው ነጥቦች ተገቢነት ደግሞ መመርመር ያለበት የማሻሻያ ትዕዛዙ ከመሰጠቱ በፊት እንጂ ክሱ ተሻሽሎ ከቀረበ በኃላ አይደለም፡፡ክሱ ተሻሽሎ የቀረበው ፍርድ ቤቱ ፈቃድ ከሰጠበት ነጥብ ውጪ ስለመሆኑ ፍርድ ቤቱ በውሳኔው ላይ አልገለጸም፡፡ተጠሪውም የዚህ ዓይነት ክርክር አላቀረቡም፡፡ይህም አመልካች ክሱን የሚያሻሽሉበት ነጥብ ትዕዛዙ ከመሰጠቱ በፊትም ይታወቅ የነበረ መሆኑን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡በመሆኑም ፍርድ ቤቱ ክሱ ተሻሽሎ ከቀረበ በኃላ በተሻሻለው ክስ መሰረት ክርክሩን መቀጠል ሲገባው ተጠሪው ያቀረቡትን መቃወሚያ ተቀብሎ በመጀመሪያው ክሳቸው አካተው ማቅረብ ሲችሉ በተሻሻለው ክስ ሌላ ንብረት አካተው ማቅረባቸው የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 216 (3) ድንጋጌን የሚቃረን ነው በማለት በተሻሻለው ክስ የተጠየቀውን የተጨማሪ ንብረት ክፍያ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 91 ድንጋጌን ትክክለኛ ዓላማ፣ይዘት እና አፈጻጸም መሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ

አልተገኘም፡፡የክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶችም ጉዳዩን ከዚህ አንጻር ተመልክተው ማረም ሲገባቸው ተቀብለው ማጽናታቸው ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት እና ሊታረም የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በኮፈሌ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 10991 በ27/06/2006 ዓ.ም. ተሰጥቶ በምዕራብአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበርችሎት እንደቅደም ተከተሉ በ/መ ቁጥር 20374 በ23/07/2006 ዓ.ም እና በመዝገብ ቁጥር 184251 በ05/10/2006 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች በፍርድ ቤቱ ፈቃድ አሻሽለው ያቀረቡትን ክስ ውድቅ በማድረግ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
3. የኮፈሌ ወረዳ ፍርድ ቤት አመልካች አሻሽለው ያቀረቡትን ክስ መሰረት አድርጎ ክርክሩን በመቀጠል ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 343 (1) መሰረት ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡
4. የውሳኔው ቅጂ ተገቢውን መፈጸም ያስችለው ዘንድ ለኮፈሌ ወረዳ ፍርድ ቤት፣እንዲያውቁት ደግሞ ለምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ይላክ፡፡
5. ቀሪው የውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡
6. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
7. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ጌ

የሰ/መ/ቁ. 119571

ሕዳር 14 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

አብዬ ካሳሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አቶ ባብሶ ቃልቦሬ - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ኩዘይማ ሁሴን - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 65573 መስከረም 04 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ዳኝነት መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ሊታረምልኝ ይገባል በማለት አመልካች ጥቅምት 30 ቀን 2008 ዓ.ም የተጻፈ 02 ገጽ የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ክርክሩ የገንዘብ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን በተጀመረበት የሀላባ ልዩ ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁን አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ለጉዳዩ መነሻ ምክንያት የሆነው የአሁን ተጠሪ ከአመልካች /በብር 1000/አንድ ሺህ ብር/ መስከረም ወር 2001 ዓ.ም የገዟትን አንዲት ላም ከአመልካች ዘንድ እንድትቆይ በተስማሙት መሠረት ከአመልካች ጋር ሶስት ጥጆችን ወልዳ በአሁኑ ጊዜ 14,500 ብር ሊገመቱ በሚችሉበት ደረጃ ላይ የደረሱ ቢሆንም አመልካች ከብቶችን ለተጠሪ ለመስጠት ፈቃደኛ ባለመሆኑ ከብቶችን በዓይነት እንዲመልስ ወይም ግምታቸውን እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ያቀረቡት ክስ ነበር፡፡

አመልካችም በተከሳሽነት ክሱ ደርሷቸው በሰጡት መልስ የተጠሪን ክስ በመካድ ከአመልካች ዘንድ የተጠሪ ከብቶች የሉም፡፡ ክሱም የሚታመን አይደለም ካሉ በኋላ ከብቶችን እንዲመልሱ ወይም

ግምታቸውን እንዲከፍሉ የሚወሰንበት ምክንያት ቢኖር እንኳን ከብቶችን ለመንከባከብ ያወጡትን ብር 12,800 የሚገመት ገንዘብ ተጠሪ እንዲከፍሉ ሊወሰንልኝ ይገባል በማለት ክርክር አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የሀላባ ልዩ ወረዳ ፍርድ ቤትም የግራቀኙን ወገኖች የቃል ክርክር እና ማስረጃዎች በመመርመር ተጠሪ ለአመልካች የመጀመሪዋን ላም መስጠታቸው፤ይህችም ላም ጥጆችን ወልዳ በቁጥር አራት መሆናቸው፤ አመልካችም እነዚህን ከብቶች ለመመለስ ፈቃደኛ አለመሆናቸው ተረጋግጧል በማለት አመልካች ተጠሪ በክሳቸው ዘርዝረው ያቀረቧቸውን ከብቶች እንዲያስረክቡ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለሀላባ ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ በማቅረባቸው ፍ/ቤቱ ቅሬታቸው መልስ ሰጭን ያስቀርባል በማለት ግራቀኙን አከራክሮ ሲያበቃ አመልካች የተጠሪን ከብቶች ተረክበው ቆይተው ሊመልሱ ባለመቻላቸው በእምነት ማጉደል ወንጀል ተከሰው መቀጣታቸው የተረጋገጠ ቢሆንም የወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች ከብቶችን እንዲመልስ መወሰኑ ተገቢነት የለውም፡፡ ይልቁንም አመልካች በወንጀል ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡ በመሆኑ በፍትሐ ብሔር ህግ አንቀጽ 1751 መሠረት 9% በዓመት ታስቦ አስቀድመው ተጠሪ የሰጡትን ብር አንድ ሺህ ላቆዩት ስድስት ዓመት ብር 1,585/አንድ ሺህ አምስት መቶ ሰማንያ አምስት ብር/ ሊከፍሉ ይገባል እንጂ ከብቶችን እንዲመልሱ አይገደዱም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁን ተጠሪ ቅር ተሰኝተው ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቅሬታቸውን አቅርበው የሀላባ ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማፅናት ወስኗል፡፡ ተጠሪ በዚህም ዳኝነት ላይ ባለመስማማታቸው የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ክርክር ሲያደረጉ ከቆዩ በኋላ አመልካች ለተጠሪ ጊደር እንዳልሸጡ፤ እንዲሁም ጊደሯም ከ2001 እስከ 2006 ዓ.ም ሶስት ጥጆች አትወልድም በማለት ቢከራከሩም በአማራጭ ባቀረቡት ክርክር ጊደሯን ለመጠበቅ እና ለእንክብካቤ ያወጡትን ብር 12,800 መጠየቃቸውን ከምስክሮች ቃል ጋር በማገናዘብ ሲታይ ጊደሯ ከተጠሪ ጋር እንደቆየችና አራት ራስ መሆንዋ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም በጉዳዩ ላይ የወረዳው ፍርድ ቤት አጣርቶ የወሰነው ውሳኔ ተገቢ ሲሆን የሃላባ ልዩ ወረዳ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት ሽሮ የአላባ ልዩ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማፅናት ከወሰነ በኋላ በአመልካች በኩል በቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ላይ ምንም ሳይል በዝምታ አልፎታል፡፡ ይህ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የህግ ስህተት ፈፅሟል በሚል ይህንኑ ዳኝነት ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበው የስር ፍ/ቤቶች ዳኝነት መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል በሚል ሲሆን አቤቱታው በአጭሩ፡-የተጠሪን ጊደር ከ2001 ዓ.ም እስከ 2006 ዓ.ም በመያዝ ሶስት ጥጆችን አልወለደችም እንጂ ወልዳ ከእኔ ጋር ቆይታለች ቢባል እንኳን ከብቶችን ለመንከባከብ ያወጣሁት ወጭ ሊታሰብ ይገባል በሚል ያቀረብኩት ክርክር በዝምታ ታልፎ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ ባለመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

ሰበር አጣሪው ችሎቱም መዝገቡን መርምሮ በጉዳዩ ላይ አከራካሪዎቹ ጊደሮች ከአመልካች ዘንድ ከ2001 ዓ.ም እስከ 2006 ዓ.ም ቆይተዋል በተባሉበት ሁኔታ በዚህ ጊዜ ውስጥ ለጊደሮች መኖና ለመሳሰሉት የወጣ ወጭ በሥር ፍርድ ቤቶች አለመታሰቡን አግባብነት ለማጣራት አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል በማለቱ ተጠሪ መልሳቸውን አመልካችም የመልስ መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡

ክርክሩ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ተጠናቋል፡፡ እኛም አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አንጻር ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የተጠሪ ከብቶች ከአመልካች ጋር ከ2001 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2006 ዓ.ም መቆየታቸው በመረጋገጡ ምክንያት ከብቶችን አመልካች ለተጠሪ እንዲመልሱ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተወስኗል፡፡ በመሆኑም አመልካች የተጠሪን ከብቶች እየጠበቀ መቆየቱ አከራካሪ አይሆንም ማለት ነው፡፡ ተጠሪ ለከብቶች ጥበቃ አገልግሎት ለአመልካች የከፈሉት ክፍያ ስለመኖሩም ሆነ አመልካች ከብቶች በነፃ የሚንከባከብበት ስምምነት ለመኖሩ አላረጋገጡም፡፡ አመልካች ለከብቶች እንክብካቤ ብር 12,800 ማውጣታቸውን ገልፀው ክርክር አቅርበዋል፡፡ ይሁን እንጂ በየደረጃው ያሉ የክልሉ ፍርድ ቤቶች ይህንን ነጥብ በጭብጥነት ይዘውና አከራክረው ውሳኔ ከመስጠት ይልቅ በዝምታ ማለፍን መርጠዋል፡፡

በፍትሐ ብሔር ህጉ አንቀጽ 2784 ሥር እንደተመለከተው ያለዋጋ ወይም በደመወዝ ስለሚሰጥ አደራ ሲደነግግ አደራ ሰጭና አደራ ተቀባዩ ስምምነት ካላደረጉ በስተቀር በአደራ የሚቀመጥ ዕቃ ዋጋ የማይከፈልበት መሆኑን ደንግጓል፡፡ በሌላ በኩል አደራ ሰጭው አደራ ተቀባዩ ዕቃውን በመልካም አያያዝ ለማኖር ያወጣውን ወጭ ሁሉ ሊከፍለው እንደሚገባ በዚሁ ህግ አንቀጽ 2793(2) ሥር ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም ለአመልካች በህግ የተሰጠው መብት ለመኖሩ ከተጠቃሹ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻል ሲሆን በጉዳዩ ላይ የዳኝነት ጥያቄ እየቀረበ የሥር ፍርድ ቤቶች ዝምታን መምረጣቸው ተገቢነት ያለው አይደለም፡፡ ይልቁንም የአመልካች ጥያቄ ሥነ ሥርዓቱን ተከትሎ የቀረበ መሆኑን በመመልከት ተቀብለው ተጠሪም የበኩላቸውን ክርክር እንዲያቀርቡ ካደረጉ በኋላ ጉዳዩን በማጣራት ተገቢው ዳኝነት ሊሰጡበት የሚገባው የክርክር ነጥብ ነበር፡፡ ስለሆነም የደቡብ ብሔር ብሔረሰብ ክልል ፍርድ ቤቶች አመልካች የተጠሪን ከብቶች እየጠበቁ የቆዩ ለመሆኑ ወይንም ከብቶቹ በአመልካች ጥበቃ ሥር ለመቆየታቸው ካረጋገጡ በኋላ አመልካች ለከብቶቹ መልካም አያያዝ ያወጡት ወጭ እንዲተካ ያቀረቡትን ዳኝነት አጣርተው

አለመወሰናቸው፤ የዚህ ዓይነት ወጭ ሊተካ የማይችልበት ምክንያት ቢኖር እንኳን ጉዳዩን ባግባቡ መርምረው ተገቢውን ዳኝነት አለመስጠታቸውን ከመዝገቡ ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም የሚከተለውን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የደቡብ ብሔር ብሔረሰብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 65573 መስከረም 04 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2. በዚህም መሰረት አመልካች ለአላባ ልዩ ወረዳ ፍርድ ቤት ያቀረቡት የተጠሪን ከብቶች በመልካም አያያዝ ለማኖር ያወጡት ወጭ ይከፈለኝ ጥያቄ በአግባቡ ተመርምሮ ተገቢው ዳኝነት ሊሰጥበት የሚገባው በመሆኑ አመልካች የተጠሪን ከብቶች ለመንከባከብ ያወጡት ወጭ ምን ያህል ነው? ይህንን ወጭ ተጠሪ የማይሸፍኑበት ምክንያት አለ ወይስ የለም? የሚሉ ነጥቦች በግራቀኙ ወገኖች ክርክርና ማስረጃ በማጣራት ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/ 343(1) መሠረት መልሰንለታል፡፡ ሌላው የውሳኔ ክፍል አልተነካም፡፡

3. በዚህ ችሎት ክርክር ለወጣ ወጭና ኪሳራ ግራቀኙ የእየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

4. በዚህ ችሎት የተሰጠው እግድ ተነስቷል፤ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ይ

የሰ/መ/ቁ.116860

ታህሳስ 26 ቀን 2009 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

አብዬ ካሣሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- ወ/ሮ አስቴር ሌንጂሶ ጠበቃ ገናናው ተሾመ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ሽታዬ ግርማ ቀረቡ

2. አቶ ተስፋዬ ወ/እየሱስ ታልፏል

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 278(2) ድንጋጌ መሰረት የተዘጋ ክስ አዲስ ክስ የሚቀርበበት መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀረመው የአሁኑ አመልካች በተጠሪዎች ላይ በኩዩ ወረዳ ፍርድ ቤት በ09/06/2007 ዓ/ም በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ አመልካች በክሳቸው ላይ በገብረ ጉራቻ ከተማ ቀበሌ 02 ክልል ውስጥ በ264 ካ/ሜትር ለመኖሪያ ቦታ ቀርቶላቸው ቁጥሩ 505-02 የሆነውን ሁለት ክፍል ቆርቆሮ ቤት ሰርተው ይዘው እንደሚገኙ፣ በተጠሪዎች መካከል በተደረገው ክርክር በመ/ቁጥር 116321 በሆነው ላይ የተሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 አግባብ ሲቃወሙም ፍርዱ ተፈፅሟል በሚል ምክንያት ተቀባይነት ያጡ ቢሆንም አዲስ ክስ የማቅረብ መብታቸው የተጠበቀላቸው መሆኑን፣ በመ/ቁጥር 32342 በሆነው ላይ ክሱን አቅርበውም በወቅቱ ክርክሩን ለመቀጠል በቂ ማስረጃ ባለማቅረባቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 278 መሰረት የተዘጋውና አዲስ ክስ የማቅረብ መብታቸው የተጠበቀላቸው መሆኑን ዘርዝረውና ተጠሪዎች በውሳኔ ቤቱን የያዙባቸው መሆኑን ጠቅሰው ውሳኔው ተነስቶ ቤቱን እንዲለቁላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የአሁኗ 1ኛ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስም ለክሱ ምክንያት በሆነው ጉዳይ ላይ አመልካች በመ/ቁጥር 32342 ክስ ከፍተው የተዘጋው አመልካች በመ/ቁጥር

30084 በሆነ ላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 41 መሰረት ጣልቃ ገብተው አቤቱታው ውድቅ የሆነባቸው መሆኑን፣ ይግባኝ ጠይቀው ተቀባይነት ሲያጡም በጉዳዩ ላይ የሰበር አቤቱታ አቅርበው በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እየታየ መሆኑን፣ቤቱ በመ/ቁጥር 11631 በሆነ ላይ በተወሰነላቸው ውሳኔ መሰረት በመ/ቁጥር 15736 በሆነ የአፈፃፀም መዝገብ ቤቱን የተረከቡ መሆኑን ዘርዝረው ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጎአል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም ጉዳዩን መርምሮ በመ/ቁጥር 11631 በሆነ ተጠሪዎች ባቀረቡት ክርክር ቤቱ የባልና ሚስት የጋራ ሃብት ነው ተብሎ መወሰኑን፣ በዚህ ውሳኔ መሰረት አፈጻጸም ቀጥሎ ውሳኔው መፈጸሙን፣ አመልካች በመ/ቁጥር 11631 የፍርድ መቃወሚያ አቅርበው ፍርዱ ተፈጽሞአል በሚል ምክንያት ተቀባይነት ያጡ መሆኑን፣ በመ/ቁጥር 32342 ክስ አቅርበው መልስ ከተሰጠበት በኂላ አመልካች በ22/10/06 በተጻፈ ማመልከቻ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 278 መሰረት ክሱን ያነሱት ጉዳያቸው በመ/ቁጥር 30084 በሆነ መፍትሔ ሊያገኝ ይችላል በሚል ምክንያት መሆኑንና በዚህ መዝገብ ያቀረቡት ጥያቄም ቤቱ የእኔ ነው የሚል ቢሆንም ክርክሩ ቀጥሎ መብት የላቸውም ተብሎ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ በተመለከተው ፍርድ ቤት ውደቅ ተደርጎ አመልካች በይግባኝ ወደ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወስደው በመ/ቁጥር 196228 በሆነው ላይ ውድቅ ከሆነባቸው በኂላ ጉዳዩን ወደ ክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ወስደው በመታየት ላይ የሚገኝ መሆኑን ዘርዝሮ አመልካች በመ/ቁጥር 30084 በሆነ ላይ መፍትሔ ያገኛል በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 287(2) በመ/ቁጥር 323412 የቀረበውን ክስ ከአዘጉ በኂላ አዲስ ክስ ማቅረባቸው ስነ ስርዓታዊ አይለም በማለት ክሱን በብይን ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ብይን አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ ከዚህም በኂላ የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ብይን የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ተብሎ አቤቱታቸው ተሰርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ብይን በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘት በመ/ቁጥር 30084 በተሰጠው ብይን በይግባኝና በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት እየታየ ያለው ጭብጥ ጉዳዩ መቅረብ የሚችልበት የስነ ስርዓት አግባብን ሲሆን አዲስ የቀረበው ክስ ግን መሰረታዊ መብትን ለማስከበር የቀረበ ሁኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች በመ/ቁጥር 32342 የቀረበው ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 278(2) የተዘጋ ነው በማለት ውድቅ ማድረጋቸው ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡አቤቱታው ተመርምሮም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 278(2) የተዘጋ መዝገብ አዲስ ክስ ሊቀርብበት አይገባም ተብሎ የአመልካች ክስ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ለዚህ ችሎት የቀረበ ሲሆን 1ኛ ተጠሪ ቀርበው ከአመልካች ጋር በፅሑፍ ክርክር ያደረጉ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ ግን በሕጉ አግባብ ጥሪ ተደርጎላቸው ባለመቅረባቸው ምክንያት በፅሑፍ መልስ የመስጠት መብታቸው

ታልፏል፡፡ በወረዳው ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 32342 የተሰጠው ትዕዛዝ ግልባጭም እንዲቀርብ ተደርጎ ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዝ ተደርጓል፡፡

ከክርክሩ መገንዘብ የተቻለው አመልካች በመ/ቁጥር 32342 ያቀረቡትን ክስ ያስዘጉት በመ/ቁጥር 30084 ላይ ያቀረቡት የቤቱ ባለቤትነት ጥያቄ ምላሽ ያስገኝልኛል ሲሆን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 278(2) መሰረት በመ/ቁጥር 32342 ያቀረቡት ክስ ሲዘጋውም አዲስ ክስ የማቅረብ መብታቸው የተጠበቀ መሆኑን የትዕዛዙ ግልባጭ የማያሳይ መሆኑን ነው፡፡

ከዚህ አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተውም የወረዳው ፍርድ ቤት በሰጠው ብይን እንደተመለከተው አመልካች አከራካሪውን ቤት በተመለከተ ቤቱ ይለቀቅልኝ በማለት በመ/ቁ 32342 አቅርበውት የነበረውን ክስ በራሳቸው ፈቃድ በመ/ቁጥር 30084 በቀረበው ክስ እልባት ያገኛል በሚል እምነት ክሱን አንስቻለሁ በማለት አቤቱታ አቅርበው መዝገቡን ስለማዘጋታቸው ፍርድ ቤቱ ማስረጃውን በመመልከት አረጋግጧል፡፡ አመልካች በዚህ መልኩ በተውት ነገር አዲስ ክስ ለማቅረብ የሚችሉበትን መብት ፍርድ ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 278(2) ድንጋጌ መሰረት የጠበቀላቸው ስለመሆኑ በአመልካች በኩል የቀረበ ክርክርና ማስረጃ የሌለ ከመሆኑም በላይ በመ/ቁጥር 32342 የተሰጠው ትዕዛዝ ይዘትም ይህንኑ አያሳይም፡፡ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 279(1) ግልፅ ድንጋጌ መረዳት እንደሚቻለውም ከሳሽ ያለፈቃድ በተውት ወይም በሰረዙት ነገር ሌላ ክስ ሊያቀርቡ አይችሉም፡፡ ስለሆነም አከራካሪውን ቤት በተመለከተ አመልካች በተጠሪዎች ላይ ቤቱ ይለቀቅልኝ በሚል ክስ አቅርበው በራሳቸው ፈቃድ ክሱን ያነሱ መሆኑን ገልፀው ፍ/ቤቱ መዝገቡን የዘጋውና አዲስ ክስ የማቅረብ መብታቸው የተጠበቀላቸው ስለመሆኑ ክርክርና ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ ያለ ፍርድ ቤት ፈቃድ በተውት ወይም በሰረዙት ነገር ክስ ሊያቀርቡ አይችሉም ተብሎ የተሰጠው ብይን ህጉን የተከተለ ነው ከሚባል በቀር የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በኩዩ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 34512 በ11/07/2007 ዓ/ም ተሰጥቶ በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 49489 በ21/07/2007 ዓ/ም፣ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር204171 በ11/09/2007 ዓ/ም የፀናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. አመልካች በተጠሪዎች ላይ ቤቱ ይለቀቅልኝ በሚል ክስ አቅርበው በራሳቸው ፈቃድ ክሱን ያነሱ መሆኑን ገልፀው ፍ/ቤቱ መዝገቡን የዘጋውና አዲስ ክስ የማቅረብ መብታቸው የተጠበቀላቸው ስላልሆነ ያለ ፍርድ ቤት ፈቃድ በተውት ወይም በሰረዙት ነገር ክስ ሊያቀርቡ አይችሉም ተብሎ በተሰጠው ብይን የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ

ስህተት የለም ብለናል፡፡ ሆኖም አመልካች በመ/ቁጥር 30084 ባቀረቡት የባለቤትነት ጥያቄ ላይ ክርክራቸውን በስርዓቱ መሰረት ከማቅረብ ይህ ብይን አያግዳቸውም ብለናል፡፡

3. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

<u>ት ዕ ዛ ዝ</u>

በ14/07/2008 ዓ/ም የተሠጠው እግድ ተነስቷል፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ.121938

ታህሳስ 27 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዳኜ መላኩ

ተኽሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነዉ

ጳዉሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- የድሬ እንጭኒ ወረዳ መንገዶች ባለስልጣን - ነ/ፈጅ ወልዴ ዋቆ ቀርበዋል

ተጠሪ፡- እንጭኒ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የገንዘብ ክፍያን መነሻ ያደረገ ክርክር ሲሆን፣ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.202599 በ18/4/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታ በማቅረቡ ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ በምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች የሥር 1ኛ ተከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ የሥር ከሳሽ፣ በዚህ ችሎት ተከራከሪ ያልሆነዉ 2ኛ ተከሳሽ የምዕራብ ሸዋ ዞን ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ሆኖ ሲከራከሩ የነበረ ሲሆን፣ የሥር ከሳሽ አምስት ሚሊዮን ብር ተከሳሾች እንዲከፍሉት በድሃ ደንብ መዝገብ በማስከፈት ዳንኝነት ጠይቋል፡፡

ይህን ክስ በተመለከተ የሥር 1ኛ ተከሳሽ ባቀረበዉ መልስ ከሳሽ ብር 9,307,479 ስለተከፈለዉ ድሃ ነዉ ለማለት ስለማይቻል በድሃ ደንብ ክስ ማቅረብ አይችልም በማለት ተከራክሯል፡፡ የሥር 2ኛ ተከሳሽ በዚህ ጉዳይ ባቀረበዉ መልስ ለከሳሽ በነጻ መዝገብ በነጻ ቢከፈትለት ተቃዉሞ የለንም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን በማየት በሰጠዉ ዉሳኔ ከሳሽ በንግድ ሕጉ አግባብ የከሰረ ስለመሆኑ ዉሳኔ ካልተሰጠዉ በቀር በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ በድሃ ደንብ ክስ ማቅረብ አይችልም፣ ከሳሽ አስቀድሞ በንግድ ሕጉ አግባብ የከሰረ መሆኑን ዉሳኔ ማስጠት አለበት በማለት አቤቱታዉን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡

የሥር ከሳሽ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኛቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ ይግባኝ ባይ የዳኝነት ክፍያ ለመክፈል አቅም እንደሌለዉ በቂ ማስረጃ አቅርቦ እያለ የሥር ፍ/ቤት አቤቱታዉን ዉድቅ ማድረጉ ተገቢ አይደለም በማለት የሥር ዉሳኔ በመሻር ለከሳሽ በድሃ ደንብ ፋይል እንዲከፈትለት በማለት ወስኗል። የሥር 1ኛ ተከሳሽ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን፣ ችሎቱ ግራ ቀኛቸዉን በማከራከር የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል። የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ።

የአሁን አመልካች በ29/4/2008 ዓ.ም የተጻፈ ሶስት ገጽ አቤቱታ የአሁን ተጠሪ በድሃ ደንብ መሰረት ክስ ለማቅረብ በቅድሚያ ድሃ ስለመሆኑ በሂሳብ ባለሙያ የተረጋገጠ ማስረጃ ወይም በፍ/ቤት ከስሯል ተብሎ የተሰጠ ዉሳኔ ባለቀረበበት፣ ተጠሪ ወደ አስር ሚሊዮን ብር ክፍያ ተከፍሎ እያለ ግብር ያልከፈለበት ምክንያት ባልተጣራበት፣ የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪ በድሃ ደንብ ክስ እንዲያቀርብ የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልን በማለት አመልክቷል።

የሰበር አጣሪ ችሎት ይህን ጉዳይ በማየት ፣ተጠሪ በድሃ ደንብ ክስ እንዲያቀርብ የመወሰኑን አግባብነት፣ ለመመርመር ሲባል አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘዉ መሰረት በ16/7/2008 ዓ.ም የተጻፈ ሁለት ገጽ መልስ አቅርቧል። የመልሱም ይዘት፡- የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ በሕግ አግባብ ስለሆነ የቀረበዉን አቤቱታ ዉድቅ የሥር ዉሳኔ እንዲጸናልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኛቸዉን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርመሮታል። መዝገቡን እንደመረመርነዉ የአሁን ተጠሪ በድሃ ድንብ ክስ ለማቅረብ ይችላል ወይስ አይችልም የሚለዉ ነጥብ ምላሽ ማግኘት ያለበት ጉዳይ ነዉ። በመሰረቱ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ.ሕገ መንግስት አንቀጽ 37 /1/ እንደተመለከተዉ ማንኛዉም ሰዉ በፍርድ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠዉ አካል የማቅረብና ዉሳኔ የማግኘት መብት አለዉ በማለት ይደነግጋል። በዚህ ድንጋጌ የተመለከተዉ ፍትሕ የማግኘት መብት ለተፈጥሮ ሰዉም ሆነ በሕግ ሰዉነት የተሰጠዉን አካል የሚያጠቃልል ይሆናል። ይህ ፍትሕ የማግኘት መብት አግባብነት በሌላቸዉ ምክንያቶች ሊደናቀፍ አይገባም። ይህን መብት ተፈጻሚ ለማድረግ በፍ/ቤትም ሆነ በሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን የተሰጠዉ አካል አቤቱታ ወይም ክስ የማቅረብ ሂደት ምቹ ሁኔታ ሊኖር እንደሚገባ የሚያከራክር አይሆንም። ነገር ግን ፍትሕ የማግኘት መብት ተግባራዊ ሲደረግ በዝርዝር ህጎች የተመለከተዉን የክርክር አቀራረብ ሥርዓትን በአስጠበቀ መልኩ መሆን እንዳለበት

ሊሰመርበት ይገባል፡፡ አንድ በፍትሐብሔር ጉዳይ ክስ የሚያቀርብ ወገን የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕጉ የደነገገዉን የክስ ወይም አቤቱታ የማቅረብ ሥርዓትን በጠበቀ መንገድ መሆን አለበት፡፡ በዚህ አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.215 /1/ እንደሚደነግገዉ አቤቱታ ወይም ክስ የሚያቀርብ ሰዉ፣ በድሃ ደንብ መሰረት ያላቀረበ እንደሆነ፣ የዳኝነት ክፍያ እስካልተከፈለ ድረስ ተቀባይነት ሊያገኝ እንደማይችል ያመለክታል፡፡ እዚህ ላይ መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ በሕጉ በግልጽ ያለ ዳኝነት ክፍያ ሊቀርቡ የሚችሉ አቤቱታዎች ወይም ክሶች ያሉ መሆናቸዉን ነዉ፡፡ ስለዚህ ለዳኝነት ሰጭ አካል አቤቱታ ወይም ክስ የሚያቀርብ አካል የገንዘብ አቅም ያለዉ እንደሆነ በደንቡ መሰረት ተገቢዉ የዳኝነት ክፍያ ሊፈጽም እንደሚገባ ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት አቤቱታ ወይም ክስ የሚያቀርብ ሰዉ በዚህ አግባብ ተገቢዉን ሳይፈጽም ፍትሕ የማግኘት መብት ሊጠበቅልኝ ይገባል ለማለት አይችልም፡፡

ከዚህ ዉጭ ደግሞ ማንኛዉም ሰዉ አቤቱታ ወይም ክስ ለማቅረብ የሚፈልግ ሆኖ ሳለ የዳኝነት ገንዘብ ለመክፈል የገንዘብ አቅም የሌለዉ እንደሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.467--479 መሰረት ዳኝነት ሳይከፈልበት በነጻ ስለሚቀርብ ክስ መሰረት መብቱ ሊከበርለት ይገባል፡፡ የዳኝነት ገንዘብ በሙሉን ወይም በከፊል የመክፈል ገንዘብ የሌለዉ ወይም ሊያገኝ የማይችል ሰዉ፣ ድሃ መሆኑን አግባብነት ባለዉ ማስረጃ ያረጋገጠ እንደሆነ ነጻ ፋይል ተከፍቶለት መሰረታዊ መብቱን መጠየቅ እንደሚችል ሥርዓት ተዘርግቷል፡፡ በድሃ ደንብ በነጻ ፋይል ለማስከፈት አቤቱታ ወይም ክስ ሲቀርብ ፍ/ቤቱ የግራ ቀኛቸዉን ማስረጃ በማጣራት እንዲሁም አግባብነት ባለዉ ማስረጃ አጣርቶ ክስ አቅራቢዉ የገንዘብ አቅም የሌለዉ ድሃ መሆኑን ማረጋገጥ እንደሚገባዉ ያሳያል፡፡ አቤቱታ ወይም ክስ አቅራቢዉ ሰዉ በዚህ አግባብ አግባብነት ባለዉ ማስረጃ የዳኝነት ገንዘብ በከፊልም ሆነ በሙሉ ለመክፈል የገንዘብ አቅም የሌለዉ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡ ከዚህ ዉጭ ግን የዳኝነት ገንዘብ ላለመክፈል ሲባል የተለያዩ ዘዴዎች ወይም የማጭበርበር ድርጊት የሚፈጽም እንደሆነ በዚህ ደንብ መሰረት መዝገቡ በነጻ ሊከፈትለት አይገባም፡፡ ይህ ማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.470 ሥር የተመለከቱት ሁኔታዎች አለመኖራቸዉ እስካልተረጋገጠ ድረስ በድሃ ደንብ ፋይል ማስከፈት አይቻልም፡፡

በመሆኑም አንድ አቤቱታ ወይም ክስ አቅራቢ ሰዉ የዳኝነት ገንዘብ መክፈል አለበት? ወይስ በድሃ ደንብ መሰረት ፋይል ሊከፈትለት ይገባል? የሚለዉ የፍሬ ነገር ጉዳይ፣ ፍሬ ነገርን የማጣራት እና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባለዉ ፍ/ቤት አግባብነት ባለዉ ማስረጃ ተጣርቶ ሊወሰን የሚገባ ጉዳይ ነዉ፡፡

በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የአሁን ተጠሪ ላቀረበዉ ክስ የዳኝነት የሚከፍለዉ የገንዘብ አቅም ስለሌለኝ በድሃ ደንብ መዝገብ እንዲከፈትልኝ የሚል ሲሆን፣ የአሁን አመልካች ባቀረበዉ ክርክር ደግሞ ተጠሪ ከዚህ ቀደም ወደ አስር ሚሊዮን ብር ክፍያ የተቀበለ ስለሆነ በድሃ ደንብ ፋይል ሊከፈትለት አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ ከዚህ አንጻር የአሁን

ተጠሪ ይህን ክስ ባቀረበበት ወቅት የገንዘብ አቅሙ ምን ደረጃ ላይ እንዳለ የሚያረጋግጥ አግባብነት ባለዉ ማስረጃ የማስረዳት ግዴታ አለበት፡፡ የአሁን ተጠሪ ደግሞ የንግድ ድርጅት እንደመሆኑ መጠን የገንዘብ አቋም/ደረጃ ምን ላይ እንዳለ ለማወቅ የድርጅቱ ሂሳብ በንግድ ሕጉ አግባብ በገለልተኛ የሂሳብ ባለሙያ ወይም በኦዲት ባለሙያ ተጣርቶ የቀረበ ማስረጃ ሊኖር እንደሚገባ ግልጽ ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት ሲታይ የአሁን ተጠሪ የገንዘብ አቅሙን የሚያረጋግጥ ይህን ዓይነት ማስረጃ ያቀረበ መሆኑን የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔዎች የሚያመለክቱት ነገር የለም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች በዉሳኔዎቻቸዉ ተጠሪ አቀረበ የሚሉት ማስረጃዎች መካከል የሚፈለግበትን የመንግስት ግብር ያለመከፈሉን የሚያሳይ ማስረጃ እንደሆነ ነዉ፡፡ ይህ ማስረጃ ግን አጠቃላይ የተጠሪን የገንዘብ አቋም የሚያረጋግጥ አግባብነት ያለዉ ማስረጃ ነዉ ብሎ ለመዉሰድ የሚያስችል ሆኖ አይገኝም፡፡ በዚህ ረገድ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.79555 የሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ተፈጻሚነት እንዳለዉ ማየት ይቻላል፡፡ ስለሆነም የአሁን ተጠሪ ላቀረበዉ ክስ የዳኝነት ገንዘብ ለመክፈል በቂ የገንዘብ አቅም የሌለዉ መሆኑን አግባብነት ባለዉ ማስረጃ በሥር ፍ/ቤት ያረጋገጠዉ ነገር ስለሌለ ተጠሪ በሕገ መንግስቱ የተመለከተዉ ፍትሕ የማግኘት መብት ሊጠበቅልኝ ይገባል የሚል ከሆነ ይህን የዳኝነት ገንዘብ ከፍሎ መዝገብ ተከፍቶለት ክርክሩን የማስቀጠል መብት አለዉ ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ ላቀረበዉ ክስ ተገቢዉን የዳኝነት ገንዘብ ከፍሎ ክርክሩን መቀጠል አለበት በማለት የሰጠዉ ዉሳኔ በሕጉ አግባብ ሆኖ ሳለ፣ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተጠሪ አግባብነት ባለዉ ማስረጃ የገንዘብ አቅም የሌለዉ መሆኑን ባላስረዳበት ሁኔታ በነጻ እንዲከፈትለት የሰጡት ዉሳኔዎች መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

<u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.196192 በ24/4/2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህን ዉሳኔ በማጽናት የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 202599 በ18/4/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 348 /1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 00057 በ9/11/2006 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በዉጤት ደረጃ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለዉ ስለሆነ በፍ.ብ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ. 348 /1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
3. የአሁን ተጠሪ ላቀረበዉ ክስ በደንቡ መሰረት ተገቢዉን የዳኝነት ገንዘብ የከፈለ እንደሆነ ፋይል ተከፍቶለት ክርክሩን የማቅረብ መብት አለዉ ብለናል፡፡

4. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
5. ግራ ቀኛቸዉ በዚህ ችሎት ለደረሰባቸዉ ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉ ይቻሉ፡፡
6. በ15/6/2008 ዓ.ም የተሰጠዉ እግድ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

ብ/ይ

የሰ/መ/ቁ. 97023

ታህሳስ 28 ቀን 2009 ዓ/ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገዶች ባለስልጣን - ፋሲል በለጠ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ አምባቸው ፈቀደነህ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

1. ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ለተጠሪ ሊከፈለው የሚገባው ክፍያ ምን ያህል እንደሆን ሂሳቡ በአግባቡ ተጣርቶ አልቀረበም በማለት አመልካች የሚያቀርበውን ክርክር በማለፉ፣ የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ህጋዊ ስርዓትንና አሰራርን የተከተለ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪን የሚያከራክራቸው አመልካች 1998 ዓ/ም የበጀት አመት ላከናወነው የመንገድ ስራ ፕሮጅት የሚያገለገል ገረጋንቲ፣ ሶቦ ቤዝ የተፈጨ ገረጋንቲ፣ የአስፓልት ጠጠርና ቀይ አሸዋ ለማጓጓዝና አፈር እንዲደፋለት ባወጣው ጨረታ ተወዳድሮ ተጠሪ በማሸነፉ ተጠሪ ለአመልካች የሰጠው የማጓጓዝ ግልጋሎት መጠንና ዋጋ የሚመለከት ሆኖ ተጠሪ ለአመልካች የሚከፈለው ቀሪ ክፍያ አለ ወይስ የለም? አመልካች ለተጠሪ የሚከፍለው ቀሪ ክፍያ አለ ከተባለ፤ የክፍያው መጠን ምን ያህል ነው? የሚሉት ጭብጦች ናቸው፡፡
2. ተጠሪ አመልካች በውሉ መሰረት ለሰጠው የማቴሪያል ማጓጓዝ ግልጋሎት ሊከፍለው የሚገባ ብር 3,204,391.23 (ሶስት ሚሊዮን ሁለት መቶ አራት ሺ ሶስት መቶ ዘጠና አንድ ብር ሃያ ሶስት ሳንቲም) ያልከፈለን ስለሆነ ቀሪ ክፍያ እንዲከፈል ይወሰንልኝ በማለት ሀምሌ 2 ቀን 1999 ዓ/ም የተጻፈ ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች ውል መኖሩን ሳይክድ ተጠሪ በተጭበረበረ

ሰነድ ክፍያ የወሰደ መሆኑን ገልፆና የተጠሪን ክስ ክዶ ተከራክሯል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሰይድ ዓሊ የተፈቀደላቸው የሒሳብ አዋቂዎችሒሳቡን አጣርቶ እንዲያቀርብ ካደረገ በኋላ፣ አመልካች ለተጠሪ ብር 3,747,741.44 (ሶስት ሚሊዮን ሰባት መቶ አርባ ሰባት ሺ ሰባት መቶ አርባ አንድ ብር ከአርባ አራት ሳንቲም)ሊከፍል ይገባል በማለት በመዝገብ ቁጥር 57330 ህዳር 19 ቀን 2001 ዓ/ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡

3. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች የስር ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 57330 ህዳር 19 ቀን 2001 ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ባቀረበው የይግባኝ ቅሬታ ላይ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ካደረገና የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ፡- (ሀ) ተጠሪ የኮንስትራክሽን ማቴሪያሎች ያጓጓዘበት ዕርቀት ቀድሞ ተለክቶ የውሉ አካል ሆኗል ወይስ አልሆነም? (ለ) አመልካችና ተጠሪ አፈር ለማጓጓዝና ሌሎች የኮንስትራክሽን ማቴሪያል ለማጓጓዝ በአንድ ጨረታ ሁለት የተለያዩ ውሎች ተዋውለዋል? በክፍያ ሂደት ተጠሪ አፈር ለማጓጓዝና ሌሎች የኮንስትራክሽን ማቴሪያሎችን ለማጓጓዝ የሰራቸውን ስራዎች ቀላቅሎ የክፍያ ጥያቄ አቅርቦ ክፍያ ወስዷል ወይስ አልወሰደም (ሐ) ተጠሪ ለክፍያ አቅርቦ ክፍያ ከወሰደባቸው ሰነዶች መካከል የተጭበረበሩና በመመሳጠር አግባብ ክፍያ የተፈጸመባቸው ሰነዶች አሉ ወይስ የሉም? (መ) ሒሳቡ በገለልተኛ ባለሙያ እንደያጣራ ማድረግ የሚመለከቱ ጨብጦችን በመያዝ የስር ፍርድ ገለልተኛ ባለሙያ መድቦ ሒሳቡን በማጣራት ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል በማለት የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ሽሮ፣ ጉዳዩን በፍ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 343(1) በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 42620 መስከረም 24 ቀን 2003 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ መልሶ ልኮለታል፡፡

4. ለዚህ ሰበር ክርከር መነሻ የሆነው፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን እንደገና አጣርቶ እንዲወሰን በመዝገብ ቁጥር42620 መስከረም 24 ቀን 2003 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ ከመለሰለት በኋላ የመደበው ልዩ አዋቂ ባለሙያ ስራውን ያከናወነበት አግባብናየስር ፍርድ ቤት የልዩ አዋቂውን ባለሙያ በመቀበል የሰጠው ውሳኔ ህጋዊ አግባብነት ያለውን ስርዓት የተከተለ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ችሎት ጉዳዩን ከመለሰለት በኋላ የስር ፍርድ ቤት ሒሳቡን አጣርቶ እንዲያቀርብ አቶ በየነ ፈቀደ የተባሉ የሒሳብ ባለሙያ መድቧል፡፡ የሒሳብ ባለሙያ ከተመደቡ በኋላ አመልካች ለባለሙያው ጽ/ቤት የሰጣቸው ቢሆንም ሁለት ቀናት ብቻ የታዩ መሆኑን፤ የአመልካችን ሰነዶች በአግባቡ ተረክቦ ያልወሰደ መሆኑንና የሒሳብ ባለሙያው በገለልተኝነት ሒሳቡን ያጣራል የሚል ዕምነት የሌለው መሆኑን ገልጾ አቤቱታ ያቀረበ መሆኑንናበየነፈቀደ የተፈቀደለት የሒሳብ አዋቂ በበኩሉ አመልካች የሒሳብ ሰነዶቹን በሁለት ቀናት ውስጥ አደራጅቶ ካላቀረበለት በስራው ላይ ለሚፈጠረው ጉድለት አመልካች

ኃላፊነቱን የሚወስድ መሆኑን ገልጾ ሚያዝያ 28 ቀን 2004 ዓ/ም ለአመልካች በቀጥታ ደብዳቤ መጻፉንና አመልካች በበኩሉ የሒሳብ ባለሙያው ለጻፉት ደብዳቤ ግንቦት 2 ቀን 2004 ዓ/ም ለበየነ ከበደ በቀጥታ በጻፈው ደብዳቤ መልስ የሰጠ መሆኑን፣ የሒሳብ ባለሙያና አመልካች ልዩነት የፈጠሩባቸው ጉዳዮች ላይ የስር ፍርድ ቤት መመሪያ ሳይሰጥ፣ የሒሳብ ባለሙያው በመሰለው ሒሳቡን ሰርቶ ሪፖርት ማቅረቡንና አመልካች የሒሳብ ሪፖርቱን በመቃወም አስተያየት ማቅረቡን፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበውን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ በየነ ከበደ የተፈቀደለት የሒሳብ ባለሙያ የቀረበውን ሪፖርት መሰረት በማድረግ አመልካችብር 3,757,077.56 (ሶስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃምሳ ሰባት ሺ ሰባ ሰባት ብር ከሃምሳ ስድስት ሳንቲም) ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በመዝገብ ቁጥር 57330 ሰኔ 21 ቀን 2005 ዓ/ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

5. አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቀጥር 57330 ሰኔ 21 ቀን 2005 ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 337 መሰረት በመሰረዝ በመዝገብ ቁጥር 92820 ጥቅምት 25 ቀን 2006 ዓ/ም በዋለው ችሎት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ጥር 20 ቀን 2006 ዓ/ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 42620 መስከረም 24 ቀን 2003 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔና መመሪያ መሰረት ተገቢውን ማጣራት ሳያደርግ ውሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት የዕርቀት ልኬትን በተመለከተ ለሁሉም ቦታ በ27 ኪሎ ሜትር ሒሳብ ክፍያ እንድንፈጽም መወሰኑ፣ አመልካች በተጭበርበሩና በመመሳጠር ክፍያ የወሰደባቸው ሰነዶች እያሉን ሰነዶች በማስረጃነት ሳያቀርቡና ይህንኑ የሚያስረዱ ምስክሮቸ ሳይሰሙ መወሰኑ፤ ሂሳቡን እንዲያጣሩ የተመደቡት ባለሙያ ሒሳቡን በአግባቡ ሳይሰሩ ሰነዶቹን ፈርመው ካቀረቡበት ሚያዝያ 8 ቀን 2004 ዓ/ም በፊት ሚያዚያ 3 ቀን 2004 ዓ/ም ሰርተው እንዳጠናቀቁ በመግልጽ ያቀረቡትን ሪፖርት በመቀበል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

6. ተጠሪ በበኩሉ መጋቢት 3 ቀን 2006 ዓ/ም በተጻፈ መልስ የዕርቀት የልኬቱን መጠን አመልካች አስቀድሞ በመወሰን የውሉ አካል አድርጎታል ይህንን ዕውነት የስር ፍርድ ቤት ግራ ቀኛችን ከተለዋወጥናቸው ደብዳቤዎች የማስረጃ ይዘት በመገንዘብ በውሳኔው በግልጽ አስፍሮታል፡፡ ተጠሪ አመልካች ያሳተማቸውን 20,000 የጭነት ደርሰኞች አቅርበሌለሁ ሒሳቡም በገለልተኛ ባለሙያዎች ተጣርቶ ትክክል እንዲሆን ተረጋግጧል፡፤ አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት መቅረብ የሌለባቸውን የፍሬ ነገር ክርክሮችን በማቅረቡ የህግ መሰረት የሌለው

ክርክር በመሆኑ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች መጋቢት 24 ቀን 2006 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

7. ከስር የክርክር አመጣጥና ግራቀኙ ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛ የስር ፍ/ቤት የአመልካችና የተጠሪን ሒሳብ በገለልተኛነት አጣርቶ እንዲቀርብ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 136/1/ መሰረት የመደበው በየነ ፈቀደ የተፈቀደለት የሒሳብ አጣሪ ባለሙያ ሂሳቡን በገለልተኛነት እንዲያጣራ ተገቢውን መመሪያ በመስጠትና የሒሳብ ባለሙያው ግራቀኙ አሉን የሚሏቸውን ሰነዶችና አንደኛቸው ሌላው ባቀረበው ሰነድ ላይ ያቀረቧቸውን ተቋውሞዎች ከሙያ አንጻር በመመርመር ሚዛናዊ የሆነ የሒሳብ ሪፖርት እንዲቀርብና ሃላፊነቱን እንዲወጣ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቷል ወይስ አልሰጠም? የሚለው ጭብጥ ተመልክተናል፡፡

8. ይህንን ጭብጥ ለመወሰን፣ በአገራችን የፍትህ ስርዓት በፍርድ ቤት የሚመደብ የልዩ አዋቂ፣ በሙያው አጣርቶ እንዲያቀርብ በፍርድ ቤት የታዘዘውን ነገር ሲያጣራ ስላለበት ሃላፊነትና ሊከፍለው ስለሚገባው የአሰራር ስርዓትና ሊከተለው ስለሚገባ ስነ ምግባር በጥልቀት ማየት ያስፈልጋል፡፡ በአገራችን የሕግ ስርዓት አንደኛው ወገን ከሌላው አካል ሊከፈለኝ ይገባል ስለሚለው ገንዘብ በግሉ ልዩ አዋቂ ቀጥሮ በማስጠናት፣ በግል የቀጠረው ልዩ አዋቂ የቀረበለትን የምርመራ ውጤት በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 223 እና በፍታብሔር ስነ-ስርዓት ሕግ ቁጥር 137/1/ መሰረት በማስረጃነት በማያያዝና ልዩ አዋቂውን በምስክርነት በመዘርዘር የዳኝነት ጥያቄውን ወይም ክርክሩን ለማቅረብ የሚችል መሆኑን ከድንጋጌዎቹ ይዘትና አላማ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ሆኖም በአንደኛው ወገን ቀጣሪነት በልዩ አዋቂ ተመርምሮ የቀረበው ግኝት ተዓማኒነትና ክብደት ያለው ማስረጃ ተደርጎ በፍርድ ቤት የሚወስደው የልዩ አዋቂውን የምርመራ ውጤት ሌላኛው ወገን ሳይቃወም ትክክለኛ የምርመራ ውጤት ነው ብሎ የተቀበለው በሆነ ጊዜ ብቻ እንደሆነ የፍታብሔር ስነ ስርዓት ሕግ አንቀጽ 250 " ተከራካሪዎቹ ወገኖች ወይም አንደኛው ወገን ክስ የቀረበበት ሃብት ግምት ወይም ዋጋ ምክንያት ባለመስማማት ክርክር ያቀረቡ እንደሆነ ፍ/ቤቱ ጭብጡን ከመመስረቱ በፊት ነገሩ የሚሰማበትን ቀነ ቀጠሮ ወስኖ በዚህ ሕግ ቁጥር 132 ወይም በፍታብሔር ስነ-ስርዓት ሕግ ቁጥር 136 በተነገረው መሰረት የሃብቱን ግምት የሚያሳውቁ ምትክ ዳኞች ይሾማል" በማለት ደንግጓል፡፡

9. ከዚህ ድንጋጌ የምንረዳው በአንደኛው ተከራካሪ ወገን የተቀጠረ ልዩ አዋቂ ባለሙያ በምርመራ ሒደት አገኘሁት የሚለው ግኝትና ውጤት ሌላው ተከራካሪ ወገን ካልተስማማበት፣ ጉዳዩን የሚያየው ፍ/ቤት የምትክ ዳኛ ስልጣን ያለው ልዩ አዋቂ ባለሙያ የመመደብ ግዴታ ያለበት መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ የአመልካችንና የተጠሪን ሒሳብ አጣርቶ እንዲቀርብ በስር ፍ/ቤት በሒሳብ አጣሪነት የተሾመው "በየነ ፈቀደ

የተፈቀደለት የሒሳብ አጣሪ ባለሙያ" አመልካችና ተጠሪ በየግላቸው የሒሳብ ባለሙያዎች አሰርተው ባቀረቡት የሒሳብ ምርመራ ውጤት ባለመስማማታቸው ምክንያት በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 250 መሰረት የስር ፍ/ቤት የመደበው ልዩ አዋቂና መርማሪ ብቻ ሳይሆን፣ የስር ፍ/ቤት ህዳር 14 ቀን 2001 ዓ.ም ለሰጠው ውሳኔ መሰረት የሆነውን የሒሳብ ሪፖርት ያቀረበው ሰይድ አሊ የተፈቀደላቸው የሂሳብ አጣሪ፣ ሒሳቡን ገለልተኛ ሆኖ አላጣራም በሚል ምክንያት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር ሂሳቡ በገለልተኛ የሂሳብ ባለሙያ እንዲጣራ ለማድረግ ውሳኔ እንዲሰጥበት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 42620 መስከረም 20 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔና መመሪያ መሰረት የተመደበ የሂሳብ አጣሪ ነው፡፡

10. የሂሳብ አጣሪው የስር ፍ/ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 136 መሰረት የመደበው የልዩ አዋቂ /ኤክስፐርት/ ነው፡፡ ሒሳብ አጣሪው በፍ/ቤቱ ሒሳቡን አጣርቶ እንዲቀርብ የተሾመ በመሆኑ ስራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ሁሉ ከግራቀኝ ተከራካሪ ወገኖች ጋር ያለው ግንኙነት የሙያውን ስነ-ምግባርና ገለልተኛነትን መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፡፡ የሒሳብ አጣሪው በስራ ሂደት ሊቀርቡለት የሚገቡ ጠቃሚ ማስረጃዎች ከአንደኛው ተከራካሪ ወገን ወይም በሁለቱም ወገን ተከራካሪዎች ወይም በሌላ ሶስተኛ ሰው ሳያቀርቡለት ቢቀሩ ወይም ቢዘገዩበት ይህንኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 136 መሰረት በሂሳብ አጣሪነት ለሾመው ፍርድ ቤት በማሳወቅ ፍ/ቤቱ ስለሰነዶቹ አቀራረብ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 132፣ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁጥር 145 /1/ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች መሰረት ትእዛዝ እንዲሰጥበትና የማጣራት ስራው ስለሚከናወንበት ሁኔታ መመሪያ እንዲሰጠው ከመጠየቅ ውጭ፣ አንደኛውን ወገን፣ ማስረጃዎችህን በሁለት ቀን፣ ወይም በአንድ ሳምንት ውስጥ ካላቀረብክ፣ ያንተን ሰነዶች የማልቀበልና በሂሳብ ሪፖርቴም የማላካትተው መሆኑን እንድታውቀው በማለት በቀጥታ ለአንደኛው ወገን ማስጠንቀቂያ መስጠትና የአንደኛውን ወገን ሰነድ ሳይቀበልና ሳያካትት የሒሳብ ሪፖርቱን ሰርቶ የማቅረብ ተልዕኮው የማይፈቅድና ስልጣንም የሌለው መሆኑን፣ ከፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 132 እስከ ፍታብሔር ስነ-ስርዓት ሕግ ቁጥር 136 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ይዘትና መሰረታዊ አላማ በማገናዘብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

11. በያዝነው ጉዳይ የአመልካችና የተጠሪን ሂሳብ የሙያውን ስነ-ምግባርና የፋይናንስና የክፍያ ሕጎችንና ደንቦችን መሰረት በማድረግ፣ የግራቀኙን የሰነድ ማስረጃዎችና አንደኛው በሌላው ሰነድ ላይ የሚያቀርቡትን ተቃውሞ ከሙያ አንጻር መርምሮ ሪፖርቱን እንዲያቀርብለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሾመው "በየነ ፈቀደ የተፈቀደለት የሂሳብ አጣሪ" ለምርመራ የሚያስፈልጉ ሰነዶችን በማቅረብ ሂደት የተፈጠሩ ችግሮችን በምትክ ዳኝነት ለሾመው ፍ/ቤት በማሳወቅ ፍ/ቤቱ ትእዛዝና መመሪያ እንዲሰጥበት የማድረግ አሰራርን ተከትሎ ሒሳቡን

በማጣራት ሪፖርቱን ያላቀረበ መሆኑን የሒሳብ አጣሪው ለአመልካች በቁጥር በከሂአ/014/2004 ሚያዝያ 28 ቀን 2004 ዓ/ም በቀጥታ ከሰጠው ማስጠንቀቅያ ይዘትናማስጠንቀቅያው የሒሳብ አጣሪውን ገለልተኝነትና በተሰጠው የስልጣን ወሰን ስር ሆኖ ሒሳቡን ያከናወነ መሆኑን በመመዘን ሂደት ከሚኖረው ህጋዊ ውጤት ከመረመረው ለመረዳት ይቻላል፡፡

12. የሒሳብ አጣሪው ሒሳቡን በሚመረምርበት ጊዜ የሰነዶች አቀራረብ ሂደት ያጋጠመውን ችግር ለሾመው ፍ/ቤት በማሳወቅ ፍ/ቤቱ ቀጣዩ ትእዛዝ እና የስራ መመሪያ እንዲሰጥበት መጠየቅ ሲገባው ራሱ ውሳኔ ሰጭ በመሆን አመልካች በሁለት ቀናት ውስጥ ሰነዶችን አደራጅቶ ካላቀረበለት የሌላኛውን ወገን /የተጠሪን/ ሰነዶች መሰረት በማድረግ ሪፖርቱን ሰርቶ እንደሚያቀርብና በዚህ ምክንያት ለሚፈጠረው ችግር አመልካች ሀላፍነቱን የሚወስድ መሆኑን የሚገልፅ የማስጠንቀቅያ ደብዳቤ በመፃፍ አመልካችም ለሒሳብ አጣሪው ማስጠንቀቅያ ተገቢነት የሌለው መሆኑን የሚገልፅ ምላሽና ደብዳቤ ለሒሳብ አጣሪው በአድራሻቸው በቀጥታ በቁጥሩ 2132/ዎ/ሥ/አስ/9314 ግንቦት 2 ቀን 2009ዓ/ም ደብዳቤ ፅፎለታል ፡፡ ይህም የሚያሳየው በሥራ ሂደት የሒሣብ አጣሪው አንደኛውን ተከራካሪ /አመልካችን/ የሚኮንን አኳኋን አቋምን በቀጥታ ለአመልካች በመግለፅ የሒሳብ አጣሪው ገለልተኝነት ጥርጣሬ ውስጥ የሚጥሉ ተግባራትን በፍርድ ቤት ከተሰጠው የአጣሪነት ሹመት ወሰን በማለፍ የፈፀመ መሆኑን ነው፡፡

13. የሒሳብ አጣሪው አመልካችን ሰነድህን አልቀበልህም በማለት የሰጠው ማስጠንቀቅያ በሒሳብ ሪፖረቱም ላይ የተንፀባረቀ መሆኑን የሚያሳይ መሰረታዊ ነጥቦች አሉ፡፡ በአብነት ለማንሳትም አመልካች ተጠሪ በተጭበረበሩ የሒሳብ ሰነዶችና በመመሳጠር የማጓጓዣያ አገልግሎት ሳይሰጥ ክፍያ ወስዶባቸዋል የሚላቸውን ደረሰኝ ቁጥሮት ፕሮጀክቱን የሚገኝበትን ስፍራ በዝርዝር በመመስረት ለፍ/ቤቱ ያቀረበው መሆኑን በትእዛዝ ካስቀረበ ነው የፌ/ከ/ፍ/ቤት የመዝገብ ቁጥር 57330 ተረድተናል፡፡ በአንፃሩ የሒሳብ አጣሪው ባቀረበው ሪፖርት ውስጥ አመልካች በተጭበረበረ ሰነድና በመመሳጠር ተጠሪ ያልሰጠው አገልግሎት ክፍያ ወስዶባቸዋል በማለት ለይቶ በዝርዝር ስላወጣቸው ሰነዶች የተሰጠው ሙያዊ አስተያየት አለመኖሩ የሒሳብ አጣሪው ሚያዝያ 28 ቀን 2004 ዓ/ም በሰጠው ማስጠንቀቅያ መሰረት የሒሳብ ሪፖርቱን የአመልክችን ሰነዶች ሳይመለከትና በአግባቡ ሳይመረምር ያዘጋጀው ስለመሆኑ በእርግጠኝነት ለመናገር ለመደምደም የማያስችል ሆኖ አግኝተነዋል፡፡የስር ፍ/ቤት የሒሳብ ምርመራ ሂደት ሒሳብ አጣሪው ያጋጠመውን ችግር ለፍ/ቤቱ እንዲያሳውቅ እና በጎንዮሽ ከአንዳቸው ተከራካሪ ወገኖችጋር ማስጠንቀቅያ የመፃፍ እና የሒሳብ አጣሪውን ገለልተኝነት ጥያቄ ውስጥ የሚጥሉ ተግባራትን መመሪያና ትእዛዝ መስጠት ሲገባው የሒሳብ አጣሪው በፍትሐብሔር ስነስርዓት ህግ ቀጥር 136(2) ከተደነገገው

ውጪ የአመልካችን የሒሳብ ሰነድና መቃወሚያና አስተያየት ሳያካትት መርምሮ ያቀረበለትን ሪፖርት ተቀብሎ ውሳኔ መስጠቱ የፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 134 የፍታብሄር የስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 135 እና የፍታሐብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 136 ድንጋጌዎች ያልተከተለ እና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

14. ከላይ በዝርዝር የገለፅነው እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠሪ አመልካች እንዲከፍለው የጠየቀው ብር 3,204,391.33 መሆኑ ሐምሌ 2 ቀን 1999ዓ/ም ፅፎ ባቀረበው የክስ ማመልከቻ በግልፅ ሰፍሮ እያለ የስር ፍ/ቤት ተጠሪ በግልፅ ዳኝነት ያልተጠየቀበትን 3,757,077.56 እንዲከፍል የሰጠው ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 182 ንኡስ አንቀፅ (2) የሚጥስና መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በአጠቃላይ የፌ/ከ/ፍ/ቤት የሒሳብ አጣሪው የተሰጠውን በገለልተኝነት የግራ ቀኙን ሒሳብ አጣርቶ የማቅረብ ሀላፊነት በአግባቡ እንዲወጣ ተገቢውን መመሪያ ሳይሰጥ የሒሳብ አጣሪው አመልካች የተጭበረበሩና በመመሳጠር ሒሳብ ተከፍሎባቸዋል የሚላቸውን ሰነዶች በአግባቡ ሳይመረምር ያቀረበውን የሒሳብ ሪፖርት ተቀብሎ የሰጠውን ውሳኔ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በይግባኝ አይቶ ማረም ሲገባው በትዕዛዝ ማፅናቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

**ው ሳ ኔ**

1. የፌ/ከ/ፍ/ በመቁ 57330 ሰኔ 21 ቀን 2005 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት የፍትሐብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 92820 ጥቅምት 25 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የፌ/ከ/ፍ/ቤት የፌዴራል ኦዲት ኮሚሽን ልምድና ዕውቀት ያላቸው የሒሳብ ባለሞያዎች በመመደብ የአመልካች እና የተጠሪን ሒሳብ አጣርተው እንዲያቀርቡለት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 136(1) መሰረት ትእዛዝ በመስጠት በማጣራቱ ሂደት ከባለሙያዎች ለሚቀርቡለት ጥያቄዎች ተገቢውን መመሪያና ትእዛዝ በመስጠት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ 343(1) መሰረት ጉዳዩ መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት የወጡትን ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደመዝገብ ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

የሰ/መ/ቁ.100295

ህዳር 26 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ
ተኽሊት ይመሰል
ቀነዓ ቂጣታ
ሰናይት አድነዉ
ጳዉሎስ አርሺሶ

አመልካች.............አቶ ደጓለ ገዳሙ -ቀርበዋል

ተጠሪዎች..............1. አቶ ሳይኩን ሙሉጌታ -ቀርበዋል

2. ወ/ሮ አለምፀሐይ ወርቄ
3. ወ/ሮ አይችል እጅጉ
4. ወ/ሮ ትዕግስት እጅጉ
-የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የመኖሪያ ቤት ሽያጭ ዉል ለማስፈጸም የቀረበ ክስን መነሻ ያደረገ ሲሆን፣ በምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ጣልቃ ገብ፣ የአሁን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ከሳሾች እና የአሁን 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች ተከሳሾች ሆኖ ሲከራከሩ እንደነበር መዝገቡ ያመለክታል፡፡ የሥር ከሳሾች ባቀረቡት ክስ 1ኛ ተከሳሽ ወ/ሮ አይችል እጅጉ በ2ኛ ተከሳሽ ወ/ሮ ትዕግስት እጅጉ በተሰጣት የዉክልና ስልጣን መሰረት በብቸና ከተማ 01 ቀበሌ የሚገኘዉን በ2ኛ ተከሳሽ ስም የሚታወቀዉን የመኖሪያ ቤት ቁጥር 1326 ስለሸጠችልኝ ዉሉ እንዲፈጸምልኝ ቤቱን ከነወጪዉ እንዲያስረክቡኝ በማለት ከሷል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የሥር ጣልቃ ገብ አቶ ደጓለ ገዳሙ ባቀረበዉ የጣልቃ ገብ አቤቱታ ጣልቃ ገብ እና 1ኛ ተከሳሽ ወ/ሮ ትዕግስት እጅጉ በባህል ጋብቻ ባልና ሚስት ሆነን ሲንጋባ በፈጸምነዉ የጋብቻ ዉል ይህን መኖሪያ ቤት የጋራ ንብረታችን ያደረግን በመሆኑ እኔ ሳላዉቅ ተከሳሾች ቤቱን ለከሳሾች ስለሸጡ ጣልቃ ገብቼ እንድከራከር በማለት አመልክቷል፡፡

የሥር ጣልቃ ገብ አቤቱታ ላይ የሥር ከሳሾች ባቀረቡት መልስ ከዚህ ቀደም ጣልቃ ገብ በዚህ ጉዳይ በወረዳዉ ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርቦ በሁለት መዝገቦች በመ.ቁ.5444 እና 5520 ላይ ዉድቅ የተደረገበት በመሆኑ ጣልቃ ለመግባት የቀረበዉ አቤቱታ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በመመርመር በሰጠዉ ብይን ጣልቃ ገብ ይህን መኖሪያ ቤት በተመለከተ ከዚህ ቀደም ሁለት ጊዜ አቤቱታ አቅርቦ በመ.ቁ.5520 እና 5444 ላይ አቤቱታዉ ዉድቅ ያደረገ በመሆኑ አሁንም ጣልቃ ገብቼ ልከራከር በማለት ያቀረበዉ አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.5 መሰረት ተቀባይነት የለዉም በማለት ወስኗል፡፡ የሥር ጣልቃ ገብ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኙን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት እና የሰበር አቤቱታዉን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቶቹ የቀረበዉን ቅሬታ ዉድቅ በማድረግ የሥር ፍ/ቤት ብይን በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ28/08/2006 ዓ.ም የተጻፈ አምስት ገጽ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአቤቱታዉም ይዘት፡--የአሁን አመልካች እና 4ኛ ተጠሪ ጥር 21 ቀን 2000 ዓ.ም ባልና ሚስት ሆነን ስንጋባ ለክርክር ምክንያት የሆነዉን ቤት በብቸና ከተማ 01 ቀበሌ የቤት ቁጥር 1326 የሆነዉን የጋራ ንብረት ያደረግነዉን እኔ ሳልሰማ እና ሳልፈቅድ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ያለ አግባብ በብር 140,000 ገዛን በማለት ዉል እንዲፈጸምላቸዉ 3ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎችን በመክሰሳቸዉ ጣልቃ ለመግባት አቤቱታ አቅርቤአለሁ፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ግን አቤቱታዉን መቀበል ሲገባቸዉ ከዚህ ቀደም የወረዳዉ ፍ/ቤት የማይንቀሳቀስ ንብረት በተመለከተ ከ100,000 ብር በላይ የሆነ ጉዳይ የመወሰን የሥረ ነገር ስልጣን የለኝም በማለት በመ.ቁ.05444 እና 5520 የሰጠዉን ብይን እንደመጨረሻ ዉሳኔ በመቁጠር በአዲስ ስልጣን ላለዉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡትን የጣልቃ ገብ አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.5 መሰረት ዉድቅ ማድረጋቸዉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲሻርልኝ አመልካች በክርክሩ ጣልቃ ገብቼ እንድከራከር እንዲፈቀድልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ይህ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣የወረዳዉ ፍ/ቤት ይህን የቤት ሽያጭ በተመለከተ የማየት ስልጣን የለኝም ያለበት ሲሆን ጉዳዩ ስልጣን ላለዉ ለከፍተኛ ፍ/ቤት ሲቀርብ የአሁን አመልካች ጣልቃ ለመግባት ያቀረበዉ አቤቱታ ከዚህ ቀደም በወረዳዉ ፍ/ቤት ዉድቅ ስለሆነ እንደገና የጣልቃ ገብ አቤቱታ ማቅረብ አትችልም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ በታዘዘዉ መሰረት የአሁን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በ18/10/2006 ዓ.ም የተጻፈ አምስት ገጽ መልስ እና 3ኛ ተጠሪ ሰኔ 17 ቀን 2006 ዓ.ም የተጻፈ አንድ ገጽ መልስ እና 4ኛ ተጠሪ በ18/10/2006 ዓ.ም የተጻፈ ሁለት ገጽ መልስ አቅርቧል፡፡ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ያቀረቡት መልስ ይዘት ሲታይ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት በመሆኑ የቀረበዉ ቅሬታ ዉድቅ ተደርጎ የሥር ፍ/ቤት እንዲጸናልን በቂ ኪሳራ እንዲወሰንልን በማለት ተከራክሯል፡፡ የአሁን 3ኛ ተጠሪ ያቀረበችዉ መልስ ይዘት ሲታይ በተሰጣት ዉክልና መሰረት ቤቱን የሸጠች መሆኑን በመግለጽ በሐሰት ችግር እየፈጠረች ያለችዉ 4ኛ ተጠሪ እንደሆነች በመጥቀስ በሕግ አግባብ ዉሳኔ ቢሰጥ የማትቃወም

መሆኖዋን በመግለጽ ተከራክራለች፡፡ የአሁን 4ኛ ተጠሪ መልስ ይዘት ሲታይ የአመልካችን ቅሬታ በሚደግፍ መልኩ በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኛቸዉን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነዉ ለክርክር መነሻ የሆነዉ መኖሪያ ቤት የአሁን 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ከ3ኛ ተጠሪ ጋር በተደረገዉ የቤት ሽያጭ ዉል በብር 140,000 /አንድ መቶ አርባ ሺህ/ ስለገዛን በዉሉ መሰረት እንዲፈጸምላቸዉ ክስ በማቅረብ ዳኝነት የጠየቁ ሲሆን፣ የአሁን አመልካች ባቀረበዉ የጣልቃ ገብ ጥያቄ ይህ ቤት በጋብቻ ዉል የጋራ ንብረት ስለሆነ ወደ ክርክሩ ገብቼ እንድከራከር እንዲፈቀድልኝ የሚል ነዉ፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ግን ጉዳዩን በማየት ከዚህ ቀደም አመልካች ይህን ቤት በተመለከተ አቤቱታ አቅርበዉ ዉድቅ ስለሆነ አሁን ማቅረብ አይችልም በማለት መወሰናቸዉ የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔዎች ያመለክታል፡፡

ነገር ግን የየእነማይ ወረዳ ፍ/ቤት የመ.ቁ.5444 እና 5520 የሆኑትን መዝገቦች የዘጋዉ ጉዳዩን ለማየት የሥር ነገር ስልጣን ስለሌለዉ እንደሆነ ከሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ የአሁን አመልካች አስቀድሞ ያቀረበዉ አቤቱታ በእነዚህ መዝገቦች ላይ በተሰጠዉ ትዕዛዝ ዉድቅ የተደረገ መሆኑ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ የወረዳዉ ፍ/ቤት ይህን መኖሪያ ቤት በተመለከተ የቀረበዉን ክርክር ለማየት የሥረ ነገር ስልጣን ስለሌለዉ መዝገቡን የዘጋ እንደሆነ ፍ/ቤቱ ዋናዉን ክርክር እንዳላየ ስለሚቆጠር መዝገቡን ከመዝጋቱ በፊት የሰጠቸዉ ትዕዛዞች ምንም ዓይነት የአስገዳጅነት ዉጤት የላቸዉም፡፡ የወረዳዉ ፍ/ቤት መጀመሪያዉኑ ይህን ቤት በተመለከተ የቀረበለትን ክስ ተቀብሎ ትዕዛዝ ከመስጠቱ በፊት በሕጉ አግባብ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን ስልጣን ያለዉ መሆን አለመሆኑን የክልሉ የፍ/ቤቶች መቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 169/2002 ዓ.ም መሰረት በማድረግ፣ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.9 /1/ እና 231 /1/ /ለ/ በሚደነግገዉ አግባብ ክሱ ተቀባይነት የለዉም በማለት መመለስ ይገባዉ ነበር፡፡ የወረዳዉ ፍ/ቤት ይህን ሳያደርግ የቀረበዉን ክስ ተቀብሎ ከአከራከረ በኂላ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.244 /2፣ ሀ/ እና 245 /2/ መሰረት መዝገቡን ዘግቶ ተከራካሪዎቹን ያሰናበታቸዉ መሆኑን የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔዎች ያመለክታል፡፡ የወረዳዉ ፍ/ቤት በዚህ መሰረት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን የዘጋ እንደሆነ ዋናዉን ክርክር እንዳላየ ስለሚያስቆጥረዉ በመዝገቡ ላይ የሰጣቸዉ ማናቸዉም ትዕዛዞች በማንኛዉም ወገን ላይ ሕጋዊ የሆነ አስገዳጅነት ዉጤት የላቸዉም፡፡ የወረዳዉ ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን የዘጋ እንደሆነ፣ ይህ ደግሞ ክርክሩን እንደአዲስ ስልጣን ባለዉ ፍ/ቤት ከማቅረብ የሚከለክል ባለመሆኑ የወረዳዉ ፍ/ቤት የሰጣቸዉ ትዕዛዞች አዲስ በቀረበዉ ክርክር ላይ ዉጤት ሊኖራቸዉ የሚችልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ የወረዳዉ ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን

የለኝም በማለት የወሰነ እስከሆነ ድረስ አስቀድሞ የሰጣቸዉ ትዕዛዞችን ሕጋዊ ዉጤት ስለሌላቸዉ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ማሻር አስፈላጊ አይደለም፡፡ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክሩን እንደአዲስ የሚያይ በመሆኑ የወረዳዉ ፍ/ቤት የሰጠዉን ትዕዛዝ ታሳቢ በማድረግ የሚሰራበት አግባብ የለም፡፡ የወረዳዉ ፍ/ቤት የሰጠዉ ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.5 /1/ መሰረት ጉዳዩ ከዚህ ቀደም የመጨረሻ ፍርድ ወይም ዉሳኔ አግኝቷል ሊባል ስለማይችል በዚህ ምክንያት የሥር ከፍተኛዉ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ያቀረበዉን አቤቱታ ዉድቅ ማድረጉ የሕግ መሰረት የለዉም፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች ከዚህ ቀደም የወረዳዉ ፍ/ቤት ይህን ቤት በተመለከተ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን የዘጋ መሆኑን በመገንዘብ፣ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የቀረበዉ አዲስ ክርክር ሆኖ ሳለ የአመልካች ክርክሩ መብቴን ስለሚነካ ጣልቃ ገብቼ እንድከራከር እንዲፈቀድልኝ በማለት የቀረበዉን አቤቱታ በመቀበል ወደ ክርክሩ ገብቶ እንዲከራከር ማድረግ ሲገባቸዉ፣ ከዚህ ቀደም የወረዳዉ ፍ/ቤት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ስላደረገ ጣልቃ መግባት አይችልም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ የሰጡት ዉሳኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ በመሆኑ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.108283 በ10/03/2005 ዓ.ም የሰጠዉ ብይን እና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ.34629 በ03/03/2006 ዓ.ም የሰጠዉ ፍርድ እና ይህን ፍርድ በማጽናት የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.35215 መጋቢት 15 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የምስራቅ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህን ጉዳይ በድጋሚ በማየት የአሁን አመልካች ያቀረበዉን የጣልቃ ገብ አቤቱታ በመቀበል ግራ ቀኞቸዉ በጉዳዩን ላይ እንዲከራከሩ በማድረግ ጉዳዩን በማጣራት ተገቢ ነዉ ያለዉን ዉሳኔ እንዲሰጥበት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.341 /1/ መሰረት ተመልሶለታል፡፡
3. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኛቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
5. በዚህ መዝገብ ሰኔ 18 ቀን 2006 ዓ.ም የተሰጠዉ የእግድ ትዕዛዝ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ. 124669

ሕዳር 30 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሀመድ

ተኽሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- የሳስኮ ኢንዱስትሪያል ንግድና ትራንስፖርት ድርጅት፡-

ጠበቃ አቶ አብደላ አሊ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር፡- ነ/ፈጅ አማረች መለስ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የስር ከሳሽ የአሁን አመልካች በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አራዳ ምድብ ችሎት ያቀረቡት ክስ ከተከሳሽ ጋር ውል የፈፀምን ሲሆን ይኸውም የመስታዋት ማጓጓዝ ስምምነት ሆኖ ለሆሳዕና ዩንቨርስቲ 400 ኩንታል መስተዋት የአንዱ ዋጋ 69.00 /ስልሳ ዘጠኝ ብር/ በቀጥላላ 27,600.00 /ሃያ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ብር/ ለደብረታቦር ዩኒቨርስቲ 400 ኩንታል መስተዋት የአንዱ ዋጋ በብር 114.00 /አንድ መቶ አስራ አራት ብር/ በቀጥላላ 45,600 /አርባ አምስት ሺህ ስድስት መቶ ብር/ ለቡሬ ሆራ ዩኒቨርስቲ 400 ኩንታል መስተዋት በብር 114.00 /አንድ መቶ አስራ አራት ብር/ በጠቅላላ 45,600 /አርባ አምስት ሺህ ስድስት መቶ ብር/ ከላይ የተጠቀሰው ሰራዎች በጠቅላላው ድምር 118,800.00 /አንድ መቶ አስራ ስምንት ሺህ ስምንት መቶ ብር/ የሚያወጣ ስራ ሰርቼ ተከሳሽ ሊከፍለኝ ሲገባ ያልከፈለኝ ስለሆነ እርክክቡ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ህጋዊ ወለድ፣ ወጪና ኪሳራ ጋር ይወሰንልኝ የሚል ዳኝነት በመጠየቃቸው ነው፡፡

ተከሳሽ በወኪሉ አማካኝነት በሰጠው መልሰ የመጀመሪያ ደረጃ መቃመሚያ ከሳሽ ችሎታ የለውም በሚል መከራከሪያ አቅርቦ በተጨማሪም ይህ ቢታለፍ ብለው ተከሳቭ መሰሪያ ቤት አስተዳደር

መ/ቤት በመሆኑ ከከሳሽ ጋር የሚደረግ ውል በጽሁፍ መሆን ሲገባው በጽሁፍ የተደረገ ውል የለንም ስለሆነም ከሳሽ ክስ ማቅረብ አይችልም ይችላል እንኳን ቢባል ከሳሽ ለአስሩ ዩኒቨርስቲዎች መስተዋቱን ለማቅረብ ጨረታ አሸንፎ ለሶስት ዩኒቨርስቲ ብቻ በማቅረብ ክፍያ መጠየቅ አይችልም ከሳሽ ካንዝሪው መስተዋት ውስጥም በከፊል የተሰበረ በመሆኑ ይኸው ተቀንሶ እንዲከፈለው ሲባል ከሳሽ ያልተስማማ በመሆኑ ውሉን ያፈረሰ በመሆኑ ከክሱ በነፃ ልሰናበት ይገባል ብሏል፡፡

ፍ/ቤቱም በተከሳሽ በኩል የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ዉድቅ በማድረግ ካከራከረ በኃላ በከሳሽና በተከሳሽ በኩል የተፈፀመው ዉል በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3131-3132 ድረስ በተገለፀው መሠረት ከአስተዳደር መስሪያ ቤት ጋር የተፈፀመ ውል ሲሆን ይህ ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1724 መሠረት በጽሁፍ ሊደረግ ሲገባው ባለመደረጉ ውሉ በህጉ መሠረት የተቀመጠው የአጻጻፍ ስርአትን ያሟላ አይደለም በማለትና ይህ ደግሞ በ1720/1/ መሠረት ከረቂቅ የዘለለ ውጤት የለውም በማለት ክሱን ውደቅ በማድረግ ሲወሰን የአሁን አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ቅሬታው በይግባኝ የቀረበለት ከፍተኛ ፍ/ቤት መዝገቡን መርምሮ ቅሬታው መልስ ሰጪን እያስጠራም በማለት ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

ለሰበር የቀረበው አቤቱታ በአመልካችና በተጠሪ መሀከል የተፈፀመ ውል የጨረታ ሆኖ እያለ የአስተዳደር ውል ነው ተብሎ በጽሁፍ ሊደረግ ሲገባ በጽሁፍ አልተደረገም ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ውሉ የአስተዳደር ቢሆን እንኳን በፍ/ብ/ህ/ቁ 3141-3117 ድረስ የተደረገ ህጋዊ ውል ሆኖ እያለ በስር ፍ/ቤቶች ክሱ ውድቅ ተደርጎ የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታልና ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

በሰበር አጣሪው ችሎት ተጠሪ ሚኒስቴር መሰሪያ ቤት መስተዋት የማቅረብ ማንዝሪ ጨረታ አውጥቶ አመልካች ተወዳድሮ አሸንፎ ለሶስት ዩኒቨርስቲዎች ያቀረበ መሆኑ ባልተካደበት ያንዝሪበት ዋጋ ሲጠየቅ ውላችን በጽሁፍ አልተደረገምና ሊከሰኝ አይገባም ተብሎ በቀረበ ክርክር መነሻነት ክሱ ውድቅ የተደረገበትን አግባብነት ለማጣራት ተጠሪ ይጠራ በማለቱ ተጠሪ መስሪያ ቤት በሰጠው መልስ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ ተገቢና መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ስለሆነ ሊፀና ይገባል ካለ በኃላ አመልካች ድርጅት በውሉ መሠረት ለአስር ዩኒቨርስትዎች ያላቀረቡ ስለሆነ ልንከፍል አይገባም ብለዋል፡፡

በመሠረቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 3132/2/ ስር እንደተመለከተው ውሉ ከህግ አገልግሎት ስራ ጋር የተያያዘና ለስራውም አፈፃፀም የተዋዋዩን ስራ ተካፋይነት ሳያቋርጥ የሚጠይቅ በሆነ ጊዜ ውሉ የአስተዳደር መ/ቤት ውል እንደሆነ ይደነግግና በፍ/ብ/ህ/ቁ 3131/1/ ስር እንደተመለከተው መንግስት ወይም ሌሎች የአስተዳደር ሰራተኞች የሚዋዋሏቸው ውሎች ስለውሎቹ በጠቅላላና ስለ

ልዩ ልዩ ውሎች የተሰጡት የዚህ ውል ድንጋጌዎች በጠቅላላው እንደሚፀናላቸው ይደነግጋል፡፡ ስለ ውሎች በጠቅላላው በተፃፈው የፍ/ብ/ህ/ቁ 1724 ስርም እንደተመለከተው ከአስተዳደር መ/ቤት ጋር የሚደረጉ ውሎች በጽሁፍ ሊደረጉ እንደሚገባ ይደነግግና በፍ/ብ/ህ/ቁ 1720 ስር እንደተመለከተው ውልን ለማቋቋም በጽሁፍ እንዲደረጉ የታዘዙ ውሎች በጽሁፍ ካልተደረጉ እንደ ረቂቅ እንደሚቆጠሩ ይደነግጋል፡፡

በሌላ በኩል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 242 ስር እንደተደነገገው ማናቸውም ተከራካሪ ወገን በመከላከያ መልሱ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ የተከሰሰበትን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል የሚያምን መሆኑን የገለፀ እንደሆነ ወይም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 241 መሠረት በሚደረግ ምርመራ የእምነት ቃሉን የሠጠ እንደሆነ ፍ/ቤቱ በታመነው ነገር ላይ ብቻ ፍርድ መስጠት እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ይህ ማለት ለአንድ ለቀረበ ክርክር የተሰጠው መልስ የታመነ እስከሆነ ድረስ ፍ/ቤቱ በታመነው መሠረት ውሳኔ ሊሰጥ እንደሚገባና ወደ ማስረጃ የሚገባው በክስ አይነት ካልታመነ ብቻ እንደሆነ የተደነገገ ነው፡፡ ስለሆነም ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ውሉ በጽሁፍ ነው ወይስ በቃል የውሉ ይዘት ምን ነበር እየተባለ የሚጣራው በክሱ መሠረት ካልታመነ ነው፡፡ በቀረበው ክርክር የስር ተከሳሽ /የአሁን ተጠሪ/ ለቀረበበት ክስ የሰጠው መልስ የእምነት መሆኑ ከክርክሩ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ እስከሆነ ድረስ ፍርድ ቤቱ ከቀረበው ክስ እና መልስ አንጻር ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል፡፡

ከዚህ መነሻ ሲደረግ የስር ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክርክሩን ከሰማ በኃላ ውሉ ከአስተዳደር መ/ቤት ጋር የተፈፀመ በመሆኑ በጽሁፍ መደረግ ሲገባው አልተደረገም በማለት ክሱን ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሲሰጥ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የስር የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ማረም ሲገባው አልፎ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔ በማጽናት መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል በመሆኑም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የስር የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 111159 በቀን 21/2007 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የስር የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንን ውሳኔ በማጽናት በመዝገብ ቁጥር 170506 በቀን 26/4/2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሸሯል፡፡
2. አመልካች በስር ክሳቸው ለሶስት ዩኒቨርስቲዎች መስታወቶችን አንገጤአለሁ ሲሉ ተጠሪም ለሶስት ዩኒቨርሰቲዎች አመልካች ያቀረበ ቢሆንም ካቀረባቸው መስታውቶች ዉስጥ የተሰባበሩ መስተዋቶች መኖራቸውን በገለፀው መሠረት አመልካች በሶስት

ዩኒቨርስቲዎች ለእያንዳንዱ ዩኒቨርስቲ ምን ያህል ኩንታል መስታወት እንዳጓጓዙ የአንዱ ኩንታል ዋጋ ምን ያህል እንደሆነ አመልካች ካጓጓዘው ውስጥ ምን ያህሉ እንደተሰበረ በግራ ቀኙ ውል መሠረት ለተጠሪ ሊከፈላቸው የሚገባ ክፍያ አለ ወይስ የለም የሚከፈላቸው ከሆነስ ሊከፈላቸው የሚገባው የገንዘብ መጠን ምን ያህል እንደሆነ በማስረጃ ተጣርቶ ይወሰን ዘንድ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 341/1/ መሠረት ልከናል፡፡

3. ለዚሁ ፍ/ቤት ክርክር የተደረገ ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

<u>ት ዕ ዛ ዝ</u>

የውሳኔው ግልባጭ በየደረጃው ለሚገኙ የስር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ በውሳኔ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

የሰ/መ/ቁ. 99474

ሕዳር 30ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች(ዎች)፡- 1. ወ/ሮ ሙሉነሽ ደሬሳ

2. አቶ ዮሐንስ ይባስ — ጠበቃ መስፍን እሸቱ ቀረቡ

3. ወ/ሮ ቆንጂት ይባስ

4. ወ/ሮ መቅደስ ይባስ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ማሚቴ ጌታቸው ቀረቡ

2. ወ/ሮ ፍርኖ ከበደ ተወካይ ደረጃ አያሌው ቀረቡ

3. የአዲስ አበባ ከተማአስተዳደር ልማትና የቤቶች ጉዳይ ኤጀንሲ.ተተኪ /የቦሌክፍለከተማ ቀበሌ 14/15 የዲዛይንና ግናባታ ልማት አስተዳደር ጽ/ቤትደረጀ ማርቆስ ነ/ፈጅቀ

4. የቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 14/15 አስተዳደር ጽ/ቤት ደረጀ ማርቆስ ነ/ፈጅ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች በውርስ ያገኙናቸው ሁለት ቤቶች ሽራ-ተን አዲስ ሲገነባ በልማት ምክንያት የፈረሱ በመሆኑ፣ የመንግስት አልታድ ከሚባለውድርጅት ጋር አድርጎት በነበረው

ስምምነት መሰረት በፈረሱት ሁለት ቤቶች ምትክ የተሰሩትን የቤት ቁጥር 459 እና የቤት ቁጥር 530 ተከሳሾች /ተጠሪዎች/ እንዲያስረክቡ ውሳኔ ይሰጥልን በማለት ያቀረቡትን ጥያቄ የበታች ፍርድ ቤቶች ውድቅ ያደረጉትን በህግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት አመልካቾች ከሳሽ ተጠሪዎች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

2. የክርክሩ መነሻ ከሳሾች /አመልካቾች/ ለስር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ አመልካቾች አንደኛ አመልካች የአቶ አብተስላሴ ወራሽ መሆኗንና ስማቸው ከሁለተኛ እስከ አራተኛ ተራ ቁጥር የተገለጹት አመልካቾች የሚች ይባስ ሰዳን ወራሽ መሆናቸውን ገልጸው፤ የከሳሾችአውራሽ ሚች ይባስ ሰዳን በህይወት እያለ በወረዳ 14 ቀበሌ 24 ቁጥር 382 እና ቁጥር 379 የሆነ ቤቶች አፍርተዋል፡፡ ሚች ከዚህ አለም በሞት ሲለይ 1964 ዓ/ም የሚች ወራሾች በመሆናችን ከፍርድ ቤት አረጋግጠን ሚች ያፈራቸውን ቤቶች ወርሰናል፡፡ የሚች አባታችን ሀብት የነበሩትና ከሳሾች በውርስ ያገኘናቸው ቤቶች ቦታው ሸራተን አዲስ ሆቴል ለመገንባት በመፈለጉ ምክንያት ስፍራው በአልታድ ኩባንያ በኩል ወረዳ 28 ቀበሌ 04 ክልል በአሁኑ አጠራር በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ14/15 በፈረሰው ቤት ቁጥር 379 ምትክ የቤት ቁጥር 459፣ በፈረሰው የቤት ቁጥር 382 ምትክ የቤት ቁጥር 530 የሆኑት ተገንብተዋል፡፡ ከሳሾች የውርስ ያገኛቸውን ቤቶች ተካፍለው እንዲቀርቡ በሚመለከተው አካል በተሰጣቸው ትዕዛዝ መሰረት በልማት ምክንያት የፈረሰው የቤት ቁጥር 382 የአንደኛና ሁለተኛ ከሳሾች ድርሻ መሆኑና የቤት ቁጥር 382 የሶስተኛና አራኛ ከሳሾች ድርሻ ተገልፆ የሚመለከተው አካል መዝግቦታል፡፡ በመሆኑም ከሳሾችበውርስ ባገኘናቸው ቤቶች ምትክ የተሰሩትን የቤት ቁጥር 459 እና የቤት ቁጥር 430 አንደኛና ሁለተኛ ተከሳሾች ከሶስተኛና አራተኛ ተከሳሾችተከራይተው እየኖሩባቸው በመሆኑ አንደኛና ሁለተኛ ተከሳሾች ቤቶቹን ለቅቀው እንደወጡ፣ ሶስተኛና አራኛ ተከሳሾችከአንደኛና ሁለተኛ ተከሳሾች ጋር ያደረጉትን የክራይ ውል በማቋረጥና ቤቶቹን በማስለቀቅ ለከሳሾች በድርሻችን መሰረት እንዲያስረክቡ ውሳኔ ይሰጥልን የሚል ይዘት ያለው ክስ አቅርበዋል፡፡

3. ተከሳሾች የፈረሱት የቤት ቁጥር 379 እና የቤት ቁጥር 382 በአዋጅ ቁ/47/67 መሰረት የተወራሾችፍርድ ቤቱ ስልጣን የሌለው መሆኑን ገልጸው ተከራክረዋል ፡፡ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን እንደሌለው ገልፆ መስከረም 1 ቀን 2002 ዓ/ም በዋለው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ ዘግቶታል፡፡ አመልካቾች በዚህ ብይን ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኙን በይግባኝ መዝገብ ቁጥር

97896 ከሰማ በኋላ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ በመሻር የፌ/የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን መልሶለታል፡፡

4. ጉዳዩን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከመለሰው በኋላ አንደኛ ተከሳሽ /አንደኛ ተጠሪ ብቻ ቀርበው ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ 1972 ዓ/ም ጀምሮቤቱን ከመንግስት ተከራይቼ በመኖር ላይ እገኛለሁ፡፡ ተከሳሾች የቤት አበል ይወስዱ ነበር በማለትየተከራከሩ ሲሆን ሁለተኛ ተጠሪ፣ ሶስተኛ ተጠሪና አራተኛ ተጠሪዎች ክርክሩ በሚሰማበት ቀነቀጠሮ ባለማቅረባቸው ጉዳዩ እነርሱ በሌሉበት እንዲታይ የስር ፍ/ቤት ብይን ሰጥቶ፣ ጉዳዩን ሁለተኛና አራተኛ ተጠሪዎች በሌሉበት አይቶ ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡ የስር ፍ/ቤት የሽግግር መንግስት የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የቤት ቁጥር 379 የሶስተኛና አራተኛ ከሳሽ ድርሻ፣ የቤት ቁጥር 382 የአንደኛ አመልካች ልጅና አውራሽ የሆነው የሀብተስላሴ ይባስና የሁለተኛ ከሳሽ ድርሻ መሆኑን የመግለጽ በወቅቱ ለነበረው የክልል 14 አስተዳደር የፃፈው ደብዳቤ በማስረጃነት ከሳሾች ያቀረቡ መሆኑን ገልፆ፣እነዚህ የሰነድ ማስረጃዎች ከሳሾች ክስ ባቀረቡባቸው ቤቾችላይ መብትና ጥቅም ያላቸው መሆኑን አያረጋግጡም በማለት የስር ከሳሾች /አመልካቾች/ ያቀረቡትን ክስ ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች ከዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበዋል የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

5. አመልካቾች ለዚህ ሰበር ችሎት መጋቢት 2 ቀን 2006 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ፣ ስማችን ከሁለተኛ እስከ አራተኛ ተራ ቁጥር የተገለጸው አመልካቾች አቶ ሀብተሰባሲ ይባስ የሚች የአቶ ይባስ ሰዴ ወራሽ መሆናችን በመዝገብ ቁጥር 221/65 በፍርድ ቤት ውሳኔ ተረጋግጧል፡፡ ሀብተስላሴ ይባስ የጠፋና አንደኛ አመልካች የሀብተስላሴ ወራሽ መሆናቸው በፍርድ ቤት አስወሰነናል፡፡ አዋጅ ቁ/ 47/67 ከመውጣቱ በፊት የአባታችን ንብረት የነበሩት ሁለት ቤቶች ባለቤትነት ለወራሾች የተላለፈልን ሲሆን፣ የውርስ ንብረቶቹን በመከፋፈል የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የባለሀብትነት ማስረጃ እንዲሰጠን፣ ቤቶቹ የከሳሾች ድርሻ መሆናቸውን በአዋጅ ቁ/ 47/1967 ስልጣን የተሰጠው የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር አጣርቶና አረጋግጦ የሰጠንን ማስረጃ የበታች ፍ/ቤቶች ውድቅ ያደረጉት ከህግ አግባብ ውጭ በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡

6. ተጠሪዎች በተለያዩ ጊዜ በተናጥል ፅፈው ባቀረቡት መልስ፣ የፈረሱት ቤቶች የአመልካቾች አውራሽ ንብረት ስለመሆናቸው አመልካቾች ያቀረቡት ማስረጃ የለም፡፡ የሚች ይባስ ሰዴ ወርሶ በውርስ አጣሪ በኩል ተጣርቶ፣ ቤቶች ለአመልካቾች ያደረሱ ስለመሆናቸው አመልካቾች አላስረዱም የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የፃፈው ደብዳቤ አመልካቾች የቤቶች

ባለሀብት መሆናቸውን የማስረዳትና የማረጋገጥ የአስረጂነት ብቃት የለውም ቤቶች በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት ተወርሰው መንግስት ለረዥም ጊዜ ስያስተዳድራቸውና እያከራየ ሲጠቀምባቸው የኖሩ በመሆኑ፣ ቤቶች ያልተወረሱ መሆናቸውን የማስረዳት ግዴታ ያለባቸው ከሳሾች /አመልካቾች/ በመሆናቸው አመልካቾች የማስረዳት ግዴታቸውን ስላልተወጡ የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የህግ ስህተት የለበትም፡፡ አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪ ቤቶችን ከሶስተኛና አራኛ ተጠሪዎች ተከራይተን እየኖርን ሲሆን፣ ከከሳሾች ጋር የሚያገናኘን ከውል ወይም ከህግ የመነጨ ግንኙነት የለንም በማለት የተከራከሩ መሆኑን ተረድተናል፡፡ አመልካቾች የመልስ መልሳቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡

7. ከስር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ለዚህ ሰበር ችሎት የቀረቡ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን የሰበር ችሎት ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት እንድችል የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመዝገብ ቁ/ 171029 አስቀርቦ መመልከቱ አስፈላጊ ሆኖ በማግኘቱ መዝገቡ እንዲቀርብ በማድረግ ተመልክቶታል፡፡ በስር ፍ/ቤት በማስረጃነት ተያይዘው ከሚገኙ የፍ/ቤት ውሳኔዎችና ሌሎች የሰነድ ማስረጃዎች፣ አመልካቾች በአከራካሪዎቹ ቤቶች ላይ ያላቸውን መብት ለማረጋገጥ፣ በተለያየ ጊዜ ለተለያዩ ፍርድ ቤቶች፣ ክስ ሲያቀርቡና ሲከራከሩ የቆዩ መሆኑን አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት የማስረጃ ዝርዝር መግለጫ የገለጽዋቸውና በማስረጃነት ካያያዟቸው የተለያዩ የፍርድ ቤት ውሳኔዎች ለመረዳት ችለናል፡፡

8. አመልካቾች በአከራካሪዎች ቤቶች የአባታቸው የሟች ይባስ ሰዴ መሆናቸውን ለማስረዳት ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነውን የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የመዝገብ ቁ/ 171029 ከማስከፈታቸው በፊት ክስ አቅርበው በተከራከሩባቸው ሌሎች መዛግብት ላይ በማስረጃነት አቅርበው የያዛቸው ጠቃሚ የሰነድ ማስረጃዎች በፍ/ስ/ስ/ህግ/ቁ145/1/ መሰረት አስቀርቦ ማየትና መመርመር ያስፈልጋል፡፡ ይህም የሚሆነው አመልካቾች በቤቶች ላይ ያላቸውን መብት ለማስከበር ክርክር የጀመሩት ከሁለት አስር ዓመት በፊት መሆኑና በጉዳዩ በተለያዩ ፍርድ ቤቶች ሲከራከሩ ረዥም ዘመን ያስቆጠረ መሆኑን፣ የአመልካቾች የሰነድ ማስረጃዎች በተለያዩ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ተያይዞ የሚገኝ መሆኑን፣ አመልካቾች በማስረጃ ዝርዝር መግለጫቸው ዘርዝረው በማስረጃነት ካያያዟቸው የፍርድ ቤት ውሳኔዎች ተገልፀው እያለ፣ እነዚህን ጠቃሚ ሰነዶች ያለባቸውን የፍርድ ቤት መዝገቦች በፍ/ስ/ስ/ህግ/ቁ/ 145/1/ መሰረት አስቀርበው ሳያዩ፣ አመልካቾች አከራካሪዎቹ ቤቶች የሟች አባታቸው ይባስ ሰዴ ለመሆናቸው የስራና ከተማ ልማት ሚኒስተር ከፃፈዉ ደብዳቤ ዉጭ ሌሎች ደጋፊ ማስረጃዎች አላቀረቡም በማለት

የበታች ፍርድቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ እዉነታዉን የማያንጸባርቅና ከላይ የጠቀሳቸዉን የህግ ድንጋጌዎች ያልተከተለ ሆኖ አግኝተነዋል ፡፡

9. አመልካቾች ክስ ያቀረቡባቸው የቤት ቁጥር 379 እና የቤት ቁጥር 382 የሚች ይባስ ሰዴ ንብረቶች እንዲሆኑ፣ የአመልካቾች አውራሽ አዋጅ ቁጥር 47/67 ከመታወጁ በፊት መሞታቸውናአመልካቾች የሚች ወራሾች መሆናቸውን በስር ፋይል መዝገብ ቁጥር 221/65 በፍርድ ቤት ውሳኔ ያረጋገጡ መሆኑን፣ አመልካቾች ከአባታቸው በውርስ የተላለፉላቸውን ሁለት ቤቶች 1974 ዓ/ም ወራሾቹ ባደረጉት የውርስ ንብረት ክፍያ ስምምነት መሰረት፣ የቤት ቁጥር 379 የአንደኛና የሁለተኛ አመልካቾች ድርሻ መሆኑን የቤት ቁጥር 352 ደግሞ የሶስተኛ አራተኛ አመልካቾች ድርሻ መሆኑ ተረጋግጦ የተላኩለትና ይህንንም በአግባቡ መዝግቦ ያያዘ መሆኑን በመግለጽ የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የካቲት 10 ቀን 1987 ዓ/ም እና ጥቅምት 25 ቀን 1990 ዓ/ም በፃፈው ደብዳቤ የረጋገጠ መሆኑን በትዕዛዝ ባስቀረብነው በስር ፍርድ ቤት መዝገብ ውስጥ አመልካቾች ካቀረቡአቸው የሰነድ ማስረጃዎች ይዘት መረዳት ችለናል፡፡

10. የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የካቲት 10 ቀን 1987 ዓ/ም እና ጥቅምት 25 ቀን 1990 ዓ/ም ለአዲስ አበባ አስተዳደር የጻፋቸው ደብዳቤዎች መሆናቸውን ገልጸው፣አመልካቾች ያቀረባቸው ሰነዶች፣ የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የመንግስት ደብዳቤ አፃፃፍ ስርዓት ጠብቆ ለክልሉ 14 መስተዳደር ጽፎና ወጭ አድርጎ የላካቸው ደብዳቤዎች መሆናቸውን ተጠሪዎች በመካድ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ ሰነዶቹ ሀሰተኛ ሰነድ ናቸው በማለት አልተከራከሩም፡፡ ይህም ማለት ሰነዶቹ በእርግጠኝነት የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የመንግስት አሰራርና የጽሁፍ ማረጋገጫ አፃፃፍ ስርዓትን ጠብቆ ለክልሉ 14 መስተዳደር የፃፋቸው፣ ዕውነተኛ ደብዳቤዎች መሆናቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ደብዳቤዎችን የፃፈው ባለው አሰራር መሰረት ተገቢውን ማጣራት በማድረግና አከራካሪዎቹ ቤቶች የሚች ይባስ ሰዴ ንብረቶቹ መሆናቸውን፣ የንብረቶቹ ባለቤት አዋጅ ቁጥር 47/67 ከመታወጁ በፊት ከዚህ አለም በሞት መለየቱንና አመልካቾች የሚች ወራሽ መሆናቸውን አዋጅ ቁጥር 47/67 ከመታወጁ በፊት መዝገብ ቁ/ 221/65 ማረጋገጣቸውንና አመልካቾች በውርስ ያገኘዋቸውን ቤቶች፣ በወራሾች ስምምነት 1974 ዓ/ም ተከፋፍለው ለስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የውርስ ንብረቶቹን የተከፋፈሉበትን ሰነድ አቅርበው ሰነዱ በአግባቡ ተቀምጦ የሚገኝ መሆኑን የሚገልጽ ደብዳቤዎች ናቸው፡፡

11. አዋጅ ቁጥር 47/67 የማስፈጸም ኃላፊነትና ስልጣን የተሰጠው የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀጽ 2 እና አንቀጽ 15 ተደንግጓል፡፡ ይህ በህግ

ስልጣን የተሰጠው የመንግስት መስሪያ ቤት በህግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት በየደረጃው ያዋቀራቸውን አደረጃጀቶች በመጠቀም ተገቢውን ማጣራት በማድረግ፣ የቤት ቁጥር 379 እና የቤት ቁጥር 382 የአመልካቾች አውራሽ ሚች ይባስ ሰዴ እንደሆኑ በማረጋጥ የፃፈው ደብዳቤ፣ አከራካሪዎቹ ቤቶች የሚች ይባስ ሰዴ ስለመሆናቸው የሚያስረዳ ብቃት ያለው ማስረጃ ሆኖ እያለ ደብዳቤዎቹን የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የመንግስት አሰራር ስርዓትን ተከትሎ የፕሮቶኮል ቁጥር፣ ቀን፣ የባለስልጣን ፊርማና የሚኒስቴር መስሪያ ቤት የራስጌና የግርጌ ማህተም በማረጋገጥ ውጭ አድርጎ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፃፏቸው መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ፣ ደብዳቤዎቹ ውስጥ በግልጽ የቤት ቁጥር 379 የአንደኛና ሁለተኛ አመልካች ድርሻ፣ የቤት ቁጥር 382 የሶስተኛና የአራኛ አመልካቾች ድርሻ መሆኑን በግልጽ በሰፈራበት ሁኔታ፣ የበታች ፍርድ ቤቶች በህግ ቤቶቹ በትርፍነት የተወረሱ መሆን አለመሆናቸውን፣ ቤቶቹ በመጀመሪያ የማን ሀብት እንደነበሩ የማጣራትና የንብረቱ ባለሀብት የሆኑት ወራሾች መብት ከአዋጅ ቁጥር 47/67 አንፃር የማጣራትና ውሳኔ የመስጠት ስልጣን ያለው የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የፃፈው እውነተኛ ደብዳቤ፣ የአስረጂነት ብቃት፣ ተአማኝነትና ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት ውድቅ ማድረጋቸው የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር በአዋጅ ቁ/ 47/67 በተሰጠው ስልጣን የሚወሰናቸው ውሳኔዎች ውጤት አልባ የሚያደርግና ህግን ያልተከተለ የማስረጃ አመዛዘን በመሆኑ የህግ መሰረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

12. የስርና ከተማ ልማት ሚኒስቴር አዋጅ ቁጥር 47/67 የማስፈጸም፣ በአዋጅ መሰረት አንድ ቤት በትርፍነት ሊወረስ የሚገባው መሆኑን ወይም አለመሆኑን የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን ያለው ከፍተኛ አስተዳደራዊ አካል ነው፡፡ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የአዲስ አበባ አስተዳደር /ክልል 14 መስተዳደር/ እና በእሱ ስር የተደራጀ ሌሎች የመንግስት አካላት አዋጅ ቁጥር 47/67 በማስፈጸም ሂደት የሰጡት ውሳኔ አዋጁን መሰረት ያደረገ መሆኑን መርምሮ የማሻሻል፣ የመለወጥ ወይም የመሻር አስተዳደራዊ ስልጣን በአዋጅ ቁጥር 47/67 የተሰጠው የመንግስት አካል ነው፡፡ ሌሎች የከተማው አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በህግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት አጣርቶ ለሚሰጠው ውሳኔ የሚከበርና የማስፈጸም ህጋዊ ግዴታና ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 47/67 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመለከተው የስራና ከተማ ልማትሚኒስቴር የካቲት 10 ቀን 1987 ዓ/ም እና ጥቅምት 25 ቀን 1990 በፃፈው ደብዳቤ የወሰናቸውን ውሳኔዎች የማክበርና የማስፈጸም ግዴታ በህግ የተጣለባቸው 3ኛ ተጠሪና አራኛ ተጠሪ፣ የሚኒስተሩ ውሳኔ ውድቅ እንዲያረግ ለበታች ፍርድ ቤቶች ጽፈው ያቀረቡት ክርክር፣ በህግ የተጣለባቸውን አስተዳደራዊ ኃላፊነት ያልተወጡ መሆኑን የሚያሳይና የህግ መሰረት የሌለው ክርክር ነው፡፡ በወቅቱ በነበሩ የህግ

ማዕቀፎች የሚኒስቴር መ/ቤቱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፣ የክፍለ ከተማውንና የሶስተኛና አራተኛ ተጠሪዎች ትርፍ ቤትን በተመለከተ የሰጡትን ውሳኔ የመሻር፣ የመለወጥ ወይም የመሻሻል ከፍተኛ የሆነ የአስፈጻሚነትና አስተዳዳራዊ ስልጣን ያለው ሲሆን፣ የከተማው አስተዳደር፣ ክፍለ ከተማውም ሆነ ለሶስኛና አራተኛ ተጠሪዎች የሚኒስቴር መስሪ ቤቱ የሰጠውን ውሳኔ አፈፃጸም የማስተጓጎል፣ የማጓተት፣ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ውሳኔ ህጋዊ ውጤት እንዳይኖረው የሚያደርጉ ተግባራትን የፈጸም፣ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን ውሳኔ የመሻር ወይም የመለወጥ አስተዳደራዊ ስልጣን አልነበራቸውም፡፡ በመሆኑም ሁለተኛ ተጠሪና አራተኛ ተጠሪ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ውሳኔ ተፈፃሚ መሆን የለበትም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ምንም አይነት የህግ መሰረት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

13. የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሁብት መሆኑን ለማረጋገጥ በክፍሉ አስተዳደር የተመዘገበና ተረጋግጦ የተሰጠ የባለሀብነት ካርታና ፕላንና ማስረጃ የሚያስፈልግ መሆኑ ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 1195 ተደንግጓል፡፡ መርሁ ይህ ሆኖ አንድ ሰው በጉልበቱ፣ በገንዘቡና በዕውቀቱ ያፈራው የማይንቀሳቀስ ሀብት ባለሀብት ስለመሆኑ በክፍሉ አስተዳደር የተሰጠ የባለሀብትነት ማስረጃ የሌለው ሰው፣ የንብረቱ ባለሀብት መሆኑን ሌሎች የሰነድና የሰው ማስረጃዎችንበማቅረብ ለማስረዳት የሚችል ስለመሆኑ ይህ ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 36320 አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የአመልካቾች አባት ሟች ይባስ ሰዴ፣ የአከራካሪዎች ቤቶች ባለሀብት እንደሆነና አመልካቾች የውርስ ድርሻ ስለሆኑ ቤቶች የማያስረዳ የሰነድ ማስረጃ አመልካቾች ለበታች ፍ/ቤቶች አቅርበው እያለ፣ ቤቶች የአባታችሁ ስለመሆናቸው የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት ያላቀረባችሁ በመሆኑ፣ ክስ የማቅረብ መብትና ጥቅም የላችሁም በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ከላይ የገለጽነውን የሰበር ችሎት አስገዳጅ የህግ ትርጉም ያልተከተለና የአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ2/1/ ድንጋጌ የሚጥስ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

14. ከላይ ከተገለጸው በተጨማሪ የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር የሰጠው ውሳኔና የፃፈው ደብዳቤ የአዋጅ ቁ/ 47/67 እና የሌሎች አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ መሆኑን መርምረናል፡፡ የአመልካቾች አባት አቶ ይባስ ሰዴ ከዚህ አለም በሞት የተለዩት በ1964 ዓ/ም መሆኑ ተረጋግጧል ይህም ማለት በሟች /የአንድ ሰው/ ሀብት የነበሩት ሁለት ቤቶች ሟች በሞት ከተለዩበት ጊዜ ጀምሮ የሟች ወራሾች ሀብት የባለመብትነት መብታቸው ሊተላለፍላቸው የሚችል መሆኑን ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 826 ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ይህም የሟች ይባስ ሰዴ ሁለት ቤቶች፣ አዋጅ ቁጥር 47/67 ከመታወጁ በፊት የሟች አምስት ወራሾች ንብረት ሆኖ በኢትዮጲያ የውርስ

አወራረስ ስርዓት መሰረት ከሟች ወደ ወራሾቹ የሚተላለፍ መሆኑን ያሳያል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 47/67 የተወረሰው ትርፍ ቤትና የከተማ ቦታ ነው፡፡ ሆኖም አዋጅ ቁጥር 47/67 በሚታወጅበት ወቅት አምስት የሚሆኑት የሟች ይባስ ሰዴ ልጆችን ወራሾች የአዋጅ ቁጥር 47/67 አንቀጽ 5 በሚደነግገው መሰረት የነበራቸው ትርፍ ቤት ሳይሆን፣ ለአምስቱ ወራሾች ከነቤተሰባቸው ለመኖሪያነት የማይበቁ ከአባታቸው በውርስ ያገኛቸው አከራካሪዎቹ ቤቶች ናቸው፡፡ ይህም በመሆኑ የሟች ሰራተኞች የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1079 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት በስምምነት ሁለቱን ቤቶች ተካፍለው፣የባለሀብትነት ማስረጃ ለሚሰጠው የስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ጥያቄያቸውንና ማስረጃዎችን አቅርበው እያለ ቤቶች በልማት ምክንያት የፈረሱ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሰጠው ውሳኔና የፃፈው ደብዳቤ አግባብነት ያላቸውን የአዋጅ ቁጥር 47/67 እና የውርስ ህግ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ መሆኑን ያሳያል፡፡ ከላይ በዝርዝር በገለጽናቸው ምክንያቶች ተጠሪዎች አመልካቾች በውርስ አግኝተዋቸው በነበሩ የቤት ቁጥር 375 እና 382 ምትክ የተሰሩትን የቤት ቁጥር 459 እና የቤት ቁጥር 375 እና 382 ምትክ የተሰሩትን የቤት ቁ/ 459 እና የቤት ቁ/530 ለአመልካቾች እንዲያስረክቡ መወሰን ሲገባቸው፣የአመልካቾቹን ክስ ውድቅ በማድረግ የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 171029 የካቲት 10 ቀን 2005 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 135103 ጥር 22 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካቾች ክስ ያቀረቡባቸውና በልማት ምክንያት የፈረሱት በወረዳ 14 ቀበሌ 24 ይገኙ የነበሩት የቤት ቁጥር 382 እና የቤት ቁጥር 379 የሆኑት ቤቶች አመልካቾች ከሟች አባታቸው አቶ ይባስ ሰዴ በውርስ ያገኟቸውና በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሰረት በትርፍነት ያልተወረሱ የግል ሀብታቸው ናቸው በማለት ወስነናል፡፡
3. አመልካቾች በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1079/1/ መሰረት በስምምነት ተካፍለው ለስራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ባስመዘገቡት መሰረት፣ አንደኛ አመልካችና ሁለተኛ አመልካች የውርስ ድርሻ በሆነው የቤት ቁጥር 382 ምትክ በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 14/15 አልታድ የተባለውን ድርጅት የሰራውን የቤት ቁር 530 ተጠሪዎች ለአንደኛና ሁለተኛ አመልካቾች ያስረክቡ በማለት ወስነናል፡፡

4. የሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች የውርስ ድርሻ በሆነው በቤት ቁጥር 459 ተጠሪዎች ለሁለተኛና ሶስተኛ አመልካቾች ያስረክቡ በማለት ወስነናል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

የሰ/መ/ቁ/ 123833

መጋቢት 29 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች----ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ

አይሸሹም መለሰ

ፀሐይ መንክር

አመልካች----------አቶ ለሜሳ ደገፋ ቀረቡ

ተጠሪ---------------የአዳማ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ነ/ፈጅ ቅድስት ቤክሲሳ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የእግድ ትዕዛዝን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም በኦሮሚያ ክልል ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፣ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ከሣሽ ሲሆኑ እነ ቡኔ በዳኔ / 4 ሰዎች/ ተከሳሾች ነበሩ፡፡

ለእግዱ መሰጠት ምክንያት የሆነው የቤት ክርክር ሲሆን የስር ወረዳ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 154 መሠረት በቃለ መሐላ ተደግፎ በአሁን አመልካች ያቀረቡትን አቤቱታ በአዳማ ከተማ ቀበሌ 05 የቤት ቁጥር 369 የሆነውን ቤት እንዲታገድ በመጠየቁ ምክንያት በመ/ቁ/ 90352 ሰኔ 29 ቀን 2007 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ቤቱ እና በቤቱ ውስጥ ያለው ንብረት ጭምር ሌላ ትዕዛዝ እስኪሰጥ ድረስ ለ3ኛ ወገን ተላልፎ እንዳይሰጥ ሲል የእግድ ትዕዛዝ ፍ/ቤቱ ሰጥቷል፡፡

ይህን የእግድ ትዕዛዝ በመቃወም የአሁን ተጠሪ ይግባኝ ብሎ ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም በመ/ቁ/ 21371 ሐምሌ 02 ቀን 2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤትን እግድ ትዕዛዝ እንዳይፈፀም ሲል እግድ ሰጥቷል፡፡

አመልካች የስር ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ በማለታቸው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አስቀርቦ መርምሮ በስር ፍርድ ቤት ክርክር የተነሳው በአመልካች እና ሌሎች 4 ሰዎች መሐከል ሲሆን ተጠሪ የሆነው /አስተዳደሩ/ ግን በክርክር ተካፋይ ያልሆነ፣ ወይም በሕግ መሠረት ወደ ክርክሩ የገባ ሳይሆን ተከሶ መልስ ሳይሰጥ እግድ እንዲነሳ አቤቱታ የማቅረብ መብት ሳይኖረው፣ እንዲሁም የተሰጠው እግድ ጊዜያዊ ሆኖ እያለ የወረዳው ፍርድ ቤት የእግድ ትዕዛዝ ስህተት የሌለበት ሆኖ እያለ በመሻር እንዳይፈፀም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ መሻር ያለበት ነው በማለት የወረዳው ፍርድ ቤትን ትዕዛዝ በማፅናት በመ/ቁ/ 226292 ሐምሌ 23 ቀን 2007 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁን ተጠሪም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት በሰበር ታይቶ እንዲታረምለት አቤቱታ በማቅረቡ መነሻነት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 231128 ታህሳስ 18 ቀን 2008 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ጉዳዩን መርምሮ ክርክር ያስነሳው የመንግሥት ቤት በአዳማ ከተማ መስተዳድር የሚተዳደር መሆኑን ፣ በከተማ ውስጥ የሚገኙ የመንግሥት ቤቶችን የማስተዳደር፣ የመቆጣጠር እና የማከራየት የከተማ መስተዳድሩ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህ የከተማ መስተዳድር በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 158 መሠረት አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው፡፡ ስለዚህ የስር ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በዚህ ሁኔታ ሳያየው የአዳማ ከተማ መስተዳድር ክርክሩ ውስጥ ሳይኖር የእግድ ይነሳልኝ አቤቱታ ማቅረብ አይችልም ብሎ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለው ሆኖ በመገኘቱ በሙሉ ድምጽ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና የወረዳ ፍርድ ቤቱ የሰጡትን ውሣኔ በመሻር የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በማጽናት ወስኗል፡፡

አመልካች የሰበር ሰሚው ፍርድ ቤት የተሰጠውን ፍርድ በመቃወም በ15/6/2008 ዓ.ም.የተፃፈ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ሲሰጥ የሕግ ስህተት ፈጽሟል የሚሉበትን ነጥቦች በመዘርዘር በሰበር ታይቶ እንዲታረምላቸው አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

በአቤቱታው ከዘረዘሩት በአጭሩ፡- በስር ፍርድ ቤት እግድ እንዲሰጥልኝ ጠይቄ ፍ/ቤቱ እግዱን የሰጠልኝ ሲሆን፣ የአሁን ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ተከሣሽ ያልነበረ፣ ወይም በሕግ አግባብ ወደ ክርክሩ ጣልቃ ሳይገባ፣ ወይም ለወረዳው ፍርድ ቤት እግዱ እንዲነሳ አቤቱታ ሳያቀርብ የእግድ ትዕዛዙን በከፍተኛ ፍርድ ቤት አሸሯል፡፡

እግዱን ያነሳው ፍርድ ቤት የፍትሕ ስርአቱን ጥያቄ ውስጥ በሚጥል መልኩ አቤቱታ ሲቀርብለት መጥሪያ ሳይልክልኝ በጉዳዩ ላይ ምንም አይነት መልስ ሳልሰጥ ሕገመንግስታዊ

መብቱን ተጠቅሜ ክርክር ሳላደርግበት የአዳማ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠውን ትዕዛዝ የሻረበት ትዕዛዝ እንዲደርሰኝ አድርጓል፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ጊዜያዊ እግዱ እንዲቆይ ማድረጉ የማስተዳደር እና የመቆጣጠር መብቱን በምንም መልኩ የሚነፍግ አይደለም፡፡ በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ እና የአዳማ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለተፈፀመበት ይታረምልኝ በማለት ሰፊ አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

አቤቱታው የቀረበለት የሰበር አጣሪም ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ በስር ተከራካሪ ባልነበረበት በሥር ፍ/ቤት በተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ላይ ያቀረበው ይግባኝ ተቀባይነት አግኝቶ እግድ የተነሳበትን አግባብ የሕግ መሠረት ያለው መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለሰበር ችሎት ይቅረብ በማለቱ ሊቀርብ ችሏል፡፡

አጣሪው ከያዘው ጭብጥ አኳያ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ መጥሪያ ተልኮለት በ19/1/09 የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ ከመልሱም በአጭሩ እንደተመለከትነው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠው ውሣኔ የተፈፀመ ስህተት የለም፣ ምክንያቱም አንድ አቤቱታ አቅራቢ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 154 የተሰጠውን እግድ እንዲነሳለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 158 መሠረት እግዱን ለሰጠው ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ የሚችለው ከሳሽ ወይም ተከሣሽ ነው የሚል የሕግ ድንጋጌ የለም፡፡ የአሁን ተጠሪ በክርክሩ ተካፋይ ሳይሆን የተሰጠውን እግድ እንዲነሳለት የመጠየቅ የሕግ አግባብ የለውም የሚለው ጥያቄ በሕግ ድንጋጌው ስር የሚወድቅ አይደለም፡፡ በመሆኑም ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሚነቀፍ ውሣኔ ስላልሰጠ ይፅናልን፡፡ አመልካች ቤቱን ያገኘሁት ከተለያዩ አካላት ድጋፍ ደብዳቤ ተጽፎልኝ ነው ይበል እንጂ ማስረጃ ግን የለውም፣ ተጠሪ ባልተከሰበሰበት እና በማያውቀው ጉዳይ ንብረቱ በግለሰቦች መካከል በተፈጠረ ግጭት መታገዱ አግባብ አይደለም በማለት በመልሱ ከገለፀው ውስጥ ለጉዳዩ አግባብ ነው ያልነውን መዝግበናል፡፡

አመልካችም ለቀረበው መልስ የመልስ መልሳቸውን አቤቱታቸውን በሚያጠናክር መልኩ አቅርበው ተያይዟል፡፡

እኛም የቀረበውን ጉዳይ በአጣሪው ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከስር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ከአመልካች አቤቱታ እና መልስ ፣ የመልስ መልስ እና አግባብነት ካለቸው የሕጉ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

ከላይ እንደተመለከትነው ጉዳዩ በስር ፍርድ ቤት እግድ ከመስጠት ጋር ተያይዞ የተነሳ ክርክር ሲሆን፣ የስር ፍርድ ቤት ክርክር ያስነሳውን ቤት እግድ የሰጠው በስር ከሳሽ በአሁን አመልካች ጠያቂነት ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ተከሣሽ የነበረው ሌላ ሰው እንደነበረ እና ተጠሪ ግን በክርክሩ

ተካፋይ እንዳልሆነ ተጠሪም ያመነው እና በስር ፍርድ ቤቶችም ሲገለፅ የመጣ ነገር በመሆኑ አያከራክርም፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 40፣ 41፣ 42፣ 358፣ 418 በተደነገገው ሥርዓት ተጠሪ ወደ ክርክሩ ውስጥ ተሳታፊ መሆኑም አልተመለከተም፡፡ ክርክር ያስነሳው ቤት ግን የአስተዳደሩ /ተጠሪ የሚያስተዳድረው / ነው የተባለ በመሆኑ ተጠሪው በሚያስተዳድረው ቤት ላይ ሁለት ወገኖች ክርክር አንስተው ጉዳዩ በፍርድ ቤት የተያዘ በመሆኑ አመልካች እግድ በቤቱ ላይ እንዲሰጥበት ጠይቀው እግዱን የወረዳ ፍርድ ቤቱ ሰጥቷል፡፡

እግድ የተሰጠው በክርክሩ ውስጥ ተሳታፊ ባልሆነው ተጠሪ በሚያስተዳድረው ቤት ላይ በመሆኑ ተጠሪ ይህ ጉዳይ አይመለከተውም ምንም ጥያቄ የማንሳት መብት የለውም ለማለት የሚቻል አይሆንም፡፡ ቁም ነገሩ ግን አንድ በንብረቴ ላይ እኔ ሳላውቀው ትዕዛዝ ተሰጥቶብኛል የሚል ወገን ፍርድ ቤቱ እኔን ሳያሳትፍ ያልተገባ ትዕዛዝ ሰጥቶብኛል በማለት አሁን በዚህ መዝገብ የተሰጠው እግድ አይነት ትዕዛዝ በተሰጠ ጊዜ አቤቱታ የማቅረብ መብት ያለው መሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 158 በግልጽ ተደንግጓል፡፡

አቤቱታውንም ተቀብሎ የማስተናገድ እና የተሰጠው የማገጃ ትዕዛዝ በቀረበው አቤቱታ መሠረት ሊያሻሽል ፣ሊያነሳ፣ ሊሠርዝ የሚችለውም እግዱን የሰጠው ፍርድ ቤት ሲሆን፣ የቀረበውን አቤቱታ እግዱን የሰጠው ፍርድ ቤት ሳይቀበል ውድቅ ያደረገ እንደሆነ ይግባኝ የሚባልበት ከሚሆን በቀር በክርክር ተሳታፊ ያልሆነ ወገን በስር ፍርድ ቤት በተሰጠ እግድ ትዕዛዝ በቀጥታ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይግባኝ የሚያቀርብበት እና ትዕዛዙ ላይ ውሣኔ የሚያሰጥበት ስርዓት ግን በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ ውስጥ የተደነገገ አይደለም፡፡

የእግድ ትዕዛዙ ጠቀሜታው ለጊዜው የተሰጠ በመሆኑም ይህ እግድ ሳይነሳ መቅረቱ በአመልካች ላይ የሚያስከትለው ችግር ካለ እግዱን ለሰጠው ፍርድ ቤት አቤቱታ አቅርቦ በስር ፍርድ ቤት ቀርቦ አቤቱታም አቅርቦ የስር ፍርድ ቤቱ በቀረበው አቤቱታ ላይ የሰጠው የተለየ ትዕዛዝ ስለመኖሩ የስር ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ግልባጭ አያመለክትም፡፡ አመልካችም እግድ የተሰጠው አላግባብ ነው የሚል አቤቱታውን በስር ፍርድ ቤት አቅርቦ ትዕዛዝ ባላሰጠበት ሁኔታ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በክርክር ተሣታፊ ባልሆነበት ጉዳይ በቀጥታ ይግባኝ በማቅረብ የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ማሻሩ ፣ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ሥነ ሥርዓታዊ መስመሩን ጠብቆ የቀረበ ይግባኝ መሆን ያለመሆኑን ሳያረጋግጥ እና በስር ፍርድ ቤት ታይቶና ትዕዛዝ የተሰጠበት መሆን ያለመሆኑን ሳይመረምር በመዝገቡ ላይ ከሣሽ ወይም ተከሣሽ ወይም ጣልቃ ገብ ያልሆነ ወገን ይግባኝ ቅሬታ ሲቀርብለት ተቀብሎ የስር ፍርድ ቤትን ትዕዛዝ መሻሩ ፣ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የፈፀመውን ስህተት ማረም ሲገባው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የይግባኝና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት

የሰጠውን ውሣኔ ማጽናቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

**ው ሣ ኔ**

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝሰሚ ችሎት በመ/ቁ/ 231128 ታሕሳስ 18 ቀን 2008 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡ ፡፡
3. የውሣኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይድረስ መዝገቡ ውሣኔ ስላገኘ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

   ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ. 123123

ሚያዚያ 16 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ

አይሸሹም መለሰ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- አቶ ተኽሊት አፈወርቂ - አልቀረበም

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን - የመቀሌ ቅርንጫፍ አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

**ፍ ር ድ**

1. ጉዳዩ የቀረበው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የአመልካች ክስበ ይርጋ ቀሪ ነው በማለት የሰጠውን ውሳኔ የህግ መሰረት ያለው መሆኑን በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የአመልካች መኪና የኮንትሮባንድ ዕቃጭና ተገኝታለች በማለት ተጠሪ በቁጥጥር ስር ካዋላት በኋላ የካቲት 26 ቀን 2004 ዓ.ም በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ተለቅቃለች፡፡

   አመልካች ተጠሪ መኪናዬን አላግባብ ቁጥጥር ስር በማዋል ጉዳት አድርሶብኛል በማለት ግንቦት 29 ቀን 2004 ዓ.ም የተጻፈ ክስ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ፣ በቀረበው ክስ ውስጥ ያሰፈረው ፍሬ ነገር ዕውነት ስለመሆኑ የአመልካች ጠበቃ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 92 መሰረት ለማረጋገጥ እንደማይቻልና አመልካች በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 92 መሰረት የክሱን እውነተኛነት ቀርቦ ያረጋግጥልን በማለት በመቃወሙ፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከጅምሩ በሬጅስትራር በኩል ቴክኒካል መስፈርቶች የተሟሉ መሆኑ ተረጋግጦ ያልቀረበ መዝገብ ነው በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

2. ከዚህ በኋላ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረብኩት ክስ የተጋነነ ስለሆነ አስተካክዬ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት እንዳቀርብ ይፈቀድልኝ በማለት ጥቅምት 5 ቀን 2007 ዓ/ም አመልክቷል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም አመልካች ስልጣን ላለው

ፍርድ ቤት ክስ ለማቅረብ እንደሚችሉ በመግለጽ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ጥር 4 ቀን 2007 ዓ.ም ለመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ ያቀረበ ሲሆን፣ ተጠሪ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ቴክኒካል ሁኔታዎችን ባለማሟላቱ የተዘጋ በመሆኑ ይርጋ ሊያቋርጥ አይችልም፡፡ ስለዚህ ክሱ በይርጋ ይቋረጣል በማለት ያቀረበውን መቃወሚያ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በማለፉ፣ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ የወሰነ ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ያለ ፍርድ ቤቱ ፈቃድ ክሱን ያቋረጠ በመሆኑ፤ ለክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦት በነበረው ክስ ይርጋ አይቋረጥም፡፡ ስለዚህ መኪናዋ ከተለቀቀችበት ጊዜ ጀምሮ ሲታሰብ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንን በመቃወም ሲሆን ተጠሪም በጽሁፍ መልስ ሰጥቷል አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

3. ከስር የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተገለጸው ሲሆን፣ በእኛ በኩል እንዳየነው አመልካች ተጠሪ መኪናዬን ከህግ አግባብ ውጭ በመያዝ፣ ጉዳት ስላደረሰብኝ ካሳ ይክፈለኝ በማለት በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 53029 ግንቦት 24 ቀን 2004 ዓ.ም አቅርቦት የነበረው ክስ በፍታሐ ብሔር ሥነ- ሥርዓት ህግ ቁጥር 92 መሰረት ዕውነት መሆኑ ተረጋግጦ ያልቀረበ መሆኑን በመግለጽ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ክሱን ውድቅ በማድረግ መዝገቡን የዘጋው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ አመልካች በህጉ የተገለጸው ቴክኒካል መስፈርት አያሟላም ተብሎ የተዘጋበት መዝገብ እንዲንቀሳቀስለት ያመለከተው ፍርድ ቤቱ አልተሟላም ያለውን መስፈርት ለማሟላት ሳይሆን፣ በቀረበው ክስ የተገለጸው የገንዘብ መጠን የተጋነነ በመሆኑ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክሳችንን እንድናቀርብ በማለት እንደሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ ይዘት ተረድተናል፡፡ ይህም አመልካች በተጠሪ ላይ በመዝገብ ቁጥር 53029 ግንቦት 24 ቀን 2004 ዓ.ም አቅርቦት የነበረው ክስ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 278 ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) በተደነገገው መሰረት የአመልካች ክስ በፍ/ስ/ስ/ህግቁጥር በተደነገገው መሰረት ዕውነት ስለመሆኑ ተረጋግጦ በከሳሽ (አመልካች) ባለመቅረቡ ምክንያት ውድቅ ያደረገው መሆኑንና አመልካች ጥቅምት 5 ቀን 2007 ዓ.ም ባቀረበው ማመልከቻ፣ በክሱ ውስጥ ተጠሪ (ተከሳሽ) እንዲከፍል የተጠየቀው ገንዘብ ዕውነትነት የሌለውና የተጋነነ መሆኑን የሚገልጽ በመሆኑ ከሳሽ ክሱን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 92 መሰረት ዕውነት መሆኑን በማረጋገጥ ክሱ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለማስቀጠል እንደማይችል መሆኑን በማረጋገጥ ክሱን ስልጣን ላለው ፍርድቤት ለማቅረብ እንዲችል ጥያቄ ያቀረበበት ነው፡፡

4. ይህም አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.ር92 መሰረት ዕውነት መሆኑን በማረጋገጥ ያቀረበው ክስ የሌለና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህ ቴክኒካል

ሁኔታ ካልተሟላ ጉዳዩን ልመለከተው አልችልም በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.ር 278 ንዑስ አንቀጽ 2 (ሀ) መዝገቡ እንዲዘጋ የሰጠውን ትዕዛዝ ለማስለወጥ የሚያስችል በቂ ምክንያት በማቅረብ ክሱ እንዲቀጥል ያላደረገ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች በመዝገብ ቁጥር 53029 ግንቦት 24 ቀን ያቀረበው ክስ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.92 የተደነገገውን አስገዳጅ መስፈርት የማያሟላ መሆኑን በማረጋገጥ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መዝገብ እንዲዘጋ የሰጠው ትዕዛዝ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምንም አይነት ክስ እንዳላቀረበ የሚያስቆጥርና የይርጋ ጊዜ የማቋረጥ ውጤት የሌለው መሆኑን በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.278 ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) እና ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌዎች ይዘትና ይህ ሰበር ችሎት ስለድንጋጌዎቹ ዓላማ ተግባራዊ አፈጻጸምና ህጋዊ ውጤት በሰበር መዝገብ ቁጥር 90361 ከሰጠው አስገዳጅ የህግ ትርጉም ለመረዳት ይቻላል፡፡

5. ከዚህ አንጻር ሲታይ አመልካች መኪናዋ እንድትለቀቅ በፍርድ ከተወሰነበት የካቲት 26 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ ለመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ እስካቀረበበት ጥር 5 ቀን 2007 ዓ.ም ድረስ፡፡ መብቱን ለማስከበር ህጋዊና ቴክኒካዊ መስፈርቶችን ያሟላ ክስ አቅርቦ እንደማያውቅ ተቆጥሮ የይርጋው ጊዜ መሰላት ያለበት በመሆኑ አመልካች የፍታሐ ብሔር ህግ ቁጥር 2143 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው የሁለት ዓመት የይርጋ የጊዜ ገደብ ካለፈ ከአስር ወራት በኋላ ክሱን ለመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ መሻሩ ከላይ የተጠቀሱትን የህግ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገና የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 76156 መስከረም 5 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
2. ግራ ቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

የሰ/መ/ቁ. 124552

ሚያዝያ 16 ቀን 2009 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ

ቀነዓ ቂጣታ

ፀሐይ መንክር

**አመልካች** ፡- አቶ ምትኩ አበበ - ከጠበቃ ነቃጥበብ ገ/ሚካኤል ጋር ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- የከሰረው ሆላንድ ካር ኃ/የተ/የግ/ማሕበር - ነ/ፍጅ ፍቃዱ አስፋው

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የጀመረው በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 196585 በተሠጠው ውሣኔ እንደታየው በዱቤ የመኪና ሽያጭ ውል ምክንያት መኪና እንዲረከቡ በተወሰነው መሠረት አባይ መኪናን መውሰድ ሲገባቸው ውል ከገቡለት መኪና በዋጋው የብር 66,100.00 ብር ልዩነት ያለውን ተከዜ መኪና በመውሰዳቸው በብልጫ የወሰዱትን የመኪና ዋጋ ብር 66,100.00 እና ቅድሚያ ክፍያ ከፍለው የቀረባቸውን ገንዘብ ተደምሮ በጥቅሉ ብር 192,100.00 ብር እንዲከፍሉ በማለት ነሐሴ 21 ቀን 2007 ዓ.ም. በአጭር ሥነ ሥርዓት ታይቶ እንዲወሰንለት ክስ ያቀረበ ሲሆን፣ የቀረበውን ክስ እና ማስረጃ ከመጥሪያ ጋር ለአመልካች ተልኮላቸው የመከላከያ ማስፈቀጃ ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ የስር ተከሣሽ በችሎት ቀርበው እዳቸውን ያመኑ በመሆኑ እና የመከለከያ ማስፈቀጃ ቢያቀርቡም እዳቸውን እያመኑ እና እዳ እንደሌለባቸው ሣይክዱ ወይንም በዋጋ ልዩነት ያለውን መኪና አልወሰደኩም ወይም ደግሞ እዳውን ከፍያለሁ በማለት ሣይገልፁ ወይም በመከላከያ ማስፈቀጃቸው ጽሁፍም ላይ ሣያነሱ መ/ማስፈቀጃ ይፈቀድልኝ በማለት ብቻ ሊፈቀድ የሚገባው ሕግ በሚያዘው መሠረት ሲቀርብ እንጂ መከላከያ ማስፈቀጃ ይፈቀድልኝ በማለት አይደለም ሲል ማስፈቀጃውን ውድቅ አድርጌዋለሁ በማለት አመልካች በሰጡት የእምነት ቃል መሠረት በክሱ የተገለፀውን ገንዘብ እንዲከፍሉ በአጭር ሥነ ሥርዓት የወሰነ መሆኑን ገልጾ በስር ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሣኔ

እንዲሻርለት፤ አመልካች እና ክርክሩ በአጭር ስነ ሥርዓት ሊታይ ስለማይገባው መከላከያ ማስፈቀጃው ተቀባይነት አግኝቶ ጉዳዩ እንዲታይለት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታቸውን ቢያቀርቡም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ግድፈት የተፈፀመበት አይደለም በሚል የይግባኝ ቅሬታውን ሰርዞታል፡፡

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነውም ይህው በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ ሲሆን፣ አመልካች ሚያዝያ 7 ቀን 2008 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ የስር የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያለሕጋዊ ምክንያት የመከላከያ ማስፈቀጃውን ውድቅ ያደረገው እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩ በይግባኝ ቀርቦለት የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.337 ጠቅሶ የስር ፍርድ ቤት በውሣኔው ላይ ግድፈት አልተገኘም በማለት ይግባኙን የሠረዘው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሞ ነው፡፡ በአጭር ስነ ስርዓት እንዲታይ ክስ የቀረበው በደሀ ደንብ ነው፡፡ ተጠሪ ደሀ ሊባል አይገባም፡፡ ምክንያቱም ተጠሪ የከሰረውን የሆላንድ ካር ከብር 83 ሚሊዩን ብር በላይ ንብረት እንዲያስተዳድር ተረክቧል፡፡ በመሆኑም ዳኝነት ሣይከፍል ክስ ሊያቀርብ አይገባም፡፡

የተጠሪ ክስ ጥያቄ የቀረበው ፍርድ ባረፈበት አፈፃፀም በከፈተበትና በይግባኝ በፀና የሽያጭ ውል ጉዳይ ላይ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 284 መሠረት በአጭር ሥነ ሥርዓት ክስ ሊቀርብበት ስለማይችል የተጠሪን ክስ የስር ፍርድ ቤት ተቀብሎ ያስተናገደው ከሕግ ውጭ ነው፡፡ በውል መሠረት በነበረ መኪና ዋጋ በተመሣሣይ የተረከበው መኪና ስለሆነ የዋጋ ልዩነት ሊጠየቅበት አይገባም በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል ተብሎ ይወሰንልን፣ የስር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ተሽሮ አመልካች ክሱን እንዲከላከል እንዲፈቀድልኝ ሲሉ አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ አመልካች በአጭር ስነ ስርዓት ታይቶ እንዲወሰን ለቀረበባቸው ክስ ያቀረቡት ማስፈቀጃ ማመልከቻ በሕጉ መሠረት የቀረበአይደለም በማለት ሳይቀበለው የተሰጠው ውሣኔ አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መጥሪያ ደርሷቸው መልሣቸውን እንዲያቀርቡ መዝገቡ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ችሏል፡፡

ተጠሪም ግንቦት 10 ቀን 2008 ዓ.ም የተፃፈ መልስ ያቀረበ ሲሆን በመልሱ የገለፀውም ማህበሩ ጥር 07 ቀን 2005 ዓ.ም በመ/ቁ/ 20080 የመክሰር ውሣኔ ተሰጥቶበታል፣ አመልካችም ከማህበሩ ጋር ለተከዜ መኪና የሽያጭ ውል መዋዋላቸውን፣ ተከዜ መኪና እንዲረከቡ አልያም በግማሽ የከፈሉት ገንዘብ እንዲመለስ አመልካች መክሰሳቸውን፣ በዚሁ መሠረት በመ/ቁ/ 196585 በሆነው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አመልካች ተከዜ መኪና እንዲረከቡ እና ለማህበሩም ቀሪ ገንዘብ ብር 126,000.00 እንዲከፍሉ መወሰኑን፣ ነገር ግን አመልካች በውሣኔው መሠረት ገንዘቡን ያለመክፈላቸውን፣ እንዲሁም አመልካች የተዋዋሉት መኪና ተከዜ ሆኖ ዋጋውም 218,000.00

ሲሆን አመልካች በአፈፃፀም መዝገብ ቁ. 197933 በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በፍ/ብሔር ችሎት ዋጋው 285,000.00 የሆነውን እና ከተከዜ መኪና ልዩነት ያለውን አባይ መኪና የወሰዱ ሲሆን ልዩነቱን ብር 66,100.00 ስለመክፈላቸው ያላረጋገጡ መሆኑን በአጠቃላይ ከአመልካች የሚፈለግ ብር 192,100.00/አንድ መቶ ዘጠና ሁለት ሺህ አንድ መቶ ብር/ የሚፈለግባቸው መሆኑን ጠቅሶ ክስ መመስረቱን እና አመልካችም ቀርበው ዋጋው ልዩነት ያለውን መኪና ያለመውሰዳቸውን፣ እዳም የሌለባቸው መሆኑን ሳይሆን የተከራከሩት እዳው መኖሩን አምነው ከተጠሪ የሚፈለግበት ገንዘብ ያለ በመሆኑ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ በመሆኑም የስር ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 242 መሠረት የሚፈለግባቸውን እንዲከፍሉ የወሰነ ሲሆን፣ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያላነሱትን ክርክር የአባይ መኪና የወቅቱ ዋጋ 285,000.00 አይደለም በማለት መከራከራቸው ተቀባይነት የሌለው መሆኑን እና ችሎቱም በሕግ መሠረት የፍሬ ጉዳይ ክርክር የማድረግ ሥልጣን የሌለው መሆኑን ገልፆ የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ እንዲፀናለት ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም በቀደመው አቤቱታ ያቀረቡትን በመልስ መልስ በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገብ ተያይዟል፡፡

ፍ/ቤቱም የቀረበውን አቤቱታ እና መልስ ከስር ፍርድ ቤት ውሣኔ እና በአጣሪው ከተያዘው ጭብጥ አንፃር አግባብነት ካለው ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

አመልካች ከተጠሪ ጋር የመኪና ሽያጭ ውል መኖሩ ያላከራከረ ሲሆን ግራ ቀኙም በመኪናው እርክክብ ላይ ያነሱት የተለየ ነገር የለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ተጠሪ በአጭር ስነ ሥርዓት ያቀረቡት ክስ ደርሷቸው የመከላከያ ማስፈቀጃ ማቅረባቸውን የስር ፍርድ ቤት በውሣኔው ላይ የመዘገበ ሲሆን ያቀረቡት የመከላከያ ማስፈቀጃ ጥያቄን ማቅረባቸውን ጠቅሶ ነገር ግን ያቀረቡት የመከላከያ ማስፈቀጃ ይዘት በክሱ ላይ ያለውን ገንዘብ መልሻለሁ፣ እዳም የለብኝም በማለት ሳይሆን በቃል በችሎትም ሲጠየቁ ገንዘቡ እዳቸው መሆኑን አምነው ነገር ግን ከተጠሪ የምፈልገው ገንዘብ ስላለ ነው በማለት እንዲፈቀድላቸው መጠየቃቸውን ገልጿል፡፡

ተጠሪ ከላይ የተገለፀውን መኪና ያስረከበው በፍርድ አስገዳጅነት ሳይሆን ተከዜ መኪና እንዲያስረክብ ተወስኖ አባይ መኪና ያስረከበው ፍርድ ከተሰጠና በዋናው ጉዳይ አፈፃፀም ላይ እያሉ ግራ ቀኙ ባደረጉት ስምምነት መሠረት መሆኑን የስር ፍርድ ቤት መዝገብን አስቀርበን ተመልክተናል፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 284 መሠረት በአጭር ስነ ሥርአት የሚቀርብ ክስ ሊቀርብ የሚችለው ምንም አይነት መከራከሪያ በሌላኛው ወገን የማይቀርብ መሆኑ ሲረጋገጥ እና ወዲያው ሊወሰን የሚችል ሲሆን መሆኑን የሕጉ ድንጋጌ ያሳያል፡፡

የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 284/ሀ/ በአጭር ሥነ ሥርዓት ክስ ለማቅረብም በግልጽ ውል ወይም በነገሩ አካባቢ ሁኔታ በሚመሠረት ውል ወይም በሐዋላ ወረቀት ወይም በገንዘብ አለብኝ ሰነድ ወይም በቼክ ወይም ተራ የሆነ ባለዕዳነትን የሚመለከት ውል መሆን እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ አመልካች እና ተጠሪ በቅድሚያ የተገናኙት በውል ቢሆንም ነገር ግን አሁን የሚፈለገውን ገንዘብ ስር ከሳሽ እየጠየቀ ያለው የቀደመውን ውል ለማስፈፀመ በተደረገ ስምምነት ላይ የተጨመረው እንጂ በግልጽ ውል ላይ የተመሠረተ ባለመሆኑ እንዲሁም ስር ከሳሽ ባቀረበው ክስ ስር ተከሣሽ ደግሞ የምጠይቀው ገንዘብ አለኝ እያለ ያለ በመሆኑ በግራ ቀኙ መሐከል ክርክር ያለ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 284 ከሚፈቅደው የአጭር ስነ ሥርዓት ውጭ መሆኑን የሚያሳይና የክርክሩ አመራርም በመደበኛው የሙግት ሥርዓት መመራት የሚገባው መሆኑን ተረድተናል፡፡

በመሆኑም የቀረበውን ክስ ተከሣሽ አልካደም በማለት ብቻ ተከሣሽ የሚያቀርበውን ሌሎች ገንዘቡን ልከፍል አይገባም በማለት የሚያቀርባቸውን መከራከሪያ ነጥቦች በመገደብ እና የመከላከያ ማስፈቀጃውን ውድቅ በማድረግ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 231275 ሕዳር 30 ቀን 2008 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ እና ፍርድ ከዚህ በፊት በተመሳሳይ ጉዳይ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰ/መ/ቁ/ 43315 የሰጠውን አስገዳጅ ውሣኔ ካለማገናዘብ እና የቀረበውን ጉዳይ ካለመመርመር የሰጠው ውሣኔ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሲሆን፣ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ በመ/ቁ 174388 የካቲት 21 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት በስር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ እና ውሣኔ ላይ የተፈፀመውን የሕግ ስህተት ሳያርም የስር ፍርድ ቤት ፍርድ ጉድለት የሌለበት ነው በማለት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 231275 ሕዳር 10 ቀን 2008 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ እና ፍርድ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 174388 የካቲት 21 ቀን 2008 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ በመገኘቱ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሕዳር 10 ቀን 2008 ዓ.ም. በውሣኔ የዘጋውን የመ/ቁ/ 231275 በማንቀሳቀስ ጉዳዩ በመደበኛ ስነ ስርዓት እንዲገባ በማድረግ የግራ ቀኙን ማስረጃ በመመልከት ተገቢ ህጋዊ ውሳኔ እንዲሰጥ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/ 343/1/ መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡

3. ከስር ፍርድ ቤት የቀረበው የመ/ቁ/ 231275 የሆነው መዝገብ በመጣበት አኳኋን ተመላሽ ይደረግ፡፡
4. የውሣኔው ትክክል ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች  እንዲላክ ታዟል፡፡
5. መዝገቡ ውሣኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

የሰ/መ/ቁጥር 127580

ሚያዚያ 26 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሀመድ

ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ

ቀነዓ ቂጣታ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን - አልቀረቡም፡፡

ተጠሪ፡- ዲኖ ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - አልቀረበም፡፡

**መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

**<u>ፍ ር ድ</u>**

1. ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍታብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ ለአመልካች መክፈል የሚገበው የመኪኖች ዋጋ እንደገና ተጣርቶ ሊወሰን ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ በሕግአግባብ የተሰጠ ነው ወይስ አይደለም?የሚለውን ጭብጥ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በተጠሪ ሥም፤ በአመልካች ገንዘብ፤ ተጠሪ የሚሠራውን መንገድ ለመቆጣጠር አመልካች ለቀጠራችውን ተቆጣጣሪ መሀንድሶች አገልግሎት ሲሰጡ የቆዩ የሰሌዳ ቁጥር 3-43969 ኢ.አ እና የሌዳ ቁጥር 3-43997 ኢ.አ የሆኑ መኪኖች አመልካች ለመረከብ ያቀረበውን ክስና የዳኝነት ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡
2. ተጠሪ ከላይ ቁጥራቸው የተገለፁትን መኪኖች የሥር ከሳሽ /አመልካች/ብር 1,185,688.16 /አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰማንያ አምስት ሺህ ስድስት መቶ ሰማንያ ሥምንት ብር ከአስራ ስድስት ሣንቲም/ ለተጠሪ ሰጥቶ፤ የተገዙና መኪኖቹ አመልካች ለመደባቸው ተቆጣጣሪ መሀንዲሶች አገልግሎት ሲሰጡ የቆየ መሆናቸውን ገልፃ፣ ሁለቱም መኪኖች የድርጅቱን ሥራ በመምራት ላይ እያሉ የተገለፀው ሙሉ በሙሉ ከጥቅም ውጭ ሆነዋል፡፡ ይህንን ዕውነታ ተከሳሽ የሚያውቀው ሲሆንአዋሽ ኢንሹራንስ /አ.ማ/ ሊያረጋግጠው የሚችለው ፍሬ ነገር ነው፡፡ ተከሳሽ መኪኖች አገልግሎት የሰጡት ሶስት ዓመት ከሥምንት ወር ዲፕሪሴሽን ዋጋ ተጠቅሶ ቀሪውን ለከሳሽ ለመክፈል በፅሑፍ ጥያቄ አቅርቧል፡፡ በሌላ

በኩል የመኪኖቹ ዋጋ በፊት ከተገዙበት ከእጥፍ በላይ ስለጨመረ ልዩነቱን ከሳሽ ሸፍኖ አዲስ መኪኖች ገዝተው እንዳስረክበው ጥያቄ አቅርቤለታለሁ በማለት ተከራክሯል፡፡

3. የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ለአመልካች የተስማማው መኪኖቹን እንደሆነና መኪኖቹ ተገልብጠው ከጥቅም ውጭ በሆኑ የአገልግሎት ቅናሽ ከዋጋቸው ቅናሽ የሚደረግ ስለመሆኑ አመልካችን ተጠሪ ያልተስማሙ መሆኑን ገልዖ፣ ተጠሪ መክፈል የሚገባው መኪኖቹ በወቅቱ ገበያ የሚያወጡትን ገንዘብ መሆን አለበት፡፡ ተጠሪ የሶስት አመት ከስምንት ወር የአገልግሎት ቅናሽ ከዋጋቸው ላይ ይደረግልኝ በማለት የተከራካሪ ቢሆንም፤ መኪኖቹ በአደጋ ሙሉ በሙሉ በመውደማቸው፣ ለመኪኖቹ የመድን ሽፋን የሰጠው የኢንሹራንስ ድርጅት፤ አመልካች ክስ ካቀረበበት ገንዘብ ያሰ ገንዘብ የከፈለው መሆኑን፤ በማስረጃ አላረጋገጠም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የመኪኖቹ ግምት እንዲሰራ ትእዛዝሰጥቸ የሰሌዳ ቁጥር 3-43969 አ.አ ብር 780,000 /ሰባት መቶ ሰማንያ ሺህ ብር/የሚያወጣ እንደነበርና የሰሌዳ ቁጥር 3-43997 ብር 820,000 / ሥምንት መቶ ሃያ ሺህ ብር/ያወጣ እንደበር ቢርቢስ ገዝሙ የንብረት ጉዳት ገማች ሪፖርት አቅርቦልኛል፡፡ ይህም አመልካች ተጠሪ እንዲከፍለው የጠየቀው ብር 118568348/አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሰማኒያ አምስት ሺህ ስድሰት መቶ ሰማኒያ ሶስት በር ከርባ ሥምንት ሣንቲም/ መኪኖቹ በወቅቱ ከሚያወጡት ዋጋ በታች በመሆኑ ይህንን ገንዘብ ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ፤ ከዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ይክፈል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

4. ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ፤ በአንድ በኩል መኪኖቹ በደረሰባቸው አደጋ ምክንያት በመወደማቸው ይግባኝ ባዩ /ተጠሪ/ የመድን ሽፋን ከሰጠው የኢንሹራንስ ድርጅት አመልካች የመልሰ ሰጭ እንዲቀበል ማድረግ ሲገባው ራሱ ተቀብሎ ወስዷል ካለ በኋላ፤ በሌላ በኩል ባለሙያው የመኪኖቹ ዋጋ እየጨመረ እንደሚሄድ ታሳቢ በማድረግና የመኪኖቹን የአገልግሎት እርጅና ቀናሽ ታሳቢ ሣያደርግ ግምቱን ሠርቶ ማቅረቡ ስህተት ያለበት ነው በማለት የመኪኖቹ ዋጋበሌላ ገለልተኛ ባለሙያ ተሠርቶ እንዲቀርብ በማድረግ፣ የሥር ፍርድ ቤት ይግባኝ ባይ ለመልስ ሰጭ ሊከፍል የሚገባውን የገንዘብ መጠን ውሣኔ ይሰጥበት በማለት በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 343/1/ መሠረት መልሶልኮለታል፡፡

5. አመልካች ውሣኔ ያረፈበት ገንዘብ ባለሙያ ገምቶ ካቀረበው ያነሰ ሆኖ እያለና፤ የመኪኖች ዋጋ የእርጅና ተቀንሶ ተጠሪ የሚከፍል ስለመሆኑ አመልካችና ተጠሪ በተዋዋሉት ውሉ ላይ ባልተገለፀበትና ባልተስማማንበት ሁኔታ፤ የባለሙያ ግምት ውድቅ ለማድረግ ወደ ምክንያት ሣይኖረው ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ መሻሩና ወደ ሥር ፍርድ ቤት ሌላ የባለሙያ ግምት እንዲያሰራ ጉዳዩ መልሶ መላኩ መሠረታዊ የህግ ስህተት

ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ ተፈልጎ ሊገኝ ያልቻለ መሆኑን አመልካች የቃለመሀላ ማመልከቻ በማቅረቡ ህዳር 15 ቀን 2009 ዓ.ም በታተመው አዲስ ዘመን ጋዜጣ  ጥሪ ተደርጎለት ባለመቅረቡ፣ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

6. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና አመልካች የቀረበው የሰበር አቤቱታ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ተጠሪ መኪኖቹን እንዲመልስለት መኪኖቹን መመለስ የማይችል ከሆነ መኪኖቹን ለመግዛት የሰጠውን ገንዘብ እንዲከፍል የዳኝነት ጥያቄ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ መኪኖቹ በአደጋ የወደም ለመሆኑ መኪኖቹን በአካል ላስረክበው አልችልም፡፡ ተመሣሣይ ይዘት ያላቸው መኪኖች ገዝቸ ለአመልካች ለመተካት፤ የመኪኖቹ ዋጋ ከእጥፍ በላይ ያደገ ስለሆነ፣ ቀሪውን ዋጋ ከሳሽ አመልካች ችሎ ገዝቸ እንድተካለት ጥያቄ አቅርቤያለሁ፡፡ የመኪኖቹ የእርጅናና የአገልግሎት ዋጋ ቅናሽ ተደርጎልኝ የመኪኖቹን ዋጋ ልክፈል የሚል መከራከሪያ አቅርቧል፡፡ ይህ የተጠሪ ክርክር በጉዳት ካሣ ምክንያት የወደሙት መኪኖች፣በአደጋው ምክንያት ከጥቅምውጭ በሆኑበት ወቅት መኪኖቹ ከተገቡበት ዕጥፍ የሆነ የገበያ ዋጋ የነበራቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ መከራከሪያ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

7. ከላይ ከተገለፀው በተጨማሪ መኪኖቹ በአደጋው ሙሉ በሙሉ ወደመው ከአገልግሎት ውጭ በመሆናቸው ምክንያት፣ ተጠሪ ለመኪኖቹ የመድን ሽፋን  ከሰጠው የኢንሹራንስ ድርጅት፣ የመኪኖቹ የሚከፈለውን የመድን ገንዘብ የተቀበለ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ለመኪኖቹ የመድን ሽፋን የሰጠው ድርጅት መኪኖቹ ሶስት ዓመት ከስምንት ወር አገልግሎት ከሰጡ በኂላ በአደጋ ምክንያት ከጥቅም ውጭ በመሆናቸው ምክንያት ለተጠሪ የከፈለው ገንዘብ፣ አመልካች ተጠሪ እንዲከፍለው በክሱ ከጠየቀው ገንዘብ ያነሰ መሆኑን በማንሣት ተጠሪ ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ በአንፃሩ ተጠሪ የኢንሹራንስ  ድርጅቱ ለመኪኖቹ የከፈለው ምን ያህል እንደሆነ ለሥር ፍርድ ቤትም ሆነ ለይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ባቀረበው ክርክር አልገለፀም፡፡ ተጠሪ የኢንሹራንስ ድርጅቱ ለመኪኖቹ የከፈለው አመልካች በክሱ ከጠየቀው ገንዘብ በታች መሆኑን እስካላስረዳና በተቃራኒው ከኢንሹራንስ ድርጅቱ የተከፈለውን ገንዘብ ለመግለፅ ፈቃደኛ ካልሆነ፡ ተጠሪ መኪኖቹ ላይ በደረሰው አደጋ ከኢንሹራንስ ድርጅቱ የተከፈለው ገንዘብ አመልካች በክሱ ከጠየቀው ገንዘብ ያልተናነሰ ወይም ከዚህ በላይ ነው የሚለውን የህሊና ግምት ለመያዝ የሚያስችል ነው፡፡

8. ሶስት ዓመት ከስምንት ወራት ካላገለገሉ በኂላ የመገልበጥ አደጋ ደርሶባቸው ከአገልግሎት ውጭ የሆኑት መኪኖች፣ በወቅቱ የነበራቸው የገበያ ዋጋና፣የቅሪት ዋጋቸው ምን ያህል እንደሆነ የሥር ፍርድ ቤት ገለልተኛ ባለሙያ መድቦ አሰርቷል፡፡ የተመደበው ባለሙያ የመኪኖቹን ዋጋ የገመተው መኪኖቹ ከፋብሪካ ተመርተው እንደመጡ አዲስ መኪኖች

በማድረግ ሣይሆን መኪኖቹ ሶስት ዓመት ከሥምንት ወራትአገልግለው በሚኖራቸው ይዞታ፣ መኪኖቹ ሶስት ዓመት ከሥምንት ወር አገልግሎት ሰጥተው የሚያወጡትን ዋጋመሠረት በማድረግ እንደሆነ ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔና አመልካችካቀረበው ክርክር ተረድተናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ገለልተኛ የንብረት ገማች የሆነው ባለሙያ ያቀረበውን የመኪኖች ዋጋ ግምት ተጠሪ የሌላ የባለሙያ ግምት ወይም የተሻለ ዕውቀትናክህሎት ያለው ባለሙያ የሙያ ምስክርነት እንዲሰጥ በማድረግ አላስተባበለም፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ባለሙያው መኪኖቹ የሰጡትን አገልግሎት ከግንዛቤ ውስጥ ሣያስገባ የመኪኖቹን ግምት ሠርቶ እንዳቀረበ አድርጎ በመውሰድ ጉዳዩ እንደና በባለሙያ ይገመት በማለት የሰጠው ውሣኔ የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 136/1/ እና የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343/1/ ድንጋጌዎች መሠረታዊ ዓላማ ያላገናዘበና የሥር ፍርድ ቤት በጭብጥነት ይዞ ያላጣራው ምንም አይነት ፍሬ ጉዳይ ሣይኖረው ያለበቂና ህጋዊ ምክንያት የተጣራውን ፍሬ ነገር በድጋሚ እንዲያጣራ የሰጠውና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ውሣኔ ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍታብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 120329 የካቲት 22 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በድምፅ ብልጫ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 138747 የሰጠው ውሣኔ በድምፅ ብልጫ ፀንቷል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት የወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

**መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## የልዩነት ሐሳብ

ስሜ በተራ ቁጥር ሁለት የተመዘገብኩት ዳኛ የሥራ ባልደረቦቼ በሰጡት ውሣኔ ላይ ሥነ ሥርዓታዊ በሆነ ጉዳይ ባለመስማማት የልዩነት ሐሳቤዬን እንደሚከተለው አስፍሬለሁ፡፡

ከክርክሩሂደት መገንዘብ እንደሚቻለው አመልካች እና ተጠሪ በሚከራከሩበ የተሽርካሪዎች ዋጋ ክፍያ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊከፍል ይገባል ያለው መጠን ለይቶ የወሰነ ቢሆንም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተሽከርካሪዎች በገበያ ላይ የሚኖራቸው ዋጋ በገለልተኛ ገማች ተጠንቶና ተገምቶ

እንዲቀርብ በደድረና ሊከፈል የሚገባው የገንዘብ መጠን ይወሰን ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1/ መሰረት ለስር ፍርድ ቤት መልሶታል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ፍሬ ነገሩ ከመታየቱ በፊት ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ብቁ መሆን አለመሆኑን መታየት ነበረበት፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው የሥር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩ በነጥብ የመለሰው በመሆኑ ጉዳዩ  የመጨረሻ ውሣኔ አግኝቷል ለማለት አይችልም፡፡ በእርግጥ የሰበር ሰሚ ችሎቱ እንደመጨረሻ ውሣኔ  በሚታዩ ትእዛዞች ላይ መዝገቦችን እየመረመረ ውሣኔ የሰጠበት ሁኔታ ያለ ስለመሆኑ የሚያከራክር ጉዳይ ቢሆንም በተያዘው ጉዳዩ ግን ሊጣሩ የሚገባቸው ነጥቦች ተለይተው ለሥር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተመለሰ በመሆኑ የሥር ፍርድ ቤቶች አጣርተው የሚሰጡት ውሣኔ ሳይታወቅ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ብቁ ነው ተብሎ መቅረቡ የኢፌዲሪ  ሕገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ /ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10/2/ ድንጋጌዎች መሠረታዊ ይዘትና መንፈስ ያገናዘበ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መግንስት አንቀጽ 80/3//ሀ/ እና አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ አንድ ጉዳይ ለዚህ ችሎት ብቁ የሚሆነው መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት የመጨረሻ ውሣኔ /any final court decisions/ መስጠቱ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የይግባኝ ሂደቱን ያጠናቀቀ ጉዳይ ለሰበር መቅረቡ እንዲሁም ይህ ችሎትም ለሥር ፍርድ ቤት በነጥብ የተመለሰው ጉዳይ ተመልክቶ መወሰኑ ከላይ የተጠቀሱትን የኢፌዲሪ ሕገ መንግስትና አዋጅ ቁጥር 25/88 የላገናዘበ በመሆኑ ጉዳዩ ለሰበር ብቁ አይደለም ተብሎ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት በሐሳብ ተለይቻለው፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

የሰ/መ/ቁ.102668

ሰኔ 12 ቀን 2009 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ዓሊ መሃመድ

ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ

ቀነአ ቂጣታ

ፀሃይ መንክር

**አመልካች/ዎች/፡-** 1. ማክሲመም ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ወኪል አንዋር አሊ ቀረቡ

2. አቶ መሊክ ዓሊ አልቀረቡም

**ተጠሪ-፡** የደቡብ ብሔር ብሔረሰብና ህዝቦች ክልል የሆሳዕና ከተማ የቤቶች ልማት ፕሮጀክት ጽ/ቤት

አልቀረበም

በዚህ መዝገብ አመልካችዎችና ተጠሪ ያቀረቡትን ክርክር፣ አንደኛ አመልካችና ተጠሪ በመዝገብ ቁጥር 95733 ካቀረቡት ክርክር ጋር በማጣመር በፍ/ስ/ስ/ህግ/ቁ/11/4/ መሰረት በማጣመር መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

1. ጉዳዩ የቀረበው የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ተጠሪ በሁለተኛው አመልካች ላይ ያቀረበው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በመቀበል አከራክረው ውሳኔ መስጠታቸውና አንደኛ አመልካች ህንፃን በጊዜዊነት ሲያስረክብ፣ የአንደኛ አመልች ወኪል ፣ አንደኛ አመልካች ዕዳ ያለበት መሆኑን በማመን የእዳ መተማመኛ ሰነድ ፈርሟል በማለት አንደኛ አመልካች ተጠሪ በተከሳሽነት ከሳሽነት ክሱ የጠየቀውን ገንዘብ እንዲከፍል የሰጡት ውሳኔ ህጋዊ መሰረት ያለው መሆኑን በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ፍርድ ቤት አንደኛ አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በአመልካችዎች ላይ አቅርቦ፣ አንደኛና ሁለተኛ አመልካችዎች ስማቸው በከሳሽ ተከሳሽነት ተመዝግቦ ጉዳያቸው ታይቷል፡፡ ከዚህ መዝገብ ጋር በተጣመረው በሰበር መዝገብ ቁጥር 95733፣ ያቀረበው ጉዳይ በመጀመሪያ የታየው በሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትሲሆን፣ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ ከሳሽ በዚህ ክርክር ተሳታፊ ያልሆነው ህብረት ኢንሹራስ አ.ማ ተከሳሽ አንደኛ አመልካች ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

2. በዚህ መዝገብ ለተያዘው ጉዳይ ክርክር መነሻ የሆነው አንደኛ አመልካች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው የክስ ማመልከቻ ነው፡፡ አንደኛ አመልካች ተጠሪ ከሚያሰራቸው ኮንደሚኒየም ቤቶች አምስት ኮንደሚኒየም ቤቶችን በብር 1,862,626.74 /አንደ ሚሊዮን ስምንት መቶ ስልሳ ሁለት ሺኅ ስድስት መቶ ሃያ ስድስት ብር ከሰባ አራት ሳንቲም/ ከሳሽ ለተከሳሽ ሰርቼ ላስረክብ ውል ተዋውያለሁ፡፡ በውላችን መሰረት፣ ከሳሽ ሶስት ኮንደሚኒየም ቤቶችን ስራ ሙሉ በሙሉ አጠናቅቄ አስረክቤአለሁ፡፡ ሁለት የኮንደሚኒየም ቤቶች ተከሳሽ አለባቸው የሚለውን የግንባታ ጉድለት አስተካክዬ ለማስረከብ ከሳሽ ጥያቄ ባቀርብም ተከሳሽ ባለመፈቀዱ፣ በሁለቱ ቤቶች ላይ አለ የተባለውን ጉድለት ለማስተካከል የሚሆን ገንዘብ አስቀርቶ ሌላውን ክፍያ እንዲከፍለኝ ብጠይቀው ተከሳሽ ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ስለዚህ የሁለት ህንፃ የጉድለት ማስተካኪያ ወጭ በመቀነስ፣ ለሰራሁት ጠቅላላ ስራ ተከሳሽ ብር 1,018,898 /አንድ ሚሊዮን አስራ ስምንት ሺህ ስምንት መቶ ዘጠና ስምንት ብር/ መክፈል ሲገባው ያልከፈለኝ በመሆኑ እንዲከፍል ውሳኔ ይሰጥልኝ የሚል ይዘት ያለው ክስ አቅርቧል፡፡

3. ተጠሪ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተከሳሽነት ቀርቦ፣ ህንፃዎቹ ሲገነቡ ለህንጻዎች ግንባታ የሚያገለግሉት የግንባታ ማቴሪያሎች ያቀረበው ተከሳሽ ነው፡፡ በዚህ መሰረት ከሳሽ ከሰሪው ስራ ላይ ግንባታ ማቴሪያል ዋጋ ተከሳሽ ቀንሶ የማስቀረት መብት አለው፡፡ በዚህ መሰረት የአምስቱ ኮንዶሚኒየም ቤቶች ጠቅላላ ዋጋ ከሳሽ በክስ ማመልከቻው ላይ የገለጸው ሲሆን፣ ከሳሽ በቅድመ ክፍያነት ብር 323934.90 /ሶስት መቶ ሃያ ሶስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰላሳ አራት ብር ከዘጠና ሳንቲም/ ወስዷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከሳሽ የመጀመሪያ ዙር ክፍያ ብር 157,109.07 /አንድ መቶ ሃምሳ ሰባ ሺኅ አንድ መቶ ዘጠኝ ብር ከዜሮ ሰባት ሳንቲም/ ተከፍሎታል፡፡ ከሳሹ በአጠቃላይ ብር 481,043.97/አራት መቶ ሰማንያ አንድ ሺህ አርባ ሶስት ብር ከዘጠና ሰባት ሳንቲም/ ተከፍሎታል፡፡ ከሳሽ ከሰራቸው አምስት ህንፃዎች ውስጥ ሁለቱ ለሰው መኖሪያነት ሊያገለግሉ እንደማይችሉ በአማካሪ መሀንዲስና በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የምድህስና የትምህርት ክፍል ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም ከሳሽ ለተከሳሽ የሚከፈለውና የሚመልሰው ሂሳብ ያለበት መሆኑን በማረጋገጥ መተማመኛ የሰጠ በመሆኑ ተከሳሽ ገንዘብ እንድከፍለው የቀረበው ክስ የህግ ድጋፍ የሌለውና በማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

4. የስር ተከሳሽ የሆነው ተጠሪ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርቧል፡፡ የተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ ይዘት ከሳሽ ለህንፃዎቹ ግንባታ ከተከሳሽ የተረከበውን በቀድመው ዋጋው ብር 370,666.87 /ሶስት መቶ ሰባ ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት ብር ከሰማኒያ ሰባት ሳንቲም/ አሁን ባለው ሆሳዕና ከተማ ውስጥ ባለው የገባያ ዋጋ ብር 1,195,231.55/አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ዘጠና አምስት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ አንድ ብር ከሃምሳ አምስት ሳንቲም/ ለህንፃ ግንባታ ሳይሆን ለግል ጥቅሙ ያዋለ ለመሆኑ አሁን ባለው

የገበያ ዋጋ ሊከፍል ይገባዋል፡፡ በመጀመሪያ ዙር ከተከፈለ ገንዘብ ተመላሽ ሊደርግ የሚገባው ብር 137,147 አንድ መቶ ሰላሳ ሰባት ሺህ አንድ መቶ አርባ ሰባት ብር/ እንዲመለስና በሁለቱ የተበላሹ ህንፃዎች ሊከፍል የሚገባው መቀጫ ብር 75,808.81 /ሰባ አምስት ሺህ ስምንት መቶ ስምንት ብር ከሰማኒያ አንድ ሳንቲም በድምሩ ብር 1,590,187.37 /አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ዘጠና ሺህ አንድ መቶ ሰማኒያ ሰባት ብር ከሰላሳ ሰባት ሳንቲም/ ከሳሽና የተከሳሽ ስራ አስኪያጅ አቶ መልክ ዓሊ /ሁለተኛ አመልካች በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

5. ሁለተኛ ተጠሪ በተከሳሽ ላይ ያቀረብኩት ክስ ስሌለ እኔን ተከሳሽነት ከሳሽነት ባቀረበው ክስ ገንዘብ በአንድነትና በነጠላ ያቀረበው ክስ ስነ ስርዓታዊ አይደለም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ የተከሳሽ ከሳሽ የከሳሽ ተከሳሽና አቶ መልክ ዓሊ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉት በተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ ያቀረበው ገንዘብ የህግ መሰረት የሌለው ነው፡፡ ከሳሽ ከተከሳሽ የሚጠይቀው ቀሪ ሒሳብ ያለበት ሆኖ እያለ፣ እንደገና ገንዘብ ሊከፍሉኝ ይገባል በማለት ያቀረበው ክስ የህግ ድጋፍ የሌለውና በማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ ውድቅ ይደረግልኝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና የሰነድ ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ከሳሽ /አንደኛ አመልካችና/ ተከሳሽ /ተጠሪ/ የአምስቱን ህንፃዎች እርክክብ ሲፈጽሙ፣ ከሳሽ በተከሳሽ የሚከፍለው ብር 406,446.49 /አራት መቶ ስድስት ሺህ አራት መቶ አርባ ስድስት ብር ከአርባ ዘጠኝ ሳንቲም/ ያለበት መሆኑን በመግለጽ የዕዳ መተማመኛ ፈርሞና በመሀተም አረጋግጦ ሰጥቷል፡፡ ይህም ከሳሽ በተከሳሽ ላይ ያቀረበው የክፍያ ጥያቄ ተገቢነት የሌለው መሆኑን ስለሚያረጋግጥ፣ ከሳሽ ያቀረበውን ክስ ሙሉ በሙሉ ውድቅ አድርጌዋለሁ፡፡ በአንፃር ተከሳሽ በተከሳሽ ከሳሽነት ከጠየቀው ገንዘብ ውስጥ ብር 406,446.49 /አራት መቶ ስድስት ሺህ አራት መቶ አርባ ስድስት ብር ከአርባ ዘጠኝ ሳንቲም/ እና የመቀጫ ገንዘብ ብር 257,808.81 /ሁለት መቶ ሀምሳ ሰባት ሺህ ስምንት መቶ ስምንት ብር ከሰማኒያ አንድ ሳንቲም በድምሩ ብር 664,255.30 /ስድስት መቶ ስልሳ አራት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ አምስት ብር ከሰላሳ ሳንቲም/ ከሳሽና አቶ መለክ ዓሊ በአንድነትና በነጠላ ለተከሳሽ ይክፈሉ በማለት በመዝገብ ቁጥር 111544 ግንቦት 7 ቀን 2006 ዓ/ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካችዎች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 101881 ሰኔ 25 ቀን 2006 ዓ/ም በሰጠው ትዕዛዝ የአመልካችዎችን በፍ/ስ/ስ/ህግ/ቁ/ 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

6. በሰበር መዝገብ ቁጥር 95733 መነሻ የሆነውን ክስ ለሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ተጠሪ ነው፡፡ ተጠሪ ለሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 09656 ባቀረበው ክስ ከአንደኛ አመልካች አምስት የኮንዶሚኒየም ቤቶች ሰርቶ የማስረከብ ከከሳሽ ጋር የህንፃ ስራ

ውል ሲዋዋል ተከሳሽ ህብረት ኢንሹራንስ /አ.ማ/ እስከ ብር 182,262.64 /አንድ መቶ ሰማኒያ ሁለት ሺ ሁለት መቶ ስልሳ ሁለት ብር ከስልሳ አራት ሳንቲም/ የመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና ሰጥቷል፡፡ የስራ ተቋራጩ ስራውን በተሟላ ሁኔታ ያላስረከበ በመሆኑ ተከሳሽ ዋስትና የሰጠበትን ገንዘብ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተከሳሽ የነበረው ህብረት ኢንሹራንስ /አ.ማ/ ክስ ያቀረበበትን የዋስትና ገንዘብ የማይከፍልበትን ምክንያት ዘርዝሮ ተከራክሯል፡፡ አንደኛ አመልካች ጣልቃ ገብቶ፣ በህንጻዎቹ ግንባታ ላይ ጉድለት የሌለ በመሆኑ የከሳሽ ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ የሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኂላ የስራ ተቋራጭ /ጣልቃ ገብ/ ከሰራቸው አምስት ህንጻዎች ውስጥ ሁለቱ ህንጻዎች ጉድለት ያለባቸው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ ተከሳሽ ዋስትና የሰጠበትን ብር 182,262.24 /አንድ መቶ ሰማኒያ ሁለት ሺ ሁለት መቶ ስልሳ ሁለት ብር ከሃያ አራት ሳንቲም / ለከሳሽ ሊከፍል ይገባል በማለት በመዝገብ ቁጥር 09656 ሰኔ 7 ቀን 2005 ዓ.ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አንደኛ አመልካች ይህንን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 01945 ህዳር 12 ቀን 2006 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ የአመልካችን የይግባኝ ቅሬታ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

7. አመልካች በሰበር መዝገብ ቁጥር 95733 የሆሳዕና ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሳኔ በመቃወም ታህሳስ 8 ቀን 2006 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ አመልካች ከተጠሪ የምጠይቀው ቀሪ ክፍያ ያለኝ መሆኔን ገልጬ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ክስ አቅርቤአለሁ፡፡ የተሰሩት ቤቶች ጉድለት አለባቸው ወይም የለባቸውም የሚለው ጭብጥ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ታይቶ ከመወሰኑ በፊት፣ የሀዲያ ዞን የሕንጻው ግንባታ ጉድለት ያለበት ነው በማለት ለመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና ከሕብረት ኢንሹራንስ /አ.ማ/ የተያዘው ገንዘብ ለተጠሪ እንዲከፍል መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው የሚል የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ ጥር 16 ቀን 2006 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ አመልካች ባቀረበው የሰበር አቤቱታ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን የአንደኛ አመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚልበትን ምክንያት በመዘርዘር መልስ ሰጥቷል፡፡ ጉዳዩ ለዚህ ሰበር ችሎት ሲቀርብ የተያዘው ጭብጥ የሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አንደኛ አመልካች የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 8 በመጥቀስ ያቀረበው መቃወሚያ የማለፋቸው አግባብነት በሰበር አጣርቶ ለመወሰን የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ በሰበር መዝገብ ቁጥር 102668 /በዚህ መዝገብ የቀረበው አቤቱታ ያስቀርባል የሚባል ቢሆን ለመጠባበቅ በሚል ከመጋቢት 29 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ቀነ ቀጠሮ ሲለወጥ ቆይቶ፣ ጥቅምት 2 ቀን 2008 ዓ.ም በመዝገብ ቁጥር 95733 ያቀረበው የሰበር አቤቱታ ግራቀኙ

ያደረጉት ክርክር ከዚህ መዝገብ ጋር ተጣምሮ እንዲታይ ትእዛዝ የተሰጠበት በመሆኑ ከዚህ መዝገብ ጋር ተጣምሮ ታይቷል፡፡

8. በዚህ መዝገብ ማለትም በሰበር መዝገብ ቁጥር 102668 አመልካችዎች ሐምሌ 2 ቀን 2006 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡትን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካችዎች በጋራ ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ሁለተኛ አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረበው ክስ የለም፡፡ ተጠሪ ክስ ያላቀረበበት ሁለተኛ አመልካችን በመጨመር ያቀረበውን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ከሕግ አግባብ ውጭ ተቀብለው የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሳኔ የሕግ መሰረት የሌለው በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባዋል፡፡ የህንጻዎቹ ጊዜዊ እርክብክብ ሲፈጸም ሁለቱ የኮንዶሚኒየም ቤቶች ሙሉ ለሙሉ እንዲፈርሱ አንደኛ አመልካች እንደተስማማ፣ አንደኛ አመልካች ለተጠሪ ብር 406,446.59 /አራት መቶ ስድስት ሺ አራት መቶ አርባ ስድስት ብር ከሃምሳ ዘጠኝ ሳንቲም/ እንዳለበት የዕዳ መተማመኛ ፈርሞ ሰጥቷል የተባለው ሰው ይህንን ለማድረግ የውክልና ስልጣን የሌለው መሆኑን ገልጸን ተከራክረን እያለን የስር ፍ/ቤት ፣ ለጉዳዩ የማይመለከተው ሰው የፈረመውን ፊርማ ሰነድ መሰረት በማድረግ የአንደኛ አመልካች ክስ ሙሉ በሙሉ ውድቅ በማድረግና የተጠሪን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በመቀበል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የስር ፍ/ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካችዎች የመቀጫ ገንዘብ እንዲከፍል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡

9. ተጠሪ ታህሳስ 16 ቀን 2007 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ 2ኛ አመልካች የአንደኛ አመልካች ስራ አስኪያጅ በመሆኑና አንደኛ አመልካች ለፈጸመው ጉድለትና ጥፋት በንግድ ሕጉ መሰረት ሃላፊነት ስላለበት፣ በአንድነትና በነጠላ ተጠያቂ እንዲሆን መወሰኑ ተገቢ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ የውክልና ስልጣን በተመለከተ አዲስ ያቀረበ የፍሬ ጉዳይ ክርክር ነው ከዚያም በኋላ አንደኛ አመልካች ያደረጋቸው መጻጻፎች ስላሉ የአመልካችዎች ክርክር ውድቅ ይደረግልኝ በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ በግራቀኙ በኩል የሁለቱም የሰበር መዛግብት ማለትም በዚህ መዝገብና በሰበር መዝገብ ቁጥር 95733 ግራቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ በአጭሩ የተገለጸው ሲሆን በትክክለኛ ፍርድ አሰጣጥ ይረዳን ዘንድ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የመዝገብ ቁጥር 111544 ቀርቦ ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዝ ተደርጓል፡፡

10. ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሁለቱ የሰበር መዛግብት ግራቀኙ ያቀረቡት የጽሑፍ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር በተጠሪ ላይ ክስ ያቀረበው አንደኛው አመልካች ነው፡፡ ተጠሪ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ሲያቀርብ፣ በተጠሪ ላይ ክስ ያላቀረበውን ሁለተኛውን አመልካች በተከሳሽ ተከሳሽነት በመጨመር ክስ የቀረበ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ የከሳሽ ተከሳሽ ከሳሽነት

ክስ ሊያቀርብ የሚችለው በከሳሽ ላይ እንደሆነና፣ ተከሳሽ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ሊያቀርብ በፍታብሔር ስነ-ስርዓት ሕግ ቁጥር 224 የተገለጸውን ስርዓት መከተል ያለበት መሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁ. 234 ንዑስ አንቀጽ 1/ረ/ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ተከሳሹ ሲያቀርብ የፍርድ ቤቱ ስልጣን እንዴት እንደሚወሰን በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 30 ተደንግጓል፡፡ ተጠሪ በከሳሽነት ያልተሳተፈ ሶስተኛ ወገን /ሁለተኛ አመልካች/ ከአንደኛ አመልካች ጋር አጣምሮ ክስ ለማቅረብ ከፈለገ፣ በፍታብሔር ስነ-ስርዓት ሕግ ቁጥር 36 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት አንደኛ አመልካችንና ሁለተኛ አመልካችን አጣምሮ በአዲስ መዝገብ በመክሰስ መዝገቡ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁ. 11/1/ አንደኛ አመልካች ካቀረበው ክስ ጋር ተጣምሮ እንዲታይለት ከሚያመለክት በስተቀር፣ በተጠሪ ላይ ክስ ያላቀረበውን ሁለተኛ አመልካችን በተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ውስጥ ስሙን መዝግቦና ጨምሮ ማቅረቡ፣ ከላይ የተጠቀሱትን የሕግ ድንጋጌዎች ያልተከተለ ሆኖ እያለ፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ በሕግ ከተደነገገው ስርዓት ውጭ ሁለተኛው አመልካች ላይ ያቀረበውን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ተቀብለው ውሳኔ መስጠታቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

11. ሁለተኛ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ለውሳኔው መሰረት ያደረገው መስከረም 21 ቀን 2004 ዓ.ም የተደረገው የጊዜዊ እርክብክብ ቅጽ ላይ አንደኛ አመልካች ለተጠሪ የሚመልሰው ብር 406,446.49 /አራት መቶ ስድስት ሺ አራት መቶ አርባ ስድስት ብር ከዜሮ አርባ ዘጠኝ ሳንቲም/ እዳ ያለበት መሆኑን ያሚገልጽ ሰነድ ነው ፡፡ አመልካች ይህ በጊዜዊ እርክብክብ ቅጹ ላይ የተገለጸው የሒሳብ ስሌት ትክክል አለመሆኑን በመግለጽ አንደኛ አመልካች ሙሉ በሙሉ ሰርቶ ለስራ ከባቻው ሶስት ህንጻዎች መክፈል የሚገባውን ክፍያ ያልከፈለ መሆኑን፣ በመግልጽ የተከራከር ሲሆን ይህንኑ በተመለከተ ያስረዱልኛል የሚላቸውን የሰነድ ማስረጃዎች በማስረጃነት ያቀረበ መሆኑን፣ አንደኛ አመልካችና ተጠሪ በቃል በጽሁፍ ካደረጉት ክርክር ተረድተናል፡፡ ይህንንም ክርክር መነሻ በማድረግ የተለያዩ የሙያ አስተያየቶች ከተለያዩ መስራያ ቤቶች የተሰጡ መሆኑን ተረድተናል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ መስከረም 22 ቀን 2004 ዓ/ም በተዋለው ጊዜዊ የእርክብክብ ቅጽ ላይ ያስፈሩትን የሒሳብ ስሌቶ በማስረጃነት የሚጠቀም ከሆነ፣ የጊዜዊ የእርክብክብ ቅጽ ላይ የሰፈሩ ፍሬ ነገሮች አገልግሎት የሚስጡት ሙሉ እርክብክብ እስኪፈጸምና የመጨረሻው ሒሳብ ተሰርቶ ውጤቱ እስኪታወቅ ድረስ ብቻ ነው ወይስ አይደለም? ጊዜዊ እርክብክብ ቅጹ ላይ የተገለጸው የሒሳብ ስሌት በስራ ተቋራጩና በአሰሪው መካከል የሚፈለገውን ክፍያና ሒሳብ ለማስረዳት የሚችላ ሰነድ ነው ከተባለ፣ የዕዳው መታማመኛ የተፈርመው አመልካችን ወክሎ የዕዳ መተማመኛ የመፈርም ስልጣን ባለው ሰው ነው ወይስ አይደለም? የሚሉትን ነጥቦች በጭብጥነት ይዞ ማጣራት ነበረበት፡፡ በዚህ ቅጽ ላይ የፈረመው ሰው ማንነቱ ያልተገለጸ

ወይም ስሙን ያልተጻፈ ሲሆን ተጠሪ ጊዜዊ እርክብክብ ቅጹ የተፈርመው በአንደኛ አመልካች ስራ እስኪያጅ ነው የሚል ክርክር በስር ፍርድ ቤትና ለዚህ ሰበር ችሎት በቀረበው ክርክር አላቀረበም፡፡

11. ሰነዱ አመልካች ስራ አስኪያጅ በወከለው ሰው የተፈርመ ነው የሚል ክርክር ቀርቧል፡፡ የአንደኛ አመልካች ስራ አስከያጅ ወርቅነህ አብዩ ህዳር 24 ቀን 2003 የሰጡት የውክልና ሰነድ ተወካዩ በኩንባያው ስም የዕዳ መተማመኛ እንዲፈርም ስልጣን የማይሰጠው መሆኑን በትዕዛዝ ከቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገብ ለመረዳት ችለናል፡፡ ኩባንያውን ወክሎ የዕዳ መተማመኛ ለመፈርም የውክልና ስልጣን በሌለው ሰው የተፈረው የዕዳ መተማመኛ ሰነድ መነሻ የስር ፍርድ ቤት አንደኛ  አመልካች ያቀረበውን ክስ ሙሉ በሙሉ ውድቅ ማድርጉና በተጠሪን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ተቀብሎ ውሳኔ መስጠቱ ህጋዊ መሰረት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በዚህ ምክንያት የስር ፍርድ ቤት የፍታብሔር ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 136(1) መሰረት ባለሙያዎችን በመመደብ፤

(ሀ) አንደኛ አመልካች በውሉ መሰረት ሰርቶ ላስረከባቸው ሶስት የኮንደሚኒየም ህንጻዎች ግንባታ ተጠሪ መክፈል የሚገባው ጠቅላላ ክፍያና አንደኛ ተጠሪ ለአመልካች መመለስ የሚገባው የግንባታ የማቴሪያል ዋጋ ምን ያህል ነው፡፡

(ለ) ጉድለት አለባቸው የተባሉት ሁለት ህንጻዎች ላይ ያሉ ሁሉም ኮለኖችና የመሬት ውስጥ ስራዎች ሙሉ በሙሉ ፈራሽ ይሆናሉ አይሆኑም? አንደኛ አመልካች ከመሬት በታችና መሰረቱን ለማውጣት ለሁለቱ ህንጻዎች የሰራው ስራ ግምትና፣ ህንጻዎቹን በመስራት የወሰደው የማቴሪያል ግምት ምን ያህል እንደሆነ ተመዝኖ እንዲመጣ በማድረግና፣ ሁለቱ ህንጻዎች ላይ ለታየው ጉድለት ተጠሪ ሊጠይቅ የሚችለው የጉዳት ካሳ ነው ወይስ የመቀጫ ገንዘብ የሚለውን፣ በማመዛዘን የአንደኛ አመልካችን ክስና የተጠሪን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ መወሰን ሲገባው መስከረም 22 ቀን 2004 ዓ/ም በተምላው የጊዜዊ ዕርክብክብ ቅጽ ላይ ብቻ በመመስረት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

12. ሶስተኛው በሰበር መዝገብ ቁጥር 95733 የተያዘው ጭብጥ የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ በሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ ያቀረበው ለመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና በሰጠው በህብረት ኢንሹራንስ (አ.ማ) ላይ ነው፡፡ የመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና የሰጠው የኢንሹራንስ ድርጅት አንደኛ አመልካች ሊያነሳቸው የሚችላቸውን መከራከሪያዎች ሁሉ በማንሳት ለመከራከር የሚችል መሆኑ በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1926 ንዑስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንጻር ተጠሪ ለመልካም ስራ አፈጻጸም ዋስትና የሰጠውን የኢንሹራንስ ድርጅት

በሰጠው የዋስትና ግዴታ መሰረት እንድፈጽምለት በሀዲያ ዞን ክስ ያቀረበው ዋስትና ቦንድ የሰጠውን ድርጅት ዋስትና የገባቢትን ገንዘብ እንዲከፍል ለመጠየቅ በመሆኑ አንደኛ አመልካች የፍ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 8 በመጥቀስ ያቀረበውን መቃወሚያ የበታች ፍርድ ቤቶች ማለፋቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

13. አንደኛ አመልካች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ ሲያቀርብ ከሰራቸው አምስት ህንጻዎች ውስጥ ሁለቱ ጉድለት ያለባቸው መሆኑንና የሁለቱን ጉድለት ለማስተካከል የሚያስፈልገውን ገንዘብ ገምት አቅርቧል፡፡ የአንደኛ አመልካች የስራ አፈጻጸም ዋስትና የሰጠው ህብረት ኢንሹራንስ (አ.ማ) ለተጠሪ እንዲከፍል የተወሰነበት ብር 186,262.62 /አንድ መቶ ሰማኒያ ስድስት ሺ ሁለት መቶ ስልሳ ሁለት ብር ከስልሳ ሁለት ሳንቲም/ የአንደኛ አመልካች የተጠሪ ሒሳብ ተሰርቶ አንደኛ አመልካች ለተጠሪ የሚከፍለው ዕዳ ካለ፣ ከአንደኛ አመልካች ዕዳ ላይ ሊቀነስ የሚገባው በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት በዚህ ፍርድ ተራ ቁጥር 11 የተያዙትን ጭብጦች ካጣራ በኋላ ሊከተለው የሚገባ የክርክር አመራር ነው፡፡ ከዚህ ውጭ የሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጠሪ ለአንደኛ አመልካች የስራ አፈጻጸም ዋስትና ቦንድ በሰጠው የኢንሹራንስ ድርጅት ላይ ያቀረበውን ክስ ተቀበለው የሰጡት ውሳኔ የፍ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 8 ድንጋጌን የማይጥስና መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

14. ከላይ በዝርዝር በገለጽናቸው ምክንያቶች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አንደኛ አመልካች ያቀረበውን ክስ ሙሉ በሙሉ ውድቅ በማድረግና የተጠሪን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በመቀበል የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 111544 ግንቦት 7 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 101881 ሰኔ 25 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ ፍርድ በተራ ቁጥር 11 የተያዙትን ጭብጦች በገለልተኛ ባለሙያዎች ተጣርተው እንዲቀርቡለት በፍ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 136(1) መሰረት ትዕዛዝ በመስጠትና ዕውነቱን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ማስረጃዎችን በማስቀረብ ወይም ምስክሮችን በመስማት የአንደኛ አመልካች ክስና የተጠሪን የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ላይ ላቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 343(1) መሰረት መልስን ልከንለታል፡፡

3. ሁለተኛ አመልካች ላይ ተጠሪ ያቀረበው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ፣ በህጉ ከተደነገገው ስርዓት ውጭ የቀረ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስነናል፡፡
4. የሀዲያ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 09656 ሰኔ 7 ቀን 2005 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔና የደቡብ ብሔርብሔረሰቦችና ህዝቦች ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 01945 ህዳር 12 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
5. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአንደኛ አመልካችንና ተጠሪ አከራክሮ ውሳኔ ሲሰጥ፣ ለአንደኛ አመልካች የስራ አፈጻጸም ዋስትና የሰጠው ህብረት ኢንሹራንስ (አ.ማ) ለተጠሪ እንዲከፍል በፍርድ የተወሰነበትን ገንዘብ ከግምት ውስጥ በማስገባት የሂሳብ ስሌቱ እንዲሰራ በማድረግ ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባዋል በማለት ወስነናል፡፡
6. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለራሳቸው ይቻሉ፡፡
7. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ከሰበር መዝገብ ቁጥር 95733 ጋር ይያያዝ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ተ

የሰ/መ/ቁ.132208

ሰኔ 28 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ጸጋዬ አስማማው

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ አርሺሶ

ሠናይት አድነው

አመልካች፡- ወ/ሮ ጸሀይ አጎናፍር ቀረቡ

ተጠሪ ፡-አቶ ጌራ ላቀው አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ሀብት ክርክርን ይመለከታል የአሁን ተጠሪ የስር አመልካች ሆነው ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ወላጅ አባቴ ኮ/ል ላቀው ወ/ሰንበት ከቤት ወጥቶ ሳይመለስ በመቅረቱ ሚያዚያ 21 ቀን 2007ዓ.ም የመጥፋት ውሳኔ አሰጥቼ ወራሽነቴን አረጋግጫለሁ በመሆኑም የሟች አባቴን የውርስ ሀብት የውርስ አጣሪ ተሹሞ ይጣራልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል ፡፡

ፍ/ቤቱም የውርስ አጣሪ በመሾም የሟች የውርስ ሀብት ተጣርቶ እንዲቀርብ ትእዛዝ ሰጥቷል ውርስ አጣሪው በትእዛዙ መሰረት ኮ/ል ላቀው ወ/ሰንበት ከ10/7/2007ዓ፣ም ጀምሮ ያሉበት ሁኔታ ባለመታወቁ ከሚያዚያ 20/2007ዓ.ም ጀምሮ የመጥፋት ውሳኔ የተሰጠ መሆኑን፣ ኮ/ል ላቀው አመልካችን ብቻ የወለዱ መሆናቸውን፣ ኮ/ል ላቀው ከስር አመልካች እናት ጋር ከተለያዩ በኋላ የአሁን አመልካች ወ/ሮ ፀሀይ አጎናፍርን አግብተው መኖራቸውንና ልጅ ያለመውለዳቸውን፣ ኮ/ል ላቀው ከአሁን አመልካች ወ/ሮ ፀሀይ ጋር በባልና ሚስትነት ሲኖሩ በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 የቤት ቁጥር 2489 የሆነ ቤት ማፍራታቸውን ቤቱ በአሁን አመልካች እጅ የሚገኝ መሆኑን ሲያጣራ የስር አመልካች የክርክሩ ቤት በወላጅ አባታቸው እና በአሁን አመልካች በጋራ የተፈራ መሆኑን በመግለጻቸው ውርስ አጣሪው የአሁን አመልካች

በጉዳዩ ጣልቃ ገብተው እንዲከራከሩ በሰጠው ትእዛዝ መሰረት የአሁን አመልካች የክርክሩን ቤት ከኮ/ል ላቀው ጋር በጋብቻ እያለን 70% ቢሰራም 30% ግን እሳቸው ከቤት ከወጡ በኋላ የሰራሁት የግል ንበረቴ ነው በማለት ክርክር ያቀረቡ በመሆኑ ውርስ አጣሪው ግራ ቀኙ ማስረጃ እንዲያቀርቡ ትእዛዝ ቢሰጥም የስር አመልካች አቅርበው ሲያስሙ የአሁን አመልካች በተደጋጋሚ ምስክሮች እንዲያቀርቡ ታዘው ካለማቅረባቸውም በተጨማሪ ምስክር የሌላቸው መሆኑን በመግለጽ ምስክሮች ያላቀረቡ ሲሆን የውርስ አጣሪው ከግራ ቀኙ የቀረበውን ክርክር እና የቀረቡትን ማስረጃዎች መርምሮ የስር አመልካች የክርክሩ ቤት ወላጅ አባታቸው እና የአሁን አመልካች አብረው ባሉበት ተጠናቆ የተሰራ መሆኑን ሲያስረዱ የአሁን አመልካች ግን ኮ/ል ላቀው ከሄዱ በኃላ ለብቻዬ የቤቱን 30 ፐርሰንት ሰርቻለሁ ቢሉም አላስረዱም በማለት አትቶ የክርክሩ ቤት ኮ/ል ላቀው ወ/ሰንበት እና የአሁን አመልካች ወ/ሮ ፀሀይ አጎናፍር የጋራ ንብረት ነው ስለሆነም የስር አመልካች የአባቱን ድርሻ 50% የአሁን አመልካች ድርሻቸውን 50% እኩል ይካፈሉ በማለት ሪፖርት ሲያቀርብ ቤቱ የተከራየ ለመሆኑ የስር አመልካች ሲያስረዱ የአሁን አመልካች አለመከራየቱን አላስረዱም በማለትና እስከ አሁን የተከራየው ብር 84ሺ ነው በማለት ብር 42ሺ የስር አመልካች ድርሻ ነው በማለት ሪፖርቱ አቅርቧል ፡፡

እዳን በተመለከተ እዳ አለኝ ብሎ የመጣ ስለሌለ ኮ/ል ላቀው እዳ የለባቸውም በማለት ሪፖርቱ ገልጾ ሪፖርቱን ከፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተሰጠው ትእዛዝ መሰረት ለፍ/ቤቱ ቀርቧል፡፡ ፍርድ ቤቱም በቀረበው የውርስ አጣሪ ሪፖርት ላይ ግራ ቀኙ አስተያየት እንዲሰጡበት በሰጠው ትእዛዝ መሰረት የስር አመልካች በውርስ አጣሪ ሪፖርቱ ላይ ያቀረቡት ቅሬታ የሌለ ሲሆን ጣልቃ ገብ በሰጡት አሰተያየት የክርክሩን ቤት ከኮ/ል ላቀው ጋር ስንሰራ በየካቲት ወር 1985 ዓ.ም ከባንክ ብድር የወሰድን መሆኑን የሚገልጽ እና ኮ/ል ላቀው ከሄዱ በኃላ ለመክፈል ተቸግሬ ባንኩ ማስጠንቀቂያ የሰጠበትን እና ኮ/ል ላቀውም የጻፉትንም ደብዳቤ አቅርቤያለሁ በተጨማሪም ኮ/ል ላቀው ከሄዱ በኃላ ለቤቱ ጠቅላላ ዋጋ 30 ፐርሰንት የሚሆን ወጪ አድርጌያለሁኝ በማለት ሰነዶች ያያያዝኩኝ ስለሆነ ቤቱን የሰራንበት የጋራ እዳ ያለብን መሆኑ እና በግል የሰራሁት 30 ፐርሰንት የግሌ ሊባል ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከውርስ አጣሪው ሪፖርት ጋር መርምሮ የአሁን አመልካች ያቀረቡትን 2 ቅሬታ መሰረት በማድረግ 1ኛ.ለክርክሩ ቤት ከባንክ ተወሰደ የተባለውን ብድር አስመልክቶ የአሁን አመልካች ያቀረቡት የሰነድ ማስረጃ ማለትም አመልካች እና ባለቤታቸው ኮ/ል ላቀው በየካቲት ወር 1983 ዓ.ም ከቤቶች እና ገንዘብ ቁጠባ በጋራ ለቤት መስሪያ በማለት ገንዘብ የወሰዱ መሆኑን፣ ኮ/ል ላቀው በግንቦት ወር 1983 ከሀገር ወጥተው በ1985ዓ.ም ለአሁን አመልካች የጻፉት ደብዳቤ ቤቱ ተሰርቶ ያልተጠናቀቀ መሆኑን ያሳያል፡፡ በማለት አትቶ ምንም እንኳን የስር አመልካች ኮ/ል ላቀው ከቤት ሲወጡ ቤቱ ተሰርቶ አልቆ

ነበር በማለት ቢከራከሩም የአሁን አመልካች ማስረጃ ኮ/ል ላቀው ከቤት ሲወጡ ቤቱ ተጠናቆ ያላለቀ መሆኑን በተሻለ አስረድተዋል በማለት አትቶ ቤቱ ተሰርቶ የተጠናቀቀው ኮ/ል ላቀው ከቤት ከወጡ በኃላ ነው በማለት አመልካች ለቤቱ ማሰሪያ ያወጡትን ወጪ የሚያሳዩ ሰነዶች ያቀረቡ ስለሆነ ይህ ገንዘብ ከነወለዱ የአሁን አመልካች እና የአሁን ተጠሪ የጋራ እዳ ነው በማለት ሲወስን የአሁን አመልካች ኮ/ል ላቀው ከቤት ከወጡ በኃላ የተሰራው ቤት የግል ንብረቴ ይባልልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ በተመለከተ ምንም እንኳን ኮ/ል ላቀው ከቤት የወጡት በ1983 ዓ.ም ቢሆንም ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ እስከ መጋቢት 22/2002 ዓ.ም ድረስ ከአሁን አመልካች ጋር በደብዳቤ ይገናኙ የነበረ መሆኑን አመልካች ካቀረቧቸው የሰነድ ማስረጃዎች መረጋገጥ መቻሉን ገልጾ አመልካች እና ኮ/ል ላቀው በዚህ ጊዜ ውስጥ ሁሉ አብረው ባይኖሩም በጋብቻ የነበሩ ባል እና ሚስት ነበሩ በማለት አትቶ በጋብቻ ጊዜ የተፈራ ሀብት በሙሉ የባል እና ሚስቱ የጋራ ሀብት ነው በማለት የክርክሩ ቤት የአመልካች እና የባለቤታቸው የኮ/ል ላቀው ነው፡፡ ስለሆነም የአሁን ተጠሪ የአባታቸውን ድርሻ አመልካች የራሳቸውን ድርሻ የቤቱን ግምት እኩል ይካፈሉ በማለት የውርስ አጣሪውን ሪፖርት በማሻሻል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁን አመልካች ለስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታቸውን ቢያቀርቡም ተቀባይነት ባለማግኘቱ ለፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታቸውን ያቀረቡ ሲሆን ለዚህ ሰበር ችሎት የቀረበው አቤቱታ ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡ የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም የቀረበውን የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ከቀረበው ክርክር እና ማስረጃ አንጻር የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን መርምረነዋል፡፡ እንደመረመርነውም የአሁን አመልካች ዋና ቅሬታ የተጠሪ አቤቱታ በይርጋ የሚታገድ ሆኖ እያለ ይህ ታልፎ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚል እና የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክርክሩ በይርጋ አይታገድም በማለት ውሳኔ የሰጠው እና የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያጸነው የአሁን ተጠሪ ክርክሩን ያቀረቡት በ6/9/2007ዓ.ም ሲሆን የአባታቸውን የመጥፋት ውሳኔ በፍርድ ቤት ያሳወጁት በ21/8/2007 ዓ.ም በመሆኑ ክርክሩ በይርጋ አይታገድም በማለት ነው፡፡

በፍትሀብሄር ህግ ቁጥር 165(1)ላይ በጠፋው ሰው መሞት ምክንያት መብት የሚያገኙ ሰዎች በመብታቸው መጠቀም የሚችሉት መጥፋቱን የሚወስነው ፍርድ የመጨረሻ ከሆነ በኃላ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡ የአሁን ተጠሪ ክርክሩን ያቀረቡት በ6/9/2007ዓ.ም ሲሆን የአባታቸውን የመጥፋት ውሳኔ በፍርድ ቤት ያሳወጁት በ21/8/2007 ዓ.ም መሆኑ የተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በመብታቸው መጠቀም የሚችሉ መሆኑ በህጉ የተመለከተ ሲሆን የመጥፋት ውሳኔ አሰጥተው የውርስ ሀብት ያቀረቡበት ጊዜ ሲቆጠር በፍ/ብ/ህግ ቁጥር 1000(1)

መሰረት ክርክሩ በይርጋ የሚታገድ ባለመሆኑ ይርጋን አስመልክቶ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሌላውን ክርክር በተመለከተ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የውርስ አጣሪውን ሪፖርት ምክንያት በማሻሻል በውጤት ደረጃ ያጸናው ውሳኔ እና የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ያጸነው ውርስ አጣሪው ኮ/ል ላቀው ከቤት ሲወጡ ቤቱ ተጠናቅቆ የነበረ መሆኑን የስር አመልካች በሰው ማስረጃ አስረድተዋል ስለሆነም የአሁን አመልካች ኮ/ል ላቀው ከቤት ከወጡ በኃላ የሰሩት ተጨማሪ ስራ ለመኖሩ ያላስረዱ በመሆኑ የግል የሚባልላቸው መብት የለም በማለት ሲሆን፤ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ይህንን ክርክር አስመልክቶ ኮ/ል ላቀው ከቤት ከወጡ በኃላ ቤቱ ያልተጠናቀቀ መሆኑን እራሳቸው በጻፉት ደብዳቤ ተረጋግጧል በማለት ነው፡፡

ነገር ግን ኮ/ል ላቀው ከቤት የወጡት በ1983 መሆኑ ክርክር ያልተነሳበት ጉዳይ ቢሆንም እስከ 2002 መጋቢት ወር ድረስ በደብዳቤ ከአሁን አመልካች ጋር ይገናኙ የነበረ መሆኑን አመልካች ካቀረቧቸው ማስረጃዎች ማረጋገጥ የተቻለ ስለሆነ ምንም እንኳን አመልካች ኮ/ል ላቀው ከቤት ከወጡ በኃላ የሰሩት ተጨማሪ ቤት መኖሩን በመግለጽ የግላቸው እንዲባልላቸው የጠየቁ ቢሆንም በዚህ ግንኙነት የተፈራ ንብረት የባል እና ሚስቱ የጋራ ንብረት ነው በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ማድረጉን በስር ከተደረገው ክርክር እና ማስረጃ መረዳት ተችሏል፡፡

በመሰረቱ በፌደራሉ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 63(1) ላይ አንደኛው ተጋቢ የግል ሀብቱ መሆኑን እስካላስረዳ ድረስ የተጋቢዎች ንብረት በአንደኛው ተጋቢ ስም ብቻ ቢመዘገብም የተጋቢዎቹ የጋራ ንብረት እንደሆነ እንደሚገመት ተደንግጓል፡፡ የአመልካች ክርክር በቤቱ ላይ ተጨማሪ ስራ የተሰራው ኮ/ል ላቀው ከቤት ከወጡ በኃላ ነው በማለት ቢከራከሩም እስከ 2002 መጋቢት ወር ድረስ ይጻጻፉት የነበረውን ደብዳቤ አመልካች በማቅረብ ያስረዱ መሆናቸውን ከመረጋገጡም በተጨማሪ ኮ/ል ላቀው በ1983 ከቤት ወጥተው የመጥፋት ውሳኔ በፍርድ ቤት የተሰጠው ሚያዝያ 21 ቀን 2008ዓ.ም በመሆኑ የአመልካች እና የኮ/ል/ላቀው ጋብቻ እና ግንኙነት በኮ/ል ላቀው ከቤት መውጣት ያልተቋረጠ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም በጋብቻ ጊዜ የተፈራ ንብረት የባል እና ሚስቱ የጋራ ንብረት ሆኖ እንደሚገመት በህጉ የተደነገገ እና የግል ሊባል የሚችለው የግሌ ነው የሚለው ተጋቢ የግሉ መሆኑን በማስረዳት እንደሆነ በህጉ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ የአሁን አመልካች ኮ/ል ላቀው ከሄዱ በኃላ የተሰራ በመሆኑ የግል ንብረቴ ነው ከማለት በስተቀር በግል ገንዘቤ ሰርቻለሁ በማለት ያነሱት መከራከሪያ የሌለ በመሆኑ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የውርስ አጣሪውን ሪፖርት ምክንያት በማሻሻል በውጤት ደረጃ ኮ/ል ላቀው ከቤት ከወጡ በኃላም ተሰራ የተባለው ቤት የባል እና ሚስት የጋራ ንብረት ነው በማለት ውሳኔ መስጠቱ እና የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንን ውሳኔ በማጽናት

መወሰኑ ህግን መሰረት ያደረገ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. .የስር የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 100091 በቀን 6/8/2008ዓ.ም የውርስ አጣሪውን ሪፖርት በማሻሻል የሰጠው ውሳኔ እና ይህንን ውሳኔ በማጽናት የስር የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 172889 ሀምሌ 8 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
3. በየደረጃው ለሚገኙ የስር ፍርድ ቤቶች የውሳኔው ግልባጭ ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ. 131622

ሰኔ 20ቀን 2009 ዓ/ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ አርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- ወ/ሮ አልማዝ እምሩ - ተወካይ አቶ ኢማሙ እብራሂም ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አይጠገብ ቀሬ- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዮ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የጉዳዩ መነሻ የባልና ሚስት ንብረት ክርክርን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ የአሁኗ ተጠሪ በተወካያቸው በኩል በጋምቤላ ክልል መንግሥት ሥር ለሚገኘው ለማጃንግ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በቀን 16/10/2007 ዓ/ም ጽፈው ያቀረቡት ክስ የሟች አቶ ደምሴ ጋሻው የመጀመሪያ ሚስት መሆናቸውን፣ አመልካች /የሥር ተከሳሽ/ ሁለተኛ ሚስት ነኝ በማለት የእሳቸውን የሚስትነት ድርሻ ንብረት እና የሟች ልጅ የውርስ ድርሻ ንብረቱን ለብቻቸው ይዘው የሚጠቀሙ በመሆኑ የተጠሪ የሚስትነት እንዲሁም የሟች ልጅ የውርስ ንብረት ድርሻ ይገባኛል የሚል ነው፡፡

የአሁኗ አመልካች /የሥር ተከሳሽ/ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚዎችን ያቀረቡ ሲሆን ይዘታቸውም፡-

1. ከሳሽ /የአሁኗ ተጠሪ/ በክሳቸው ዘርዝረው ያቀረቡት ጉዳይ በአሁኗ አመልካች /በሥር ተከሳሽ/ በኩል በአሁኗ ተጠሪ/ በሥር ተከሳሽ/ ላይ በሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቴፒ ምድብ ችሎት ክስ ቀርቦ የክሱ መጥሪያ ቀድሞ ለተጠሪ ደርሶዋቸው መልሳቸውን በጽሁፍ አቅርበው የቃል ክርክር ካደረጉ በኃላ ያቀረቡት ክስ ስለሆነ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 7 መሠረት መጀመሪያ ክሱ በቀረበው በሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቴፒ ምድብ ችሎት እንዲቀጥል ፋይሉ እንዲዘጋልኝ፣

2. የከሳሽ ተወካይ ክስ ለማቅረብና ለመከራከር የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 58 እና 63 ድንጋጌን መሠረት በማድረግ ያሟላ የውክልና ሥልጣን አይደለም፣
3. ከሳሽ የሟች ባለቤት ነኝ በማለት ክስ ያቀረቡ ቢሆንም በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 33 እና 244 /2/ /ሠ/ መሠረት የመክሰስ መብት የሌላቸው በመሆኑ ንብረቶቹን ለመጠየቅ በይርጋ ቀሪ የሆነ ጉዳይ በመሆኑ መብት የላቸውም እንዲባልልኝ የሚል ነው፡፡

የማጃንግ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁኗ ተጠሪ በመቃወሚያዎቹ ላይ መልስ እንዲሰጡ ካደረገ በኃላ የአመልካችን መቃወሚያዎችን በብይን ውድቅ አድርጎ በማለፍ የፍሬ ነገር ክርክሩን ከሰማ በኃላ የግራ ቀኙን የሰው ምስክሮችን ቃል ሰምቶ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ይህን ውሳኔ የአሁኗ አመልካች ቅር በመሰኘት ለጋምቤላ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኙን ተቀብሎ የግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡ ቀጥሎም የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱም አቤቱታውን ተቀብሎ ክርክራቸውን ከሰማ በኃላ የሥር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ ለማስለወጥ ሲሆን በአቤቱታቸውም በመጀመሪያ ደረጃ መሠረት የሚያደርጉት የማጃንግ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከአመልካች በኩል የቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን በብይን ያለፈው ያለአግባብ ሆኖ እያለ ቀጥሎ ያሉት ፍርድ ቤቶችም ይህንን ሳያርሙ ማለፋቸው መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ካሉ በኃላ በፍሬ ነገርም ረገድ በስር ፍርድ ቤቶች ተፈጽሞዋል የሚሉዋቸውን ዝርዝር የቅሬታ ነጥቦችን አቅርበዋል፡፡

የሰበር አቤቱታውን አጣሪው መርምሮ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ያደረገ ሲሆን ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ህዳር 29 ቀን 2009 ዓ/ም በነበረው ቀጠሮ መልሳቸውን ያላቀረቡት መጥሪያ ስላልደረሳቸው መሆኑን ገልጸው ተለዋጭ ቀጠሮ እንዲሰጣቸው በጠየቁት መሠረት መልስ በተለዋጭ ቀጠሮ ቀን እንዲያቀርቡ ተፈቀደላቸው ሳያቀርቡ በመቅረታቸው መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን የሚመስል ሲሆን ወደ ፍሬ ነገሩ ክርክር መግባት ሳያስፈልግ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን ብቻ መሰረት በማድረግ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ በዚሁ መሠረት፡-

1. አመልካች አስቀድመው ክስ ለሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል ወይስ አላቀረቡም? ክስ በቅድሚያ ለሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበው ከሆነ መቃወሚያቸው በሥር ፍርድ ቤት መታለፉ ከፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 7 አንፃር እንዴት ይታያል?
2. የአመልካች ተወካይ በውክልና ክስ ለማቅረብ ይችላሉ ወይስ አይችሉም? የሚሉ ጭብጮች ተይዘዋል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡-

የአሁኗ ተጠሪ የሟች ባለቤታቸው ንብረት በአሁኗ አመልካች እጅ ስለሚገኝ የልጃቸውና የእርሳቸው ድርሻ እንዲወሰንላቸው ክስ በጋምቤላ ክልል ሥር በሚገኘው በጎዳሬ ወረዳ ፍርድ ቤት መሥርተው የሥረ ነገር ሥልጣን ክርክር በመነሳቱ ምክንያት ክስ የማቅረብመብት ያለው ወገን ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ ያቅርብ ተብሎ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ የወረዳ ፍርድ ቤት ብይንም በየደረጃ ላሉት ፍርድ ቤቶች ቀርቦ ፀንቷል፡፡

ከዚህ በኃላ የአሁኗ አመልካች ለሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቴፒ ምድብ ችሎት በቀን 09/10/2007 ዓ/ም የተጻፈ ክስ በአሁኗ ተጠሪ ላይ አቅርበው የክስ መጥሪያ ደርሶዋቸው በቀን 13/10/2007 ዓ/ም የተጻፈ መልስ አቅርበው የቃል ክርክር እንደተደረገና ከዚህ በኃላ የቀረበ ክስ መሆኑን በመጥቀስ አመልካች መቃወሚያ አቅርበው ተከራክረዋል፡፡ የአሁኗ ተጠሪም የአመልካችን መቃወሚያ ክደው አልተከራከሩም፡፡

የማጃንግ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ በቀደምትነት የቀረበው ሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው? ወይስ በማጃንግ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው? የሚል ጭብጥ ይዞ ቀደም ሲል በጎዳሬ ወረዳ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ ሲከራከሩ ቆይተው በ26/6/2007 ዓ/ም በዋለው ችሎት በተሰጠው ውሳኔ የአሁኗ ተከሳሽ /አመልካች/ ቅር በመሰኘት በከፍተኛ ፍርድ ቤት በክርክር ላይ የቆዩ ከመሆኑ ባለፈ ተከሳሽ /የአሁኗ አመልካች/ ያነሱትን መቃወሚያ ውድቅ በማድረግ በቀደምትነት ክስ የቀረበው በማጃንግ ብሔረሰብ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሆኑ ግራ ቀኙ ወደ ፍሬ ነገር ገብተው ክርክራቸውን እንዲቀጥሉ ሲል በፍ/መ/ቁ. 02223 በቀን 27/11/ 2007 ዓ/ም ብይን እና በቀን 4/2/2008 ዓ/ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የማጃንግ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስለ ክስ ቀደምትነት መሠረት ያደረገው በጎዳሬ ወረዳ ፍርድ ቤት የቀረበውን ክስ ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከተው የአሁኗ ተጠሪ በዚህ ወረዳ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ ነው ተብሎ በሥረ ነገር ሥልጣን ምክንያት የተዘጋ ነው፡፡ በዚህ ብይን ላይ የመክሰስ መብት ያለው ሰው ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ ለማቅረብ

እንደሚችል ተቀምጧል፡፡ ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ንብረት በጋምቤላ ክልል እና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ህዝቦች ክልል ሥር ባሉት ዞኖች ውስጥ የሚገኝ በመሆኑና የግራ ቀኙም የተለያዩ ክልል ነዋሪዎች ስለሆኑ አመልካች በሚኖሩበት ክልል በሚገኘው ሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ አቅርበዋል፡፡ ለዚህ ክስ ተጠሪ ቀርበው መልስ ሰጥተዋል፡፡ የቃል ክርክርም አድርገዋል፡፡ ይህ ከሆነ በኃላ ለማጃንግ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሌላ ክስ የአሁኗ ተጠሪ ማቅረባቸውን ከሥር ፍርድ ቤት ብይን ተመልክተናል፡፡

በመሠረቱ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ክርክር የሚመራበትን ሥርዓት በግልጽ ያስቀምጣል፡፡ የሥነ ሥርዓት ህጉም ዓላማ ክርክር ቀልጣፋ፣ ወጪ ቆጣቢ፣ ተገማች እና ተደራሽ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ የተያዘውን ጉዳይ በተመለከተ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ እንዲቀርብ ብይን ከተሰጠ በኃላ በቅድሚያ የቀረበው ለሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 7 /1/ ሥር አንድ የፍትሐብሔር ክስ መታየት የሚገባው በአንድ የፍትሐብሔር ፍርድ ቤት ብቻ እንደሆነ በመርህ ደረጃ ይደነግጋል፡፡ በንዑስ አንቀጽ 2 ላይ አንዱን የፍትሐብሔር ክስ ባንድ ወይም ካንድ በበለጡ ፍርድ ቤቶች ዘንድ ለማቅረብ የሚቻል ሲሆን የክሱ ማመልከቻ በቀደምትነት የቀረበለት ፍርድ ቤት ብቻ የዳኝነት ሥልጣን እንዳለው ተቆጥሮ ለክርክሩ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል በማለት ተቀምጧል፡፡ አሁን ለተያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው የተጠቀሰው ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 7/2/ ሲሆን ይህም ከላይ ከተመለከተው ከፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ዓላማ አንጻር ሊታይ የሚገባ ነው፡፡ የማጀንግ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወረዳ ፍርድ ቤት ቀርቦ በሥረ ነገር ሥልጣን ምክንያት የተዘጋውን ጉዳዩ በይግባኝ ቀደም ሲል አይቶ የዘጋ ሆኖ እያለ አዲስ ክስ ሲቀርብለት መጀመሪያ በሥልጣን ምክንያት በይግባኝ ታይቶ የታለፈውን ግምት ውስጥ በማስገባት የአመልካችን መቃወሚያ ውድቅ ማድረጉ ሲታይ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 7 /2/ ድንጋጌን የጣሰ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ የተሰጠው ብይን መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡-

በከሳሽነት ወይም በተከሳሽነት የሙጉት ተከፋይ ሆነው ለመከራከር የሚችሉ ሰዎችን በተመለከት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ በሁለተኛ መጽሐፍ አንቀጽ 32 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ሥር ዝርዝር ድንጋጌዎችን አስቀምጧል፡፡ እነዚህን ተከራካሪዎችን ወክለው ለመከራከር የሚችሉ ሰዎችንም በተመለከተ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 57 እና ተከታዮቹ አንቀጾች ሥር ዝርዝር ድንጋጌዎችን ደንግጓል፡፡ አሁን በተያዘው ጉዳይ ተጠሪን ወክለው በሥር ፍርድ ቤት ክስ ያቀረቡት የተጠሪ ወኪል አንቀጽ 58 ወይም 63 ‘ን’ ድንጋጌ የሚያሟሉ ናቸው ወይስ አይደሉም? የሚለውን መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡ አመልካች የተጠሪ ወኪል ከእነዚህ ሁለቱ

ድንጋጌዎች አንዱንም የማያሟሉ በመሆናቸው ሊከራከሩ አይችሉም በማለት በሥር ፍርድ ቤት ተቃውሞዋቸውን አሰምተዋል፡፡ የማጃንግ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለዚህ መቃወሚያ ምንም ብይን ሳይሰጥ በዝምታ እንዳለፈ ከሰጠው ብይን ላይ ተመልክተናል፡፡

አንድ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ለቀረበለት መቃወሚያ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 245 /2/ መሠረት ተገቢውን ብይን መስጠት እንዳለበት በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ተከራካሪ ወገኖች የሚያቀርቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ላይ ብይን ሳይሰጥ በማለፍ የሚሰጥ ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁ 59294 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ይህንን በአግባቡ ሳይመለከተውና ለቀረበለት መቃወሚያ ብይን ሳይሰጥ በዝምታ ማለፉ ሲታይ ህጋዊ መሰረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የተጠሪ ተወካይ ክስ አቅርበው ለመከራከር እንዲችሉ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 58 ድንጋጌን የማያሟሉ እንዳልሆነ የተጠሪ ተወካይ ለማጃንግ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ካቀረቡትና በብይኑ ላይ ከሰፈረው ለመመልከት ችለናል፡፡ በተጨማሪ የፍትሐብሔር ሥነ ህግ ቁጥር 63 ድንጋጌንም የሚያሟሉ እንዳልሆነ በሥር ፍርድ ቤት ከተደረገው ክርክር ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በዚሁ መሠረት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 58 ወይም 63 ድንጋጌን የማያሟሉትን የተጠሪን ወኪል የሥር ፍርድ ቤት እንዲከራከሩ ማድረጉ ድንጋጌዎቹን የጣሰ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንድን ሰው በመወከል በፍርድ ቤት ቀርቦ ለመሟገት በህጉ የተቀመጠውን የዝምድና ደረጃ ወይም በህጉ የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟላ የውክልና ስልጣን የሚያስፈልግ ስለመሆኑ ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁ.91493 የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉምን፣እንዲሁም በፍርድ ቤት በሚደረግ ክርክር ስለዋናዎቹ ባለጉዳዮች በመሆን ሌሎች ሰዎች በተሟጋችነት ሊቀርቡ ስለሚችሉበት ስርዓት፣ በህጉ የተቀመጠውን መስፈርት አሟልቶ አለመገኘት የሚያስከትለው ህጋዊ ውጤትን በተመለከተ በሰ/መ/ቁ. 94302 ሥር የተሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ያላገናዘ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሚሰጠው ውሳኔ በማንኛውም ደረጃ በሚገኙት ፍርድ ቤቶች ላይ አስገዳጅነት እንዳለው አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2 /1/ ይደነግጋል፡፡

በአጠቃላይ የማጃንግ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከላይ የተመለከቱትን መሠረታዊ ነገሮችን በአግባቡ ሳያጤን የሰጠው ብይን እንዲሁም ቀጥሎ ያሉት የበላይ ፍርድ ቤት ችሎቶችም ይህን ሳያርሙ ማለፋቸው ሲታይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የማጃንግ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/መ/ቁ 02223 በቀን 27/11/2007 ዓ/ም የሰጠው ብይን እና በቀን 4/2/2008 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ፣ የጋምቤላ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ.01850/08 በቀን 11/04/2008 ዓ/ም እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በፍ/ሰ/ቁ. 00500/08 በቀን 16/09/2008 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348 /1/መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በቀን 09/10/2007 ዓ/ም ባቀረቡት ክስ መሠረት የተጀመረውን ክርክር በተጀመረው መዝገብ ላይ በመቀጠል የሸካ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክርክሩን ተመልክቶ የመሰለውን ውሳኔ እንዲሰጥ ተብሎ ተወስኗል ፡፡
3. ከላይ በሁለተኛ ጭብጥ በፍርድ ሀተታ ላይ በተገለጸው መሠረት ቀደም ሲል ለተጠሪ ወኪል በመሆን የተከራከሩት አቶ ሞገስ አለምነህ ጉዳዩን ለመከራከር አይችሉም ብለናል፡፡
4. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይላክላቸው፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

የሰ/መ/ቁ.113613

ግንቦት 30 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ

ቀነዓ ቂጣታ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- በደቡብ ወሎ ዞን የለገሂዳ ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ፅ/ቤት ዓ/ሕግ አበበ ሙሉ ቀርበዋል

ተጠሪ፡- ሰለሞን አባይ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ ቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የግንባታ ዉልን መነሻ ክፍያ ለመጠየቅ የቀረበዉን ክስ የሚመለከት ክርክር ሲሆን፣ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.97192 በ5/9/2007 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት የአሁን አመልካች የቀረበዉን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

የጉዳ ዩአመጣጥ ሲታይ በደቡብ ወሎ መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ፣የአሁን ተጠሪ ተከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ የነበረ ሲሆን፣ የለገሂዳ ትምህርት ጽ/ቤት በወረዳዉ 012 ቀበሌ የሸክፍ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ለማሰራት ያወጣዉን ጨረታ ከሳሽ አሸንፎ በ12/10/2002 ዓ.ም ዉል የተዋዋልን ሲሆን፣ በዚህ ዉል መሰረት ሥራዉን አጠናቅቁ ጊዜያዊ ርክክብ ተደረጓል፤ ነገር ግን ተከሳሽ ቀሪ ክፍያ ብር 86,944.26 ስላልከፈለኝ ይህን ገንዘብ ለዘገየበት ጊዜ መቀጫ 1% ጋር እንዲከፍለን፣ እንዲሁም በዚህ ምክንያት የደረሰብኝ ኪሳራ ብር 52,324 ስለሆነ በአጠቃላይ ብር 380,383.53 እንዲከፍለን በማለት ከሷል፡፡ ተከሳሽ ባቀረበዉ መልስ ይህን ዉል ማድረጋችን የማይካድ ቢሆንም ከሳሽ የቀረበዉ ክፍያ ብር 63,791.63 ብቻ ነዉ፤ እንዲሁም ከሳሽ የግንባታዉን ሥራ በጥራት ሳይሰራ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑን የኦዲት ሪፖርት ያረጋገጠ ስለሆነ ብር 58,659.20 እንዲካካስልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በማጣራት በሰጠዉ ዉሳኔ ተከሳሽ ለከሳሽ ያልከፈለዉን ክፍያ ብር 86,949.26 ሊከፍል ይገባል የዚህ ገንዘብ ክፍያ ለዘገየበት 1% መቀጫ እንዲከፍል፣ ከሳሽ ያጣዉን ጥቅም በተመለከተ ተከሳሽ ብር 1,683.00 ለከሳሽ እንዲከፍለዉ፣ ተከሳሽ ከሳሹ ሥራዉን

በጥራት ስላልሰራ ብር 58,659.20 እንዲመልስልን በማለት የጠየቀዉን በተመለከተ ተቀባይነት የለዉም ከሳሽ ይህን ገንዘብ ለተከሳሽ ሊመልስ አይገባም፤ ተከሳሽ የጠበቃ አበል በተወሰነ ገንዘብ ልክ 10% እና ወለድ ዉሳኔ ከተሰጠበት እስከሚከፈልበት በማለት ወስኗል፡፡ የሥር ተከሳሽ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት በመ.ቁ.9121 ብር 58,659 እንደተወሰነለት በመግለጽ ይግባኙን ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኛቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ ከሳሽ ባቀረበዉ ክስ የመቀጫ ክፍያ 1% ክስ እስከቀረበበት እንዲከፈል ጠይቆ እያለ ዉሳኔ እስከተሰጠበት የተባለዉ ያልተጠየቀ ዳኝነት ስለሆነ ተገቢ አይደለም፤ ወለድን በተመለከተ ክስ ከቀረበበት ጀምሮ እስከ ዉሳኔ ድረስ ባለዉ ጊዜ ተከሳሽ በተወሰነዉ ገንዘብ ልክ 9% ተከሳሽ ለከሳሽ ሊከፍል ይገባል በማለት የሥር ዉሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡ የሥር ተከሳሽ አሁንም ይህን ዉሳኔ በመቃወም የሰበር አቤቱታ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም ችሎቱ ያቀረበዉን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ የሥር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች በ5/9/2007 ዓ.ም የተጻፈ አምስት ገጽ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአቤቱታዉም ይዘት በአጭሩ፡-የአሁን ተጠሪ ቀሪ ክፍያ እንዲፈጸምለት በመ.ቁ.5402 ክስ ያቀረበ ሲሆን፣ አመልካች ደግሞ ተጠሪ የሰራዉ የግንባታ ሥራ ጥራት ጉድለት ስላለበት ለማስተካከል ግንባታዉን ለማስተካከል ብር 58,659.00 ወጪ ያደረገ ስለሆነ ይህን ገንዘብ እንዲከፍለን በመ.ቁ.9121 ክስ አቅርበናል፣ የሥር ፍ/ቤት እንዲጣመር በማድረግ አጣርቶ ዉሳኔ መስጠት ሲገባዉ ይህን ሳያድርግ ዉሳኔ መስጠቱ ተገቢ አይደለም፡፡ የሥር ፍ/ቤት በመ.ቁ.9121 ተጠሪ ለአመልካች ብር 58,659 እንዲከፍለን ዉሳኔ ተሰጥቶ እያለ ይህ ዉሳኔ ጸንቶ እያለ ለአመልካች ገንዘብ እንድንከፍል ዉሳኔ መስጠቱ ጉዳዩን በአግባቡ አለማጣራቱን ያመለክታል፡፡ ስለዚህ የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲሻርልን በማለት አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣በመ.ቁ.9121 በተሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪ የግንባታ ሥራዉን በጥራት ስላልሰራ ብር 58,659.00 ለአመልካች እንዲከፍል ተወስኖ እያለ፣ በመ.ቁ.5402 ደግሞ አመልካች ለተጠሪ ቀሪ ክፍያ ብር 86,944.26 እና ክፍያ ለዘገየበት የመቀጫ እና የወለድ ገንዘብ እንዲከፍለዉ የመወሰኑን እና የሁለቱ ፋይሎች በአንድ ላይ ተጣምሮ ያለመወሰን ያስከተለዉን የሥነ ሥርዓት ጉድለት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.11 አንፃር ለመመርመር ሲባል አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጣሪ መልስ እንዲያቀርብ በታዘዘዉ መሰረት በ4/4/2008 ዓ.ም የተጻፈ ሁለት ገጽ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡-የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ በአግባቡ ስለሆነ የቀረበዉ የሰበር አቤቱታ ዉድቅ እንዲደረግልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የሰበር ሰቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኛቸዉን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአሁን ተጠሪ የግንባታ ዉልን መነሻ በማድረግ ቀሪ ክፍያ እንዲከፈለዉ አመልካች ላይ ክስ አቅርቦ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራ ቀኛቸዉን በማከራከር በመ.ቁ.5402 ላይ አመልካች ለተጠሪ ብር 86,944.26 እና የዚህን ገንዘብ 1% መቀጫ ተሰልቶ እንዲከፍል፣ ወለድ ዉሳኔ ከተሰጠበት ገንዘቡ እስከሚከፈል ድረስ እና የጠበቃ አበል በተወሰነ ገንዘብ ልክ 10% እንዲከፍል ወስኗል፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሊከፈል የሚገባ የመቀጫ ገንዘብ እና የወለድ መጠን ላይ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ በማሻሻል ወስኗል፣ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ይህን ዉሳኔ ማጽናቱን የቀረበዉ የዉሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች በሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪ የሰራዉ የግንባታ ሥራ ጥራት ስላልነበረዉ ይህን ጉድለት ለማስተካከል ብር 58,659.20 ወጪ ስላደረግን ይህን ገንዘብ እንዲከፍለን በማለት በመ.ቁ.9121 ግንቦት 15 ቀን 2005 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ ተጠሪ የሰራዉ ሥራ ጥራት የሌለዉ መሆኑን በማረጋገጥ ተጠሪ ይህን ጉድለት እንዲያስተካክል ወይም በክሱ የተመለከተዉን ብር 58,659.20 ለአመልካች እንዲከፍል ወስኗል፡፡ የአሁን አመልካች ባቀረበዉ ክርክር የሥር ፍ/ቤቶች እነዚህ መዝገቦች አጣምረዉ ዉሳኔ መስጠት ሲገባቸዉ ይህን ሳያደርጉ ዉሳኔ መስጠታቸዉ ተገቢ አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡ የአሁን ተጠሪም ባቀረበዉ ክርክር እነዚህ ሁለት ዉሳኔዎች መሰጠቱን ክዶ የተከራከረ ነገር የለም፡፡ ይህ ችሎት የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ እንደተመለከተዉ በዚህ ጉዳይ ሁለት መዝገቦች መከፈታቸዉን የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ ባያመለክትም፣ አመልካች ይህ ገንዘብ እንዲካካስለት የጠየቀ መሆኑን ያሳያል፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች በዚህ ጉዳይ በሁለት መዛግብት ዉሳኔ እንደተሰጠበት ግልጾ የተከራከረ ቢሆንም በዚህ ጉዳይ ላይ ተገቢ ዉሳኔ ሳይሰጡበት አልፈዉታል፡፡ ከዚህ መገንዘብ እንደሚቻለዉ ግራ ቀኛቸዉ በየፊናቸዉ የየራሳቸዉን ክስ አቅርበዉ መዝገብ አስከፍቶ ዉሳኔ ያገኙ መሆናቸዉን ያመለክታል፡፡

በመሰረቱ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ክሶች ወይም ይግባኞች በሚቀርቡብት ጊዜ በሕጉ የተመለከተዉ መስፈርት ተሟልቶ እንደሆነ ተጣምሮ መታየት እንዳለባቸዉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.11 ያስገናዝባል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ክሶች ወይም ይግባኞች በአንድ ፍ/ቤት ቀርበዉ በመሰማት ላይ በሚገኙበት ጊዜና ተከራካሪዎቹም ወገኖች ባንድ ዘንግ የተመደቡ ሲሆኑ የቀረበዉም የሕግ ክርክር ወይም የነገር ጭብጥ ተመሳሳይና አንድ ዓይነት ሲሆን ከባለጉዳዮቹ አንደኛዉ ወገን ባመለከተ ጊዜ ወይም ፍ/ቤቱ ተገቢነቱን የገመተ እንደሆነ ክሶቹ ተጣምረዉ በአንድነት እንዲታዩ አስፈላጊዉን ትዕዛዝ ለመስጠት ይቻላል፡፡ በማለት ደንግጓታል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ይዘትና ዓላማ መገንዘብ እንደሚቻለዉ እነዚህ ክሶች ወይም ይግባኞች መጣመራቸዉ ተከራካሪ ወገኖችን ተገቢ ካልሆነ

ወጪ ለማስቀረትና ጊዜያቸዉን ለመቆጠብ ሲባል፣ እንዲሁም በጉዳዩ ላይ የሚሰጠዉ ዉሳኔ ተመሳሳይ እና የማይጣረስ ወይም የማይጋጭ እንዲሆን ለማስቻል መሆኑን ያመለክታል፡፡ በዚህ አግባብ አሁን ወደ ተያዘዉ ጉዳይ ስንመለስ የግራ ቀኛቸዉ ክርክር አንድ የግንባታ ዉልን መነሻ ያደረገ በመሆኑ፣ ከግንባታ ሥራዉ ጋር በተያያዘ ተጠሪ ቀሪ ክፍያ እና ሌሎች ክፍያዎችን የጠየቀ መሆኑን፣ አመልካች ደግሞ የግንባታዉ ሥራ በጥራት ስላልተሰራ አመልካች ይህን ጉድለት ለማስተካከል ያወጣዉን ወጪ ተጠሪ በማለት የጠየቀ በመሆኑ፣ የሥር ፍ/ቤቶች የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ11 በሚደነግገዉ አግባብ መዝገቦቹን በማጣመር ዉሳኔ ቢሰጡ ኖሮ አሁን የተፈጠረዉ ሁለት ዉሳኔዎች ባልተወሰነ ነበር፡፡ አሁን ግን በዚህ ጉዳይ በሁለት መዝገቦች ሁለት ዉሳኔዎች እንዳሉ ችሎቱ ተገንዝቦታል፡፡ በአንድ ጉዳዩ ግራ ቀኛቸዉ ባለመብት የሆኑበት ሁለት ዉሳኔዎች እንዳሉ ያመለክታል፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች እነዚህን መዝገቦች አጣምሮ ዉሳኔ ባይሰጡም፣ እነዚህ ዉሳኔዎች ተጣጥሞ እንዲፈጸሙ ካልተደረገ ለአፈጻጸምአስቸጋሪ ሁኔታ የሚፈጥሩ እንደሚሆኑ ግልጽ ነዉ፡፡ ስለሆነም ግራ ቀኛቸዉ የየራሳቸዉን ክስ አቅርበዉ የፍርድ ባለመብት እስከሆኑ ድረስ ዉሳኔዎቹ ተጣጥሞ ሊፈጸሙ ይገባል ብለናል፡፡

በዚህ መሰረት ሲታይ የአሁን አመልካች ለተጠሪ ብር 86,944.26 ከመቀጫ እና ከወለድ እንዲሁም ከጠበቃ እና ከሌሎች ወጪዎች ጋር እንዲከፍል የተወሰነ ሲሆን፣ ተጠሪ ደግሞ ብር 58,659.20 ለአመልካች እንዲከፍል የተወሰነ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡ አሁን ተጠሪ ከአመልካች ጋር ባደረገዉ ክርክር ሥራዉን በጥራት እንዳልሰራ ተረጋግጦ ይህን ለማስተካከል አመልካች ያጣዉን ወጪ እንዲተካ በተወሰነበት ሁኔታ የአሁን አመልካች ለተጠሪ የመቀጫ ገንዘብ፣ የጠበቃ አበል እና ሌሎች ክፍያዎችን የሚከፍልበት አግባብ ሊኖር አይችልም፡፡ ስለሆነም የአሁን አመልካች የገንዘብ መቀጫ፣ የጠበቃ አበል እና ሌሎች ወጪዎችን ለተጠሪ ለመክፈል ኃላፊነት የለበትም ብለናል፡፡ በሌላ በኩል የአሁን አመልካች ለተጠሪ ሊከፍለዉ የሚገባዉ የገንዘብ መጠን ተቀንሶለት ብር 27,840.06 /ሀያ ሰባት ሺህ ስምንት መቶ አርባ ከዜሮ ስድስት ሳንቲም/ እና የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ ከሰጠበት ከ17/6/2006 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ሕጋዊ ወለድ ጋር ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች ይህን ጉዳይ በዚህ አግባብ አይተዉ ሁለቱን መዝገቦች አጣምረዉ ዉሳኔ መስጠት ሲገባቸዉ የአሁን አመልካች በፍርድ መብት ባገኘበት ይህን ዉሳኔ ባለመቀበል ለተጠሪ ገንዘብ እንዲከፍል የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

<u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.5402 በ17/6/2006 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህን ዉሳኔ በማሻሻል የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.01-02009 ታህሳስ 8 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት

በመ.ቁ.97192 በ5/9/2007 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመባቸዉ ስለሆነ ተሻሽሏል፡፡

2. የአሁን አመልካች ብር 27,840.06 /ሀያ ሰባት ሺህ ስምንት መቶ አርባ ከዜሮ ስድስት ሳንቲም/ እና የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ ከሰጠበት ከ17/6/2006 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ሕጋዊ ወለድ ጋር ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል ብለናል፡፡
3. የአሁን አመልካች በግንባታ ዉሉ መሰረት የገንዘብ መቀጫ፣ የጠበቃ አበል እና ሌሎች ወጪዎችን ለተጠሪ ሊከፍል አይገባም ብለናል፡፡
4. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
5. ግራ ቀኛቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉ ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ፍ

የሰ/መ/ቁ. 136775

ሐምሌ 19 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡-ጸጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሠለ

ሠናይት አድነው

አመልካች፡- ህዳሴ 1ኛ ደረጃ ከፍተኛ አገር አቋራጭ የህዝብ ባለንብረቶች ማህበር

ዳዊት ጌታቸው ነ/ፈጅ

ተጠሪ፡- የፌደራል ትራንስፖርት ባለስልጣን ነ/ፈጁ ብሩክ ሀይሌ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተሻሻለ መተዳደሪያ ደንብ ይመዝገብልኝ ክርክርን ይመለከታል፡፡ ከሳሽ አመልካች ሆኖ በወኪሉ አማካኝነት በተከሳሽ የአሁን ተጠሪ ላይ ለፌደራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ ከሳሽ ማህበር በህግ አግባብ የተቋቋመ በመሆኑ አላማውን ለማሳካት እንዲችል በጠቅላላ ጉባኤው የጸደቀ መተዳደሪያ ደንቡን አሻሽሎ እንዲመዘግብለት በህግ ግዴታ ለተጣለበት ተከሳሽ ቢያቀርብም ተከሳሽ ፍቃደኛ ባለመሆን ያልመዘገበልኝ ስለሆነ ይህንን በጠቅላላ ጉባኤ የጸደቀ መተዳደሪያ ደንብ እንዲመዘግብ እና ወጪ እና ኪሳራ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ፍርድ ቤቱ የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ ተከሳሽ የመተዳደሪያ ደንቡን የሚመዘግበው ወይም የማይመዘግበው በስራ መመሪያው መሰረት ነው፡፡ ስለሆነም ፍርድ ቤት ይህ መተዳደሪያ ደንብ እንዲመዘገብ የሚወስንበት የህግ አግባብ የለም በማለት የከሳሽን ክስ ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ቅሬታው የቀረበለት ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቅሬታው መልስ ሰጪን ያስቀርባል በማለት

አስቀርቦ ሲያከራክር አመልካች በስር ፍርድ ቤት ያነሳውን ክርክር ሲያቀርብ መልስ ሰጪ በስር ፍርድ ቤት ባለመጠራቱ መልስ አልሰጠም ነበር እና በዚህ ክርክር ያነሳው የተሻሻለው መተዳደሪያ ደንቡ ያልተመዘገበው ከሞዴል መተዳደሪያ ደንቡ ጋር የሚቃረን ስለሆነ እና ሞዴል መተዳደሪያደንቡን መሰረት ያላደረገ ማሻሻያ ሊመዘገብ ስለማይገባ ነው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ይህ የመልስ ሰጪ ክርክር በስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር በመሆኑተቀባይነት የለውም በማለት አትቶ በውጤት ደረጃ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በማጽናት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች የሰበር አቤቱታውን ለዚህ የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበው በነዚህ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን መሠረታዊ ይዘቱም፡- የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን በጠቅላላ ጉባኤ የጸደቀ መተዳደሪያ ደንብ እንዲመዘግብ ይወሰንልኝ አቤቱታ የማየት ስልጣን የለኝም በማለት መወሰናቸው ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡

የሰበር አጣሪው ችሎትም ቅሬታው ለሰበር ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክራቸውን በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ ይህ ችሎትም የግራቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ የአመልካችን በጠቅላላ ጉባኤ የጸደቀ መተዳደሪያ ደንብ የተሻሻለ ስለሆነ እንዲመዘግብ ይወሰንልኝ በማለት የቀረበውን አቤቱታ የስር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን የማየት ስልጣንየለንም በማለት መወሰናቸው ተገቢ መሆን ያለመሆኑን በሚከተለው መልኩ መርምረነዋል፡፡

በመሰረቱ አንድ በፍርድ ቤት የቀረበ ጉዳይ የክስ ምክንያት አለው ብሎ ለመወሰንየሚቻለውበክሱ ላይ የተገለፀው ነገር ቢረጋገጥ ከሳሹ የጠየቀውን ዳኝነት ለማግኘት ሕግ ይፈቅድለታል ወይ?የሚለው ጥያቄ ሲነሳ ፍርድ ቤቱ አዎንታዊ ምላሽ ለመስጠት የሚችል የሆነ እንደሆነ ስለመሆኑበዚህ ረገድ የተፃፉት የማብራሪያ ፁሑፎች ያሳያሉ፡፡

ትራንስፖርትን ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ ቁጥር 468/1997አንቀጽ 15 (2) ስር በትራንስፖርት የስራ ዘርፍ የተሰማሩ ማህበሮችበጠቅላላ ጉባኤ የጸደቀ መተዳደሪያ ደንብ ሲያሻሽሉበተጠሪ እንደሚመዘገብተደንግጎ ይገኛል፡፡ስለሆነም ማንኛውም የትራንስፖርትማህበር የማህበሩን አላማ ለማሳካት በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ወጥቶ የጸደቀውን መተዳደሪያ ደንብ ካሻሻለ በተጠሪ ባለስልጣን መ/ቤት አቅርቦ ማስመዝገብ አለበት፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስአመልካች በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የጸደቀ መተዳደሪያ ደንብ በመሻሻሉ በተጠሪ እንዲመዘገብጥያቄ ማቅረቡየሕግ አግባብ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች

እንዲመዘገብለት ለተጠሪ ቢያቀርብም መ/ቤቱ ለመመዝገብ ፍቃደኛ ያለመሆኑን በመግለጹ በፍርድ ቤት ትእዛዝ እንዲመዘገብ ይወሰን ዘንድ የቀረበውን አቤቱታ የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን የማየት ስልጣን የፍርድ ቤቶች አይደለም በማለት ድምዳሜ ላይ ደርሰው አቤቱታውን ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡

በኢፌድሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37(1)ስር እንደተመለከተው ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብ እና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት እንዳለው ይደነግግ እና በዚሁ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (2) ስር ደግሞ ማንኛውም ማህበር የአባላቱን የግል ወይም የጋራ ጥቅም በመወከል የመጠየቅ እና ፍትህ የማግኘት መብት እንዳለው ደንግጓል፡፡

አመልካች የተሻሻለው መተዳደሪያ ደንብ እንዲመዘገብለት ለሚመለከተው አካል አቅርቦ ተቀባይነት ማጣቱ አስከተረጋገጠ ድረስ መብቱን ያጣው በህግ አግባብ መሆን ያለመሆኑ ሊመረመር የሚገባው በመሆኑ አመልካች ይኸው እንዲመረመርለት ያቀረበውን አቤቱታ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪን አስቀርቦ መልስ እንዲሰጥበት እንኳን ሳያደርግ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠውን ውሳኔጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት ከፍተኛ ፍርድ ቤት በቀረበለት የይግባኝ ቅሬታ መነሻነት ይህንን የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ ማረም ሲገባው ባለማረም የሰጠው ውሳኔ ስለክስ ምክንያት አጠቃላይ መንፈስ እና ይዘት በሕጉ ላይ የተመለከተውን መመዘኛንያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚሁም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ.237969 መጋቢት 23 ቀን 2008 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 176926 ጥቅምት 30 ቀን 2009 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ስለሆነም ጉዳዩ በፍርድ ቤት የሚታይ ነው ብለናል፡፡
3. የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ተጠሪ መ/ቤት በቀረበው ክስ ላይ መልስ እንዲሰጥ በማድረግ አመልካች ማህበር እንዲመዘገብለትያቀረበውን የተሻሻለ መተዳደሪያ ደንብ ተጠሪ መ/ቤት አልመዘግብም በማለት የወሰነው በአዋጁ እና በመመሪያው መሰረት መሆን ያለመሆኑን አጣርቶ የመሰለውን ይወስን ዘንድ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 341(1) መሰረት ይመለስ ብለናል፡፡

4. የውሳኔው ግልባጭ በየደረጃው ለሚገኙ የስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡
5. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፋ/ዘ

# ንብረት

የ ሰ/መ/ቁ. 102406

ሕዳር 9 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተክሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጠታ

ክፍለጽዮን ማሞ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- የወንጂ ሸዋ ስኳር ፋብሪካ

ተጠሪ፡- አቶ ባጫ አለሙ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ከተጠሪ ጋር ያለውን የመሬት ይዞታ ክርክር በተመለከተ በሽማግሌዎች ታይቶ የካቲት 17 ቀን 2005 ዓ/ም ውሳኔ ከሰጡበት በኋላ በአዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 1/መ/ እና /ሠ/ በተደነገገው የሰላሳ ቀናት የይርጋ የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ ሚያዚያ 30 ቀን 2005 ዓ/ም ክስ ያቀረበ በመሆኑ፣ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት የሰጡት ብይን አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡
2. የክርክሩ መነሻ አመልካች ለአዳማ ልዩዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው የክስ ማመልከቻ ነው፡፡ ከሳሽ/አመልካች/ ከምስራቅ ሸዋ ዞን ከተማ ልማት ጽ/ቤት በህጋዊ ካርታ ተረክቦና የሸንኮራ አገዳ አልምቶ ከሚጠቀምበት የይዞታ መሬት ተከሳሽ /ተጠሪ/ ስፋቱና መጠኑ እንደዚሁም አዋሳኝ ምልክቱ በክስ ማመልከቻው የተገለጸውን ሸንኮራ አገዳ ተክልና የይዞታ መሬት ከሀምሌ 1 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ በመያዝ ሁከት እየፈጠረብኝ ስለሆነ ሁከቱ እንዲወገድ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ ጉዳዩ በሽማግሌዎች ታይቶ ውሳኔ ከተሰጠውና ውሳኔው በቀበሌው አስተዳደር ከተመዘገበ በኋላ በህጉ የተመለከተው የሰላሳ ቀናት የይርጋ ጊዜ ካለፈው ያቀረበ ስለሆነ በይርጋ ቀሪ ይሆናል የሚል

መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአመልካችን ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት የተጠሪን መቃወሚያ በመቀበል ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡

3. አመልካች በዚህ ሰበር ችሎት ሰኔ 25 ቀን 2006 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የሸንኮራ ተክልና የመሬት ይዞታ ክርክር በጅምሩ በኦሮሚያ ክልል ምክር ቤት በወጣው አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀጽ 16 መሰረት ለአስማሚ ሽማግሌ የሚቀረብ አይደለም፡፡ ጉዳይ ስለ ዕርቅ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች የሚያሟላ አይደለም፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ አስታራቂ ሽማግሌዎቹ ውሳኔ በሰጡ በሰላሳ ቀናት ክስ ያላቀረብክ ስለሆነ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ መስከረም 1 ቀን 2007 ዓ/ም በተፃፈ መልስ፣ አመልካች ጉዳዩ በሽማግሌ እንዲታይለት ከጠየቀ በኋላ የቀበሌው አስተዳደር ሽማግሌዎች መድቦ ጉዳዩ ታይቶ ከተወሰነ በኋላ በስልሳ ቀን ውስጥ ክሱን ያላቀረበ በመሆኑ ለዚህ ሰበር ችሎት የቀረበው ቅሬታ የህግ መሰረት የለውም በማለት መልስ ሰጥቷል አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

4. ከስር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው፣ የኦሮሚያ ክልል ምክር ቤት ባወጣው አዋጅ ቁጥር 130/99 አንቀጽ 16 ግጭትና አለመግባባት በመጀመሪያ በአስታራቂ ሽማግሌዎች እንደፊቱ የሚደነግጉ ድንጋጌዎች መሰረታዊ ዓላማ በሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ አርሶ አደሮች መካከል በእርሻ መሬት ይዞታ ምክንያት የሚነሳ አለመግባባት፣ ጉዳዩን በቅርብ አይተውና ተመልክተው፣ወደ ሙግት ሳይገባ በሽማግሌዎች የሚፈቱበትን ስርዓት ለመዘርጋትና አርሶ አደሩ በመሬት ይዞታ ግጭት ምክንያት ለምርት ስራ የሚያውለውን ጊዜ በፍርድ ቤት ክርክር እንዳያሳልፍ ለማድረግ ነው፡፡ የዚህ አዋጅ ድንጋጌ የፌዴራል መንግስት ካወጣው አዋጅ ቁጥር 456/97 ድንጋጌዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ መተርጎም ያለባቸው መሆኑ የሚያከራክር ነጥብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

5. የክልሉ ም/ቤት ያወጣው የአዋጅ ቁጥር 130/99 አንቀጽ 16 ድንጋጌዎች በፌዴራል ወይም በክልል ደረጃ የተመዘገበና ህጋዊ እውቅና ያገኘ ህግ ወለድ ሰው ከአንድ አርሶ አደር ጋር በመሬት ድንበር ወይም ይዞታ ጥያቄ ምክንያት በሚፈጥር አለመግባባት የሚያገለግል እንዳልሆነ በአዋጅ ድንጋጌዎች መሰረታዊ ዓላማ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ የአሁን አመልካች በህጋዊ ካርታ ተረክቦ ለስኳር ምርት ካለማው ልማትና ሸንኮራ አገዳ ተክል ተጠሪ እንዲለቅለት ክስ ለማቅረብ፣ ጉዳዩ በመጀመሪያ በሽማግሌዎች

የማሳየት ኃላፊነት ቅድመ ሁኔታ የለበትም፡፡ ይርጋውም ጊዜ የሚቆጠረው በቀበሌ አስተዳደር የተመደቡ አስታራቂ ሽማግሌዎች ውሳኔ ከሰጡበት ጊዜ ጀምሮ ሳይሆን ተጠሪ የሽንኮራ እርሻውን በሀይል ይዟል ከተባለበት ሀምሌ 1 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ መሆን አለበት፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች ክስ ያቀረበው ተጠሪ በይዞታው ላይ ሁከት ከፈጠረበት ጀምሮ በህግ የተደነገገው የይርጋ የጊዜ ገደብ ከማለፍ በፊት ማለትም ሀምሌ 25 ቀን 2005 ዓ/ም በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች አግባብነት የሌለውን የኦሮሚያ ክልል አዋጅ ቁጥር 130/99 አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀፅ 1/1/ ጠቅሰው የአመልካች ክስ በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 16577 ጥቅምት 2 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 172112 ሰኔ 11 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ይዞታውን ለማስከበር ያቀረበው ክስ በይርጋ ቀሪ አልሆነም በማለት ወስነናል፡፡
3. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ የሚያቀርቡትን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ስ/ስ/ህግ/ቁ/ 341/1/ መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ፍ

የሰ/መ/ቁ.100395

ሕዳር 29 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

ቀነዓ ቂጣታ

ሡናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች ወ/ሮ አማረች ማሬ ጠበቃ ማስታወል ሀብታሙ ቀረበ

ተጠሪዎች፡- 1. ወ/ሮ ሜሪ ታደሰ

2. ወ/ሪት ፈጣኑ ታደሰ

3. ወ/ሪት ሮማን ነስሩ

} ጠበቃ ሀይሉ ዓይናለም ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ተጠሪዎች እየኖሩበት ያለውንና በ 300 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያረፈ ቤት ለቅቀው እንዲያስረክቧት የመጠየቅ መብት የላትም ንብረቱን የሸጠችላትን ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት ከስሳ ትጠይቅ በማለት የሰጡት ውሳኔ አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ጭብጥ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪዎች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል ፡፡
2. ከሳሽ ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት የመፈላም ክስ ነው ከሳሽ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በቀበሌ 03 የቤት ቁጥር 287 የግል ሀብቴ ስለመሆኑ በክፍሉ አስተዳደር የባለሀብትነትና ባለይዞታነት ማረጋገጫ ማስረጃ (ካርታ) በእጄ ይገኛል፡፡ ተከሳሾች ከቤቱ

ውስጥ በጥገኝነት እንዲኖሩ ፈቅጄላቸው ሲኖሩ ቆይተዋል ፡፡ አሁን ግን ቤቴን እንዲለቁ ብጠይቃቸው ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ፍርድ ቤቱ ተከሳሾች ቤቴን እንዲለቁና እንዲያስረክቡ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ክስ አቅርባለች

3. ተጠሪዎች በተከሳሽነት ቀርበው እኛ በከሳሽ ቤት በከሳሽ ፈቃድ በጥገኝነት የምንኖር ሰዎች አይደለም ፡፡ ተከሳሾች በእጃችን አድርገን ይዘን እየኖርንበት ያለው ቤትና ይዞታ አያታችንና እናታችን ከዛሬ አርባ ዘጠኝ ዓመት ጀምሮ ይዘውት ሲኖሩበት የነበረ ቤት ነው፡፡ተከሳሾች ከአያታችንና ከእናታችን ጋር ክስ ያቀረበበትን ቤት ይዘን ስንኖር ፣ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት በአያታችን ባዶ የይዞታ ቦታ ላይ በአንድ በኩል ቤት ሠርታ ስትጠቀም ቆይታ ፣ቤቱን ለአሁን ከሳሽ ሸጣለታለች ሆኖም እኛ የምንኖርበት ቤት ወ/ሮ ሂሩት አበራሽ በእጇ አድርጋ ይዛው የማታውቅና የራሱ የሆነ ይዞታና የወሰን አጥር ያለው በመሆኑ ከሳሽ ቤቱን ለከሳሽ የሸጠችውም ሆነ ከሳሽ የእኛን ቤትና ይዞታ በማጠቃለል እንዴት ካርታና ፕላን እንዳወጡ የክፍሉ አስተዳደር እንዴት የእኛን ቤትና ይዞታ በማጠቃለል እንዴት ካርታና ፕላን እንደሰጠ ይጠየቅልን በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የክፍሉ አስተዳደር ተገቢዉን ማጣሪያ በማድረግ መግለጫ እንዲሰጥ ትዕዛዝ የቤቱ ስመ ሀብትና ከወ/ሮ እህተ ገብረማርያም ሂሩት አበራሽ ስም ሂሩት ስም የተዛወረዉ በስር ትዕዛዝ ፋይል ቁጥር 139/84 መስከረም 25 ቀን 1985 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ መሠረት እንደሆነና ከዚያ በኃላ ሂሩት አበራሽ በውልና ማስረጃ ከከሳሽ ጋር በተዋዋለችው የቤት ሽያጭ ውል 1189 ሜትር ካሬ ላይ ያረፈው ቤትና ይዞታ በከሳሽ ስም እንዲዘዋወር ተደርጎ ከሳሽ የባለሀብትነት ማስረጃ የሰጠ መሆኑን ተረጋግጧል ፡፡

4. የሥር ፍርድ ቤት የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ በወ/ሮ አበራሽ ሂሩት ወ/ሮ እህተ ገብረማሪያም ጋር ባደረጉት የቤት ሽያጭ ውል የገዙት ዋናውን ቤት የቤት ቁጥር 287 እንደሆነ የሚገልፅ ቢሆንም ገዥ ይህንን ዋናውን ቤት ተረክበውና በእጃቸው አድርገውት አያውቁም ፡፡ ወ/ሮ ሂሩት አበራሽ ገብተውና ከሻጭም ተረክበው.ይኖሩ የነበሩት ሰርቪስ ቤትና በባዶ ይዞታ ላይ ራሳቸው የሠሩትን ቤት ነው ፡፡ ገዥ ገዥቻለሁ የሚሉትን የቤት ቁጥር 287 በ 300 ካሬ ሜትር ላይ 1984ዓ.ም ጀምሮ ተረክበውና በእጃቸው አድርገውት አያውቁም ነገር ግን የሻጭን መሞት ምክንያት በማድረግ ይህንን 1984ዓ.ም ተረክበውና ይዘው የማያውቁትን ቤት ጨምሮ በሽያጭ ውሉ መሠረት ተረክበው የሚኖሩበትን ይዞታ ላይ ያለው ቤት ስመሀብት እንዲዛወርላቸው በማድረግ የባለሀብትነት ማስረጃ ተሰጥቷቸዋል ፡፡ ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት በፍርድ ቤት ውሣኔ መነሻ የተሰጣቸውን የባለሀብትነት ሰነድ በማየት ፣ከሟች እህት ገ/ማሪያም ቤቱን ከገነባች ጀምራ ተረክባና በእጇ አድርጋ የማታውቀውን የቤት ቁጥር 287 ዋናውን ቤት በ 300ካሬ ሜትር እንዳለፈ ፣በእጇ አድርጋ ስታካብት ከኖረችው ቤት ጋር አንድ ላይ

ለከሳሽ ሸጣ ቤቱና ይዞታው በተከሳሾች እጅ ባለበት ከሳሽ በሻጭ ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት እጅ ባልነበረና ሆኖ በማያውቅ ቤትና ይዞታ ላይ ጭምር የባለሀብትነት ማስረጃ አውጥታለች ። ይህም ለከሳሽ ቤቱን የሸጠችው ወ/ሮ ሂሩት አበራሽ ተከሳሾች ይዘው የሚኖሩበትን ቤትና የይዞታ ቦታ በሽያጭ ውሉ መሠረት ያላስረከበቻትና ቤቱና ይዞታው በተከሳሽ እጅ ባለበት የሰነድ ርክክብ ብቻ ያደረገች መሆኑን ስለሚያሳይ ከሳሽ ሻጭዋን ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት እንጂ ተከሳሾች ቤቱን  እንዲያስረክቧት መክሰስ አትችልም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል ።

ይህንን ውሣኔ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ እንዲያየው አመልካች ጠይቃ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አፅንቶታል።

5. አመልካች ሚያዝያ 27 ቀን 2008ዓ.ም አመልካች አከራካሪውን ቤት በውል ገዝታ የንብረት ባለሀብት መሆኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃ አባት ይህ ከሆነ ንብረቷ እንዲለቀቅ የመክሰስ መብት የላትም በማለት መወሰኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው። የበታች ፍርድ ቤቶች ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ጭብጦችን አልመሰረቱም ተጠሪዎች ቤቱን በጥገኝነት ስለመያዛቸው ለቀበሌ ለአስተዳደር አመልክተዋል በሻጭና በከሳሽ መካከል የተደረገው ውል ተጠሪዎችን የሚመለከት አይደለም ። አመልካች የቤቱ ሻጭ በዋቢነት እንድትቀርብላት ሣትጠራ ፣ንብረቱ ላይ ያገኛቸው የባለሀብትነት መብት ለማስከበርና ለመፋለም የሚከለክላት ህግ በሌለበት ሁኔታ የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን ክስ ውድቅ ማድረጋቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው ያለበት ነው በማለት አመልክታለች ።
6. ተጠሪዎች በመጀመሪያም ሂሩት አበራሽ ከሚች አያታችን እህተ ገ/ማሪያም ጋር ያደረጉት የሽያጭ ውል አስመልክቶ ለአውራጃው ፍርድ ቤት ክስ ስታቀርብ ሚች የሸጠችላትን ቤት እጇ አድርጋና ተረክባ እየኖረችበት መሆኑን ገልፃለች። ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት እኛ የምንኖርበትን ቤትና በአዋሳኝ አጥር ታይቶ ያለውን 300 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ተረክባም ሆነ ይዛው አታውቅም ። እኛ በማናውቀው ሁኔታ የእኛን ቤትና ይዞታ ካርታና ፕላን ማውጣቷና ለከሳሽ መሸጧ ከሳሽን የቤቱ ባለመብት አያደርጋትም ። የባለሀብትነት ካርታና ማስረጃውም በክፍሉ አስተዳደር የታገደ በመሆኑ ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት መልስ ሰጥተዋል ። አመልካችዎች የመልስ መልስ አቅርበዋል ። ግራቀኙ የሚያከራክራቸውን ጭብጥ ለመረዳት ችሎቱ የግራቀኙን የቃል ክርክር ሰምቶ የቃል ክርክሩ ከትራንስክራይበር ማሽን ተገልብጦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል ። የክፍሉ አስተዳደር በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የፃፈውን  መግለጫ ለማየት የፌዴራል ከፍተኛ

ፍርድ ቤት የመዝገብ ቁጥር 135280 እንዲቀርብ በታዘዘው መሠረት መዝገቡ ቀርቦ ተያይዟል ፡፡

7. ከሥር የክርክሩ አመጣጥ በዚህ ሰበር ችሎት ግራቀኙ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀ ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች በተጠሪዎች ላይ ቤቱና ይዞታው እንዲለቀቅላቸው ክስ ያቀረቡት ተጠሪዎች የሚኖሩበትን ቤትና ይዞታና ከሻጭ ተረክበው የያዙትን ቤትና ይዞታ በድምሩ 1139 ካሬ ሜትር ላይ ያሉትን ቤቶችና ይዞታ በብር 120,000 የካቲት 3 ቀን 1997 ጋብቻ የቤቱ ስመሀብት የተሰራልኝ በመሆኑ ተከሳሾች (ተጠሪዎች) የግል ሀብቴና ንብረቴ የሆነውን ቤትና ይዞታ ይለቀቅልኝ በማለት ነው፡፡ ተጠሪዎች የሚከራከሩበት ከሳሽ የቤትና ይዞታውን ባለቤትነት መብት በሽያጭ አስተላልፋልኛለች የምትሉት አበራሽ ሂሩት እኛ የያዝነውን ቤትና 300 ካሬ ሜትር ይዞታ ለከሳሽ በሽያጭ ለማስተላለፍ መብት የላትም ፡፡ ከሳሽ እኛን ከመጠየቋ በፊት በሽያጭ ውሉ መሠረት እኛ የምንኖርበትን ቤትና 300 ካሬ ሜትር የይዞታ ቦታ ሻጭ ነፃ አድርጋ እንድታስረክባትና የሽያጭ ውሉን እንድትፈፅምላትና ከምትጠይቅ በስተቀር ከሳሽ የሽያጭ ውሉ ሙሉ በሙሉ እንደተፈጸመላትና ንብረቱንም ከሻጭ እንደተረከበች አድርጋ በመቁጠር በቀጥታ እኛን ከቤት እንድንወጣ የመጠየቅና ክስ የማቅረብ መብት የላትም በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ተረድተናል፡፡

8. ግራቀኙ በሥር ፍርድ ቤትና በዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት ክርክር አመልካችና ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት ውል ለማዋዋል ሥልጣን ባለው አካል ፊት የካቲት 3 ቀን 1997 ዓ.ም የተዋዋሉት የቤት ሽያጭ ውል ሻጭ ሙሉ ለሙሉ ፈፅማለች ወይስ አልፈፀመችም ሻጭ በሽያጭ ውሉ መሠረት ግዴታዋን ሙሉ በሙሉ ካልፈፀመችና ውሉን በከፊል የፈፀመች መሆኑ ቢረጋገጥ ገዥዋ ሻጭ ቀሪውን ግዴታዋን እንድትፈፅምላት በሻጭ ላይ ክስ ሣታቀርብ ወይም በተከሳሽነት አጣምራ ሳትከስ የውሉ ተዋዋይ ያልሆኑ ሶስተኛ ወገኖች ላይ በቀጥታ ክስ በማቅረብ ትችላለች ወይስ አትችልም ?የሚሉት ነጥቦች መታየት ያለባቸው ናቸው፡፡

9. ከላይ ከተገለፁት ነጥቦች አንፃር ስንመለከተው የማይንቀሳቀስ ንብረት የሸጠ ሰው የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል የገባውን ግዴታ የሚፈፅምባቸው ሁለት መሠረታዊ ኃላፊነቶች አሉ፡፡ የመጀመሪያው ሻጭ በሸጠው የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ በአንዱ ወይም በሌላ መልኩ ስፍራው የሚገኙ ሰዎች የተሸጠውን የማይንቀሳቀስ ንብረት እንዲለቁ በማድረግ የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ይዞታ ከሌሎች ሶስተኛ ወገኖችና ከሻጭ ቁጥጥርና ይዞታ ነፃ በማድረግ የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ለገዥ ማስረከብ እንደሆነ ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2875 እና ከፍትሃብሄር ህግ ቁጥር 2274 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ ለመረዳት ይቻላል ሻጭ ከዚህ በተለየ ሁኔታ በማይንቀሳቀሰው ንብረት ርዕስ

መዝገብ ላይ የተመዘገበና ገዢውንም ሊያስገድዱ የሚችሉ የሶስተኛ ወገኖች መብት በሰጠው የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ ካሉ ይህንኑ የሶስተኛ ወገኖች መብት ካለ ሻጭ ለገዥ ማስታወቅ ያለበት መሆኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2880 እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2881 ተደንግጓል ።

10. የሻጭ የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ከሶስተኛ ወገን ይዞታና ቁጥጥር ነፃ በማድረግ የማስረከብ ግዴታ ገዥ ለሻጭ ከሚሰጠው የመነቀል ዋስትና ግዴታ የተለየ ነው ። ሻጭ በንብረቱ ላይ ያስፈሩና በንብረቱ መዝገብ የተመዘገበ መብት የሌላቸውን ሰዎች የማይንቀሳቀሰውን ንብረት እንዲለቁ በማድረግ ለሻጭ የማስረከብ ግዴታ የማይንቀሳቀስ ንብረት ውል በመፈፀም ሂደት ገዥ ሻጭ ሊያከናውነው የሚገባ የመጀመሪያ ግዴታ ሲሆን በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2882 እና ተከታይ ድንጋጌዎች መሠረት ሻጭ ለገዥ የሸጠለት የማይንቀሳቀስ ንብረት የማይነቀል ስለመሆኑ የሚሰጠው ዋስትና ገዥ የገዛውን የተረከበውን የማይንቀሳቀስ ንብረት ከሌሎች ሰዎች ቁጥጥር ነፃ ሆኖ ከተረከበ በኃላ ንብረቱ የእኔ ነው ባይ ቢመጣ ሻጭ በዋቢነት ሊቆምለት የሚገባ መሆኑን የሚያመለክቱ ድንጋጌዎች ናቸው።

11. የማይንቀሳቀስ ንብረት የሸጠ ሰው ንብረቱን ከሌሎች ሰዎች ቁጥጥር ይዞታ ሥር ነፃ አድርጎ በማጓጓዝ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2875 እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2274 መሠረት የማስረከብ ግዴታ ያለበት ከመሆኑ በተጨማሪ የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ባለሀብትነት ለማስተላለፍ የሚችሉ አስፈላጊ ሰነዶች ለገዢ የማስረከብና የማይንቀሳቀሰ ዉን ንብረት የማይነካ የባለሀብትነት መብት ለገዥ ለማስተላለፍ አስፈላጊ የሆነ ተግባራትን የመፈጸም ግዴታ መሆኑ በፍትሀብሄር ህግ ቁጥር 2875 በፍትሃብሄር ህግ ቁጥር 2879 ንኡስ  አንቀጽ 1 እና የፍትሃብሄር ህግ ቁጥር 2281 ድንጋጌዎችን በጣምራ በማየት ለመረዳት ይቻላል።

12. ከላይ በዝርዝር ካየናቸው የህግ ድንጋጌዎች አንጻር ሲታይ 1139 ካሬ ሜትር የይዞታ ቦታ ላይ ያረፈውን የማይንቀሳቀስ ንብረት ሙሉ በሙሉ ለአመልካች የሸጠችው ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት፣በሽያጭ ውሉ መሰረት የማይንቀሳቀስውን ንብረትና ይዞታውን ከሌሎች ሰዎች ቁጥጥርና ይዞታ ስር በማስለቀቅ የማይንቀሳቀስ ንብረትና ይዞታውን በፍትሃብሄር ሕግ ቁጥር 2875 በፍትሃብሄር ሕግ ቁጥር 2274 እና በፍትሃብሄር ሕግ ቁጥር 2888 መሰረት ለገዥ(ለአመልካች)የመፈጸም ግዴታውን የተወጣችው ሙሉ በሙሉ ሳይሆን በከፊል ነው።ሻጭ ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት ተጠሪዎች የሚኖሩበትን ቤትና 300 ካሬ ሜትር ይዞታ.ከተጠሪዎች አውራሽ ንብረቱን ገዛሁ ከምትልበት 1984 ዓ.ም ጀምሮ ተረክበውና በእጇ አድርጋው የማይታወቅ መሆኑና፣ቤቱን ለአመልካች ከሸጠችላት በኂላ ተጠሪዎች የሚኖሩበትን ቤትና ይዞታ፣ ተጠሪዎች በህግ አግባብ እንዲለቁ በማድረግ ለአመልካች

ያላስረከበችበት አመልካችም በሽያጭ ውሉ የተገለጸውን ቤትና ይዞታ ሙሉ በሙሉ ሳይሆን፣ሻጭ(አበራሽ ሂሩት)ይዛው የነበረውን ቤትና ይዞታ ብቻ ከሻጭ የተረከበች መሆኑን ተረድተናል፡፡

13. ገዥ ሻጭ በሽያጭ ውሉ የገለጸችውን የማይንቀሳቀስ ንብረትና ይዞታ፣ ተጠሪዎች የሚኖሩበት ቤትና ይዞታ ሳይጨምር በሻጭ እጅና ይዞታ ስር ያለውን ቤትና ይዞታ የተረከበች ቢሆንም፣ሻጭ የሰጠቻትን ሰነድ በመጠቀም በሽያጭ ውሉ ላይ የተመለከተውን የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለመብት መሆኗን የሚሳይ ማስረጃ ከክፍሉ አስተዳደር ተሰጥቷታል፡፡ይህም ገዥዋ(አመልካች)ከሌሎች ሰዎች ይዞታና ቁጥጥር እንደዚሁም የመብት ጥያቄ ነጻ ሆኖ ከሽያጭ ያልተረከበችውን ተጠሪዎች የሚኖሩበት ቤትና ይዞታ ባለመብት መሆኗን የሚያረጋግጥ የባለሀብትነት ማስረጃ የተሰጣት መሆኑን ያሳያል፡፡አመልካች የቤቱ ባለሃብትነት መብት በሽያጭ ውል ከወ/ሮ አበራሽ ሂሩት የተላለፈላት መሆኑን የሚያሳይ የሽያጭ ውል ሰነድና በሽያጭ ውሉ መሰረት በማይንቀሳቀሰው ንብረት ባለሀብትነት የተዛወረላት መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ በማያያዝ በፍትሃብሄር ህግ ቁጥር 1206 መሰረት ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብትና ጥቅም አላት፡፡ነገር ግን አመልካች ባቀረበችው የክስ መነሻ አከራካሪ ሆኖ የተገኘው ጭብጥ፤(ሀ) ቤቱን ንብረቴ ነው ካለ ለአመልካች የሸጠችው ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት አከራካሪውንና ተጠሪዎች የሚኖሩበትን ቤትና ይዞታ ባለሃብትነት መብት ለአመልካች የማስተላለፍ እርግጠኛ የሆነ የባለሀብትነት መብት በንብረቱ ላይ አላት ወይስ የላትም?

(ለ)ሻጭ ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት የተጠሪዎች የሚኖርበትን ቤትና 300 ካሬ ሜትር ይዞታ ጨምራ የባለሀብትነትን ማስረጃና ካርታ የሰራችው በህግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም?አመልካችስ 1139 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያለው የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትና ባለይዞታ መሆኗን የሚያረጋግጥ የባለሀብትነት ማስረጃና ካርታ የተሰጣት በህግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም?(ሐ)ተጠሪዎች እየኖሩበት ያለውን ቤትና 300 ካሬ ሜትር ይዞታ ቦታ ለአመልካች የመልቀቅና የማስረከብ ግዴታ አለባቸው ወይስ የለባቸውም?የሚሉት ለአመልካች 1139 ካሬ ሜትር የይዞታ ቦታ ላይ ያለውን የማይንቀሳቀስ ንብረት በሽያጭ ውል አስተላልፋለች የተባለችው ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት በክርክሩ ተሳታፊ ስትሆን ውሳኔ ሊሰጥባቸው የሚችሉ ጭብጦች አይደሉም፡፡

14. የስር ፍርድ ቤት አመልካች የቤቱ ሻጭ የሆነችውን ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት ከሚከሰሱ በስተቀር በቀጥታ ተጠሪዎች ቤቱን እንዲለቁለት ክስ ማቅረብ አትችልም በማለት የሰጠው ውሳኔ ሻጭ በሽያጭ ያስተላለፈው ንብረት ላይ ያለውን መብትና ጥቅም ለማስከበር ገዥው ከውል የመነጨ መብት ያለው መሆኑን ያላገናዘበና የፍትሃብሄር ህግ ቁጥር 1195 የፍትሃብሄር ህግ ቁጥር 1206 እና የፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 33(2)

ድንጋጌዎች ያላገናዘበ በመሆኑ ስህተት ያለበት ነው፡፡ነገር ግን የበታች ፍርድ ቤቶች ቤቱን ለአመልካች የሰጠችው ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት በክርክሩ ተከሳሽ መሆን አለባት በማለት የደረሱበት ድምዳሜ የፍትሃብሄር ህግ አንቀጽ 2875፣ አንቀጽ 2274፣አንቀጽ 2888 እና የፍትሃብሄር ስነ-ስርዓት ህግ ቁጥር 40 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ በመሆኑ ፍርድ ቤቶች ሻጭ ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት በጉዳዩ ተከሳሽ መሆን አለባት በማለት የደረሱበት መደምደሚያ በውጤት ደረጃ የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

15. የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች የቤቱን ሻጭ ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት መክሰስ አለባት ካሉ በኋላ፣ይህ ውሳኔአቸው የሚያስከትለውን ህጋዊ ውጤት ሳይመዝን ተጠሪዎችን ከክስ ማሰናበታቸው አግባብነት ያላቸውን የስነ-ስርዓት ህግ ድንጋጌዎች የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም አመልካች ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት በሽያጭ ውሉ መሰረት ተጠሪዎች የያዙትን ቤት አስለቅቀው ታስረክበኝ የሚል ክስ ስታቀርብ በማይንቀሳቀሰው ንብረት ላይ በማናቸውም ሁኔታ የሚገኙ ሰዎችን በተከሳሽነት አጣምራ መክሰስ እንዳለባት የፍትሃብሄር ስነ-ስርዓት ህግ ቁጥር 36 ንዑስ አንቀጽ 4 አስገዳጅ በሆነ ሁኔታ ይደነግጋል፡፡ይህም አመልካች ሻጭዋን ወ/ሮ አበራሽ ሂሩትን በምትከስበት ጉዳይ ተጠሪዎች የግድ በተከሳሽነት እንዲሳተፉ ማድረግ የሚገባ መሆኑ በህግ የተደነገገ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ከሳሽ ዳኝነት ከፍላ ያቀረበችውን ክስ የቤቱ ሻጭ በጉዳዩ የመጀመሪያ ተከሳሽ መሆን አለባት በሚል ምክንያት ዘግቶ አመልካችን ከሚያሰናብት፣በጉዳዩ የቤቱ ሻጭ በክርክሩ በተከሳሽነት ተሳታፊ እንድትሆን በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 40 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ትዕዛዝ መስጠት በዚህ ፍርድ አንቀጽ ተራ ቁጥር 13 በተመለከቱና በሌሎች ጭብጦች ላይ አመልካች (የቤቱ ገዥ)፣ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት ሻጭና በአከራካሪውን ቤትና ይዞታ ይዘው የሚኖሩት ተጠሪዎች የሚያቀርቡትን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ መወሰን ሲገባው፣አመልካች ተጠሪዎችን የመክሰስ መብት የላትም በማለት መዝገቡን መዝጋቱና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ማጽናቱ ከላይ በዝርዝር የጠቀስናቸውን የህግ ድንጋጌዎችና የዳኝነት አካሄድ ስርዓት ያልተከተለና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 66605 የካቲት 29 ቀን 2005 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመዝገብ ቁጥር 135280 መጋቢት 2 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወ/ሮ አበራሽ ሂሩት በተከሳሽነት በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 40 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት በመጨመር፣በዚህ ፍርድ በተራ

ቁጥር 13 የተመለከቱትንና ሌሎች አከራካሪ ጭብጦች ላይ ግራ ቀኙ የሚያቀርቡትን ክርክርና ማስረጃ በማሰማትና ተገቢውን ማጣራት በማድረግ ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 343(1) መልሰን ልከንለታል፡፡

3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ጌ

የሰ/መ/ቁ.120087

ታህሳስ 7 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

አብዪ ካሣሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡-አቶ አስራት ኩምሳ - ጠበቃ ረጅብ ኡስማን ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-

1. አቶ ጉደታ በዳዳ
2. አቶ ገነነ ከበደ

} ጠበቃ ባይሳ ዲንሳ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩከገጠር መሬት የተገኘ ነው የተባለን አላባ ለማስከፈል ከቀረበ ክስ ጋር ተያይዞ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡት በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 29557 በ04/03/2006 ዓ.ም ተሰጥቶ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ ታይቶበመዝገብ ቁጥር 170570 በ30/07/2006 በፍርድ የጸናውን ውሳኔ በመሻር ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች ቀደም ሲል በመሬት ይዞታው ላይ የይገባኛል ክስ ባቀረቡበት ጊዜ አሁን በመዝገብ ቁጥር 29557 ክስ ያቀረቡበትንም የአላባ ጥቅም አካተው መክሰስ ሲችሉ ነጥለው በማስቀረት አሁን አዲስ ያቀረቡት ክስ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 216 (4) እና 218 ድንጋጌዎች መሰረት ተቀባይነት የሌለው ሆኖ እያለ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ ከተጠሪዎቹ የቀረበውን መቃወሚያ ተቀብሎ መዝገቡን መዝጋት ሲገባው ወደ ፍሬ ጉዳይ ክርክሩ ገብቶ ውሳኔ መስጠቱ እና ውሳኔው በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ተቀባይነት ማግኘቱ ተገቢነት የለውም በማለት የክልሉ ጠቅላይ

ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 185098 በ22/02/2008 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

ክርክሩ በተጀመረበት ፍርድ ቤት ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ አመልካች ሲሆኑ ክሱን ያቀረቡትም በአሁኖቹተጠሪዎች ላይ ነው፡፡በ14/09/2005 ዓ.ም. ተዘጋጅቶ የቀረበው ክስ አጭር ይዘትም ተጠሪዎቹ የአመልካች ሕጋዊ ይዞታ የሆነውን እና አዋሳኞቹ በክሱ ላይ የተጠቀሰውን አስር ሄክታር የሳር መሬት ምንም መብት ሳይኖራቸው በ1993 ዓ.ም.በመያዛቸው አመልካች ይዞታውን ለማስለቀቅ በቀርሳና ማሊማ ወረዳ ፍርድ ቤት የመሰረቱት ክስ ውድቅ የተደረገ ቢሆንም በይግባኝ ለደቡብ ምዕራብሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትአቅርበው ተጠሪዎቹ ይዞታውን እንዲለቁ በመዝገብ ቁጥር 24028 በ08/02/2004 ዓ.ም.ውሳኔ የተሰጠ መሆኑን፣ተጠሪዎቹ በይዞታው ከ1993 ዓ.ም.ጀምሮ እስከ 2005 ዓ.ም. ድረስ ለአስራ ሁለት ዓመታት የተገለገሉበት መሆኑን፣ከይዞታው በዓመት ግምቱ ብር አምስት ሺህ የሆነ ሳር የሚገኝ መሆኑን የሚገልጽ ሆኖ ተጠሪዎቹ የ12 ዓመታትን አላባ ብር 60,000 (ስድሳ ሺህ) እንዲከፍሏቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡

ተጠሪዎቹ በ24/10/2005 ዓ.ም.በሰጡት መልስ አመልካች ቀደም ሲል በመሬት ይዞታው ይገባኛል ጉዳይ ክስ ባቀረቡበት ጊዜ አሁን ክስ ያቀረቡበትንም የአላባ ግምት አካተው መክሰስ ሲችሉ ነጥለው በማስቀረት አሁን አዲስ ያቀረቡት ክስ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 216 (3) ድንጋጌ መሰረት ተቀባይነት የለውም የሚል መቃወሚያ ካስቀደሙ በኃላ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተም በቀድሞው ክስ ፍርድ ያረፈበት ይዞታ አሁን በክሱ ላይየተገለጸውን መጠን የሚያህል ባለመሆኑ ክሱ የተጋነነ ነው፣በመሬቱ ላይ በግጦሽ ተሰማርተው የቆዩትም የተጠሪዎቹ ብቻ ሳይሆኑ የሌሎችም አርሶ አደሮች ከብቶች ጭምር በመሆናቸው መከሰስ የሚገባን በድርሻችን መጠን ብቻ ነው፣በአላባው 12 ዓመት ሙሉ ተጠቅማችኋል የተባልነውም አላግባብ ነው የሚሉ እና መሰል የክርክር ነጥቦችን በማንሳት ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክረዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም አመልካቹ በይዞታው ጉዳይ አስቀድሞ ክስ ባቀረቡበት ጊዜ የሚጠይቁት አላባ የስንት ዓመት እንደሆነ ማወቅ የሚችሉበት ሁኔታ ስላልነበረ ይዞታው እና ከይዞታው ላይ የሚገኘው አላባ ግምት አብሮ ሊጠየቅ የሚችል አይደለም የሚል ምክንያት ሰጥቶ መቃወሚያውን በማለፍ በፍሬ ጉዳዩ ረገድ በቀድሞው መዝገብ የቀረበውን ማስረጃ ከተመለከተ እና የአላባውን መጠን በባለሙያ ካስገመተ በኃላ አጠቃላይ ክርክር እና ማስረጃውን መርምሮ ተጠሪዎቹ በይዞታው ለ12 ዓመታት መጠቀማቸው በመረጋገጡ በባለሙያ በቀረበው ግምት መሰረት የ12 ዓመት አላባ ብር 49,280 (አርባ ዘጠኝ ሺህ ሁለት መቶ ሰማንያ) ከብር 1,551.50 የዳኝነት

ክፍያ ጋር ከብር 500 ወጪና ኪሳራ ጋር ለአመልካች እንዲከፍሉ ውሳኔ የሰጠ ሲሆን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በፍርድ ያጸናው ይህንኑ ውሳኔ ነው፡፡

ጉዳዩ በመጨረሻ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በበኩሉ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ የሻረው አመልካች ቀደም ሲል በመሬት ይዞታው ላይ የይገባኛል ክስ ባቀረቡበት ጊዜ አሁን ክስ ያቀረቡበትንም የአላባ ጥቅም አካተው መክሰስ ሲችሉ ነጥለው በማስቀረት አላባውን በተመለከተ አዲስ ክስ ማቅረባቸው በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 216 (4) እና 218 ድንጋጌዎች መሰረት ተቀባይነት ስለሌለው የአላባው ክስ ከቀድሞው የይዞታ ክስ ጋር አብሮ መቅረብ ነበረበት ተብሎ ውድቅ መደረግ ነበረበት የሚል ምክንያት በመስጠት ነው፡፡አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች ከመሬት ይለቀቅልኝ ክስ ጋር ከመሬቱ የሚገኝ አላባን አጣምሮ መጠየቅን በተመለከተ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 217 እና 218 ድንጋጌዎች ለከሳሽ ወገን አማራጭ የሚሰጡ እንጂ የሚያስገድዱ አይደሉም በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ ከድንጋጌዎቹ ይዘት አንጻር ተጠሪዎቹ ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው፡-

1. የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለማስመለስ ከሚቀርብ ክስ ጋር ከንብረቱ የሚገኝ አላባን ወይም ጥቅምን ጉዳይ አጣምሮ መክሰስን በተመለከተ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 217 እና 218 ድንጋጌዎች ፈቃጆች እንጂ አስገዳጆች አይደሉም በማለት አመልካች ያቀረቡት ክርክር ሕጋዊ ተቀባይነት ያለው ነው ወይስ አይደለም?
2. አመልካች ቀደም ሲል በመሬት ይዞታው ላይ የይገባኛል ክስ ባቀረቡበት ጊዜ አሁን ክስ ያቀረቡበትንም የአላባ ጥቅም አካተው መክሰስ ሲችሉ ነጥለው በማስቀረት አላባውን በተመለከተ አዲስ ክስ ማቅረባቸው በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 216 (4) እና 218 ድንጋጌዎች መሰረት ተቀባይነት የለውም በማለት የክልሉ ሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ ተቀባይነት ያለው ነው ወይስ አይደለም?

የሚሉ ነጥቦች መሆናቸውን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከእነዚሁ ነጥቦች አንጻር መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ አመልካቹ ይዞታውን ለማስለቀቅቀደም ሲል በተጠሪዎቹ ላይ ክስ አቅርበው የነበረ እና በክርክሩም ተጠሪዎቹ መሬቱን እንዲለቁየተወሰነ መሆኑ አላከራከረም፡፡የክስ አቀራረብ ስርዓትን በተመለከተ በአንድ በኩል በሌላ አኳኃን እንዲቀርብ ካልተፈቀደ በቀር ማናቸውም ከሳሽ ለሚያቀርበው ክስ መሰረት ሊሆን የሚችል ከአንድ በላይ

የሆነ ነገር ካለው ሁሉንም በአንድነት አጣምሮ በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ተከሳሾች ላይ የተጣመረ ክስ ለማቅረብ የሚችል ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 217 (1) ስር የተመለከተ ሲሆን በሌላ በኩል ግን የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለማስመለስ ክስ የሚያቀርብ ሰው ከዚህ ዓይነቱ ክስ ጋር አጣምሮ ማቅረብ የሚችለው በድንጋጌው ስር ከፊደል “ሀ” እስከ “ሐ” የተመለከቱትን የክስ ምክንያቶች ብቻ ስለመሆኑ በዚሁ ሕግ በቁጥር 218 ተደንግጓል፡፡የእነዚህ ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብም የማይንቀሳቀስ ንብረት ለማስመለስ ክስ የሚያቀርብ ሰው ከዚሁ ንብረት የሚገኘውን ጥቅም ለማስከፈል የሚቀርበውን ክስ የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ለማስመለስ ከሚያቀርበው ክስ ጋር አጣምሮ ማቅረብ የሚችል መሆኑን የሚያስገነዘብ ነው፡፡በሌላ በኩል ከሳሽ ሊከስበት ሲችል ሆነ ብሎ በመቀነስ ባስቀረው ሀብት ምክንያት እንደገና ሌላ ክስ ማቅረብ የማይችል ስለመሆኑ እና ከሳሽ ያቀረበው ክስ በአንድ ጉዳይ ላይ የተመሰረተ ሆኖ የሚጠይቀው ዳኝነት ግን ከአንድ በላይ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ሳይፈቀድለት ሊጠይቅ ይገባው ከነበረው ዳኝነት ውስጥ በከፊል ራሱ ቀንሶ ባስቀረው መብት እንደገና ሊከስበት የማይችል ስለመሆኑ በዚሁ ሕግ በቁጥር 216 (3) (4) ስር ተመልክቷል፡፡ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብም የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለማስመለስ ክስ የሚያቀርብ ሰው ከንብረቱ የሚገኘውን አላባ ወይም ሌላ ጥቅም ጭምር በክሱ አጣምሮ እንዲከስ በቁጥር 218 (ሀ) ስር የተመለከተው ድንጋጌ የአስገዳጅነት ባህርይ ያለው እንጂ አመልካች እንደሚሉት ፈቃጅ እና ክሱን ነጣጥሎ የማቅረብ አማራጭን ለከሳሽ ወገን የሚተው አይደለም፡፡በመሆኑም የማይንቀሳቀስ ንብረትን ለማስመለስ ከሚቀርብ ክስ ጋር ከንብረቱ የሚገኝ አላባን ወይም ጥቅምን ጉዳይ አጣምሮ መክሰስን በተመለከተ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 217 እና 218 ድንጋጌዎች ፈቃጆች እንጂ አስገዳጆች አይደሉም በማለት አመልካች ያቀረቡት ክርክር የድንጋጌዎቹን ይዘት እና ዓላማ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አስቀድመው በቀረቡለት ተመሳሳይ ጉዳዮች በመዝገብ ቁጥር 98639 እና በሌሎችም መዝገቦች የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ ተጠሪዎቹ አጥብቀው የሚከራከሩትአመልካቹከይዞታው የሚገኝ ነው ያሉትን የአላባ ጥቅም ጥያቄ ቀደም ሲል ካቀረቡት ይዞታ የማስለቀቅ ክስ ጋር አጣምረው ማቅረብ የሚችሉ ሆኖ ሳለ በዚህ አግባብ ሳያቀርቡ ቀርተው የመጀመሪያው ጉዳይ ውሳኔ ካገኘ በኃላ አላባውን በተመለከተ አዲስ ክስ ማቅረባቸው ከላይ ከተጠቀሱት የስነ ስርዓት ድንጋጌዎች ውጪ በመሆኑ በክልሉ ሰበር ችሎት የተሰጠው ውሳኔ ስህተት የለበትም በማለት መሆኑን የሰበር መልሳቸው  ይዘት ያመለክታል፡፡ተጠሪዎቹ ከላይ በተጠቀሱት ድንጋጌዎች የተመለከተውን የክስ አቀራረብ ስርዓት መሰረት አድርገው ያቀረቡት ክርክር በመርህ ደረጃ ተቀባይነት ያለው ቢሆንም

በሌላ በኩል ግን ይህ ክርክራቸው ለክሱ ምክንያት ከሆነው ጉዳይ ልዩ ባህርይ ጋር ተገናዝቦ በአግባቡ ሊመረመር የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

አመልካቹ የመጀመሪያውን ክስ ያቀረቡት ይዞታውን ለማስለቀቅ ነው፡፡በገጠር የእርሻ መሬት የይዞታ መብት ላይ የሚነሳው ክርክር ጉዳዩ በሚመለከታቸው ተከራካሪዎች በውይይትና በስምምነት እንዲፈታ ጥረት የሚደረግ ስለመሆኑ እና በስምምነት ሊፈታ ካልቻል በተከራካሪ ወገኖች በተመረጠ ሽምግልና ወይንም በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር ሕግ በተደነገገው መሰረት የሚወሰን ስለመሆኑ በፌዴራል መንግስት በወጣው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/1997 አንቀጽ 12 ስር ተደንግጎ ይገኛል፡፡በሌላ በኩል ከእርሻ መሬት ይዞታ ጋር ተያይዘው የሚነሱ ክርክሮች በወረዳ ፍርድ ቤት ቀርበው ከመታየታቸው በፊት በስምምነት እና ቀጥሎም በሽምግልና መታየት የሚገባቸው ስለመሆኑ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ባወጣው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀጽ 16 እና አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው ደንብ ቁጥር 151/2005 አንቀጽ 18 ተመልክቷል፡፡

ከላይ በተጠቀሱት አዋጆች እና ደንብ ድንጋጌዎች መሰረት ለፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት በስምምነት እና ቀጥሎም በሽምግልና እንዲታይ የሚደረገው ጉዳይ የእርሻ ይዞታ ክርክር እንጂ ከእርሻ ይዞታው የሚገኘው ጥቅም ወይም አላባ ጭምር አይደለም፡፡እንዲህ ከሆነ ደግሞ ከሳሽ የሆነ ወገን አላባውን የሚመለከተውን ክስ ይዞታውን ለማስለቀቅ ከሚያቀርበው ክስ ጋር አጣምሮ ሊያቀርብ የሚችልበት አግባብ አይኖርም፡፡ከእርሻ መሬት የሚገኘውን ጥቅም አስመልክቶ በሚቀርቡ ክሶች ጉዳይ ተጠሪዎቹ ጠቅሰው የሚከራከሩባቸው የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 218 (ሀ) እና 216 (3) ድንጋጌዎች መተርጎም የሚገባቸው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀምን አስመልክቶ ከወጡ ሕጎች ዓላማ እና መንፈስ ጋር ተገናዝበው ነው፡፡ቀደም ሲል በቀረበለት ተመሳሳይ ጉዳይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 108060 በ18/07/2007 ዓ.ም. የሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉምም በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2 (1) መሰረት በዚህ መዝገብ ለቀረበው ጉዳይ አስገዳጅነት ያለው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡በመሆኑም አመልካቹ ቀደም ሲል በሳር መሬት ይዞታው ላይ የይገባኛል ክስ ባቀረቡበት ጊዜ አሁን ክስ ያቀረቡበትንም የአላባ ጥቅም አካተው መክሰስ ሲችሉ ነጥለው በማስቀረት አሁን አዲስ ያቀረቡት ክስ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 216 (4) እና 218 ድንጋጌዎች መሰረት ተቀባይነት የለውም በማለት የክልሉ ሰበር ችሎት የደረሰበት መደምደሚያ እና ይንንኑ መደምደሚያ መሰረት አድርጎ የሰጠው ውሳኔ የጉዳዩን ልዩ ባህርይ፣ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ሕጎች እና ቀደም ሲል በጉዳዩ ላይ የተሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባው ሆኖ አልተገኘም፡፡በሌላ በኩል የክልሉ ሰበር ችሎት ውሳኔውን የሰጠው ተጠሪዎቹ ያቀረቡትን መቃወሚያ መሰረት በማድረግ በመሆኑ እና

የፍሬ ጉዳይ ክርክሩን መርምሮ የመጨረሻ ፍርድ ያላስረፈበት በመሆኑ በዚህ ረገድ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ ወደ ክልሉ ሰበር ችሎት ሊመለስ የሚገባው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 185098 በ22/02/2008 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፍሬ ጉዳይ ክርክሩን መርምሮ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 341 (1) ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት እንዲመለስ ወስነናል፡፡ተገቢውን መፈጸም ያስችለው ዘንድ የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ አመልካቾቹ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡

ብ/ግ

የሰ/መ/ቁ.121663

ታህሳስ 25 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

አብዬ ካሳሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አቶ ሀጋዚዘውዱ VC በሌሉበት ችሎት ስላስቻለ የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ራኽብ ቸኮለ VC በሌሉበት ችሎት ስላስቻለ የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት ሊቀርብ የቻለው የትግራይ ብሔራዊ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 79704 ህዳር 23 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠውን ውሳኔ አመልካች በመቃወም ታህሳስ 21 ቀን 2008 ዓ.ም የተፃፈ 01 ገጽ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

የክርክሩ አመጣጥም የአሁን ተጠሪ ክርክሩ በጀመረበት በትግራይ ብሐራዊ ክልል ኦፍላ ወረዳ ዓዲጉሎ ቀበሌ የመሬት ዳኝነት ከሳሽ በመሆን ለሰበር አቤቱታቸው ምክንያት የሆነውን በዓዲጉሎ ቀበሌ ዓዲጉሎ በተባለው ቦታ 1ኛ በምስራቅ ሻረው በርሀ፤በምዕራብ መንገድ፤በሰሜን ጥዑማይ ካህሳይ በደቡብ ሻረው በርሀ በሚያዋስኑት መካከል የሚገኝ እና 2ኛ በምስራቅ ታደገ ግርበቱ፤በምዕራብ ጣሰው አብርሃ፤በሰሜን መንገድ፤ በደቡብ ታደገ ግርበቱ በሚያዋስኑት መካከል የሚገኝ መሬት ተጠሪ በሽግሽግ የደረሳቸውን የእርሻ ይዞታ መሬታቸውን አመልካች በኃይል ተጠቅመው የያዙባቸው በመሆኑ ለቀው እንዲያስረክቡ እንዲወሰንላቸው ያቀረቡትን ክስ መሠረት ያደረገ ነው፡፡

አመልካችም በተከሳሽነት ቀርበው አከራካሪው መሬት የሟች አባታቸው ይዞታ መሆኑን ገልፀው በህግ አግባብ በውርስ ያገኙት በመሆኑ መሬቱ በሽግሽግ ለተጠሪ ሊሰጥ አይገባም በማለት ክርክር አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የዓዲጉሎ ቀበሌ መሬት ዳኝነትም አመልካች በክርክሩ መሬት ወራሽነት ማስረጃ ያወጡት መሬቱ ወራሽ የሌለው ለመሆኑ ተረጋግጦ ለተጠሪ ከተሸጋሸገ በኂላ ነው በማለት አመልካች መሬቱን ለቀው ለተጠሪ እንዲያስረክቡ ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ላይ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦፍላት ወረዳ ፍርድ ቤት አቅርበው የነበሩ ሲሆን ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የወረዳው ፍርድ ቤትም ይግባኙ መልስ ሰጭን ያስቀርባል በማለት ሲያከራክር ቆይቶ አከራካሪው መሬት በህጋዊ ሽግሽግ ለተጠሪ የተሰጣቸው ጥር 29 ቀን 2007 ዓ.ም መሆኑንና አመልካች በክርክሩ መሬት የወራሽነት ማስረጃ ያወጡት ደግሞ የካቲት 19 ቀን 2007 ዓ.ም ለመሆኑ ካረጋገጠ በኂላ አመልካች አከራካሪውን የይዞታ መሬት በውርስ አግኝቻለሁ የሚሉት መሬቱ በሽግሽግ ከተሰጠ በኂላ በመሆኑ የመሬት ዳኝነት የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት አፅንቶታል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው የነበሩ ቢሆንም የሥር ፍርድ ቤቶች ዳኝነት መሰረታዊ የህግ ስህተት አልተፈፀመበትም በማለት ሳይቀበል ቀርቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን ዳኝነት ለማስለወጥ ነው፡፡ መዝገቡ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርመሮ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ በመወሰኑ ተጠሪ መስከረም 09 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ መልስ ያቀረቡ ሲሆን አመልካችም ጥቅምት 28 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ በማቅረብ የጽሑፍ ክርክራቸውን አጠናቀዋል፡፡

ክርክሩ በዚህ አግባብ ተጠናቋል፡፡ እኛም መዝግቡን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም ለክርክር መነሻ የሆነውን መሬት አስመልክቶ ለአሁን ተጠሪ ይገባል ተብሎ የተወሰነው ባግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ምላሽ ማግኘት ያለበት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በመሠረቱ የፍትሐብሔር ክርክሮች ሲነሱ ምላሽ ለመስጠት የግራቀኙን ክርክር መሠረት በማድረግ ባግባቡ በማጣራት ተገቢውን ማስረጃ መርምሮ መወሰን ይገባል፡፡ የሥር የመሬት ዳኝነትም ሆነ ወረዳ ፍርድ ቤት ለውሳኔው መሰረት ያደረጉት ግራቀኙ ወገኖች ያቀረቧቸውን ማስረጃዎች በመመልከት ነው፡፡ በዚህ ረገድ ከሥር መዝገቡ መገንዘብ እንደቻልነው አከራካሪው መሬት ለተጠሪ በሽግሽግ ከተሰጠ በኂላ አመልካች የወራሽነት ማስረጃ ያወጡ መሆናቸው፤

ለተጠሪ አከራካሪው መሬት በተሰጠበት ወቅትም ተቃዋሚ ካለ እንዲቀርብ ጥሪ ተደርጎ እንደነበርና አመልካች በወቅቱ ሳይቀርቡ ቆይተው መሬቱ ለተጠሪ ከተሰጠ በኋላ ወራሽ መሆናቸውን አረጋግጠው ማስረጃ ማቅረባቸውን በማረጋገጥ የሥር ፍርድ ቤቶች አከራካሪው መሬት ለአመልካች የማይገባ ስለመሆኑ ወስነዋል፡፡

በትግራይ ብሔራዊ ክልል የገጠር መሬት አስተዳዳር አዋጅ ቁጥር 239/2006 አንቀጽ 14(8) እንዲሁም ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በወጣው ደንብ ቁጥር 85/2006 አንቀጽ 22(1)(ሀ) ሥር እንደተመለከተው ወራሽ የሌለው መሬት በቀበሌው የገጠር መሬት አስተዳደር ኮሚቴ መሬት ለሌላቸው ይሸጋሸጋል በማለት ደንግጓል፡፡ በዚሁ ደንብ አንቀጽ 21(8) ሥር እንደተመለከተው ከሽግሽግ በኋላ የሚቀርብ አቤቱታ ከመሬት ዳኝነትና ከፍርድ ቤት ውሳኔ ውጭ ተቀባይነት እንደሌለው ደንግጓል፡፡ የእነዚህ ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ የሚያስረዳው አንድ የገጠር መሬት ባለይዞታ የሞተ እንደሆነ መሬቱ ያለወራሽ ስለመቅረቱ ተገቢ ማጣራት በማድረግ እውነትም ወራሽ የሌለው ሆኖ የተገኘ እንደሆነ መሬት ለሌላቸው የቀበሌ ነዋሪዎች በሽግሽግ ሊሰጥ የሚገባ መሆኑን፤ መሬቱን ከማሸጋሸጉ በፊት የቀበሌ ገጠር መሬት አስተዳደር ኮሚቴው መሬቱ ወራሽ ያለው እንደሆነ ተገቢ ማጣራት ማድረግ ያለበት ሆኖ በዚህ ሂደት አልፎ የተሸጋሸገ መሬት ይመለስልኝ የሚል አቤቱታ በመርህ ደረጃ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን በልዩ ሁኔታ በመሬት ዳኝነት አካል ወይም በፍርድ ቤት ከተወሰነ ተቀባይነት ሊኖረው እንደሚችል የሚያስረዳ ነው፡፡ ስለሆነም አንዴ ወራሽ የለውም ተብሎ በሽግሽግ የተሰጠ መሬት በመሬት ዳኝነት ውሳኔ ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ አርፎበት ወራሽ የሆነ ሰው ከመጣ አቤቱታ ቀርቦበት በሽግሽግ ያገኘው ሰው ሊለቅ እንደሚችል የትግራይ ብሔራዊ ክልል የገጠር መሬት አስተዳዳር አዋጅ ቁጥር 239/2006ን ለማስፈፀም ከወጣው ደንብ ቁጥር 85/2006 አንቀጽ 22(1)(ሀ) ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ አመልካች አሁን በያዙት የወራሽነት ማስረጃ መነሻነት በመሬት ዳኝነት ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ በአከራካሪው መሬት ላይ ወራሽ ሊሆኑ የሚችሉ ከሆነ መሬቱ አንዴ ለተጠሪ በሽግሽግ ተሰጥቷል ተብሎ መብታቸውን መንፈግ ከክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር ህግ ዓላማና መንፈስም አንፃር ሲታይ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች በክርክሩ መሬት የወራሽነት ማስረጃ ማውጣታቸውን ግንዛቤ ከወሰዱ በኋላ የወራሽነት ማስረጃ በፍርድ ቤት የተሰጣቸው ቢሆንም መሬቱ ከተሸጋሸገ በኋላ የቀረበ የወራሽነት ማስረጃ ውሳኔ ተቀባይነት የለውም ማለታቸው የክልሉን የገጠር መሬት አስተዳደር ህግ ድንጋጌዎች ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች የያዙት የወራሽነት ማስረጃ ለማስረጃነት የሚያገለግል በመሆኑ ተጠሪ ጋር ክርክር ሊደረግበት የሚገባውና ሊስተባበልም የሚችል ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በጉዳዩ ላይ ተጠሪ የሚያቀርቡት ክርክርና ማስረጃ አመልካች ካቀረቡት የወራሽነት ማስረጃ ጋር ተገናዝቦ ሊመረመር የሚገባው ነው፡፡ ይሁን እንጂ በጉዳዩ ላይ

ዳኝነት የሰጡት የሥር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በዚህ አግባብ ተመልክተው ያስተናገዱት ሳይሆን አመልካች የወራሽነት ማስረጃ ያቀረቡት መሬቱ ከተሸጋሸገ በኋላ ነው በሚል ምክንያት ብቻ አመልካች አከራካሪውን መሬት መውረስ የሚገባቸው ወይም የማይገባቸው ስለመሆኑ ሳያጣሩ መሬቱን ለተጠሪ እንዲያስረክቡ መወሰናቸውን ከመዝገቡ ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በዓዲጉሎ ቀበሌ የመሬት ዳኝነት አካል ተወስኖ በኦፍላ ወረዳ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 12291/07 መስከረም 06 ቀን 2008 ዓ.ም  በዋለው ችሎት እንዲሁም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 79704 ህዳር 23 ቀን 2008 ዓ.ም ተቀባይነት ያገኘው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በመሆኑም አመልካች የያዙት የወራሽነት ማስረጃ በክርክሩ መሬት ላይ የሚሰጣቸው መብት ምን እንደሆነ ተጠሪው አመልካች ባቀረቡት የውርስ ማስረጃ ላይ ያላቸው ክርክርና ማስረጃ እንዲያቀርቡ በማድርግ ከግራቀኙ ክርክርና ማስረጃ አንፃር ጉዳዩን ካጣራ በኋላ አከራካሪው መሬት ለአመልካች በውርስ ይገባቸዋል ወይስ አይገባቸውም? በሚለው ጭብጥ ላይ ተገቢውን እንዲወስን የዚህ ችሎት ውሳኔ ቅጅ ለዓዲጉሎ ቀበሌ መሬት ዳኝነት ይተላለፍ ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት የወጣ ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡን ዘግተናል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ.115399

ታሕሳስ 24 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሠለ

አብዬ ካሣሁን

እትመት አሠፋ

አመልካች፡-1.ተስፋዬ ተሾመ } አልቀረቡም

2. ኤፍሬም መኮንን

ተጠሪዎች፡- 1.ሞላየ ወልዴ ………………… አልቀረበም

2.ይመር ወልዴ …………………….ቀረበ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍረድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የእርሻ መሬትን በሚመለከት ሁከት ይወገድልኝ በማለት የቀረበን ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ክርክሩ የጀመረው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በሰሜን ወሎ ጉባ ላፍቶ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪዎች ከሳሾች አመልካቾች ደግሞ ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የተጠሪዎች ክስ ይዘት በአጭሩ አዋሳኙ በክሱ የተጠቀሰውን እና ከሟች አቶ አሠፋ እውነቱ በኑዛዜ ያገኙትን የእርሻ መሬት አመልካቾች አታርሱም በማለት ሁከት የፈጠሩባቸው መሆኑን በመግለጽ አመልካቾች የፈጠሩት ሑከት እንዲወገድ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት አመልካቾች መልስ ለመስጠት በተያዘው ቀነቀጠሮ ባለመቅረባቸው ጉዳያቸው በሌሉበት እንዲታይ በማለት ትዕዛዝ ከሰጠ እና ምስክር ለመስማት ቀጠሮ ከያዘ በኂላ አመልካቾችን በመወከል የክልሉ ዐቃቤሕግ የቀረበ በመሆኑ የክልሉ ዐቃቤሕግ አመልካቾችን በመወከል ያቀረበውን መልስ በመቀበል የግራቀኙን ምስክሮች ሰምቷል፡፡ ስለመሬቱም ጉዳዩ ከሚመለከተው የወረዳው መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት በትዕዛዝ እንዲጣራ ካደረገ በኂላ

የተጠሪዎች ምስክሮች ተጠሪዎች መሬቱ ከአቶ አሠፋ እውነቱ በኑዛዜ የተሠጣቸው መሆኑን በመግለጽ መስክረዋል፤የአመልካች ምስክሮች አመልካቾች ሁከት ያልፈጠሩ መሆኑን፤በጽ/ቤቱ የኑዛዜ ሰነድ የሌለ መሆኑን፤በጊዜው የነበረው ኮሚቴ መሬቱ ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ የወሰነ መሆኑን፤ተጠሪዎች ይዞታችን ነው የሚሉት መሬት በሕግ ያልተረጋገጠ በመሆኑ አታርሱም የተባሉ መሆኑን በመግለጽ መስክረዋል፤የጉባላፍቶ ወረዳ አካባቢ ጥበቃ መሬት አስተዳደር በጻፈው ደብዳቤ ሟች አቶ አሠፋ እውነቱ አድርገውታል የተባለው የኑዛዜ ሰነድ ከወረዳው አካባቢ ጥበቃ መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ጽ/ቤት ያልገባ መሆኑን አረጋግጧል፤በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አካባቢ ጥበቃ መሬት አሥተዳደር እና አጠቃቀም ቢሮ በወረዳው ጽ/ቤት አስቀድሞ ሳይመዘገብ የሚቀርብ የይዞታ መብት የኑዛዜ ውርስ ይተላለፍልኝ ጥያቄ ጉዳዩ ተቀባይነት የለውም በማለት ወዲያውኑ መመለስ አለበት በሚለው መሠረት በጽ/ቤታችን ያልተገኘን የኑዛዜ ሰነድ አልተቀበልነውም በማለት ማብራሪያ ልኳል፤ተጠሪዎች የያዙት መሬት በመሬት ዴስክ ያልተመዘገበ እና የኑዛዜ ሰነዱም በወረዳው ጽ/ቤት ያልተመዘገበ መሆኑ እና ወደ መሬት ባንክ የገባ መሆኑን በጉዳዩ ባለቤት ተረጋግጧል፤አንድ ተከራካሪ ወገን ሁከት ይወገድልኝ በማለት ክስ ማቅረብ የሚችለው ይዞታውን በእውነት ይዞ የሚያዝበት ሆኖ ሲገኝ ነው፤ተጠቃሹ ይዞታ በአቶ አሠፋ እውነቱ ሥም የሚገኝ በመሆኑ የተፈጠረ ሁከት የለም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪዎች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ለሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ ተጠሪዎች የኑዛዜውን ሰነድ ለቀበሌው መሬት ዴስክ አቅርበው ያለምንም ምክንያት አይገባችሁም የተባሉ መሆኑን፤መሬቱ የተጠሪዎች አጎት የአቶ አሠፋ እውነቱ መሆኑን እና ኑዛዜው በቀበሌው የመሬት ዴስክ ባለሙያ ፊት የተደረገ እና በአራት ምስክሮች ተፈርሞ እና ተነቦ ተናዛዡ የጣት አሻራውን ያሣረፈበት መሆኑን ተረጋግጧል፤በተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/98 እና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በወጣው ደንብ ቁጥር 51/99 ኑዛዜው በወረዳው መሬት ዴስክ ሳይጸድቅ ቢቀር ውጤቱ ምን እንደሚሆን የሚገልጽ ድንጋጌ የለም፤በልዩ ሕጉ ላይ ስለኑዛዜው አለመመዝገብ ውጤት ሳይገለጽ ከቀረ ጉዳዩ ሊዳኝ የሚገባው በጠቅላላ የኑዛዜ ሕጉ መሠረት ነው፤ሟች ያደረጉት ኑዛዜ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 881 ሥር የተመለከቱትን ሥርዓቶች ያሟላ በመሆኑ እና ተጠሪዎች መሬቱ በዚህ ኑዛዜ መሠረት ተላልፎላቸው የወረሱ በመሆኑ ኑዛዜው በወረዳው የመሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ጽ/ቤት ቀርቦ አልጸደቀም በማለት ተጠሪዎች ሕጋዊ ይዞታ ስለሌላቸው ሁከት የለም በማለት የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ አይደለም በማለት የሥር ፍ/ቤት የሠጠውን ውሳኔ በመሻር አመልካቾች የፈጠሩት ሁከት እንዲወገድ በማለት በአብላጫ

ድምጽ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡አመልካቾች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት አቤቱታቸው ተሰርዟል፡፡በመቀጠል አመልካቾች ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው በትዕዛዝ ውድቅ ተደርጓል፡፡የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡-ተጠሪዎች መሬቱን መያዝ የሚገባቸው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/98 አንቀጽ 23/4 እና ይህንኑ አዋጅ ለማስፈጸም በወጣው ደንብ ቁጥር 51/99 አንቀጽ 24/4 መሠረት ኑዛዜውን በወረዳው ጽ/ቤት አስመዝግበው መሆን አለበት፤የመሬት አስተዳደርን እና አጠቃቀምን በሚመለከት በክልሉ የወጣው መመሪያም በወረዳው ጽ/ቤት ያልተመዘገበ ኑዛዜ የማይጸና መሆኑን ይደነግጋል፤ተጠሪዎች የሟች ኑዛዜ ወራሽነታቸው ያልተመዘገበ እና የማይጸና በመሆኑ መሬቱ በሞተከዳ ወደ መሬት ባንክ የገባ እና አመልካቾችም የመሬት አስተዳደር ኮሚቴ በመሆናችን ተጠሪዎች ወደ መሬት ባንክ የገባውን መሬት እንዳያርሱ መከልከላችን ሁከት ፈጥረዋል የሚያሰኝ ባለመሆኑ አመልካቾች ሁከት ፈጥረዋል በማለት ሁከቱ ሊወገድ ይገባል በማለት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ችሎት መታየት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎ ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡እኛም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ኑዛዜው በወረዳው አስተዳደር ቀርቦ ሳይመዘገብ ቢቀር ውጤቱ ምን እንደሆነ የክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅም ሆነ አዋጁን ለማስፈጸም የወጣው ደንብ የማይደነግግ በመሆኑ ጉዳዩ ሊዳኝ የሚገባው በመደበኛው ሕግ ነው በማለት የደረሰበት መደምደሚያ ተገቢ መሆን አለመሆኑ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የገጠር መሬት አስተዳደርን እና አጠቃቀምን ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 133/98 አንቀጽ 23/4 ድንጋጌ ከመሬት ጋር የተያያዘ ማናቸውም መብትና ግዴታን የሚመለከት ተግባር መሬቱ በሚገኝበት ወረዳ ባለው የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ቀርቦ ካልተመዘገበ በስተቀር በሦስተኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሆኖ ሊቀርብ እንደማይችል ይደነግጋል፤ይህንኑ አዋጅ ለማሰፈጸም የወጣው ደንብ ቁጥር 51/99 አንቀጽ 24/4 ድንጋጌ በመሬት መመዝገቢያ መዝገብ ውስጥ መሬቱ ኪራይን፣

ውርስን ወይም ስጦታን የተመለከተ ግዴታ ያለበት እንደሆነ ይኸው መመዝገብ ያለበት መሆኑ፤ ግዴታው በሚሻሻልበት ወይም በሚያበቃበት ጊዜም መረጃው በዚሁ መሠረት መስተካከል የሚኖርበት መሆኑ ይደነግጋል፤የገጠር መሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/98 ን እና ደንብ ቁጥር 51/99 ን ለማስፈጸም የወጣው መመሪያ አንቀጽ 13 ንዑስ ቁጥር 1 እና 2 ድንጋጌ ማንኛውም በህግ በኑዛዜ ይዞታውን የማስተላለፍ ስልጣን የተሰጠው አካል ይዞታውን በክልሉ ውስጥ በህግ የገጠር መሬት የማግኘት መብት ለተሰጠው ሰው ከሞተ በኋላ ይዞታው እንዲተላለፍለት በጽሁፍ መናዘዝ የሚችል መሆኑን፤ኑዛዜዉ በፍ/ቤት እንዲጸድቅ ከተደረገ በኋላ በወረዳው አካ/ጥ/መ/አስ/አጠ/ጽ/ቤት ቅጂውን አስመዝግቦ ተናዛዡ ከሞተ በኋላ የይዞታ ዝውውሩ ተጨማሪ ማስረጃ ማቅረብ ሳያስፈልገው በቀጥታ የሚከናወን መሆኑን ይደነግጋል፡፡ከነዚህ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለው በኑዛዜ መሬት ተላልፍልኛል የሚል አካል ኑዛዜዉን በፍ/ቤት እንዲጸድቅ ካደረገ በኋላ በወረዳው አካ/ጥ/መ/አስ/አጠ/ጽ/ቤት ቅጂውን ሊያስመዘግብ የሚገባ መሆኑን እና በዚህ አግባብ ያልተመዘገበ ኑዛዜ ውጤት የሌለው መሆኑን ነው፡፡የገጠር መሬትን አስመልክቶ የወጡት ልዩ ሕጎች በፍ/ቤት ያልጸደቀ እና በወረዳው መሬት አስተዳደር እና አጠባበቅ ጽ/ቤት ቀርቦ ያልተመዘገበ ሰነድ ውጤት የሌለው መሆኑን የሚያስገነዝቡ ሆነው ሳለ የሰሜን ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የገጠር መሬትን አስመልክቶ በክልሉ የወጡት ሕጎች ኑዛዜው በወረዳው አስተዳደር መሬት ጽ/ቤት ቀርቦ ካልተመዘገበ ውጤቱ ምን እንደሚሆን የማይደነግጉ በመሆኑ ጉዳዩ ሊዳኝ የሚገባው በጠቅላላ ሕጉ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ነው በማለት የሟች ኑዛዜ ፎርማሊቲውን ያሟላ በመሆኑ አመልካቾች የፈጠሩት ሁከት ሊወገድ ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ የገጠር መሬትን አስመልክቶ በክልሉ የወጡትን የሕግ ማዕቀፎች ያላገናዘበ እና መሠረታዊ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 13027 ታሕሳስ 24 ቀን 2007 ዓ.ም ተሰጥቶ፤በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 0102797 የካቲት 25 ቀን 2007 ዓ.ም በትዕዛዝ፤በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 03-10933 ግንቦት 26 ቀን 2007 ዓ.ም በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በሰሜን ወሎ ጉባላፍቶ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ 0104522 ጥቅምት 25 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሰ/መ/ቁ. 125186

ሰኔ 26 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነው

በእውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- ወ/ሮ አዛል አይናለም -ተወካይ ጌትነት ተረፈ

ተጠሪ፡- 1ኛ፣ አቶ ምህረት በላይ -ቀረቡ

2ኛ. የቡሬ ዘ/ወ/አከ/ጥ/መ/አስ/አጠ/ፅ/ቤት -አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የእርሻ መሬት ክርክርን የሚመለከት ሆኖ ክርክሩም የተጀመረው በአ/ብ/ክ/መንግስት የቡሬ ወረዳ ፍ/ቤት ነው ፡፡ በዚያ ደረጃ አመልካች ከሳሽ ተጠሪዎች ደግሞ ተከሳሾች ነበሩ ፡፡ አመልካች በስር ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አቤቱታ፡- ከሳሽ የፈፀምኩት የስጦታ ውል መንፈስ ልልነት እና አቅመደካማ በመሆኔ የፈፀምኩት ስለሆነ የስጦታ ውሉ ሊፈርስ ይገባል በማለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡1ኛ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት ተከሳሽ በመሆን ባቀረበው መልስ ከሳሽ ያቀረበው ስጦታ ይፍረስልኝ ጥያቂ ይርጋ ጊዜው ያለፈው ስለሆነ በይርጋ ቀሪ ሊሆን ይገባል በማለት የተከራከረ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ በበኩሉ ከሳሽ የፈፀመው ስጦታ ውል በህግ መሰረት የተደረገ ስለሆነ የቀረበው አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የወረዳው ፍርድ ቤትም በስር ተከሳሾች የቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወምያ መሰረት በማድረግ ስጦታው ተደረገ ከተባለው ጊዜ ጀምሮ በሁለት አመት ውስጥ የይረሰዝልኝ ጥያቄ ስላልቀረበበት ክሱ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2441 መሰረት በይርጋ የታገደ ነው በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ብይን የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ እንዲሁም የሰበር አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር አቅርቦም መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም ተብሎ ተሰርዞበታል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ብይን በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም፡- በተጠሪዎች የቀረበው መቃወምያ የፍትሃብሄር ህጉን በመጥቀስ ሲሆን ይህ ክርክር ግን የሚዳኘው በክልሉ የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 133/98 ፣እና ደንብና መመሪያ እንጂ በፍትሃብሄር ህጉ መሰረት ባለመሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ሊሻር ይገባል የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም ለዚህ ችሎት ቀርቦ እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው የፅሁፍ ክርክራቸው ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዮ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የአመልካችን የሰበር ቅሬታ የሠበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ጭብጥ የአመልካች ክስ በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ ውድቅ መደረጉ ባግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ አመልካች በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሰረቱት የፈፀምኩት የስጦታ ውል መንፈስ ልልነት እና አቅመ ደካማ በመሆኔ የፈፀምኩት ስለሆነ ስጦታው ሊሰረዝ ይገባል በማለት መሆኑን፣ ተጠሪ ደግሞ ጉዳዩ በሁለት አመት ይርጋ የሚዘጋ ነው በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበው የበታች ፍርድ ቤቶችም የተጠሪን  የመቃወሚያ ነጥብ በመያዝ ክሱን በይርጋ ውድቅ ያደረጉ መሆኑን ነው፡፡
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 133/98 አንቀጽ 16/3 እና ይህንኑ አዋጅ ለማስፈፀም ባወጣው ደንብ ቁጥር 51/99 አንቀጽ 11/2 እንደተደነገገው የአሁኑ ተጠሪ ዋጋ ያለው የስጦታ ማስረጃ አቅርበናል እንኳ ቢባል ስጦታው በተደረገበት የእርሻ መሬት ላይ በቤተሰብነት የተመዘገበ አባልን ያገለለ መሆኑ ከታወቀ ይኸው ሰነድ በህግ ተቀባይነት የማይኖረው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በደንብ ቁጥር 51/99 አንቀጽ 11/2/ በተመለከተው መስፈርት መሰረት መሬት ያገኙ በሞተበት ወቅት የእራሱ የሆነ ቤተሰብ እያለው ባደረገው ስጦታ ቤተሰቡን የሚነቅል ሆኖ በመገኘቱ የተነሣ ስጦታ በህግ ፊት ተቀባይነት የሌለው ሆኖ በተገኘ ጊዜ የእርሻ መሬት ለማን እና እንዴት በውርሱ ሊተላለፍ እንደሚገባ በዚሁ ደንብ አንቀጽ 11/7/ ስር ከፊደል /ሀ/ እስከ /መ/ የተቀመጠውን ቅደምተከተል በመጠበቅ እንደሆነ ተደንግጓል፡፡

የስር ፍርድ ቤቶች ክሱ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2441 ድንጋጌ መሰረት በሁለት አመት ይርጋ የሚታገድ መሆኑን የሰጡት ውሳኔ አግባብነት ተመልክተናል፡፡ ጉዳዩ የገጠር እርሻ መሬት ስጦታን የሚመለከት ሲሆን ጉዳዩ የሚገዛው ልዩ በሆኑት የገጠር መሬት አስተዳደር ሕጎች ነው፡፡ በዚህ ረገድ ተፈጻሚነት ያላቸው ሕጎች በፌዴራሉ መንግስት የወጣው አዋጅ ቁጥር 456/97፣በክልሉ

ምክር ቤት የወጣው አዋጅ ቁጥር 133/98 እና ደንብ ቁጥር 51/99 እንዲሁም ይህንኑ ተከትሎ በክልሉ የወጣው መመሪያ ናቸው፡፡ እነዚህ ሕጎች አንድ የገጠር እርሻ መሬት የሚተላለፍባቸውን መንገዶች የሚያሳዩ ሲሆን ከእነዚህ መንገዶች መካከል በውርስና በስጦታ ይዞታው የሚተላለፍበትን አግባብ የሚመለከቱ ይገኙበታል፡፡ የገጠር እርሻ መሬት በውርስና በስጦታ ሲተላለፍም በሕጎቹ የተቀመጡ ክልከላዎችና እነዚህ ክልከላዎች ሳይከበሩ የሚደረግ ኑዛዜ መኖሩ ሲረጋገጥ የይዞታ መብቱ የሚተላለፍላቸው ወገኖች ቅደም ተከተል መኖሩን የደንብ ቁጥር 51/99 አንቀጽ 11(2) እና (7) ድንጋጌ በግልጽ ያሳያል፡፡

ስለሆነም በሕጉ ክልከላ የተደረገባቸው የይዞታ ማስተላለፍ ሁኔታዎች ያሉ ሲሆን ሕጉን ያልጠበቀ የገጠር መሬት ይዞታ በኑዛዜ ወይም በስጦታ ተላልፏል የሚለው ወገን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2441 አግባብ በሁለት አመት መጠየቅ ነበረበት ሊባል የሚችል ያለመሆኑን ከልዩ ሕጎቹ ድንጋጌዎች ይዘት እና መሰረታዊ አላማ የምንረዳው ሁኖ አግኝተናል፡፡ የሁለት አመት ይርጋ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለው ነው ከተባለ ደግሞ ከአመልካቾች እድሜና ሌሎች ሕጋዊ ምክንያቶች ጋር ተያይዞ በመታየት እልባት የሚያገኘው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች በእድሜ የገፉ መሆናቸውን የክርክሩ ሂደት ስለሚያሳይ እና ይህም ጉዳዩ በሌላ የይርጋ ዘመን የሚቋረጥ መሆን ያለመሆኑ ላይ ክርክር ሊያስነሳ የማይገባ ሁኖ ስለአገኘው አግባብነት ያለውን የይርጋ ዘመን ከወዲሁ መለየቱ ተገቢ ሁኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ክሱ በይርጋ የሚታገድ ሁኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለልም የበታች ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የክስ ይዘት የፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2441 ድንጋጌ ይዘት፣መንፈስና ዓላማ ጋር በአግባቡ ሳያገናዝቡናያለ ቦታው ጠቅሰው የአመልካች ክስ ውድቅ ማድረጋቸው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ብይን ሁኖ አግኝተናል፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በቡሬ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 23260 ህዳር 20 ቀን 2008 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 01-65729 ህዳር 27 ቀን 2008 ዓ/ም እንዲሁም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 53060 ታህሳስ 14 ቀን 2008 ዓ/ም በትዕዛዝ የፀናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች ክስ በይርጋ የታገደ አይደለም ብለናል፡፡
3. የቡሬ ወረዳ ፍርድ ቤት ክርክሩን በመ/ቁጥር 23260 በሆነው ቀጥሎና በስነ ስርዓቱ ሕጉ መሰረት በመምራት ተገቢውን ይወሰን በማለት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ.114670

ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም.

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነው

በእውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- 1ኛ አቶ ባንኩ ኢሩስ

2ኛ አቶ ኤሊያስ ታኒ

ተጠሪ፡- አቶሳምሶን ገ/ዬሀንስ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የገጠር እርሻ መሬትን የሚመለከት ሆኖ የግራ ቀኙ ክርክር የተጀመረው በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ/ በበንች ማጂ ዞን የሸኮ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኖቹ አመልካቾች ከሳሽ የአሁኑ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡የአሁኖቹ አመልካቾች ከሳሽ በመሆን በስር ፍ/ቤት ያቀረቡት የክስ ማመልከቻ ይዘት ባጭሩ፡- ከተከሳሽ ጋር ግንቦት 19 ቀን 2004 ዓ/ም በተፃፈ ውል በጅምርሶ ቀበሌ ልዩ ስሙ ምንካታ ተብሎ በሚጠራው መንደር በምስራቅ የአቶ አዲሱ ገመዳ የእርሻ ማሳ፣በምእራብ የጋቸብ ወንዝ፣በስሜን የአቶ ሳሙኤል የቡና ማሳ፣በደቡብ የአቶ አዲሱ ገመዳ ይዞታ መሬት የሚያዋስነው የራሱ የሆነ ለመልማት የሚችል ይዞታ መሬት ተከሳሽ ለለማው የቡና ይዞታ 150,000 (አንድ መቶ አምሳ ሺህ ብር) ተገምቶ ገንዘቡን ለተከሳሽ ከፍለን ያልለማው ቡና ውሉ ከተፈፀመበት ቀን ጀምሮ የእኛ እና የተከሳሽ የጋራ የቡና ልማት እንዲሆን ተስማምተናል ፡፡ ለተከሳሽ ከከፈልነው ገንዘብ በተጨማሪ የለማውን ቡና ለመንከባከብ አዲስቡናለማስተከል

ብር 50,000(አምሳሺ.ህብር ) ወጪ በማድረግ አልምተናል፡፡ለጀምሩስ ቀበሌ ፅ/ቤትበቡናው ይዞታ ውስጥ ከሳሾች እንዳይገቡ በማለት ተከሳሽ ህዳር 21 ቀን 2006 ዓ/ም ፅፎ ያስገባ በመሆኑ እኛም

ከተጠቀሰው ቀን ጀምሮ በይዞታው መሄድ አቁመናል፡፡ተከሳሽ የ2006 ዓ/ም የቡና አላባ ለብቻው የተጠቀመ ስለሆነ ድርሻችን 112,666ብር ተከሳሽ እንዲከፍለንና በውሉ መሰረትቡናው የጋራ ተብሎ እንዲወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡የአሁኑ ተጠሪ የስር ተከሳሽ በመሆን ባቀረበው መልስ ከከሳሾች ጋር በጋራ ለመስራት ውል ያደረግን ቢሆንም ይህንን መሰረት አድርገው ይዞታው የጋራ ነው ተብሎ ይወሰንልን ብለው ያቀረቡትጥያቄ ውሉ ህግ የሚጠይቀውን መስፈርት ያላሟላ ስለሆነ የህግ መሰረት የለውም ፡፡ የ2006 ዓ/ም አላባ እንድከፍላቸው ያቀረቡት ጥያቄም በማስረጃ የተደገፈ አይደለም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ በመጀመርያ ደረጃ የተመለከተው የሸኮ ወረዳ ፍርድ ቤት ክሱንና የግራ ቀኙን ምስክሮች ሰምቶ አጠቃላይ ክርክሩን ከመረመረ በኋላ ተከሳሽ 95,962 (ዘጠና አምስት ሺህ ዘጠን መቶ ስልሳ ሁለት ብር ) ይክፈል፤ክርክር ያስነሳውብጀምሩስ ቀበሌ ልዩስሙ ሞንኪታየሚባለው ቦታ ያለው የቡና ይዞታየግራቀኙ የጋራ ይዞታ ሆኖ በጋራ እንዲጠቀሙ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በዚሁ ውሳኔ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበውም የቀረበው ይግባኝ ሰርዞታል፡፡የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ተጠሪ ቅር በመሰኘት አቤቱታው ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍ/ቤቱ የቀረበው አቤቱታና የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ አጠቃላይ ክርክሩን ከመረመረ በኋላአመልካቾች በይዞታው ላይ አወጣነው የሚሉትን ገንዘብ አግባብ በሆነ መንገድ ከመጠየቅ ውጪ ህገወጥና ፈራሽ በሆነ ውል መሠረት ያቀረቡት ክስ መነሻነት የስር ፍርድ ቤቶች የቡና ማሳው የጋራእንዲሆን የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመሻር ውሳኔ ሰጥቷል፡፡አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን የአመልካቾች አቤቱታ ተመርምሮለሰበር ችሎት ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው የጽሁፍ ክርክራቸው ተለዋውጠዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙ ፅሑፍ ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

የመጀመሪያው ጭብጥ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 110/1999 አንቀፅ 12(4) መሰረት ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ቀርቦ ሳይታይ በቀጥታ ተቀብሎ ማየቱ ስነ-ስርአታዊ ነው? ወይስ አይደለም? የሚል ሲሆን ጉዳዩ የመሬት መጠቀም መብት ይገባኛል ጥያቄ ጋር የተያያዘ በመሆኑ መታየት ያለበት በመሬት አዋጁ መሰረት ስለመሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ የደቡብ ብሄር ብሔረሰቦች ሕዝቦች ክልል መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 110/1999 የክርክሮች አወሳሰን አስመልክቶ በአዋጁ

አንቀፅ 12(1) እንደተደነገገው የገጠር መሬት ይዞታ መብትን በተመለከተ ክርክር ሲነሳ አቤቱታ ለቀበሌው የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ ቀርቦ በተከራካሪ ወገኖች በፍቃደኝነት በተመረጡ ሽማግሌዎች አማካኝነት ታይቶ በእርቅና በድርድር እንዲፈታይደረጋል፡፡በሽማግሌዎቹ እርቅና ድርድር ያልተስማማወገን ለወረዳው መደበኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ የማቅረብ መብት እንዳለው በዚሁ አዋጅ አንቀፅ 12(2) ተመልክቷል፡፡ይህ በእንዲህ እንዳለ የወረዳው መደበኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ያልተስማማ ወገን ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ እንደሚችል ፣በዚህ ውሳኔ ያልተስማማ ወገን በተጨማሪ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ የማቅረብ መብት እንዳለው በአዋጁ አንቀፅ 12(4) ተደንግጎ እናገኛለን ፡፡ ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ከክርክሩ ይዘት ለመረዳት የተቻለውየሸኮ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ባለመስማማት ተጠሪ ለክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍርድ ቤቱ የስር ወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ በማፅናቱ ተጠሪ በቀጥታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ መሆናቸው መዝገቡ ያመለክታል፡፡

በመሠረቱ በገጠር የእርሻ መሬት የመጠቀም መብት፣መብቱን በዉርስ የማስተላለፍ እና መሰል መብቶች ጥበቃ ያገኙት በፌደራል መንግስት በወጣዉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/1997 ሲሆን ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም ደግሞ ዝርዝር ሕጎች የሚወጡት በእያንዳንዱ ክልል ምክር ቤት ስለመሆኑ በአዋጅ አንቀፅ 17 ስር በግልፅ ተመልክቷል ፡፡ እንዲሁም በገጠር የእርሻ መሬት የይዞታ መብት ላይ የሚነሳው ክርክር ጉዳዩ በሚመለከታቸው ተከራካሪዎች በውይይትና በስምምነት እንዲፈታ ጥረት የሚደረግ ስለመሆኑ እና በስምምነት ሊፈታ ካልቻለ በተከራከሪ ወገኖች በተመረጡ ሽምግልና ወይንም በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደር ሕግ በተደነገገው መሰረት የሚወሰን ስለመሆኑ በዚሁ አዋጅ አንቀፅ 12 ስር ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 456/1997 አንቀፅ 17 ድንጋጌ መሰረትም የደቡብብሔሮች ብሔረሰቦችክልል መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 110/1999 እና አዋጁን ለማስፈፀም ደንብ አውጥቶ በስራ ላይ ያዋለሲሆን በዚህ አዋጅ እና ደንብ በተዘረጋዉ ስርዓት መሰረት በስምምነት እና በሽምግልና እልባት ያላገኙ ጉዳዩችን በመጀመርያ ደረጃ አይቶ የመወሰን የስረ ነገር ስልጣን አስመልክቶ የክርክሮች አወሳሰን በሚል ርእስ ስር በአዋጁ አንቀፅ 12ስር ተመልክቷል፡፡ ከገጠር የእርሻ መሬት ጋር ተያይዘዉ የሚነሱ አለመግባባቶች እና ክርክሮች በስምምነት እና በሽምግልና መፈታት ካልቻሉ ክልሎች በሚያወጡት ሕግ መሰረት ውሳኔ እንዳያገኙ እንደሚደረግ የሚደነግገዉ አዋጅቁጥር 456/1997 እና የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች ክልል መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 110/1999 በክልሉ ምክር ቤት የወጣው የተሻሻለውየክልሉ ፍርድ ቤቶች ማቋቋምያ አዋጅ ቁጥር 43/94 ከወጣ በኃላ ነው፡፡ አዋጅ ቁጥር 43/94 የወረዳ ፍርድ ቤት እና ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተመሳሳይ

ውሳኔ የሰጡ እንደሆነ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት መሆኑ ከታመነበት አቤቱታውበቀጥታ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሚቀርብ ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡

ሕግ አውጪው የአዋጅ ቁጥር 43/94 ምእራፍ ሶስት “የፍርድ ቤቶች የዳኝነት ስልጣን” በሚለው ርእስ ስር የተመለከተው ድንጋጌ መኖሩን እያወቀ ከገጠር የእርሻ መሬት ጋር ተያይዘው የሚነሱት አለመግባባቶች እና ክርክሮች በስምምነት እና በሽምግልና መፈታት ካልቻሉ በሚያወጡት ሕግ መሰረት ውሳኔ እንዲያገኙ በአዋጅ ቁጥር 456/1997 መደንገጉና በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 110/1999 አንቀፅ 12(4) የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ያልተስማማ ወገን ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጨማሪ ይግባኝ ማቅረብ እንደሚችል መደንገጉ ከእርሻ መሬት ጋር ተያይዘው የሚነሱት ክርክሮች ካላቸው ልዩ ባህርይ አንጻር ከሌሎች ጉዳዬች በተለየ ሁኔታ ተጨማሪ የይግባኝ መብት መስጠቱ እና ከገጠር መሬት የይዞታ ክርክር አንፃር ቁጥር 456/1997 ልዩ ሕግ መሆኑን ከአጠቃላይ የሕግ አወጣጥ ስርዓት መርህ መገንዘብ ይቻላል ፡፡ይህም ከገጠር የእርሻ መሬት ይዞታ ጋር ተያይዞ ለሚነሳው ክርክር በመሬት አዋጁ መሰረት ሊመራ የሚገባው ነው ብለናል፡፡

ከላይ በዝርዝር በተመለከተው መሰረት አቤቱታው የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 110/1999 አንቀፅ 12(5) መሰረት በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ይኖራል ተብሎ ከታሰበ የማየት ስልጣን እንዳለው ተመልክቷል፡፡በዚህ ጉዳይ መታየት ያለበት መሰረታዊ የክርክር ነጥብ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ የሰበር አቤቱታ ለማቅረብ የሚያስችል ህጋዊ መሰረት አለው ወይስ የለውም? የሚል ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ ጉዳይ ለሰበር ሰሚ ችሎት ብቁ ሁኖ ሊታይ የሚችለው ጉዳዩ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ ስለመሆኑ በቅድሚያ ሲረጋገጥ ነው፡፡ በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(3) (ሀ) ፣ በክልሉ ህገ መንግስት አንቀፅ 75 (2(ሐ)) እና የክልሉ ፍርድ ቤቶች እንደገና ለማቋቋም በወጣው የተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 43/1994 አንቀጽ 5(3) ድንጋጌ በግልጽ እንደተመለከተው አንድ ጉዳይ ለሰበር ሰሚ ችሎት ብቁ የሚሆነው አቤቱታ የቀረበበት ጉዳይ የመጨረሻ ውሳኔ (Final court decision) ያገኘ መሆን ያለመሆኑን በቅድሚያ መረጋገጥ ያለበት መሰረታዊ ነጥብ ስለመሆኑ የድንጋጌዎቹ ይዘትና መንፈስ ያስገነዝቡናል፡፡ በመሆኑም ሰበር ሰሚ ችሎት የመጨረሻ ፍርድ ባላገኙ ጉዳዮች ውሳኔ የመስጠት ስልጣንና ኃላፊነት ያልተሰጠው መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በሌላ አገላለጽ ለሰበር ብቁ ያልሆኑ የመጨረሻ ፍርድ ያላገኙ ጉዳዮች በሰበር ሰሚ ችሎት ሊስተናገዱ የሚችሉበት ስርዓት አይኖርም፡፡

ስለሆነም በክልሉ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 110/1999 አንቀፅ 12(4) የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ያልተስማማ ወገን ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጨማሪ ይግባኝ ማቅረብ እንደሚችል እንዲሁም በዚሁ አዋጅ አንቀፅ 12(5) እንደተደነገገው በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ይኖራል ተብሎ ከታሰበ ሰበር ሰሚ ችሎቱ የማየት ስልጣን እንዳለው በግልፅ ተደንግጓል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያልደረሰና የመጨረሻ ፍርድ ያላገኘ ስለሆነ ፣ ሰበር ሰሚ ችሎቱ የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበት አለመሆኑን ተገንዝቦ ስልጣንን በተመለከተ ከተከራክሪ ወገኖች የቀረበለት ተቃውሞ ባይኖርም በፍትሃብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 9(1)እና 231(1) (ለ) እንደተመለከተው በራሱ አነሳሽነትም ቢሆን ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ቀርቦ ሊስተናገድ በሚችል ደረጃ የመጨረሻ ውሳኔ ያልተሰጠበት በመሆኑ ለዚህ ችሎት ብቁ አይደለም ስልጣን የለኝም በማለት መመለስ ና ማረም ሲገባው ተቀብሎ በማስተናገዱም ሆነ ውሳኔ መስጠቱየህግ ድጋፍ የለውም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የቀረበው ጉዳይ የገጠር መሬት አዋጅ ልዩ ከመሆኑና ገጠር መሬትን መሰረት በማድረግ ለሚነሱ ክርክሮች አወሳሰን፣ በአዋጁ አንቀፅ 12 የተደነገገውን ድንጋጌመሰረት ያደረገ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም አቤቱታ የቀረበበት ውሰኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት እና ሊታረም የሚገባው ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች ክልል መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 02504 ሚያዝያ 13 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ሥ/ሥሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት በአብላጫ ድምፅ ተሽሯል፡፡

2. በአመልካች ላይ ክስ የቀረበው የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦች ክልል መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 110/1999 "ን" መሰረት በማድረግ በመሆኑ እና በዚህ አዋጅ መሰረት የሚቀርቡ ክርክሮች የሚመሩትም በዚሁ አዋጅ በመሆኑ፤በአዋጁ አንቀፅ 12(4) መሰረት የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለው ወገን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ሳይታይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ተቀብሎ ማስተናገዱ አግባብ አይደለም ብለናል፡፡
3. ተጠሪ ጉዳዩን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ከማቅረቡ በፊት በሕጉ አግባብለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚችሎት የማቅረብ መብቱን ይህ ውሳኔ ቀሪ አላደረገውም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ አራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

<u>የልዩነት ሐሳብ</u>

ስሜ በተ.ቁ 5 ላይ የተሰየመው ዳኛ አብላጫው ድምጽ ጉዳዩ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ ሊስተናገድ በሚችል ደረጃ የመጨረሻ ውሳኔ ያልተሰጠበት ሆኖ ሳለ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ተቀብሎ ማስተናገዱ ተገቢ አይደለም በማለት በደረሰበት መደምደሚያ ስላልተስማማሁ በሐሳብ ተለይቻለሁ፡፡

አብላጫው ድምጽ ጉዳዩ የገጠር እርሻ መሬት ክርክርን የሚመለከት በመሆኑ ለጉዳዩ አወሳሰን ተፈጻሚነት ያለው ሕግ የክልሉ የገጠር መሬት አሥተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 110/99 ነው፡፡በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 (4) መሠረት የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል በማለት የሚደነግግ በመሆኑ እና ተጠሪ የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያላቀረቡ በመሆኑ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ የተመለከተው የመጨረሻ ውሳኔ ባላገኘበት ሁኔታ ነው በማለት ጉዳዩን ተቀብሎ ማስተናገዱ ተገቢ አይደለም ከሚል መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡

የክልሉን ፍ/ቤቶች እንደገና ለማቋቋም ተሻሽሎ የወጣው አዋጅ ቁጥር 43/94 አንቀጽ 5/2 የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የከፍተኛው ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣኑ ውሣኔ የሰጠበትን ጉዳይ እንዲሁም የከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ሰሚነት ሥልጣኑ የወረዳ ፍ/ቤት ከሰጠው ውሳኔ የተለየ ውሳኔ የሰጠበትን ጉዳይ የማየት ሥልጣን አለው በማለት ይደነግጋል፤የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 5/3 የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበትን እና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት ያለበትን ክልላዊ ጉዳይ የማየት ሥልጣን እንዳለው ይደነግጋል፡፡

የክልሉ የገጠር መሬት አሥተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 110/99 አንቀጽ 12/4 ከፍተኛው ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ወገን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል በማለት የሚደነግግ ቢሆንም ይህ አዋጅ የክልሉን የገጠር መሬት አሥተዳደር እና አጠቃቀም ለመወሰን የወጣ አዋጅ እንጂ የሰበር አቤቱታ አቀራረብ ሥርዓትን ለይቶ ለመወሰን የወጣ ባለመሆኑ የድንጋጌው ይዘት እና ዓላማ የክልሉን ፍ/ቤቶች ለማቋቋም ተሻሽሎ ከወጣው አዋጅ ቁጥር 43/94 ድንጋጌዎች እና ከይግባኝ መብት ተፈጻሚነት ጋር ተጣጥሞ ሊተረጎም የሚገባው ነው፡፡በመሠረቱ ይግባኝ ማቅረብ ሕገመንግሥታዊ ዋስትና ያለው የተከራካሪዎች መሠረታዊ መብት ነው፡፡ሕግ አውጪው በአዋጅ ቁጥር 110/99 አንቀጽ 12/4 ላይ

ያስቀመጠው ድንጋጌም ይህን መሠረታዊ መብት ለማስከበር እንጂ ለተከራካሪ ወገኖች ተደጋጋሚ የሆነ የይግባኝ መብት ለመስጠት እንዳልሆነ ከአዋጁ አጠቃላይ ይዘት እና ዓላማ መገንዘብ ይቻላል፡፡ከይግባኝ መብት ተፈጻሚነት አኳያ በአዋጁ አንቀጽ 12/4 ንኡስ 4 የተቀመጠው የይግባኝ መብት ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚገባው የወረዳው ፍ/ቤት ውሳኔ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሳኔ ለተሻሻለበት ወይም ለተሻረበት ወገን እንጂ የወረዳው ፍ/ቤት ውሳኔ ለጸናበት ወገን አይደለም፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ የወረዳው ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ከፍተኛው ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ የወረዳውን ፍ/ቤት ውሳኔ ያጸናው በመሆኑ እና የወረዳው ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ በከፍተኛው ፍ/ቤት በይግባኝ ታይቶ ባልተሻረበት ወይም ባልተሻሻለበት ሁኔታ ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ድጋሚ ይግባኝ የሚያቀርቡበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡በመሆኑም ከፍተኛው ፍ/ቤት በይግባኝ ሰሚነት ሥልጣኑ የወረዳውን ፍ/ቤት ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ውሳኔ በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 75/2(ሐ) እና በአዋጅ ቁጥር 43/94 አንቀጽ 5/3 መሠረት ጉዳዩን የመመልከት ሥልጣን  አለው፡፡

በአጠቃላይ ከፍተኛው ፍ/ቤት በይግባኝ ሰሚነት ሥልጣኑ ጉዳዩን አይቶ የወረዳው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ ያጸናው  በመሆኑ ውሳኔው የመጨረሻ ነው፡፡በመሆኑም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 75/2/ሐ እና በተሻሻለው የክልሉ ፍ/ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 43/94 አንቀጽ 5/3 መሠረት ጉዳዩን አይቶ መወሰኑ ተገቢ ነበር በማለት በሀሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ሰ/ጌ

ቀን ሚያዚያ 30/2009 ዓ.ም

ዳኞች:-ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች:-አቶ ጤና ጋርደዉ - አልቀረቡም

ተጠሪ:- ወ/ሮ መደቅሴ ገርቢ - ወኪል ያደታ ጋሪደ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ ሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የእርሻ መሬት ጉዳይ ሆኖ የተጀመረው በጉደያ ቢላ ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የአሁንተጠሪ ከሳሽ የነበሩ ሲሆን አቶ ታከለ ቁያሳ ተከሳሽ እንዲሁም የአሁን የሰበር አመልካች ጣልቃ ገብ ነበሩ፡፡ተጠሪ አቅርበዉት የነበረዉ ክስ ይዘት:-የስር ተከሳሽ የነበረው አቶ ታከለ ቁያስ መጠኑ 1½ ሄክታር የሆነውን ይዞታ በ2006 ዓ.ም እኔ በማላውቀው ሁኔታ ያለ ፈቃዴ ይዞብኛል፡፡ ስለዚህ ተከሳሹ በሕገ-ወጥ መንገድ የያዘብኝን ይዞታዬን እንዲለቅልኝ የሚል ነው፡፡

የስር ተከሳሽ በሰጡት መልስ ይዞታዉን በ01/08/2004 ዓ.ም በተፃፈው ውል አቶ ጤና ጋረደው ላይ ኮንትራት ወስጄ እያረስኩ እገኛለሁ እንጂ ከሳሽ እንደሚሉት አይደለም፣ ከሳሽ እኔ ኮንትራት የወሰድሁት መሬት ላይም ምስክር ሆነው በውላችን ላይ ስለነበሩ ሊጠይቁኝ አይችሉም በማለት ተከራክሯል፡፡የአሁኑ አመልካችም የስር ጣልቃ ገብ ሲሆኑ ከሳሽ ድንበሩን እና ቦታውን ጠቅሳ ክስ የመሰረተችበት ይዞታ መሬት በአከባቢያችን ባህል መሰረት በ1986 ዓ.ም እኔ ጋብቻ ስፈፅም ከሳሽ እና አባቴ አብረው በመሆን ሰጥተውኛል፡፡ ከዚያ ወዲህም ይህንን ንብረት እየተጠቀምኩበት ቆይቼ በ01/08/2004 ዓ.ም በተፃፈው ውል እስከ 2007 ዓ.ም ለ3 /ሶስት/ አመት ለተከሳሹ አከራይቻለሁ፡፡ ስለዚህ ከሳሽ የእሷ ባልሆነ ይዞታ ላይ የእሷ አስመስላ ክስ ማቅረቧ ትክክል

ስላልሆነ መዝገቡ እንዲዘጋ በማለት አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ጣልቃ ገብ ክርክር ያስነሳው ይዞታ በወቅቱ በአካባቢያችን ባህል መሰረት ጋብቻ ስፈፅም በስጦታ መልክ ተሰጥቶኛል በማለት ያቀረበው አቤቱታ እውነት አይደለም፡፡ እኔም ሆንኩ አባቱ ይህንን ይዞታ ለጣልቃ ገብ አልሰጠንም፡፡ እስካሁን ድረስም በባሌ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ስለሆነ የጣልቃ ገቡ አቤቱታ ውድቅ ሆኖ ከክርክር ውስጥ እንዲወጣ በማለት ተከራክሯል፡፡

የወረዳ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃዎችን ተመልክቶ ክርክር ያስነሳው ይዞታ በፊት የከሳሿ እና የባሏ የነበረ መሆኑ ከቀረበው የሰውና የፅሁፍ ማስረጃ መረዳት ይቻላል፡፡ ተከሳሽ ደግሞ ይዞታውን ከጣልቃ ገብ በኮንትራት ወስዶ ይዞታውን በተከታታይ ለሶስት አመታት ያረሰ መሆኑ፣ ይዞታው ደግሞ በ1986 ዓ.ም ጣልቃ ገቡ በሚያገባበት ወቅት በአካባቢው ባሕል መሰረት "ጎጆ መውጫ" በሚል ስጦታ ተሰጥቶት ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ይዞታውን በመያዝ እንደአስፈላጊነቱ ሲፈለግ በራሱ እያረሰ ሌላ ጊዜ ደግሞ እኩል እየሰጠ የሚጠቀምበት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ከሳሽ ተከሳሹ ክርክር የተነሳበትን መሬት ለሶስት አመት ማረሱን እና ጣልቃ ገቡ ደግሞ ለረጅም አመታት ይዞ መቆየቱን እያወቀች ይህንን ሁሉ ጊዜ ቆይታ በአሁኑ ወቅት በ2006 ዓ.ም ተይዞብኛል በማለት ክስ ማቅረቧ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1149/2/ ድንጋጌ መሰረት የሕግ አግባብነት የሌለው ስለሆነ ክርክር የተነሳበት ይዞታም ለረጅም ጊዜ በተለያየ ምክንያት ከከሳሿ እጅ የወጣ በመሆኑ ያቀረበችው ክስ የሕግ አግባብነት ያለው ስላልሆነ ተከሳሹን አያስጠይቅም በማለት ዓ.ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ የወረዳው ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮ ክርክር የተነሳበት ይዞታ የአሁን ተጠሪ መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የስር ፍርድ ቤት ይህንን አልፎ ክርክር የተነሳበትን መሬት ይግባኝ ባይዋ በፍ/ሕ/ቁ. 1149/2/ መጠየቅ አትችልም ብሎ ክሷን ውድቅ ማድረጉ ከደንብ ቁጥር 152/32 ጋር የሚቃረን ስለሆነ የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነዉ በማለት ዉሳኔዉን በመሻርክርክር ያስነሳዉ ይዞታ ለአሁን ተጠሪ ይገባል ሲል አመልካች እንዲለቅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁኑ አመልካች በውሳኔው ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ አያስቀርብም በማለት ይግባኙን ዘግቷል፡፡አመልካች የከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጡትን ውሳኔ በመቃወም ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን የክልሉ ሰበር ሰሚ የግራ ቀኙን ካከራከረ በኂላ ውሳኔውን አፅንቷል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት ነዉ፡፡

አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት፡- ከከፍተኛ ፍርድ ቤቱ እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአካባቢውን ባህልና ወግ መሰረት ሳያደርጉ በጋብቻ ላይ በጎጆ መውጫነት የሚሰጠው መሬት ሰጪው በሕይወት እያለ ወደ ራሴ ይዙርልኝ ጥያቄ መቅረብ እንደማይገባ፣ አመልካች ግን በዚሁ በተሰጠኝ ቦታ ላይ ቤት ንብረት አፍርቼ የወለድኩበት መሆኑን ሳይረዱ የመሬቱ ስምም ሆነ መታወቂያው በወላጅ አባቴ ስም ስለሚገኝ ብቻ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ንብረት እና ይዞታ እንድለቅ መወሰኑ ሕግን የተከተለ አይደለም፡፡ የአሁኗ ተጠሪም ለክርክሩ መነሻ በሆነው ይዞታ ኮንትራት ውል ላይ እንደምስክር ሆና የፈረመችበት ስለመሆኗ በስር ወረዳ ፍርድ ቤት ላይ በግልፅ ተቀምጦ እያለ ከከፍተኛ ፍርድ ቤቱ እስከ ክልሉ ሰበር ሰሚ ያሉት ችሎቶች ግን ሌላ ማስረጃ ሳያስቀርቡ ከ20 አመት በላይ በእጄ ይገኘ የምጠቀመበት ይዞታ መሆኑ በማስጃዎቼ ተረጋግጦልኝ እያለ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ ሕግ ስህተት ስለሆነ ተሽሮ የጉደያ ቢላ ወረዳ ፍርድ ቤት ዉሳኔ እንዲፀናልኝ የሚል ነዉ፡፡

አቤቱታው ተመርምሮ አመልካች አከራካሪውን መሬት በ1986 ዓ.ም በስጦታ አግኝቶ እስካሁን እየተጠቀመበት ባለበት ሁኔታ እንዲያስረክብ መወሰኑን ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ መልስ ባለማቅረባቸዉ መልስ የመስጠት መብታቸዉ ታልፎ ጥቅምት 07 ቀን 2009 ዓ.ም ዉሳኔ ተሰጥቶ የነበረ ቢሆንም በሌሉበት የተሰጠዉ ዉሳኔ እንዲነሳላቸዉ ተጠሪ አቤቱታ አቅርበዉ ተቀባይነት በማግኘቱ ዉሳኔዉ ተነስቶ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ ለአቤቱታዉ የሰጡት መልስ ይዘት፡- አመልካች ክርክር ያስነሳዉን መሬት አንዴ በሕጋዊ መንገድ ተሰጥቶኛል እያለ፤ አንዴ ደግሞ ስጦታዉ ተፈጻሚ የሚሆነዉ የአካባቢዉን ባሕል መሰረት በማድረግ ነዉ በማለት የሚያነሳዉ ነጥብ የሕግ ድጋፍ የለዉም፡፡ተጠሪ ዉል አለማድረጓን ከሥር ጀምራ የተከራከረች ሲሆን የወረዳዉ መሬት እና የአከባቢዉ ጥበቃ ጽ/ቤት በጻፈዉ ደብዳቤ ይዞታዉ በተጠሪ ባለቤት ስም እንዳለ እንጂ በስጦታ ስለመተላለፉ የቀረበ ማስረጃ የለም የሚል ሆኖ እያለ አመልካች ዉል ለመኖሩ ተረጋግጦልኛል የሚለዉ ተቀባይነት የለዉም፡፡ አመልካች በ1986 ዓ.ም ሲያገባ ሁለት ሄክታር መሬት ተሰጥቶት ነበር ቢባል እንኳ አንድም ቀን ተጠቅሞበት እንደማያዉቅ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ መሬቱን ይዛ እስከ አሁን ግብር እየከፈለች ስትጠቀምበት እንደነበረ እና አመልካች ደግሞ የገጠር መሬት ትቶ ቢላቲ ከተማ ይኖር እንደነበረ በመ/ቁ 09086 ላይ በቀረበዉ ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም የአመልካች አቤቱታ ዉድቅ ተደርጎ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ዉሳኔ ይጽናልኝ የሚል ነዉ፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታቸዉን በሚያጠናክር መልኩ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከላይ የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን ከስር ፍ/ቤት ዉሳኔ እና ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል ተብሎ ከተያዘዉ ጭብጥ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነዉም የአሁኑ አመልካች ያቀረባቸው ሁለት የሰው ምስክሮች ክርክር የተነሳበትን ይዞታ እንደሚያውቁ፣ በ1986 ዓ.ም ጣልቃ ገቡ ሲያገባ በአካባቢው ባሕል መሰረት ለጎጆ መውጫ ተጠሪ ከባሏ ጋር ክርክር ያስነሳዉን ይዞታ ለአመልካች መስጠታቸውን እና ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ይዞታዉን አመልካቹ ይዞ አንዳንዴ በራሱ እያረሰ እየተጠቀመ፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የእኩል ሰጥቶ የሚጠቀምበት መሆኑን፣ በአሁኑ ወቅት ደግሞ ለሶስት አመት ኮንትራት ለስር ተከሳሹ መስጠቱን እንደሚያውቁና ይዞታው ከ20 አመት በላይ በአመልካች እጅ የሚገኝ መሆኑን እንደመሰከሩ የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔ ያረጋግጣል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአካባቢው ባህል መሰረትአመልካቹ ክርክር የተነሳበት ይዞታ መስጠቱን የሚገልፅ መጋቢት 12 ቀን 1986 ዓ.ም የተፃፈ የስጦታ ውል ቀርቧል፡፡ ሌላዉ በአመልካች እና በስር ተከሳሽ መካከል በተደረገዉ የኪራይ ዉል ተጠሪ በምስክርነት መፈረሟና በስር ፍ/ቤት በተደረገዉ ክርክር ይህንኑ በግልጽ ክዳ አለመከራከሯ መሬቱ ለአመልካች በስጦታ የተሰጠ መሆኑን በተጨማሪነት የሚያረጋግጥ ነዉ፡፡ የተጠሪ ምስክሮችም ቢሆኑ የስር ተከሳሽ መሬቱን በምን መልክ መያዙን ባያዉቁም ለ3 ተከታታይ ዓመት ይዞ እያረሰ ይጠቀምበት መሆኑን መመስከራቸዉ ሲታይ ተጠሪ በመሬቱ መጠቀም ካቆሙ ረጅም ጊዜ ያለፈዉና የአመልካችን ክርክር የሚያጠናክር መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የወረዳዉ ፍ/ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ ለመሻር የሰጠዉ ምክንያት የእርሻዉ መሬት እስካሁን በተጠሪ ባለቤት ስም ተመዝግቦ የሚገኝ እና ግብር የሚከፈልበት መሆኑን ነዉ፡፡ ነገር ግን ክርክር ያስነሳዉ መሬት በ1986 ዓ.ም አመልካች ሲያገባ ለጎጆ መዉጫ ተብሎ እስከተሰጠዉና በተግባር በይዞታዉ ስር አድርጎ በራሱም ሆነ እያከራዩ ከ20 ዓመት በላይ እየተጠቀመበት የሚገኝ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ በአባቱ ስም መሆኑና ግብር መከፈሉ ብቻ በመሬቱ ላይ ያለዉን የባለይዞታነቱን መብት አያስቀርበትም፡፡

በመሠረቱ የኦሮሚያ ክልል ገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 130/1999 አንቀፅ 2/3/ ሕጋዊ የመሬት ይዞታ ማለት ሕጋዊ በሆነ ሁኔታ አግባብ ባለው አካል ለተጠቃሚዎች የተሰጠ መሬት፣ ወይም በውርስ ወይም በስጦታ የተገኘ መሬት ማለት ነው በማለት ሲደነግግ፤ የአዋጁ አንቀጽ 9(5) ደግሞ ባለይዞታዉ በመሬት ይዞታው የመጠቀም መብቱን በዚያ መሬት ገቢ ለሚተዳደሩ ወይም ሌላ ገቢ ለሌላቸው የቤተሰብ አባላት ወይም መሬት ለሌላቸው ልጆቹ በስጦታ ማስተላለፍ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ተጠሪና ባለቤታቸው ለአሁኑ አመልካች ክርክር የተነሳበትን ይዞታ በስጦታ አስተላልፈዉ ተጠቃሚ አድርገዉታል፡፡ አመልካች ከ20 ዓመት በላይ ተጠቃሚ የሆነበት መሬት መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ መሬቱ በስጦታ

ሰጪዉ ስም እስከአሁን ተመዝግቦ መገኘቱ እና ግብር በስሙ መከፈሉ ብቻ ይዞታዉ በስጦታ ዉል አልተላለፈም የሚያሰኝ አይሆንም፡፡

ሲጠቃለል አመልካች ክርክር የተነሳበትን መሬት በሕጋዊ መንገድ አግኝተው ከ20 /ሃያ/ አመት በላይ በእጃቸው ይዘው በራሳቸዉም ሆነ አከራይተዉ ሲጠቀሙበት የቆዩ መሆናቸው በሚገባ ተረጋግጦ እያለ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች ይዞታውን ለተጠሪ እንዲመልሱ በማለት ዉሳኔ መስጠቱ የአመልካችን ከይዞታዉ ያለመፈናቀል ሕገ-መንግስታዊ መብት የሚጥስ ሆኖ እያለየክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ሆነ ሰበር ሰሚ ይህን ተቀብለው በማጽናት የሰጡት ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በምስራቅ ወለጋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 35592 ጥር 18 ቀን 2007 ዓ.ም ተሰጥቶ፤በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 191823 የካቲት 20 ቀን 2007 ዓ.ም በተሰጠ ዉሳኔእናበኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ በመ/ቁ 203567 ታሕሳስ 18 ቀን 2008 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የጉደያ ቢላ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 69933 ታሕሳስ 02 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
3. ክርክር ያስነሳዉ የእርሻ መሬት አመልካች ለተጠሪ ለማስረከብ አይገደድም ተብሎ ተወስኗል፡፡
4. አፈጻጸሙ ለጊዜዉ ታግዶ እንዲቆይ ታሕሳስ 19 ቀን 2009 ዓ.ም የተሰጠዉ የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡
5. የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

የሰ/መ/ቁ. 115387

ሚያዚያ 26 ቀን2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሀመድ

ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ

ቀነዓ ቂጣታ

ፀሐይ መንክር

አመልካቾች፡- 1ኛ አቶ መክብብ ተስፋ } ጠበቃ ወረቅአገኘሁ ፀጋው

2ኛ ወይዘሪት እስራኤል ተስፋ

ተጠሪ፡- 1ኛ ወ/ሮ ፀሐይ ለገሰ ቀረቡ

2ኛ ወ/ሮ ጽጌ አሰፋ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

1. ጉዳዩ የመንግስት ቤት ከመከራየት መብት ጋር የተያያዘ ሲሆን የጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር አመልካቾች ከሳሾች ተጠሪዎች ተከሳሾች በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁኑ አመልካቾች ሐምሌ 23 ቀን 2006 ዓ.ም ባቀረቡት ክስ በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 በቀድሞ ወረዳ 01 ቀበሌ 04 ቤት ቁጥር 085 ሦስት ክፍልና ሰርቪስ ያለው ቤት ከመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ንብረት የሆነውን ቤት ተከራይተው እንደሚኖሩ፤እስከ 2006 ዓ.ም ድረስም የመንግስት ኪራይ እንደከፈሉ፤ የአሁኑ ተጠሪዎች መንግስት ባከራያቸው የቤት ቁጥር 085 ገብተው ይኖራሉ፡፡ ተጠሪዎች ቤቱን ለቀው እንዲወጡ ቢጠይቋም ለቀው ለመውጣት ፈቃደኛ አይደሉም፡፡ በመሆኑም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1206/2035 መሰረት ቤቱን ያስረክቡ፤ያለአግባብየተጠቀሙበትን የቤት ኪራይ የመጠየቅ ይጠበቅልን እንዲሁም በክርክሩ ያወጣነው ወጪና ኪሣራ እንዲተኩ የመጠየቅ መብታችን ይጠበቅልን ሲሉ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

2. የአሁኑ ተጠሪዎች ባቀረቡት የመከላከያ መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እንዲሁም በፍሬ ነገር ጉዳዩ መልስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪዎች ባቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በቤቱ መኖር ከመጀመሩ ከ10 ዓመት በላይ በመሆኑ ክሱ በይርጋ ቀሪ እንደሚሆን የተከራከሩ ሲሆን በፍር ጉዳዩም 1ኛ ተጠሪ ወላጅ አባታቸው ከ1982 ዓ.ም ጀምሮ አባቴ ከአቶ ተስፋ አበበ ተከራይቶ ሲኖር ቆይቷል፡፡ አመልካቾች የተከራዩት የቤት ቁጥር 085 ብቻ እንጂ 3 ሰርቪስ ቤት ለመሆኑ ማስረጃ የላቸውም፡፡ ጉዳዩ በዚህ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 121070 እየታየ በመሆኑ ተጣምሮ እንዲታይ እና ክሱ ውድቅ እንዲደረግ የጠየቁ ሲሆን፤2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው አመልካቾች የተከራዩት ፎቁን ብቻ ነው፡፡ ቤቱ ከዛሬ 16 ዓመት በፊት ድሀ በመሆኔ በቀበሌ አመራሮች የተሰጠኝ ነው፡፡ አመልካቾች ተከራዩት ቤት ውጪ ባለው ይዞታ ላይ ክስ ሊያቀርቡብኝ አይገባም ክሱ ወድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

3. የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ በተጠሪዎች የቀረበው የመጀመሪያ መቃወሚያ ክሱ የመፋለም ክስ በመሆኑ የይርጋ መቃወሚያው ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም፡፡ አመልካቾች ያቀረቡት ክስ የመፋለም ክስ የሚመለከት ቢሆንም የቤት ቁጥር 085 የሆነ ቤት ባለቤት አመልካቾች እንዳልሆኑ እና ቤቱ በመንግስት የሚተዳደር ቤት ስለመሆኑ ከሳሾች በኪራይ ከመንግስት የያዙት ስለመሆኑ በቀን 01/13/2004 ዓ.ም በአመልካቾች እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ማዕከል የተደረገው ውል መረዳት የሚቻል ሲሆን ይህ ፍሬ ነገር በግራ ቀኙ ያልተካደ ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ አመልካቾች በቤቱ ላይ ያላቸው መብት የባለሀብትነት ሳይሆን ቤቱን በመከራየታቸው የባለይዞታነት መብት ብቻ እንዳላቸው መረዳት ይቻላል፡፡ አመልካቾች ያላቸው መብት የባለይዞታነት መብት ቢሆንም ያቀረቡት ክስ የመፋለም ይዘት ያለው ክስ ነው፡፡ የመፋለም ክስ ማቅረብ የሚችለው የባለሀብትነት መብት አለኝ የሚል ወገን ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ አመልካቾች ያላቸው መብት የተከራይነት ወይም ባለይዞታነት መብት እንደመሆኑ መጠን የባለቤትነት ወይም የመፋለም ክስ ለማቅረብ የሚችሉ አይሆንም፡፡ ስለሆነም አመልካቾች የባለመብትነት መብት ሳይኖራቸው ተጠሪዎች የቤት ቁጥር 085 የሆነውን ቤት ለቀው ያስረክቡኝ ሲሉ ያቀረቡት የመፋለም ክስ በሌላቸው መብት ያቀረቡት እና ህጉን ያላገናዘበ ዳኝነት በሆኑ ፍርድ ቤት ጥያቄው እንዳልተቀበለው፤አመልካቾች የማከራየት መብት ያላቸው ስላልተረጋገጠ ከተጠሪዎች ኪራይ ለመጠየቅ የሚችሉበት የህግም ሆነ የውልምክንያት ስላላቀረቡና ስላላስረዱ ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡ የአሁኑ አመልካቾች የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት

አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ በመቃወም ለማሳረም ነው፡፡

4. አመልካቾች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታም የቤት ቁጥር 085 ህጋዊ ተከራይ መሆናቸው በተረጋገጠበት እንዲሁም የመንግስት ቤቶችኤጀንሲ ስለ ሰርቪስ ቤቶች አስተያየት ሳይሰጥ የአመልካቾች ክስ የመፋለም ይዘት ያለው ነው፡፡ ተብሎ ውድቅ መደረጉ በአግባቡ አይደለም የሚል ክርክር ማቅረባቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካቾች አቤቱታ ተመርምሮ አከራካሪው ቤት ከመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ የተከራዩት መሆኑ እየገለፁ እና ተጠሪዎች ሠርቪስ ቤቶች ለቀው እንዲያስረክቡ በመጠየቃቸው እየታየ ክሱ ያመፋለም ይዘት ያለው በመሆኑ የመፋለም ክስ የማቅረብ መበት የላቸውም ተብሎ ውድቅ የመደረጉ አግባብነት ተጠሪዎች ባሉበት ይጣራ ዘንድ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ተጠሪዎችምበተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ቀርበው በሰጡት መልስ የስር ፍርድ ቤቶች ውሣኔና ትእዛዝ እንዲፀና አመልክቷል፡፡

የመልሰ መልስም ቀርበዋል፡፡

5. ከሥር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የስር ፍርድ ቤቶች ውሣኔና ትእዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

6. ከክርክሩ ሂደት እንደተገነዘብነው አመልካቾች ንብረትነቱ የመግንስት የሆነው የቤት ቁጥር 085 መከራየታቸውን የተከዳ ጉዳይ የአይደለም፡፡ በዚህ መዝገብ አከራካሪ የሆነው በተጠሪዎች የተያዙት ሰርቪስ ቤቶች የቤት ቁጥር 085 አካል ቻው ወይስ አይደለም?ሰርቪስቤቶቹ የቤት ቁጥር 085ቢሆኑ ተጠሪዎች ለረጅም ዓመት እንዴት ሊኖሩበት ቻሉ? የሚል ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎች አጥብቀው የሚከራከሩት ከ1982 ዓ.ም ጀምሮ 1ኛ አመልካች ከወላጅ አባታቸው አቶ ለገሰ ገመታ በዚህ ቤት ሲኖሩ እንደነበር 2ኛ ተጠሪም ከ16 ዓመት በፊት ደሀ በመሆናቸው ቤቱ በቀበሌ አመራር እንደተሰጣቸው ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩ ያየው ከመፋለስ ክስ ጋር በማያያዝ በመሆኑ በግራ ቀኙ ያለው ክርክር ባህሪና ይዘት ባገናዘበ መልኩ ጉዳዩን ያጣራው አይደለም፡፡

7. አመልካቾች ያቀረቡት ክስ የመፋለም ይዘት አለው እንኳ ቢባል የመንግስት ቤት ተከራይቶ የሚኖሩ መሆኑ በክሳቸው በመግለፅ ባመለከቱበት ሁኔታ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.1206 በመጠቀሱ ብቻ ክሱ የባቤትነት መብት የመጠየቅ ክስ ነው የሚባልበት ህጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡ የአመልካቾች መብት በተከራዩነት የተገደበ መሆኑ ከተረጋገጠ ያቀረቡትክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.91 መሰረት ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ በሚያግዝ መልኩ እንዲሻሻሉ ማዘዝም ይቻል ነበር፡፡ አመልካቾች የተከራዩት ቤት ቁጥር 085 የአሁኑ ተጠሪዎች የያዙት ክፍል የሚያጠቃልል ከሆነ ክሱ ለማቅረብ አይችሉም የሚባልበት ሁኔታ

አይኖርም፡፡አንድ ተከራይ የተከራየው ቤት ላይ ያለውን ህጋዊ መብት ለማስከበር የክርክር አድማሱን የይዞታ ክርክር አደርጎ በመገደብ ማጣራት የሚቻልበት ሁኔታ ሕጉ የሚከለክል ሆኖ አልተገኘም፡፡

8. አከራካሪው ቤት የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ መሆኑ አልተካደም፡፡ የቤቱ አከራይ የሆነውመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ ግራ ቀኙ እያከራከረባለው ጉዳይ የበኩሉን አስተያየት እንዲሰጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.39/1/ እና 40/2/ መሰረት የክርክሩ ተከፋይ ሊሆን ይገባ ነበር፡፡ በተያዘው ጉዳይ አከራካሪ የሆነው ነጥብ የባለቤትነት መብት መፋለም ክስ ሳይሆን ተከራይነት የተገኘው የባለይዞታነት መብት ለማስከበር የቀረበ ክስ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም የአሁኑ ተጠሪዎች ለክሱ መነሻ የሆኑ ሰርቪስ ቤቶች መቼ እንደያዙት ?ቤቶቹ ለመያዝ የቻሉበት ህጋዊ ምክንያት መኖሩ አለመኖሩን?በተጠሪዎች የተያዙት ሰርቪስ ቤቶች ላይ የመከራየት መብት ያቋቋሙ መሆን አለመሆናቸው?በአጠቃላይ ተጠሪዎች ሰርቪስ ቤቶቹ ይዘው የሚቀጥሉበት ህጋዊ ምክንያት መኖር አለመኖሩን?በዝርዝር መጣራት ያለበት ጉዳዩ ነው፡፡ ከዚህ በተያያዘ የመንግስት ቤቶች ኤጀሲ ከአመልካቾች ጋር የቤት ቁጥር 085 አደረገው የተባለው የኪራይ ውል ለክርክሩ መነሻ የሆኑትን ሰርቪስ ቤቶቹን የሚያጠቃልል መሆን አለመሆኑን የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 39/1/ እና 40/2/ መሰረት ወደ ክርክሩ እንዲገባ ተደርጎ ጉዳዩ መጣራት ያለበት ስለመሆኑ የክርክር ይዘትና ባሕሪ ያለመክታል፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የስር ፍርድ ቤቶች ግራ ቀኙ እያከራከረ ያለው የተከራይነት መብት ሆኖ ሳለ በአመልካቾች ክስ የፍ/ሕ/ቁ. 1205 በመጥቀስ ብቻ የመፋለም ክስ የማቅረብ መብት የላቸውም በማለት ውድቅ ማድረጋቸው በጉዳዩ መሠረታዊ የህግ ስህተት መፈፀሙን የሚያሳይ በመሆኑ ሽረን ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 120983 በ03/04/2007 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ፤የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 165941 በ29/08/2007 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽሮአል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የተዘጋው መዝገብ በማንቀሳቀስ በፍርድ ይዘቱ በተገለፀው አግባብ አመልካቾች እና ተጠሪዎች እያከራከረ ያለው የተከራይነት መብት የመንግስት ቤች ኤጀንሲ ወደ ክርክሩ እንዲገባ በማድረግ ለክርክሩ መነሻ የሆኑት ሰርቪስቤቶች የቤት ቁጥር 085 አካል ናቸው ወይስ አይደሉም?የአሁኑ ተጠሪዎች በሰርቪስ ቤቶቹ መኖር የጀመሩት ከመቼ ጊዜ ጀምሮ ነው? ሰርቪስ ቤቶቹ እንዴት ሊይዙት ቻሉ?ተጠሪዎች ከ10 ዓመት በላይ ቤቱን ይዘው እየኖሩ ከሆነ የሚኖረው

ሕጋዊ ውጤት ምንድን ነው?የአሁኑ ተጠሪዎች ሰርቪስ ቤቶቹ ይዘው የሚቀጥሉበት ህጋዊ ምክንያት መኖር አለመኖሩን በግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ እንዲሁም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 145 በሚያዘው አግባብከሚመለከተው አካል ተገቢ ማስረጃ በማስቀረብ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 264/1/ የሰው ምስክሮች ጭምር በመስማት ተገቢ ህጋዊ ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1/ መሰረት መልሰንለታል፡፡ይፃፍ፡፡

3. የዚህ ፍርድ ቤት ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. የዚህ ፍርድ ቤት ውሣኔ ለስር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ ብለናል፡፡ መዝገቡን ዘግተን ወደ መ/ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

# የዳኘነት ሥልጣን

የሰ/መ/ቁ.121660

ሕዳር 26 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች(ዎች)፡- አቶ ለገሰ ገለታ ቀርቧል

ተጠሪዎች ፡- 1. የአ/አ/አስ/መሬት ልማትና ማኔጅመንት } ነ/ፈጅ በሀይሉ ክብረት ቀረቡ

2. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት ተጠሪዎች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ፣ አመልካች ምትክ ቦታ ሊሰጣት ይገባል በማለት፣ የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ተጠሪዎች ያቀረቡትን የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ተቀብሎ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ ውሳኔ ሊሰጥ ይገባል በማለት የሰጡት የሕግ ትርጉምና ውሳኔ ሕጋዊ አግባብነት ያለው መሆኑን በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡
2. የጉዳዩ መነሻ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ፣ አመልካችና በዚህ ሰበር ችሎት የክርክሩ ተሳታፊ ባልሆነውና በሥር ሁለተኛ የፍርድ መቃወም ተጠሪ ሆኖ ስሙ በተገለጸው የቀድሞው የቦሌ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና ባንክ የከተማ ልማት ማደስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት( በአሁኑ አጠራርየቦሌ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር መምሪያ) መካከል የነበረውን የካሳና የምትክ

ቦታ ክርክር ሰምቶ፣ መልስ ሰጭ ለአመልካች ምትክ ቦታ የመስጠት ግዴታ አለበት በማለት በመዝገብ ቁጥር 330/99 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ነው፡፡ ተጠሪዎች ይህ የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሰጠውን ውሳኔ፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የከተማው አስተዳደር አካላት(ተጠሪዎች) በመልሥ ሰጭነት ሳይጠሩና ክርክራቸውን ሣያቀርቡ የተሰጠና የከተማውን አስተዳደር፣ ሕዝብ መብትና ጥቅም የሚጎዳ በመሆኑ ጉዳዩ የሚመለከተን የከተማው አስተዳደር አካላት(ተጠሪዎች) ባለንበት እንደገና ታይቶ ሊወሰን ይገባል በማለት ሀምሌ 6 ቀን 2007 ዓ.ም የተጻፈ የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ፣ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 358 በመጥቀስ ለከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ አቅርበዋል፡፡

3. የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተጠሪዎችን ፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ ከመረመረ በኋላ ለጉዳዩ አግባብነት አላቸው የሚላቸውን የህግ ድንጋጌዎች በመጥቀስ፣ ተጠሪዎች የፍታብሔር ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 358 በመጥቀስ ያቀረቡትን የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ ተቀብሎ ለማስተናገድና ቀደም ብሎ የሰጠውን ፍርዱ እንደገና ለማየት የሚያስችለው የህግ መሰረትና ሥልጣን የሌለው መሆኑን ገልጾ፣ ተጠሪዎች ያቀረቡትን መቃወሚያ አይቶ ውሳኔ ለመስጠት ሥልጣን የለኝም በማለት የጉ/መዝገብ ቁጥር 330/99 ሀምሌ 16 ቀን 2007 ዓ.ም በሰጠው ብይን ውድቅ አድርጎታል፡፡

4. ተጠሪዎች የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት፣ ይግባኝ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት፣ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የፍታብሔር ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 358ና ተከታይ ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ ተጠሪዎች ያቀረቡትን የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ ለመቀበልና የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት ውሳኔ መስጠት ስልጣን አለው በማለት የይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ሰጠውን ብይን በመሻር ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ይግባኝ ሰሚው ችሎት የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተጠሪዎችን የፍርድ መቃወሚያ በመቀበልና የግራ ቀኙን ክርክር በመስማት ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነሥርዓት ሕግ ቁጥር 341(1) መሰረት መልሶ ልኮለታል፡፡

5. አመልካች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት፣ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም የሰበር አቤቱታ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ የከተማው የሰበር ችሎት የአመልካችን ሰበር አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ፣የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ጉዳዩን

መጀመሪያ አይቶ ውሳኔ የሰጠው ተጠሪነቱ ለአንደኛ ተጠሪ ሆነው የቀድሞው የቦሌ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና ባንክ ከተማ ልማት ማደስ ፕሮጀክት ጽ/ቤት( በአሁኑ አጠራር የቦሌ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር መምሪያ) በሁለተኛው ተጠሪ በኩል ተወክሎ ያለውን ክርክርና ማስረጃ ካቀረበ በኂላ ነው፡፡ ስለዚህ ተጠሪዎች ጉባኤው ቀደም ብሎ ውሳኔ የሰጠው የሚመለከታቸው የከተማው አስተዳደር አካላት(ተጠሪዎች) በመልሥ ሰጭነት ሳይጠሩና ክርክራቸውን ሣያቀርቡ የተሰጠ ነው በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተገቢነት የሌለውና የህግ መሰረት የሌለው ነው፡፡ ጉባኤው የሰጠው ውሳኔ ተጠሪዎችን መብትና ጥቅም የሚጎዳ ባለመሆኑና በአጠቃላይ ተጠሪዎች ያቀረቡት የፍርድ መቃወሚያ የህግ መሰረት የሌለው በመሆኑ፣የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ተጠሪዎች ያቀረቡትን የፍርድ መቃወሚያ ተቀብሎ እንዲያይ የሰጡት ብይን በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል በማለት አመልክተዋል፡፡

6. ተጠሪዎች በጋራ ባቀረቡት መልስ በጉዳዩ ተከራካሪ መሆን የነበረብን እኛ ነን፡፡ ጉባኤው እኛን በመልስ ሰጭነት ሣይጠራ የሰጠው ውሳኔ የከተማው አስተዳደርና ሕዝብ ጥቅም የሚጎዳ ነው፡፡ ተጠሪዎች በዚህ አይነት ሁኔታ የተሰጠን ፍርድ በመቃወም የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ ማቅረብ እንደምንችል የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 37502 አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሰጠበት በመሆኑ፣ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

7. ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በዚህ ሰበር ችሎት ግራ ቀኙ ያቀረቡት የጽሁፍ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ፣ ቀደም ብሎ በሰጠው ውሳኔ ላይ በፍ/ሥ/ሥ ሕግ ቁጥር 358ና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረት የሚቀርብለትን የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው፣ ቀደም ብሎ የሰጠውን ፍርድ እንደገና እንዲመረምር በሌሎች የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ተቀብሎ የማየት፣ ክርክር የመስማትና መርምሮ የመወሰን ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

8. ጉዳዩን እንደመረመርነው ከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ፣ በልማት ከይዞታቸው ለሚነሱና ንብረታቸውን ለሚያነሱ ሰዎች የካሣ ክፍያና ምትክ ቦታ ጥያቄና አቤቱታ ላይ አስተዳደራዊ ውሳኔ የመሥጠት ኃላፊነት ያለበትና በከተማ ቦታ በሊዝ ስለመያዝ ለመደንገግ የወጣው አዋጅ ቁጥር 272/1994 እና ይህንን አዋጅ ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 721/2004 መሰረት ሥልጣን የተሰጠው የከተማው አስተዳደር

"አግባብ ያለው አካል" ፣ ስለ ምትክ ቦታ ጥያቄውና ስለ ካሳ ክፍያ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኙ ሰዎች የሚቀርቡትን የይግባኝ ቅሬታ ተቀብሎና የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶና አጣርቶ ውሳኔ የመስጠት በሕግ የዳኝነት ሥልጣን የተሰጠው አካል ነው፡፡

9. ከላይ በተጠቀሱት አዋጆች የከተማ ቦታ እንዲለቅ የውሳኔ ማስታወቂያ የደረሰውና በአስተዳደራዊ ውሳኔው መብቴን ነክቶብኛል የሚል ሰው ለከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ይግባኝ ቅሬታ ከማቅረቡ በፊት አግባብ ላለው የአስተዳደር አካል በሰባት ቀናት ውስጥ አቤቱታ ማቅረብ አለበት፡፡የከተማ ቦታ እንዲለቅ የተሰጠውን ውሳኔ ማስታወቂያ በመቃወም አቤቱታ የቀረበለት አግባብ ያለው አስተዳደሩ አካል በጽሁፍ ውሳኔ መስጠት እንዳለበት በአዋጆቹ ተደንግጓል፡፡ የአስተዳደሩ አካል በአቤቱታው ላይ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ በውሳኔው ቅር ያለው ሰው ፣ለይግባኝ ሰሚ ጉባኤው የይግባኝ ቅሬታውን ስለሚቀርብበት ሁኔታ፣ የአዋጅ ቁጥር272/1994 በአንቀጽ 16 እና አንቀጽ17 በዝርዝር ባስቀመጣቸው ድንጋጌዎችና በአዋጅ ቁጥር 721/2004 በአንቀጽ 26፣ አንቀጽ 27ና በአንቀጽ 28 ድንጋጌዎች ተደንግጎ ይገኛል ፡፡

10. ከላይ በገለጽናቸውና ሌሎች አግባብነት ባላቸው የህግ ድንጋጌዎች ለከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት፣የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በከተማ ቦታ ማስለቀቅ፣ሂደት የሚቀርቡ የምትክ ቦታና የካሳ ጥያቄ ጉዳዮች ላይ የሚመለከተው አስተዳደር አካል በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ሰው የሚያቀርበውን የይግባኝ ቅሬታ፣ የመቀበል፣ የይግባኝ ባዩንና የመልስ ሰጭ ክርክር የመቀበል፣ ማስረጃ በትዕዛዝ ማስቀረብና አስፈላጊውን ማጣራት በማድረግ ውሳኔ የመሰጠት ሥልጣንን የሚያካትት ነው፡፡ ይህ የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ሥልጣን፣በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 ንዑስ አንቀጽ1፣በአዋጅ ቁጥር 272/1994 እና ይህንን አዋጅ ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 721/2004 መሰረት የተሠጠ የዳኝነት ሥልጣን ነው፡፡

11. የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤና በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 ንዑስ አንቀጽ1 ከላይ በገለጽናቸው የህግ ማዕቀፎች የዳኝነት ሥልጣን የተሰጠው አካል መሆኑ የራሱ የሆነ መገለጫ፣ ባህሪና ሕጋዊ ውጤት አለው፡፡የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በህግ የዳኝነት ሥልጣን የተሰጠው አካል መሆኑ፣ በዳኝነት ሥልጣኑ አይቶ የሚወስናቸው ውሳኔዎች በሕግ አግባብ በሌላ ዳኝነትሥልጣን ባለው አካል ታይተው ካልተሻሩ ወይም ካልተለወጡ በስተቀር አስገዳጅነትና ተፈጻሚነት ያላቸው ውሳኔዎች ናቸው፡፡የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በህግ በተሰጠው የዳኝነት ሥልጣኑ የሚወስናቸው ውሳኔዎች በአስተዳደሩ ክፍል ውሳኔ የሚሻሻሉ፣ የሚለወጡ ወይም የሚሻሩ አይደለም፡፡

12. የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በህግ በተሰጠው የዳኝነት ሥልጣኑ የሚወስናቸው ውሳኔዎች በፍርድ ቤት የተሰጠ ፍርድና ውሳኔ ልዩ ባህሪና ሕጋዊ ውጤት ያላቸው ናቸው፡፡ ይህም ማለት የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በህግ በተሰጠው የዳኝነት ሥልጣኑ የሚወስናቸው ውሳኔዎች የሚሻሻሉት፣ የሚለወጡትወይም የሚሻሩት በሁለት መሰረታዊ መንገድና ሥርዓትና አሰራር ነው፡፡ የመጀመሪያው የይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ውሳኔ፣በህግ በተደነገገው ሥርዓት መሰረት ታይቶ የሚጸናበት፣የሚሻሻልበት፣ በሚለወጥበትና የሚሻርበት ሥርዓት የይግባኝ ሰሚ ጉባኤውን ውሳኔ በይግባኝና በሰበር ሥርዓት አይተው ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ታይቶ እንዲወሰን የሚደረግበት አሰራር ነው፡፡ ይህ አሰራር የፍርድ ቤቶችን አደረጃጀትና የይግባኝና የሰበር ሥረ ነገር ስልጣን መሰረት በማድረግ የይግባኝ ጉባኤው ውሳኔ የሚታይበት የሕግ ሥርዓት የተዘረጋለትና፣ በልምድ በዳበረ የዳኝነት አሰራር የሚደገፍ ነው፡፡

13. ሁለተኛው የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ እንደማንኛውም በህግ የዳኝነት ሥልጣን እንደተሰጠው ፍርድ ሰጭ ተቋም፣ ራሱን ውሳኔ በድጋሜ አይቶና አጣርቶ ሊወስን በሚችልባቸው የህግ ሥርዓቶች ማለትም በፍታብሔር ሥነሥርዓት ሕግ አንቀጽ 74፣አንቀጽ 78፣አንቀጽ 358ና ተከታይ ድንጋጌዎችና በአንቀጽ 6 በተደነገጉት ሥርዓቶች ጉዳዩ እንደገና በማየት፣ የሚመለከታቸውን ባለጉዳዮች ክርክርና ማስረጃ በመስማት የራሱን ውሳኔ በህግ በተደነገገው ሥርዓት መሰረት እንደገና አይቶ በማጽናት፣ በማሻሻል፣ በመለወጥና በመሻር ውሳኔ የሚሰጥበትን አሰራርና ሥርዓት በመከተልና ተግባራዊ በማድረግ ነው፡፡

14. ይህም የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የዳኝነት ነክ ሥልጣን ነጻነት፣ ተጠያቂነት ማስከበሪያና የይግባኝ ሰሚ ጉባኤው በዳኝነት ሥልጣኑ አከራክሮ ሲወስን የፈጸማቸው የዳኝነት አካሄድ፣ የስነ ሥርዓትና የፍርድ ስህተት በራሱ እንደገና ታይቶ ከሚታረምበት መሰረታዊ የዳኝነት የስራ አካሄድና የይግባኝ ሰሚ ጉባኤው በህግ ከተሰጠው የዳኝነት ስልጣን መሰረታዊ ተቋማዊ ባህሪው የሚመነጭ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር በህግ በተደነገገው ሥርዓት መሰረትየከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ቀደም ብሎ የሰጠው ውሳኔ በድጋሜ አይቶ ውሳኔ እንዲሰጥ የሚቀርብለትን አቤቱታ በመቀበልና መርምሮ ውሳኔ መስጠት ከተፈጥሯዊ ተቋማዊ የዳኝነት ነክ ሥልጣኑ የሚመነጭ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

15. ከላይ በዝርዝር ከገለጽናቸው ሕገ መንግስቱና ሌሎች የህግ ድንጋጌዎች ይዘትና ዓላማአንጻርበከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ቀደም ብሎ በሰጠው ፍርድ ላይ በፍታብሔር ሥነሥርዓት ሕግ አንቀጽ 358ና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረት

የሚቀርብለትን የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ ተቀብሎ የማየት፤ ተከራካሪ በመሆንየሚቀርቡ ሰዎች የሚያቀርቡትን ክርክር የመስማት አጣርቶ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣኑ የሚመነጨው፣ለይግባኝ ሰሚ ጉባኤው በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37 ንዑስ አንቀጽ1፣አዋጅ ቁጥር272/1994 እና ይህንን አዋጅ ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር721/2004 መሰረት ከተሰጠው የዳኝነት ነክ ሥልጣኑ የሚመነጭ ነው፡፡

16. ይህም የይግባኝ ሰሚ ጉባኤው የዳኝነት ሥልጣኑ ዋና ባህሪና መገለጫ፣የይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ውሳኔ መስጠት ነጻነት፣ የይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ውሳኔ አስገዳጅነት፣ ተፈጻሚነት ተጠያቂነት ማስከበሪያ መንገድ ነው፡፡ የአሰራር ሥርዓቱ የይግባኝ ሰሚ ጉባኤው በዳኝነት ሥልጣኑ አከራክሮ ሲወስን የፈጸማቸው የዳኝነት አካሄድ፣ የስነ ሥርዓትና የፍርድ ስህተት በራሱ እንደገና አይቶ የሚታረምበት አሰራር ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው በፍታብሔር ሥነሥርዓት ሕግ አንቀጽ 358 ና ተከታይ ድንጋጌዎች መሰረት ተጠሪዎች ያቀረቡትን የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ የመቀበልና መርምሮ የመወሰን ሥልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ብይን፣ ከላይ የተገለጹትን ሕግ ድንጋጌዎች ይዘት፣ መሰረታዊ ዓላማ፣ ተግባራዊ ተፈጻሚነትና ህጋዊ ውጤት ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

17. በመሆኑምየአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት፣ ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የከተማው አስተዳደር የሰበር ችሎት፣ የከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተጠሪዎችን የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ አይቼ የመወሰን ሥልጣን የለኝም በማለት የሰጠውን ብይን በመሻር፣ ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ተጠሪዎች ያቀረቡትን የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ በመቀበል መርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነሥርዓት ሕግ አንቀጽ 341(1) መሰረት መመለሳቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 24033 ህዳር 10 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔና የከተማው አስተዳደር የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 24581 ታህሳስ 05 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ጸንቷል፡፡
2. አዲስ አበባ ከተማ ቦታ ማስለቀቅና የካሳ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ተጠሪዎች ያቀረቡትን የፍርድ መቃወሚያ ማመልከቻ ተቀብሎ የማየትና የመወሰን ሥልጣን አለው በማለት ወስነናል፡፡

3. በዚህ ሰበር ችሎት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት፣ ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተጀመረው የይግባኝ ክርክር የዚህ ክርክር ውጤት እስኪታወቅ ታግዶ እንድቆይ ተብሎ የተሰጠው የዕግድ ትእዛዝ ተነስቷል ፡፡
4. ዕግዱ የተነሳ ስለመሆኑ ለከተማው አስተዳደር ይግባኝ ሰሚው ችሎትና ለሚመለከተው አካል ይጻፍ፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ. 129430

ታኅሳስ 26 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጸውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- የእነማይ ወረዳ ንግድ ትራንስፖርት ጽ/ቤት - ዐ/ህግ አቶ ታምሩት ወርቁ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ጎበዜ አሰፋ - ቀረቡ

**መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ ያለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡**

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ ከገንዘብ ክፍያ ጋር በተያያዘ የቀረበ የፍትሓብሔር ክስ ሲሆን ተጠሪ በአሁን አመልካች ላይ በእነማይ ወረደ ፍርድ ቤት ያቀረበው በተሽካርካሪ ተጭነው የነበሩ ስድስት የቁም እንስሶችን አመልካች የወሰደብኝ በመሆኑ እንስሶቹን እንዲመልስልኝ ወይም ግምታቸው ብር 35000.00/ሰላሳ አምስት ሺህ ብር/ እንዲከፍለኝ በሚል ነው፡፡

የአሁን አመልካች የቁም እንስሳት ግብይት አዋጅ ቁጥር 819/2006 ን ለማስፈጸም በወጣው ደንብ 341/2007 አንቀጽ 19/4 እና 5/ መሠረት በህገወጥ መንገድ ተይዘው በተገኙ የቁም እንስሳት ላይ አግባብ ያለው አካል በሚወስደው እርምጃ ላይ ሊቀርብ የሚችለው ይግባኝ መሆኑ በግልጽ የተመለከተ ስለሆነ ለወረዳው ፍርድ ቤት የቀጥታ ክስ መቅረቡ ተገቢ አይደለም፡፡ በመሆኑም የወረዳ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ሥልጠን የለውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የወረዳ ፍርድ ቤት በተጠቀሰው አዋጅ እና ደንብ መሠረት ጉዳዩን የማየት ሥልጣን የለኝም በማለት በመ/ቁ.0119015 በቀን 29/02/2008 ዓ/ም ብይን ሰጥቷል፡፡ የአሁን ተጠሪ ብይኑን ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን

ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በመ/ቁ. 0123900 ህዳር 6 ቀን 2008 ዓ/ም ይግባኙን ሰርዟል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ አቤቱታ ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ ችሎቱም የግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ ደንብ ቁጥር 341/2007 አንቀጽ 19 /4 እና 5/ ን በመተርጎም ጉዳዩ በቀጥታ ለፍርድ ቤት ሊቀርብ ይችላል በማለት የሥር ፍርድ ቤቶችን ብይንም ሆነ ትዕዛዝ በመሻር የወረዳ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አይቶ ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 341 መሠረት መልሷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠውን ውሳኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታ ይዘትም በአጭሩ፡- በቁም እንስሳት ግብይት አዋጅ ቁጥር 819/2006 አንቀጽ 15 /5 እና 8/ መሠረት እንዲሁም አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው ደንብ ቁጥር 341/2007 አንቀጽ 17 እና 19 መሰረት ተጠሪ በህገወጥ መንገድ እያጓጓዛቸው የተገኙ ስድስት የቁም እንስሶች ላይ በሰጠው ውሳኔ ላይ ሊቀርብ የሚችለው ይግባኝ እንጂ ቀጥታ ክስ አይደለም፡፡ ስለሆነም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የወረዳ ፍርድ ቤት በመቃወሚያው ላይ የሰጠውን ብይን በመሻር የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ የሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ተሽሮ የወረዳ ፍርድ ቤት ብይን እንዲፀናልን እንጠይቃለን የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በአስተዳደር አካሉ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን የይግባኝ አቤቱታ ሳይሆን ቀጥታ ክስ ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ማቅረብ ይችላል በማለት አዋጅ ቁጥር 819/2006 እና አዋጁን ተከትሎ የወጣ ደንብ ቁጥር 341/2007 ደንጋጌዎችን በመተርጎም የደረሰበት ድምዳሜ የህጉን ዓላማ፣ መንፈስና ይዘት በአግባቡ ያገናዘበ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ ለአመልካች አቤቱታ በቀን 01/11/2008 ዓ/ም የተጻፈ መልስ ሰጥቷል፡፡ የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ እንደቀረበው ሲሆን ጉዳዩን ከሥር ፍርድ ቤቶች ብይን፣ ትዕዛዝ እና ውሳኔ እንዲሁም በዚህ ችሎት ከተደረገው ክርክርና አጣሪ ከያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡ የግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው የስልጣን ጥያቄ መሠረት ያደረገው የአዋጅ ቁጥር 819/2006 አንቀጽ 15 /5 እና 8/ እና አዋጁን ለማስፈጸም የወጣ ደንብ ቁጥር 341/2007 አንቀጽ 19 /4 እና 5/ ነው፡፡ አግባብ ያለው አካል በአዋጁ አንቀጽ 15/5/ ማንኛውም የቁም እንስሳት ግብይት ተሳታፊ የግብይት ሂደቱን የሚያዛባ አሳሳች ድርጊት ፈጽሞ ሲገኝ ተገቢውን አስተዳዳራዊ እርምጃ የመውሰድ ሥልጣን እንዳለው ሲደነግግ፣ የአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ 8 ደግሞ በህገወጥ መንገድ ሲጓጓዙ ወይም ግብይት ሲፈጸምባቸው የተገኙ የቁም እንስሳትን የመያዝ፣ የቁም እንስሳቱን እንደ አግባቡ በመጀመሪያ ወይም በሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት የግብይት

ማዕከል አቅርቦ በጨረታ በመሸጥ ገንዘቡን በዝግ የባንክ ሂሳብ እንዲቀመጥ የማድረግ፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 መሠረት እንዲወረስ ሲወሰንም ለመንግሥት ገቢ እንዲሆን የማድረግ ሥልጣን የተሠጠው እንደሆነ ይደነግጋል፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች አግባብ ያለው አካል ሊወስድባቸው የሚችልባቸውን አስተዳዳራዊ እርምጃ የሚገልጹ ናቸው፡፡ አግባብ ያለው አካል ማነው? ለሚለው ጥያቄ አዋጁ በአንቀጽ 2 (24) "አግባብ ያለው አካል"እንደአግባቡ ሚኒስቴሩ ወይም የንግድ ፈቃድ ለመስጠት ሥልጣን የተሰጠው የክልል አካል ነው በማለት ይተረጉማል፡፡ እርምጃዎቹ ሲወሰዱ ክስ ለማን እንደሚቀርብ ግን አዋጁ አይገልጸም፡፡ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የወጣው ደንብ ቁጥር 341/2007 አንቀጽ 19/4/ የአስተዳደር አካሉ እርምጃ ሲወስድ ክስ ለማን እንደሚቀርብ ይደነግጋል፡፡ ይኸውም "ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ ይችላል" የሚለው ነው፡፡ ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት የትኛው ነው? የሚለውን ደንቡ በግልጽ ባያስቀምጥም ሥልጣን በሥረ ነገር ወይም በገንዘብ መጠን ሊወሰን ይችላል፡፡ በሌላ አነጋገር ክስ አቅራቢ የሚጠይቀው የዳኝነት ዓይነት ወይም የገንዘብ መጠን የፍርድ ቤቱን ሥልጣን ይወስናል ማለት ነው፡፡ በዚህ በዳኝነቱ መጠን ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ ይቀርባል ማለት ነው፡፡ ይህም የሚያመለክተው ክስ የሚቀርበው ለይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ሳይሆን ጉዳዩን ለማየት የስረ ነገር ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ነው ፡፡ ይህም ወረዳ ፍርድ ቤት ወይም የከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊሆን ይችላል፡፡ ክስና ይግባኝ የተለያዩ ነገሮች ናቸው፡፡ በዚህ ንዑስ አንቀጽ መሠረት የህግ አውጪው ሀሳብ ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ቀጥታ ክስ ሊቀርብ እንደሚችል መደንገጉን ነው፡፡ የእንግሊዘኛው ትርጉምም ቢሆን " May institute case in a court of law having jurisdiction within 30 day after the decision is passed or after laps of period specified for decision" የሚለው ከላይ የገለጽነውን ያረጋግጣል፡፡ ይህ ቢሆንም የአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ 5 ደግሞ "ይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤት" በማለት የሚገልጽ ሲሆን ይህ በንዑስ አንጽ 4 ላይ ከተደነገገው ጋር ይቃረናል፡፡ሆኖም ግን ከእንግሊዘኛው ትርጉም ሲታይ የህግ አውጪው ሀሳብ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ እንዲቀርብ መሆኑን ነው፡፡ እነዚህን ሁለቱን ንዑስ አንቀጾች ህግ አውጪው ከሰበው ግብ አንጻር መተርጎም የፍርድ ቤት ድርሻ ነው፡፡ በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት እነዚህን ሁኔታዎችን በማጤን የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ሲጠቃለልም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 52382 በቀን 17/09/2008 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ጸንቷል፡፡

2. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
3. በቀን 23/10/2008 ዓ/ም የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው አካል ይጻፍ፡፡
4. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረስ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

የሰ/መ/ቁ.123986

ግንቦት 18 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች:- አቶ መቻልደጉ ሰሙር ጠበቃ አብዱርሃማን ሰይድ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የሚዛን አማን ከተማ ገቢዎች ባለስልጣን ቅ/ጽ/ቤት አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የአሁን አመልካች ተጠሪው ከ2000 እስከ 2005 ዓ.ም ባለዉ የግብር ዘመን በኦዲት ምርመራ ዉጤት ላይ በመመስረት የገቢ ግብር፣ አስተዳደራዊ መቀጫና ወለድን ጨምሮ ብር 2,779,095.30 ሲወስን የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ አስተዳደራዊ መቀጫና ወለድ ደግሞ ብር 1,972,184.97 በመወሰን ጥር 30 ቀን 2006 ዓ.ም በተጻፉ የግብር ማስታወቂያ ደብዳቤዎች አሳዉቋል፡፡ አመልካች በዉሳኔዉ ቅር ተሰኝቶ ባቀረበዉ ይግባኝ መነሻነት የሚዛን አማን ከተማ አስተዳደር የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ መርምሮ አመልካች ፍሬ ግብር እና ፍሬ ታክስ ሙሉ በሙሉ እንዲከፍል ሆኖ ከወለድ 25% ከፍሎ 75% እንዲነሳለት እንዲሁም አስተዳደራዊ መቀጮ ሙሉ በሙሉ እንዲነሳለት በመሻሻል ወስኗል፡፡

በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝተዉ ግራቀኙ ባቀረቡት ይግባኝ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተዉ የቤንች ማጂ ዞን የቤንች አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኃላ መርምሮ ወለድ 75% እና አስተዳደራዊ መቀጮ ሙሉ በሙሉ ይነሳ ሲል የሰጠዉ ዉሳኔ ሕግን መሠረት ያላደረገ ነዉ በማለት ሲሽር ፍሬ ግብርና ፍሬ ታክሱን በተመለከተ በአግባቡ ሳይጣራ ሙሉ በሙሉ ይክፈል መባሉ ተገቢ አይደለም በማለት ሽሮት ግብር ይግባኝ ሰሚዉ ጉባኤ እንደገና አጣርቶ እንዲወስን ጉዳዩን በመመለስ ወስኗል፡፡

በዚህ ዉሳኔ ቅር ተሰኝቶ የአሁኑ ተጠሪ ባቀረበዉ ይግባኝ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተዉ የደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ግራቀኙን ካከራከረ በኃላ መርምሮ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የፍሬ ግብር እና የፍሬ ታክስ እንደገና ተጣርቶ እንዲወሰን ለጉባኤዉ መመለሱም ሆነ ጉባኤዉ አስቀድሞ በሰጠዉ ዉሳኔ ወለድ 75% እና አስተዳደራዊ መቀጮ ሙሉ በሙሉ እንዲነሳ መወሰኑ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ በማለት በመሻር ወስኗል። ይህን ዉሳኔ በመቃወም የአሁን አመልካች ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን ግራቀኙን ካከራከረ በኃላ የተጨማሪ እሴት ታክስ ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 285/94 መሰረት የፌዴራል ጉዳይ በመሆኑ ጉዳዩን ለማየት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን የለዉም በማለት መዝገቡን በትዕዛዝ ዘግቶታል። አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠዉን ትዕዛዝ እና በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠዉን ዉሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነዉ።

አመልካች ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- ጉዳዩ የተጨማሪ እሴት ታክስ ክርክር ያለበት ስለሆነ የተጨማሪ እሴት ታክስ ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 285/94 መሰረት የፌዴራል ጉዳይ ነዉ በማለት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የደረሰበት ድምዳሜ ሕግን መሠረት ያደረገ አይደለም። ከአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 3 እና 2(3) ድንጋጌ አንጻር ጉዳዩ በፌዴራል ፍ/ቤቶች የወል ዳኝነት ስልጣን ሥር ይወድቃል ተብሎ ሊተረጎም አይገባም። አዋጁ በመላ አገሪቱ ተፈጻሚነት ያለዉ አዋጅ በመሆኑ፣ አዋጁን መሰረት አድርገዉ ክልሎች የተጨማሪ እሴት ታክስ ሕግን የሚያስከብሩና ታክሱን የሚሰበስቡ በመሆኑ በአዋጁ ላይ ለሚነሳ ክርክር በክልል ፍ/ቤቶች የመጨረሻ ዉሳኔ ሰጪ አካል የሆነዉ የሰበር ችሎት ስልጣን የለዉም መባሉ የአዋጁን አላማ ያልተከተለ ነዉ። በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 43(4) መሰረት የይግባኝ አቀራረብ እና የግብር ይግባኝ ጉባኤ ስልጣንና ተግባር በተመለከተ የገቢ ግብር አዋጅ ተፈጻሚ እንደሚሆን የተደነገገ በመሆኑና አግባብነት ያለዉ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 56/95 የክልል አዋጅ በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን አለዉ። በመሆኑም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን እንዳያይ የሚከለክል ግልጽ ድንጋጌ በሌለበት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት መዝጋቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ጉዳዩን አይቶ እንዲወስን ሊመለስለት ይገባል።

የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ስለ አዳሪ ቡና መረጃ ከዞኑ ግብይት መምሪያ አስቀርቦ ከመረመረ በኃላ ጉባኤዉ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 56/95 አንቀጽ 116(1/ሐ) ላይ የተመለከተዉን ማስረጃን አስቀርቦ የማጣራት ሥራዉን አለመስራቱን አረጋግጦ ዉሳኔዉን በመሻር እንደገና በማስረጃ አጣርቶ ዉሳኔ እንዲሰጥ መልሷል። ይህን ማድረጉ በሕግ ጉዳይ ላይ የተሰጠ ዉሳኔ አይደለም የሚያስብል ባለመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የከፍተኛ ፍ/ቤትን ዉሳኔ መሻሩ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ። እንዲሁም የከፍተኛዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ ከሻረ በኃላ ጉዳዩን ወደ ጉባኤዉ መመለስ ሲገባዉ በዝምታ በማለፉና በተዘዋዋሪ መንገድ የተጠሪን ዉሳኔ ማጽናቱ

የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ አመልካች ያቀረብኩት የሂሳብ መዝገብ ዉድቅ መደረጉም ስህተት ነዉ፡፡ ባቀረብኩት ሒሳብ መዝገብ ብቻ ግብር እና ተጨማሪ እሴት ታክስ ልከፍል ይገባል የሚል ክርክር ባላቀረብኩበት አግባብነት የሌላቸዉ ምክንያቶች አንስቶ በመተቸት እና አከራካሪዉን ጭብጥ ባለመረዳት የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ መሻሩ መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ዉሳኔ ተሽሮ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ዉሳኔ ይጽናልኝ የሚል ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ መሆኑን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ገልጾታል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የክልሉ የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን በይግባኝ የማየት ስልጣን አለዉ ወይ? የሚለዉንና ይህን ተከትሎ የሰጠዉን ዉሳኔ አግባብነት ለማጣራት ሲባል ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ተጠሪ መጥሪያ ደርሶት መጥሪያዉ ለክልሉ ገቢዎች ባለስልጣን ተብሎ እንዲቀየር አቤቱታ ቢያቀርብም ተቀባይነት በማጣቱ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተመከተዉን የሚመስል ሲሆን አቤቱታዉ ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ እና አግባብነት ካላቸዉ ድንጋጌዎች ጋር በመገናዘብ መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነዉ ተጠሪ ከ2002 እስከ 2005 ዓ.ም ያለዉ የንግድ እንቅስቃሴ ኦዲት ከተደረገ በኃላ የገቢ ግብር፣ አስተዳደራዊ መቀጮና ወለድ እንዲሁም የተጨማሪ እሴት ታክስ አስተዳደራዊ መቀጮና ወለድ ጨምሮ የወሰነበት ሲሆን አመልካች ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ይግባኝ አቅርቦ ፍሬ ግብሩን፣ ፍሬ ታክስ እና 25% ወለድ እንዲከፍል ሲወስን 75% ወለድ እና አስተዳደራዊ መቀጮ እንዲነሳለት ወስኗል፡፡ በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ዉሳኔ ባለመስማማት ግራቀኙ ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን በከፊል ወለድ እና አስተዳደራዊ መቀጮ ሙሉ በሙሉ እንዲነሳ መወሰኑ ስህተት መሆኑን ቢገልጽም ፍሬ ግብሩና ታክሱ በአግባቡ ሳይጣራ የተወሰነ ነዉ በማለት ዉሳኔዉን ሽሮት  እንደገና ተጣርቶ እንዲወሰን ወደ ጉባኤዉ መልሶታል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በበኩሉ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የፍሬ ነገር ክርክሩ በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ እንደገና እንዲጣራ የሰጠዉ ዉሳኔ የሕግ ስህተትን ከማረም ስልጣን ዉጪ ነዉ ሲል ሽሮት የተጠሪን ዉሳኔ በተዘዋዋሪ መንገድ አጽንቶታል፡፡

አመልካች ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ጉዳዩን የተመለከተዉ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በበኩሉ ግራቀኙን ካከራከረ በኃላ የተጨማሪ እሴት ታክስ ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 285/94 መሰረት የፌዴራል ጉዳይ በመሆኑ በክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳይ በመሆኑ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ የፌዴራል በመሆኑ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም ማለቱ በአግባቡ ነዉ? ወይስ አይደለም የሚለዉን ጭብጥ ለመመለስ አግባብነት ያላቸዉን የሕግ ድንጋጌዎች እንመልከት፡፡

በመሠረቱ የተጨማሪ እሴት ታክስ የፌዴራል መንግስት የታክስ ስልጣን ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 28(2) እና አንቀጽ 30 መሠረት ታክሱን የመሰብሰብና የማስተዳደር ስልጣን

ለፌዴራል ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የተሰጠ መሆኑ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ የክልል የገቢዎች ባለስልጣን ቢሮዎች ተጨማሪ እሴት ታክስ የሚሰበስቡት ታክሱን የማስተዳደር የራሳቸዉ ስልጣን ኖሯቸዉ ሳይሆን ታክሱን ለማስተዳደር ካለዉ አመቺነት የተነሳ ስልጣን ባለዉ አካል በተሰጣቸዉ ዉክልና ነዉ፡፡ የክልሉ ገቢዎች ባለስልጣን የተጨማሪ እሴት ታክስን በዉክልና ማስተዳደሩ ብቻ ጉዳዩን የክልል ጉዳይ ሊያደርገዉ አይችልም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአዋጁ አንቀጽ 43(3) በግልጽ እንደሚደነግገዉ በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ዉሳኔ ላይ የሚቀርበዉ ይግባኝ የሚስተናገደዉ በገቢ ግብር አዋጁ መሰረት መሆኑ ተመልክቷል፡፡ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 112 ደግሞ በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ዉሳኔ ላይ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚል ወገን ስልጣን ላለዉ ፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረብ እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም የተጨማሪ እሴት ታክስ የፌዴራል ታክስ በመሆኑና የክልል የገቢዎች ቢሮዎች ታክሱን የሚያስተዳድሩት በዉክልና ስልጣናቸዉ በመሆኑ ምንም እንኳ ታክሱ የተወሰነዉ በክልሉ የገቢዎች ቢሮ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እና የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ቢሆንም የሕግ ስህተት አለበት የሚል ወገን ይግባኝ ማቅረብ የሚገባዉ ስልጣን ላለዉ የፌዴራል ፍ/ቤት ወይም የዉክልና ስልጣን ላለዉ የክልል ፍ/ቤት መሆን ይኖርበታል፡፡ ከዚህ አንጻር ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ በመሆኑ የደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም ማለቱ የሚነቀፍ አይሆንም፡፡

በሌላ በኩል ምንም እንኳ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም ማለቱ ተገቢ ቢሆንም ቀጥሎ የሚነሳዉ ጥያቄ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን ተመልክተዉ ዉሳኔ የሰጡበት ስልጣን ኖሯቸዉ ነዉ? ወይስ አይደለም የሚለዉ ነዉ፡፡ ጉዳዩ ከላይ እንደተገለጸዉ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቅ ከሆነ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 11፣ በአዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 43(4) እና በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 112 መሠረት ግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚል ወገን ይግባኝ ሊያቀርብ የሚችለዉ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነዉ፡፡ በተያዘዉ ጉዳይ የስር ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ዓይተዉ የወሰኑት የፌዴራል ጉዳይ መሆኑን ተገንዝበዉ ባላቸዉ የዉክልና ስልጣን ተጠቅመዉ ሳይሆን የክልል ጉዳይ ነዉ በሚል ነዉ፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ሆነ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጉዳዩን የማየት የስረ-ነገር ስልጣን ሳይኖራቸዉ ጉዳዩን ተመልክተዉ መወሰናቸዉን ነዉ፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍ/ቤቶች የስረ-ነገር ስልጣን ሳይኖራቸዉ ስልጣን አለን በሚል በተሳሳተ ግንዛቤ የሰጡትን ዉሳኔ የማረም ኃላፊነት እያለበት ዉሳኔውን ሳይሽር በዝምታ ማለፉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡

ሲጠቃለል የተጨማሪ እሴት ታክስ ጉዳይ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ስልጣን ስር የሚወድቅ ጉዳይ በመሆኑ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የስረ-ነገር ክርክሩን ተመልክቶ የመወሰን ስልጣን የለኝም ማለቱ ተገቢ ቢሆንም የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት

ጉዳዩ የፌዴራል መሆኑን ሳይገነዘቡና ስልጣን ሳይኖራቸዉ የሰጡትን ዉሳኔ መሻር ሲገባዉ በዝምታ ማለፉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት በመሆኑ ሊታረም የሚገባዉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የቤንች ማጂ ዞን የቤንች አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 14511 ሐምሌ 15 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔም ሆነ የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 03164 መስከረም 21 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ የስረ-ነገር ስልጣን ሳይኖራቸዉ የሰጧቸዉ ዉሳኔዎች በመሆናቸዉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 03334 ጥር 26 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ ተሻሽሏል፡፡
3. የተጨማሪ እሴት ታክስ ጉዳይ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የስረ-ነገር ስልጣን ስር የሚወድቅ ጉዳይ በመሆኑ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የፌዴራል ፍ/ቤቶች ስልጣን ነዉ ተብሏል፡፡
4. የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የስረ-ነገር ስልጣን ሳይኖራቸዉ የሰጧቸዉ ዉሳኔዎች የተሻሩ በመሆናቸዉ ይህ ዉሳኔ ግራቀኙን በግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ዉሳኔ ላይ ስልጣን ላለዉ ፍርድ ቤት ይግባኝ ከማቅረብ አይከለክልም ተብሎ ተወስኗል፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ፍ

የሰ/መ/ቁ. 123200

ሰኔ 27 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዳኜ መላኩ

ብርሃኑ አመነው

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካቾች፡- 1ኛ. ማጂኮን ኮንስትራክሽን ሊትድ

2ኛ ኢ/ር ሙሉጌታ አሰፋ ኃ/ማርያም

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. አቶ ታትገኝ ፊጣሞ ወሌቦ

2ኛ. አቶ ሃሮን ሰሌ ኡስማን

3ኛ. አቶ እስማኤል ሙሐመድ ሱሌማን

4ኛ አቶ አደም መሃመድ አደም

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ተሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው አቤቱታ ብሔራዊ የዳኝነት ስልጣን አስመልክቶ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡትን ብይን በመቃወም ለማሳረም ነው፡፡

ተጠሪዎች ከሳሾች አመልካቾች ደግሞ ተከሳሾች በመሆን በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክር አድርገዋል፡፡ ክሱ መሰረት ያደረገው በአመልካቾች እና በተጠሪዎች መካከል በደቡብ ሱዳን የተደረገ ውል ላይ ሲሆን ተጠሪዎች በውለታቸው መሰረት ግዴታቸውን የተወጡ መሆኑን ገልጸው አመልካቾች በውል መሰረት የሚፈልግባቸውን ክፍያ እንዲፈጽሙ እንዲወሰን ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካቾች በበኩላቸው ለክሱ በሰጡት መልስ 1ኛ አመልካች ጋር ውል ማደረጋቸውን አምነው ነገር ግን 1ኛ አመልካች የተቋቋመው በሱዳን ሃገር ሕግ መሆኑን፣

ከኢትዮጵያ ሕግ ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለው፣ ለክሱ መነሻ የሆነው ውል የተደረገው በሱዳን ሃገር ስለመሆኑና የውል ጉዳይ የተፈጸመው እዚያው በመሆኑ የኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ጉዳዮን በማከራከርና ለመወሰን ብሔራዊ የዳኝነት ስልጣን እንደሌላቸው በመጀመሪያ መቃወሚያነት አቅርቧል፡፡ 2ኛ አመልካችም የ 1ኛ አመልካች ስራ አስኪያጅ ከመሆኑ ውጪ በግል ክስ ሊቀርብበት እንደማይገባም አያይዘው ተቃውሞ አቅርበዋል፡፡

ክርክሩን በመጀመሪያ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ለክሱ መነሻ የሆነው ውል በሱዳን ሃገር የተደረገና የሚፈጸም ከመሆኑ የተነሳ ከኢትዮጵያ ጋር ግኑኝነት ያለው መሆኑን ከሳሾች /ተጠሪዎች/ አላስረዱም በማለት የኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ጉዳዩ ላይ አከራክሮ ለመወሰን የሚያስችላቸው ብሔራዊ የዳኝነት ስልጣን የላቸውም የሚለውን የአመልካቾች መቃወሚያ ተቀብሎ የክስ ምገቡን በብይን ዘግቷል፡፡

ተጠሪዎች /ስር ከሳሾች/ በዚህ ብይን ቅር ተሰኝተው ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቅሬታ በማቅረባቸው ፍ/ቤቱ ግራቀኙን ካከራከረ በኂላ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 7 መሰረት የውጭ ሃገር ዜጋ ተከራካሪ በሆነበት ጉዳይ የፌዴራል ፍ/ቤቶች የዳኝነት ስልጣን እንዳላቸው በመግለጽ በአዋጁ አንቀጽ 11/2/ሀ መሰረት ጉዳዩ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የዳኝነት ስልጣን ሊታይ ይገባል በማለት መዝገቡን መልሰንለታል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ሲሆን የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች በውጪ ሃገር የተቋቋመ እና በኢትዮጵያ ውስጥ ቅርንጫፍ የሌለው በሆነበት ሁኔታ ክርክሩ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ሊዳኝ ይገባል የመባሉን አግባብነት ለመመርመር እንዲቻል ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ታዟል፡፡

የተጠሪዎች ጠበቃ የፍርድ ቤቱን መጥሪያ ተቀብለው ነገር ግን መልስ ባለማቅረባቸው በዚሁ ታልፎ መዝገቡ ተመርምሯል፡፡

እንደመረመርነውም በዚህ ጉዳይ እልባት ማግኘት ያለበት ነጥብ የቀረበውን ክስ አከራክሮ ለመወሰን የኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ስልጣን አላቸውን? የሚለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በመሰረቱ የፍርድ ቤቶች ስልጣን በሶስት መሰረታዊ ጉዳዮች ተከፍሎ የሚታይ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይኸውም ብሔራዊ የዳኝነት ስልጣን /judicial jurisdiction/ ፣ የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን /material jurisdiction/ እና የግዛት ክልል ስልጣን /local jurisdiction/ ናቸው፡፡ የስረ ነገር እና የግዛት ክልል የዳኝነት ስልጣን የሚወሰነው በሐገራዊ /ብሔራዊ/ ሕጎች /domestic or national lows/ ሲሆን በዋናት በስነ ስርዓት ሕጎች አልፎ አልፎም በመሰረታዊ ሕጎች ተደንግጎ እናገኛለን፡፡

ብሔራዊ የዳኝነት ስልጣን ምንጭ በዋናነት ዓለም ዓቀፍ የግለሰብ ሕግ /private internal low/ ሲሆን ከዚህ አልፎም በሃገራት መካከል የሚደረጉ የሁለትዮሽ ወይም የሶስትዮሽ ውሎች አልያም ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያገኙ ሕጎች ወይም ልማዶች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በዚህ ዘርፍ ኢትዮጵያ ራሱን የቻለ ዓለም አቀፍ የግለሰብ ሕግ ባይኖራትም በተለያዩ ሃገሮች የዳበረ ልምድና ተቀባይነት ያገኙ መርሆዎችን መሰረት በማድረግ ለጉዳዮች እልባት ሲሰጥ እንዳለ ይታወቃል፡፡

እስከ አሁን የዳበረ ልምድና በዘርፉ ከተደረጉ ጥናቶችና ጽሑፎች መገንዘብ እንደሚቻለው አንድ ሃገር ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ብሔራዊ የዳኝነት ስልጣን አለው ወይ የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ መሰረት ተደርጎ የሚወሰደው ከተከሳሹ ጋር ያለው ግንኙነት መለኪያዎችን በመጠቀም ነው፡፡ እነዚህም ከተከሳሽ ሰው /action impersonal/ የሕግ ይሁን የተፈጥሮ ሰው በዜግነት ወይም በመደበኛ መኖሪያው ከፍርድ ቤቱ ጋር ያለው ቁርኝት፣ ለክሱ ምክንያት የሆነው ድርጊት /Act/ ውል ይሁን ከውል ውጪ የተፈጸመበት ሐገር ቁርኝት፣ ለክሱ ምክንያት የሆነው ንብረት /property/ ተንቀሳቃሽ ይሁን የማይንቀሳቀስ የሚገኝበት አሊያም የተከሳሹ ፈቃደኝነት /consent/ መኖር አለመኖር መለያዎች ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ከዚህ ባለፈ ደግሞ በጉዳዩ ላይ የሚነሳ ብሔራዊ ጥቅም ወይም በጉዳዩ ላይ የሚነሳ ብሔራዊ ጥቅም ወይም ፖሊሲ /national interest or public policy/ ጉዳይ መኖሩ ሲረጋገጥ ክሱ ከቀረበበት ሃገር ፍ/ቤት ብሔራዊ የዳኝነት ስልጣን አለው ሊባል ይችላል፡፡

ከዚህ አንጻር ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪዎች ክስ ያቀረቡት በሱዳን ሃገር የተደረገና የተፈጸመው ውልን መሰረት በማደረግ የገንዘብ ክፍያ ውሳኔ እንዲሰጥ ዳኝነት ስለመጠየቃቸው ከመዝገቡ መረዳት ተችሏል፡፡ በዚህ የውል አፈጻጸም ላይ ከኢትዮጵያ ፍ/ቤች ጋር የሚያስተሳስር ምክንያት ስለመኖሩ ተጠሪዎች አላስረዱም፡፡ ከላይ በዝርዝር ከተመለከትናቸው ምክንያቶች አንድም ምክንያት ከኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ጋር የሚያስተሳስር ምክንያት መኖሩ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ብሔራዊ የዳኝነት ስልጣን አላቸው የሚባልበት ሁኔታ አይኖርም፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ብሔራዊ የዳኝነት ስልጣን ክርክር ላይ እልባት ሳይሰጥ የስረ ነገር ስልጣን ላይ ተመርኩዞ አዋጅ ቁጥር 25/88 መሰረት አድርጎ መወሰኑ በስር ፍ/ቤት ያከራከረውን ጭብጥ በአግባቡ ባለማገናዘብ የተወሰደ አቋም እንደሆነ ተገንዝበናል ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትን ብይን በመሻር የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚሁ አግባብ ውሳኔው ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁጥር 104120 በ 08/03/08 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 130398 በ 01/11/06 ዓ.ም የሰጠው ብይን ጸንቷል፡፡ ይጻፍ፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

የሰ/መ/ቁ.119435

ሰኔ 27 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች- ዓሊ መሀመድ

ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ

ቀነአ ቂጣታ

ፀሃይ መንክር

አመልካች - አቶ አብዱልቀኒ አብዱራህማን - ጠበቆች ግርማ አለሙና አሰፋ አሊ ቀረቡ

ተጠሪዎች - 1ኛ. አቶ ዳንኤል ወ/ሃዋሪያት - ጠበቃ ግርማ ከበደ ቀረቡ

2ኛ. የን/ስ/ላ/ክ/ከተማ የይዞታ አስተዳደር ሽግግር ጊ/አገ/ፕ/ጽ/ቤት - የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በተጠሪዎች መካከል የተደረገ የሊዝ ውል እንዲፈርስ የቀረበን የዳኝነት ጥያቄ የተመለከተ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካች በተጠሪዎች ላይ በአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

የክሱ ይዘት፡- መንግስት በውጭ ሃገር ለሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን በፈጠረው ዕድል የመኖሪያ ቤት ህብረት ሥራ ማህበር ተቋቁሞ በአ/አበባ ከተማ ን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ክልል ለማህበሩ አባላት ቤት መስሪያ ቦታ ተሰጥቷል፤ በዳሽን የመኖሪያ ቤት ህብረት ስራ ማህበር አባል የነበሩት 1ኛ ተጠሪ ከማህበሩ ተሰናብተው በምትካቸው አመልካች በአባልነት ተተክቻለሁ፤ የአሜሪካን ዶላር 5,000.00 (አምስት ሺህ) አሜሪካን ሃገር ለሚገኘው ኤምባሲ ክፍያ ፈፅሜያለሁ፤ አመልካች በማህበሩ ስለመተካቴም ማህበሩ ጥቅምት 3 ቀን 1996 ዓ.ም ለአ/አበባ መስተዳድር የሥራና ከተማ ልማት ቢሮ የሊዝ አፈፃፀም መምሪያ በጻፈው ደብዳቤ አሳውቋል፤ የማህበሩ ሥራ አስፈጻሚ አመልካች በአባልነት ስለመተካቴ በዩ ኤስ አሜሪካ ለኢትዮጵያ ኤምባሲ በማሳወቁና ልዩ ልዩ ቃለጉባኤዎችን በማስተላለፉ ኤምባሲው ጥቅምት 25/1996 ዓ.ም ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በውጭ ለሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ጉዳዮች ዳይሬክተር በፃፈው ደብዳቤ ገልጿል፤ ሆኖም 1ኛ ተጠሪ በማህበሩ ያሉ በማስመሰል ከራሳቸው አንዳችም ገንዘብ ሳይከፍሉ ከሳሽ በከፈሉት የቅድሚያ ክፍያ በመጠቀም ከክፍለከተማው የመሬት ልማትና አስተዳደር መምሪያ ጋር የሊዝ ውል በመዋዋል የመኖሪያ ቤት መሥሪያ ቦታ የይዞታ ማረጋገጫ ሰርተፍኬት (ካርታ) አሳግባብ ወስደዋል፤ ስለሆነም 1ኛ ተከሳሽ ከማህበሩ ያልተሰረዙ እና ቅድሚያ ክፍያ የከፈሉ በማስመሰልና በማሳሳት በአዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ 10(10)፣ 13(2) እና (3)፣ 14 (2)(ሐ)፣ 15(1) ድንጋጌዎች

መሰረት መብት ሳይኖራቸው ከ2ኛ ተከሳሽ ጋር ታህሳስ 19 ቀን 1999 ዓ.ም ያደረጉት የመኖሪያ ቤት ሥራ ቦታ ሊዝ ውል እንዲፈርስ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ 1ኛ ተጠሪ ለክሱ በሰጡት መልስ ከሳሽ የማህበሩ አባልም ተተኪም አይደሉም፤ ተከሳሽ የማህበሩ መስራች ስለሆንኩ ማህበሩ ለሊዝ አፈጻፀም መምሪያ በላከው ዝርዝር ውስጥ ስሜ በተ.ቁ 11 ተመዝግቦ ይገኛል፤ በአዋጁ መሰረት 2ኛ ተከሳሽ መሬቱን ከካርታው አስረክቦኝ የሊዝ ውል ተፈራርመን ሥራ ጀምሬያለሁ፤ ብር 123,238.33 የሊዝ ክፍያም ከፍያለሁ፤ 1ኛ ተከሳሽ በራሱ ፈቃድና የጽሁፍ አቤቱታ ከማህበሩ የለቀቀበት ነው ተብሎ የቀረበው ማስረጃ ጽሁፍም ሆነ ፊርማው የኔ አይደለም፤ እኔ ስለመሰረዜ እና ከሳሽ ተተኪ ስለመሆኑ የተያዘው ቃለ ጉባኤ በተደረገበት ስብሰባ ላይ ስላልተጠራሁ አልተገኘሁም፤ በጽሁፍ ፊርሜ አባልነቴን ለቅቄያለሁ አላልኩም ስለሆነም ክሱ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ታዞ ስላላቀረበ በፅሁፍ መልስ የማቅረብ መብቱ ታልፏል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የከተማ አስተዳደሩ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ክርክርና ማስረጃውን መርምሮ እንዲሁም የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ እና ሌሎች ሰነዶችን ከማህበሩ አስቀርቦ ከመረመረ በኋላ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በ1ኛ ተከሳሽ ምትክ አመልካች አባል እንዲሆኑ የወሰነ መሆኑ ታውቆ አስፈላጊው ፎርማሊቲ እንዲፈፀም ለሊዝ አፈጻፀም መምሪያ ከጻፈው ደብዳቤ ባለፈ በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው የተሰጠ ውሳኔ እና ለጠቅላላ ጉባኤው ቀርቦ የፀደቀ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ የለም፤ 1ኛ ተከሳሽ በማህበሩ አልቀጥልም ሲሉ ገልጸዋል ተብሎ በተያዘው ቃለ ጉባኤ ላይ ያለው ፊርማ ስለተካደ በፎረንሲክ ተመርምሮ ፊርማው የ1ኛ ተከሳሽ አለመሆኑ ተረጋግጧል፤ ስለሆነም በተከሳሾች መካከል የተፈፀመው የሊዝ ውል እንዲፈርስ ሲሉ ከሳሽ ያቀረቡት አቤቱታ ወድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ቅሬታቸውን ለከተማው ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች መስከረም 26 ቀን 2008 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የሥር ፍርድ ቤቶች ባሳለፉት ውሳኔ ተፈጸመ የሚሉትን የህግ ስህተት በመዘርዘር ቅሬታቸውን ያቀረቡ ሲሆን ማመልከቻው ተመርምሮ አመልካች የሊዝ ውሉ እንዲሰረዝ ያቀረቡት ጥያቄ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ከማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንጻር ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል፡፡

ከፍሲል ባጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን ለሰበር ችሎቱ በተያዘው ጭብጥ መሰረት ፍሬ ጉዳዩ ከመታየቱ በፊት አመልካች ያቀረቡትን የዳኝነት ጥያቄ የከተማው ፍርድ ቤቶች አከራክረው ለመወሰን የሥረ ነገር ሥልጣን ያላቸው መሆን አለመሆኑን በጭብጥነት በመያዝ መመርመሩ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ተሻሽሎ የወጣው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41 የከተማው ፍርድ ቤቶች ስለሚኖራቸው የዳኝነት ሥልጣን የሚደነግግ ሲሆን በተጠቀሰው አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) እና (መ) ሥር የከተማውን መሪ ፕላን አፈጻፀም የሚመለከቱ የይዞታ ባለመብትነት፤ የፈቃድ አሰጣጥ ወይም የቦታ አጠቃቀምን በተመለከተ የሚነሱ ጉዳዮች፤ እንዲሁም የከተማው አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት (ተቋማት) የሚገቧቸውን አስተዳደራዊ ውሎች በተመለከተ የሚነሱ ጉዳዮችን በተመለከተ የፍትሃብሄር የዳኝነት ስልጣን እንዳላቸው ተመልክቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ያቀረቡት ክስ 1ኛ ተጠሪ ከማህበሩ ያልተሰረዙ እና ቅድሚያ ክፍያ የከፈሉ በማስመሰልና በማሳሳት በአዋጅ ቁጥር 147/1991 መሰረት መብት ሳይኖራቸው ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ያደረጉት የመኖሪያ ቤት ሥራ ቦታ ሊዝ ውል እንዲፈርስ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ ይህ ክስ ተጠሪዎች ያደረጉትን ውል መሰረት ያደረገ ቢሆንም ክሱ የከተማውን መሪ ፕላን አፈጻፀም የሚመለከት የይዞታ ባለመብትነት፤ ከፈቃድ አሰጣጥ ወይም የቦታ አጠቃቀም ጋር ያልተያያዘ ሲሆን አስተዳደራዊ ውል ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ በከተማው ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር የዳኝነት ስልጣን ሥር የሚወድቅ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የሊዝ ውል እንዲሰረዝ የሚቀርብ የዳኝነት ጥያቄን በተመለከተ በመደበኛ ፍርድ ቤት ሊታይ የማይገባው መሆኑን የሚደነግግ በግልጽ የተመለከተ ህግም የለም፡፡ ይኸው ሰበር ሰሚ ችሎት ከዚህ በፊት በሰ/መ/ቁ 77175 ፣ 57435 እና ሌሎችም መዛግብት የሰጠው ውሳኔም ይህን የሚያሳይ ነው፡፡

ስለሆነም የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች የማህበራት አዋጅ ከሚሰጠው መብት ጋር በማያያዝ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር የተደረገው የሊዝ ውል እንዲፈርስ ያቀረቡትን ክስ ተቀብሎ በማከራከር ውሳኔ የሰጠው ጉዳዩን ተቀብሎ ለመዳኘት በህግ ባልተሰጠው የዳኝነት ስልጣን በመሆኑ፤ ጉዳዩን በይግባኝ እና በሰበር የተመለከቱ ፍርድ ቤቶችም ይህን ሳያርሙ ማለፋቸው የህግ ስህተት በመሆኑ ውሳኔው ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡ ተከታዩንም ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 05435 ጥር 25 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይግባኝ ሰሚው ችሎት በመ/ቁ 2335 መጋቢት 11/2007 ዓ.ም ያሳለፈው ትዕዛዝ፤ እንዲሁም የከተማው ሰበር ችሎት በመ/ቁ 23655 ነሃሴ 8/2007 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

# ጉምሩክ

ሰ/መ/ቁ. 111960

ሕዳር 06 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናየት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የአዳማ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ዓ/ህግ - አልቀረበም

ተጠሪ፡ ሰይፈ አበበ ንጉሴ - በሌለበት ታይቶ የተወሰነ በመሆኑ አልቀረበም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የአሁኑ አመልካች ለአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ክስ ተከሳሽ (ተጠሪ) አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 በመተላለፍ የኮንትሮባንድ እቃ የጉምሩክ ስርዓት ያልተፈጸመበት መሆኑን እያወቀ ወይም ማወቅ እያለበት 21 ጀሪካን ዘይት ቀረጥና ታክስ መጠኑ በአጠቃላይ ብር 6025.45 (ስድስት ሺህ ሃያ አምስት ብር ከአርባ አምስት ሳንቲም) የሆነ በመኖሪያ ቤት ውስጥ ሽንት ቤት ክፍል ውስጥ ተከማችቶ እጅ ከፍንጅ ስለተያዘ የኮንትሮባንድ እቃ ይዞ በመገኘት ወንጀል ፈጽሞ ተከሷል የሚል ነው፡፡

ተከሳሽ በሰጠው የእምነት ክህደት ቃል ፍቃድ እያለኝ ከእኔ ላይ የተያዘው ስለሆነ ህጋዊ ነኝጥፋት የለብኝም በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ከሳሽ የአሁኑ አመልካች የሆነው ዐቃቤ ህግ ሁለት ምስክሮችን ያሰማ ሲሆን ተከሳሽም ሁለት መከላከያ ምስክሮችን አቅርቦ አስመስክሯል፡፡ የጽሁፍ መከላከያ ማስረጃ በቀን 30/01/2004 ዓ/ም የተሰጠ እስከ 2007 ዓ/ም የታደሰ የምግብ ዘይት የንግድ ፈቃድ ተከሳሽ አቅርቧል፡፡

ጉዳዩን የተመለከተው የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተከሳሽን (የአሁኑ ተጠሪን) ተከላክሏል በማለት በወንጀል ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 149(2) መሰረት በነጻ እንዲሰናበት የአሁኑ አመልካች

በውሳኔው ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ በወንጀል ስነ ስርዓት ህግ ቁጥር 195(1) መሰረት በመ/ቁ.200935 በቀን 01/07/2007 ዓ/ም ዘግቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሳኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ የአቤቱታው ይዘት በአጭሩ፡-

1. የስር ፍርድ ቤቶች በጅምላ ተጠሪው የታደሰ የንግድ ፍቃድ መኖሩን በማረጋገጡ ብቻ የኮንትሮባንድ ወንጀል ሃላፊነት ያድናል ማለት መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት ነው፣
2. የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 መሰረት ማንኛውም ስሪት ሃገሩ የውጪ የሆነ እቃ ቀረጥና ታክስሳ ይከፈልበት በነጻ ዝውውር እንደማይለቀቅ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ተጠሪው ከኮንትሮባንድ ወንጀል ሃላፊነት ነጻ ለመሆን ለእቃው የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ መከፈሉን የሚያስረዳ የእቃው ጉምሩክ ዲክላራሲዮን (ሰነድ) የማቅረብ ህጋዊ ግዴታ እያለበት የስር ፍርድ ቤቶች ተጠሪው ታክስ ከፍሎ ንግድ ፍቃድ አወጥቷል በማለት በነጻ ማሰናበታቸው የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲታረምልን እንጠይቃለን የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ ትዕዛዝ ተሰጥቶ አመልካች ተጠሪን ፈልጎ ያለማግኘቱን ገልጾ ጥሪ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡ በዚሁ መሰረት ሀምሌ 6 ቀን 2007 ዓ/ም በታተመ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎ ተጠሪ ስላልቀረበ በሌለበት ታይቶ እንዲወሰን ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡

የክርክሩ ሂደት አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ እንደተገለጸው ሲሆን ጉዳዩን ከስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ፤ አመልካች ካቀረበው አቤቱታ እንዲሁም አጣሪው ከያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነውም በተጠሪ መኖሪያ ቤት ውስጥ በሚገኘው ሸንት ቤት ውስጥ በክሱ የተጠቀሰው 21 ጀሪካን ዘይት ተይዟል፡፡ በክሱ ውስጥ የተጠቀሰ መጋዘን እየታደሰ ዘይቱ አዲስ ሸንት ቤት ውስጥ ከሌሎች የሱቅ እቃዎች ጋር መገኘቱን የከሳሽም ሆነ የተከሳሽ ምስክሮች በተመሳሳይ ሁኔታ መስክረዋል፡፡ ተከሳሽ (ተጠሪ) በ2004 ዓ/ም የተሰጠ የዘይት ንግድ ፍቃድ እስከ 2007 ዓ.ም ድረስ የታደሰውን ማቅረቡ በፍሬ ነገር ረገድ ተረጋግጧል፡፡ የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ተከላክሏል በማለት በነጻ አሰናብቷል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 መሰረት ተጠሪው ከተከሰሰበት ወንጀል ሃላፊነት ነጻ ለመሆን ለእቃው የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ መከፈሉን የሚያስረዳ የዕቃው ጉምሩክ ዲክላራሲዮን (ሰነድ) የማቅረብ ህጋዊ ግዴታ እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ በስር ፍርድ ቤት ለተጠሪው የዘይት ንግድ ፈቃድ አለው ከመባሉ በስተቀር ዘይቱን ከማንና ከየት እንደገዛ እንዲሁም ለገዛበት ዘይት የጉምሩክ ቀረጥና

ታክስ መከፈሉን የሚያስረዳ የእቃው ጉምሩክ ዲክለራሲዮን (ሰነድ) ተጠሪ አቅርቦ አላረጋገጠም፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ ተጠሪ ተከላክሏል ለማለት የሚያስችል ሆኖ አልተገኘም፡፡ ሆኖም ግን አከራካሪ ሆኖ የታየው ተጠሪ በተከሰሰበት አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 "ህገ ወጥ እቃዎች ይዞ ስለመገኘት" ተብሎ የተደነገገው ድንጋጌ ይህን አዋጅ በተካው በአዋጅ ቁጥር 859/2006 ላይ ወንጀል ሆኖ ተደንግጓል ወይስ አልተደነገገም? የሚለው ነው፡፡ የአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 ድንጋጌ በአዋጅ ቁጥር 859/2006 ላይ አልተደነገገም፡፡ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 168 የተደነገገ ነው፡፡ "የኮንትሮባንድ ወንጀል" በሚል ነው፡፡ ይህም በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 91 ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ የተደነገገ ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 የተደነገገው በአዋጅ ቁጥር 859/2006 ካልተደነገገ ህጋዊ መፍትሔ (legal remedy) ምንድነው? የሚለው ምላሽ ሊያገኝ ይገባል፡፡ ይህ አዋጅ ግን ይህንን ጥያቄ የሚመልስ የህግ መርህ አይደነግግም፡፡ በዚህ ጊዜ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት የተደነገገው መሰረታዊ መርህ እንዲሁም በወንጀል ህጉ በመርህነት የተደነገገው ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በሌላ አነጋገር በኢፌዲሪ ህገመንግስትና በወንጀል ህግ ከተደነገገው መሰረታዊ መርህ አንጻር ታይቶ መተርጎም ይኖርበታል፡፡ በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 22 የወንጀል ህግ ወደ ኋላ ተመልሶ የማይሰራ ስለመሆኑ የተደነገገ ሲሆን የኢፌዲሪ የወንጀል ህግ አዋጅ ቁጥር 414/1996 አንቀጽ 5 በተመሳሳይ መልኩ ደንግጎታል፡፡ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 22(2) ድርጊቱ ከተፈጸመ በኃላ የወጣ ህግ ለተከሳሹ ወይም ለተቀጣው ሰው ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ከድርጊቱ በኃላ የወጣ ህግ ተፈጻሚነት ይኖረዋል በማለት ተደንግጓል፡፡ በወንጀልህግአንቀጽ 5(3) የተሻረው ህግ ይሰራ በነበረበት ጊዜ የተፈጸመ ወንጀል ሲኖርና በዚህ ህግ ግን እንደወንጀል ያልተቆጠረ ሲሆን ሊያስከሰስም ሆነ ሊያስቀጣ አይችልም፤ ክሱም ተጀምሮ እንደሆነ ይቋረጣል ተብሎ ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ የፈጸመው ድርጊት ምንም እንኳን በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 99 ላይ ወንጀል ሆኖ የተደነገገ ቢሆንም በዚህ አዋጅ ምትክ በተተካው አዋጅ ቁጥር 859/2006 ወንጀል ሆኖ አልተደነገገም፡፡ ስለዚህ በኢፌዲሪ ህገመንግስት እና በወንጀል ህጉ በተደነገገው መሰረታዊ መርህ አንጻር ሲደመደም ተጠሪ ጥፋተኛ ተደርጎ ቅጣት የሚወሰንበት የህግ አግባብ የለም ብለናል፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 44610 በቀን 22/04/2007 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 200935 በቀን 01/07/2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ከላይ በፍርድ ሀተታው የተገለጸውን የኢፌዲሪ ህገመንግስቱንና የወንጀል ህጉን መሰረታዊ መርህ መሰረት ያደረገ ባይሆንም በውጤት ደረጃ ግን ልዩነት ስለሌለው በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 195(2) (ለ) (2) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የውሳኔው ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

የሰ/መ/ቁ. 133773

ሐምሌ 14 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነው

በእውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አቶ ተክሌ ፈረጃ ጋዲሳ ጠበቃ ሳሙኤል ኤፍሬም ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢ/ያ ገ/ ጉ/ ባለስልጣን የመርካቶ ቁ.1መካከለኛ ግብር ከፋዩች ቅርንጫፍ ፅ/ቤት አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የንግድ ሥራ ግብር ክፍያን በሚመለከት የአሁን አመልካች ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ያቀረቡትን ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡አመልካች ለግብር ይግባኝ ሰሚው ጉባኤ ያቀረቡት ቅሬታ ይዘት በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ በመጋዘን ማከራየት ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ መሆኑን፤በ2006 ዓ/ም ግብር ዘመን ገቢውን በመዝገብ በመያዝ እና በማሳወቅ የሂሳብ መዝገብ አቅርቤ እያለ ሳያጣራ ከግብር/ ታክስ አወሳሰን ስርአት ውጪ ከተያዘብህ ያነሰ አመታዊ ሽያጭ ነው ያሳየኸው በሚል ብቻ ውድቅ በማድረግ የወሰነበትን የቀን ገቢ ግምቱን ሳይገልፅልኝ ታክሱን በግምት በወሰንኩት ልትከፍል ይገባል በማለት ወስኗል ፡፡ ገቢያን የማሰበስበው በተጠሪ በታወቀና ራሱ አዞ ባስገዛኝ በሂሳብ መመዝገብያ ማሽን ሆኖ ባለበት እንዲሁም መብራት ሲጠፋ እና በተለያየ ምክንያት የማይሰራ ቢሆን እንኳን ለተጠሪ በማሳወቅ ራሱ በፈቀደልኝና ባወቀው ደረሰኝ የሰበሰብኩትን ገቢያን መዝገብ በመያዝ አሳውቄ እያለሁ ይህን ሁሉ እወነታ በማለፍ ድርጅቱን በግንባር አይቶ የገመተበትን ጊዜ ሳይገልፅ የወሰነው ከአወሳሰን ስርአት ውጭ ነው ፡፡ በሌላ በኩል የቀን ገቢያቸው ብር 1,000 (አንድ ሺህ ብር) መሆኑ አምነው ፈርመዋል በማለት የገለፀው እኔ በወቅቱ በቦታው አልነበርኩም የነበረው ልጄ አስፈራርተውና ተቆጥተው ያስፈረሙት መሆኑ ገልፆልኛል ፡፡ ስለሆነም የምስራበት መጋዘን እጅግ በጣም

አነስተኛ በመሆኑ ጉባኤው በአካል የስራ እንቅስቃሴውን ተመልክቶ የተሰጠው ውሳኔ ተገቢ አለመሆኑን ጠቅሰው ተጠሪው አላግባብ የጠየቃቸውን ክፍያ ጉባኤው ውድቅ እንዲያደርግላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

ተጠሪው ለግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው በሰጠው መልስ የአመልካች ለ2006 ዓ/ም የግብር ዘመን ያቀረቡትን የሂሳብ መዝገብ መርካቶ መሃል ካላቸው መጋዘን ማከራየት ስራ ጋር ሲነፃፀር በጣም ዝቅተኛና ሊቀራረብ የማይችል ከመሆኑም በላይ ግብር ከፋዩ እራሳቸው ከሰጡት የቀን ገቢ መረጃ እንኳን በጣም የራቀ መረጃ ስላቀረቡ ተጠሪ በህግ መሰረት እና ባለው መረጃ መሰረት በማድረግ መወሰኑ ተገቢ ነው ፡፡ የአመልካች መጋዘን ያለበት የስራ ቦታ ከፍተኛ የገበያ ቦታ መሃል መርካቶ ኬኔዲ ህንፃ አጠገብ ሰፊ እቃ የማስቀመጥ አገልግሎት ፈላጊና ተጠቃሚ ያለበት ላይ በመሆኑ የቦታው ስፋትም 65 ካ.ሜ.የሆነ ትንሽ ሱቅ ተከይተው የሚሰሩ ባለሱቆች ሱቆቻቸውን ለማሳያ ብቻ እየተገለገሉ እቃዎቻቸውን በማስቀመጥ የሚጠቀሙበት ነው እራሳቸው ጥቅምት 25 ቀን 2007 ዓ/ም ለቀን ገቢ ገማቾች በሰጡት መረጃ ላይ በቀን 1,000 (አንድ ሺህ ብር) አገኛለሁ ያሉትን በመውሰድ ቢታይ እንኳን የአመት ሽያጭ ብር 365,000 (ሶስት መቶ ስልሳ አምስት ሺህ ብር) ነው፡፡ ምንም ገቢ አላገኘሁም ቢሉ እንኳን ያመኑዋቸው አራት ወራት ቢሰላ የሚመጣው ብር 120,000 (አንድ መቶ ሃያ ሺህ ሆኖ ሳለ ባቀረቡት ሂሳብ መዝገብ ላይ አገኘሁ ያሉት ሽያጭ ብር 89,100 (ሰማንያ ዘጠኝ ሺህ አንድ መቶ) ሲሆን በዚህም በቀን 244.11(ሁለት መቶ አርባ አራት ብር ከአስራ አንድ ሳንቲም) በመሆኑ የአመልካች የሂሳብ መዝገብ እምነት ስላጣንበት ውድቅ አድርገነዋል ፡፡ የቀን ገቢ ግምቱ የተከናወነው በድብቅ ሳይሆን ገማች ኮሚቴ ድርጅታቸው ድረስ በመሄድ ይግባኝ ባይ በሰጡት መረጃ መሰረት በማድረግ የንግድ ቤቱ አያያዝና የመጋዘኑ ስፋት፣እቃ የመያዝ አቅም ና የአካባቢውን ሁኔታ በዚሁ ተግባር የተሰማሩ ብዙ ነጋዴዎች ውስጉን መሆናቸው በማየጥ አመልካች በሰጡት በቀን ብር 1,000 (አንድ ሺህ ብር) ላይ የተወሰነ በመጨመር ብር 1,400 (አንድ ሺህ አራት መቶ ብር) በማድረግ የተገመተ መሆኑን በመጥቀስ አቤቱታቸው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግብር ይግባኝ ሰሚው ጉባኤ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ አመልካች ከቀን ገቢ ግምት ግማሽ በታች በሆነ መልኩ በሂሳብ መዝገብ ያቀረቡትና ያሳወቁት ገቢ በበቂ እና አሳማኝ ምክንያቶች የተደገፈ ሆኖ ስላላገኘነው መልስ ሰጪ በ2006 ዓ/ም ግብር ዘመን የቀን ገቢ ግምት ብር 1,400 (አንድ ሺህ አራት መቶ) ብር በመያዝ ግብርና ታክስ የወሰነበት አግባብ የሚነቀፍ አይደለም በማለት አፅንቶታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ግራቀኙን አከራክሮ ውሳኔውን አጽንቶታል፡፡በመቀጠል አመልካች ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ

ችሎት ቅሬታ ያቀረቡ ቢሆንም መሰረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈጸመም በማለት አቤቱታቸው ውድቅ ተደርጓል፡፡የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡-አመልካች  የ2005 ዓ/ም የግብር ዘመን በተመሳሳይ ባሰራሁት የሂሳብ መዝገብ በባለሞያ ሂሳብ መዝገብ ተሰርቶ የቀረበውን ይህንኑ በህጉ በተጣለበት ግዴታ ሳይመረምር የ2006 ዓ/ም የግብር ዘመን በተመለከተ በባለሞያ ሂሳብ መዝገብ ተሰርቶ የቀረበውን ተጠሪው መስሪያ ቤት በሂሳብ መዝገብ የቀረበውን አመታዊ ሽያጭ ከቀን ገቢ ግምት ያነሰ ነው፣ በሚል ምክንያት አልቀበልም ብሎ በቀን ገቢ ግምት መወሰኑ ከአዋጁ ቁጥር 286/94 አንቀፅ 69 እና ከ64 ጀምሮ ካሉት ድንጋጌዎች የወጣ በሆነ ሁኔታ  በራሱ ግምት እንድከፍል መወሰኑ ያለአግባብ ነው፡፡ በመሆኑም ለግብር ይግባኝ ሰሚው ጉባኤ ያቀረብኩት አቤቱታ ውድቅ መደረጉ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ በዚህ ችሎት መታየት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ግራ ቀኙ በጽሑፍ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው ፡፡ ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ህጎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል ፡፡ በዚህ ችሎት ምላሽ ማግኘት የሚገባው ነጥብም ተጠሪው ባቀረበው ግምት መሰረት አመልካች እንዲከፍሉ የተወሰነው የግብር መጠን በአግባቡ ነው ?ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ ሆኖ አግኝተነዋል ፡፡ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 69 ግብር ከፋዩ የሂሳብ መዝገብ እና ሰነድ ካልያዘ ወይም በማናቸውም ምክንያት የሂሳብ መዝገቡን እና ሰነዱን የግብር አስገቢው ባለስልጣን ያልተቀበለው እንደሆነ ወይም ግብር ከፋዩ በሕጉ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ገቢውን ያላስታወቀ እንደሆነ ግብር አስገቢው ባለስልጣን የግብሩን ልክ በግምት ሊወስን እንደሚችል ይደነግጋል፡፡በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ በአመልካች ላይ የቀን ገቢ ግምትን  መሠረት የግብር ማስታወቂያ የሰጣቸው አመልካች የ2006 ዓ/ም የግብር ዘመን በተመለከተ በባለሞያ ሂሳብ መዝገብ ተሰርቶ የቀረበ ቢሆንም  ተጠሪው መስሪያ ቤት በሂሳብ መዝገብ የቀረበውን አመታዊ ሽጭ ከቀን ገቢ ግምት ያነሰ ነው በሚል ምክንያት አልተቀበላቸውም፡፡ አመልካች ከዚህ በፊት ራሳቸው ባሳወቁት የቀን ገቢ ግምት ብር1,000 (አንድ ሺህ ብር) ነው በማለት የገለፁ ሲሆን በሂሳብ መዝገባቸው ያሳወቁት አመታዊ ገቢ ብር 89,100 (ሰማንያ ዘጠኝ ሺህ አንድ መቶ) መሆኑን በዚሁ መሰረትም በዚህም በቀን 244.11(ሁለት መቶ አርባ አራት ብር ከአስራ አንድ ሳንቲም) በመሆኑ ፣አመልካች የአመት ገቢያቸው ከግማሽ በታች ያሳወቁ በመሆናቸው ተረጋግጦ ያቀረቡት የሂሳብ መዝገብ ውድቅ የተደረገ መሆኑን ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ ይቻላል፡፡

አመልካች ሂሳብ መዝገብ ነበረኝ በባለሞያም አሰርቼ ያቀረብኩት ትክክለኛ ገቢየ ነው በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም አመልካች ከሚሰሩበት መጋዘን ስፋት እንዲሁም መጋዘኑ ለእቃ ማከማቻነት በጣም አስፈካጊ በሆነ ቦታ ላይ በመሆኑ ያቀረቡት የቀን ገቢ እምነት የማይጣልበት ስለመሆኑ ፍሬ ነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ባለው የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ተረጋግጧል ፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ እና በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 112 መሰረት ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው ስልጣን መሠረታዊ የሕግ ስሕተትን የማረም ሥልጣን እንጂ ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን የለውም ፡፡ ስለሆነም በአመልካች ላይ የተጣለው የግብር መጠን በሕጉ መሰረት መሆኑን ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ባለው የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ እና በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀቡት አቤቱታ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም ፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግብር ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ በመ.ቁጥር 033/08 ግንቦት 26 ቀን 2008 ዓ/ም ተሰጥቶ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በመ.ቁጥር 25576 ሃምሌ 27 ቀን 2008 ዓ/ም እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁጥር 25816 መስከረም 10 ቀን 2009 ዓ/ም በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

# ውል

የሰ/መ/ቁ. 117036

ሕዳር 12 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- ፀጉብርሃን ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ኮሎኔል ይትባረክ አማረ - ከጠበቃ ኃይለስላሴ ገ/መድህን ጋር ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ተጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች የሽያጭ ውሉን በወቅቱ ባለመፈፀሙ በኃላፊነት ይጠየቃል በማለት አመልካች የመኪና ሽያጭ ውሉን ባለመፈፀሙ ተጠሪ ላይ የደረሰበት ጉዳት ተጣርቶ እንዲቀርብ በማለት የሰጡት ውሣኔ አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ /ከሳሽ/ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው የክስ ማመልከቻ ነው፡፡
2. ከሳሽ ለስር ፍርድ ቤት ባቀረበው ክስ ነሐሴ 7 ቀን 2006 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል፣ ከተከሳሽ ሁለት ተሽከርካሪዎችን ለመግዛት ተዋውሎ፣ የሁለቱን መኪኖች ዋጋ ብር 2,300,000 /ሁለት ሚሊዮን ሶስት መቶ ሺህ ብር/ ገቢ አድርጌያለሁ፡፡ ተከሳሽ መኪኖቹን ውሉን ከተፈራረምንበት ቀን ጀምሮ በአስራ አምስት የስራ ቀናት ማለትም እስከ ነሐሴ 27 ቀን 2006 ዓ.ም ሊያስረክበኝ የውል ግዴታ ገብቷል፡፡ ከሳሽም መኪኖቹ ከቀረጥ ነፃ እንዲያስገባ ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ሰጥቶኛል፡፡ ሆኖም ተከሳሽ በውሉ መሠረት መኪኖቹን ያላስረከበኝ በመሆኑ፣ ከሳሽ የከፈልኩትን ገንዘብ እንዲከፍል ይወሰንልኝ፡፡ ከሳሽ ከነሐሴ 27 ቀን 2006 ዓ.ም መኪኖቹን እረከባለው በሚል እምነት አንድ ተሽከርካሪ በወር

ብር 3000 /ሶስት ሺህ ብር/ ሁለቱን በብር 6000 /ስድስት ሺህ ብር/ አከራይቼ አገኝ የነበረውን ጥቅም ስለቀረብኝና በዚህ ምክንያት ለደረሰው ጉዳት ብር 354,000 /ሶስት መቶ አምሳ አራት ሺህ ብር/ እንዲከፍልና ዕዳው ተከፍሎ እስኪያልቅ ድረስ በወር ብር 6000 /ስድስት ሺህ ብር/ እየተሰላ ካሣ እንዲከፍል፤ የወሰደውን ገንዘብ ወለድ እንዲከፍልና፣ የገደብ መቀጮ ብር 5000 /አምስት ሺህ ብር/ እንዲከፍል ውሳኔ ይሰጥልኝ የሚል ይዘት ያለው ክስ አቅርቧል፡፡

3. አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ ለከሳሽ ሁለት መኪኖች ለመሸጥና የመኪኖችን ዋጋ ከሳሽ መክፈሉ የሚካድ አይደለም፡፡ ተከሳሽ ለከሳሽ መኪኖችን ለማስረከብ የተለያዩ ተግባራትን ከከሳሽ ሰራተኞች ጋር በመተባበር ሲፈፀም ቆይቷል፡፡ መኪኖችንም በውሉ በተገለፀው ጊዜ ውስጥ ለማስረከብ ፈቃደኛ ነበር፣ ነገር ግን በመዝገብ ቁጥር 24172 የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነሐሴ 21 ቀን 2006 ዓ.ም በመኪኖቹ ላይ የዕግድ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ የዕግድ ትዕዛዙን በመቃወም ተከሳሽ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቤ በመዝገብ ቁጥር 157145 የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን የዕግድ ትዕዛዝ አፅንቶታል፡፡ በመሆኑም በሽያጭ ውሉ መሠረት ያልተፈፀመው ተከሳሽ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት የፍርድ ቤት የዕግድ ትዕዛዝ በመሆኑ ከሳሽ ለውሉ አለመፈፀም ተከሳሽ ኃላፊ እንዲሆንና ካሣ እንዲከፍል ለማለት ያቀረበው ክስ የሕግ መሠረት የለውም፡፡ በሽያጭ ውሉ ውል አለመፈፀም ብር 5000 /አምስት ሺህ ብር/ የሚያስቀጣ መሆኑ ከሳሽ ካሣ ይክፈለኝ በማለት የጠየቀው ተገቢ አይደለም የውሉና ሌሎች መከራከሪያዎችን በማንሳት መልስ ሰጥቷል፡፡

4. የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ ተከሳሽ ለከሳሽ ከሸጣቸው ሁለት መኪኖች መካከል የአንደኛው መኪና የሻንሲ ቁጥር lzz5elnd77n847969 እና የሞተር ቁጥር 131107038497 መሆኑ ከሳሽ ባቀረበው የሰነድ ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ሆኖም ተከሳሽ ከከሳሽ ነሐሴ 7 ቀን 2006 ዓ.ም በመሸጥ ሙሉ ዋጋውን የተቀበለበት የሻንሲና የሞተር ቁጥሩ የተጠቀሰውን መኪና ህምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም በተደረገ ለአቶግደይ ገ/ፃዲቅ የሸጠው መኪና መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህም ተከሳሽ ለከሳሽ የሸጠውን አንደኛው መኪና የሻንሲና የሞተር ቁጥሩ ተለይቶ የታወቀውን መኪና ለከሳቭ በሽያጭ ለማስተላለፍ የሚያስችል መብት ሳይኖረው የፈፀመው የሽያጭ ውሉ በመሆኑ ለውሉ አለመፈፀምም ሆነ በከሳሽ ላይ ለደረሰው ጉዳት ተከሳሽ ኃላፊነት አለበት፡፡ በሌላ በኩል ተከሳሽ ብር 3000,000 /ሶስት ሚሊዬን ብር/ አስይዞ ዕግዱን በማስነሳት መኪኖቹን ለከሳሽ ማስረከብ እየቻለ ይህንን ያላደረገ በመሆኑ ለሽያጭ ውሉ ኃላፊ ነው በማለት ከሳሽ የከፈለውን የመኪኖቹን ዋጋ ከዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር እንዲመልስ በውሉ የተገለፀውን የገደብ መቀጫ ብር 5000 /አምስት ሺህ ብር/ እንዲከፍልና በውሉ አለመፈፀም ምክንያት

በከሳሽ ላይ የደረሰውን ኪሳራ /ጉዳት ተጣርቶ/ እንዲቀርብ በማለት በመዝገብ ቁጥር 153576 ሰኔ 12 ቀን 2007 ዓ.ም ከፊል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ይግባኝ ሰሚው ችሎት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

5. አመልካች ነሐሴ 5 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪ ከሸጣቸው ሁለት መኪኖች አንደኛው ቀደም ሲል ለአቶግደይ ገ/ፃዲቅ የሸጠው መሆኑን በመግለጽ ውሳኔ የሰጠው በማስረጃ ያልተረጋገጠ ፍሬ ጉዳይ ላይ የተመሠረተነው፡፡ አመልካች ከተጠሪዎች ጋር ሆነ ከአቶ ግደይ ገ/ፃዲቅ ጋር በተዋዋለው የመኪና ሽያጭ ውል ላይ የመኪና የሻንሲ ቁጥርና የሞተር ቁጥር አልጠቀሰም፡፡ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ አንቀጽ 223፣አንቀጽ 137/1 እና አንቀጽ 256 መሠረት ያላቀረበውን የሰነድ ማስረጃ በመቀበል አመልካች አንደኛውን መኪና ለተጠሪ ያላስረከበው ቀደም ብሎ መኪናውን በሽያጭ ለሌላ ሰው ስለሸጠው ነው በማለት የደረሰበት መደምደሚያ የማስረጃ አቀራረብ ድንጋጌዎችን የሚጥስና መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡ አመልካች ለተጠሪ የሸጣቸውን ሁለት መኪኖች ለተጠሪ ሳያስረክብ የቀረው በባልና ሚስት ክርክር መነሻ መኪኖቹ እንዳይሸጡ እንዳይለወጡና ለሶስተኛ ወገን እንዳይተላለፉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዕግድ ትዕዛዝ በመስጠቱና የዕግድ ትዕዛዙን ለማስነሳት አመልካች ጥረት ቢያደርግም ጥረቱ ውጤት አልባ በመሆኑ ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ስለገጠመው ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪ የከፈለውን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲከፍል ውሣኔ ከሰጠ በኃላ የሽያጭ ውሉ ያለመፈፀሙ ተጠሪ ላይ ያደረሰውን ኪሳራ አመልካች የመሸፈን ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጠው ውሳኔ የሕግ መሠረት የለውም፡፡ አመልካች ተጠሪ ወሉን ያልፈፀመ ወገን ምንያህል ገንዘብ መክፈል እንዳለበት ውል ተዋውለዋል፡፡የስር ፍርድ ቤት በውሉ የተገለጸውን የገደብ መቀጫ ማስከፈል ሲገባው ከገደብ መቀጫው አልፎ ለተጠሪ አመልካች ካሣ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

6. ተጠሪ በበኩሉ ህዳር 8 ቀን 2008 ዓ.ም በተሰጠ መልስ አመልካች ለተጠሪ ነሐሴ 7 ቀን 2006 ዓ.ም በተደረገው የሽያጭ ውል ከሸጣቸው መኪናዎች ውስጥ የአንደኛውን የሻንሲና የሞተር ቁጥር በመግለጽ ለገቢዎችና ጉሙሩክ ባለስልጣን ያሳወቀ በመሆኑ ተጠሪ ከገዛቸው መኪናዎች ውስጥ የአንደኛው መኪና የሻንሲ እና የሞተር ቁጥር ተለይቶ የታወቀ ነው፡፡ ሆኖም አመልካች በተጠሪ ከሸጣቸው መኪናዎች ውስጥ ይህንን የሻንሲና የሞተር ቁጥሩን ለይቶ ያሳለቀውን መኪና ቀደም ሲም ሲል ሐምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም በተደረገ ውል ለአቶግደይ ገ/ፃዲቅ የሸጠውና ይህንኑ መኪና ለአቶግደይ ገ/ፃዲቅ ለማስረከብ የሚቻል መሆኑን ገልጾ የፃፈው ደብዳቤ የአመልካች ስራ አስኪያጅ በፈፀመው የማታለል ወንጀል ክስ

የቀረበበት መሆኑንና አቶግደይ ገ/ፃዲቅ አመልካች የሻንሲና የሞተር ቁጥሩ የተገለፀውን መኪና እንዲያስረክባቸው ከፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 153390 ክስ አቅርበው ፍርድ ቤቱ ጳጉሜ 5 ቀን 2006 ዓ.ም እና መስከረም 12 ቀን 2007 ዓ.ም የዕግድ ትዕዛዝ የሰጠ መሆኑን የሚያሳዩ ማስረጃዎች መኖራቸውን ያወቅነው ክሱንና የማስረጃ ዝርዝር መግለጫ ለፍርድ ቤቱ ካቀረብን በኃላ በመሆኑ ማስረጃዎቹን የስር ፍርድ ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 256 መሠረት እንደናቀርብ ፈቃድ ጠይቀን በፍርድ ቤቱ ፍቃድ መሠረት ያቀረብናቸው የሰነድ ማስረጃዎች በመሆናቸው አመልካች የስር ፍርድ ቤት ከሥነ-ሥርዓት ሕግ ውጭ ማስረጃ እንደተቀበለ በመግለጽ ያቀረበው አቤቱታ የህግ መሠረት የለውም፡፡ ሌላውን መኪና በተመለከተ አመልካች ብር 3000,000 /ሶስት ሚሊዬን ብር/ በማስያዝ ዕግዱን ማስነሳትና የውል ግደታውን መወጣት እየቻለ ይህንን አላደረገም አመልካች ውሉን ያልፈፀመው በፍርድ ቤቱ ዕግድ ምክንያት አይደለም ስለሆነም ውሉን ያልፈፀምኩት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው በማለት ያቀረበው ክርክር የህግ ድጋፍ የለውም አመልካች የወሰደውን ገንዘብ ወለድ ተጠሪ በውሉ አለመፈፀም የደረሰበትን ኪሳራና በውሉ ላይ የተገለፀውን የገደብ መቀጫ እንዲከፍል የተወሰነው በአገባቡ ነው የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ታህሳስ 14 ቀን 2008 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልሰ አቅርቧል፡፡

7. ይኸ ሰበር ችሎት አመልካችና ተጠሪ በቃል ሊከራከሩባቸው የሚገቡ ነጥቦችን ሰኔ 22 ቀን 2008 ዓ.ም ለይቶ ለግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲደርሳቸው ካደረገና በተለያየ ምክንያት የቃል ክርክር ለማስማት የሰጠውን ቀነ ቀጠሮ ከተለወጠ በኃላ የቃል ክርክሩን የመጨረሻ ቀነ ቀጠሮ በሰጠበት ጥቅምት 24 ቀን 2009 ዓ.ም አመልካች ወኪል ወይም ጠበቃ ባለመቅረቡ የተጠሪን የቃል ክርክር ሰምቷል፡፡ አመልካች ስለ ማስረጃ አቀራረብ ሥርዓትና ሌሎች ነጥቦች የቀረበውን የሰበር ክርክር ለማረጋገጥና ለማገናዘብ እንዲቻል የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመዝገብ ቁጥር 153516 እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶ መዝገቡን በትዕዛዙ መሠረት በማስቀረብ ተመልክቷል፡፡

8. ከስር የክርክር አመጣጥና ግራቀኙ ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ነሐሴ 7 ቀን 2006 ዓ.ም ከተጠሪ ጋር በተዋዋለው ሁለት ገልባጭ መኪኖች ሽያጭ መሠረት ለተጠሪ የሚያስረክበው መሆኑን ገልጾየገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በፃፈው ደብዳቤ የገለፀውና ያሳወቀው የሻንሲ ቁጥር lzz5elnd77n847969 የሆነውና የሞተር ቁጥሩ 131107038497 የሆነውን መኪና ቀደም ብሎ ሀምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም ለአቶግደይ ገ/ፃዲቅ የሰጠውና ይህንኑ መኪና ለአቶግደይ ገ/ፃዲቅ ለማስረከብ እንደሚችል ገልጾ ደብዳቤ የፃፈበት መሆኑን በአጠቃላይ መኪናውን ለሁለት ሰው በመሸጥ ዋጋ የተቀበለበት መሆኑን ፍሬ ጉዳይ

የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍትሐብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተረጋግጧል፡፡

9. አመልካች ተጠሪ የሻንሲ ቁጥሩና የሞተር ቁጥሩ ተለይቶ የተገለፀው መኪና በሌላሰው የተሰጠ መሆኑን ተጠሪ የፍትብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ በሚደነግገው መሠረት የሰነድ ማስረጃዎቹን አላቀረበም በማለት ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታና ክርክር ተገቢነት መመርመሩ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ እኛም የስር ፍርድ ቤቶች መዝገብ በትዕዛዝ በማስቀረብ ከሳሽ /ተጠሪ/ የሻንሲና የሞተር ቁጥሩ የገለፀውን መኪና ቀደም ሲል ለአቶግደይ ገ/ፃዲቅ ይሸጠው መሆኑንና ይህንኑ መኪና ለአቶግደይ ገ/ፃዲቅ ለማስረከብ የሚችል መሆኑን ገልጾ ለገቢወችና ጉምሩክ ባለስልጣን ደብዳቤ ጽፎ እንደነበር የሚያሳይ የሰነድ ማስረጃዎች ተጠሪ ክሱን ሲያቀርብ የማያውቃቸውና ያላገኛቸው መሆኑን በመግለጽ ፍርድ ቤቱ ሰነዶቹን በተጨማሪ ማስረጃነት ለማቅረብ እንዲፈቅድለት የካቲት 12 ቀን 2007 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ጠይቋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ከሳሽ /ተጠሪ/ ባቀረበው የተጨማሪ ማስረጃ የማቅረብ ጥያቄ ላይ ተከሳሹ /አመልካች/ አስተያየቱን እንዲያቀርብ የካቲት 12 ቀን 2007 ዓ.ም ትዕዛዝ ሰጥቶ አመልካች የፍርድ ቤቱን ትዕዛዝና አባሪውን የካቲት 16 ቀን 2007 ዓ.ም የደረሰው መሆኑ በድርጅቱ ማህተም ካረጋገጠ በኃላ ተከሳሽ /አመልካች/ ከሳሽ /ተጠሪ/ ባቀረበው የተጨማሪ ማስረጃ የማቅረብ ጥያቄ ላይ አስተያየቱን ባለማቅረቡ የስር ፍ/ቤት ከሳሽ በተጨማሪ ማስረጃነት ለማቅረብ ጥያቄ ያቀረበባቸው የሰነድ ማስረጃዎች የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 256 መስፈርት የሚያሟሉ መሆኑን በማረጋገጥ ማስረጃዎቹ እንዲቀረቡና ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዙ ሰኔ 12 ቀን 2007 ዓ.ም ብይን ከሰጠ በኃላ የሰነድ ማስረጃዎችን በመቀበል ለፍርድ በግብዓትነት የተጠቀመባቸው መሆኑን ተረድተናል፡፡

10. ይኸ ሰበር ችሎት በትዕዛዝ ካስቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመዝገብ ቁጥር 153516 እንደተረዳነው የሥር ፍርድ ቤት የተጠሪን ተጨማሪ ማስረጃዎች በተጨማሪ ማስረጃነት ከመቀበሉ በፊት አመልካች አስተያየት የመስጠትና የመከራከር መብቱን ጠብቆ አመልካች ዕድሉን ተጠቅሞ አስተያየቱን ባለማቅረቡ ይህንኑ ምክንያቱን በግልጽ በመዝገብ ላይ በማስፈር ትዕዛዝ ሰጥቶ እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች ሰነዶቹ በተጨማሪ ማስረጃነት ሊቀረቡ አይገባም የሚልበትን ምክንያት ለሥር ፍርድ ቤት ያላቀረበውን ክርክርና አስተያየት ለዚህ ሰበር ችሎት ማቅረቡ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሥር ፍርድ ቤት በማስረጃ የማቅረብ ጥያቄ ውሳይ አመልካች አስተያየትና ክርክር የማቅረብ መብቱን መጠበቁ ብቻ ሳይሆን ከሳሽ /ተጠሪ/ በተጨማሪ ማስረጃነት ለማቅረብ ጥያቄ ያቀረበባቸው የሰነድ ማስረጃዎች በፍ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁጥር 256 የተደነገገውን መስፈርት የሚያሟሉ ናቸው ወይስ አይደሉም የሚለውን ነጥብ በአግባቡ በመመርመር ማስረጃዎቹን ለመቀበል ብይን የሰጠ መሆኑን ተረድተናል፡፡

11. ተጠሪ ለስር ፍርድ ቤት በተጨማሪ ማስረጃነት ያቀረባቸው የሰነድ ማስረጃዎች ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ ሲያቀርብ ተገቢውን ትጋት በማድረግ ሊያውቃቸውና ሊያገኛቸው የማይችላቸው ማለትም አመልካች ለተጠሪ የሸጠው መሆኑን ገልጾ ለአዲስ አበባ ቃሊቲጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በቁጥር TB.TP11648114 ነሐሴ 8 ቀን 2006 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ የሻንሲና የሞተር ቁጥሩ የተገለፀውን መኪና ቀደም ሲል አመልካች ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅርጫፍ ጽ/ቤት ለአቶግደይ ገ/ፃዲቅ የሸጠው መሆኑን ቁጥሩ TB.TB 1106114 ሀምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ የሻንሲና የሞተር ቁጥሩን የገለፀውን መኪና መሆኑን ይህንን መኪና ሀምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም አመልካች ለግደይ ገ/ፃዲቅ የሸጠ መሆኑ ገልፀው አቶግደይ ገ/ፃዲቅ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 153390 ክስ ማቅረባቸውን በመጀመሪያ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድቤት ጳጉሜ 4 ቀን 2006 እስከ መስከረም 9 ቀን 2007 የሚቆይ የዕግድ ትዕዛዝ መስጠቱንና መስከረም 9 ቀን 2007 ዓ.ም መኪናው ለሶስተኛ ወገን እንዳይተላለፍ የዕግድ ትዕዛዝ የሰጠ መሆኑን የሚያሳዩ የሰነድ ማስረጃዎች እንደሆኑ ተረድተናል፡፡ እነዚህ በአመልካችና በሌላ ሶስተኛ ወገን እጅ የነበሩ ማስረጃዎች ተጠሪ ክስ ሲያቀርብ የማያውቃቸውና ሊያገኛቸው የማይችል ማስረጃዎች በመሆናቸው በስር ፍርድ ቤት የሰነድ ማስረጃዎች በተጨማሪ ማስረጃነት እንዲቀርቡ በማድረግ መርምሮና መዝኖ ውሳኔ የሰጠው የፍ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 256 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሠረት በመሆኑ በዚህ አመልካች ያቀረበው የሰበር አቤቱታና ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

12. አመልካች ነሐሴ 7 ቀን 2006 ዓ.ም ከተጠሪ ጋር ባደረገው የመኪና ሽያጭ ውል በአመልካች የሸጠው የሻንሲና የሞተር ቁጥሩ የተገለፀው አንደኛውመኪና አመልካች ቀደም ብሎ ሀምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም ለአቶግደይ ገ/ፃዲቅ የሰጠው መሆኑንና አመልካች መኪናውን ለአቶግደይ ገ/ፃዲቅ የሰጠ መሆኑን ሀምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ የሻንሲና የሞተር ቁጥሩን ጠቅሶ ለኢትዩጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ያሳወቀ መሆኑ የሕጉን ሥርዓት በመከተል ተጠሪ ባቀረባቸው ተጨማሪ የሰነድ ማስረጃዎች የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ህጋዊ ውጤት ምንድን ነው የሚለውን ነጥብ ተመልክተናል፡፡ ከላይ በዝርዝር እንደተገለፀው አመልካች ነሐሴ 7 ቀን 2006 ዓ.ም በተደረገ የሁለት መኪናዎች ሽያጭ ውል መሠረት ሙሉ ዋጋውን የተቀበለበትና እስከ ነሐሴ 25 ቀን 2006 ዓ.ም ለተጠሪ ለማስረከብ የውል ግደታ የገባበት የሞተር ቁጥሩ 131107038497 እና የሻንሲ ቁጥሩ lzz5elnd77nb847969 የሆነው መኪና አመልካች ቀደም ብሎ ለሌላ ሰው የሸጠውና ለሌላ ሰው የሸጠውመሆኑንም ለገቢዎችና ጉምሩክ ጽ/ቤት ሀምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ ያረጋገጠው የመኪናውን ባለሀብትነት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2273 ንዑስ

አንቀጽ 2 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2281 በተደነገገው መሠረት ለማስተላለፍ የማይችል መሆኑን እያወቀ የተዋዋለው የሽያጭ ውል ነው፡፡

13. ከዚህ አንፃር ሲታይ ከላይ የሞተርና ያሻንሲ ቁጥር የተገለፀውን መኪና በተመለከተ አመልካች በሽያጭ ውሉ መሰረት ያልፈፀመው በባልና ሚስት ክርክር ምክንያት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነሐሴ 21 ቀን 2006 ዓ/ም የዕግድ ትዕዛዝ በመስጠቱ ምክንያት ነው በማለት አመልካች የማያቀርበው ክርክር በማስረጃ የተረጋገጡትን ኩነቶች /ፍሬነገሮች/ መሰረት ያደረገ አይደለም አመልካች ለተጠሪ ከሸጣቸው መኪናዎች ውስጥ ሲታይ የሞተር ቁጥር የሻንሲ ቁጥር የተጠቀሰውን መኪና ሙሉ የባለሃብትነት መብት ለተጠሪ ለማስተላለፍ የማይቻልበት የሶስተኛ ወገን መብትና ጥያቄ በመኪናው ላይ ያለመሆኑን ተረጋግጧል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነሐሴ 21 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ባይኖር ወይም የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቶ ቢሆንም አመልካች በሽያጥ ውሉ መሰረት የመኪናውን ሙሉባለሀብትነት ሊያስተላልፍ እንደማይችልና መኪናውን በቀዳሚነት ገዝቼ ዋጋ ከፍየበታለሁ የሚለው አቶ ግደይ ገ/ፃዲቅ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ አቅርቦ ያሳገደው መሆኑን ፣የአመልካች ድርጅት ሥራ አስኪያጅ መኪናውን ለሌላ ሰው ከሸጠ በኃላ ያንኑ መኪና ለተጠሪ መሸጥ የማታለል ተግባር የፈፀመ መሆኑ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ተረጋግጧል ፡፡

14. ይህም አመልካች የተጠሪን መብት በሚነካ ጉድለት ምክንያት የሞተርና የሻንሲ ቁጥር የተገለፀልን መኪና መኪናውን ከአመልካች ቀድሞ ሀምሌ 17 ቀን 2006 ዓ/ም በተደረገው ውል ከገዛው አቶ ግደይ ገ/ፃዲቅ መብትና ጥያቄ ነፃ አድርጎ ለተጠሪ ሊያስረክበው እንደማይችል ዕያወቀ የሽያጭ ውሉን ከተጠሪ ጋር በመዋዋሉ ምክንያት ውሉ ፈራሽ እንዲሆን ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2341 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል ተጠሪ ውሉን የተዋዋለው መኪናውን ለሌላ ሰው አመልካች የሸጠው መሆኑን ሳያውቅ በመሆኑና አመልካች የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2341 ንዑስ አንቀፅ 1 የተጣለበትን ግዴታ ያልተወጣና ሊወጣ እንደማይችል እያወቀ የፈፀመው የሽያጭ ውል በመሆኑ ተጠሪ ውሉ ፈራሽ እንዲሆን ፣ ተጠሪ የተቀበለውን የመኪናውን ዋጋ ከህጋዊ ወለድ ጋር እንዲመለስለትና አመልካች መኪናውን በውሉ መሰረት ባለመፈፀሙ ያደረሰበት ኪሣራ እንዲከፍል ያቀረበው ጥያቄ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2341 ንዑስ አንቀፅ 1፣ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2356 ንዑስ አንቀፅ 1 የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2360 ንዑስ አንቀፅ 2 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2364 ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ሆኖ አግኝቶታል ፡፡

15. ከዚህ አንፃር አመልካች የሞተርና የሻንሲ ቁጥር የተገለፀውን መኪና ሙሉ ባለሀብትነት ለተጠሪ ሊያስተላልፍ እንደማይችልና መኪናውን ለሌላ ሰው አስቀድሞ የሸጠው መሆኑን ዕያወቀ ከተጠሪ ጋር የመኪና ሽያጭ ውል በመዋዋል የመኪናውን ሙሉ ዋጋ ከተቀበለ በኃላ የመኪናውን ሙሉ ባለመብት ለተጠሪ ለማስተላለፍ የማይችል በመሆኑ ምክንያት የሽያጭ ውል ያፈረሰው በተጠሪ ጥፋት ምክንያት መሆኑን በማረጋገጥ አመልካች ከተጠሪ የወሰደውን ብር 1,150,000 ( አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሃምሳ ሺ ብር ) ነሐሴ 8 ቀን 2006 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ፣ ውሉን ባለመፈፀሙ በውሉ የተገለፀውን የገደብ መቀጫ ብር 5,000 (አምስት ሺ ብር ) እና ውሉ ባለመፈፀሙ በተጠሪ ላይ የደረሰበት ኪሣራ ተጣርቶ ለአመልካች እንዲከፍል በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ውሳኔ ከላይ የገለፅናቸውን ስለ ሽያጭ ዉሉ የተደነገጉትን ልዩ ድንጋጌዎች ማለትም የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2341 ንዑስ አንቀፅ 1 የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2356 ንዑስ አንቀጽ 1 የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2360 ንዑስ አንቀፅ 2 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2364 ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት ያደረገ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡
16. አመልካች ከተጠሪ ጋር ነሐሴ 7 ቀን 2006 ዓ/ም በተዋዋለው ውል ያሸጠለት ሌላውን አንድ መኪና በተመለከተ በባልና ሚስት ክርክር መነሻ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነሐሴ 21 ቀን 2006 ዓ/ም የዕግድ ትዕዛዝ ባይሰጥና የዕግድ ትዕዛዙን ለማስነሳት አመልካች በይግባኝ አቅርቦ የዕግድ ትዕዛዝ በይፀናበት በወሉ መሰረት ለመፈፀም የሚያስችለው ሌላ ምክንያት የሌለው መሆኑ የስር ፍ/ቤትና በውሳኔው ካሰፈራቸው ፍሬ ነገሮች ለመረዳት ይቻላል የሥር ፍርድ ቤት አመልካች መኪናውን ለተጠሪ ባለማስረከቡ አላፊነት አለበት ያለው የፌዴራል የመጀሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን የዕግድ ትዕዛዝ አመልካች ብር 3,000.000 (ሶስት ሚሊዮን ብር) በሚያሲያዝ አስነስቶ መኪናውን ለተጠሪ ለማሰረከብ የማልችልበት ሁኔታ ነበር በማለት ነው ሆኖም የስር ፍርድ ቤት በወቅቱ የባንክ ሂሳቡን በነፃነት ለማንቀሳቀስና ብር 3,000.000 (ሶስት ሚሊዮን ብር) የባልና የሚስት ክርክር ሲያይ የነበረውና የዕግድ ትዕዛዙን ለሰጠው ፍርድ ማስያዝ አቅም እና ችሎታ የነበረው ለመሆኑ በተጠሪ በኩል የቀረቡለት ማስረጃ ስለመኖሩና ስለመረጋገጡ በውሳኔው አላሰፈረም፡፡
17. ይህም አመልካች ለተጠሪ የሰጠውን ሌላውን አንድ መኪናን በተመለከተ በሽያጭ ውሉ መሰረት ያልፈፀመው በአመልካች ጥፋት ወይም ቸልተኝነት ሳይሆን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1793/ለ/ መሰረት አመልካች በገባው የውል ግዴታ መሰረት መኪናውን ለተጠሪ ሆነ ለሌላ ሶስተኛ ወገን እንዲያስተላለፍ ነሐሴ 21 ቀን 2006 ዓ/ም ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ክልከላ የተደረገበት ወይም የዕግድ ትዕዛዝ የተሰጠበት በመሆኑ ምክንያት ለመሆኑ የሥር

ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ለተጠሪ የሸጠውን አንድ መኪና ያላስረከበውን እንደ ውሉ ያልፈፀመው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት አይደለም በማለት የሰጠውን ውሳኔ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1793/ለ/ ድንጋጌ ያላገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

18. አመልካች ለተጠሪ የሸጠውን አንድ መኪና ያላስረከበውና እንደ ውል ያልፈፀመው ከእሱ አቅም በላይ በሆነ ችግር ምክንያት በመሆኑ አመልካች የወሰደውን የመኪናውን ዋጋ ብር 1,150.000 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ አምሳ ሺ ብር ) ከነሐሴ 8 ቀን 2006 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2356 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ከመመለስ ውጭውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት የተጠሪ ላይ ያደረሰውን ኪሣራ /ጉዳት/ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2364 ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት እንዲከፍል የሚገደድበት የሕግ መሰረት የለም፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች ለተጠሪ የሸጠውን አንደኛውን መኪና በተመለከተ በውሉ መሰረት ባለመፈፀሙ ተጠሪ የደረሰበት ጉዳት የመክፈል አላፊነት አመልካች አለበት በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል ፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 153516 ሰኔ 12 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ከፊል ፍርድና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍታብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 115897 ሐምሌ 23 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ የሞተር ቁጥር 131207038497 የሆነውና የሻንሲ ቁጥር LZZ5 ELND77NB 847969 የሆነውን መኪና ለተጠሪ ለመሸጥ ውል የተዋዋለውና የመኪናውን ሙሉ ዋጋ የተቀበለው የመኪናውን ሙሉ ባለሀብትነት መብት ለተጠሪ ሊያስተላልፍለት እንደማይችልና መኪናውን ለሌላ ሰው አስቀድሞ የሸጠው መሆንን እያወቀ በመሆኑ የመኪናውን ዋጋ ብር 1,150.000 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሃምሳ ሺ ብር ) ከነሐሴ 8 ቀን 2006 ዓ/ም ከሚወልደው ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር በውሉ የተገለፀውን የገደብ መቀጫ ብር 5,000 (አምስት ሺ ብር ) እና አመልካች የሽያጭ ውሉን ባለመፈፀሙ ተጠሪ የደረሰበት ኪሳራ / ጉዳት / ካሳ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ተጣርቶ ቀርቦ ሊከፍል ይገባል በማለት በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2341 ንዑስ አንቀፅ 1 በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2356 ንዑስ አንቀፅ 1 በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2360 ንዑስ አንቀጽ 2 እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2364 ንዑስ አንቀፅ 21 መሰረት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

3. አመልካች ለተጠሪ የሸጠውን ሌላውን አንድ መኪና በሽያጭ ውሉ መሰረት ያልፈፀመው በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1793 /ለ/ በተደነገገው መሰረት በፍርድ ቤት የዕግድ ትዕዛዝ በመከልከሉ ምክንያት በመሆኑ የመኪናውን ዋጋ ብር ,150.000 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሃምሳ ሺ ብር ) ከነሐሴ 8 ቀን 2006 ዓ/ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር የመመለስ ግዴታ አለበት በማለት በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1793 /ለ / እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2356 ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት ወስነናል፡፡ ይህንን መኪና ለተጠሪ ባለማስረከቡ አመልካች ለተጠሪ ኪሳራ /ካሣ/ የመክፈል ኃላፊነት የለበትም በማለት ወስነናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ ፡፡
5. በዚህ ፍርድ ብት ጥቅምት 3 ቀን 2008 ዓ/ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ. 120150

ታህሳስ 5 ቀን2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሀመድ

ተኽሊት ይመሰል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች:- አሌ ኢንተርናሺናል ቢዝነስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር-

ጠበቃ አቶ ደሱ ጩመዳ ቀረቡ

ተጠሪ:- ፋርም አፍሪካ የኢትዮጵያ ፕሮግራም - ጠበቃ አቶ ሀይሉ ቡራዩ ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ውልን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁን አመልካች የሥር ከሳሽ ሲሆን በአሁን ተጠሪ የሥርተከሳሽ ላይ ባቀረቡት ክስ ከሳሽ በደቡብ ኦሞ ዞን ሀመር ወረዳ ኩሬ ለመገንባት ተከሳሽ ደግሞ ለሥራው ቫትን ጨምሮ ብር 1,850,798.50 /አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ሃምሳ ሺህ ሰባት መቶ ዘጠና ስምንት ብር ከሃምሳ ሳንቲም/ ለመክፈል ተስማምተን እኔ በውሉ መሰረት ሠርቻለሁ ከጉድጓዱየወጣውንም አፈር በውሉ ላይ በተቀመጠው 30 ሜትር ርቀት ላይ 140 ሜትር በመጨመር 170 ሜትር ርቀት አጓጉዤ ደፍቻለሁ ተከሳሽ ግን በውሉ መሰረት መክፈል ያለበትን ገንዘብና ተጨማሪ የአፈር ማጓጓዝ ስራ የተሰራበትን ገንዘብ ለመክፈል ፈቃደኛ አልሆነም በመሆኑም ተከሳሽለውሉ ማስፈጸሚያ በቅድሚያ የተከፈለው ቀብድ ብር 555,239.35 /አምስት መቶ ሃምሳ አምስት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ብር ከሰላሳ አምስት ሳንቲም/ ተቀንሶ ቀሪውን ብር 1,295,558.95 /አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ዘጠና አምስት ሺህ አምስት መቶ ሃምሳ ስምንት ብር ከዘጠና አምስት ሳንቲም/ መክፈል ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ከሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፈልና ተጨማሪ የአፈር ማጓጓዝና መድፋት ስራ ለሰራሁበት ቫትን ጨምሮ ብር 994,450.00 /ዘጠኝ መቶ ዘጠና አራት ሺህ አራት

መቶ ሃምሳ ብር/በድምሩ ብር 2,290,308.95 /ሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ ዘጠና ሺህ ሶስት መቶ ስምንት ብር ከዘጠናአምስት ሳንቲም/እንዲከፍለኝና ወጪና ኪሳራም የመጠየቅ መብቴ ይጠበቅልኝ የሚል ዳኝነት ጠይቀዋል ፡፡

ተከሳሽም በወኪሉ አማካኝነት በሠጠው መልስ ከከሳሽ ጋር የተባለውን ውል ፈፅመናል በውሉም መሠረት ከሣሽከተከሳሽ በሚሰጠው የስራ ዝርዝር መሰረት የኩሬውን ጉድጎድ በ2.29 ሜትር ጥልቀት ለመቆፈር እና የወጣውንም አፈር በ30 ሜትር ርቀት አንገዞ ለመድፋት ይህንንም ሥራ በ20 ቀን ውስጥ ለማጠናቀቅ ተከሳሽ ደግሞ ብር 1,850,798.50 /አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ሃምሳ ሺህ ሰባት መቶ ዘጠና ስምንት ብር ከሃምሳ ሳንቲም / ለመክፈል ተስማምተናል ፡፡ከሳሽግን የቆፈረው ኩሬ 2.20 ሜትር ሳይሆን 1.92 ሜትር ነው ስራውንም አጠናቆ ማረጋገጫ አቅርቦ አላስረከበም ከሳይት እንዲወጣም በተከሳሽ ትዕዛዝ አልተሰጠውም ከቁፋሮው የሚወጣውንም አፈር ከሳሽ እንዲደፋ የተስማማነው በ30 ሜትር ውስጥ ብቻ ነው ፡፡ ከስምምነታችን ውጪ ለተሠራ ስራ ልከፍል አይገባም ካሳሽ ሥራውን በውሉ ላይ ከተቀመጠው በላይ በማዘግየቱ የሚጣልበት የውል ቅጣት ተቀናሽ መሆን አለበት በአጠቃላይ ክሱ ውድቅ ተደርጎ ወጪና ኪሳራ የመጠየቅ መብቴ ይጠበቅልኝ የሚል ነው፡፡

ፍ/ቤቱም ግራቀኙን ካከራከረ በኂላ የጊዜ መራዘሙን ከሳሽ በአካባቢው የአየር ንብረት ችግር ምክንያት የሥራው መጠናቀቂያ ጊዜ ለ15 ቀን እንዲራዘም ህዳር 4 /2005 ዓ.ም ለተከሳሽ የፃፈው ደብዳቤ ቀርቧል፡፡ሆኖም ግን ተከሳሽ መልስ ያልሰጠ ቢሆንም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1684 እና 1722 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ አንደኛው ተዋዋይ ወገን ለሌላው ወገን በጽሁፍ የሚያቀርበው የውል ማሻሻያ ሀሳብ ሌላኛው ወገን ምክንያታዊ በሆነጊዜ ውስጥ መልስ ያልሰጠ ከሆነ በዝምታ ውሉን መቀበል መሆኑ መረዳት የሚቻል በመሆኑ ከሳሽ በፅሁፍ ላቀረበው የውል ማሻሻያ ተከሳሽ ዝም ማለቱ ውሉ በ15 ቀን መራዘሙን የሚያስከትል በመሆኑ ተከሳሽ የጠየቀውን ሥራው ለዘገየበት የሚከፈል ቅጣት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ነገር ግን ውሉ የቁፋሮ ጉድጎድ ጥልቀት 2.20 ሜትር ሲሆን ከሳሽ የቆፈረው 1.92 ሜትር በመሆኑ 0.28 ሜትር ጉድለት ስላለ የዚህ ጉድለት የገንዘብ መጠን 111,840.90 /አንድ መቶ አስራ አንድ ሺህ ስምንት መቶ አርባ ብር ከዘጠና ሳንቲም/ እና የቅድሚያ ክፍያ የተከፈለ ብር 555,239.35 /አምስት መቶ ሃምሳ አምስት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ ዘጠኝ ከሰላሳ አምስት ሳንቲም/ ተቀንሶ ቀሪው ብር1,054,069.45 /አንድ ሚሊዮን ሃምሳ አራት ሺህ ስልሳ ዘጠኝ ብር ከአርባ አምስት ሳንቲም/ቫትን ጨምሮ ተከሳሽለተከሳሽ ይክፈለው በማለት ሲወስን ወለዱን በተመለከተ ለውሉ በአግባቡ ላለመፈፀምየተከሳሽ በአግባቡ የውል ግዴታውን ያለመወጣት አስተዋፅኦ አድርጓል በማለት የወለድ ይከፈለኝ ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ ሲወስን የተጨማሪ ስራን ማለትም በግራ ቀኙ ውል ላይ የተቀመጠውን አፈሩን በ30 ሜትር ርቀት አንገዞ ለመድፋት ሲሆን ከሳሽ በ170

ሜትር ርቀት ነው አንጉገኔ የደፋሁት ለዚህም የውል ማሻሻያ በፅሁፍ አድርጌ ለተከሳሽ ሰጥቻለሁ ሲል ተከሳሽም ይኸው የውል ማሻሻያ በፅሁፍ የደረሰው ለመሆኑ ካለመካዱም በተጨማሪ በ23/5/2005 ዓ.ም ከፃፈው ደብዳቤ መረዳት ተችሏል፡፡በተጨማሪም ይህንን የውል ማሻሻያ ሀሳብ አልቀበልም በማለት መቃወሙን ተከሳሽ አልገለፀም ወይም አላስረዳም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1684,1722,2625 መሠረት የማሻሻያውን ውልተከሳሽ ሳይቃወም ዝም ማለቱ ውሉን መቀበሉን ያሳያል፡፡ዋጋውን በተመለከተ በዋናው ውል ከነበረው ለሜትር ኪዩብ 25 ብር ወደ 75 ብር ከፍ ብሏል ቢልም በውል ማሻሻያው ላይ አልተገለፀም በማለት ውሉ ላይ በተቀመጠው ዋጋ መሠረት የተጨማሪው 140 ሜትር ርቀት ብር 994,450.00 /ዘጠኝ መቶ ዘጠና አራት ሺህ አራት መቶ ሃምሳ ብር/ ተከሳሽለከሳሽ ሊከፍል ይገባል በማለት በአጠቃላይዋናውን ገንዘብ ብር1,054,069.45 /አንድ ሚሊዮን ሃምሳ አራት ሺህ ስልሳ ዘጠኝ ብር ከአርባ አምስት ሳንቲም/ ፍርድ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ 9% ህጋዊ ወለድጋር ተከሳሽለከሳሽእንዲከፍል ሲወሰን የተጨማሪ ስራን በተመለከተ ብር994,450.00 /ዘጠኝ መቶ ዘጠና አራት ሺህ አራት መቶ ሃምሳ ብር/ ቫትን ጨምሮ ተከሳሽለከሳሽ ይክፈል በማለት ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁን ተጠሪ የይግባኝ ቅሬታውን ለፌደራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን የፌደራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ቅሬታው መልስ ሰጪን ያስጠራል በማለት መልስ ሰጪን አስጠርቶ ካከራከረ በኋላ ዋናው ውል ላይ የተጠየቀው ዳኝነት ላይ በተሰጠው ውሳኔ የቀረበውን የይግባኝ ቅሬታ ውድቅ በማድረግ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሳኔ በማፅናት ሲወስን፤ ተሠራ የተባለውን ተጨማሪ ስራን በተመለከተ አፈሩን ወስዶ ለመድፋት ግራ ቀኙ በ30 ሜትር የተስማሙ ሲሆን ይግባኝ ባይ ይህ ውል ቢኖርም በ30 ሜትር ርቀት ለመድፋት ቦታው ምቹ ባለመሆኑ በ170 ሜትር ርቀት ላይ ደፍቻለሁ ይህንንም ለፕሮጀክቱ ስራ አስኪያጅ አሳውቄበዚሁ እንድቀጥል በተሰጠኝ ትእዛዝመሰረት ነው በማለትየገለፀ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ በግራ ቀኙ መሀከል የተደረገው ውል የፅሁፍ እስከሆነ ድረስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1722 መሠረት የውል ማሻሻያም ሲደረግ በፅሁፍ መደረግ ነበረበት በጽሁፍ ባለመደረጉ ምክንያት ለማሻሻያ ውል የተጠየቀው የዳኝነት ገንዘብ መጠን ሊከፈል የሚገባ አይደለም በማለት የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሠኘት የአሁን የሰበር አቤቱታ አቅራቢ ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሠበር ሠሚ ችሎት የሠበር አቤቱታውን ያቀረበ ሲሆን የሠበር አጣሪ ችሎቱም ቅሬታውን ከስር መዝገብ ጋር መርምሮ ተጨማሪውን ሥራ በተመለከተ በግራቀኙ መሀከል የተደረገ ውል የለም በሚል መነሻነት የተጨማሪ ስራ ክፍያ ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍል አይገባም በማለት የተወሰነበትን አግባብነት ተጠሪ ባለበት ለማጣራት ያስችል ዘንድ ተጠሪ ቀርቦ መልስ ይስጥበት ብሏል፡፡

ተጠሪም የሰበር አጣሪው ችሎት ከያዘው ጭብጥ አንፃር የሰጠው መልስ በውሉ ከተመለከተው አፈር መድፊያ ቦታ ማለትም 30 ሜትር ወደ 170 ሜትር በመጨመር መደፋቱ ከተሰጠው የስራ ትእዛዝ ውጪ ነው፡፡በመሆኑም ተጠሪ ተጠያቂ የሚሆንበት ምክንያት የለም ፡፡ በተጨማሪም ከውል ውጪ የሆነ ግዴታን ለማካተት አንደኛው ወገን ደብዳቤ መፃፍ ብቻውን ሌላኛው ወገን ተዋዋይ እንደተስማማ አያስቆጥረውም በማለት በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1682 ሥር ተደንግጓል በመሆኑም የተጨማሪ ስራ ክፍያን አስመልክቶ የሥር ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሳኔ ይፅናልኝ ብሏል፡፡

እኛም የቀረበውን የሰበር አቤቱታ በሰበር ችሎት ከተያዘው ጭብጥ አንፃር መርምረነዋል፡፡እንደመረመርነውም ለሠበር ከቀረበው አቤቱታ ውስጥ የተጨማሪ ስራ ክፍያ ሊከፈል ይገባል በማለት በሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሠጠው ውሳኔ በሥር ጠቅላይ ፍ/ቤት መሻሩ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን በተመለከተ የሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ሊከፍል ይገባል በማለት የወሰነው  የማሻሻያው ውል በፅሁፍ ተደርጎ ለተጠሪ እንዲደርስ መደረጉንና ተጠሪም ሳይቃወም ዝም ማለቱን ከግራ ቀኙ ክርክርና ማስረጃ ተረጋግጧል በሚልና በፅሁፍ በተደረገ ውል ላይ አንደኛው ወገን ውሉን ማሻሻል ሲያስፈልገው በፅሁፍ ሌላኛው ወገን ሊያሳውቀው እንደሚገባ  ሌላኛው ወገን የማይስማማበት ከሆነ ተቃውሞውን መግለፅ አለበት ነገር ግን በበቂ ምክንያታዊ ጊዜ የማሻሻያ ውል በፅሁፍ የደረሰው ተዋዋይ መልስ ሳይሰጥ ዝም ቢል በፍ/ብ/ሕ/ቁ1684፣1722 እና 2625ን በመጥቀስ የማሻሻያ ውልን እንደተቀበለ ይቆጠራል በሚል ሲሆን የስር ጠ/ፍ/ቤት ይህንን ውሳኔ የሻረው በግራ ቀኙ መሀከል የተፈፀመው የመጀመሪያ ውል በፅሁፍ እስከተደረገ ጊዜ ድረስ ማሻሻያው ውልም በፅሁፍ መደረግ እንዳለበት በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1722 ሥር ተደንግጎ እያለአመልካች ተጨማሪ ስራ ሰርቻለሁ ያለው በፕሮጀክቱ ስራ አስኪያጅ በተሰጠኝ ትእዛዝ ነው ማለቱ የስራ ትእዛዞቹ በፅሁፍ ባልተሰጠበት ሁኔታ የተሻሻለ ውል አለ ለማለትአይቻልም በሚል ነው፡፡

በመሠረቱ በፅሁፍ የተደረጉ ውሎች አንደኛው ወገን ውሉን ለማሻሻል ሲፈልግ ዋናው ውል በተፈፀመበት አይነት ማለትም ዋናው ውል በፅሁፍ እስከተደረገ ድረስ በፅሁፍ ሊደረግ እንደሚገባ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1722  ሥር ተደንግጎ ይገኛል ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች የተጨማሪ ስራ ውልን ለማድረግ የፅሁፍ ውል ለተጠሪ መስጠቱን ተጠሪም ያምናል፡፡ነገር ግን የፕሮጀክት ስራ አስኪያጅ የተጨማሪ ስራ ትእዛዝ ለመስጠት ስልጣን የለውም ከሚለው ስንነሳ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2625  ሥር እንደተመለከተው በፅሁፍ በተደረገ ውል ላይ አንደኛው ወገን የውል ማሻሻያ ፅሁፍ ለሌላኛው ወገን ሲልክለት ሌላኛው ወገን ሊቀበለው እንደሚችል ሲደነግግ ውሉን ለመቀበሉ ግን የተለየ ስርአት ካለማስቀመጡ በተጨማሪ በምክንያታዊ ጊዜ ውሉን ያለመቀበሉን ካላስታወቀ ውሉን እንደተቀበለ እንደሚቆጠር ደንግጓል፡፡በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ፅ/ቤት በፅሁፍ የተደረገው ውል ማሻሻያ ሲደርሰው በቂ በተባለ ጊዜ አይሆንም የሚልበትን ምክንያት መግለፅ

ይጠበቅበታል ነገር ግን በቂ በሆነ ጊዜ ውል ሊሻሻል የማይችልበትን ምክንያት ካለመግለፁም በተጨማሪ በፐሮጀክት ስራ አስኪያጅ በተሻሻለው ውል መሠረት ይፈፅም በማለት የቃል ትዕዛዝ መስጠቱን ተጠሪ ፅ/ቤት ከማመኑም በተጨማሪ ተጨማሪ ስራው አልተሰራም በማለት ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ፕሮጀክት ስራ አስኪያጁ ትእዛዝ መስጠት አይችልም ካለ የማሻሻያው ውል በደረሰው ጊዜ ተቃውሞ ማቅረብ ሲገባው አላቀረበም፡፡ፕሮጀክት ስራ አስኪያጁ ተጨማሪ ትእዛዝ ባይሰጥም እንኳን የተጠሪ የፅሁፍ ማሻሻያ ውል ሲደርሰው ዝም ማለት ተጨማሪ ውሉን እንደተቀበለው ያስቆጥራል፡፡ በአመልካች በኩል ሲታይ ደግሞ ላቀረበው ተጨማሪ ማሻሻያ ውል የፐሮጀክት ስራ አስኪያጅ እንዲቀጥል ካዘዘው ውሉ ለመሻሻሉ ምንም ተጨማሪ ማረጋገጫ አስፈላጊ አይሆንም ከዚህ ሁሉ መነሻ ሲደረግ የተሻሻለ ውል አለ በተሻሻለው ውል መሰረት አመልካች ሊሰራ ይችላልና ስራውን ሰርቶታል መስራቱም ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ አመልካች ተጨማሪ ስራውን መስራቱ እስከተረጋገጠና የሰራውም በህግ አግባብ እስከሆነ ድረስ ለሰራው ስራ ክፍያ የማይፈጸምበት ምንም ምክንያት አይኖርም፡፡ ከዚህ ሁሉ ስንነሳ የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተጨማሪ ስራውን ክፍያ ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍል ይገባል በማለት ሲወስን የስር ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተጨማሪ ስራ ክፍያን ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍል አይገባም በማለት የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የስር ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁ.109882 በቀን 26/02/2008 ዓ.ም አመልካች ለተጠሪለተጨማሪስራ ክፍያ ብር 994.750.00(ዘጠኝ መቶ ዘጠና አራት ሺህ ሰባት መቶ ሀምሳ ብር) ሊከፍል ይገባልበማለት የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁ 130572 በቀን 28/4/2007 ዓ.ም የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ /ሥ/ሥ/ህግ ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁ.130572 በቀን 28/4/2007 ዓ.ም አመልካች ለተጠሪብር 994.750.00(ዘጠኝ መቶ ዘጠና አራት ሺህ ሰባት መቶ ሀምሳ ብር)ለተጨማሪ ስራ ሊከፍል ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ /ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
3. የስር ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁ.109882 በቀን26/2/2008 ዓ.ም ዋናውን ገንዘብብር 1.054 069.45 (አንድ ሚሊዮን ሀምሳ አራት ሺኅ ስልሳ ዘጠኝ ብር ከአርባ አምስት ሳንቲም) ፍርድ ካረፈበት ቀን ከሚታሰብ 9 ፐርሰንት ወለድ ጋር አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁ.130572 በቀን

28/4/2007ዓ.ምየሰጠውን ውሳኔ በማጽናት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ /ሥ/ሥ/ህግ ቁ. 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡

4. ለዚህ ፍርድ ቤት ክርክር ግራ ቀኙ ያወጡትን ወጪ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

## ት እ ዛ ዝ

የውሳኔው ግልባጭ በየደረጃው ለሚገኙ ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ፡፡

መዝገቡ በውሳኔ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይተላለፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

የሰ/መ/ቁ. 109194

ታህሳስ 25 ቀን 2005 ዓ/ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጸውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- የጎንደር ከተማ አስተዳደር አገልግሎት ጽ/ቤት ዐቃቤ ህግ ወ/ሮአይናዲስ አሰጋህኝ ቀርባለች

ተጠሪ፡- እስማኤል አህመድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር-ጠበቃ አቶ ወንድሜነህ ዳኛው ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ ያለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው የጎንደር ከተማ አስተዳደር የከተማ ነክ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 00768 በቀን 09/08/2006 ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁን ተጠሪ ይግባኝ ለጎንደር ከተማ አስተዳደር የከተማ ነክ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ያቀረበውን አከራክሮ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር በመ/ቁጥር 00943 በቀን 25/10/2006 ዓ/ም ሲወስን፣ የአሁን አመልካች ውሳኔውን ለማስለወጥ ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ አቅርቦ ለሰበር ሰሚ ችሎት የሚያስቀርብ ሆኖ አልተገኘም በማለት የሰበር አጣሪ በሰ/አ/መ/ቁ 42200 ታህሳስ 8 ቀን 2007 ዓ/ም መዝገቡን በመዝጋቱ ነው፡፡

የአሁን ተጠሪ የስር ፍርድ ቤት ከሳሽ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበረ፡፡ የክሱ ይዘትም፡- ተጠሪ በጎንደር ከተማ ቀበሌ 06 ክልል የቤት ቁጥር 18፣19፣20 እና 22 ያሉትን የመንግስት ቤቶች ተከራይቶ ለበርካታ ዓመታት ሲገለገል መቆየቱን፡ ቤቶቹን በመንግሥት ፖሊሲ መሰረት በሊዝ ገዝቶ ለማልማት እንደሚፈልግ ለተከሳሽ ጽ/ቤት ጥያቄ ማቅረቡን፣ ጥያቄውን ጽ/ቤቱ ለኪቢአድ አቅርቦ መ/ቤቱም ጥያቄያውን ተቀብሎ በባለሙያ ተገምቶ እንዲቀርብ ማድረጉን፣ግምቱ ለኪቢአድ

እንዲከፈል ተከሳሽ ጽ/ቤት በቁጥር 1762/765/2001 በቀን 7/9/2001 ዓ/ም በጻፈለት ደብዳቤ መሠረት ብር 292.235.35 (ሁለት መቶ ዘጠና ሁለት ሺህ ሁለት መቶ ሰላሳ አምስት ብር ከሰላሳ አምስት ሳንቲም) ገቢ አድረጎ ቅድመ ክፍያ ብር 89.614.80 (ሰማኒያ ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ አስራ አራት ብር ከሰማኒያ ሳንቲም) ለተከሳሽ /ለአመልካች/ ጽ/ቤት ገቢ ማድረጉን፣ የሊዝ ውል ፈርሞ 746.79 /ሰባት መቶ አርባ ስድስት ከሰባ ዘጠኝ/ ካ.ሜትር በካርታ ቁጥር 7339/02 በሆነው የሊዝ ይዞታ ቦታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መሰጠቱን፣ ወደ ግንባታ ለመግባት የግንባታ ፈቃድ ተጠይቆ ሊሰጠው ስላልቻለ ለሥራና ከተማ ልማት ቢሮ በቀረበው አቤቱታ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮው በሰጠው የተስተካከለ ሳይት ፕላንና ትዕዛዛዊ ደብዳቤ መሠረት በህግ አስገዳጅነት የግንባታ ፈቃድ ተሰጥቶት ወደ ግንባታ እንዲገባ እንዲወሰን ሲል ጠይቋል፡፡

አሁን አመልካች (የሥር ተከሳሽ) ክሱ ደርሶት በድርድር እንጨርሳለን ብሎ ከሄደ በኃላ በቀጠሮ ቀን ባለመቅረቡ መልስም ባለመስጠቱ ክርክሩ በሌለበት ቀጥሎ እያለ በመቅረቡ በቀን 4/6/2003 ዓ/ም በዋለው ችሎት ግራ ቀኙ የቃል ክርክር ማድረጋቸውን፣ አመልካች /ተከሳሽ/ በቃል ክርክሩ ወቅት ለከሳሽ /ለተጠሪ/ የተሰጠው ካርታ የተሰረዘ መሆኑን በቀን 18/5/2003 ዓ/ም በተጻፈ ዳብዳቤ ትዕዛዝ የተሰጠ መሆኑን፣ ለከሳሽ /ለተጠሪ/ በቀን 25/5/2003 ዓ/ም ካርታው የተሰረዘ መሆኑን የተገለጸለት ስለሆነ በተሰረዘ ካርታ መብት አለኝ ብሎ ክስ ሊመሰርት አይገባም በማለት በቀረበው መቃወሚያ መሠረት መቃወሚያው ተመርምሮ ብይን ተሰጥቶ ነበር፡፡

የአሁን ተጠሪ /የሥር ከሳሽም/ በብይኑ ላይ ቅር በመሰኘት እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ተከራክሮ ስለጸናበት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ ችሎቱም የግራ ቀኙን አከራክሮ በሰ/መ/ቁ. 87247 በቀን 22/01/2006 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሥር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመሻር የሥር ፍርድ ቤት ወደ ክርክሩ በመግባት ጉዳዩን ከሚከተሉት ነጥቦች አንጻር አጣርቶ እንዲወስን ፡-

1. ስለ አስተዳደር መሥሪያ ቤት ውሎች በፍትሐብሔር ህጉ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች፣
2. ከሊዝ አዋጁ፣ ከክልሉ የሊዝ ደንብ፣ በግራ ቀኙ መካከል ከተቋቋመው የሊዝ ውል እና ለተጠሪው በህግ ከተሰጠው ሥልጣን አንጻር ክርክሩን ቀጥሎ በማየት እና በማጣራት ተገቢውን ውሳኔ ይሰጥበት ዘንድ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 341/1/ መሰረት መልሷል፡፡

ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በተሠጠው ትዕዛዝ መሠረት መዝገቡ ተንቀሳቅሶ የግራ ቀኙ በጉዳዩ ላይ ክርክራቸውን አድርገዋል፡፡ የጎንደር ከተማ አስተዳደር የከተማ ነክ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የከሳሽ ከርታ የተሰረዘው በአግባቡ ነው ወይስ

አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ፣ የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃዎቻቸውን መርምሮ በውሳኔው ላይ የሚከተሉትን ነጥቦችን ካነሳ በኃላ ፍርዱን የደመደመ ሲሆን እነዚህም ነጥቦች፡-

1. በወቅቱ ሥራ ላይ የነበረው የሊዝ አዋጅ ቁጥር 272/94 አንቀጽ 15 ላይ የተቀመጠው ድንጋጌ የሚያስረዳው የሊዝ ይዞታ መቋረጥና የካሳ አከፋፈል በተመለከተ ተደንግጎ የሚገኝ ሲሆን ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የወጣው ደንብ ቁጥር 6/94 አንቀጽ 4 (4) ደግሞ የከተማ ቦታን በሊዝ ስለ መፍቀድ ሲሆን፣ በማናቸውም አግባብ በሊዝ የሚሰጥ የከተማ ቦታ ለውል ገቢው ለማስረከብ ዝግጁ የሆነ መሆን ይኖርበታል ሲል ይደነግጋል፡፡
2. እንዲሁም የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 3180 ላይ የተቀመጠው ተዋዋይ ጥፋት ባይኖርበትም የአስተዳደር መ/ቤት ውሉን ሊያፈርስ ይችላል፡፡ ይህም ውሉ ለህዝባዊ አገልግሎት የሚጠቅም ሳይሆን ሲቀር ወይም ለፍላጎቱ የማይስማማ ሆኖ ሲገኝ ነው በሚል አስቀምጧል፡፡
3. በተጨማሪም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ//ቁ. 22719 በቀን 14/02/2000 ዓ/ም በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1195 መሠረት በአስተዳደር አካሉ የተሰጠው የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ ከተሰረዘ፣ የይዞታ ማረጋገጫ ማስረጃ ባለቤትነት የተረጋገጠ ማስረጃ ሳይኖረው ለክርክር መነሻ በሆኑ ቤቶች ላይ መብት እንዳለው የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሳያቀርብ ክስ ማቅረብ በህግ ተቀባይነት የለውም ሲል የሰጠው ውሳኔ ያስረዳል፡፡
4. ሌላው ከሳሽ እና ተከሳሹ ያደረጉት የሊዝ ውል ላይ የተገለጸው በሊዝ ውል ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ በሊዝ አዋጅ ቁጥር 272/94 እና ደንብ ቁጥር 6/94 የተደነገጉትንና በውል ህግ መሠረት ተፈጻሚነት ያለው ነው ሲሉ የተስማሙበት መሆኑን በሊዝ ውል አንቀጽ 8 እና 9 ላይ ተቀምጧል፡፡

ስለዚህ እነዚህ ድንጋጌዎች ሲታዩ በሥር ከሳሽ /በአሁን ተጠሪ/ እና በሥር ተከሳሽ/ በአሁን አመልካች/ መካከል የተደረገው የሊዝ ውል የተሰረዘው በአግባቡ ነው ሲል ወስኗል፡፡

የአሁን ተጠሪ በውሳኔው ቅር ተሰኝቶ ይግባኝ ለጎንደር ከተማ አስተዳደር የከተማ ነክ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርቦ የግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር ተጠሪ በሊዝ ውሉ መሠረት የመጠቀም መብት አለው፣ የሊዝ ውሉ ሊሰረዝ አይገባም፣ ተጠሪ ዳኝነት የጠየቀውን የግንባታ ፍቃድ አመልካች ይስጥ በማለት ወስኗል፡፡

የአሁን አመልካች ይህን ውሳኔ ቅር በመሰኘት አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን የሰበር አጣሪ ቅሬታው ለሰበር ችሎት የሚያስቀርብ ሆኖ አልተገኘም ሲል መዝገቡን ዘግቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የከተማ ነክ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አጣሪ የሰጠውን ትዕዛዝ ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች በቀን 13/05/2007 ዓ/ም የተጻፈ ዝርዝር ቅሬታ ነጥቦችን አቅርቧል፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ ለሰበር እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ሐምሌ 24 ቀን 2007 ዓ/ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ እንደተመዘገው ሲሆን ጉዳዩን ከሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ፣ በዚህ ችሎት ከተደረገው ክርክር እንዲሁም አጣሪው ያስቀርባል ሲል ከያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነውም ይህ ጉዳይ ቀደም ሲል እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ቀርቦ የነበረና ድጋሚ ታይቶና ተጣርቶ እንዲወሰን የሚጣሩ ነጥቦች ተይዘው የተመለሰ ነው፡፡ ጉዳዩ ወደ ሥር ፍርድ ቤት ከተመለሰ በኃላ የግራ ቀኙ ክርክር ማድረጋቸውን፣ የጎንደር ከተማ አስተዳደር የከተማ ነክ ጉዳዮች የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኙ የቀረቡለትን የሰነድ ማስረጃዎችን የተመለከተ መሆኑን፤ የተነሱትን ፍሬ ነገሮችን ከሊዝ አዋጅ ቁጥር 272/94፣ ከደንብ ቁጥር 6/94፣ አግባብነት ካለው የፍትሐብሔር ህግ ድንጋጌ እና በግራ ቀኙ መካከል ከተደረገው የሊዝ ውል አንጻር ተመልክቶ ውሳኔ የሰጠ መሆኑን የውሳኔ ግልባጭ ያስረዳል፡፡ ይህ ውሳኔ ግን የሊዝ አዋጅ ቁጥር 272/94 አንቀጽ 15/1/ ድንጋጌን ያገናዘበ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ሊጤን ይገባል፡፡

በቀድሞው የሊዝ አዋጅ ቁጥር 272/94 አንቀጽ 15/1/ ሥር የሊዝ ውል ሊቋረጥ እና ሊፈርስ የሚችልባቸው ምክንያቶች በሊዝ የተያዘው ቦታ በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ጥቅም ላይ ሳያውለው ሲቀር፣ ቦታው ለህዝብ ጥቅም ተብሎ ለሌላ አገልግሎት ሲፈለግ እና የሊዝ ዘመኑ ሲያልቅ እንደሆነ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በዚህ ድንጋጌ ሥር የሊዝ ውል እንዲፈርስ ለማድረግ በድንጋጌው ሥር ከተቀመጡት ከሶስቱ መሰረታዊ ነገሮች ውስጥ በውል ተቀባዩ በኩል ሳይፈጸም የቀረ ስለመኖሩ ውሉ እንዲፈርስ የሚጠይቀው ወገን የማስረዳት ሸክም ይኖርበታል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የአሁን አመልካች የሊዝ ውሉ ተሰርዟል ከማለት ውጭ በሊዝ አዋጁ አንቀጽ 15/1/ ከተደነገጉት ውስጥ በተጠሪ በኩል ሊፈጸሙ የሚገባቸው ነገሮች ሳይፈጸሙ ስለመቅረታቸው ወይም ክርክር የተነሳበት ቦታ ለህዝብ ጥቅም ስለመፈለጉ በፍጹም አላስረዳም፡፡ የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት በዚህ ህግ አግባብ መሠረት በአግባቡ ሳይመረምር የይዞታ ማረጋገጫ ካርታው መሠረዙ እና ግንባታ ፈቃድ መከልከሉ ተገቢ ነው በሚል ውሳኔ መስጠቱ ተገቢነት የለውም፡፡ አመልካችም የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ሲል የሚከራከረው ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ እንዲሁም አመልካች የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በፍትሐብሔር ህግ ስለ አስተዳደር መ/ቤት ውሎች የተደነገጉትን ድንጋጌዎችን በአግባቡ ሳይመለከት የሊዝ አዋጁን ብቻ መሠረት በማድረግ የሰጠው ውሳኔ አግባብነት የለውም በማለት ለዚህ ችሎት ያቀረበው ቅሬታ ህጋዊ መሠረት ያለው አይደለም፡፡ ምክንያቱም የሊዝ አዋጅ ቁጥር 272/94 እየታየ ላለው

ጉዳይ እጅጉን አግባብነት ያለውና ልዩ ህግ በመሆኑ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይህን አዋጅ አንቀጽ 15/1 እና ደንቡን አያይዞ ከመተርጎሙም ባሻገር የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 3181 የተረጎመበትም መንገድ ሲታይ የሚነቀፍ አይደለም፡፡

በአጠቃላይ የጎንደር ከተማ አስተዳደር የከተማ ነክ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር አግባብነት ከላቸው ህጎች አንጻር ተመልክቶ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር የሊዝ ውሉ ሊፈርስ አይገባም፣ የተጠሪ መብት ሊጠበቅ ይገባል፣አመልካችም የግንባታ ፍቃድ ለተጠሪ እንዲሰጥ ሲል የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍበት ህጋዊ ምክንያት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ አጣሪም የአመልካችን የሰበር አቤቱታውን መሠረዙ ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የጎንደር ከተማ አስተዳደር የከተማ ነክ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለም፡፡ ሲጠቃለልም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. ጎንደር ከተማ አስተዳደር የከተማ ነክ ጉዳዮች ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 00943 በቀን 25/10/2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/አ/መ/ቁ. 42200 ታህሳስ 8 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. አመልካች በአዋጅ ቁጥር 272/94 አንቀጽ 15/1/ ሥር የተደነገጉትን ድንጋጌዎችን ተጠሪ ስለመጣሱ ባለማስረዳቱ እንዲሁም ክርክር የተነሳበት ቦታ ለህዝብ ጥቅም ተፈልጎ ስለመሆኑ ባለማረጋገጡ ምክንያት የሊዝ ውሉ ሊፈርስ አይገባም ብለናል፡፡
3. አመልካች ተጠሪ ዳኝነት የጠየቀውን የግንባታ ፍቃድ የጎንደር ከተማ አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በወሰነው መሠረት ሊሰጥ ይገባል ብለናል፡፡
4. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
5. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይላክ፡፤

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ተ

የሰ/መ/ቁ. 114398

ታህሳስ 25 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች ፡- አሊ መሃመድ

ተኽሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ ደስታ ኪዳነ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አመቴ ኤርታቦ ጉዳዩ ተከታታይ ልጣንጋ ኤርትቦ ቀረቡ

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት ሽያጭ ውል ክርክር ሲሆን የተጀመርው በደ/ብ/ብ/ሕ/ ሀድያ ዞን ሆሳዕና ከተማ ስተዳደር የመጀመርያ ደረጃ ፍ/ቤት ቤት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡አመልካች በስር የክልል ጥቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰበር ሰሚ ችሎት ተፈፀመ ያሉትን የህግ ስህተት ተጣርቶ እንዲወሰን የቀረበ ጉዳይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች የስር ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ይዘት ባጭሩ ከአሁኗ አመልካች ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል ህግን ያልተከተለ ውል ለመዋዋል ህጋዊ ችሎታ እንደሌላቸው ዕድሜያቸው 70 አመት እንደሆነ እንዲሁም በልብ እና በነርቭ ህመም እንደሚሰቃዩ በመግለፅ ከአመልካች ጋር የተደረገው ውል መብት እና ጥቅማቸው የጎዳ በመሆኑ እንዲፈርስላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አመልካች ባቀረቡት መልስም ተጠሪ ቤቱን ፈቅደው እንደሸጡት ልጅ አለመኖር ፣በበሽታ የተጠቁ መሆናቸው ውሉ ለማፍረስ ምክንያት እንድማይሆን፣ቤቱ በእማኞች ፊት እንደገዙት አመልካች በገንዘባቸው እንዲጦሩዋቸው ተስማምተዋል የተባለው ውሉ ለማፍረስ ምክንያት እንደማይሆን የስም ዝውውር በማዘጋጃ ቤት ተደርጎ ለተለያዩ ወጪዎች 250000 ከፍለው ቤቱን ማልማት እንደጀመሩ በመግለፅ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ውድቅ እንዲሆን አመልክቷል፡፡

የስር ፍ/ቤትም የግራቀኙ ክርክርና ማስረጃ አጠቃላይ ይዘት ከመረመረ በኃላ የተጠሪ ምስክሮች ልጅ ይሁን ባል የሌላቸው ስለመሆኑ በአመልካች ቤቱ ሲያፈርሱ ቤቱም ዕቃውም አልሸጥኩም ሲሉ እንደነበር በሽተኛ እንደሆኑም በአንድ እጃቸው የያዙት ነገር የሚረሱ እና ከሚያግዛቸው ሰው የሚጨቃጨቁ መሆናቸውን እንዳስረዱ የአመልካች ምስክሮች በአንፃሩ ተጠሪ ቤት ለመሸጥ ይፈልጉ እንደነበር 1ኛ መከላከያ ምስክር በነባርነት እንደተገኙ የቤቱ ሽያጭም ዋጋ ብር 180000 በተጠሪ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ገቢ መደረጉ መግለፃቸውን ጠቅሶ በፍታብሔር ህጉ የዕድሜ ጣርያ ገደብ የሌለ መሆኑ በእድሜ መግፋት/መጃጀት/ ውል የሚፈርስበት ምክንያት መኖሩን፣አመልካች ያደረጉት የተንኮል ተግባር ባይኖርም የተጠሪ ዕድሜ ከ90 አመት በላይ በመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1710 ንኡስ አንቀፅ 2 መሰረት የተዋዋይን ዕድሜ መጃጀት እና በንግድ/ሽያጭ/ ግልፅ የሆነ የልምድ እርቀት የሌለ ከሆነ ውሉ ሊፈርስ እንደሚችል  መደንገጉን ፍ/ቤቱ ተጠሪ በማስቀረብ እንደተመለከታቸው ዕድሜያቸው እጅግ የገፋ እና ከእድሜ መግፋት ጋር የተያያዘ የሚታይ ባህርያት ያላቸው መሆኑን በማረጋገጡ የሽያጭ ውሉ ሊፈርስ እንደሚገባ አመልካች እና ተጠሪ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1815(1) መሰረት ወደነበሩበት እንዲመለሱ ሲል በፍርድ ሰጥቷል፡፡

የአመልካች የሥር መጀመሪያ ደረጃ ውሳኔ በመቃወም ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቤቱታ አቅርበው ፍ/ቤቱም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የቤት ሽያጭ ውል በህጉ አግባብ እንደተከናወነ ፣ ተጠሪ ቤት ለመሸጥ ሲፈልጉ እንደነበረ በአመልካች ምስክሮች መረጋገጡን፣ ተጠሪ የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ የፈለጉት የቤት ዋጋ በመጨመሩ ምክንያት እንደሆነ ፣ በተጠሪ ላይ ህመም መኖሩ፣ ልጅ አለመውለዳቸው ከውሉ ጋር ተያያዥነት እንደሌለው ተጠሪ አርጅቷል፣ ጃጅቷል የሚሉ የሥር ፍ/ቤት ትችት አላስፈላጊ ናቸው በማለት ውሳኔውን ሽሮ የሽያጭ ውሉ አይፈርስም ሲል ፍርድ ሰጥቷል፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በሥር ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍ/ቤትም በስር ፍ/ቤቶች የተደረገው አጠቃላይ የክርክር ይዘት ከመዘገበ በኃላ ተጠሪ ባላቸው አነስተኛ ማህበራዊ ተሳትፎ እና በማርጀታቸው ያወቁት የገበያ ዋጋ የማያውቁ መሆኑን ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በ 15/08/2007 ዓ/ም ተጠሪ አስቀርቦ ቃለ መጠይቅ ያደረግላቸው ሲሆን በተደረገላቸው ቃለመጠይቅም በእድመ መግፋታቸው ምክንያት የሚሰሩት ስራና የሚያደርሰው ውጤት ለመገንዘብ የማይችሉ መሆኑን የከፍተኛ ፍ/ቤት የቤት ዋጋ በመጨመሩ ነው፡፡ የውል ይፍረስልኝ ጥያቄ የቀረበው የሚለው ድምዳሜ ተገቢነት እንደሌለው የአሁኑ ተጠሪ በተሸጠው ቤት ላይ አንድ ክፍል እንዲሰጣቸው፣ለማስታመም የሚሉ ነገሮች ጧሪ እና ዘመድ እንደሌላቸው የሚያሳይ መሆኑን ፣ተጠሪ በድርድር ቤቱን በአግባቡ ይሸጣል ተብሎ ሊወሰድ እንደማይቻል ቤቱ ለመሸጥ ረዳት እና ደጋፊ ያስፈልጋቸው እንደነበር በመግፅ የዞኑ ክፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ ሽሮ የመጀመርያ ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔ አፅንቷል፡፡በአመልካች በኩል የሰበር አቤቱታ

ያቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስሕተት የለም በማለት የአመልካች አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ ያቀረበውም በስር ፍ/ቤቶች ተፈፅመ የተባለው ስህተት ለማሳረም ነው፡፡

አመልካች በሰበር አቤቱታቸው የሽያጭ ውሉ የማይፈርስበት ምክንያት በማለት ዘርዝረው ያቀረቡ ሲሆን ሲጠቃለል የሽያጭ ውሉ በህጉ አግባብ የተከናወነ በመሆኑ የሚፈርስበት አንዳችም በማስረጃ የተደገፈ ህጋዊ ምክንያት በሌለበት ውል ሊፈርስ ይገባኝ ተብሎ የተሰጠውን ውሳኔ እንዲሽር እና የሀድያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀና መጠየቃቸው የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪ ቤቱን ለመሸጥ እንደሚፈልጉ የሽያጭ ውሉ በእማኝ ፊት መከናወኑ የቤቱ ስመሀብትም በአመልካች ስም መዛወሩ በፍሬ ነገር ረገድ በተረጋገጠ ቤት ሁኔታ የተጠሪ እድሜ 97 ነው መባሉ እና የልብ ህመም እንዲሁም የነርቭ ህመም አለብኝ በማለታቸው ብቻ ይህ ስለመሆኑ አግባብ ባለው ባለሞያ የተረጋገጠ ነገር ሳይኖር በፍ/ብ/ህ/ቁ 1810(2) ውሉ ይፍረስ መባሉ ተጠሪ ባለበት ይጣራ ዘንድ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሏል፡፡ ተጠሪም ጥሪ ተደርጎላቸው ቀርበው በጠበቃቸው በኩል በሰጡት መልስ የስር ፍ/ቤት ውሉ ለማፍረስ በህመም ምክንያት አለማድረጉን ውሉ እንዲፈርስ መነሻ የተደረገው በፍ/ህ/ቁ 1710(2) በመሆኑ አጣሪ ችሎቱ የያዘው ጭብጥ ተገቢነት እንደሌለው ቤቱ ለመሸጥ የተገኘው ፍቃድ ከእድሜ መግፋት ጋር የተያያዘ እንደሆነ የእድሜ ምርመራ በስር ፍ/ቤት አለመቅረቡ ቤቱ በአፈፃጸም ተረክበው እየኖሩበት እንደሚገኙ በመግለፅ ውሳኔውን እንዲፀና አመልክቷል፡፡ አመልካች አቤቱታውን የሚያጠነክር የመልስ መልስ አቀርቧል፡፡

ከስር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ይዘት ያለውነው፡፡ይህ ችሎትም ግራቀኙ በፅሁፍ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሰኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በመገናዘብ የስር የክልሉ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ በሰጠው ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመ መሆን አለመሆኑ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ክርክሩ በሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች የቤት ሽያጭ ውሉ በህጉ አግባብ የተደረገ በመሆኑ የሚፈርስበት አንዳች ህጋዊ ምክንያት የለም በማለት የተከራከሩ ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው የሽያጭ ውሉ የተደረገው የፍቃድ ጉድለት ባለበት ሁኔታ በመሆኑ በስር የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት እንዲፈርስ የተሰጠው ውሳኔ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በፅናቱ የሚነቀፍ ነጥብ የለውም በማለት መከራከራቸውን ተመልክተናል፡፡ በስር ፍ/ቤቶች በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠው የአሁኑ ተጠሪ እድሜያቸው ከ 90 አመት በላይ እንደሆነ እና ተጠሪን በአካል አስቀርበው ጉዳዩን ያጣሩት የሥር ወረዳ ፍ/ቤት እና የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ተጠሪ በእድሜ መግፋታቸው ምክንያት የሚሰሩት ስራ

የሚያደርሰው ስሜት ለመገንዘብ የማይችሉ መሆናቸውን ነው፡፡ በሌላ በኩል የሥር ፍ/ቤት በግራ ቀኙ የተደረገው የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ በመነሻነት የሥር የወሰደው የተጠሪ ጤና ሁኔታ መልካም አለመሆን ሳይሆን በዕድሜ በመግፋታቸው ምክንያት ቤቱን በአግባቡ ተደራድረው ይሸጣሉ ተብሎ ስለማይገመት ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ ውል በህግ ፊት የጸና ህጋዊ ተቀባይነት ወይም (ውጤት) እንዲኖረው ውል ለማቋቋም ከሚያስችሉ መስፈርቶች አንዱ የችሎታ መስፈርት ሲሟላ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/1678(ሀ) ስር ተመልክቷል፡፡ አንድ ውል በህጉ አግባብ ተፈፅመዋል ለማለት የሚቻለው ግራቀኙ ፍፁም በሆነ አኳሃን የተስማሙ እና ፍቃዳቸው የሰጡ መሆኑን ሲረጋገጥ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1680(1) ተደንግጓል ፡፡በተዋዋይ ወገኖች የተደረገው ውል የፈቃድ ጉድለት ያለበት መሆኑ ሲረጋገጥ የተደረገውን ውል እንዲፈርስ ዳኝነት መጠየቅ እንደሚቻል በፍ/ብ/ህ/ቁ 1696 እና ተከታይ ድንጋጌዎች የተደነገገ ጉዳይ ነው፡፡ የፍቃድ ጉድለት ከሚገለፅባቸው ነገሮች አንዱ ከተዋዋይ ወገኖች በአንዱ ውልን ለማፍረስ የሚያስችል ጉዳት መኖሩ ማሳየት ሲቻል ነው፡፡ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1710 ንኡስ አንቀፅ 2 እንደተመለከተው"…የተጎጂው ፈቃድ የተገኘው ችግሩን የመንፈስ ቀላልነቱን መጃጀቱን በእድሜ መግፋቱን ወይም በንግድ ግልፅ የሆነ የልማድ እውቀት የሌለው መሆኑን በመደገፍ እንደሆነ እና በህሊናም ግፍ መስሎ ሲታይ ውሉን ማፍረስ ይቻላል ፡፡ በማለት የተደነገገው መሆኑ ተገንዝበናል፡፡ ከላይ እንደተመለከተው የስር መጀመርያ ደረጃ ፍ/ቤት ይሁን የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪን በችሎት በማስቀረብ ቃለ መጠይቅ ስለማድረጋቸው እና በተደረገው ማጣራትም ተጠሪ በእድሜ መግፋት /መጃጀት/ ምክንያት የህጋዊ ተግባራት ውጤት (juridical acts) በአግባቡ ማመዛዘን የማይችሉ መሆኑን ማረጋገጫቸውን የሚያመለክት ነው፡፡

በተዋዋይ ወገኖች የሚደረገው ውል ተወዳዳሪ መብትና ግዴታ የሚያቋቋም በሆነ ጊዜ የግራቀኙ መብት እና ግዴታ በተቻለ መጠን ፍትሐዊ ስምምነት ላይ መድረስ አስፈላጊ መሆኑ ከአጠቃላይ የውል መርሆዎች የምንገነዘበው ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ በእድሜ በመግፋት ወይም በመጃጀታቸው ሳቢያ ከአመልካች ጋር ያደረጉት ውል የገበያ ሁኔታበአግባቡ አጥንተው ተደራድረው የገበያ ዋጋውንምን ያህል እንደሆነ ለይተው ታዋውሏል ማለት የሚቻል አይደለም፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ዕድሜያቸው ከ90 አመት በላይ ስለመሆኑ በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት በአመልካች እና ተጠሪ መካከል የተደረገው ውል እንዲፈርስ የወሰኑት የተጠሪ የጤና ሁኔታ መሰረት በማድረግ ሳይሆን በእድሜው መግፋት ወይም(በመጃጀት) ምክንያት ማህበራዊ ግንኙነታቸው የተገደበ በንግድ ግልፅ የሆነ ልማድ ወይም እውቀት የሌላቸው ስለመሆኑ በማረጋገጥ ነው፡፡ በህጉ አግባብ የተደረገ ውሎች ህጋዊ ውጤት ሊኖራቸው እንደሚገባ በመርህ ደረጃ ግልፅ ቢሆንም በፍቃድ ጉድለት የተገኘ ውል ግን የተዋዋይ ወገን ጥቅም በሚጎዳ

መልኩ የሚጸናበት የህግ ምክንያት አይኖርም በተያዘው ጉዳይ የአሁኑ ተጠሪ በዕድሜ የገፉ ከመሆናቸው አንፃር አረጋውያን የህግ ጥበቃ ከሚደረግላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች አንዱ በመሆናቸው ከአመልካች ጋር ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል ህጋዊ ውጤቱ በጥንቃቄ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ የአሁኗ ተጠሪ ከአመልካች ጋር እኩል የመደራደር አቅም እና ችሎታ የነበራቸው መሆኑን ባልተረጋገጠበት የተደረገው የሽያጭ ውል መብታቸው የነካ አይደለም የሚያስብል አይደለም፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እንዲሁም የክልሉ የጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የስር ከ/ፍ/ቤት ውሳኔ በመሻር የሽያጭ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት የሰጡት ውሳኔ ህጉ በአግባቡ ተፈፃሚ አድርገዋል ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የህግ ስህተት መፈፀማቸውን የሚያሳይ ሆኖ አልተገኘም፡፡በዚህም የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ አድርገን ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የደ/ብ/ብ/ህ/ ክልል ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ 04350 በ29/08/2007 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሀድያ ዞን ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 13636 በ08/05/2007 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሰጠው ፍርድ በመሻር የተሰጠውን ውሳኔ እና የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 65012 በ28/09/2007 ዓ/ም የተሰጠው ትእዛዝ ፀንቷል፡፡
2. የዚህ ፍ/ቤት ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡
3. የውሳኔው ግልባጭ የስር ፍ/ቤቶች ይተላለፍ፡፡
4. በዚህ ፍ/ቤት ሰኔ 09/2007 ዓ/ም የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው ክፍል ይፃፍ፡፡ መዝገቡ ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ/ገ

የሰ/መ/ቁ. 119233

ሚያዚያ 17 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ

ቀነዓ ቂጣታ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- አያት አክሲዮን ማህበር - አልቀረቡም

ተጠሪ፡- ወ/ሪት ሜሮን ክፍለሚካኤል ተክሌ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩን የቀረበው የግልግል ዳኞች ጉባኤ አመልካች ከተጠሪ ጋር በተዋዋለው የዱቤ የቤት ሽያጭ ውል መሰረት የመፈጸም ግዴታ አለበት በማለት የሰጠው ውሳኔ አመልካች በዱቤ የቤት ሽያጭ ውል ስዋዋል የባንክ ስራ የመስራት ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ ከተሰጠበት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች አንጻር በሰበር አጣርቶ ለመወሰን የሚል ጭብጥ ተይዞ ነው፡፡
2. የክርክሩ መነሻ አመልካችና ተጠሪ ጳጉሜ 5 ቀን 2000 ዓ/ም የተዋዋሉት የዱቤ የቤት ሽያጭ ውል በተለይም የክፍያ ስርዓቱ የውሉን ሁኔታዎች ለማሻሻል ወይም ለመለወጥ ወይም ወሉን ለማፍረስ የሚያበቃ ምክንያት ነው ወይስ አይደለም የሚለው ነጥብ ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪ በተዋዋሉት የዱቤ የቤት ሽያጭ ውል አመልካች በአዲስ አባበ ከተማ በቀድሞው ወረዳ 28 በተለምዶ አያት መንደር እየተባለ ከሚጠራው ስፍራ አመልካች በሚገነባው የጋራ የመኖሪ አፓርታማ ህንጻ በሁለተኛ ፎቅ ቁጥሩ አ-2-2 የሆነ ባለሶስት መኝታ ክፍል ቤት በብር 660,121 (ስድስት መቶ ስልሳ ሺ አንድ መቶ ሃያ አንድ ብር) ለተጠሪ ለመሸጥ ተስማምቷል፡፡ የቤቱን ዋጋ አከፋፈል በተመለከተ ከቤቱ ዋጋ ውስጥ 197,704 (አንድ መቶ ዘጠና ሰባት ሺ ሰባት መቶ አራት ብር) ከሳሽ (ተጠሪ) ቤቱን ከመረከቧ በፊት በስድስት ክፍያዎች እንድትከፍል ቀሪውን ብር 462,417 (አራት መቶ

ስልሳ ሁለት ሺ አንድ መቶ አስራ ሰባት ብር) ቤቱን ከተረከበች ጊዜ ጀምሮ በሰላሳ አመት ውስጥ ከነወለዱ በየወሩ ብር 5,133 (አምስት ሺ አንድ መቶ ሰላሳ ሶስት ብር) እየከፈለች ልታጠናቅቅ ሻጭና ገዥ (አመልካችና ተጠሪ) የተስማሙ መሆኑ ግራ ቀኙ የሚካካዱበት ነጥብ አይደለም፡፡

3. በአመልካችና በተጠሪ መካከል ለተፈጠረው አለመግባበትና ሙግት ምክንያት የሆነው ተጠሪ በዱቤሽያጭ ውሉ መሰረት የመጀመሪያና ሁለተኛውን ክፍያ ከከፈሉ በኂላ ቀጣዮቹን ክፍያዎች ለመክፈል ተጠሪ ጥያቄ ስታቀርብ በዱቤ ቤት በመሸጥ ከዋጋ ጋር የረዥም ጊዜ ወለድ አብሮ ከቤቱ ዋጋ ጋር ጨምሮ መሰብሰብ የወንጀል ድርጊት መሆኑ ተለግጾ አመልካችና የአመልካች ከፍተኛ የስራ አመራሮች በፌዴራል ዐቃቤ ህግ በኩል የወንጀል ክስ የቀረበባቸው መሆኑን ገልጾ የቤቱን ዋጋ በአንድ ጊዜ ካልከፈለች በስተቀር ቀደም ሲል በተዋዋልነው የዱቤ ቤት ሽያጭ ውል መሰረት ለመፈጸምና የቤቱንም ዋጋ ለመቀበል የሚቸገር መሆኑን ገልጾ ክፍያ ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆኑና ለተጠሪ በማሳወቁ ነው፡፡

4. ተጠሪ ለግልግለ ዳኞች ጉባኤ ክስ ያቀረበችው አመልካች በዱቤ ሽያጭ ወሉ መሰረት ቀጣይ ክፍያዎችን እንዲቀበልና በዱቤ ሽያጭ ወሉ መሰረት ቤቱን ለከሳሽ (ተጠሪ) እንዲያስረክብ ውሳኔ ይሰጥልኝ፡፡ አመልካች የዱቤ የቤት ሽያጭ ውሉን በራሱ ስልጣንና ፍላጎት ወደ እጅ በጅ ሽያጭ ለመለወጥ የወሰደው እርምጃ የህግ መሰረትና ህጋዊ ውጤት የሌለው ነው ተብሎ የዱቤ የሽያጭ ውል የጸናና ህጋዊ ውጤት ያለው ነው ይባልልኝ በማለት ነው፡፡ አመልካች ለግልግል ዳኞች ጉባኤ በአመልካችና በአመልካች ከፍተኛ የስራ አመራር አባላት ባልተፈቀደ ሁኔታ የባንክ ስራ ሰርተዋል በማለት ዐቃቤ ህግ ያቀረበውን ክስ ለማስረዳት በማስረጃነት ያቀረባቸው አመልካች ከሃያ ስድስት ደንበኞች ጋር ያደረገውን የዱቤ የቤት ሽያጭ ውል መሆኑንና ይህም የወንጀል ድርጊት ነው ተብሎ በአመልካችና በአመልካች ከፍተኛ የስራ አመራር አባላት ላይ የተወሰነባቸው መሆኑን ገልጾ ከሳሽ (ተጠሪ) የቤቱን ዋጋ እጅ በእጅ ከፍላ እንድትረከብ ካልተደረገ በስተቀር ህገ ወጥ ነው የተባለን የዱቤ ሽያጭ ውል መሰረት በማድረግ ከገዥ ቤቱን ዋጋ ለመስብስብና የዱቤ ሽያጭ ውሉን ለመፈጸም አልችልም በማለት ነው፡፡

5. የግልግል ጉባኤው አመልካች በሰላሳ አመት ውስጥ የቤቱን ዋጋ ከተጠሪ ለመቀበል በማስማማት የተዋዋለው የዱቤ የቤት ሽያጭ ውል እንደ ህገ ወጥ የባንክ ስራ ይቆጠራል ወይስ አይቆጠርም፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 91837 መጋቢት 2 ቀን 2005 ዓ/ም የሰጠው የወንጀል ፍርድ ውጤቱ ምንድን ነው? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ አመልካች ከተጠሪ ጋር የተዋዋለው የዱቤ የቤት ሽያጭ ውል እንደ ህገወጥ የባንክ ስራ ወንጀል የማይቆጠር መሆኑንና የወንጀል ፍርዱ የዱቤ

ሽያጭውን በጠቅላላው ህገ ወጥ የማድረግ ውጤት የሌለው ነው በማለት አመልካችና ተጠሪ የተዋዋሉት የዱቤ የቤት ሽያጭ ውል የጸናና ህጋዊ ውጤት ያለው ነው። ተከሳሽ (አመልካች) በዱቤ ሽያጭ ውሉ መሰረት ክፍያ አልቀበልም የሚልበት ምክንያት የለም። ተከሳሽ (አመልካች) በዱቤ ሽያጭ ወሉ መሰረት ቤቱን ገንብቶ ለከሳሽ (ለተጠሪ) ያስረክብ በማለት ውሳኔ ተሰጥቷል።

6. አመልካች ሚያዝያ 24 ቀን 2008 ዓ/ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ አመልካች ለተጠሪና ለሌሎች ደንበኞቹ ቤት በዱቤ በመሸጥ ከቤቱ ዋጋ ጋር ወለድ ጨምሮ በረዥም ጊዜ ቤቱን ዋጋ ለማስከፈል የተዋዋላቸው ውሎች ህገ ወጥ በሆነ መንገድ የባንክ ስራ የመስራት ወንጀል ነው ተብሎ አመልካችና የአመልካች ከፍተኛ የስራ አመራሮች በወንጀል ጥፋተኛ ተብለው ከተቀጡ በኋላ የግልግል ጉባኤው የዱቤ ሽያጭ ውሉና የአከፋፈል ስርዓቱ ህጋዊ ነው። በዱቤ ሽያጭ ውሉ መሰረት የቤቱ ዋጋ ልትቀበል ይገባል። ቤቱን ለገዥ አስርክብ በማለት የሰጠው ውሳኔ አንድ ድርጊት በአንድ ስርዓት ውስጥ ህገ ወጥ የሆነ ወንጀል ነው ከተባለ በኋላ እንደገና ህጋዊ ነው የሚባልበት ምክንያት ሳይኖር ህጋዊ ነው የተባለ መሆኑን የሚያሳይና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል። አመልካች ግንቦት 25 ቀን 2008 ዓ/ም በሰጠችው መልስ አመልካች በዱቤ በመሸጡ ሳይሆን በህገ ወጥ መንገድ የባንክ ስራ በመስራቱ ነው። በወንጀል የተሰጠው ፍርድ ከፍታብሔር ህጉ ጋር በሚጣጣም መንገድ መተርጎም አለበት። አመልካች በራሱ ስልጣን የውሉን መሰረታዊ ሁኔታ የማሻሻልም ሆነ የመለወጥ ስልጣን የለውም። ስለዚህ የግልግል ጉባኤው የአመልካችን ክርክር ውድቅ ያደረገው በአግባቡ ስለሆነ የሰበር አቤቱታው ውድቅ ይደረግልግኝ በማለት ተከራክራለች። አመልካች ግንቦት 25 ቀን 2008 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል።

7. ከስር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ በዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት የጽሁፍ ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል። ጉዳዩን እንደመርመርነው አመልካች በጳግሜ 5 ቀን 2000 ዓ/ም በተዋዋለው የዱቤ የቤት ሽያጭ ውል ለተጠሪ በብር 660,121 (ስድስት መቶ ስልሳ ሺ አንድ መቶ ሃያ አንድ ብር) ለተጠሪ ተለይቶ የተገለጸውን አፓርትመንት ቤት ለመሸጥ የተስማማና ተጠሪም ቤቱን ለመግዛት የተሰማማች መሆኑ ግልጽ ነው። ግራ ቀኙን እያከራከረ ያለው አመልካች ይህንን የቤቱን ዋጋ ከተጠሪ ለመቀበልና ተጠሪም ለአመልካች የቤቱን ዋጋ ለመክፈል የተስማሙበት የቤቱ ዋጋ የአከፋፈል ስርዓት ነው።

8. አመልካችና ተጠሪ በተዋዋሉት የዱቤ የቤት ሽያጭ ውል መሰረት ገዥዋ (ተጠሪ) ቤቱን ከመረከቧ በፊት በስድስት ክፍያዎች ብር 197,704 (አንድ መቶ ዘጠና ሰባት ሺ ሰባት

መቶ አራት ብር)ለመክፈል የተስማማች ሲሆን ቀሪውን ብር 462,417 (አራት መቶ ስልሳ ሁለት ሺ አራት መቶ አስራ ሰባት ብር) ተጠሪ ቤቱን ከተረከበች በኋላ የቤቱ ዋጋ ከሚወልደው ወለድ ጋር በወር 5,133 (አምስት ሺ አንድ መቶ ሰላሳ ሶስት ብር) እየከፈለች በሰላሳ አመት ውስጥ ከፍላ ለማጠናቀቅና አመልካችም ቀሪውን ቤቱን ዋጋ በውሉ በተገለጸው መንገድ ለመሰብሰብ ተስማምተው የዱቤ ሽያጭ ውሉን የተፈራረሙ መሆኑን ግራ ቀኙ ለግልግል ጉባኤውና ለዚህ ሰበር ችሎት ካቀረቡት ክርክር ተረድተናል አመልካች ከተጠሪ ጋር ባደረገው የቤት ሽያጭ ውል አይነታዊ ጉዳይ የሆነው የቤቱ ዋጋ አከፋፈል ስርዓት ማለትም ተጠሪ የቤቱን ዋጋ ከነወለዱ በወር የተወሰነ ክፍያ እየከፈለች በሰላሳ አመት ውስጥ ከፍላ እንድታጠናቀቅ የተዋዋልነው የውል ክፍል ያለ ህጋዊ ፈቃድ የባንክ ስራ የመስራት ወንጀል ነው ተብሎ አመልካችና የአመልካች ከፍተኛ የስራ ኃላፊ በወንጀል የተከሰሱና በፍርድ ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡ በመሆኑ አመልካች በፍርድ ወንጀል ነው የተባለ ውል የሚፈጽምበት ምክንያት የለም በማለት ነው፡፡

9. እኛም አመልካች መከራከሪያ ያደረገው የወንጀል ፍርድ፣ ፍርዱ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የጸና ወይም የተሻረ ስለመሆኑና በጉዳይ ላይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አጣሪ ችሎት የሰጠውን ትዕዛዝ መሰረታዊ ይዘት ለመረዳት አግባብነት ያላቸውን መዛግብት በማስቀረብ መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባልስልጣን ዐቃቤ ህግ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 91837 ባቀረበው የወንጀል ክስ፣ አመልካች የገንዘብና የባንክ አዋጅ ቁጥር 83/1986 አንቀጽ 59 ንዑስ አንቀጽ 1(ሸ)፣ ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) እና “ሐ” የተደነገገውን በመተላለፍ በብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ሳያገኝ 1999 ዓ/ም በተደራጀ መንገድ ቤት በዱቤ በመሸጥ የዱቤ ብድር በመስጠት ቤት በዱቤ ከገዙት ደንበኞቹ ከፍተኛ መጠን ያለው ወለድ በመሰብሰብ በህገ ወጥ መንገድ የባንክ ስራ የመስራት ወንጀል ፈጽሟል በማለት በመጀመሪያ (አንድኛው) የወንጀል ክስ የመሰረተበት ሲሆን በሁለተኛው የወንጀል ክስ የአመልካች የቦርድ ሰብሳቢ የሆኑት ሁለተኛ ተከሳሽ የነበሩት ሰው አመልካች በመጀመሪያው የወንጀል ክስ የተጠቀሰውን ወንጀል ፈጽመዋል በማለት ክስ የቀረበ መሆኑን ካስቀረብናቸው መዛግብት ተረድተናል፡፡

10. ከላይ ከተገለጸው በተጨማሪ የገቢዎችና ጉምሩክ ዐቃቤ ህግ አመልካች አዋጅ ቁጥር 592/2000 አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 1 በመተላለፍ፣ ከብሔራዊ ባንክ የባንክ ስራ ለመስራት የሚያስችለው ፈቃድ ሳያገኝ፣ በ2001 ዓ/ም ለበርካታ ደንበኞቹ ቤት በዱቤ ከሸጠ በኋላ የቤቱን ካርታ በመያዥነት በመያዝ፣ ከዱቤ ከተሸጠው የቤቶቹ ዋጋ ላይ ከፍተኛ መጠን ያለው ወለድ በማስከፈል ለደንበኞቹ የዱቤ የቤት ሽያጭ ብድር በመስጠት በህገ ወጥ መንገድ የባንክ ስራ የመስራት ወንጀል ፈጽሟል በማለት

በሶስተኛው የወንጀል ክስ፣ ክስ መስርቶበታል፡፡ እንዲሁም በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሁለተኛ ተከሳሽ በነበሩት የአመልካች የቦርድ ሰብሳቢ በሶስተኛው የወንጀል ክስ የተጠቀሱትን የህግ ድንጋጌዎች በመተላለፍ በሶስተኛው የወንጀል ክስ የተጠቀሰውን ወንጀል ፈጽመዋል በማለት በአራተኛው የወንጀል ክስ መስርቷል፡፡

11. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 91837፣ ከላይ ይዞታቸው ስለተገለጸው የወንጀል ክሶችና ሌሎች የህግ ማዕቀፎች ተጠቅሰው በቀረቡት የወንጀል ክሶች ላይ የከሳሹንና የተከሳሾችን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ፣ ከመርመርና ከመዘነ በኋላ አመልካች ህጋዊ ፈቃድ ሳይኖረው በዱቤ ቤት በመሸጥና ወለድ በማስከፈል በአንደኛው የወንጀል ክስና በሶስተኛ የወንጀል ክስ የተጠቀሱትን የህግ ድንጋጌዎች በመተላለፍ በህገ ወጥ መንገድ የባንክ ስራ የመስራት ወንጀሎችን የፈጸመ ጥፋተኛ ነው፡፡ የአመልካች የቦርድ ሰብሳቢ የሆኑት ሁለተኛው ተከሳሽም በሁለተኛው የወንጀል ክስና በአራተኛው የወንጀል ክስ የተገለጹትን በህገ ወጥ መንገድ የባንክ ስራ የመስራት ወንጀሎችን ፈጽሟል በማለት በመዝገብ ቁጥር 91837 መጋቢት 2 ቀን 2005 ዓ/ም የጥፋተኝነት ውሳኔ የሰጠ መሆኑንና በአመልካችና በአመልካች የቦርድ ሰብሳቢ በነበሩት ሁለተኛው ተከሳሽ ላይ ግንቦት 14 ቀን 2005 ዓ/ም የቅጣት ውሳኔ የወሰነ መሆኑን ተረድተናል፡፡

12. አመልካች በዱቤ ቤት መሸጥ ህገ ወጥ የባንክ ስራ የመስራት ወንጀል ነው ተብሎ የገቢዎችና ጉምሩክ ዐቃቤ ህግ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረበው በአንደኛው የወንጀል ክስ እና ሶስተኛውን የወንጀል ክስ ጥፋተኛ መባሌ ተገቢ አይደለም በማለት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ችሎት የይግባኝ ቅሬታ አቅርቧል፡፡ በስር ፍርድ ቤት ሁለተኛ ተከሳሽ የነበሩት የአመልካች የቦርድ ሰብሳቢ የገቢዎችና ጉምሩክ ዐቃቤ ህግ በሁለተኛው የወንጀል ክስና በአራተኛው የወንጀል ክስ የጠቀሳቸውን የህግ ድንጋጌዎች ተላልፈሀል ተብየ የተሰጠብኝ የጥፋተኝነት ውሳኔ ተገቢነት የሌለው በመሆኑ ሊሻርልኝ ይገባል በማለት የይግባኝ ቅሬታቸውን ማቅረባቸውን ተረድተናል፡፡

13. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካችና የአመልካች የቦርድ ሰብሳቢ እና ሌሎች ተከሳሾች እንዲሁም የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ዐቃቤ ህግ በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 90549 የቀረበውን ይግባኝ፣ በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 90222 በማጣመር፣ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማና ከመረመረ በኋላ፣ ቤት በዱቤ በመሸጥ የቤት ዋጋ ከወለድ ጋር መቀበል ህገ ወጥ የባንክ ስራ የመስራት ወንጀል ነው ሊባል የማይችልና አመልካችም አዋጅ ቁጥር 83/1986 እና አዋጅ ቁጥር 592/2000 በልዩ ሁኔታ ኮርፖሬሽኖችና ድርጅቶችን ጥፋተኛ የሚያደርግ ልዩ ድንጋጌ ባልያዙበት ሁኔታ በህገ ወጥ መንገድ የባንክ ስራ መስራት ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ ሊከሰስና ጥፋተኛ ሊባል የሚችልበት የህግ ማዕቀፍ የሌለ መሆኑን ገልጻ፣ አመልካች የከፍተኛ

ፍርድ ቤት ጥፋተኛ ብሎ የቅጣት ውሳኔ ከሰጠበት አንደኛ እና ሶስተኛው የወንጀል ክሶች በነጻ እንዲሰናበት፣ የአመልካች የቦርድ ሰብሳቢ የነበሩት ሁለተኛው ተከሳሽ የከፍተኛ ፍርድ ቤት በሁለተኛው ክስና በአራተኛው ክስ ጥፋተኛ ብሎ ከወሰነባቸው የቅጣት ውሳኔ በነጻ እንዲሰናበቱ ጥር 6 ቀን 2008 ዓ/ም በሰጠው ፍርድ ከገጽ 15 እስከ ገጽ 19 የሰጠውን ፍርድ ይዘት በማገናዘብ ለመረዳት ችለናል፡፡

14. ከዚህ በተጨማሪ የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ አመልካች በአንደኛው የወንጀል ክስና በሶስተኛው የወንጀል ክስ ከተከሰሰበት ወንጀል በነጻ የተሰናበተ መሆኑን፣ የአመልካች የቦርድ ሰብሳቢ ሁለተኛው ተከሳሽ በሁለተኛው የወንጀል ክስ እና በአራተኛው የወንጀል ክስ ከተከሰሰበት በህገ ወጥ መንገድ የባንክ ስራ የመስራት ወንጀል በነጻ እንዲሰናበቱ በግልጽ ውሳኔ የሰጠበት መሆኑን ይግባኝ ሰሚው ችሎት በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 90222 ጥር 6 ቀን 2008 ዓ/ም በሰጠው ፍርድ፣ በውሳኔው ክፍል በተራ ቁር 1 እና በተራ ቁጥር 2 ካሰፈረው ውሳኔ ይዘት ለመረዳት ችለናል፡፡ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ዐቃቤ ህግ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 90222 ጥር 6 ቀን 2008 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ እና ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት መጋቢት 27 ቀን 2008 ዓ/ም የተጻፈ ሃያ አራት ገጽ የሰበር አቤቱታ አቅርቦ፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ችሎት በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር ጥር 6 ቀን 2008 ዓ/ም የሰጠው ፍርድና ውሳኔ በሰበር ችሎት ሊታይ የሚቻል መሰረታዊ የህግ ስህተት የሌለው መሆኑን በመግለጽ፣ የሰበር አጣሪ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 126067 ታህሳስ 17 ቀን 2009 ዓ/ም በሰጠው ትዕዛዝ፣ የገቢዎችና ጉምሩክ ዐቃቤ ህግ ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ ውድቅ በማድረግ መዝገቡን የዘጋው መሆኑን ተረድተናል፡፡

15. ከላይ ከገለጽናቸው በየደረጃው ከተሰጡ የወንጀል ፍርዶች የምረዳው፣ ምንም እንኳን አመልካች ቤት በዱቤ በመሸጥ፣ ከቤቱ ዋጋ ጋር በመጨመር ወለድ መቀበሉ ያለ ህጋዊ ፈቃድ የባንክ ስራ የመስራት ወንጀል ነው በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በወንጀል መዝገብ ቁጥር 91837 በአመልካችና በአመልካች የቦርድ ሰብሳቢ ላይ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ የሰጠ ቢሆንም፣ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሲሚ ችሎት በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 90222 ጥር 6 ቀን 2008 ዓ/ም በሰጠው ፍርድና ውሳኔ አመልካችና የአመልካች የቦርድ ሰብሳቢ የአዋጅ ቁጥር 83/1986 እና የአዋጅ ቁጥር 592/2000 የወንጀል ድንጋጌዎች በመተላለፍ ያለ ህጋዊ ፈቃድ የባንክ ስራ የመስራት ወንጀል ፈጽመዋል በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በመሻር አመልካችና የአመልካች የቦርድ ሰብሳቢ ከቀረበባቸው ያለ ህጋዊ ፈቃድ የባንክ ስራ

የመስራት ወንጀል በነጻ እንዲሰናበቱ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የወንጀል ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠውን ፍርድና ውሳኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት፣ በሰበር መዝገብ ቁጥር 126067 ታህሳስ 17 ቀን 2009 ዓ/ም በሰጠው ትዕዛዝ አጽንቶታል፡፡

16. ከዚህ አንጻር ሲታይ በይግባኝ የተሻረውን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 91837 የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በማጣቀስ ከተጠሪ ጋር ጳጉሜ 5 ቀን 2000 ዓ/ም የተዋዋልኩት የዱቤ የቤ ሽያጭ ውል የወንጀል ተግባር ነው የተባለ ስለሆነ ውሉን እንዲፈጸም አልገደድም በማለት አቅርቦት የነበረው ክርክር ተገቢነት የነበረው ቢሆንም፣ በሂደት የከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 91837 የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በወንጀል ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 90222 ጥር 6 ቀን 2008 ዓ/ም በሰጠው ፍርድና ውሳኔ የተሻረ መሆኑን እያወቀ፣ ለዚህ ሰበር ችሎት ግንቦት 25 ቀን 2008 ዓ/ም ባቀረበው የመልስ መልስ ከተጠሪ ጋር የተዋዋለውን የዱቤ የቤት ሽያጭ ውል ላለመፈጸም መከራከሪያ አድርጎ ማቅረቡ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

17. በመሆኑም የግልግል ጉባኤ ዳኞች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ በመዝገብ ቁጥር 91837 የአመልካችና በአመልካች የቦርድ ሰብሳቢ፣ ያለ ህጋዊ ፈቃድ የባንክ ስራ የመስራት ወንጀል ፈጽመዋል በማለት የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ፣ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው የዱቤ የቤት ሽያጭ ውል ሊፈጽም ይገባል ወይም አይገባም የሚለውን ጭብጥ ለመወሰን አግባብነት እንደሌለው በመግለጽ የሰጠው የህግ ትርጉምና በሌሎች ነጥቦች ላይ ያስፈራቸው ትችቶች በፍርድ ወንጀል ነው የተባለን ክፍያ፣ የወንጀል ፍርዱ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ታይቶ ከመሻሩ በፊት አመልካች እንዲቀበል የሚያስገደድና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1792 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1793 ድንጋጌዎችን የሚጥስና መሰረታዊ የህግ ስህተት የነበረበት ውሳኔ እንደሆነ ተረድተናል፡፡

18. ሆኖም የግልግል ጉባኤው ነሐሴ 22 ቀን 2007 ዓ/ም የአመልካችና የተጠሪን ክርክር ሰምቶ ውሳኔ ከሰጠ በኂላ፣ አመልካች ቤት በዱቤ በመሸጥ የቤቱን ዋጋ ከነወለዱ በረዥም ክፍያ ለመሰብሰብ ከደንበኞቹ ጋር በመዋዋል የቤቱን ዋጋ ከውሉ መሰረት ከነወለዱ መቀበሉ፣ ያለህጋዊ ፈቃድ የባንክ ስራ መስራት ወንጀል አመልካችንና የአመልካችን የቦርድ ሰብሳቢ ጥፋተኛ የማያስኝና በወንጀል የማያስቀጣ መሆኑን በመግለጽ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 91837 የሰጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 90222 ጥር 6 ቀን 2008 ዓ/ም በሰጠው ፍርድና ውሳኔ የሻረው በመሆኑና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ፍርድና ውሳኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አጣሪ

ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 126061 ታህሳስ 19 ቀን 2009 ዓ/ም በሰጠው ትዕዛዝ ያጸናው በመሆኑ፣ አመልካች ከተጠሪ ጋር ጳጉሜ 5 ቀን 2000 ዓ/ም የተዋዋልኩት የዱቤ የቤት ሽያጭ ውል የወንጀል ተጠያቂነትን የሚያስከትል ህገ ወጥ ውል በመሆኑ በውሉ መሰረት እንድፈጽም ልገደድ አይገባም በማለት የሚያቀርበው ክርክር ህጋዊ መሰረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም። በመሆኑም የግልግል ዳኞች ለውሳኔያቸው የሰጡትን ምክንያትና በውሳኔያቸው ላይ የሰጧቸውን ትዕዛዞች በማሻሻል በውጤት ደረጃ አመልካች ከተጠሪ ጋር ጳጉሜ 5 ቀን 2000 ዓ/ም በተዋዋለው የዱቤ የቤት ሽያጭ ውል መሰረት ሊፈጽም ይገባል በማለት የሰጡትን ውሳኔ አፅንቶታል።

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የግልግል ዳኞች ነሐሴ 22 ቀን 2007 ዓ/ም፣ አመልካች ከተጠሪ ጋር ጳጉሜ 5 ቀን 2000 ዓ/ም በተዋዋለው የዱቤ የቤት ሽያጭ ውል መሰረት ሊፈጽም ይገባል በማለት የሰጡት የውሳኔ ክፍል ምክንያት ተለውጦ ፀንቷል።
2. አመልካች ከተጠሪ ጋር በተዋዋለው የዱቤ የቤት ሽያጭ ውል መሰረት፣ የቤቱን ዋጋ በውሉ ከተገለጸው ወለድ ጋር በውሉ በተቀመጠው የአከፋፈል ስርዓት መሰረት ነው ሊቀበል ይገባል በማለት ወስነናል።
3. አመልካች ከተጠሪ ጋር በተዋዋለው የዱቤ የቤት ሽያጭ ውል መሰረት ለተጠሪ የሸጠውን ቤት የማስረከብ ኃላፊነት አለበት በማለት ወስነናል።
4. ተጠሪ (ከሳሽ) ጉዳዩን በግልግል ዳኞች ለማሳየት ያወጣቸውን ብር 40,506 (አርባ ሺ አምስት መቶ ስድስት ብር) ተከሳሽ (አመልካች) ሊከፍላት ይገባል በማለት ወስነናል።
5. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ ብለናል።

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ሃ/ወ

የሰ/መ/ቁ.106994

ሚያዚያ 24 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ

ቀነዓ ቂጣታ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- ብሔራዊ የኢትዮጲያ ኢንሹራንስ /ኢ.ማ/ አልቀረበም

ተጠሪዎች፡-የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

1. ዘላቂ ግብርና ተሃድሶ ኮሚሽን
2. ትምህርት ቢሮ
3. የገጠር መንገዶች ባለስልጣን
4. ስራና ከተማ ልማት ቢሮ
5. የገንዘብ ቢሮ
6. ፕላንና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ

(1–6) ዐ/ህግ ሙሉ ባይለየኝ ቀረቡ

7. ዛምስ ኢንተርናሽናል የንግድ ድርጅት፣ አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ በዚህ ሰበር ችሎት ያቀረበው የግልግል ዳኞች ጉባኤ፣ የስር ከሳሾች /ተጠሪዎች/ የእቃውን ማቅረቢያ ጊዜ ካለ አመልካች ፈቅዶና ስምምነት ያራዘሙ በመሆኑ በሰጠሁት የዋስትና ሰነድ መሰረት ልገደድ አይገባኝም በማለት ያቀረበውን ክርክር በማለፍ አመልካች ለክስ ኃላፊ ነው ማለታቸውና አመልካች ዕዳው እስከከፈል ድረስ 0.07 መቀጫ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጡትን ውሳኔ አግባብነት በሰበር አጣርቶ ለመወሰን የሚል ጭብጥ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመስርቶ ነው፡፡
2. ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው የግልግል ዳኞች ጉባኤ ነው፡፡ የግልግል ዳኞች በወቅቱ አንደኛ ተከሳሽ በነበረው ሰባተኛ ተጠሪና በከሳሾች የሌሎች ተጠሪዎችመካከል ያለውን ክርክር

ሰምቶ መጋቢት 13 ቀን 2003 ዓ/ም ውሳኔ ሰጥቶ ነበር፡፡ ሁለተኛ ተከሳሽ/የአሁን አመልካች/ የግልግል ዳኞች ለእኔ በአግባቡ መጥሪያ እንዲደርሰኝ ሳያደርገው መስጠታቸው ስህተት ያለበት ነው በማለት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ፣የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የግልግል ዳኞች የሰጡትን ውሳኔ በመዝገብ ቁጥር 01-82566 ሀምሌ 11 ቀን 2004 ዓ/ም በመሻር ጉዳዩን ለግልግል ዳኞች መልሶታል፡፡

3. ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻ የሆነው የግልግል ጉባኤ ዳኞች ጉዳዩ፣ ወደ ግልግል ዳኞች ከመለሰው በኂላ፣ የግልግል ጉባኤው የስር አንደኛ ተከሳሽ /ሰባተኛው ተጠሪ/ ና ሁለተኛው ተከሳሽ /አመልካች/ ያቀረቡትን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ሀምሌ 7 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ከሳሾችያቀረቡት ክስ ነው፡፡ ከሳሾች የተለያዩ የቢሮ ዕቃዎችን ለመግዛት ባወጣው ጨረታ አንደኛ ተከሳሽ/ሰባተኛ ተጠሪ/ አሸናፊ ሆኖ ጠቅላላ ዋጋቸው ብር 468540 /አራት መቶ ስልሳ ስምንት ሺ.ህ  አምስት መቶ አርባ ብር/ የሆኑ እቃዎችን ለማቅረብ መስከረም 12 ቀን 1991 ዓ/ም ውል የተዋዋለ መሆኑን፣አንደኛ ተከሳሽ የእቃዎቹን ሙሉ ዋጋ ብር 468540/ አራትመቶ ስልሳ ስምንት ሺ.ህ አምስት መቶ አርባ ብር/ በቅድሚያ ክፍያነት የተከፈለው መሆኑን፣ አመልካች /ሁለተኛተከሳሽ/ አንደኛ ተከሳሽ እቃዎቹን ባያቀርብ፣ አንደኛ ተከሳሽ ለወሰደው ዋጋ ለመክፈል የቅድመ ክፍያ ዋስትና ሰነድ ጥቅምት 19 ቀን 1994 ዓ/ም የሰጠ መሆኑን፣ አንደኛ ተከሳሽ የውል ግዴው ከገባባቸው ዕቃዎች ውስጥ የብር 73,800 /ሰባሶስት ሺ.ህ ስምንት መቶ ብር/ የሚያወጡ እቃዎችን የቀረበና ቀሪዎቹን ዋጋቸው 394740 /ሶስት መቶ ዘጠና አራት ሺ.ህ ሰባት መቶ አርባ ብር/ የሆኑ እቃዎች ያላቀረበ በመሆኑ ይህንን ገንዘብ፣ በውሉ ላይ የተገለጸውን የመቀጫ ገንዘብና ወለድ ተከሳሾች በአንድነትና በነጠላ እንዲወሰንላቸው ከሳሾች የግልግል ዳኞች ጉባኤውን ጠይቀዋል፡፡

4. የስር አንደኛ ተከሳሽ/ሰባተኛ ተጠሪ/ በወቅቱ ያቀረባቸው እቃዎች የጥራት መስፈርት አያሟሉም በማለት ከሳሾች አላግባብ የመለሱ በመሆኑ ለውሉ አለመፈጸም ተጠያቂነት ያለባቸው ከሳሾችእንደሆኑና መቀጫም የመክፈል ኃላፊነት እንደሌለበት በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ ሁለተኛ ተከሳሽ /አመልካች/ ዕቃዎች ከሳሾች መረከብ ነበረባቸው፡፡ አላግባብ ባለመረከባቸው ለውሉ አፈፃጸም ላይ ችግር የፈጠሩት ከሳሾች ናቸው፡፡ ከሳሾች ሁለተኛ ተከሳሽ ዋናው ባለዕዳ /አንደኛ ተከሳሽ/ ዕቃዎቹን ያላቀረበ መሆኑን ቢያሳውቀኝ ኖሮ እኔ ራሴ ወይም ሌላ ሰው ወክዬ የውልን ግዴታ እፈጽም ነበር፡፡ ከሳሾች ያለሁለተኛ ተከሳሽ ፈቃድና ስምምነት ሀምሌ 25 ቀን 1993 ዓ/ም በተፃፈ ደብዳቤ ለአንደኛ ተከሳሽ የዕቃውን ማቅረቢያ ጊዜ ያራዘመ በመሆኑ ኃላፊነት የለብኝም በማለት ተከራክሯል፡፡

5. የግልግል ዳኞች የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ፣ የስር አንደኛ ተከሳሽ /ሰባተኛ ተጠሪና/ ሁለተኛ ተከሳሽ አመልካቾች/ ያቀረቧቸውን መከራከሪያዎች ውድቅ በማድረግ፣ ተከሳሾች ከሳሾች ክስ ያቀረቡበትን ብር 394740 /ሶስት መቶ ዘጠና አራት ሺ ሰባት መቶ አርባ ብር/ በአንድነትና በነጠላ ይክፈሉ። ከዚህ በተጨማሪ ፍርድ ቤት ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ይህንን ገንዘብ ከፍለው ተከሳሾች እስከሚያጠናቅቅ ድረስ፣ በውሉ ላይ የተቀመጠውን በቀን 0.007 መቀጫ በአንድነትና በነጠላ ይክፈሉ። እንዲዚሁም ተከሳሾች ጉዳዩ ለፍርድ ቤት ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ በብር 394740 /ሶስት መቶ ዘጠና አራት ሺህ ከባት መቶ አርባ ብር/ ከፍለው እስከጠናቀቁበት ጊዜ ድረስ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ለከሳሾች ይክፈሉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል። አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበዋል። የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ስ/ስ/ህግ/ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞታል።
6. አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት ህዳር 18 ቀን 2007 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ፣ ከሳሾች ለዋሱ ማስጠንቀቂያ አልሰጡም። ሁለተኛው ተከሳሽ በሰጠው ዋስትና መሰረት ኃላፊ የሚሆኑበት ምክንያት የለም። የግልግል ዳኞች መደበኛ ፍርድ ቤት ክስ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ እዳው ተከፍሎ እስኪያልቅ ድረስ ወለድ እና በቀን 0.007 መቀጫ ተከሳሾች በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍል በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል። ተጠሪዎች ጥር 29 ቀን 2007 ዓ/ም የአመልካች ክርክር አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች መሰረት ያላደረገ በመሆኑ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል። ሰባተኛ ተጠሪ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ተጠርቶ ስላልቀረበ መልስ የመስጠቱ መብት ታልፏል። አመልካች መጋቢት 4 ቀን 2007 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ  አቅርቧል።
7. ከስር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ያቀረቡት የጽሁፍ ክርከር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል። ጉዳዩን እንደመረመርነው፣ ጉዳዩ በግልግል ዳኞች ጉባኤ ሲታይ አንደኛ ተከሳሽ የነበረው ሰባተኛው ተጠሪ የተለያዩ የቢሮ እቃዎችን ለማቅረብ የጨረታ አሸናፊ ሆኖ ጠቅላላ ዋጋቸው ብር 468540 /አራት መቶ ስልሳ ስምንት ሺህ አምስት መቶ አርባ ብር/ የሆኑ የቢሮ ዕቃዎች በጨረታ ሰነድ የተገለጸውን የጥራት መስፈርትና /specification/በማሟላት ለማቅረብ ውል መዋዋል አከራካሪ አይደለም። የእቃው አቅራቢ የሆነው ሰባተኛው ተጠሪ እቃዎችን ሙሉ ዋጋ ብር 468,540 /አራት መቶ ስልሳ ስምንት ሺህ  አምስት መቶ አርባ ብር/ በቅድመ ክፍያነት የወሰደ መሆኑና፣ ሰባተኛው ተጠሪ ለወሰደው የቅድመ ክፍያ ዋስትና ይሆን ዘንድ አመልካች የቅድመ ክፍያ የዋስትና ሰነድ መስጠቱ የግልግል ጉባኤ ዳኞች አረጋግጠዋል። ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ዋስ የሆኑት ሰባተኛው ተጠሪ አቅርባለሁ ብሎ የውል ግዴታ ከገባበትውስጥ

ብር 73,800/ሰባሶስትሺህ ስምንት መቶ ብር/ የሚያወጡ የቢሮ እቃዎች በውሉ የተገለጸውን የጥራት መስፈርት በማያሟላ ሁኔታ ማቅረቡንና ቀሪዎችን ዋጋቸው ብር 394,740ሶስት መቶ ዘጠና አራት ሺህ ሰባት መቶ አርባ ብር) የሚያወጡ ዕቃዎች በውሉ የተገለፀውን የጥራት መስፈርት በሚያሟላ ሁኔታ ያላቀረበና በውል የገባውን ግዴታ ባለመፈፀሙ ለውሉ አለመፈፀም ኃላፊ ሆኖ መገኘቱን የግልግል ጉባኤው ዳኞች በግራ ቀኙ በኩል የቀረበውን ክርክርና ማስረጃ በመርመርና በመመዘን ያረጋገጡት ፍሬ ነገር ነው፡፡

8. አመልካች የቅድመ ክፍያ ዋስትና ሰናድ የሰጠው ሰባተኛው ተጠሪ የዕቃ አቅርቦት ውሉን በአግባቡ ባለመፈፀሙ ለውሉ አለመፈፀምና ውሉ በአግባቡ ባለመፈጸሙ ምክንያት ፈራሽ ለመሆኑ ኃላፊነት ያለበት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች የዕቃ አቅርቦት ውሉ በአቅረቢው (ሰባተኛ ተጠሪ) ባለመፈፀሙ ምክንያት በኃላፊነት ልጠየቅ አይገባኝም በማለት ያቀረበው ክርክር የሰጠው የዋስትና ሰነድ የሚያስከትለውን ህጋዊ ውጤት ያላገናዘበና የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡ አመልካች ስማቸው ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ተራ ቁጥር የተገለጹት ተጠሪዎች የዕቃው ማቅረቢያ ጊዜ እስከ ሀምሌ 25 ቀን 1993 ዓ/ም ያራዘሙ በመሆኑ ተጠያቂነት ያለብኝም በማለት ያቀረበው ክርክርም አመልካች ነሐሴ 28 ቀን 1991 ዓ/ም የሰጠውን የዋስትና ሰነድ ለማደስ ጥቅምት 19 ቀን 1994 ዓ/ም የተጻፈ የዋስትና ሰነድ የሰጠ በመሆኑና አመልካች ጥቅምት 19 ቀን 1994 ዓ/ም የተጻፈ የዋስትና ሰነድ የሰጠው በመጀመሪያው ውል የተገለፀው የዕቃ ማቅረቢያ ጊዜ የተራዘመ መሆኑን እያወቀ በመሆኑ ክርክሩ የህግ ድጋፍ ያሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የዕቃ አቅረቢው (ሰባተኛ ተጠሪ) በውሉ መሠረት ላላቀረበው የቢሮ ዕቃ አመልካች በሰጠው የዋስትና ሰነድ መሠረት በአንድናትና በነጠላ ኃላፊነት አለበት በማለት የግልግል ጉባኤው የሰጠው ውሳኔን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

9. በዚህ ሰበር ችሎት ሊታይ የሚገባውና አከራካሪ የሆነው ጭብጥ የእቃው አቅረቢ የነበረው (ሰባተኛው ተጠሪ) የውል ግዴታውን ባለመፈጸሙ ምክንያት አመልካች ስማቸው ከተራ ቁጥር 1 እስከ ተራ ቁጥር 6 ለተገለፀው ተጠሪዎች ከዋናው ባለዕዳ ጋር በአንድነትና በነጠላ ለመክፈል የሚገደደው ምን ያህል ነው የሚለው ነጥብ ነው፡፡ የዕቃው አቅረቢ በቅድመ ክፍያነት ከወሰደው ገንዘብ ውስጥ የብር 394740 (ሶስት መቶ ዘጠና አራት ሺህ ሰባት መቶ አርባ ብር) ዋጋ ያላቸውን የቢሮ ዕቃዎች ያላቀረበ በመሆኑ አመልካች ከዋናው ባለዕዳ ጋር በአንድናትና በነጠላ ይህንን ገንዘብ እንዲከፍል የግልግል ዳኞች የሰጡት ውሳኔ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

10. የወለድ ክፍያን በተመለከተ በመጀመሪያ የስር ከሳሾች ስልጣን ለሌላው ፍርድ ቤት ክስ አቅርበው ወደ ግልግል ዳኞች ጉዳያቸውን እንዲያቀርቡ የተወሰነ መሆኑን ጉዳዩ ለግልግል ጉባኤ ቀርቦ ላይቶ መጋቢት 13 ቀን 2003 ዓ/ም በግልግል ዳኞች ጉባኤ ውሳኔ አግኝቶ የነበረ መሆኑንና የስር ከሳሾች መጥሪያ ለአመልካች በአግባቡ አለማድረሳቸውን በማረጋገጥ የግልግል ዳኞች መጋቢት 13 ቀን 2003 ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 01-82566 ሀምሌ 11 ቀን 2004 ዓ/ም የሻረው መሆኑ ተረጋግጧል። ይህ ከሆነ አመልካችን በተመለከተ ወለድ መክፈል የሚገባው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ ከሰጠበት ከሀምሌ 11 ቀን 2004 ዓ/ም ጀምሮ የሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ታስቦ መሆን ሲገባው የግልግል ጉባኤው ክሱ መደበኛ ፍርድ ቤት ከቀረበበት ቀን አንስቶ የሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ አመልካች ለዋናው ባለ ዕዳ (ሰባተኛ ተጠሪ) ጋር በአንድናትና በነጠላ ይክፈል በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሀምሌ 11 ቀን 2004 ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔ ህጋዊ ውጤት ያላገናዘበና በከፊል መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል።
11. መቀጫውን በተመለከተ የስር ከሳሾችና የእቃው አቅራቢ ሀምሌ 12 ቀን 1991 ዓ/ም በተዋዋሉት ውል አንቀጽ 6 መሠረት ውሉ ባለመፈፀሙ 0.07 መቀጫ በቀን ታስቦ የሚከፈለው እስከ ሰባ ቀናት ድረስ ብቻ እንደሆነ በግልፅ ተመልክቷል። ይህ ከሆነ አመልካች ዋናው ባለዕዳ በቅድመ ክፍያነት ወስዶ በውሉ አግባብ ያልፈጸመውን የብር 394,740 (ሶስት መቶ ዘጠና አራት ሺህ ሰባት መቶ አርባ ብር) መቀጫ በቀን 0.07% ታስቦ ለሰባ ቀናት ብቻ መቀጫ የመክፈል ግዴታ ይኖርበታል። ከዚህ ውጭ የግልግል ጉባኤ ዳኞች አመልካች 0.07 ፐርሰንት መቀጫ ለመደበኛ ፍርድ ቤት ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ዕዳው ተከፍሎ እስከሚያልቅ ድረስ እንዲከፍል የሰጡት ውሳኔ ያውሉን አንቀፅ 6 የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1889 እና የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1924 ድንጋጌዎች መሰረት ያላደረገና በከፊል መሠረታዊ የህግ ስህታት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል።
12. ከላይ በገለፀናቸው ምክንያቶች የግልግል ዳኞች ጉባኤ አመልካችን በተመለከተ የሰጠውን ውሳኔ በከፊል በማሻሻል።

(ሀ) አመልካች ዋናው ባለዕዳ (ሰባተኛ ተጠሪ) በቅድመ ክፍያነት ወሰዶ ዕቃውን በውሉ መሠረት ባለመቅረቡ ለከሳሾች መመለስ የሚገባውን ብር 394740 (ሶስት መቶ ዘጠና አረት ሺ ሰባት መቶ አርባ ብር) ከዋናው ባለዕዳ ጋር በአንድነትና በነጠላ ሊከፍል ይገባል በማለት ወስነናል።

(ለ) አመልካች ከዋናው ባለዕዳ ጋር እንዲከፍል የተወሰነበትን ብር 394,740 (ሶስት መቶ ዘጠና አራት ሺ ሰባት መቶ አርባ ብር) የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሀምሌ 11 ቀን 2004 ዓ/ም ውሳኔ

ከሰጠበት ጊዜ ጀምሮ የሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ በአንድነትና በነጠላ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

(ሐ) አመልካች ዋናው ባለዕዳ መመለስ ያለበትን ብር 394,740 /ሶስት መቶ ዘጠና አራት ሺ ሰባት መቶ አርባ ብር) በቀን 0.07% መቀጫ ታስቦ በሰባ ቀናት ተባዝቶ የመክፈል ግዴታ አለበት በማለት የግልግል ዳኞች የሰጡትን ውሳኔ በፍ/ስ/ስ/ህግ ቁጥር 348 (1) መሠረት በማሻሻል ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የግልግል ጉባኤ ዳኞች ሀምሌ 7 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጡት ውሳኔና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 01-38894 ጥቅምት 25 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች በዚህ ፍርድ በተራ ቁጥር 12 ከ"ሀ" እስከ "ሐ" የተገለፀውን ገንዘብ ከዋናው ባለዕዳ /ሰባተኛ ተጠሪ/ ጋር በአንድናትና በነጠላ የመክፈል ኃላፊነት አለበት በማለት ወስነናል፡፡
3. የግልግል ጉባኤ ዳኞች ዋናው የፍርድ ባለዕዳ (ሰባተኛ ተጠሪ) በተመለከተ የሰጡት ውሳኔ በዚህ ሰበር ችሎት የልተያ በመሆኑ አልተነካም፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ግራ ቀኙ ያወጡትን ወጭና ኪሳራ ለያረሳቸው ይቻሉ፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ጥር 5 ቀን 2007 ዓ/ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ የዕግድ ትዕዛዝ የተነሳ መሆኑን እንዲታወቅ ለሚመለከተው ክፍል ይጻፍ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

የሰ/መ/ቁ.113013

ሚያዚያ 25 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡- ወ/ት ማሕሌት እንዳለ አልቀረቡም

ተጠሪ፡-1.አቶ አህመድ አለም } አልቀረቡም

2.ወ/ሮ ዘይነባ አብደላ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አፈጻጸምን የሚመለከት ነው፡፡በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር አመልካች የመቃወም አመልካች፤ተጠሪዎች ደግሞ እንደ የቅደም ተከተላቸው የፍርድ ባለመብት እና የፍርድ ባለዕዳ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሠረት ያቀረቡት የመቃወም አቤቱታ ይዘት በአጭሩ የአፈጻጸም ትዕዛዝ የተሠጠበት በኮልፌ ቀራንዩ ክ/ከተማ ቀበሌ 05 በደብረአባይ ቁጥር 1 እና 2 ራሥ አገዝ የመኖሪያ ቤቶች ሕብረት ሥራ ማሕበር በ175 ካ.ሜ ላይ የሚገኘውን ቤት ግንቦት 01 ቀን 1998 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል የገዙት መሆኑን በመግለጽ ተከራካሪ ሳይሆኑ በቤቱ ላይ የተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ መብታቸውን የሚጎዳ በመሆኑ ይሻርላቸው ዘንድ ዳኝነት የጠየቁ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ተጠሪዎች በጉዳዩ ላይ አስተያየት እንዲሰጡበት ትዕዛዝ የተሰጠ ቢሆንም 2ኛ ተጠሪ መጥሪያ ደርሷቸው ስላልቀረቡ ፍ/ቤቱ አስተያየት የመስጠትመብታቸውን አልፎታል፡፡1ኛ ተጠሪ በሰጡት መልስ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ በቂ ምክንያት የሌለው መሆኑን፤አመልካች ቤቱ በዕዳ መያዙን እያወቁ ዘግይተው ያቀረቡት አቤታታ ከቅን ልቦና ውጪ የቀረበ በመሆኑአቤቱታቸው ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የአፈጻጸም ችሎቱ የግራቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ አመልካች ቤቱን ገዝቸዋለሁ በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም ያቀረቡት የሽያጭ ውሉ ሥልጣን ባለው አካል ፊት ያልተመዘገበ በመሆኑ በፍርድ ባለመብት ላይ የመቃወሚያ መሠረት ሊሆን አይችልም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ አድርጎታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት  አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ አከራካሪው ቤት የማሕበር ቤት በመሆኑ ለጉዳዩ አወሳሰን ተፈጻሚነት ያለው ሕግ ሥለ ሕብረት ሥራ ማሕበራት አደረጃጀት እና አሥተዳደር የሚደነግገው አዋጅ ቁጥር 147/91 ነው፤የዚህ ሕግ አንቀጽ 19/1/ለ በማሕበሩ ውስጥ በተሠራ ቤት ላይ መብት ያገኘ ሠው ይህንኑ መብቱን ለሌላ ሠው ለማሥተላለፍ ቢፈልግ ከማሕበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ ፈቃድ ማግኘት እንደሚኖርበት ይደነግጋል፤የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም በመ.ቁ 36294 ይህንኑ በመጥቀስ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፤አመልካች ያቀረቡት የሽያጭ ውል የማሕበሩ ሥራ አመራር ኮሚቴ ፈቅዶ ያስተላለፈው መሆኑን፤የመተካካት ሥርዓቱም በማሕበሩ ዘንድ የተመዘገበ እና አግባብ ባለው አደራጅ መሥሪያ ቤት እንዲመዘገብ የተላለፈ ሥለመሆኑ የሚያስረዳ አይደለም፤በሰነዱ ላይ የማሕበሩ ማሕተም አርፎ መገኘቱ ብቻውን ሕጉ በሚጠይቀው አሠራር የመብት ማስተላለፍ ሒደት መከናወኑን የሚያረጋግጥ አይደለም፤ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የተቻለውም 2ኛ ተጠሪ የቤቱን ሥመሐብት ወደ አመልካች ሣያዞሩ እየኖሩበት የሚገኙ መሆናቸውን በመሆኑ በ2ኛ ተጠሪ ሥም በሚታወቅ ቤት ላይ በመንደር የቤት ሽያጭ ውል መብት አግኝቸበታለሁ በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም በማለት የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በውጤት ደረጃ ተቀብሎ አጽንቶታል፡፡የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡-ማሕበሩ የሽያጭ ውሉን ተቀብሎት አመልካችም በ2ኛ ተጠሪ ምትክ ተተክቼ ማሕበሩ የሚጠይቀውን ተገቢውን ክፍያ እየከፈልኩ የማሕበሩ አባል ሆኘ እንድቀጥል ፈቅዶልኝ ውሉ በማሕበሩ ከገባበት ከ1998 ዓ.ም ጀምሮ በቤቱ እየኖርኩበት እገኛለሁ፤በአሁኑ ሰዓትም ማህበሩ ካርታ በሥሜ እንዲዘጋጅ አድርጎልኝ የፍ/ቤት ክርክር አለበት የተባለ በመሆኑ ተቀምጦ ይገኛል፤ማሕበሩ ይህን እውነታ ያሳወቀኝ የይግባኝ ክርክሩ ከተደረገ በኋላ ነው፤አከራካሪው ቤት በክፍለ-ከተማውም ሆነ በማሕበሩ ተመዝግቦ የሚገኘው በአመልካች ሥም እንጂ በ1ኛ ተጠሪ ሥም አይደለም፤የማሕበሩ ማሕተም አርፎበት ከማሕበሩ የተላከው ውልም የሚያሣየው አመልካች እና ሁለተኛ ተጠሪ ያደረግነው የቤት ሽያጭ ውል የጸና መሆኑን ነው፤በማሕበሩ ትዕዛዝ በሥሜ ካርታ ተሠርቶ እያለ 1ኛ ተጠሪ ካርታው ሊሰጥ አይገባም ብለው በመከራከራቸው እንዳይሰጠኝ የተደረገ መሆኑ እየታወቀ አፈጻጸሙ እንዲቀጥል በማለት የተሠጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል

ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የአመልካችን ውል የሕብረት ሥራ አመራሮች ፈቅደው ያልተቀበሉት በመሆኑ አመልካች መቃወሚያ ማቅረብ አትችልም በማለት ውሳኔ የመስጠቱን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡እኛም የግራቀኙን ክርክር እንዲጣራ ከተያዘው ነጥብ እና ለጉዳዩ አወሳሰን አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች ለዚህ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክርክር አከራካሪው ቤት በክፍለ-ከተማውም ሆነ በማሕበሩ በአመልካች ሥም ተመዝግቦ ይገኛል፤ ከማሕበሩ የተላከው እና የማሕበሩ ማሕተም ያረፈበት ውልም የሚያሣየው ይህንኑ ነው፤በማሕበሩ ትዕዛዝ በሥሜ ካርታ ተሠርቶ 1ኛ ተጠሪ ካርታው ሊሰጥ አይገባም ብለው በመከራከራቸው እንዳይሰጠኝ ተደርጓል በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም ይህን ፍሬነገር በመግለጽ በበታች ፍ/ቤቶች የተከራከሩ ለመሆኑ የክርክሩ ሒደት አያሳይም፡፡የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 329/1 በበታች ፍ/ቤቶች ያልቀረበን አዲስ ክርክር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መቀበል የለበትም በማለት የሚደነግግ በመሆኑ አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀረቡትን አዲስ ክርክር አልተቀበልነውም፡፡ አመልካች በበታች ፍ/ቤቶች የተከራከሩት የአፈጻጸም ትዕዛዝ የተሠጠበትን ቤት ግንቦት 01 ቀን 1998 ዓ.ም በተደረገ ውል ከ2ኛ ተጠሪ የገዙ መሆናቸውን በመግለጽ መሆኑን፤በማስረጃነት ያቀረቡት ውልም ግንቦት 01 ቀን 1998 ዓ.ም ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ተፈጽሟል ያሉትን የመንደር ውል መሆኑን፤የአፈጻጸም ትዕዛዝ የተላለፈበት በኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቀበሌ 05 በደብረአባይ ቁጥር 1 እና 2 ራሥ አገዝ የመኖሪያ ቤቶች ሕብረት ሥራ ማሕበር በ175 ካ.ሜ የሚገኘው ቤት የማሕበር ቤት መሆኑን፤አመልካች ባቀረቡት የሽያጭ ውል ላይ የማሕበሩ ማሕተም አርፎ መገኘቱ ብቻውን የመብት ማስተላለፉ የማሕበሩ ሥራ አመራር ኮሚቴ ፈቅዶ ያስተላለፈው ስለመሆኑ እና የመተካካት ሥርዓቱም በማሕበሩ ዘንድ ተመዝግቦ አግባብ ባለው አደራጅ መሥሪያ ቤት እንዲመዘገብ የተላለፈ ሥለመሆኑ የማያሳይ መሆኑ ፍሬነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ሥልጣን ባላቸው የበታች ፍ/ቤቶች ተረጋግጧል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 36294 ሰዎች በመደራጀት ያቋቋሟቸው የሕብረት ስራ ማህበራትን በተመለከተ የተደነገገው የህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 147/91 ስለማሕበራቱ ዓላማ፣ ስለማሕበራቱ አመሠራረት፤ስለሚመሩባቸው መርሆዎች፣ ስለሕግ ሰውነትና ኃላፊነት፤ስለመተዳደሪያ ደንብ፣ ወዘተ በተመለከተ ዝርዝር ድንጋጌዎችን ያካተተ መሆኑን፤የአዋጁ አንቀጽ 19 የማህበሩ አባል ዕጣውን ወይም ጥቅሙን ለማስተላለፍ

እንደሚችል፣የማስተላለፉ ሁኔታም የራሱ የሆነ የተለየ ስርዓት እንዳለው፣የማህበሩ አባል ዕጣውን ወይም ጥቅሙን ለማስተላለፍ ቢፈልግ ከማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ ፈቃድ ማግኘት እንደሚኖርበት፣በማህበር ተደራጅቶ የተገኘውን መብት የማስተላለፊያ ስርዓቱ በግል ከተገኘ መብት የተለየ መሆኑን፣መብት የሚተላለፍለት ወገንም በአስተላላፊው መብት መጠቀም የሚችለው በመተካት የማህበሩ አባል መሆን ከቻለ ብቻ መሆኑን፣ይህ የማስተላለፍ ሥርዓት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 ከተመለከተው የማይንቀሣቀስ ንብረት መብት ማስተላለፊያ ስርዓት የተለየ መሆኑን፣በማህበር በመደራጀት የተሠራውን ቤት ሽያጭ ውል በፍ/ብ/ሕግ/ቁ 1723 ከተመለከተው ድንጋጌ ጋር አያይዞ ማየቱ ትክክል እንዳልሆነ እና በማህበሩ ያለውን መብት ማስተላለፍን በተመለከተ ከአዋጅ ቁጥር 147/91 አንፃር መታየት ያለበት መሆኑን በመግለጽ በየትኛውም እርከን ላይ ላሉ ፍ/ቤቶች አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሠጥቶበታል፡፡

የሰበር ሰሚ ችሎቱ ይህን የሕግ ትርጉም ከሠጠ በኋላ የሕብረት ሥራ ማሕበራት አዋጅ ቁጥር 147/91 ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 402/96 የወጣ ቢሆንም ተሻሽሎ የወጣው አዋጅ የአዋጅ ቁጥር 147/91 አንቀጽ 19 ድንጋጌን በተመለከተ ያሻሻለው ነገር የለም፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ገዝቸዋለሁ የሚሉትን የማሕበር ቤት በአዋጅ ቁጥር 147/91 መሠረት ከማሕበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ ፈቃድ አግኝተው እና በመተካት የማሕበሩ አባል ሆነው የተላለፈላቸው መሆኑን በመግለጽ በበታች ፍ/ቤቶች ያቀረቡት ክርክርም ሆነ ማስረጃ ሥለሌለ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ጉዳዩን በአዋጅ ቁ 147/91 እና ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሠረት በማድረግ የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በውጤት ደረጃ ተቀብሎ ማጽናቱ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 163565 መጋቢት 11 ቀን 2006 ዓ.ም ተሰጥቶ፣በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 150823 የካቲት 25 ቀን 2007 ዓ.ም በፍርድ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸወን ይቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ፍ

የሰ/መ/ቁ. 117953

ሚያዚያ 30 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገብሩ

ቀነዓ ቂጣታ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- አቶ ሰብስቤ አበበ  ከጠበቃ እንድሪያስ ተፈራ ጋር ቀርበዋል

ተጠሪ፡ ወ/ሮ ፍቅርተ ካህሳይ ጠበቃ ወርቁ ገበየሁ ቀርበዋል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ የኮንዶሚኒየም ቤት ለማስለቀቅ የቀረበ ክስን መነሻ ያደረገ ክርክር ሲሆን፣ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.170075 ሐምሌ 20 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት የአሁን አመልካች ያቀረበዉን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን ተጠሪ ከሳሽ፣ የአሁን አመልካች የሥር ተከሳሽ ሆኖ ሲከራከሩ የነበረ ሲሆን፣ ከሳሽ ባቀረቡት ክስ ሟች ልጄ ዘዉዱ አስራት በሕይወት በነበረ ጊዜ በአዲስ አበባ ከተማ ባልቻ ሜዳ ሳይት ቀበሌ 05/08 የሕንጸ ቁጥር ቢ1 የቤት ቁጥር 11 የወለል ስፋት 48.79 ካ.ሜ ባለ ሁለት መኝታ መኖሪያ ቤት የነበረዉ ስለሆነ ተከሳሽ ሟች ልጄ ከሞተ በኋላ ባዘጋጀዉ ሐሰተኛ እና የሕጉን ፎርም ባልተጠበቀ ዉል ቤቱን ይዘው ስላሉ ቤቱን ለቀዉ እንዲያስረክቡኝ በማለት ከሷል፡፡

የሥር ተከሳሽ ባቀረበዉ መልስ ሟች ይህን ቤት በወለድ አግድ ዉል አስይዞ ብር 350000 ተበድረዉ ገንዘቡን መመለስ ካልቻሉ መንግስት ቤቱን ለመሸጥ ያስቀመጠዉ የጊዜ ገደብ ሲያበቃ ቤቱን ለእዳዉ መክፈያ እንዲሆን እና ባለቤትነቱን ወደ ተከሳሽ ስም ለማዘዋወር ተስማምተናል ዉል ፈርመናል፡፡ በዉሉ ላይ ያለዉ ፊርማ የሟች ስለመሆኑ በፎረንሲክ ተመርምሮ ሊረጋገጥ ይችላል፡፡ ስለዚህ ከሳሽ ቤቱን ለመረከብ ያቀረቡት ክስ ዉድቅ ነዉ በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ ተከሳሽ ይህን ቤት በወለድ አግድ ዉል ይዤአለሁ ይበሉ እንጂ በፍትሐብሐር ሕጉ በተመለከተዉ አግባብ ዉሉን የማይንቀሳቀስ ንብረት

መዝገብ ላይ ስለማስመዝገባቸዉ ያቀረቡት ማስረጃ ስለሌለ የወለድ አግድ ዉል ተቋቋሚል ለማለት ስለማይቻል ቤቱን ለከሳሽ ሊያስረክብ ግዴታ አለባቸዉ በማለት ወስኗል፡፡

የሥር ተከሳሽ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ይግባኙን ዉድቅ በማድረግ የሥር ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች ጳጉሜ 4 ቀን 2007 ዓ.ም የተጻፈ አራት ገጽ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የአቤቱታዉም ይዘት በአጭሩ ሟች ዘዉዱ አስራት ከአመልካች ገንዘብ ተበድረዉ ቤቱን ማስያዛቸዉን ምስክሮች አስረድተዋል፣ ዉሉም በልደታ ክ/ከተማ የይዞታ አስተዳደር ዉስጥ መያያዙን ለፍ/ቤቱ በተላከዉ ደብዳቤ ተረጋግጧል፣ አመልካች ቤቱን የያዝኩት ያለአግባብ ሳይሆን በወለድ አግድ ዉል በመያዝ ቤቱና ሰነዶቹን ተረክቤ እያለሁ፣ የሥር ፍ/ቤቶች አመልካች ቤቱን ለተጠሪ እንዳስረክብ የሰጡት ዉሳኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት በዝርዝር አመልክቷል፡፡

የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩን በማየት ፣በአመልካችና በተጠሪዋ አዉራሽ መካከል ሰኔ 30 ቀን 1999 ዓ.ም ተደርጓል የተባለዉ የወለድ አግድ ዉሉን አከራካሪዉ ቤት በሚገኝበት ማዘጋጃ ቤት ከሚመለከተዉ ማህደር ጋር በወቅቱ እንዲያያዝ እንደተደረገ መሆኑን ማዘጋጃ ቤቱ ግለጾ እያለ የሥር ፍ/ቤት በዚህ ዉል ሊይዙ አይችሉም በማለት ቤቱን ለተጠሪዋ እንዲያስረክቡ የመባሉን አግባብነት፣ ለመመርመር ሲባል አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ በታዘዘዉ መሰረት ህዳር 7 ቀን 2008 ዓ.ም የተጻፈ አምስት ገጽ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡- የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔ የሚነቀፍበት ምንም የሕግ ምክንያት ስለሌለ እንዲጸናልኝ በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኛቸዉን ክርክር ለሰበር አቤቱታዉ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነዉ የአሁን ተጠሪ ባቀረቡት ክስ ተከሳሽ ከሳሽን የሚያስገድድ ዉል ሳይኖር በሐሰተኛ ዉል እና የሕጉን ፎርም ባልጠበቀ ዉል የሟች ልጄ ንብረት የሆነዉን የኮንዶሚኒየም ቤት ይዞ ስለሚገኝ ቤቱን ለቀዉ እንዲያስረክበኝ በማለት የከሰሱ ሲሆን፤ የአሁን አመልካች በበኩሉ ባቀረበዉ መልስ ሟች በሕይወት በነበረበት ወቅት ሰኔ 30 ቀን 1999 ዓ.ም ወለድ አግድ ዉል ቤቱን አስይዞ ብር 350000 ተበድረዉ ቤቱን እና ሰነዱን ስላስረከበኝ የቀረበዉ ክስ ተቀባይነት የለዉም የሚል ነዉ፡፡ ከዚህ አንጻር የአሁን አመልካች ከሟች ጋር ይህ ዉል ተዋዉለናል ባሉበት ወቅት በሕግ የተቀመጠ በኮንዶሚኒየም ቤት በተመለከተ ዉል የማድረግ ክልከላ ጊዜ ሳያልቅ መሆኑን አመልካች ራሳቸዉ ባቀረቡት ክርክር ያረጋገጡት ጉዳይ ነዉ፡፡

በመሆኑም በሕግ የተቀመጠ ክልከላ እያለ በዚህ ኮንዶሚኒያም ላይ የተደረገ ዉል ሕግን የሚቃረን እስከሆነ ድረስ ፍ/ቤት ለዚህ ዉል ዋጋ በመስጠት አመልካች በሕግ ፊት ዋጋ ባለዉ ዉል ቤቱን ይዟል ለማለት የሚቻልበት አግባብ የለም፡፡

ከዚህም በላይ የአሁን አመልካች ቤቱን በወለድ አግድ ይገፍለሁ እያለ ስለሆነ በሕግ ፊት ዉጤት ያለዉ ዉል አለ ወይስ የለዉም? የሚለዉም ነጥብ መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ፡፡ ወለድ አግድን በተመለከተ የፍትሐብሐር ሕግ ቁጥር 3117--3130 ሥር ተመልክቷል፡፡ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.3117 እንደሚደነግገዉ ‹‹ወለድ አግድ ማለት አንድ ባለዕዳ ግዴታዉን ለመፈጸም ማረጋገጫ በማድረግ ለገንዘብ ጠያቂዉ የማይንቀሳቀስዉን ንብረት ለማስረከብ የሚገደድበት ዉል ነዉ›› በማለት ደንግጎታል፡፡ የወለድ አግድ ዉልን ለማቋቋም የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣን መቋቋም የሚመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት እንዳላቸዉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.3118 ተመልክቷል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ ዉል የሚያቋቋሙት ድንጋጌዎች ማየቱ አስፈላጊ ነዉ፡፡ በዚህ መሰረት የፍ/ብ/ሕ/ቁ.3052 እንደሚያመለክተዉ ይህ ዉል ከተደረገበት ቀን ጀምሮ በማይንቀሳቀስበት ሀብት መዝገብ ካልተጻፈ ምንም ዓይነት ዉጤት እንደሌለዉ ነዉ፡፡ ይህ የምዝገባ አፈጻጸም ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.3053 ሥር ተመልክቷል፡፡ የአሁን አመልካች ይህን የወለድ አግድ ዉል አደርገናል የሚለዉን ዉል በዚህ አግባብ የማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ እንዳልተመዘገበ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር ነዉ፡፡ የአሁን አመልካች በዚህ አግባብ ተፈጽሟል እና የሰበር አጣሪ ችሎትም እንደጭብጥ አድርጎ የያዘዉ ይህ ዉል በቤቱ ማህደር ዉስጥ መገኘቱን ነዉ፡፡ ነገር ግን ይህ ዉል መቼ የቤቱ ማህደር ዉስጥ እንደተገኘ እና ይህ በሕጉ የተመለከተዉን የምዝገባ ሥርዓት ያሟላ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉ ነጥብ መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ፡፡

በዚህ ረገድ የልደታ ክ/ከተማ ይዞታ አስተዳደር ጽ/ቤት ለሥር ፍ/ቤት በጻፈዉ ደብዳቤ ከሳሽ የቤቱ ስመ ሀብት ከሟች ወደ እሳቸዉ እንዲዛወርላቸዉ ጠይቀዉ፣ ነገር ግን ካርታ ጠፋኝ ስላሉ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ በ4/2/2004 ዓ.ም ታዉጆ፣ አመልካች በ25/3/2004 ዓ.ም የስም ዝዉዉር ቢደረግ መብቴን ይነካል በማለት በማመልከቱ በዚህ ምክንያት ከማህደሩ ጋር እንደተያያዘ ገልጸዋል፡፡ ከዚህ መገንዘብ እንደሚቻለዉ የአሁን አመልካች ይህን ዉል ከላይ በተመለከተዉ የሕግ ድንጋጌዎች አግባብ ዉሉ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ የማይንቀሳቀስ ንብረት መዝገብ መመዝገቡን የሚያመለክት አይደለም፡፡ ይህ ዉል ለክርክር ምክንያት በሆነዉ ኮንዶሚኒያም ቤት ላይ የተደረገዉ በሕግ የተቀመጠዉ ክልከለ ባለበት ሁኔታ ስለሆነ የልደታ ክ/ከተማ ይዞታ አስተዳደር ጽ/ቤት ዉሉን ይመዘግባል ተብሎም አይገመትም፡፡ በመሆኑም በሕግ ፊት የሚጸና የወለድ አግድ ዉል በአመልካች እና በሟች ዘዉዱ አስራት መካከል ተደርጓል ለማለት አይቻልም፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች በአመልካች እና በሟች መካከል በሕግ ፊት የጸና የወለድ አግድ ዉል መደረጉን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ስለሌለ አመልካች ቤቱን ያለ አግባብ ይዞ ስለሚገኝ ቤቱን ለተጠሪ እንዲያስረክብ መወሰናቸዉ በሕጉ አግባብ ነዉ ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ የሚከተለዉ ተወስኗል፡፡

ዉ ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ.191279 በ12/10/2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህን በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.170075 ሐምሌ 20 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመባቸዉ ስለሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.348 /1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ዉሳኔ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኛቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉ ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
4. በ15/2/2007 ዓ.ም የተሰጠ የአፈጻጸም እግድ ትዕዛዝ በዚህ ዉሳኔ ተነስቷል፡፡ ይጻፍ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

# ከውል ውጭ ኃላፊነት

የሰ/መ/ቁ. 127587

ሚያዝያ 16 ቀን 2009 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጸውሎስ ኦርሺሶ

ሰናይት አድነው

**አመልካች፡-** ፐርፌክት ትራንዚትና ትራንስፖርት ኃላ/የተ/የግ/ ማኅበር - አልቀረበም

**ተጠሪ፡-** አቶ አህመድ ዳውድ ( አቶ አህመድ ሁሴን ወኪል) - አልቀረበም

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ ያለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው የአሁኑ አመልካች ሚያዝያ 28 ቀን 2008 ዓ/ም በተጻፈ አቤቱታ የአውሲረሱ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/መ/ቁ. 4627 ታኅሳስ 27 ቀን 2008 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይ/መ/ቁ. 4105 መጋቢት 13 ቀን 2008 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት ዳኝነት በመጠየቁ ነው፡፡

የክርክሩ መነሻ ንብረትነቱ የአመልካች የሆነ የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3- 30303 ኢት የተሳቢ ቁጥር 09839 ከባድ ተሽካርካሪ መኪና ከጅቡቲ አዲስ አበባ በመጓጓዝ ላይ እያለ በአፋር ክልል ዲቻአቶ ተብሎ በሚታወቀው ቦታ በደረሰው ግጭት ንብረትነቱ የተጠሪ በሆነ መኪና ላይ ጉዳት በመድረሱ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በመኪናው ላይ ለደረሰበት ጉዳት ብር 350.000.00 /ሶስት መቶ ሃምሳ ሺ.ህ/፤ መኪናው የሚንቀሳቀስበት ከፒታል ቢያንስ ከአደጋው በኃላ ሶስት ዙር ሽያጭ ተካሂዶበት ሊገኝ የሚችለው በአንድ ዙር ብር 20.000.00 /ሃያ ሺ.ህ ብር/ x የ3 ዙር 60.000.00 /ስልሳ ሺ.ህ/ ብር፣ መኪናው አደጋው በደረሰበት ቦታ ከአንድ ወር በላይ አመልካች በ3ኛ ወገን ኢንሹራንስ አስገምታለሁ ብሎ ሲያጉላላ በዘብ ለማስጠበቅ ብር 5.000.00 /አምስት ሺ.ህ ብር/፣

የትራንስፖርት ማስጫኛና ማውረጃ ለሰራተኛ 1000.00 /አንድ ሺህ/ ብር እንዲሁም በዚህ ጉዳይ አደጋው ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ያወጣሁት የአልጋ፣ የምግብና የትራንስፖርት ወጪና ኪሳራ ብር 20.000.00 /ሃያ ሺህ/ እንደሆነ ገልጾ በድምሩ 441.000.00 /አራት መቶ አርባ አንድ ሺህ/ ብር አመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል ሲል ዳኝነት ጠይቋል፡፡

አመልካችም በበኩሉ በተጠሪ መኪና ላይ ለደረሰው ጉዳት ለአመልካች የመድን ሽፋን የሰጠው ሕብረት ኢንሹራንስ ኩባንያ የጉዳቱን ካሳ ለመክፈል ወይም እንደአስፈላጊነቱ መኪናውን ለማስጠገን ዋስትና ሰጥቶ እያለ ተጠሪ አመልካች ለጉዳቱ ዋስትና አላቀረበም በማለት በተሳሳተ መንገድ የመዳኘት ሥልጣን ለሌለው አፋር ክልል አልዳአር ወረዳ ፍርድ ቤት የእግድ ትዕዛዝ በማሰጠት የአመልካች መኪና እንዳይንቀሳቀስ ከሶስት ወራት በላይ እንዲቆም በማድረጉ አመልካች በዚህ ምክንያት የተቀቋረጠበትን አንድ ወር ገቢ 50.000.00 /አምሻ ሺህ/ ብር የሶስት ወር 150.000.00 /አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ/ ብር እንዲከፍል ሲል የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርቧል፡፡

ሁለቱንም ክሶች የተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን እና የጣልቃ ገቡን የህብረት ኢንሹራንስ አክሲዮን ማኀበር ክርክር ፣ የምስክሮችን ቃል እንዲሁም የሰነድ ማስረጃን መርምሮ የአሁኑን አመልካች የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ውድቅ በማድረግ የአሁኑ አመልካች ለአሁኑ ተጠሪ የመኪናውን ግምት 350.000.00 /ሶስት መቶ ሃምሳ ሺህ/ ብር፣ የተቋረጠ የሶስት ወር ገቢ 60.000.00 /ስልሳ ሺህ/ ብር፣ ለመኪናው ጥበቃ የተከፈለውን 5.000.00 /አምስት ሺህ/ ብር በድምሩ 415.000.00 /አራት መቶ አስራ አምስት ሺህ/ ብር ከ10% የጠበቃ አበል እንዲሁም ዳኝነት በታርፍ መሠረት እና ሌሎች ወጪዎች ካሉ ዝርዝር የማቅረብ መብት ለረቺ ጠብቀናል በማለት ወስኗል፡፡

ይህን ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይግባኙን ተቀብሎ የግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የሥር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ለማስለወጥ ሲሆን የአቤቱታ ይዘቱም በአጭሩ፡-

1. ፍርድ ቤት በገለልተኛ ባለሙያ የተገመተው ግምት እያለ በፖሊስ ግምት ተመስርቶ 350.000.00 /ሶስት መቶ ሃምሳ ሺህ/ ብር የጉዳት ከሳ መወሰኑ ያለአግባብ ነው፡፡
2. ተጠሪ የተቋረጠበት 60.000.00 /ስልሳ ሺህ/ ብር እንዲሁም ለጥበቃ የወጣ ወጪ ብር 5000.00 /አምስት ሺህ/ እንዲከፈለው የሥር ፍርድ ቤት ከመወሰኑ ወጪ  አንዳችም

ማስረጃ ሳይቀርብ የሰጠው ውሳኔ አቤቱታን ሳይሆን ማስረጃን መሠረት አድርጎ የመወሰን መሠረታዊ መርህን የተጻረረ ፍጹም የዳኝነት ግድፈት ነው፡፡

3. ተጠሪ ለጠበቃ ስለመክፈላቸው ያቀረቡት ማስረጃ በሌለበት እና መኪና ወደ ሀገር ቤት እየገባ እያለ በመሆኑ ገቢ ማስገባት ባልጀመረበት ሁኔታ የሥር ፍርድ ቤት የተቋረጠ ገቢ እንዲከፈል መወሰኑ ፍርድ ቤቱ ፍትሓዊ እንዳልሆነ በቂ ማስረጃ ነው፡፡
4. አመልካች በተከሳሽ ከሳሽነት ያቀረበውን ክስ የሥር ፍርድ ቤት ውድቅ ያደረገው በህግ አግባብ አይደለም፡፡

ስለሆነም የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ እንዲሻርልኝ የሚል ነው፡፡

የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ኃላፊነትን በተመለከተ ያቀረቡት ክርክር ባይኖርም የከሳ መጠኑን በተመለከተ ግን ያቀረቡት ክርክር በአግባቡ በሥር ፍርድ ቤቶች ተጣርቶ ውሳኔ የተሰጠበት መሆን ያለመሆኑንና እንዲሁም በአመልካች የቀረበው የተከሳሽ ከሳሽት ክስ ውድቅ ተደርጎ የታለፈበትን አግባብ ለመመርመር ሲባል መዝገቡ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ በቀን 20/01/2009 ዓ/ም የተጻፈ ዝርዝር መልስ አቅርቦ የተከራከረ ሲሆን አመልካቹም ጥቅምት 21 ቀን 2009 ዓ/ም የተጻፈ መልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ እንደተመለከተው ሲሆን ጉዳዩን በሶስት ጭብጮች ከፍለን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

1. ፖሊስ በተጠሪ መኪና ላይ የደረሰውን ጉዳት ገምቶ ለማቅረብ በህግ የተሰጠ ሥልጣን አለው ወይስ የለውም? በዚህ ረገድ የተገመተው ግምት በገለልተኛ ባለሙያ የተገመተ ነው ለማለት ያስችላል ወይስ አያስችልም?
2. አመልካች የተቋረጠበትን ገቢ ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል ወይስ አይገባም? ለመኪና ጥበቃስ የወጣውን ወጪ ሊከፍል ይገባል ወይስ አይገባም?
3. አመልካች በተከሳሽ ከሳሽነት ያቀረበውን ክስ የሥር ፍርድ ቤት ውድቅ ያደረገው በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚሉ ናቸው፡፧

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ በተጠሪ መኪና ላይ በደረሰ ጉዳት ምክንያት ኃላፊነትን መሠረት አድርጎ የተነሳ ክርክር ባይኖርም ጉዳቱን ተከትሎ ሊካስ የሚገባው የካሳ ግምት በግራ ቀኙ መካከል ክርክር ያስነሳ ከሆነ ሊጣራ የሚገባው እንዴት ነው? ግምቱን አጣርቶ የሚያቀርበውስ ማነው? የሚሉ ነጥቦች በቅድሚያ ሊታዩ የሚገባቸው ናቸው፡፡ መኪናው ላይ በደረሰው ጉዳት ከጥቅም ውጪ የሆኑ የመኪና እቃዎች በማንኛውም ምስክር የሚረጋገጡ ሳይሆኑ በዘርፉ እውቀት ባላቸው ባለሙያዎች የሚረጋገጡ እንደሆኑ መረዳት ያስፈልጋል፡፡

እንደዚህ ያሉ ነገሮች በሚከሰቱበት ጊዜ ፍርድ ቤት የፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 136 ድንጋጌን በመከተል ልዩ አዋቂ (ኤክስፐርት) በመሾም እንዲጣራ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ምክንያቱም ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት ያስችል ዘንድ ጉዳዩ በሚመለከው ባለሙያ እንዲጣራ ማድረግ የዳኝነት አካሉ ዋነኛው ተግባር ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ትራፊክ ፖሊስ በመኪናው ላይ የደረሰውን የጉዳት ካሳ ግምት ለማረጋገጥ ሙያው ብቃት መኖር ያለመኖሩን እንዲሁም ለዚህ አካል በህግ የተሰጠውን ሥልጣን ከዋጅ ቁጥር 681/2002 አንጻርመመልከት ተገቢ ነው፡፡ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 2 /25/ እና 37 /2/ /ሐ/ እንደሚያመለክተውየትራፊክ ተግባርና ኃላፊነት ተሽከርካሪዎች በመንገድ ላይ ለመንቀሳቀስ አስፈላጊውን ቴክኒካዊ ብቃት እንዳላቸው መመርመር እና በአደጋው ጊዜ የአደጋውን መንሥኤ ማጣራት እንዲሁም ከአደጋው በኃላ ተሽከርካሪው መንገድ ላይ ለመንቀሳቀስ ቴክኒካዊ ብቃት እንዳለው ማረጋገጥ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ በተሽከርካሪዎች ላይ የደረሰ ጉዳትን በተመለከተ የገበያ ዋጋ አስልቶ ግምት ለማቅረብ በህግ ለትራፊክ ፖሊስ የተሰጠው ተግባርም ሆነ ኃላፊነት የለም፡፡ በሌላ አነጋገር በመኪናው ላይ የደረሰውን ጉዳት ብቻ ሳይሆን ንብረቱ በወቅቱ ለገበያ ቀርቦ ሊያወጣ የሚችለው የገበያ ዋጋ /Market Value/ ገምቶ ለማቅረብ የሚችለው ፖሊስ ሳይሆን በዚህ ዘርፍ በቂ እውቀት፣ ክህሎት እና ሙያ ያለው ሰው ነው፡፤ ስለሆነም በተያዘው ጉዳይ በፖሊስ የቀረበው ግምት መኪናው ላይ የደረሰውን ጉዳት በተመለከተ የገበያ ዋጋን ግምት መጠን በአግባቡ አጣርቶ ለማቅረብ በቂ ሙያዊና ቴክኒካዊ ብቃት ባለው ባለሙያ የቀረበ ግምት ባለመሆኑ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የተሽከርካሪ ዋጋ ግምት የመተመን አገልግሎት መስጠት በአዋጅ ቁጥር 468/97 አንቀጽ 7 /1/ዘ/ መሠረት የትራንስፖርት ባለሥልጣን ስለመሆኑ የሚደነግግ ቢሆንም የገበያ ቃጋን መሰረት አድርጎ እስካልቀረበ ድረስ ተቀባይነት የሚሰጠው አይሆንም፡፡

በሌላ በኩል የአሁኑ አመልካች በግራ ቀኙ በኩል በተደረሰው ስምምነት መሠረት ጉዳት የደረሰበት መኪና ወደ አዳማ ከተማ ተጓጉዞ በገለልተኛ ባለሙያ ከተመረመረ በኃላ የጉዳቱ ካሳ መጠን ብር 108.747.83 /አንድ መቶ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ አርባ ሰባት ብር ከሰማኒያ ሶስት ሳንቲም/ ተረጋግጦ ያለና ሕብረት ኢንሹራንስ ግምቱን ለመክፈል ፍቃደኛ ሲሆን ተጠሪ ግን የተገመተውንም ግምት ለመቀበል እምቢተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ሊወስን የሚገባውም ይህ ግምት ነው ሲል ይከራከራል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ተገምቷል በተባለው አካል መኪናው ላይ የደረሰው የጉዳት መጠን እንዲገመት ያለመስማማቱን ገልጾ ተከራክሯል፡፡ ይህ ክርክር የሚያመለክተው በግራ ቀኙ መካከል የጋራ መስማማት እንዳልነበረ ነው፡፡ ይህ ብቻ አይደለም የተደረሰበት ስምምነት ስለመኖሩ ለሥር ፍርድ ቤት የቀረበና ያስረዳ ማስረጃ እንደሌለ ውሳኔው ያመለክታል፡፡ በመሆኑም አመልካች በዚህ ረገድ የሚያቀርቡት ክርክር በግራ ቀኙ በጋራ በተደረሰ ስምምነት መሠረት

ግምት የተሠራለት /የወጣለት/ ስለመሆኑ በማስረጃ የተደገፈ ክርክር ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም በመኪናው ላይ የደረሰው ጉዳት በዘርፉ በቂ እውቀትና ክህሎት ባለው /ባላቸው/ ባለሙያ /ባለሙያዎች/ ተጣርቶ ሊወሰን ይገባል ብለናል፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ የአሁን ተጠሪ መኪናው ጉዳት ሳይደርስበት ቢሸጥ ኖሮ በሶስት ወር ውስጥ ሊያተርፍ የሚችለውን ብር 60.000.00 /ስልሳ ሺህ/ ገምቶ ያቀረበው በሥር ፍርድ ቤት ተፈርዶለታል፡፡ በመኪናው ላይ የደረሰው ጉዳት ጠቅላላ ጉዳት / Total Loss/ እንደሆነ ከተጠሪ ክርክር ተረድተናል፡፡ እንዲህ ዓይነት ጉዳት በሚደርስበት ጊዜ በንብረቱ ላይ የደረሰውን አጠቃላይ ግምት ከመጠየቅ ውጭ ይገኛል ተብሎ የሚታሰበውን ገቢ መጠየቅ አግባብነት አይኖረውም፡፡ በህጉ መሠረት የጉዳት ካሳ ክፍያ ዓላማው ተጎጂው በደረሰበት ጉዳት ልክ ጉዳት አድራሹ ተመጣጣኝ የሆነ ክፍያ እንዲከፍል በማድረግ ወይም የደረሰውን ጉዳት በማሠራት /በማስጠገን/ ጉዳት ከመድረሱ በፊት ወደ ነበረበት ሁኔታ እንዲመለስ ማድረግ ነው፡፡ ይህንን ከፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2090 /1/፣ 2092 እና 2119 /1 እና 2/ መረዳት ይቻላል፡፡ በተያዘውም ጉዳይ የአመልካች ኃላፊነት በተጠሪ መኪና ላይ ለደረሰበት ጉዳት በጉዳቱ ልክ ተመጣጣኝ ካሳ መክፈል ወይም ጉዳቱን በመጠገን መኪናው ጉዳቱ ከመድረሱ በፊት ወደ ነበረበት ሁኔታ እንዲመለስ ማድረግ ነው፡፡ ከዚህ ወጭ ከደረሰው አደጋ ጋር ግንኙነት የሌለውን ክፍያ አመልካች የሚከፍልበት ህጋዊ ግዴታ ሊኖር አይችልም፡፡

የመኪና ጥበቃ ወጪን በተመለከተ አመልካች መኪናው ፖሊስ ዘንድ ስለቆየ ተጠሪ ለመኪና ጥበቃ የሚከፍልበት ምክንያት አይኖርም ሲል የተከራከረ ቢሆንም ይህን የሚደግፍ ማስረጃ ለሥር እንዳቀረበ የሚያመለክት ነገር ተያይዞ በቀረበልን ውሳኔ ላይ ስለሌለ በዚህ ረገድ በሥር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሶስተኛውን ጭብጥ በተመለከተ የአመልካች መኪና በወረዳ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ታግዶ መቆየቱን የግራ ቀኙ አይካካዱም፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንደሚያመለክተው መኪና ለጊዜው ታግዶ የቆየው አመልካች ዋስትና እንዲያስይዝ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 151 እና 152 መሠረት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ፍርድ ቤቱ የተከሰተውን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባትና በማጤን የሰጠ ትዕዛዝ በመሆኑ በተጠሪ ክፉ ልቦና ምክንያት የተፈጸመ ድርጊት ሆኖ አይታይም፡፡ አመልካች ተጠሪ ሥልጣን በሌለው ፍርድ ቤት መኪናውን አሳግዶ በማቆየቱ የሶስት ወር 150.000.00 /አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ/ ብር ኪሳራ አድርሶብኛል በማለት ያቀረበው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በሥር ፍርድ ቤት ተቀባይነትን ማጣቱ የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በመጨረሻም በመኪናው ላይ የደረሰውን የጉዳት ካሳ ግምት ብር 350.000.00 /ሶስት መቶ ሃምሳ ሺህ/ እንዲሁም ይገኝ የነበረ ገቢ ነው ተብሎ 60.000.00 /ስልሳ ሺህ /ብር አመልካች ለተጠሪ

እንዲከፍል የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ከላይ በዝርዝር ከተገለጹ ህጋዊ ምክንያቶች አንጻር ሲታይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአውሲረሱ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/መ/ቁ. 4627 በቀን 04/05/2008 ዓም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይ/መ/ቁ. 4105 መጋቢት 13 ቀን 2008 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348 /1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. ለተጠሪ መኪና ጥበቃ የተከፈለ ብር 5000.00 /አምስት ሺህ/ አመልካች እንዲከፍል የተሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የአመልካች የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ተቀባይነት የለውም ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ፀንቷል፡፡
3. በተጠሪ መኪና ላይ ለደረሰ ጉዳት የካሳ ግምት ብር 350,000.00 /ሶስት መቶ ሃምሳ ሺህ ብር/ እንዲሁም ለተቋረጠበት ገቢ ብር 60,000.00 አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል ተብሎ የተወሰነው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
4. ለተቋረጠ ገቢ አመልካች ብር 60,000.00 /ስልሳ ሺህ/ ለተጠሪ ሊከፍል አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡
5. በመኪናው ላይ የደረሰውን የጉዳት ካሳ ግምት በተመለከተ ከላይ በፍርድ ሀተታ ላይ በአንደኛ ጭብጥነት ተይዞ በዝርዝር በተገለጸው መሠረት ስለ ጉዳዩ በቂ እውቀትና ክህሎት ባለው ባለሙያ በመኪናው ላይ የደረሰው ጉዳት ተጣርቶ እንደገና እንዲወሰን በፍትሓብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 343 /1/ መሠረት ለአውሲረሱ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት መልሰናል፡፡
6. ሐምሌ 20 ቀን 2008 ዓ/ም የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው አካል ይጻፍ፡፡
7. ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
8. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይላክላቸው፡፡ በ20/11/08 ዓ/ም የተሰጠ እግድ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

   መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

መ/ተ

# ቤተሰብ

የሰ/መ/ቁ. 117164

ታህሳስ 25 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

አብዩ ካሳሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- ወ/ሮ ተክአ ሐጎስ አልቀረቡም

ተጠሪ፡- አቶ ፀጋዬ ገ/ፃዲቅ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳይ የቀረበው አመልካች የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ከተጠሪ ጋር በጋብቻ ወቅት ያፈራናቸው የማይንቀሳቀስ የጋራ ንብረቶች በን/ስ/ላ/ክ/ከ ቀበሌ 09/14 የቤት ቁጥር 889፤890 እና 936 በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኘው ቅድስት ማሪያም ከፍተኛ ክሊኒክ የንግድ ድርጅት ከነቤቱ በተጠሪ ስም በአዲግራት ከተማ ቀበሌ 05 የቤት ቁጥር 461 የሆነ መኖሪያ ቤት፤በቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 5 ቤት ቁጥር 081 በተጠሪ ስም የተመዘገበ የጎማና ባሌስትራ የንግድ ድርጅት እና ልደታ ክ/ከተማ ወረዳ የቤት ቁጥር 1035 በተጠሪ ስም የተመዘገበ የንግድ ድርጅት፤በተጠሪ ስም የተመዘገቡ የተለያዩ መኪኖች፤የአክስዮን ድርሻ በፋርማ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግ/ ማህበር በአመልካችና ተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ደርሻ እናበአሉላ አባነጋ ማህበር ውስጥ በተጠሪ የተከፈለን ገንዘብ፤ ከን/ስ/ላ/ክ/ከተማ፤ቂርቆስና ልደታ የሚገኙ ድርጅቶች የተገኘው ገቢ አመልካች ከቤት ከወጡበት ከየካቲት ወር 2005 ዓ.ም ጀምሮ የተሰበሰቡ ገቢዎች፤በዳሽን እና ህብረት ባንክ የተቀመጠ ገንዘብ እነዚህ የተዘረዘሩት የጋራ ሀብቶችን ተጠሪ እንዲያከፍሉኝ ይወሰኝልኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

በተጠሪ በኩል የተሰጠ መልስ ከድርጅቶቹ የሚፈለግ እዳ አለ፤እንዲሁም አመልካች ልጆቻችንን ስንድርና ለንግድ ስራ የሚሆን ገንዘብ ተበደር ብላኝ በጠቅላላው ብር 3,880,000/ ሶስት ሚሊየን ስምንት መቶ ሰማንያ ሺህ ብር/ ተብድሬያለሁ፤በመሆኑም አመልካችና ተጠሪ ለዚህ ገንዘብ ባለእዳዎች ስለሆንን በቅድሚያ ይህ ገንዘብ እንዲከፈል ሲሉ ተከራክረዋል፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ ህዳር 24 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በን/ስ/ላ/ክ/ከ ወረዳ 1 በካርታ ቁጥር ሊዝ-እጣ-408-93-24552/01 የሆነው አቶ ተከስተ ጸጋዬ ለአመልካች በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት በተፈፀመ ስጦታ ውል በስጦታ የተላለፈላቸው ቤትእና የቤት ቁሳቁሶች የጋራ ሀብት ይባልልኝየሚል ክስ አቅርበዋል፡፡አመልካቾም ለተከሳሽ ከሳሽነት ክሱ ታህሳስ 11 ቀን 2006 ዓ.ም የተፃፈ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የመከላከያ መልስ አቅርበዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የአመልካች ክርክር ከሰማና ማስረጃ ከመዘነ በኋላአመልካች ያቀረቡትን መቃወሚያ በማለፍ በፍሬ ነገሩም ላይ በን/ስ/ላ/ክ/ከ ቀበሌ 09/14 የቤት ቁጥር 889፤890 እና 936 በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኘው ቅድስት ማሪያም ከፍተኛ ክሊኒክ በውስጡ የሚገኙና በቬርቫል ተቆጥሮ በዝርዝር ከተከበሩ እቃዎች ጭምር፤በአዲግራት ከተማ ቀበሌ 05 የቤት ቁጥር 461 የሆነ መኖሪያ ቤት፤በቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 5 ቤት ቁጥር081 የጎማና ባሌስትራ የንግድ ድርጅት፤ሶስት መኪኖች መኖራቸው የተረጋገጡትን ኮድ 3-1160 አ/አ የሆነ አንቡላስ፤ኮድ 2-15532 አ.አ እና ኮድ3-11628 ኢ.ት ተሳቢ የጋራ ስለሆኑ ከተስማሙ በአይነት እኩል እንዲካፈሉ ወይም አንዱ ለሌላው ግምቱን በመክፈል እንዲያስቀር ወይም በዚሁ ካልተስማሙ ንብረቱ በሀራጅ ተሸጦ ገንዘቡን እኩል እንዲካፈሉት ተወስኗል፡፡

ልደታ ክ/ከተማ ወረዳ የቤት ቁጥር 1035 በተጠሪ ስም የተመዘገበ የንግድ ድርጅት በተመለከተ የመንግስት ወይም ቀበሌ ቤትን በተመለከተ ባካራያቸው ቀበሌ ወይም መንግስት በሚያስተዳድረው የአስተዳደር ደንብ መሰረት አስተዳዳራዊ መፍትሄ እና ምላሽ በዚያው ጠይቆ ከማረጋገጥ ባለፈ ፍርድ ቤቱ ለድርጅት ስራ የተከራዩትን የመንግስት ቤት የጋራ ንብረት ነው ብሎ በትዳር እንደተፈራ ንብረት ይከፋፈሉ በሚል ውሳኔ ውስጥ አይገባም በማለት ባለመቀበል ወስኖ አልፎታል፡፡ ፋርማ ትሬዲንግ ሊንክ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የባላና ሚስት የጋራ ድርሻ መኖሩ የታመነ ቢሆንም ክፍፍሉን በተመለከተ በንግድ ህግ መሰረት የሚፈርስና ሂሳብ የሚጣራ ካልሆነ በቀር እንደሌላው የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍሉ የሚወሰንበት የህግ አግባብ አይኖርም ሲል ውሳኔ ሰጥቦታል፡፡ በአሉላ አባነጋ ማህበር ድርሻ እንዲከፈል ያቀረቡት ጥያቄ በማስረጃ ያልደገፈ እና በተጠሪ ስም በራሱ ተክል ማህበር ድርሻ መኖሩ ያልተረጋገጠ ነው በማለት ባለመቀበል አልፎታል፤ህብረት ባንክ አ/ማ ጎፋ ቅርንጫፍ መኖሩን የተረጋገጠው ብር 402.30 እኩል እንዲካፈሉ፤ከአራቱ የንግድ ዘርፍ ክሊኒክ፤ ከጎማ መሸጫ፤ከፔንስዬንና ትራንስፖርት ከተሰበሰበው ገቢ ብር 293,985.60 የዚህ ግማሹ ተጠሪ ለአመልካች ብር 146,992.80 እንዲከፍሏቸው

ተወስኗል። በሲፒኦ ቁጥር 942560 በሆነው ለገቢዎች እና ጉምሩክ መከፈሉን የተረጋገጠው ብር 206,441.43 አመልካች ለተጠሪ ከተከፈለው ብር 103,220.71 ሊጋሩ እና ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወስኗል። በሌላ በኩል በተጠሪ ክስ የቀረበበት በሁለት ፎቅ መኖሪያ ቤት አመልካች በስጦታ የተሰጠኝ የግል ንብረት በማለት ያቀረቡት ክርክር ውድቅ በማድረግ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት በመሆኑ እንዲሁምየቤት ቁሳቁሶች በተመለከተ ድሬሲንግ ቴብል፤አልጋ የሽሚዝ ማስቀመጫ፤ኮሚዶኖ፤የጫማ መደራደሪያ፤ሁለት ቁም ሳጥን የሳሎንና የኪችን እቃዎችን፤6 አልጋዎችን ፤2 ትላልቅ ፍሪጆችን፤አንድ ቋሚ ፊሪጅ፤አንድ ቡታ ጋዝ ምድጃ፤የሳሎን የሌዘር ሶፋ እና ትልቅ ቴሌቪዥን የባልና ሚስት የጋራ ንብረታቸው ነው በማለት ከተስማሙ በአይነት እኩል እንዲካፈሉ ወይም አንዱ ለሌላው ግምቱን በመክፈል እንዲያስቀር ወይም በዚሁ ካልተስማሙ ንብረቱ በሀራጅ ተሸጦ ገንዘቡን እኩል እንዲካፈሉት ሲል ውሳኔ ሰጥቷል።

በተሰጠው ውሳኔ ላይ አመልካች ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን በሰጠው ማስረጃ ላይ የስር ፍርድ ቤት ሒሳቡን ሲሰራ በፈጸመው ስህተት ላይ የቀረበውን ቅሬታ ላይ የተመለከተውን ነጥብ ብቻ በማሻሻል ሌላው የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ክፍል በማፅናት ወስኗል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው። አመልካች ነሐሴ 11ቀን 2007 ዓ.ም በፃፉት አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል። የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 7 የቤት ቁጥር 1035 በተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ድርጅት ቤቱ የቀበሌ ስለሆነ የጋራ አይደለም በማለት የተሰጠው ውሳኔ ጉዳዩ በቤት ነው መታየት ያለበት ወይስ በድርጅት በድርጅቱ ውስጥ ያለው ንብረት ሳይወሰን መታለፉ አግባብነት በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበተበታዘዘው መሰረት መጋቢት 1 ቀን 2008 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል። አመልካችም አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ ባጭሩ ከላይ እንደተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል።

እንደመረመርነውም የአመልካች ጥያቄ በልደታ ክ/ከተማ የቤት ቁጥር 1035 የሆነ ንግድ ድርጅት ያለ መሆንና በትዳር ዘመን የተፈራ መሆኑ ያልተካደ በንግድ ህጉ መሰረት የንግድ ድርጅት/መደብር/ ከንግድ ቤቱ ተለይቶ የሚታወቅና ይህ የጋራ ሀብት የሆነው የንግድ ድርጅት ክፍፍል እንዳይፈፀምበት የሚከለክል ህግ ሳይኖር ክፍፍል ሊፈፀምበት አይችልም በማለት

የሰጠው ውሳኔ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ሲሆን በተጠሪ በኩል ደግሞ የንግድ ቤት ቁጥር 1035 የሆነው የንግድ ድርጅት እንደመሆኑ መጠን ክፍፍል የሚፈፀምበት ሆኖ ክፍፍል ከመፈፀሙ በፊት ድርጅቱ የግብር ዕዳ ያለበት በመሆኑ ይህ የግብር ዕዳ በቅድሚያ ሊከፈል ይገባል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ከመንግስት በኪራይ የተገኘው ቤት የጋራ ንብረት ነው ብሎ መጠየቁ አግባብነት የለውም፤የንግድ ቤቱ አስመልክቶ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈፀመበት ስለሆነ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ከክርክሩ ሂደትና በአመልካች ከቀረበው ክስ ይዘት መገንዘብ የተቻለው በልደታ ክ/ከተማ የሚገኘው የንግድ ድርጅት የጋራ ንብረት ተብሎ ክፍፍል እንዲደረግ እንጂ የመንግስት ቤት የሆነው የንግድ ቤቱ አይደለም፡፡ በተጠሪ በኩልም መልስ ሲሰጡ ድርጅቱ መኖሩን አልተካደም፡፡ በንግድ ቤቱ የጋራ ንብረት ተብሎ ክፍፍል እንዲደረግ የቀረበበት ጥያቄ ተደርጎ በተጠሪ በዚህ ችሎት ያቀረቡት መልስ ተቀባይነት የለውም፡፡አመልካች በጋራ ንብረትነት ፍርድ ቤቱ እንዲያካፍላቸው የጠየቁት በልደታ ክ/ከተማ የቤት ቁጥር1035 ያለውን የንግድ ድርጅት ንግድ ህግ ቁጥር 124 በሚደነግገው መሰረት በንግድድርጅትነቱ መጠሪያና በውስጡ የሚገኘው የንግድ ማካሄጃ ዕቃ የሚመለከት ሆኖ እያለ እንደ ባልና ሚስት የጋራ ንብረት በፍርድ ቤት ውሳኔ የሚሰጠው አይደለም በማለት መወሰኑ አግባብነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ከንግድ ህግ ቁጥር 127 ድንጋጌ መረዳት እንደሚቻለው የአንድ ንግድ ድርጅት መሰረታዊ አካል የንግድ ድርጅቱ መልካም ዝና፤ ስም፤ በደንበኞች የተለመደ መሆኑ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ሌሎች ነገሮች አካትቶ የሚይዝ ነው፡፡ከዚህ ውስጥ ንግዱ የሚከናወንበትን ክፍል የመከራየት መብት የንግድ ድርጅት አንደኛው ክፍል እንደሆነ ይህ ሰበር ችሎት በተመሳሳይ ጉዳይ የን/ሕ/ቁጥር 127 ድንጋጌ ይዘቱና መንፈሱ ይህ ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 454/1997 አንቀጽ 2/1/ መሰረት በየትኛውም እርከን የሚገኝ ፍርድ ቤት የሚያስገድድ የሕግ ትርጉም በሰ/መ/ቁጥር 33760፣ 33954 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት የሰጠበት ጉዳይ ነው፡፡

በመሆኑም የድርጅቱን መልካም ስም፤የመከራየት መብትና በቤቱ ውስጥ የሚገኘው የንግድ ዕቃ የጋራ መሆኑ በተጠሪ ሳይካድ የመንግስት ወይም ቀበሌ ቤትን በተመለከተ ባካራያቸው ቀበሌ ወይም መንግስት በሚያስተዳድረው የአስተዳደር ደንብ መሰረት አስተዳዳራዊ መፍትሄ እና ምላሽ በዚያው ጠይቆ ከማረጋገጥ ባለፈ በፍርድ ቤት ክፍፍል እንዲደረግ ውሳኔ ሊሰጥበት አይቻልም በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.76838 ሐምሌ 28ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 157144 ሰኔ24 ቀን 2007 ዓ.ም የተሰጠ ውሳኔበፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.348/1/ መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. በስር ፍርድ ቤቶች በልደታ ክ/ከተማ ወረዳ የቤት ቁጥር 1035 በተጠሪ ስም የተመዘገበ የንግድ ድርጅት የመንግስት ንግድ ቤት ስለሆነ በሚያስተዳድረው አካል የሚታይ ነው በማለት የተሰጠ ውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
3. አመልካችና ተጠሪ በልደታ ክ/ከተማ ወረዳ የቤት ቁጥር 1035 በተጠሪ ስም የተመዘገበ የንግድ ድርጅትን በንግድ ቤቱ የመከራየት መብት ጭምር የጋራ ሀብት ነው ብለናል፡፡
4. በሌሎች ጉዳዮች የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔዎች እንደፀኑ ናቸው፡፡
5. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በልደታ ክ/ከተማ ወረዳ የቤት ቁጥር 1035 በተጠሪ ስም የተመዘገበ የንግድ ድርጅት ውስጥ የሚገኙ ዕቃዎች ተገቢውን ማጣራት ካደረገ በኋላ ዕቃዎቹእንዲሁም የንግድ ድርጅቱ ግምት የመከራየት መብትን ጨምሮ ክፍፍል በተመለከተ ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.343/1/ መሰረትተመልሶለታል፡፡
6. በዚህ ችሎት ለተደረገው ወጭ እና ኪሳራ የግራ ቀኙን ተከራካሪ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግተዋል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የሰ/መ/ቁ. 127714

መጋቢት 26 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ አርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- ወ/ሮ ቃልኪዳን ይኸነው     የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- አቶ ኢብሳ ያደታ        ጠበቃ ዘውዱ እንዳለው ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከጋብቻ መኖር አለመኖር ጋር ተያይዞ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡትም በባህርዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤትበመዝገብ ቁጥር 03-01390 በ01/10/2007 ተሰጥቶ በአማራብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 41000 በ13/07/2008 ዓ.ም የተሻሻለው ውሳኔ  መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

ግራ ቀኙ የተለያዩ ክልሎች ነዋሪዎች ነው በሚል አመልካች ክሱን ያቀረቡት ለባህርዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን በ23/04/2007 ዓ.ም ተዘጋጅቶ የቀረበው ክስ  አጭር ይዘት፡- ከተጠሪው ጋር በ1999 ዓ.ም ጋብቻ መስርተው ሲኖሩ በ2005 ዓ.ም ያብስራ ኢብሳ የተባለች ልጅ መውለዳቸውን፣ጋብቻውን በመሰረቱበት ጊዜ ተጠሪው ከጋብቻው በፊት ያፈሩት ንብረት የጋራ እንዲሆን መስማማታቸውን፣የውሉ ቅጂም የሚገኘው  በተጠሪው እጅ መሆኑን፣በተጠሪው እጅ የሚገኝ የግራ ቀኙ የጋራ ሀብት ግምት ብር 16,960,000 መሆኑን የሚገልጽ ሆኖ ጋብቻው እንዲፈርስ፣ተጠሪው የልጅ ቀለብ እንዲቆርጡ እና የጋራ ንብረቱን አጋማሽ ብር 8,480,000 ለአመልካች እንዲያካፍሉ እንዲወሰን ዳኝነት የተጠየቀበት ሲሆን ተጠሪው በበኩላቸው በ05/06/2007 ዓ.ም. በሰጡት መልስ መደበኛ ነዋሪነታቸውም ሆነ ንብረቶቹ የሚገኙት በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ውስጥ በመሆኑ እና የአመልካቿ መኖሪያ አድራሻም እንደዚሁ

በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ውስጥ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል ስልጣን የለውም የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ካስቀደሙ በኃላ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ ከአመልካች ጋር ጋብቻ የሌላቸው መሆኑን፣የጋብቻ ጽሁፍ በተጠሪው እጅ ይገኛል የተባለውም ሀሰት መሆኑን፣ልጅም ያልወለዱ መሆኑን ገልጸው ክሱ ውድቅ እንዲደረግ በዝርዝር የተከራከሩ መሆኑን መዝገቡ ያመለክታል፡፡

ፍርድ ቤቱም ክሱን እና የግራ ቀኙን ምስክሮች ከሰማ በኃላ የአመልካቿ መደበኛ መኖሪያ ቦታ ባህርዳር ከተማ እንደሆነ በመረጋገጡ በተጠሪው የቀረበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን፣ይሁን እንጂ በግራ ቀኙ መካከል ጋብቻ መኖሩን አመልካች ማስረዳት ያልቻሉ መሆኑን፣ጋብቻ ከሌለ ደግሞ አመልካች የልጅ ቀለብ መጠየቅ የሚችሉት በቅድሚያ የልጁን አባትነት በማረጋገጥ በመሆኑ ቀለብ ሊቆረጥ የሚችልበት አግባብ አለመኖሩን ገልጾ ክሱን ሙሉ በሙሉ ውድቅ በማድረግ ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡ይግባኙን የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ ውሳኔውን አሻሽሎ ጋብቻ የለም መባሉ ተገቢ ቢሆንም ህጻኗ ልጃቸው መሆኗን ግን ተጠሪው በሽማግሌዎች ፊት ማመናቸው በምስክር የተገለጸ ሆኖ ሳለ መታለፉ ተገቢ ባለመሆኑ ህጻን ያብስራ ኢብሳ የተጠሪው ልጅ ናት፣ተጠሪው በየወሩ ብር 1,000 ቀለብ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡

አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የሰጡት ጋብቻ ስለመኖሩ በአመልካች በኩል የቀረበውን ማስረጃ መዝነው/አገናዝበው/ መሆን አለመሆኑን ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡በሌላ በኩል ህጻን ያብስራ የተጠሪው ልጅ ናት በሚል በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተሰጠው ውሳኔ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 127767 በ30/02/2009 ዓ.ምየተሻረ መሆኑን በመግለጽ ውሳኔው ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዝላቸው ተጠሪው 29/03/2009 ዓ.ም. በተጻፈ አቤቱታ ጠይቀዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ለጉዳዩ በጭብጥነት ወደተያዘው የፍሬ ነገር ክርክር ከመገባቱ በፊት የባህርዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን አስተናግዶ ውሳኔ የሰጠው ጉዳዩን ለማየት የሚያስችል የስረ ነገር ስልጣን ኖሮት ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ አስቀድሞ እልባት ማግኘት የሚገባው መሆኑን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከዚሁ ነጥብ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት አመልካች ክሳቸውን ለባህርዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ጋብቻው የተፈጸመው እና ግራ ቀኙም አብረው ሲኖሩ የነበረው በአማራ ብሔራዊ ክልል

በባህርዳር ከተማ ውስጥ ሆኖ ክሱ በተመሰረተበት ጊዜ ግን አመልካቿ እዚያው ባህርዳር ከተማ የሚኖሩ ሆኖ ተጠሪው የሚኖሩት ደግሞ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ውስጥ መሆኑን መሰረት በማድረግ እንደሆነ የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡እንደተባለው መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች ውስጥ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሱ ክርክሮችን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 (እንደተሻሻለ) በአንቀጽ 5 (2) ስር ተመልክቶአል፡፡ከጋብቻ ጉዳይ ጋር ተያይዘው የሚነሱት የክልል ጉዳዮች የሚታዩት በክልሉ ወረዳ ፍርድ ቤት መሆኑ እየታወቀ የባህርዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ተቀብሎ ለማስተናገድ የቻለውም ይህንኑ አዋጅ መሰረት አድርጎ ጉዳዩ የፌዴራል ነው በማለት ነው፡፡ይሁን እንጂ የተጋቢዎቹ መደበኛ ነዋሪነት በተለያዩ ክልሎች ውስጥ እንደሆነ ተቆጥሮ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 (እንደተሻሻለ) በአንቀጽ 5 (2) ስር የተመለከተው ድንጋጌ ከጋብቻ ጋር ተያይዘው በሚነሱ ጉዳዮች ረገድ ተፈጻሚነት ሊኖረው የሚገባ መሆን አለመሆኑ በአግባቡ ሊጤን የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡

በጋብቻ የተሳሰሩ አንድ ወንድ እና አንዲት ሴት በተለያዩ ምክንያቶች ተለያይተው የሚኖሩባቸው ሁኔታዎች በተግባር እንደሚያጋጥሙ ይታወቃል፡፡ተለያይተው የሚኖሩትም በአንድ ክልል ውስጥ ወይም በተለያዩ ክልሎች ውስጥ እንዲሁም በተለያዩ አገሮች ውስጥ ጭምር ሊሆን ይችላል፡፡ይህ ማለት ግን የተጋቢዎቹ መደበኛ መኖሪያ ቦታ የተለያየ ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያስችል አይደለም፡፡ይልቁንም ጋብቻው ከተቋቋመበት መሰረታዊ ዓላማ አንጻር ተጋቢዎቹ በመርህ ደረጃ አንድ መደበኛ መኖሪያ ቦታ እንዳላቸው ግምት የሚወሰድበት ነው፡፡በመሆኑም ጋብቻው እስካልፈረሰ ወይም በተራዘመ የጊዜ ቆይታ ምክንያት በተግባር እንደፈረሰ እስካልተቆጠረ ድረስ የተጋቢዎቹ በተለያዩ ምክንያቶች ለጊዜው በተለያዩ ቦታዎች መኖር መደበኛ መኖሪያቸውን በተለያዩ ቦታዎች አድርገዋል ከሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ የሚያስችል አይደለም፡፡

በተያዘው ጉዳይ ጋብቻው የተፈጸመው እና ግራ ቀኙም አብረው ሲኖሩ የነበረው በአማራ ብሔራዊ ክልል በባህርዳር ከተማ ውስጥ መሆኑን አመልካቿ በክስ ማመልከቻቸው ላይ ገልጸዋል፡፡ በክሳቸው መሰረት ማስረዳት የሚጠበቅባቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ጋብቻው የተመሰረተው እና ግራ ቀኙም ከጋብቻው በኃላ ሲኖሩ የነበረው በአማራ ክልል ውስጥ ነው እስከተባለ ድረስ ክሱ መቅረብ የሚገባው በክልሉ ሕግ መሰረት ከጋብቻ ጉዳዮች ጋር ተያይዘው የሚነሱ የክልል ጉዳዮችን የማየት ስልጣን ላለው የክልሉ ወረዳ ፍርድ ቤት ከሚሆን በቀር ግራ ቀኙ መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች ውስጥ እንደሆነ ተደርጎ በአዋጅ ቁጥር 25/1988 (እንደተሻሻለ) በአንቀጽ 5 (2) ስር በተመለከተው ስርዓት መሰረት አይደለም፡፡ጋብቻው የተፈጸመው በአንድ ክልል ውስጥ እና በዚያው ክልል የቤተሰብ ሕግ መሰረት በሆነ ጊዜ ከፍቺ ጋር ተያይዞ ጥያቄ በተነሳበት ወቅት ተጋቢዎቹ በተለያዩ ምክንያቶች የሚኖሩት በተለያዩ ክልሎች

ውስጥ መሆኑ ቢረጋገጥ እንኳ ከፍቺ እና መሰል ጥያቄዎች ጋር ተይይዘው የሚነሱ ጉዳዮችን የማስተናገድ የስረ ነገር ስልጣን በክልሉ ሕግ መሰረት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የተሰጠው የክልሉ ፍርድ ቤት ከሚሆን በቀር ተጋቢዎቹ መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች ውስጥ እንደሆነ ተቆጥሮ ጉዳዩ ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5 (2) ድንጋጌ አንጻር በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር የሚወድቅ ነው ሊባል የሚችልበት የሕግ አግባብ ስላለመኖሩ የፌዴዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አስቀድሞ በቀረበለት ተመሳሳይ ጉዳይ በመዝገብ ቁጥር 119582 በ26/04/2009 ዓ.ም. የሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ለተያዘው ጉዳይ ተፈጻሚነት ያለው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በባህርዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤትበመዝገብ ቁጥር 03-01390 በ01/10/2007 ተሰጥቶ በአማራብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 41000 በ13/07/2008 ዓ.ም. የተሻሻለው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ፀንቶአል፡፡
2. ጋብቻ የተፈጸመው በአንድ ክልል ውስጥ እና በዚያው ክልል ሕግ መሰረት ሆኖ ክስ በቀረበበት ጊዜ ተጋቢዎቹ በተለያዩ ምክንያቶች የሚኖሩት በተለያዩ ክልሎች ውስጥ መሆኑ ቢረጋገጥ እንኳ ከፍቺ እና መሰል ጥያቄዎች ጋር ተይይዘው የሚነሱ ጉዳዮችን የማስተናገድ የስረ ነገር ስልጣን በክልሉ ሕግ መሰረት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የተሰጠው የክልሉ ፍርድ ቤት ከሚሆን በቀር ተጋቢዎቹ መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች ውስጥ እንደሆነ ተቆጥሮ ጉዳዩ ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 5 (2) ድንጋጌ አንጻር በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የስረ ነገር ስልጣን ስር የሚወድቅ ነው ሊባል የሚችል አይደለም በማለት ወስነናል፡፡
3. እንዲያውቁት የውሳኔው ቅጂ ለባህርዳርና አካባቢዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይላክ፡፡
4. አመልካቿን ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ክስ ከማቅረብ ይህ ውሳኔ የሚያግዳቸው አይሆንም፡፡
5. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
6. በዚህ መዝገብ በ23/01/2009 ዓ/ም ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ይፃፍ፡፡

ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

የሰ/መ/ቁ 123132

ሚያዝያ 30 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጸውሎስ አርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- አቶ ከሳሁን ታደሰ - ጠበቃ አቶ ዘበነ ፍቅሬ ቀርቧል፡፡

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ፀዳለ ሀፍታይ- ጠበቃ አቶ ኤልያስ ወርቁ ቀርቧል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ ያለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የጉዳዩ መንሥኤ የባልና ሚስት ንብረት ክፍፍልን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ የአሁኗ ተጠሪ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ከአሁን አመልካች /ከሥር ተከሳሽ/ ጋር ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደ ባልና ሚስት በመሆን አብረው በሚኖሩ ጊዜ ያፈሩዋቸው በየካ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 20 የቤት ቁጥር አዲስ የሆነ ቤት እና የሠሌዳ ቁጥሩ ኢት 03-01-52703 የሆነ የጭነት መኪና የጋራ በመሆናቸው ተከሳሽ /አመልካች/ ንብረቶቹን እንዲያካፍለን ይወሰንልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

የሥር ተከሳሽ /የአሁኑ አመልካች/ የግራ ቀኙ በጣልያን ሀገር የሚኖሩ በመሆናቸው የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ተፈጻሚነት የለውም፣ የተከሳሽ ነዋሪነት ውጭ አገር በመሆኑ በኢትዮጵያ ፍርድ ቤት ጉዳዩ መቅረብ አይችልም፣ የግራ ቀኙ እንደ ባልና ሚስት ለመኖር የተስማሙት ጣልያን አገር በመሆኑ ተጠሪ/ከሳሽ/ በኢትዮጵያ ክስ መመስረት አይችሉም፣ ስለ ንብረት የሚያነሱትም ክርክር በጣልያን አገር ህግ መሠረት ከጋብቻ ውጭ እንደባልና ሚስት የሚኖሩ ሰዎች በሚለያዩበት ጊዜ በአንዱ ስም የተመዘገበውን ሌላኛው መጠየቅ እንደማይቻል በጣልያን አገር ከሚያገለግል ጠበቃ የቀረበ የሕግ አስተያየት አስተርጉመን ስላቀረብን እና ከሳሽ /ተጠሪ/ ለክርክሩ መነሻ ያደረጉዋቸው ንብረቶች በተከሳሽ ስም የተመዘገቡ በመሆናቸው ከሳሽ መብት የላቸውም

በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን አቅርቧል፡፡ ፍርድ ቤቱም የአሁኗ ተጠሪ በመቃወሚያዎቹ ላይ መልስ እንዲሰጡበት ካደረገ በኃላ የአሁኑን አመልካችን መቃወሚያዎችን ውድቅ በማድረግ በከ/መ/ቁ.138413 ሰኔ 2 ቀን 2006 ዓ/ም ብይን ሰጥቷል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ በፍሬ ነገሩ ላይ ክርክር እንዲያደርጉ ትዕዛዝ ሰጥቶ የአሁኑ አመልካች ንብረቶቹ ስለመኖራቸው ሳይክድ ተከራክሯል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የአሁኗ ተጠሪ የጠየቁዋቸው ንብረቶች የጋራ ስለሆኑ እኩል እንዲካፈሉ ሲል በኮ/መ/ቁ. 138413 የካቲት 24 ቀን 2007 ዓ.ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁኑ አመልካች በሥር ፍርድ ቤት ብይን እንዲሁም ውሳኔው ላይ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቦ ይግባኝ ሰሚው ችሎትም ይግባኙ በመቀበል ክርክራቸውን ከሰማ በኃላ በፍ/ይ/መ/ቁ. 111588 ህዳር 8 ቀን 2008 ዓ/ም በዋለው ችሎት የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የሥር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ ለማስለወጥ ሲሆን የአቤቱታ ይዘቱም በአጭሩ የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካች ያቀረቡቸውን መቃወሚዎችን በማለፍ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት እንደተፈጸመበት የሚገልጽ ሲሆን ሌሎች ነጥቦች በፍሬ ነገር ረገድ ተፈጸሙ ያሉዋቸውን ስህተቶች በመዘርዘር የቀረቡ ናቸው፡፡

የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ የግራ ቀኙ በጣሊያን አገር ሳሉ የፈጠሩት ግንኙነት የባልና ሚስት ዓይነት ግንኙነት ነበር የመባሉንና ይህ ቢታለፍ ግራ ቀኙ የንብረት ግንኙነት ነበራቸው ወይስ አልነበራቸውም? የሚለው የመጣራት አለመጣራቱን አግባብነት ለመመርመር ሲባል አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው በጠበቃቸው በኩል ህዳር 1 ቀን 2009 ዓ/ም በተጻፈ መልስ ዝርዝር ነጥቦችን አንስተው ተከራክሯል፡፡ የአመልካች ጠበቃም ታህሳስ 5 ቀን 2009 ዓ.ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት በአጭሩ ከላይ የተመለከተው የሚመስል ሲሆን አመልካችና ተጠሪ በጣሊያን ሀገር ህግ መሠረት እንደባልና ሚስት አብረው መኖራቸው በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 5 መሠረት ሊታይ ይገባል ወይስ አይገባም? በኢትዮጵያ የቤተሰብ ህግና በጣሊያን ህግ መካከል የሕግ ግጭት አለ ወይስ የለም? የአመልካችና የተጠሪ ንብረት ክርክር እልባት ሊያገኝ የሚችለው በኢትዮጵያ ህግ መሠረት ነው ወይስ በጣሊያን ህግ መሠረት ነው? የሚሉት ነጥቦች ሊታዩ የሚገባቸው ናቸው፡፡ አመልካችና ተጠሪ ጣሊያን አገር መኖራቸው፣ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው የኖሩ መሆናቸው፣ በዚህ ግንኙነት ልጅ የወለዱ መሆናቸው በግራ ቀኙ መካከል ክህደት የለም፡፡

በመሠረቱ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 5 ሥር በውጭ አገር የተፈጸመ ጋብቻ በኢትዮጵያ ውስጥ ለህግና ለሞራል ታቃራኒ እስካልሆነ ድረስ ተቀባይነት አለው የሚለውን በጣሊያን አገር እንደ ባልና ሚስት አብረው የኖሩበትን ሁኔታ አመሳስለው መተርጎም ተገቢ ነው ወይ? የሚለውን ከድንጋጌው ዓላማና መንፈስ ጋር አያይዞ መመልከት ያስፈልጋል፡፡ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 5 " በተፈጸመበት አገር የጋብቻ አፈጻጸም ህግ መሠረት ከኢትዮጵያ ውጭ የተፈጸመ ጋብቻ የህዝቡን ሞራል እስካልተቃረነ ድረስ በዚህ ህግ ተቀባይነት ይኖረዋል" በማለት ይደነግጋል፡፡ የዚህ ህግ ድንጋጌ ዓላማ በውጭ አገር ጋብቻ የፈጸሙ ባልና ሚስት የጋብቻ ማስረጃቸው በኢትዮጵያ ህግ ተቀባይነት የሚያገኝበትን ሁኔታ የሚያመለክት ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት ተጋቢዎች በውጭ አገር ህግ መሠረት ተጋብተው ነገር ግን ጋብቻቸው ከኢትዮጵያ ህዝብ ሞራል ጋር የማይቃረን ከሆነ ተቀባይነት ይኖረዋል ማለት ነው፡፡ ይህ አንቀጽ ከኢትየጵያ ወጭ ጋብቻው ቢፈጸምም የጋብቻ አፈጻጸም ሥርዓቱ ጋብቻን ለመመሥረት የሚያስችል ከመሆኑ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ድንጋጌውም እውቅና የሚሰጠው በውጭ አገር ለተፈጸመ ጋብቻ እንጂ ለሌሎች ግንኙነቶች አይደለም፡፡ በውጭ አገር በአንድ ወንድና ሴት መካከል እንደባልና ሚስት አብረው መኖርን ከዚህ ድንጋጌ ጋር በማመሳሰል መተርጎም የህግ ስህተት ነው፡፡ በዚህ ረገድ የሥር ፍርድ ቤት የደረሰው ድምዳሜ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በኢትዮጵያ የቤተሰብ ህግና በጣሊያን ህግ መካከል የህግ  ግጭት አለ ወይስ የለም? የሚለውን ሁለተኛውን ነጥብ ከክርክሩ እንዲሁም ከሥር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ አንጻር ተመልክተናል፡፡ ይህን ጭብጥ በተመለከተ የሥር ፍርድ ቤት በሁለቱም አገር ህጎች መካከል ግጭት እንዳለ ተቀብሎ መሆን የሚገባውን በተመለከተ ግን በቂ ምላሽ ሳይሰጥ እንዳለፈ የሥር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ያሣያል፡፡ አመልካች በጣሊያን አገር ህግ መሠረት ሁለት ግለሰቦች ጋብቻ ሳይመሰርቱ እንደባልና ሚስት ከኖሩ በጋራ የሚያፈሩት ንብረት እንደሌለ፣ ሁለቱም በስማቸው ተመዝግቦ የሚገኘው ንብረት ባለቤት ተደርገው  ስለሚቆጠሩ ሲለያዩም በየግላቸው ያላቸውን ንብረት ይዘው እንደሚቀሩ ከሥር ፍርድ ቤት ጀምሮ ተከራክሯል፡፡ አመልካች በዚህ ጉዳይ ላይ የጣሊያን ህግ በተመለከተ ኤሌክሳድሮ ለፒዛ ከሚባል በጣሊያን አገር ህጋዊ ከሆነ ጠበቃ ማብራሪያ በታች ፍርድ ቤት በማስረጃነት አስተርጉመው ጣሊያን አገር በሚገኘው የኢትዮጵያ ኢምባሲ እና በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል አረጋግጠው ማቅረባቸውን ተያይዞ የቀረበልን የሥር ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ያመለክታል፡፡ በዓለም አቀፍ የግለሰብ ህግ /Private International law/ መሠረት በዘርፉ እውቀት ያለ ወይም ምሁር /Scholar/ የሰጠውን አስተያየት በማስረጃነት ማቅረብ እንደሚቻል የተረጋገጠ ነው፡፡ የቀረበውን አስተያየት እንደማንኛውም ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ግን አስተያየቱ የቀረበለት ፍርድ ቤት ነው፡፡

በሌላ በኩል በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 102 /1/ ላይ የንብረት አስተዳደራቸውን አስመልክቶ የሚያደርጉት ውል እንደተጠበቀ ሆኖ፣ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ሰዎች ለሶስት ዓመት ላላነሰ ጊዜ አብረው ከኖሩ በግንኙነቱ ውስጥ እያሉ ያፈሩዋቸው ንብረቶች የጋራ ሀብታቸው ይሆናሉ በማለት ይደነግጋል፡፡ ይህም የኢኮኖሚ ግንኙነታቸውን ለማጠናከር፣ በመተማመን መንፈስ ሆነው ንብረት እንዲያፈሩ ለማድረግ እና ለዚሁም የህግ ጥበቃና ዋስትና እንዲኖር ለማድረግ ታስቦ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ በሌላ አነጋገር እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ሰዎች ከሶስት ዓመት ላላነሰ ጊዜ አብረው ከኖሩ የሚያፈሩት ንብረት የጋራ እንደሆነና ለዚህም ህጉ ጥበቃ እንደሚያደርግ ነው፡፡

በዚህ መሠረት አመልካች ካቀረቡት ክርክር አኳያ የጣሊያን ሀገር ህግ እና የኢትዮጵያ የቤተሰብ ህግ የተለያየ ድንጋጌ እንዳላቸው ነው፡፡ ይህም በሁለቱ ህጎች መካከል ግጭት እንዳለ ያሳያል፡፡ ስለሆነም ይህ በአግባቡ ሳይጣራ የሚሰጥ ውሳኔ የተሳሳተ ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ ይሆናል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የሥር ፍርድ ቤት የጣሊያን አገር ህግ አመልካች እንደሚሉት መሆን ያለመሆኑን ህጉ እንዲቀርብ በማድረግ አጣርቶ መወሰን ሲገባው ይህንን ሳያደርግ እና የህግ ግጭቱን ለይቶ ሳያረጋግጥ የሰጠው ውሳኔ የሚነቀፍ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል የአመልካችና የተጠሪ ንብረት ክርክር እልባት ሊያገኝ የሚችለው በኢትዮጵያ ህግ መሠረት ነው ወይስ በጣሊያን ህግ መሠረት? የሚለው ነጥብ እልባት ሊያገኝ የሚችለው ከላይ በተመለከተው መሠረት የህግ ግጭት መኖር አለመኖሩ ከተረጋገጠ በኃላ ነው፡፡ ስለዚህ የህግ ግጭት መኖር አለመኖሩ ሳይረጋገጥ ክርክር የተነሳባቸው ንብረቶች የጋራ ናቸው ተብሎ የተሰጠው ውሳኔ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በመጨረሻም የሥር ፍርድ ቤቶች ከላይ የተመለከቱትን መሠረታዊ ነጥቦችን በአግባቡ ሳያጣሩ የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፤ በመሆኑም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 138413 የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍ/ይ/መ/ቁ. 111588 ህዳር 8 ቀን 2008 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 348 /1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ከላይ በፍርድ ሀተታው በተገለጸው መሠረት በጣሊያን አገር ህግ እና በኢትዮጵያ የቤተሰብ ህግ መካከል እንደባልና ሚስት አብረው በመኖር ግንኙነት ውስጥ የተፈራ ንብረት የጋራ እንዲሆን ለመወሰን በሁለቱም ህጎች መካከል ግጭት መኖር ያለመኖሩን

የጣሊያን አገር ህግ እንዲቀርብ ተደርጎ ጉዳዩ ውሳኔ እንዲሰጥበት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መልሰናል፡፡

3. ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. የውሳኔ ግልባጭ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይድረስ፡፡
   መዝገቡ ስለተወሰነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

የሰ/መ/ቁ. 130931

ሰኔ 19 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ አርሺሶ

ሰናይት አድነው

አመልካች፡- አቶ በላይ ዘለቀ - የቀረበ የለም።

ተጠሪ፡- ወ/ሮ ትዕግስት ዳባ /የህፃን ሀሴት በላይ ሞግዚት/- ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል።

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው።ጉዳዩ ከህፃን ልጅ ማሣደጊያ የሚቆረጥ ገንዘብ መጠን የሚመለከት ክርክር ነው። ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው። በሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል።

የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበችው ክስ ነው። ከግራ ቀኛቸው ሕፃን ሀሴት በላይ በጥር 25 ቀን 2004 ዓ.ም የተወለደች መሆኑንና የአመልካች አባትነትም በፍርድ ቤት ውሳኔ የተረጋገጠ መሆኑን፤ ለልጅቷ ቀለብ ብር 5,750.00 (አምስት ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ ብር) እንዲከፍሉና አመልካች ነዋሪነታቸው ስዊዘርላንድ በመሆኑ ቀለቡን በየወሩ ሳያቋርጡ የሚከፈሉ ስለመሆኑ በቂ ዋስ ወይም መያዣ እንዲያቀርቡ እንዲታዘዝላቸው፤ ይህ ካልተቻለም የህፃኗ ዕድሜ 18 ዓመት እስኪሞላት ድረስ ያለውን ቀለብ ፍርድ ቤቱ አስልቶ አመልካች በአንድ ጊዜ በህፃኗ ሞግዚት ስም በሚከፈት የባንክ ሂሳብ ገቢ እንዲያደርጉላቸው እንዲወሰንላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል።

አመልካች በተከሳሽነት ቀርበው ተጠሪ የጠየቀችውን ገንዘብ አመልካች በየወሩ ለህፃኗ ማሳደጊያ ለመክፈል አልችልም፤የምችለው በወር ብር 1,000.00 (አንድ ሺህ ብር) መሆኑን ወርሐዊ

ገቢያቸው በኢትዮጵያ ብር ከ4,000.00 (አራት ሺህ ብር) እንደማይበልጥ፣ለሌላ ልጃቸው ቀለብ እንደሚቆርጡ፣ዕዳ እንደሚከፍሉና ሌላ ትዳርም መስርተው እየኖሩ በመሆኑ ወጪ ያለባቸው መሆኑን በመግለፅ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍርድ ቤት አመልካች ተጨባጭ ማስረጃ አላቀረቡም የቀለብ መጠን ሲወሰን ለቀለብ ተቀባዩ የሚያስፈልጉ ተጨባጭ ወጭዎች እንዲሁም የቀለብ ክፍያ አቅም ተገናዝቦ መሆን አለበት፡፡ በዚሁ መሰረትም አመልካች ከነሐሴ ወር 2007 ዓ.ም ጀምሮ ለልጅቷ ቀለብ በየወሩ ብር 4,000.00 (አራት ሺህ ብር) እንዲከፍሉ ክፍያውንም አመልካች በጠየቁት መሰረት የ6 ወርን በአንድ ጊዜ በተጠሪ የባንክ ሂሳብ ገቢ እንዲያደርጉ፣ለዚሁ ክፍያ መፈፀምም ዋስትና የሚሆን ለብር 696,000.00 (ስድስት መቶ ዘጠና ስድስት ሺህ ብር) የሚበቃ የሰው ዋስ ወይንም የንብረት ማስያዣ እንዲያሲይዙ ይህንን ማድረግ ካልቻሉ ለቀሪው የ14 ዓመትና 6 ወራት የሚሆን የቀለብ ክፍያ ብር 696,000.00 (ስድስት መቶ ዘጠና ስድስት ሺህ ብር) የህፃን ሞግዚት ለዚሁ ጉዳይ በሚከፍቱት የባንክ ሂሳብ በአንድ ጊዜ እንዲያደርጉ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ በስር ፍርድ ቤቱ የተሰጠው ውሳኔ ስህተት ያለበት ሆኖ አልተገኘም በማለት በውሳኔ አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ሰኔ 20 ቀን 2008 ዓ.ም በፃፉት አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ አመልካች ከኢትዮጵያ ዉጪ ስለሚኖር የገቢውን መጠን የማስረዳት ሸክም በርሱ ላይ ያርፋል ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት ሚያዚያ 17 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ የአመልካች አቤቱታቸውን የመልስ መልስ የማቅረብ መብት በመታለፉ የቀረበ የመልስ መልስ የለም፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው የፅሑፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የስር ፍርድ ቤቶች ለህፃን ማሳደጊያ አመልካች እንዲከፍል ውሳኔ የሰጠው በሕግ የተመለከቱትን ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ ነው ወይስ አይደለም ? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የአመልካች ጥያቄ በወር ብዙ ውጭ ማለትም የባንክ ዕዳ፣የልጅ ቀለብ፣የቤተሰብ ማስተዳደር ሁሉ ወጭዎች ያሉብኝ መሆኑን በማስረጃ አስደግፌ አቅርቤ እያለሁና የምችለውም በወር ብር 1,000.00 (አንድ ሺህ ብር ) ብቻ መሆኑን እያስረዳሁ

ከአቅሜ በላይ የተጋነነ ቀለብ በወር ብር 4,000.00 (አራት ሺህ ብር) እንድከፍልና እና በአንድ ጊዜ በሞግዚት አድራጊዋ በተከፈተ ባንክ ብር 696,000.00 (ስድስት መቶ ዘጠና ስድስት ሺህ ብር) ገቢ እንዳደርግ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩላቸው ልጅ ወልዶ ማሳደግ ከፍተኛ ሀላፊነት የሚጠይቅ እና እንደ አባት እንደ እናት ተንከባክቦ ፍቅርን፣ጊዜን እንዲሁም ገንዘብን ሰውቶ ለቁም ነገር ማብቃትን ይጠይቃል፡፡ ተጠሪም እስከ አሁን ድረስ ይህን ሀላፊነት ለብቻቸው በመወጣት ላይ ይገኛሉ፤ በአንፃሩ አመልካች ከመኖሪያ ቤት ሽያጭ ከፍተኛ ገንዘብ(ከአምስት ሚሊዮን ብር) በላይ ማግኘታቸው በተረጋገጠበት ሁኔታ ልጅነትን ሳይክዱ ከሚጠበቅባቸው የበዛ ሀላፊነት የህፃኗን አስተዳደግ በገንዘብ የመደገፍ ሀላፊነትን ሊወጡ እንደሚገባ በማመን እንዲሁም ኢፌዴሪ ህገመንግስት እና ሀገራችን ባጸደቀቻቸው ዓለምአቀፍ የሰብአዊ መብት ሰነዶች እንዲሁም የሰበር ችሎቱ በተደጋጋሚ በሰጣቸውን ውሳኔዎች ፍርድ ቤቶች ህፃናትን አስመልክቶ የሚወሰኑ ውሳኔዎች የህጻናቱን ጥቅም ከግምት ሊያስገቡ እንደሚገባ የተመለከተውን ግምት ውስጥ በማስገባት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ የስር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች ለወለዳት ህፃን ሀሴት በላይ ለማሣደግ የሚያስፈልገውን ወጪ የመጋራትና የመሸፈን ግዴታ ያለበት መሆኑ አላከራከረም አመልካችንና ተጠሪ የሚያከራከረው አመልካች ለህፃኗ አስተዳዳግ ሊከፍለው የሚገባው የገንዘብ መጠን ነው፡፡ ለህፃን ልጅ ማሳደጊያ ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለበት ወላጅ፣ የሚከፍለው የገንዘብ መጠን የሚወስነው እንደባለጉዳዩ ሁኔታና እንደ አካባቢው ልምድ የሚስማማውን በመከተል በቀለብ ተቀባዩ ምግብ፣ መኖሪያ፣ ልብስ፣ ጤናውን የሚጠብቅበትና እንደ ሁኔታው ለትምህርት አስፈላጊ የሆኑትን ወጭዎች የሚሸፈን መሆን እንደሚገባው በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 197 አንቀጽ 2 ይደነግጋል፡፡

ከዚህ አንፃር ሲታይ አመልካች በተወሰነ መልኩ ከኢትዮጵያ ውጭ ገቢ እንዳለቸው ከመታመኑ በላይ በኢትዮጵያ ውስጥም ከመኖሪያ ቤት ሽያጭ ከ2.5 ሚሊዮን ብር ያገኙ መሆኑን ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡አንድ ወላጅ ህፃን ልጁን በጥሩ ሁኔታ ለመመገብ፤ በጥሩ መኖሪያ አካባቢ ለማኖርና ጤናውን ለመጠበቅ እንዲሁም ጥሩ ትምህርት እንዲያገኝ ለማድረግ የሚያስፈልገውን ወጭ መሠረት በመድረግ ሊወሰን እንደሚገባና ከአመልካች ገቢ አንፃር ሲታይ ከብር 1,000.00 /አንድ ሺህ ብር/ በላይ ለመክፈል አቅም የለኝም በማለት ያቀረቡትን ክርክር በተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 197 እና አንቀጽ 202 ድንጋጌዎችን መሠረት ያላደረገ በመሆኑ አልተበቀልነውም፡፡

ሲጠቃለል የስር ፍርድ ቤቶች አመልካች ለህፃኗ አስተዳደግ እንዲከፍሉየሰጡት ውሳኔ የቀለብ ገንዘብ መጠኑ ሆነ የአከፋፈሉ ሁኔታ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ስላልተገኘ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

7. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.108713 ነሐሴ 6 ቀን 2007 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 173752 ሚያዚያ 28 ቀን 2008 ዓ.ም በውሳኔ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
8. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

የሰ/መ/ቁ.129933

ሰኔ 28 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጻውሎስ አርሺሶ

ሠናይት አድነው

አመልካች፡- አቶ አየለ ወ/አለማው -ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1.ወ/ሮ እመቤት ማሞ
2.አቶ ሄኖክ ገ/ጻዲቅ
} ስለሁለቱም ተጠሪዎች 2ኛ ተጠሪ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሰኔ 29 ቀን 2008 ዓ/ም በተጻፈ አቤቱታ በመዝገብ ቁጥር 51387 በቀን 27/12/2007ዓ.ም የሥር የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 170917 የካቲት 30 ቀን 2008 ዓ/ም የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 125536 በ14/8/2008ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ስህተቱ እንዲታረምልኝ በማለት ዳኝነት በመጠየቃቸው ነው፡፡

የክርክሩ መንሥኤ የውርስ ሀብት ክርክር ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች በ7/11/ 2007 ዓ/ም በተጻፈ በአሁኑ ተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ ከሟች አቶ ገ/ጻዲቅ ደስታ በኑዛዜ የተላለፈልንን በቀድሞ ወረዳ 23 ቀበሌ 16 የቤት ቁጥር 207 የሆነ ቤት 1ኛ ተከሳሽ የሟች ሚስት ሳይሆኑ ሚስት ነኝ በማለት እና 2ኛ ተከሳሽም የሟች ልጅ ሳይሆኑ ልጅ ነኝ በማለት በኑዛዜ የተላለፈልኝን ቤት ይዘው ስለሚገኙ 1ኛ ተከሳሽ ሚስት አይደሉም 2ኛ ተከሳሽም ልጅ አይደሉም በማለት ይወሰንልኝ በማለት ያቀረቡትን የውርስ ሀብት

ጥያቄ ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ሰምቶ 1ኛ ተከሳሽ የሚች አቶ ገ/ጻዲቅ ደስታ ሚስት 2ኛ ተከሳሽም ልጅ አይደሉም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁን ተጠሪዎች 1ኛተጠሪ የሚች ሚስት አይደሉም 2ኛ ተጠሪ የሚች ልጅ አይደሉም በማለት በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርበው ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የሥር ፍርድ ቤት የወሰነውን እና 1ኛ ተጠሪ የሚች ሚስት አይደሉም 2ኛ ተጠሪ የሚች ልጅ አይደሉም በማለት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የስር ከሳሽ የስር ተከሳሾችን 1ኛ ተከሳሽ ሚስት አይደሉም 2ኛ ተከሳሽም ልጅ አይደሉም በማለት ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት የላቸውም በማለት ውሳኔ የሰጠ ሲሆን ይህ ውሳኔ በስር የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ በአመልካች የቀረበውም ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በስር ጠቅላይ ፍርድ ቤት የጸናውን ውሳኔ ለማስለወጥ ሲሆን የአቤቱታው ይዘትም በአጭሩ፡- የኑዛዜ ተጠቃሚ የሆንኩበትን ንብረት ተጠሪዎች መብት ሳይኖራቸው መያዛቸውን በመግለጽ መብቴ እንዲከበርልኝ ያቀረብኩት ክርክር ውድቅ ተደርጎ በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ በስር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመጽናት የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ እንዲታረም የሚጠይቅ ነው፡፡

የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ አመልካች 1ኛ ተጠሪ ከሚች ጋር ጋብቻ እንደሌላቸው እና ከሚች ጋር በጋራ ያፈሩት ንብረት የሌለ መሆኑን የሚያስረዳ የሰነድ ማስረጃ አቅርቤያለሁ እያሉ ይህ ታልፎ አመልካች በተጠሪዎች ላይ ክስ የማቅረብ መብት የላቸውም በማለት በስር ከፍተኛ እና ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎላቸው የካቲት 16 ቀን 2009 ዓ/ም በተጻፈ መልስ ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡትን ክርክር አጠናክረው ተከራክረዋል፡፡ አመልካቹም መጋቢት 19 ቀን 2009 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡የነገሩ አመጣጥና የክርክሩ ሂደት አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ እንደተገለጸው ሲሆን በስር ፍርድ ቤት ከቀረበው ክርክር አንጻር በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡት ውሳኔዎች መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን አጣሪው ከያዘው ጭብጥ አንጻር ጉዳዩ ተመርምሯል፡

የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካችን ክስ ተቀብሎ እና የስር ተከሳሾችን ክርክር ውድቅ በማድረግ 1ኛ ተጠሪ የሚች ሚስት 2ኛ ተጠሪ የሚች ልጅ አይደሉም በማለት ውሳኔ የሰጠው ሚች ለአመልካች የእህታቸው ልጅ መሆናቸውን በመግለጽ እና የክርክሩ ይዞታ በስተ ግራ ባለው ክፍት ቦታ የተሰራውን ቤት ከሚች ጋር በጋራ የሰሩ መሆናቸውን በመግለጽ ከሞትኩኝ በኃላ አመልካች በስማቸው አዙረው እንዲጠቀሙበት፣ እንዲሸጡ እና እንዲለውጡ ያደረጉት እና

ስልጣን ባለው አካል የጸደቀ የቁም ኑዛዜ ማቅረባቸውን እና ሚች ከ1ኛ ተጠሪ ጋር በ23/11/1992ዓ.ም በተጻፈ ከሚያዝያ 12 ቀን 1978ዓ.ም ጀምሮ 1ኛ ተጠሪ እንደ ሚስት በ80 እንደ ሰራተኛ በደመወዝ ልጅ ሳንወልድ አብረን ስንኖር በእድሜ ባለመመጣጠናችን የሰራሁበትን ደመወዝ ብር 3000.00 ተቀብዬ ወደፊት ቀሪ ንብረት እና ሀብት አለኝ በማለት ላልጠይቅ ተስማምቻለሁ በማለት የፈረሙበትን ማስረጃ አቅርበዋል በማለት ሲሆን የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህንን የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ውሳኔ የሻረው አመልካች በተጠሪዎች ላይ ክስ የማቅረብ መብት የላቸውም በመሆኑም ተጠሪዎች ይህንን አስመልክቶ ያቀረቡትን መቃወሚያ የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውድቅ በማድረግ የሰጠው ብይን ተገቢ አይደለም በማለት ሲሆን ይህ ውሳኔ በስር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ እንደተመለከተው የቀረበ ሲሆን እኛም የሰበር አመልካች 1ኛ ተጠሪ የሚች ሚስት 2ኛ ተጠሪ የሚች ልጅ አይደሉም ይባልልኝ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ በስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተቀባይነት ቢያገኝም በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውድቅ በማድረግ መወሰናቸው በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ይዘን ክርክሩን እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

አመልካች በስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ 1ኛ ተጠሪ የሚች ሚስት አይደሉም 2ኛ ተጠሪም የሚች ልጅ አይደሉም ይባልልኝ የሚል ሲሆን ለዚህም ምክንያታቸው 1ኛ ተጠሪ ከሚች እንደ ሚስት በ80 እንደ ሰራተኛ በደመወዝ ልጅ ሳይወልዱ አብረው ለመኖር ተስማምተው ሲኖሩ ቆይተው 1ኛ ተጠሪ የነበራቸውን ብር 3000.00 ወስደው ከአመልካች ጋር ወደፊት ምንም የቀረ ንብረት እና መብት አለኝ በማለት ላልጠይቅ ብለው የተስማሙበት የሰነድ ማስረጃ አለኝ በማለት አቅርበው በዚህ ምክንያት 1ኛ ተጠሪ የሚች ሚስት 2ኛ ተጠሪም የሚች ልጅ አይደሉም ይባልልኝ በማለት ነው፡፡

ከተጠሪዎች በኩል የቀረበው እና ምላሽ ማግኘት የሚገባው መከራከሪያ አመልካች ይህንን ክስ በማቅረብ የመከራከር ህጋዊ መብት የላቸውም የሚለው ነው፡፡

በመሰረቱ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀጽ 177/1-3/ ያሉ ድንጋጌዎች በአባት በኩል ያለን መወለድ መቃወም የሚቻለው የመካድ ክስ በማቅረብ ብቻ ሲሆን ክሱንም የሚያቀርበው የልጅ አባት ነህ የተባለ ሰው ነው፡፡ ሆኖም በህግ ግምት የልጁ አባት ነህ የሚባለው ሰው የሞት ወይም የመካድ ክስ ለማቅረብ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ አባት ነህ የተባለው ሰው ችሎታ ያጣ እንደሆነ ከተወላጆች አንዱ በእርሱ ፋንታ ሆኖ የመካድ ክስ ማቅረብ እንደሚችል የፌደራል የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 177/1/ ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን ተወላጆች የሌሉ እንደሆነ እናት እና አባት የመካድ ክስ የማቅረብ መብት ያላቸው ሲሆን እነዚህም በሌሉ ጊዜ ደግሞ ወደ ላይ ከሚቆጠሩ ወላጆች አንዱ መብቱን ሊሰራበት እንደሚችል ከዚህ በላይ

የተጠቀሰው የህግ አንቀጽ 177/2/ ላይ ተመልክቷል፡፡ በመጨረሻም ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች የሌሉ እንደሆነ በመካድ ክስ መብት ሊሰራበት የሚችለው ከወንድሞቹ ወይም ከእህቶቹ አንዱ እንደሆነ የቤተሰብ ህጉ አንቀጽ 177/3/ ይደነግጋል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች የሚች የእህት ልጅ መሆናቸው በኑዛዜ ሰነዱ ላይ የተመለከተ በመሆኑ ይህንን ክስ ለማቅረብ ህጋዊ መብት የላቸውም ሌላው ሚስትነት በተመለከተ የቀረበው መቃወሚያ እንደመረመርነው አመልካች ሚች አለ የሚሉት ኑዛዜ አመልካች የእህቴ ልጅ ስለሆነ በአዲስ ከተማ ወረዳ 23 ቀበሌ 16 የቤ.ቁ 207 ከሆነው መኖሪያ ቤቴ በስተግራ ባለው ክፍት ቦታ ወጪ በማውጣት አብሮ ስለሰራ ይህንን የተሰራ ቤት ከህልፈተ ህይወቴ በኂላ በስሙ አዙሮ እንዲጠቀም ተናዝዣለሁ የሚል ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች ኑዛዜ አለኝ የሚሉት ከዋናው ቤት በስተግራ በኩል ባለው ክፍት ቦታ ላይ የተሰራ ቤትን በተመለከተ በመሆኑ የጠቅላላ ሀብት ነኑዛዜ ተጠቃሚ ነኝ በማለት ያቀረቡት ክርክር በሌለበት የአሁን 1ኛ ተጠሪ ሚስትነት በመቃወም አቤቱታ ለማቅረብ የሚያስችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 33 መሰረት መብት ወይም ጥቅም የላቸውም፡፡

በመሆኑም የስር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪዎች በቀረበለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መሰረት ክሱን ውድቅ በማድረግ ሊወስን ሲገባ መቃወሚያውን ውድቅ በማድረግ በአመልካች ክስ መሰረት 1ኛ ተጠሪ የሚች አቶ ገ/ጻዲቅ ደስታ ሚስት አይደሉም 2ኛ ተጠሪም የሚች ልጅ አይደሉም በማለት የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ የስር ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በማጽናት የሰጠው ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አላገኘንም፡፡ በመሆኑም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በስር የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 51387 በ27/12/2007 ዓ.ምተሰጥቶ በስር የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 170917 በ30/6/2008ዓ.ም ዓ.ም የተሻረው እና በስር የፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 125536 በ14/8/2008ዓ.ም ዓ.ም የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
2. ይህ ውሳኔ አመልካችን በኑዛዜው መሰረት የውርስ ሃብት ክርክር ከማቅረብ አያግዳቸውም ብለናል፡፡
3. የዚህን ችሎት ወጪና ኪሳራ የግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. በዚህ ክርክር ምክንያት የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ለሚመለከተው አካል ይጻፍ፡፡
5. የውሳኔው ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረሳቸው፡፡

መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

# ውርስ

ሰ/መ/ቁ.124313

ሚያዚያ 16 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሡናይት አድነው

አመልካች፡-1ኛ. ወ/ሪት ቅድስት ዮሴፍ

2ኛ. አቶ ኃይለየሱስ ዬሴፍ ጠበቃ ምትክ ኦሉማ ቀረቡ

ተጠሪ፡- 1. ወ/ሮ ምስራቅ አለማየሁ

2. አቶ አብነት አለማየሁ - የቀረበ የለም

3. ወ/ሮ ስንታየሁ አለማየሁ

በሰ/መ/ቁጥር 125453 የሆነውን መዝገብ ከዚህ መዝገብ ጋር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 11 መሰረት አጣምረን በመመርመር ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት ይለቀቅልን ክርክርን መሰረት ያደረገ ሲሆን የተጀመረውም በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍርድ ቤት ከሳሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪዎች ሲሆን ተጠሪዎችና ሔለን አለማየሁ የተባሉት ግለሰብ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ አመልካቾች ባቀረቡት ክስም ወ/ሮ ምንትዋብ አለማየሁ የተባሉት ግለሰብ ወላጅ እናታቸው መሆናቸውንና ወራሽነታችን ማረጋገጣቸውን፣ ሟች በሕይወት እያሉም ግምቱ ብር 250,000.00 የሆነ ቤት በሰበታ ከተማ አስተዳደር ቀበሌ 02 ክልል ውስጥ ያፈሩ መሆኑን፣ ይህንን ቤት ከሕግ ውጪ ተከሳሾች ይዘው እንደሚገኙ ገልጸው ቤቱ እንዲለቀቅላቸው ይወሰን ዘንድ ጠይቀዋል፡፡ የሥር ተከሳሾችም ከሳሾች የንብረት ባለቤትነት ክርክርና የውርስ ክርክር አደባልቀው የባለቤትነት መብት ሳይኖራቸው መከራከር ስለማይችሉ ክስ ለማቅረብ እንደማይችሉ፣ ጉዳዩ በመ/ቁጥር 22056 የታዬና በድጋሚ

ክስ ሊቀርብበት የማይገባ መሆኑን፣ አውራሻቸው አቶ አለማየሁ በላቸው የውርስ ማስረጃ በስር ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 22056 ያገኙትን በማሻር የተሰጠውን ውሳኔ ይግባኝ ብለው ክርክር ላይ መሆናቸውን፣ ክሱ በሶስት አመት ይርጋ የታገደ መሆኑን የሚመለከቱ ነጥቦችን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አስነተዋል፡፡ በፍሬ ነገሩ ላይም ተገቢ ነው ያሉትን ክርክር አቅርበዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤትም በተከሳሾች በኩል ከቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥቦች መካከል ይርጋን የሚመለከተውን መቃወሚያ ብቻ ተቀብሎ ክሱ በሶስት አመት ይርጋ የታገደ ነው በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዚህ ብይን የስር ከሳሾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካቾች የእናታቸው የወ/ሮ ምንትዋብ አለማየሁ ወራሽ ነን በማለት የሚከራከሩና ተከሳሾች ደግሞ የአቶ አለማየሁ በላቸው ወራሽ ነን በማለት የሚከራከሩ በመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 1000 ለጉዳዩ ተፈፃሚነት የለውም በማለት የአመልካቾች ክስ በይርጋ የሚታገድ አይደለም፣ ፍሬ ነገሩ ተጣርቶ ሊወሰን ይገባል በማለት ጉዳዩን ለዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መልሶ ልኮለታል፡፡ በዚህ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ውሳኔ የአሁኑ ተጠሪዎች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄ በገንዘብ ሊገመት በማይቻል ርእስ እንጂ ተገምቶ ሊቀርብ አይገባም፣ ስለሆነም በገንዘብ ግምት ሊቀርብ የማይቻል ክርክር የማየት ስልጣን የወረዳ ፍርድ ቤት ሆኖ ንብረቱ ተገምቶ በንብረት ግምቱ መሰረት ጉዳዩ ለስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት መቅረቡ ተገቢ በሚል ድምዳሜ ጉዳዩ ከመነሻው የቀረበው የሥረ ነገር ስልጣን በሌላቸው ፍርድ ቤቶች ነው በማለት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመሻር ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ እነ ወ/ት ቅድስት ዩሴፍ፤የስር ከሳሾች፣ በሰ/መ/ቁጥር 124313 የሠበር አቤቱታ ያቀረቡት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቀረበው ያለስረ ነገር ስልጣኑ ነው መባሉ ያላግባብ ነው በሚል ሲሆን የስር ተከሳሾች ከነበሩት ውስጥ የአሁኑ ተጠሪዎች በሰ/መ/ቁጥር 125453 የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ደግሞ የስር ከሳሾች ክስ በይርጋ ሊታገድ የሚገባው ነው በሚል ነው፡፡

አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ግራ ቀኙ በሁለቱም መዝገቦች የጽሑፍ ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱም ምላሽ የሚያስፈልጋቸው አበይት ነጥቦች፡-

1. ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የየትኛው ፍርድ ቤት ነው?

2. የስር ተከሳሾች ክሱ በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ ሊወሰን ይገባል በማለት ያቀረቡት አቤቱታ በዚህ ችሎት ሊስተናገድ የሚችል ነው ወይስ አይደለም የሚሉ ሁነው ተገኝተዋል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡- ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የሥር ከሳሾች ከወላጅ እናታቸው ሊተላለፍላቸው የሚገባውና ግምቱ ብር 250,000.00 (ሁለት መቶ ሃምሳ ሺህ) የሆነ መኖሪያ ቤት በስር ተከሳሾች ከሕግ ውጪ መያዙን በክሳቸው ገልጸው ይህ ቤት እንዲለቀቅላቸው ይወሰን ዘንድዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ መሆኑን ነው፡፡ የሥር ተከሳሾች በቤቱ ላይ ከአመልካቾች እናት ያገኙት የውርስ መብት አለን የሚል ክርክር የሌላቸው ከመሆኑም በላይ ቤቱን ለስር ከሳሾች ያስተላለፉት ሟች አቶ አለማየሁ በላቸው ከሕግ ውጪ የሟች ወ/ሮ ምንትዋብ አለማየሁ ወራሽነታቸውን በወረዳው ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 22056 አረጋግጠው የሟች ወ/ሮ ምንትዋብ ሕጋዊ ወራሾች ተቃውሞ አቅርበው የሥር ከሳሾች ወላጅ አባት ያገኙት የወራሽነት ማስረጃ ከመሰረዙም በላይ ይህንኑ የወራሽነት ማስረጃ የተሰረዘበትን ውሳኔ በሕግ አግባብ ስለማስለወጣቸው የሥር ተከሳሾች የሚያቀርቡት ክርክር የሌለ መሆኑን ከክርክሩ ሂደት ተመልክተናል፡፡ የሥር ከሳሾች አጥብቀው የሚከራከሩት አከራካሪውን ቤት አቶ አለማየሁ በላቸው ከአቶ ካሳሁን ጥላሁን የገዙት ነው የሚለውን ነጥብም በማንሳት ነው፡፡ በመሆኑም የስር ከሳሾች ግልፅ የዳኝነት ጥያቄ በውርስ የተላለፈላቸው ቤት ከሕግ ውጪ በስር ተከሳሾች የተያዘ መሆኑን የሚያሳይ የክስ ፍሬ ነገር ተጠቅሶ ቤቱ እንዲለቀቅላቸው ይወሰን ዘንድ የሚጠይቅ በመሆኑ አከራካሪው ቤት የስር ከሳሾች አውራሽ የወ/ሮ ምንትዋብ በላቸው ነው ወይስ የስር ተካሶሾች ወላጅ አባት የሆኑት የሟች አቶ አለማየሁ በላቸው ነው? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ፍሬ ነገሩን በሚገባ አጣርቶ ተገቢውን ዳኝነት መስጠትን የሚጠይቅ እንጂ የውርስ ማጣራት ሒደትን ተከትሎ በንብረቱ ላይ ወራሾች ያላቸውን የድርሻ መጠን ለይቶ ዳኝነት መስጠትን የሚጠይቅ አይደለም፡፡የሥር ተከሳሾች ቤቱ አንድ መሆኑንና ግምቱ ተለይቶ ክስ መቅረቡን ጠቅሰው ጉዳዩን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንጂ የወረዳው ፍርድ ቤት አይደለም በማለት የስር ከሳሾችን የሠበር አቤቱታ ደግፈው መልሳቸውን ለዚህ ችሎት አቅርበዋል፡፡

ከእነዚህ ነጥቦች አንጻር ጉዳዩን ስንመለከተው የስር ከሳሾች ክስ በማይገመት የውርስ ሃብት ላይ የቀረበ ያለመሆኑን ነው፡፡ ይልቁንም ከሳሾቹ በውርስ ሊተላለፍልን የሚገባው ቤት ከሕግ ውጪ ተይዞአል ከአሉና ይህ የውርስ ንብረት ተለይቶ የታወቀ እስከሆነ ድረስ ውርስ የሚጣራበት ወይም ሃብቱ የውርስ ስለሆነ ግምቱ ሊታወቅ የሚችል አይደለም ለማለት የሚቻልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 34703 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት በሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉምም የውርስ ሃብቱን የመከፋፈል ጥያቄ ንብረቱ በአይነት ተለይቶና ተገምቶ እስከቀረበ ድረስ በቀረበው ግምት መሰረት የፍርድ ቤቶችን የስረ ነገር ስልጣን ሊወሰንበት የሚገባ

መሆኑን ገልጾ ወስኖል፡፡ በተያዘው ጉዳይ የስር ከሳሾች የክፍፍል ጥያቄ ያቀረቡበት ጉዳይ ሳይሆን የውርስ ንብረቱ ይለቀቅልኝ ጥያቄ ያቀረቡበትና ንብረቱም ተለይቶ የታወቀ በመሆኑ በንብረቱ ግምት የፍርድ ቤቱ የሥረ ነገር ስልጣን የማይወሰንበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ በተሻሻለው የኦሮሚያ ክልል ፍርድ ቤቶች ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 141/2000 አንቀጽ 27 (3) መሰረት ግምቱ ከብር 50,000.00 በላይ የሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት እና ግምቱ ከብር 30,000.00 በላይ የሆነ የሚንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚነሳ ክርክርንአይቶ የመወሰን ስልጣን ያለው መሆኑንም በግልጽ ተመልክቶአል፡፡ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 18 እንደተደነገገው የገንዘብ ግምት ሊወሰን የማይችል ወይም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 23 ስር እንደሰፈረው የውርስ ማጣራት ስራ የተጀመረበት ነው ለማለት የሚቻልበት አግባብም አላገኘንም፡፡

ስለሆነም የሥር ከሳሾች በጠየቁት ግምት መሰረት ጉዳዩ የቀረበለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን ማየቱና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም የስረ ነገር ስልጣኑን ማለፉ ተገቢ ሁኖ እያለ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤቶችን ውሳኔ በመሻር ጉዳዩ በወረዳ ፍርድ ቤት የስረ ነገር ስልጣን የሚውድቅ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ  መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡- ከላይ እንደተገለፀው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ክሱ በይርጋ የሚታገድ አይደለም በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሰጠው ውሳኔ ላይ የቀረበለትን የስር ተከሳሾችን ቅሬታ አልተመለከተውም፡፡ ይህም የሆነው ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የማየት የስረ ነገር ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት የወረዳው ፍርድ ቤት ነው በሚል ድምዳሜ ችሎቱ በመያዙ ምክንያት ነው፡፡ ይህ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት እያሳዩ የስር ተከሳሾች ክሱ በይርጋ ሊታገድ ይገባል፣ ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ይርጋም በውርስ ሕጉ የተመለከተው ነው በማለት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመጨረሻ ፍርድ ሳይሰጥበት ነው፡፡ ከክልል ፍርድ ቤቶች የተነሳ ጉዳይ የሰበር ስርዓት በተዘረጋባቸው ክልሎች በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሳይታይ ለዚህ ችሎት የሚቀርብበት የሕግ አግባብ የሌለ መሆኑን ይህ ችሎት በሰ/መ/ቁጥር 83261 እና በሌሎችም በርካታ መዛግብትበአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀፅ 2(1) መሰረት አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም በአንደኛው ጭብጥ ጉዳዩ በዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሥረ ነገር ስልጣን የሚወድቅ ነው ከተባለና በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ከጸና ወይም ከተለወጠ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት መሆን ያለመሆኑ ተለይቶ ሳይወሰን ለዚህ ችሎት የሠበር አቤቱታ የሚቀርብበት ስነ ስርዓታዊ አግባብ የሌለ በመሆኑ የሥር ተከሳሾች የይርጋ ክርክርን

አስመልክቶ ያቀረቡት አቤቱታ በቅድሚያ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቀርቦ መታየት ያለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡ በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች በመሆኑም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁ. 199980 በ04/04/2008 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 199980 ክርክሩ እንዲቀጥል በማድረግ ከስረ ነገር ውጪ ባሉት ሌሎች ክርክሮች እነ ምስራቅ አለማየሁ (ሶስት ሰዎች) ያቀረቡትን አቤቱታ መርምሮ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 171320 በ27/01/2007 ዓ/ም በሠጠው ውሳኔመሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት መሆን ያለመሆኑን መርምሮ ተገቢውን ውሣኔ ይሰጥ ዘንድ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 341/1/ መሠረት መልሰንለታል፡፡
3. በዚህ ችሎት በሁለቱም መዛግብት ለተደረጉት ክርክሮች ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

የሰ/መ/ቁ.135694

ሐምሌ 20 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሡናይት አድነው

አመልካች፡-

1. አቶ ይርዳው ሽፈራው
2. አቶ መኮንን ሽፈራው
3. አቶ ወርቁ ሽፈራው
4. አቶ ደምሴ ሽፈራው
5. ወ/ሮ ጽጌሬዳ ሽፈራው

1ኛ አመልካች በራሳቸውና በሌሎች ወኪልነታቸው ቀረቡ

ተጠሪ

1. አቶ መስፍን ሽፈራው
2. አቶ ተክሌ ሽፈራው
3. አቶ ደረጀ ሽፈራው
4. አቶ ስብሰቤ ሽፈራው
5. ወ/ሪት ሳቢዘር ሽፈራው
6. ወ/ሪት መስከረም ሽፈራው
7. አቶ አማኑኤል ሽፈራው
8. አቶ ዳዊት ሽፈራው
9. አቶ ጥላሁን ሽፈራው
10. ወ/ሪት አበባ ሽፈራው

1ኛ ተጠሪ በራሳቸውና በሌሎች ወኪልነታቸው ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር ኑዛዜ እንዲፈርስ ከቀረበው ክስ ጋር ተያያዞ የተነሳውን የስልጣን ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የጀመረው የአሁኑ አመልካቾች ባሁኑ ተጠሪዎች ላይ በከምባታ ጠምባሮ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ሲሆን የክሱ ይዘትም የግራ ቀኙ ወላጅ አባት የሆኑት ሟች አቶ ሽፈራው መብራቴ በ13/02/2002 ዓ/ም ለተጠሪዎች ያደረጉት ኑዛዜ በሕገ ወጥ መንገድ የተደረገ ስለሆነ ፈራሽ ሊባል ይገባል የሚል ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎች ለክሱ በሠጡት መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርበዋል፡፡ ተጠሪዎች በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አንስተው እስከዚህ ችሎት የሚያከራክራቸው ነጥብ አመልካቾች በክሳቸው ላይ የጠቀሱት የውርስ ንብረት ግምት 10,000,000.00(አስር ሚሊዮን ብር) በመሆኑና ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ በመሆኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሕጉ ባለው የውክልና ስልጣን ክርክሩን ለማየት የስረ ነገር ስልጣን የለውም የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ የቀረበበት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ይህንኑ መቃወሚያ መሰረት አድርጎ ጉዳዩን መርምሮ ጉዳዩ የፌዴራል ጉዳይ መሆኑን፣ የፌዴራል ጉዳይ በመሆኑ ደግሞ በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ ጉዳዩን ለማየት የስረ ነገር ስልጣን ያለው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመሆኑ ጉዳዩን ለማየት በሕጉ የተሠጠው የውክልና ስልጣን ስር እንደማይወድቅ በምክንያትነት ይዞ ክሱን ዘግቶታል፡፡ በዚህ ብይን የአሁኑ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸው ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርበው ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ሲያከራክር ከቆየ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ብይን ሙሉ በሙሉ አፅንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም አመልካቾች ክስ ሲመስርቱ ግምቱ 10,000,000.00(አስር ሚሊዮን ብር) የሆነ የውርስ ንብረት ለተጠሪዎች በኑዛዜ የተሰጠው በሕገ ወጥ ኑዛዜ ነው፣ ኑዛዜው ፈራሽ ሊሆን ይገባልወ በማለት ዳኝነት የጠየቁት ጠቅላላውን የሟች የውርስ ንብረት እንጂ ለአመልካቾች ሊደርስ የሚገባው ነው በማለት ስላለመሆኑ፣ የንብረት ግምትን ንብረቱ ሊጣራ ይገባል በሚል የተዘረዘረው አመልካቾች ከውርስ የተነቀሉ ስለመሆኑ ፍርድ ቤቱ ሲያጣራ መነሻ እንዲሆን በሚል ሃሳብ እንጂ ለአመልካቾች የሚደርሰውን ንብረት ድርሻ በትክክል በማወቅ ያለመሆኑን ዘርዝረው ጉዳዩ የኑዛዜ ይፍረስልኝ ሁኖ እያለ እንደ ውርስ ንብረት ድርሻ ክፍፍል ጥያቄ ተደርጎ ስልጣኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባለው የፌዴራል የውክልና ስልጣን ስር የሚወድቅ አይደለም ተብሎ ብይን መሰጠቱ ያላግባብ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪዎች በመቅረባቸውም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጎአል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን ከውርስ ሕጉ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮአል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች ሟች አቶ ሽፈራው መብራቴ በ13/02/2002 ዓ/ም ለተጠሪዎች ያደረጉት ኑዛዜ ሕገ ወጥ በመሆኑ ፈራሽ ሊባል ይገባል በማለት አመልካች ክስ ሲመሰርቱ አጠቃላይ የሟች የውርስ ንብረት ግምቱ ብር 10,000,000.00(አስር ሚሊዩን ብር) እንደሆነ ጠቅሰወ ክስ መመስረታቸውን ነው፡፡ ተጠሪዎች የሟች የማይንቀሳቀስ ንብረት ብቻ አጠቃላይ ግምት 10,060,000.00 መሆኑን የጠቀሱና ከዚህ ውስጥ እኩል እንድንካፈል ባሉት መሰረት ቢወሰንላቸው እንኳን አመልካቾች ድርሻችን ነው የሚሉት ንብረት ግምት ከብር 3.3 ሚሊዩን የበለጠ መሆኑንና አመልካቾች ድርሻቸውን በማስላት ያቀረቡት ክስ በመሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች ጉዳዩ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስልጣን ስር የሚወድቅ አደይደም በማለት መወሰናቸው ተገቢ ነው በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በመሰረቱ አንድ ፍርድ ቤት ዳኝነት የሚሰጠው በሕጉ አግባብ በተጠየቀው ጉዳይ ላይ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 182(1) ድንጋጌ ይዘት የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ዳኝነት የሚሰጠውም በከሳሽ የቀረበውን ዳኝነትና በተከሳሽ በኩል የቀረበው መከላከያ መልስ መሰረት በማድረግ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 247፣248 እና 249 ድንጋጌዎች አግባብ ጭብጥ ተይዞ የፍሬ ነገርና የሕግ ነጥብ በጭብጥነት ተይዞ መሆኑ የዳኝነት አሰጣጥ ስርዓት የሚያስገነዝበን ጉዳይ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካቾች የሚች አባታቸውን የውርስ ንብረት ግምት በክሳቸው ላይ መጥቀሳቸውን ሳይክዱ የጠየቁት ዳኝነት ግን ሟቹ በ13/02/2002 ዓ/ም ለተጠሪዎች ያደረጉት ኑዛዜ ሕገ ወጥ በመሆኑ ፈራሽ ነው ሊባል ይገባል የሚል ነው፡፡ በመሆኑም ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤትምበሟቹ በ13/02/2002 ዓ/ም ተደረገ የተባለው ኑዛዜ ሕገ ወጥ ተብሎ ተብሎ ፈራሽ ነው ሊባል ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለውን ጭብጥ ይዞ የኑዛዜውነ ሕጋዊ መሆን ያለመሆኑን ከውርስ ህግ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ አንጻር በመመርመር በኑዛዜው ሰነድ ፈራሽ መሆን ያለመሆን ላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 182(1) አግባብ ዳኝነት ከመስጠት አልፎ አመልካቾች ከሟቹ ውርስ ንብረት ንብረት ላይ በተወላጅነታቸው በሚደርሳቸው የውርስ ንብረት መጠን ላይ ሊፈጸም የሚችል ዳኝነት ሊሰጥ የሚችልበት አግባብ የለም፡፡ አመልካቾች የሟቹን ኑዛዜ ፈራሽ ለማስደረግ ያቀረቡት ዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት ከአገኘ በኂላ በሕጉ አግባብ በሚደርሳቸው የውርስ ንብረት ላይ ተገቢውን ዳኝነት አቅርበው ሌላ ዳኝነት የሚያገኙ ከሚሆኑ በስተቀር በኑዛዜ ፈራሽ ይደረግልኝ ክስ ላይ በድርሻቸው መጠን የዳኝነት ገንዘብ ሳይከፍሉ ሊፈፀም የሚችል ውሳኔ ሊያገኙ የሚችሉበት አግባብ የለም፡፡ ስለሆነም አመልካች የጠየቁት ዳኝነት ኑዛዜው ይፍረስልኝ ሆኖ እያለ በኑዛዜ የሚደርሳቸውን ድርሻ በትክክል ለይተው ሳይጠይቁ የሟችን የውርስ ንብረት ግምት በማስቀመጣቸው ብቻ ይኼው ግምት መሰረት ተደርጎ ከፍርድ ቤት ስረ ነገር ስልጣን ጋር የተነሳው ጥያቄ ተቀባይነት አግኝቶ ክሱ መዘጋቱ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ ተገኝቶአል፡፡

በዚህም መሰረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. በከምባታ ጠምባሮ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 08187 በ3/13/2008 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር06881 በ20/03/2009 ዓ/ም የፀናው ብይን በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካቾች ያቀረቡት ክስ የኑዛዜ ይፍረስልኝ በመሆኑና ይህ ደግሞ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀፅ 14 የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስር ስለሚወድቅ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሕጉ በተሰጠው የውክልና ስልጣን መሰረት ጉዳዩን የማየት ስረ ነገር ስልጣን አለው ብለናል፡፡ በዚህም መሰረት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ተመልክቶ ተገቢው ዳኝነት እንዲሰጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341(1) መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡ ይጻፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሠ/አ

# ንግድ

የሰ/መ/ቁ. 110149

ታህሳስ 27 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

ተፈሪ ገብሩ

አብዬ ካሣሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡-ምድረ ሎዛ የጋራ ሕንጻ መኖሪያ ቤት የህብረት ስራ ማህበር

-ም/ሊ/መንበር አቶ ኃይሌ ገ/ማርያም ቀረቡ

ተጠሪ፡-አቶ ይሕደጎ ኪዳኔ -ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከማህበር አባልነት ማሰናበትን በመቃወም ከቀረበ ክስ ጋር ተያይዞ የተነሳ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን አመልካች አቤቱታውን ለዚህ ችሎት ያቀረበው በኅብረት ስራ ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991 መሰረት በተቋቋመው የሽምግልና ጉባኤ በ01/11/2003 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 115209 በ16/03/2007 ዓ.ም የተሻሻለው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

ተጠሪው በ28/06/2003 ዓ.ም. አዘጋጅተው ለሽምግልና ጉባኤው ያቀረቡት ክስ አጭር ይዘት የማህበሩ መስራች አባል መሆናቸውን፣ማህበሩ አባላት ባልሆኑ ግለሰቦች የሚመራ መሆኑን፣ ወጪና ገቢውም የማይታወቅ መሆኑን፣የቤቶች ዕደላም በማህበሩ ውስጠ ደንብ መሰረት በዕጣ መሆን ሲገባው ከዚህ ውጪ በሆነ አሰራር የታደለ መሆኑን እና ማህበሩ ሌሎችንም ጥፋቶች እየፈጸመ መሆኑን ገልጸው ተገቢው እርማት እንዲደረግ ለማህበሩ እና ቀጥለውም ማህበሩን ለሚቆጣጠረው የቦሌ ክፍለ ከተማ የህብረት ስራ ማህበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ጽ/ቤት በ14/06/2000 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ መጠየቃቸውን፣ይህን የመብት ጥያቄ በማቅረባቸውም ምልዓተ ጉባኤው ሳይሟላ እና ምንም ዓይነት ማስጠንቀቂያ ሳይሰጣቸው ማህበሩ በ07/07/2000

ዓ.ም እና በ02/13/2000 ዓ.ም ባደረጋቸው ስብሰባዎች ተጠሪን ከማህበሩ አባልነት ያሰናበተ መሆኑን የሚገልጽ ሆኖ ውሳኔው ተሽሮ ወደ ማህበሩ እንዲመለሱ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት የተጠየቀበት ነው፡፡

አመልካቹ በ23/07/2003 ዓ.ም በፍሬ ጉዳዩ ረገድ በሰጠው መልስ ተጠሪው ከማህበሩ እንዲሰናበቱ የተደረገው በማህበሩ ላይ በፈጸሙት በደል መሆኑን፣ከእነዚህም መካከል በፀሀፊነት ተመርጠው አልሰራም ማለታቸው፣በማህበሩ ላይ የማቴርያል ኪሳራ እንዲደርስ ማድረጋቸው/ለምሳሌ በብር 290 የሚገዛን አንድ መኪና ድንጋይ በራሳቸው ፈቃድ በብር 300 መግዛታቸው/፣ክፍያን በወቅቱ አለመፈጸማቸው፣ቤቶቹ ተሰርተው ካለቁ በኃላም ቢሆን እቀያይራቸዋለሁ ብለው መዛታቸው እና ፀሐፊ ሆነው በሰሩበት ጊዜ የያዟቸውን ሰነዶች እንዲያስረክቡ ሲጠየቁ ማዘግየታቸው የሚጠቀሱ መሆኑን  እና ከአባልነት የማሰናበት ውሳኔው የተላለፈው በተሟላ ምልዓተ ጉባኤ መሆኑን በመግለጽ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ተከራክሮአል፡፡

ጉባኤውምየግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ በ07/07/2000 ዓ.ም ውሳኔ የተላለፈው ባልተሟላ ምልዓተ ጉባኤ እንደሆነ በአመልካቹም መታመኑን፣በ02/13/2000 ዓ.ም በተደረገው ስብሰባም ከማህበሩ 24 መስራች አባላት መካከል በአካል ተገኝተው ድምጽ የሰጡት ዘጠኝ አባላት ብቻ መሆናቸውን፣አራቱ መስራች አባላት ድምጽ  ሰጥተዋል የተባለው በአዋጅ ቁጥር 147/1991 አንቀጽ 18 ከተመለከተው ውጪ በውክልና በመሆኑ ድምጻቸው ሊቆጠር የማይገባው መሆኑን፣ተተኪ አባላት ናቸው የተባሉት ስምንት ሰዎች ስለመተካታቸው ለማህበራት ማደራጃ ጽ/ቤት በደብዳቤ የተገለጸ ቢሆንም በማህበሩ ውስጥ የተተኩበትን አግባብ የሚመለከት ሰነድ እንዲያቀርብ ተጠይቆ ማህበሩ ማናቸውንም ሰነድ ማቅረብ ያልቻለ በመሆኑ ድምጻቸው ሊቆጠር የማይገባው መሆኑን፣በዚህ አግባብ በማህበሩ ውስጠ ደንብ ከተመለከተው ስርዓት ውጪ ቁጥራቸው ከግማሽ በታች በሆነ የማህበሩ አባላት የተሰጠ ውሳኔ አንድን አባል የማሰናበት ውጤት ሊኖረው የማይገባ መሆኑን፣ተጠሪው የፈጸሙት ጥፋት አለ ቢባል እንኳ በማህበሩ ውስጠ ደንብ አንቀጽ 17 እና 23 መሰረት ቅድመ ማስጠንቀቂያ እና ተግሳጽ በጽሁፍ ሳይሰጣቸው በቀጥታ የስንብት እርምጃ መውሰድ የማይቻል መሆኑን ገልጾ ተጠሪው ወደ ማህበሩ አባልነት ተመልሰው ድርሻቸውን በዕጣ የማግኘት መብትን ጨምሮ መብቶቻቸው እንዲከበሩ እና ግዴታዎቻቸውን እንዲወጡ እና የማህበሩ ሂሳብም በውጪ ኦዲተር እንዲመረመር በአብላጫ ድምጽ ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት አመልካች ባቀረበው ይግባኝ ሳቢያ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የሽምግልና ጉባኤው በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ እንዲሰናበት የተደረገን አባል ወደ ማህበሩ እንዲመለስ የመወሰን ስልጣን እንደሌለው እና ክሱም በይርጋ

የታገደ እንደሆነ ገልጾ የሽምግልና ጉባኤውን ውሳኔበመዝገብ ቁጥር 115209 በ22/08/2004 ዓ.ም ሽሮት የነበረ ቢሆንም የአሁኑ ተጠሪ በተራቸው ባቀረቡት ይግባኝ ሳቢያ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔን ሽሮ የፍሬ ጉዳይ ክርክሩን መርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥበት በመዝገብ ቁጥር 80395 በ30/07/2005 ዓ.ም በተሰጠ ውሳኔ ጉዳዩን ለከፍተኛ ፍርድ ቤት የመለሰው መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭ ያመለክታል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በተመለሰለት መሰረት የፍሬ ጉዳይ ክርክሩን መርምሮ የማህበሩ ሂሳብ እንዲጣራ ውሳኔ የተሰጠው ባልተጠየቀ ዳኝነት መሆኑን ገልጾ በዚህ ረገድ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል በመሻር እና ተጠሪው ወደ ማህበሩ እንዲመለሱ የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል ግን በማጽናት የጉባኤውን ውሳኔ አሻሽሎአል፡፡አመልካች ለዚህ ችሎት ያቀረበው አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ ተጠሪን ከማህበሩ ለማሰናበት በውክልና ድምጽ የሰጡት እና ተተኪ አባላት የሆኑትም ጭምር የማህበሩ አባላት ናቸው ወይም አይደሉም ሳይባል ድምጻቸው አይቆጠርም ተብሎ በስር ፍርድ ቤቶች የመወሰኑን አግባብነት ከአዋጁ እና ከማህበራት መተዳደሪያ ደንብ እንጻር ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ነጥብ አንጻር መርምረናል፡፡

በዚህም መሰረት ተጠሪውን ከማህበር አባልነት ለማሰናበት በውክልና ድምጽ የሰጡት አባላት ድምጽ ሊቆጠር አይገባውም በሚል የተሰጠውን የውሳኔ ክፍል በተመለከተ ማንኛውም የመሰረታዊ ማህበር አባል በስብሰባ ላይ ተገኝቶ ራሱ ድምጽ መስጠት ያለበት ስለመሆኑ በኅብረት ስራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 147/1991 /በአዋጅ ቁጥር 402/1996 እንደተሻሻለ/ በአንቀጽ18 (2) ስር ተመልክቶአል፡፡ማንኛውም አባል በጠቅላላ ጉባኤ ላይ በአካል ተገኝቶ ድምጽ መስጠት ያለበት ስለመሆኑም የአመልካች ማህበር መተዳደሪያ ደንብ በአንቀጽ 8 (1) ስር በግልጽ ያመለክታል፡፡ይህ አጠቃላይ መርህ ሊታለፍ የሚችለው መረጃ ሊቀርብበት የሚችል ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ሲያጋጥም ስለመሆኑም በዚሁ ደንብ በአንቀጽ 21.1.5 ስር ተመልክቶአል፡፡በተያዘው ጉዳይ ተጠሪውን ከማህበሩ አባልነት ለማሰናበት አራት ሰዎች ድምጽ የሰጡት በውክልና መሆኑ አልተካደም፡፡ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ሲያጋጥም በውክልና ድምጽ መስጠት እንደሚቻል ገልጾ አመልካች በሰበር አቤቱታው የተከራከረ ቢሆንም አራቱ ሰዎች በውክልና ድምጽ እንዲሰጡ የተደረገው ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ምክንያት ስለመሆኑ በ02/13/2000 ዓ.ም. በተያዘው ቃለ ጉባኤ ላይ የተገለጸ ነገር ስላለመኖሩ እና በዚህ ረገድ አመልካቹ በስር ፍርድ ቤቶች ያቀረበው ማስረጃ ስላለመኖሩ ተጠሪው በሰበር መልሳቸው ያቀረቡትን የክርክር ነጥብ አመልካቹ በመልስ መልሱ ማስተባበያ አልሰጠበትም፡፡ጉዳዮችን በውክልና የማስፈጸም መብትን አስመልክቶ በአዋጁ

እና በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች በሕገ መንግስቱ፣በቤተሰብ ሕጉ እና በፍትሐብሔር ሕጉ የተመለከቱትን አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች የሚቃረኑ ናቸው በማለት አመልካች እያቀረበ ያለው ክርክርም የአዋጅ ቁጥር 147/1991 "ን" ዓላማ እና የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 8 (1) እና 21.1.5 ግልጽ ድንጋጌዎች መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ ተቀባይነት ሊሰጠው የሚገባ ሆኖ አልተገኘም።በመሆኑም ማንኛውም የማህበሩ አባል በጠቅላላ ጉባኤ በሚተላለፉ ውሳኔዎች ላይ ድምጽ መስጠት ያለበት በመርህ ደረጃ በአካል ተገኝቶ ስለመሆኑ በአዋጁ እና በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ በግልጽ የተመለከተ እስከሆነ ድረስ እና የዚህን መርህ ተፈጻሚነት የሚያስቀር የተለየ ሁኔታ የነበረ ስለመሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች በአመልካቹ የቀረበ ክርክር እና ማስረጃ እስከሌለ ድረስ ተጠሪውን ከማህበሩ አባልነት ለማሰናበት በውክልና ድምጽ የሰጡት አባላት ድምጽ ሊቆጠር የሚገባው አይደለም በማለት በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የውሳኔ ክፍል የሚነቀፍበትን ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም።

ተተኪ አባላትን በተመለከተ ስምንቱ ተተኪ አባላት በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ተገኝተው ተጠሪውን ከማህበር አባልነት በማሰናበት ውሳኔ ላይ ድምጽ የሰጡት በ02/13/2000 ዓ.ም መሆኑ እና አመልካቹ ማህበር ተጠቃሾቹ ግለሰቦች በሌሎች አባላት ምትክ በማህበሩ የገቡ ስለመሆኑ ለክፍለ ከተማው የማህበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ጽ/ቤት የገለጸው ድምጹ ከተሰጠ ከአንድ ወር በኃላ በ27/01/2001 ዓ.ም መሆኑን የሽምግልና ጉባኤው ውሳኔ ያመለክታል።አመልካቹም የእነዚህን ፍሬ ነገሮች ክንውን ቅደም ተከተል አስመልክቶ ያቀረበው የማስተባበያ ክርክር የለም። ስምንቱ ተተኪ አባላት በማህበሩ አባልነት የተተኩበትን አግባብ በሚያመለክት ማህበሩ ማናቸውንም ዓይነት ሰነድ ማለትም የውርስ፣የስጦታ፣የሽያጭ፣ድርሻ የማስተላለፍ፣በተተኪ አባልነት የመቀበል ቃለ ጉባኤ እና መሰል ሰነዶችን እንዲያቀርብ ተጠይቆ ማቅረብ ያልቻለ ስለመሆኑም በጉባኤው ውሳኔ ላይ ሰፍሮ ይገኛል።አመልካቹ እነዚህ ሰነዶች ተሟልተው የነበረ ስለመሆኑ በሰበር አቤቱታው ላይ ያቀረበው ክርክር የለም።እንዲህ ከሆነ ደግሞ ተተኪ አባላቱ ተጠሪው ከማህበር አባልነት እንዲሰናበቱ ድምጽ በሰጡበት ቀን በርግጥ የማህበሩ አባላት የነበሩ መሆኑን ማረጋገጥ የሚቻልበት አግባብ አይኖርም።በመሆኑም ተተኪ አባላት ናቸው በተባሉት ሰዎች የተሰጠውንም ድምጽ ባለመቀበል በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የውሳኔ ክፍልም የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም።

ተጠሪን ከማህበሩ ለማሰናበት በውክልና ድምጽ የሰጡት እና ተተኪ አባላት የሆኑትም ጭምር የማህበሩ አባላት ናቸው ወይም አይደሉም ሳይባል ድምጻቸው አይቆጠርም ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለማጣራት በሚል ለክርክሩ በጭብጥነት የተያዘውን ነጥብ በተመለከተ በመሰረቱ በጉባኤው ዘንድ አከራካሪ ሆኖ የቀረበው እና ውሳኔ ያረፈበት ጭብጥ ተጠቃሾቹ ግለሰቦች ተጠሪውን ከማህበሩ አባልነት ለማሰናበት በተላለፈው ውሳኔ ላይ የሰጡት ድምጽ ሊቆጠር ይገባል

ወይስ አይገባም? የሚል እንጂ የማህበሩ አባላት ናቸው ወይስ አይደሉም? የሚል ባለመሆኑ የጉባኤው ውሳኔ የድምጽ አሰጣጥ ስርዓቱን በተመለከተ ካልሆነ በቀር በሌሎች ጉዳዮች ረገድ የተጠቃሾቹን ግለሰቦች መብት የሚነካ አይደለም።በመሆኑም በውክልና ድምጽ የሰጡትም ሆነ ተተኪ አባላት ከማህበሩ ጋር ያላቸውን የግንኙነት ሁኔታ በጭብጥነት መያዙም ሆነ በዚህ ነጥብ ላይ ውሳኔ ማሳረፉ አስፈላጊ የሚሆንበት ምክንያት አልተገኘም።

ሲጠቃለል አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል።

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በአዋጅ ቁጥር 147/1991 መሰረት በተቋቋመው የሽምግልና ጉባኤ በ01/11/2003 ዓ.ም. በአብላጫ ድምጽ ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 115209 በ16/03/2007 ዓ.ም. የተሻሻለው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ፀንቶአል።
2. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ።
3. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

መ/ይ

የሰመ/ቁ.123984

ሚያዚያ 25 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

ተፈሪ ገበሩ

ቀነዓ ቂጣታ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- አቶ ጌታቸዉ መሸሻ - ጠበቃ አለማየሁ ብርሀኔ ቀርበዋል፡፡

ተጠሪ፡- አቶ ተሾመ ወልዴ - ጠበቃ ገመዳ ስፋው ቀርበዋል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.232927 በ26/04/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልኝ በማለት የአሁን አመልካች ያቀረበዉን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ በአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ፣ የአሁን ተጠሪ ተከሳሽ ሁኖ ሲከራከሩ የነበረ ሲሆን፣ ከሳሽ ባቀረበዉ ክስ ከሳሽ በ16/3/2006 ዓ.ም በቼክ ቁጥር ሲ 926821 በሆነዉ ብር 100000 /አንድ መቶ ሺ.ህ/ ለተከሳሽ አበድሬዉ ስላልመለሰልኝ ይህን ገንዘብ ከሕጋዊ ወለድ 9% ጋር እንዲከፍለኝ በማለት ከሷል፡፡ የሥር ተከሳሽ ባቀረበዉ መልስ ከከሳሽ ገንዘብ አልተበደርኩም እኔን ለመክሰስ መብቱን አላስረዳም በማለት ተከራክሯል፡፡

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ ከሳሽ በክስ የተጠቀሰዉን ብር 100000 /አንድ መቶ ሺ.ህ/ ለተከሳሽ ስለማበደሩ የፍ/ብ/ሕ/ቁ.2472 በሚደነግገዉ አግባብ ያቀረበዉ ማስረጃ ስለሌለ ከሳሽ በዚህ ገንዘብ ተከሳሽን ለመጠየቅ ሕጋዊ መብት የለዉም፣ ቼኩን የተቀበልኩት ከሳሽ ገንዘብ አበድሮኝ ሳይሆን አስቀድሞ የሰጡሁትን ገንዘብ ከፍሎኝ ነው በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡

የሥር ከሳሽ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኛቸዉን በማከራከር የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የሥር ከሳሽ አሁንም ይህን ዉሳኔ በመቃወም የሰበር አቤቱታ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም ችሎቱ የቀረበዉን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ የሥር ፍ/ቤት ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡

የአሁን አመልካች የካቲት 17 ቀን 2008 ዓ.ም የተጻፈ ሶስት ገጽ አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን፣ የሥር ፍ/ቤቶች ዉሳኔዎች መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመመባቸዉ በመሆናቸዉ ተሽረዉ ተጠሪ የተበደረዉን ብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ/ ከሕጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍለዉ በዝርዝር ቅሬታቸዉን አቅርቧል፡፡

የሰበር አጣር ችሎት ይህን ጉዳይ በማየት ፣አመልካች ለተጠሪ ቼክ ሰጥቷቸዉ ከባንክ ገንዘብ መዉሰዳቸዉ ተረጋግጦ እያለ የብድር ዉል አቅርበዉ አላስረዱም በማለት የተከሰሱበትን ገንዘብ እንዳይከፍሉ የመወሰኑን አግባብነት ከሰ.መ.ቁ.31737 ከተሰጠዉ ትርጉም አንጻር ለመመርመር ሲባል፣ አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘዉ መሰረት በ1/2/2009 ዓ.ም የተጻፈ ሶስት ገጽ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት በአጭሩ፡--የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ዉሳኔዎች የሕግ ስህተት የሌላቸዉ ስለሆነ የቀረበዉ አቤቱታ ዉድቅ ሆኖ የሥር ዉሳኔ እንዲጸናልኝ በማለት በዝርዝር ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኛቸዉን ክርክር ለሰበር አቤቱታዉ መነሻ ከሆነዉ ዉሳኔ እና አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር እንደሚከተለዉ መርምሮታል፡፡ የአሁን አመልካች ባቀረበዉ ክስና ክርክር ለተጠሪ በቼክ አንድ መቶ ሺህ ብር አበድሬዉ ስላልከፈለኝ እንዲከፍለኝ በማለት ጠይቋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ቼኩን መቀበሉን ሳይክድ ቀደም ሲል የሰጠሁትን ገንዘብ መልሶልኝ ነዉ፣ ገንዘብ አልተበደርኩም፣ ገንዘብ የተበደርኩኝ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/2472 መሰረት የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረበም በማለት ተከራክሯል፡፡ ከግራ ቀኛቸዉ ክርክር መገንዘብ እንደሚቻለዉ የአሁን ተጠሪ ከአመልካች ቼኩን ተቀብሎ ገንዘቡን ከባንክ መዉሰዱን ሳይክድ፣ ነገር ግን ገንዘብ ተብድሬዉ አይደለም በማለት የብር 100000 /አንድ መቶ ሺህ/ ብድር መኖሩን ክዶ ተከራክሯል፡፡ ይህ ከሆነ የአሁን አመልካች ለተጠሪ ይህን ገንዘብ በብድር ስለመስጠቱ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.259 /1/ በሚደነግገዉ አግባብ የማስረዳቱ ሸክም የእርሱ ነዉ፡፡ አመልካች በዚህ መሰረት አግባብነት ባለዉ ማስረጃ ብድር መኖሩን ያስረዳ እንደሆነ ተጠሪ ደግሞ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.259 /2/ በሚደነግገዉ መሰረት የመከላከያ ማስረጃ አቅርቦ የማስረዳት ሸክም ይኖርበታል ማለት ነዉ፡፡

ይህ ከሆነ የአሁን አመልካች ያቀረበዉን የብር 100000 /አንድ መቶ ሺህ/ ብድር ገንዘብ ለማስረዳት አግባብነት ያለዉ ማስረጃ ምንድን ነዉ? የሚለዉ ነጥብ መታየት ያለበት ጉዳይ ነዉ፡፡ አመልካች ባቀረበዉ ክርክር ከክሱ ጋር አያይዞ ያቀረበዉ ቼክ የብድር ዉሉን ለማስረዳት አግባብነት እንዳለዉ ነዉ፡፡ ነገር ግን በመሰረቱ ቼክ የተወሰነ ገንዘብ ለመክፈል ሐተታ የሌለበት ትዕዛዝ የያዘና ቼኩም እንደቀረበ የሚከፈል ስለመሆኑ በንግድ ሕጉ ቁጥር 827 /ሀ/ እና 854 ሥር ተደንግጓል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለዉ ቼክ ክፍያ የሚፈጸምበት ወይም

የክፍያ ሰነድ መሆኑን ነዉ፡፡ ከዚህ ዉጭ ግን ቼክ የብድር ዉልን ተክቶ ብድር መኖሩን ለማስረዳት አግባብነት ያለዉ ሰነድ ነዉ ለማለት የሚያስችል የሕግ መሰረት የለም፡፡ ይህ ከሆነ አመልካች ከክሱ ጋር የቀረበዉ ቼክ የብድር ዉል መኖሩን ያረጋግጣል በማለት ያቀረበዉ ክርክር ተቀባይነት የለዉም፡፡

የአሁን አመልካች በክሱ የጠቀሰዉ ብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ/ ለተጠሪ በብድር ሰጥቼዋለሁ የሚል ከሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.2472 የተመለከተዉን አግባብነት ያለዉን ማስረጃ በማቅረብ የማስረዳት ሸክም አለበት፡፡ የዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀጽ 1 እንደሚደነግገዉ ፣በብድር የተሰጠዉ ገንዘብ 500 /አምስት መቶ/ የኢትዮጵያ ብር በላይ ሲሆን የብድሩ ዉል በጽሑፍ ወይም በፍ/ቤት በተደረገ የእምነት ቃል ወይም መሐላ ካልሆነ በቀር ለማስረዳት አይቻል፣ በማለት ደንግጓታል፡፡ በዚህ አግባብ ሲታይ የአሁን አመልካች ለተጠሪ ብር 100,000 ስለማበደሩ ወይም የብድር ዉል ስለመኖሩ በዚህ ድንጋጌ አግባብ በሚቀርብ ማስረጃ ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡ ነገር ግን አመልካች ደግሞ በዚህ መሰረት ያቀረበዉ የብድር ዉል ሰነድ ስለሌለ ለተጠሪ ገንዘቡን ስለማበደሩ የማስረዳት ሸክሙን ተወጥቷል ለማለት አይቻልም፡፡ የአሁን አመልካች ከጀምሩ በሕጉ አግባብ የብድር ዉል መኖሩን ባላስረዳበት ሁኔታ ተጠሪ የመከላከያ ማስረጃ አቅርቦ ገንዘቡን እንዳልተበደረዉ የሚያስረዳበት የሥነ ሥርዓት ሕግ አካሄድ ስለሌለ በዚህ ረገድ ያቀረበዉ ቅሬታ ተቀባይነት የለዉም፡፡ የሰበር አጣር ችሎት አቤቱታዉ ያስቀርባል በሚልበት ጊዜ የጠቀሰዉ የሰ.መ.ቁ.31737 /ቅጽ 5/ ላይ የተሰጠዉ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሲታይ በመጀመሪያ ደረጃ ጉዳዩ የሚመለከተዉ የሐዋላ ወረቀት እንጂ ቼክን ስላልሆነ በዉሳኔዉ የተጠቀሱት ፍሬ ነገሮችም ተመሳሳይነት ስለሌላቸዉ ተፈጻሚነት የለዉም ብለናል፡፡

ሲጠቃለል የሥር ፍ/ቤቶች የአሁን አመልካች ለተጠሪ ብር 100000 /አንድ መቶ ሺህ/ ያበደረ ስለመሆኑ አግባብነት ባለዉ ማስረጃ ስላላስረዳ ክሱ ተቀባይነት ያለዉም በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ የሰጡት ዉሳኔ በሕጉ አግባብ የተሰጠ ነዉ ከሚባል በስተቀር በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለሌለዉ የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.20647 በ15/11/2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እና ይህን ዉሳኔ በማጽናት የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.226770 በ07/04/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ እንዲሁም የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.232927 በ26/4/2008 ዓ.ም የሰጠዉ ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመባቸዉ ስለሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.348 /1/ መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ ብለናል፡፡

3. ግራ ቀኛቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

4. በ27/12/2008 ዓ/ም እና ጥቅምት 16 ቀን 2009 ዓ/ም የተሰጠው የእግድ ውሳኔ ተነስቷል ይፃፍ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

የሰ/መ/ቁጥር 118246

ሰኔ 23 ቀን 2009 ዓ/ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ አርሺሶ

ሠናይት አድነው

አመልካች፡- የሲዳሞ ተራ ህንጻ ስራ አክሲዮን ማህበር - ጠበቃ ሰላም ተሾመ ቀረቡ

ተጠሪ፡- ወ/ሮ አብረኸት ሀብተእዝጊ ተማኑ ወራሾቾች

1. አቶ ሚካኤል አብርሃ
2. አቶ ሳሙኤል አብርሃ
3. አቶ ጴጥሮስ አብርሃ
4. ወ/ሮ ሳባ አብርሃ
5. ወ/ሮ ሄለን አብርሃ
6. ወ/ሮ ፀጉ አብርሃ
7. ወ/ሮ ዘውዲቱ አብርሃ
8. ወ/ሮ አይዳ አብርሃ
9. አቶ ጳውሎስ አብርሃ

ተወካይ በርሄ ፀጋዬ ቀረቡ

በዚህ መዝገቡ የቀረበው የአመልካች የሠበር አቤቱታ እና በሰ/መ/ቁጥር 120709 የቀረበው የተጠሪዎች የሠበር አቤቱታ መነሻቸው በስር ፍርድ ቤትም ሆነ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም አንድ ላይ በተካሄዱ የክርክር መዛግብት በመሆኑ መዛግብቱን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 11 መሰረት በማጣመር መርምረን ተከታዩን ወስነናል፡፡ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአክሲዩን ብዛት ከፍ ብሎ እንዲመዘገብ የቀረበውን ክስ መነሻ አድርጎ የተደረገን ክርክር የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች አውራሽ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሚያዚያ 29 ቀን 2005 ዓ/ም በአመልካች ማህበር ላይ በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም፡- በጥቅምት 22 ቀን 1993 ዓ/ም ከሌሎች 27 ሰዎች ጋር በመሆን በአመልካች ማህበር ውስጥ በመስራችነት የተደራጁ መሆኑን፣ በመስራች አባልነታቸውም 4 ሼር በመግዛት ለእያንዳንዱ ብር 50,000.00 በጠቅላላው ብር 200,000.00 መክፈላቸውን፣ በተጨማሪም በጥቅምት 22 ቀን 1993 ዓ/ም በተካሄደው ጉባኤ በተወሰነው መሰረት ለህንጻው ግንባታ

የሚውል አባላቱ እንዲያዋጡ በተወሰነው መሰረት ብር 100,000.00 መክፈላቸውን፣ ይህን በተጨማሪ የተከፈለውን ብር 100,000.00 በተመለከተ በቃለ ጉባኤው እንደተገለፀው ላዋጡት አባላት በአክሲዮን ግዥ እንደሚታሰብላቸው መመልከቱን፣ በዚህ መሰረትም ከሳሽ በድምሩ 6 የአክሲዮን፣ ዋጋቸውን ብር 300,000.00 ከፍለው እያለ መብታቸውን በሚጎዳ አኳኃን የአክሲዮን ብዛቱ አራት አክሲዮን ብቻ ሁኖ ተመዝግቦ እንደሚገኝ፣ በሌላ በኩልም የአክሲዮን ድልድልን በተመለከተ ከሳሽ የ6 አክሲዮን ዋጋ ብር 300,000.00 በመክፈል መስራች አባል መሆን የሚገባቸው መሆኑ እንደተጠበቀ የአክሲዮን ማህበሩ አባላት በሕጉ በሼራቸው መጠን እኩል ድርሻ እንዳላቸው የተመለከተ ቢሆንም መንግስት ለተከሳሽ ማህበር በሰጠው የግንባታ ቦታ ሰፋሪ የነበሩት ሰዎችም በአባልነት እንዲካተቱ በተወሰነው መሰረት 81 አባላት እንዲኖሩት መደረጉን፣ ይሁን እንጂ ነባር መስራች አባላት የሼር መጠን በተጨማሪ አክሲዮን የማግኘት መብት እንዳላቸው በሕጉ ተቀመጦ የተጨማሪ አክሲዮን ድርሻ ድልድል በምን መልኩ እንደተከናወነ ሳይታወቅ ቀደም ሲል አንደ፣ሁለት እና ሶስት የአክሲዬን ድርሻ የነበራቸው በአሁኑ ወቅት ባለ 8 እና 10 ባለአክሲዮን እንዲሆኑ መደረጉን፣ በዚህም መሰረት ወደ 13 የሚሆኑ አባላት ከ8-20 አክሲዮን እንዲኖራቸው መደረጉን፣ ይህም አዲስ ገቢዎችና ነባር አባላትን የሚመለከት መሆኑን፣ በመሆኑም ከሳሽ በመስራች አባልነታቻውና በከፈሉት የ6 አክሲዮን ዋጋ የ6 አክሲዮን ድርሻ ሲገባቸው አራት አክሲዮን ብቻ እንዲኖራቸው በማድረግና ከአዲስ አክሲዮኖች በተጨማሪ አክሲዮን ሊሰጣቸው ሲገባ ባልታወቀና ከመተዳደሪያው ደንቡ ውጪ በተከናወነ የአክሲዮን ድልድል ተከሳሽ ማኅበር የከሳሽን መብት መንፈጉን፣ የተከናወነው የአክሲዮን ድልድል ተገቢ እንዳልሆነ በመግለፅ ከሌሎች አምስት አባላት ጋር በመሆን ለማህበሩ ቦርድ ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት በ12/02/2005 ዓ/ም በተጻፈ ደብዳቤ በተሰጠ መልስም በመስከረም 2004 ዓ/ም በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት ለፊርማ የቀረበው ቃለ ጉባኤ በጉዳዩ ላይ በ13/08/2004 ዓ/ም ተወያይተንበታል በሚል እምነት በቅን ልቦና የተደረገ ሲሆን ቅሬታ ካስከተለ ግን ቀሪ ሆኖ ለጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ እንደሚቀርብ ገልፀው በደብዳቤ መልስ የሰጧቸው ቢሆንም በዚህ ደብዳቤ መሰረት የተወሰደ ማስተካከያ እርምጃ የሌለ መሆኑንና የማህበሩ አባላት በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት በመቅረብ የአባልነት ፊርማቸውን እንዲያኖሩ በተነገረው መሰረት ለመፈረም በቦታው ሲሄዱም የአባላቱ ቁጥር በጉባኤው በተነገረው መሰረት 81 አባላት ሳይሆን 89 ተብሎ ተዘርዝሮ መገኘቱን፣ ይህም ተጨማሪ 8 አባላት በምን መልኩ እንደተጨመሩ የማይታወቅ መሆኑን፣ ጉባኤው ያሳለፋቸው ውሳኔዎችና አዲስ አክሲዮን መጨመር እና ድልድሉን በተመለከተ የመተዳደሪያ ደንቡና የመመስረቻ ፅሁፍ አባላት በሚፈርሙበት ቦታ ከፊርማ ወረቀቱ ጋር አብሮ መቀመጥ እንዳለበትና ከፈለጉ ፊርማቸውን የሚያኖሩ አባላት ይህንኑ ፅሑፍ እየተመለከቱ ተረድተው መፈረም እንዳላባቸው በሕጉ ተደንግጎ እያለ እነዚህ ሰነዶችን ለማየት ጥያቄ ቢያቀርቡም ከፈለጋችሁ ፊርማችሁ ውጪ እንጂ አይሰጥም በማለታቸው የተወሰኑት አባላት

ሳይፈርሙ ሊወጡ መቻላቸውንና በዚህ የማህበሩ ድርጊትም የከሳሽ መብት መነፈጉን እንዲሁም ሌሎች አባላት በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የፈረሙትን ሰነድ ተከሳሽ ማኅበር ለማፅደቅ በዝግጅት ላይ እንደሚገኝ ዘርዝረው ከሳሽ የተከሳሽ ማህበር  መስራች አባል በመሆን የከፈሉት የስድስት አክሲዮን ዋጋ ብር 300,000.00 ታሳቢ ተደርጎ ተጨማሪ የ14 አክሲዮን ዋጋ ከፍለው የ20 አክሲዮን ባለቤት እንዲሆን ይወሰንልኝ፣ የተከሳሽ ማኅበር የመተዳደሪያ ደንብና የመመስረቻ ፅሑፍ በዚህም መሰረት የሆነው የቃለ ጉባኤ ሰነድ የማንበብ መብታቸው እንዲከበርና ሰነዶቹ እንዲሰጧቸው፣ በተጨማሪ እንዲገቡ የተደረጉት 8 አዲስ አባላትም በምን ሁኔታ አባል እንደሆነ ተጣርቶ  ውሳኔ እንዲሰጣቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች ለክሱ ግንቦት 21 ቀን 2005 ዓ/ም በሰጠው መከላከያ መልስም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክሮችን አቅርቧል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነትም ክሱ በተፋጠነ ስነ ሰርዓት ለመቅረብ በሕጉ የተመለከቱትን መመዘኛዎችን የማያሟላ መሆኑን፣ የማህበሩ አባላት 81 ሁነው እያለ 89 የተባለው በማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን፣ ከሳሽ ከኢትዩጵያ ከወጡ ከ15 አመት በላይ የሆናቸው ከመሆኑም በላይ ኤርትራዊ ዜግነት እንዳላቸው ውክልና የሰጡት ኢትዩጵያ ኢምባሲ ሳይሆን ኢትዩጵያዊ ስም ካለው የአሜሪካን አዋዋይ ዘንድ ሆኖ ከዩ.ኤስ. ውጭ ጉዳይ በአሜሪካ የኢትዩጵያ ኢምባሲ መረጋገጡ ሁሉንም ነገር በወኪል የሚሰራ በመሆኑ በግለሰቧ ሁኔታ የተጣራ ባለመሆኑ ከሳሽ ራሳቸው እንዲቀርቡ ወይም አሜሪካ አገር ኢትዩጵያ ኢምባሲ በአካል ቀርበው ለፍርድ ቤቱ ሪፖርት እንዲደረግ የሚሉትን ነጥቦችን አንስቶ ተከራክሯል፡፡ በፍሬ ነገር ደረጃ ደግሞ የተከሳሽ ማህበርን ሕጋዊ አቋም አስመልክቶ ማህበሩ በ1992 ዓ/ም በሶስት ሰዎች ሲቋቋም የመርካቶ አካባቢ የመልሶ ማልማት ፕሮግራም ያልወጣ ስለመሆኑ ከሳሽ በ1993 ዓ/ም ባለአክሲዩን ሲሆኑም ከሳሽ ተጨማሪ አክሲዩን ያወጣ  ስለመሆኑና ከዚህ በኋላ ግን በ18/06/99 ዓ/ም ማህበሩ የሊዝ ውል ተዋውሎ በ28/07/98  9430 ካ/ሜትር ቦታ ሲዳሞ ተራ አከባቢ በሊዝ ቦታ መግዛቱን፣ ይሁን እንጂ ከዚህ ቦታ ውስጥ ሌሎች በማህበርነት የተደራጀ ሶስት ማህበራት ለአዲስ አበባ አስተዳደር መሬት ልማትና አስተዳደር ቦርድ ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት የተወሰነው ቦታ ተቀንሶ ለሌሎች ማህበራት እንደተሠጠና ለእያንዳንዱ ማህበር በተሰጠው ቦታ ላይ የነበሩና በማህበር ያልተካተቱት ተነሺዎች በነበሩበት ቦታ በተደራጁት ማህበራት እንዲካተቱና ይህም ሲረጋገጥ ማህበራቱ የሊዝ ውሉን እንዲዋዋሉ መወሰኑን፣ ከሳሽም በተከሳሽ ማህበር ባለአክሲዩን ቢሆኑም የነበራቸውን ነባር ይዞታና የቤት ቁጥር መሰረት አድርገው በልጃቸው በአቶ ኤፍሬም አብርሃ ወ/ጊዩርጊስ ስም በሲኒማ ራስ ማህበር ውስጥ የተደራጁ መሆኑን፣ ይሁንና ማህበሩ ኃ.የተ.የግል ማህበር በመሆኑ ከሳሽ ሌላ ማኅበር ውስጥ ስለተደራጁ ብቻ ከአባልነት ለማስወጣት ባለመቻሉ በባለአክሲዮንነታቸው እንዲቀጥሉ መደረጉን፣ በሌላ በኩል በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሊዝ አፈጻፀም መመሪያ ቁጥር 1/2002

አንቀፅ 34.10 ድንጋጌ መሰረት ለሚደራጁ የንግድ ማህበራት የተወሰነው ቦታ ላይ የነበሩና ይዞታቸው የፈረሰባቸው ነጋዴዎች/ሰዎች/ በማህበራቱ በአባልነት እንዲካተቱ መደረጉን፣ በዚህም መሰረት በተከሳሽ ማህበር አባል ከነበሩት 27 ባለአክሲዮኖች በተጨማሪ 54 አዲስ አባላት ባለአክሲዮኖችን ማካተት የግድ መሆኑን፣የማህበሩ አመራር አካላት የነባርና አዲስ የሚገቡ አባላት የአክሲዮን ድልድል ምን መሆን እንደአለበት በሚለው ጉዳይ ላይ ከህግ አንጻር ተወያይተውበት የአባላቱን፣ የነባር ይዞታ መጠንና የነባር ባለአክሲዮኖችን የጎላ አስተዋጽኦ መሰረት በማድረግ ፍትሃዊ የሆነ አጠቃቀም መመዘኛ ተደርጎ ቀድሞ በነበራቸው የይዞታ መጠን/ስፋት/ አክሲዮን ድልድል መከናወኑን፣ በዚህም መሰረት የአንድ አክሲዮን ዋጋ ብር 50,000.00 ሁኖ ትንሽ ይዞታ የነበረው ሰው ዝቅተኛውን አራት አክሲዮን እንዲይዝና ከፍተኛ ይዞታ የነበረው ደግሞ 20 አክሲዮን እንዲይዝ፣ይዞታ ያልነበራቸው ከሳሽን ጨምሮ ባለአክሲዮን የነበሩ ሰዎች ዝቅተኛ የአክሲዮን መጠን እንዲሰጣቸው እንዲሁም በልዩ ሁኔታ ማህበሩ ባልተደራጀበት ወቅት ምንም ክፍያ ሳይሰጣቸው በግል ጥረታቸው ማህበሩን አሁን በሊዝ የያዛቸውን ሶስት ካርታዎች እንዲያገኙ ምክንያት ለሆኑት የተከሳሽ ሊቀመንበር በነበራቸው ስድስት አክሲዮን ላይ አራት አክሲዮን እንዲጨመር መደረጉን፣ ይህ ጥናትም ለጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ ጉባኤውም ተስማምቶበት በ30/08/2005 ዓ/ም ማጽደቁን፣የባለአክሲዮኖቹ ጠቅላላ ጉባኤ በሕግ አግባብ ተጣርቶና ምልዓተ ጉባኤው ተሟልቶ የአክሲዮን ድልድሉን በተመለከተ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ከሳሽም ተስማምተው በቃለ ጉባኤው ላይ ከፈረሙ በኋላ እንደገና የሰረዙት በመሆኑ የ14 ሼር ከፍዬ የ20 ሼር ባለቤት ልሆን ይገባል በማለት ያቀረቡት ጥያቄም የሕግም ሆነ የፍሬ ነገር አመክንዮ የሌለው መሆኑን፣ ከሳሽ ከአራት አክሲዮን ዋጋ በተጨማሪ ከፍያለሁ ያሉት ብር 100,000.00 ከሳሽ እንዳሉት የተከፈለው በ1993 ዓ/ም ሳይሆን በ2002 ዓ/ም ስለመሆኑ፣ ክፍያውን እንዲፈጽሙ ስለመጠየቃቸውም ማስረጃ ያላቀረቡና የደረሰባቸው ጉዳት ባለመኖሩ ከማህበሩ የአክሲዮን ድልድል መርህ አንፃር በብር 300,000.00 ታስቦ አክሲዮን ይደረግልኝ በማለት የቀረበው ክርክር ተቀባይነት የሌለው መሆኑን፣ከሳሽ መስራች ባለአክሲዮን ያለመሆናቸውንና ባለአክሲዮን የሆኑትም የማህበሩ ካፒታል ባደገበት ጊዜ መሆኑን፣ የአንድ ባለአክሲዮን የአክሲዮን ድርሻ የሚረጋገጠው በአክሲዮን ምስክር ወረቀት ወይም በመመስረቻና መተዳደሪያ ደንብ ወይም በማሻሻያው ላይ በተገለፀው የአክሲዮንና የገንዘብ መጠን ነው እንጂ በኩባንያው የባንክ ሂሳብ ገንዘቡን ገቢ በማድረግ ብቻ አክሲዮን የማሳደግ መብት የሌለ መሆኑን፣ ብር 100,000.00 የከፈሉቱም ባለአክሲዮን ከሆኑ ከአስር አመት በኋላ ስለመሆኑ፣ የአክሲዮን ድልድል የሚወሰነው በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ እንጂ ከጉባኤው እውቅና ውጪ ባለአክሲዮኖቹ በኩባንያ የባንክ ሂሳብ ገንዘብ ገቢ ስለአደረጉ ብቻ ያለመሆኑንና በዚህ ረገድ መብት ሰጪ የሆነ የንግድ ህግ ድንጋጌ የሌለ መሆኑን፣ በመስከረም ወር 2005 ዓ/ም ሲፈረም በነበረው ቃለ ጉባኤ ላይ ከሳሽና ሌሎች አራት ሰዎች ቅሬታ አቅርበው በጥያቄው መሰረት ቀሪ የሆነ ቢሆንም ከዚህ በኋላ ሁለት

ቃለጉባኤዎች በፍርድ ቤት ትዕዛዝና ለአባላቱ በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎ በጠቅላላ ጉባኤው በህግ መሰረት የተፈረመ በመሆኑ በ21/02/2005 ተፅፏል የተባለው ደብዳቤ ለክሱ ምንም ፋይዳ የሌለው መሆኑን፣ ተከሳሽ ማህበር በፅሑፍ ከአደረገው ጥሪ በተጨማሪ የካቲት 20 ቀን 2005 ዓ/ም በሪፖርተር ጋዜጣ ላይ በድጋሚ ባደረገው የባለአክሲዮኖች ጥሪ ላይ የከሳሽ ተወካይ ተገኝተው መፈረማቸውን፣ በስብሰባ ላይም ረቂቅ ቃለጉባኤውና የተሻሻለው የመተዳደሪያ ደንቡና የመመስረቻ ፅሑፍ በንባብ ተሰምቶ ውይይት ከተደረገበት በኂላ በጠቅላላ ጉባኤው የፀደቀና በዚህ መሰረትም የመግባቢያ ሰነድ ሲፈረም ተወካይዋ ተስማምተው የፈረሙ መሆኑን፣ ሆኖም ከፈረሙ በኃላ በድጋሚ የማየው ነገር አለኝ በማለት ፊርማቸውን የሰረዙ ቢሆንም ተወካይዋ ስብሰባውን አውቀው ሰነዱን አይተውና ተስማምተው የፈረሙና ከስርዓት ውጪ ፊርማቸውን በሰረዙበት ሁኔታ ቃለጉባኤውም 94.12% በላይ በሆኑት የማህበሩ ባለአክሲዮኖች የወሰኑትን ውሳኔ የተቃወሙት ከሕግ ውጪ መሆኑን፣ የፈራሚዎች ጉባኤ አሰራርና ሰነዶችን የማየት መብት ከከሳሽ ክርክር ጋር አግባብነት የሌለው መሆኑን፣ ከሳሽ የአክሲዮን ድልድሉን በተመለከተ የተዘጋጀው ቃለ ጉባኤ አልጸደቀም ይበሉ እንጂ ሰነዱ ሚያዚያ 30 ቀን 2005 ዓ/ም በ94% የማህበሩ አባላት ፀድቆና ተረጋገጦ የተሰጠ በመሆኑ ክሱ ህግን መሰረት ያላደረገ መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሁኖ በቂ ወጪና ኪሳራ እንዲወሰን ዳኝነት መጠየቁን የሚያሳይ ነው፡፡

ከዚህም በኂላ ማኅበሩ ግንቦት 21 ቀን 2005 ዓ/ም የተጻፈ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርቧል፡፡የክሱ ይዘትም፡-ከሳሽ ማኅበር በሶስት ሰዎች በ11/02/92 ዓ/ም ከተቋቋመ በኂላ በ15/03/93 ዓ/ም በቁጥር 332/4ለ/93 በተፈረመ ቃለ ጉባኤ ከሳሽ ብር 200,000.00 ከፍለው የአራት አክሲዩን ባለቤት የሆኑ መሆኑን፣ በዚህ ቃለ ጉባኤ ላይ የከሳሽ ዜግነት ኢትዩጵያዊ በመባሉ ማህበሩ በአከባቢው የንግድ ስራ የነበራቸው መሆኑንና እርሳቸው በግምባር ቀርበው መፈረማቸውን በመገመት ብቻ በአባልነት የተቀበሏቸው መሆኑን፣ ከሳሽ በዚህ ፍርድ ቤት ክስ ከማቅረባቸው በፊትም እንደኢትዩጵያዊ ስለሚቆጠሩ ወኪላቸው በየስብስባው ላይ ሲገኙ መቆየታቸውን፣ ይሁንና ከክሱ በኂላ ተከሳሽ ልዩ ልዩ ሰነዶችን በጥንቃቄ ሲመረምር ከሳሽና ባለቤታቸው በ08/01/93 ዓ/ም በጻፉት የውክልና መሻሪያ ሰነድ ላይ የገለሰቧ ዜግነት ኤርትራዊ መሆኑ መረጋገጡን፣ በተጨማሪም ከሳሽ ለወኪላቸው ወ/ሮ ጊዜሽወርቅ ተሰማ ዋሽንግተን ውስጥ ሆነው ውክልና የሰጡት አንድ አንድ ዋሽንግተን ውስጥ ለተመዘገበና ነጋሽ ተስፋዬ በሚባል አዋዋይ ፊት ሆኖ በኂላ ሰነድ ለአሜሪካ ውጭ ጉዳይ በመቀጠልም ዋሽንግተን ለሚገኘው የኢትዩጵያ ውጭ ጉዳይና በሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ፅ/ቤት መደረጉ ከሳሽ ኢትዩጵያ ያለመሆናቸውን አመላካች የሆነ መሆኑን፣ ለዚህም ምክንያት ዋሽንግተን ያሉ የኢትዩጵያዊያ ዜጎች የሚዋዋሉት የኢትዩጵያ ኤምባሲ ጋር በመቅረብ ስለመሆኑና ከሳሽ የውጪ አገር ዜጋ በመሆናቸው በኢትዩጵያ ውስጥ ባሉ የንግድ ማህባራት ባለአክሲዩን መሆን የሚችሉበት

በኢንቨስትመንት አዋጅና በደንቡ ውስጥ የተመለከቱትን ግዴታዎችን ሲያሟሉ ስለመሆኑ፣ በሌላ በኩል የከሳሽ ወኪል ተከሳሽ ማህበር ባለአክሲዮኖች ስብስባ ላይ በመገኘት በመስማማት ስምምነት ላይ ከፈረሙና በዚሁ መሰረት በሰነዶች ምዝገባ ማረጋገጫ ጽ/ቤት በአባላት የተፈረመውን የማህበሩን ቃለ ጉባኤ የተሻሻለ የመመስረቻ ፅሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ላይ ከፈረሙበት በኃላ ፊርማቸውን መሰረዛቸውን፣ እርሳቸው የተሰረዙ ቃለጉባኤና ማሻሻያዎች አጀንዳ የአክሲዮን ድልድል በማድረግ ማህበሩን ወደ አክሲዮን ማህበርነት የለወጠ መሆኑን፣ ከሳሽ ጠቅላላ ጉባኤው በሰጠው ውሳኔ ላይ የማይስማሙ ከሆነ በንግድ ሕጉ መሰረት ከአባልነት የሚሰረዙ መሆኑን፣ ከሳሽ በማህበሩ በአክሲዮን መዋጮና በሌላ ጊዜ የከፈሉት አክሲዩኑን በመሸጥ ተከሳሽ የሚከፍላቸው መሆኑን ዘርዝሮ ከሳሽ የውጭ አገር ዜጋ በመሆናቸው የኢንቨስትመንት ህግና ደንቡን ሳያሟሉ በተከሳሽ ማኅበር ውስጥ ባለአክሲዩን ሊሆኑ አይገባም ተብሎ እንዲወሰን፣ ይህ የሚታለፍ ከሆነም የተከሳሽ ማኅበር ጠቅላላ ጉባኤ አክሲዩን አደላድሎና አባላት ጨምሮ ማህበሩን ወደ አክሲዩን ማህበርነት የቀየረ ስለሆነና ከሳሽም በዚህ ውሳኔ ያልተስማሙ ስለሆነ አክሲዮናቸው ተሽጦ ከማህበሩ ባለአክሲዮንነት እንዲሰናበቱ ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የስር ከሳሽ በስር የተከሳሽ ከሳሽ በቀረባበቸው ክስ መከላከያ መልስ ያቀረቡ ሲሆን በመልሳቸው ላይም ከሳሽ ከሌሎች 27 አባላት ጋር በመስራችነት ሲመዘገቡ በአካል መታወቂያቸውን ይዘው በመቅረብ መመዝገባቸውን የተከሳሽ ከሳሽ ያለመካዱን፣ ይህም በቀረበው የመመስረቻ ጽሑፍና መተዳደሪያ ደንብ ሊታይ የሚችል መሆኑን፣ ተከሳሽ ከሳሽ የመብት ጥያቄ በማንሳታቸው ምክንያት ለምን ተነካን በሚል አስተሳሰብ ጥፋት ለመፈገለግ ሰነድ ማፈላለጉ ከቅን ልቦና የጎደለው አካሄድ መሆኑን፣ አስፈላጊ ከሆነውም ከሳሽ ኢትዩጵያዊ ናቸው ወይስ አይደሉም የሚል ጥያቄ ቢነሳ እንኳን ይህን የማጣራት ስልጣን ያለው ተከሳሽ ሳይሆን የሚመለከተው ራሱን የቻለ አካል እንጂ ተከሳሽ ስልጣን የሌለው መሆኑን፣ ውክልና በኢትዩጵያ ኢምባሲ በኩል ስላልተሰጠ ከሳሽ ኤርትራዊ ናቸው በማለት ያቀረቡት ከግምት በመነሳት ስለመሆኑ፣ የሰጡት ውክልና ህጋዊ እስከሆነ ድረስ የዜግነቱ ጉዳይ ተከሳሽን የማይመለከተውና ከሳሽ ኤርትራዊ ናቸው ቢባል እንኳን በየትኛው ሕግና አዋጅ ኢትዩጵያዊ ያልሆነ ሰው አክሲዩን ለመግዛት አይችልም በሚል እንደተደነገገ ተከሳሽ በአግባቡ ጠቅሶ ያላቀረበ መሆኑን፣ በወቅቱ የአክሲዩን ድልድሉን የያዘው ቃለ ጉባኤ በተመለከተ ብዙ ሰው ጥያቄ ያነሳና በርካታ ልዩነትና ጭቅጭቅ አስነስቶ እያለ የተቋቋሙትን ሳትፈርሙ ከወጣችሁ ከማህበሩ ትሰረዛላችሁ በማለት በማስፈራራታቸው ብዙ አባላት የፈረሙ መኖራቸውን፣ በዚህ ሁኔታ ከሳሽ የመብት ጥያቄ በማንሳታቸው ከማህበሩ እንዲወጡ በሚል የቀረበው ክርክር ተገቢነት የሌለው መሆኑን ዘርዝረው ተከሳሽ በተከሳሽ ከሳሽነት የጠየቁባቸው ነጥቦች ከሳሽ ያነሱትን የመብት ጥያቄ ለመቃወም በማሰብ ስለሆነ ፍርድ

ቤቱ ጥያቄዎቹን ውድቅ በማድረግ ተከሳሽ ተገዶ መብታችንን እንዲያስከብርልን ሊወሰንልኝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ በቅድሚያ ተከሳሽ በተከሳሽ ከሳሽነት ያቀረበውን ክስ መሰረት አድርጎ የአሁኑ አመልካች ኃላፊነቱ የተወሰነው የግል ማህበር ሁኖ ከተቋቋመ በኃላ ወደ አክሲዮን ማህበርነት መወለጡንና የተደረገውን የአክሲዮን ድልድል የተቃወሙ በመሆኑ እንዲሁም ዜግነታቸው ኤርትራዊና የውጭ አገር ዜጋ በመሆናቸው ከማህበሩ አባልነት ሊወጡ ይገባል በማለት ያቀረበውን ክስ በመመልከት ከሳሽ የውጭ አገር ዜጋ/ኤርትራዊ ናቸው ለመደምደም የሚያስችሉ ማስረጃዎች ካለማቅረባቸውም በላይ የውጭ አገር ዜጋ የሆነ ሰው ባለአክሲዮን ከመሆን በግልጽ የሚከለክል ድንጋጌ በኢንቨስትመንት ህጎች አለመመልከቱን፣ የተከሳሽ ማኅበር ወደ አክሲዮን ማህበር መለወጥና የአክሲዮን ድልድል ባለመስማማት መቃወም ለአባሉ በሕግ የተሰጠው መብት በመሆኑ ይህን ተቃውሞ ያቀረበ የማህበሩ አባል ከማህበሩ በግድ እንዲወጣ የሚደረግበት አግባብ የሌለ መሆኑን እንዲሁም ተጠሪ/የስር ከሳሽ) ባቀረቡት ክስ የማህበሩን ወደ አክሲዮን ማህበርነት የመለወጥ ጉዳይ በተመለከተ ተቃውሞ ያላነሱና ዳኝነት ያልጠየቁበት ነጥብ መሆኑን በምክንያትነት ይዞና የን/ህ/ቁጥር 547/3/ ድንጋጌን በዋቢነት ጠቅሶ አመልካች ያቀረበውን ክስ ውድቅ አድርጎአል፡፡ በመቀጠል የተጠሪን ክስ በመመርመር አመልካች ያቀረባቸውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥቦችን ውድቅ አድርጎ ፍሬ ነገሩን በተመለከተ ደግሞ የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብና መመስረቻ ጽሑፍ በመመልከት መርምሮ ማህበሩ በ1992 ዓ/ም ሲመሰረት የነበሩት አባላት ብዛት ሶስት ብቻ እንደነበሩ፣ ማህበሩ የተቋቋመበት መሰረታዊ አላማ የማህበሩ አባላት የንግድ ስራዎችን የሚያከናውንባቸው መደብሮችን በዘመናዊ መልክ ደረጃውን ጠብቀው እንዲደራጁና ለንግድ ስራ የተመቻቹ እንዲሆኑ ለማስቻል መደብሮቹ የሚገኙበትን የቦታ ክልሎች ከመንግስት አስፈቅዶ በሊዝ ለመግዛትና በመረከብ እንዲሁም የሕንጻ ስራ ፈቃድ በማውጣት ለንግድና ለቢሮ አገልግሎት የሚወሉ ህንጻዎች ለመስራት እንደአስፈላጊቱም ለአባላቱ ለማከፋፈል በማሰብ የተቋቋመ ስለመሆኑ በመመስረቻ ጽሑፉ በግልጽ መመልከቱንና አንድ ሰው የማህበሩ አባል የሚሆንበት አግባብም በዚሁ በመተዳደሪያ ደንቡ የተገለፀ መሆኑን፣ በ22/02/1993 ዓ/ም በተደረገው ጠቅላላ ጉባኤም ከሳሽና ሌሎች 23 ሰዎች ወደ ማህበሩ ለመግባት አመልክተው እንዲገቡ እንደተወሰነ እንዲሁም ይህን ውሳኔ ተከትሎ የማህበሩ ዋና ገንዘብ እንዲጨምር የማህበሩ የአክሲዮን ዋጋ እና ብዛትም እንዲሁ ከፍ እንዲል የተወሰነና በውሳኔው መሰረትም የአንድ አክሲን ዋጋ ከብር 1000.00 ወደ 50,000.00 ከፍ ያለ እንዲሆን የተወሰነና ከሳሽም በወቅቱ በድምሩ 200,000.00 ለማህበሩ በመክፈል የአራት አክሲዮን ባለቤት የሆኑ መሆኑን፣ ከዚህም በኂላም 32 ሰዎች በፍርድ ቤት ክስ በመመሰረት በአመልካች ማህበር አባል እንዲሆኑ

የተወሰነ በመሆኑ የማህበሩ አባላት ቀድሞ ከነበረው 27 አባላት ወደ 59 ከፍ ያለ በመሆኑና ኃ.የተ.የግል ማህበር አባላት ቁጥር ከ50 ሊበልጥ እንደማይገባ በንግድ ሕጉ የተደነገገ በመሆኑ አመልካች ማህበር ከነበረበት ኃ.የተ.የግል ማህበርነት ወደ አክሲዮን ማህበርነት እንዲለወጥ ለመወሰን አዲስ የሆኑትን 32 አባላትን በባለአክሲየንነት ለመመዝገብ በሚል አጀንዳ በመያዝ የቦርድ አባላትን ብቻ ስብሰባ በመጥራትና ሌሎች ባለአክሲዮኖችን መጥራት አያስፈልግም በሚል የቦርድ አባላቱ ውይይት ካደረጉ በኋላ የፍርድ ቤቱን ውሳኔ ለማስፈጸም አዲስ ወደ ማህበሩ የሚገቡትን አባላት አክሲዮን ድርሻ ማደላደል የሚያስፈልግ በመሆኑ ድርሻቸውን መደልደሉን፣ አዲስ ባለአክሲዮን ለሆኑት አባላት አክሲዮን የመደልደሉ ጉዳይም በቀጥታ የማህበሩን ዋና ገንዘብ እንዲያደግ የሚያስገድድ በመሆኑ ቦርዱ ቀደም ሲል የነበረውን ብር 3,000,000,.00 የማህበሩና ዋና ገንዘብ ወደ 10,200,000.00 ከፍ እንዲል በማለት መወሰኑን፣ የማህበሩ አክሲዮን ብዛትም ከ60 ወደ 204 ከፍ እንዲል ተደርጎ ቦርዱ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ለመፈፀም ሲል ጠቅላላ ጉባኤው በአጭር ጊዜ ተጠርጥሮ ማህበሩ ወደ አክሲዮን ማህበርነት እንዲለወጥ እንዲወሰን በማለት ውሳኔ መስጠቱን፣ ከዚህ በኋላም በመጋቢት ወር 2005 ዓ/ም የማህበሩን ጠቅላላ ጉባኤ የተሰበሰበና ከማህበሩ አጠቃላይ ዋና ገንዘብ እና የአክሲዮን ብዛት ውስጥ 192 የአክሲዮን ድርሽ ወይም 94.12% ድርሻ ያላቸው ባለአክሲዮኖች በተገኙበት በፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረት የአክሲዮን ዝውውር ማድረግ፣ አዲስ ባለአክሲዮኖችን መቀበልና የሚገበቡትን የአክሲዮን ብዛት መወሰን፣ የነባር ባለአክሲዮኖችን የአክሲዮን ድርሻ ማሳደግና በዚህ መብት መጠቀም ያልቻሉትን መብት መጠበቅ፣ ይህን ተከትሎም የማህበሩ ዋና ገንዘብ ማሳደግና በአጠቃላይ የማህበሩን ባለአክሲየኖችን የአክሲዮን ድልድል መወሰንና ሌሎች ነጥቦች ላይ በመወያየት ውሳኔ ተላልፏል በማለት ቃለ ጉባኤው እንደተዘጋጀ መመልከቱን፣ ከዚህ ጋር በተያያዘም በተጠቃሹ ቃለ ጉባኤ እንደተመለከተው በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሰረት የባለአክሲኖችን የአክሲዮን ድርሻ ድልድል ለማድረግ በዋነኛነት መሰረት የተደረገው ማህበሩ በሚያለማው መሬት ላይ ቀደም ሲል የነበራቸውን የይዞታ መጠንና አባላቱ ለማህበሩ ያደረጉትን አስተዋጽኦ ግምት ውስጥ በማስገባት እንደሆነ መመልከቱን፣ እንዲሁም ነባር አባላት ከነባራች የአክሲዮን ድርሻ ላይ ተጨማሪና የፈለጉትን/አቅማቸው የፈቀደውን/ የአክሲዮን ድርሻ እንዲኖራቸው ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት በጉባኤው እየተፈቀደ የልዩነቱን/የተጨማሪ አክሲዮን ዋጋ እንዲከፍሉ በቃለ ጉባኤ መመልከቱ ፣ በዚህም መሰረትም የአክሲዮን ብዛት ቀድሞ ከነበረው 204 አክሲዮኖች ወደ 495 እንዲሁም የማህበሩ ዋና ገንዘብ ቀድሞ ከተመዘገበው ብር10,200,000.00 ወደ 24,750,000.00 እንዲያድግና የአንድ አክሲዮን ዋጋም በብር 50,000.00 በነበረበት እንዲሆን በሚል መወሰኑ መደንገጉን፣ ከዚህ በመቀጠልም በዚሁ ተጠቃሹ ቃለ ጉባኤ መጨረሻ ላይ ቀድሞ የነበረው ኃ.የተ.የግል ማህበር ወደ አ/ማህበርነት እንዲለወጥ ለጥር 10 ቀን 2005 ዓ/ም በቁጥር ዋ/መ/5872/4ለ/2005 በተላለለፈው ውሳኔ መሰረት የነባር ማህበር መመስረቻ ፅሑፍና

መተዳደሪያ ደንብ ተሻሽሎ መፃፍ ያለበት ስለሆነ በሚል ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሰረት ተሻሽሎ እንዲዘጋጅ የተደረገና የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ፅ/ቤት እንዲቀመጡና አባላት እንዲፈርሙ ተደርጎ 75 ባለአክሲዮኖች የፈረሙ ስለመሆኑ ቃለ ጉባኤው የሚያሳይ መሆኑንና ብር 100,000.00 ተጠሪ ማስገባታቸው በማስረጃ መረጋገጡን ዘርዝሮና ለጉዳዩ አግባብነት አላቸው ያላቸውን የንግድ ህግ ቁጥር 536(1-2)፣ 544(1-3፣ 547 ለሌሎች አባላት አክሲዮን ቁጥር ለመጨመር መሰረት የሆኑት አባላቱ ቀደም ሲል የነበራቸው የይዞታ ስፋት መጠንና ለማህበሩ መቋቋም ያደረጉት አስተዋጽኦ በመስፈርትነት እንዲያዙ አባላቱ የተስማሙባቸው ስለመሆኑ ተሻሽለው በተዘጋጁት ጽሑፎች ያለመመልከታቸውን ደምድሞ አመልካች ለተጠሪ አስራ አራት አክሲዮን ጨምሮ ሃያ አድርጎ እንዲመዝግባላቸውና ተጠሪም የአስራ አራቱን አክሲኖች ዋጋ እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡

በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ከሳሽ ኤርትራዊ መሆናቸው በሰነድ ማስረጃዎች የተረጋገጠ ቢሆንም የውጭ አገር ዜጋ አክሲዮን ገዝቶ በኢንቨስትመንት ላይ እንዳይሳተፍ የሚከለክል ሕግ የለም በማለት የስር ፍርድ ቤት የአሁኑን አመልካች የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ ውድቅ አድርጎ የከሳሽ የማህበሩ አባልነት እንዲቀጥል ሲል የሰጠውን የውሳኔ ክፍል ያጸና ሲሆን ከሳሽ በማህበሩ ሊኖራቸው የሚገባውን የአክሲዮን ብዛት በተመለከተ ግን አመልካች ማህበር መጋቢት ወር 2005 ዓ/ም የያዘውና በሚያዚያ 30 ቀን 2005 ዓ/ም በፀደቀው ቃለ ጉባኤ የማህበሩ አባላት ቀድሞ የነበራቸው የቦታ ስፋትና ለማህበሩ መመስረት ያደረጉት አስተዋጽኦ ግምት ውስጥ ገብቶ የአክሲዮን ቁጥር እንዲጨምርላቸው የተደረጉ አባላት መኖሩን እንደሚያሳይ እና ከሳሽ ደግሞ ይዞታ ያልነበራቸውና ለማህበሩም ያደረጉት አስተዋፅኦ የሌለ መሆኑን በማህበሩ ይዞታ ላይ ቦታ ያላቸው አብዛኞቹ ባለአክሲዮኖች የያዙትን የአክሲዮን መጠን በመመልከት ከሳሽ ተጨማሪ አራት አክሲዮኖችን በመግዛት በድምሩ በማህበሩ ውስጥ አስር አክሲዮኖች ባለቤት ሊሆኑ ይገባል ሲል የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ አሻሽሎ ወስኗል፡፡ በዚሁ በተሻሻለው የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሥር ከሳሽ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም በመ/ቁጥር 117601 በ30/02/2008 ዓ/ም ተሰርዞባቸዋል፡፡

ግራ ቀኙ የሰበር አቤቱታቸውን ያቀረቡት ከላይ በተመለከተው አግባብ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን በሰ/መ/ቁጥር 118246 የቀረበው አመልካች በሠበር ነው፡፡ በዚህም የአመልካች ጠበቃ መስከረም 09 ቀን 2008 ዓ/ም የጻፉት 8(ስምንት) ገፅ የሠበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘቱም የሥር ከሳሽ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ሳይኖራቸውና በአዋጅ ቁጥር 769/2004 አንቀጽ

12(1(ሀ)፣ 2(6) እና 38 ድንጋጌዎች አግባብ በኢትዮጵያ ውስጥ ባለ ኢንቨስትመንት መሳተፍ የሚችሉ ስለመሆኑ ሳይረጋገጥ የውጪ አገር የሆነ የሰው አክሲዮን ለመግዛት የሚከለክል ሕግ የለም በማለት መወሰኑ ያላግባብ መሆኑንና ተጠሪ እንዲሸርላቸው የጠየቁት በ30/08/2005 ዓ/ም በ94.12% ባለአክሲዮኖች የተደረገውን የማህበሩን ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ በመሆኑ በተወካያቸው በስብሰባው ላይ ተገኝተው ከፈረሙ በኋላ ፊርማቸውን ስለሰርዙ ብቻ የጉባኤው ውሳኔ ተቀባይነት እንደሌለው ተደርጎ የሥር ፍርድ ቤት ወስኖ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በመርህ ደረጃ በ30/08/2005 ዓ/ም በተደረገው ጠቅላላ ጉባኤ የተደረገውን የአክሲዮን ድልድሉን ከተቀበለ በኋላ የጉባኤውን ውሳኔ ለውጦ የሥር ከሳሽ በድምሩ አስር አክሲዮን እንዲኖራቸው በማለት የሠጠው ውሳኔ በሕጉ ለጠቅላላ ጉባኤ የተሰጠውን ስልጣን ያላገናዘበ የሚል እና በእነዚህ ምክንያቶች የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ተሽሮ ዳኝነት እንዲሰጥ መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም አመልካች የተጠሪን ዜግነት መሰረት በማድረግ ያቀረበው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ በስር ፍርድ ቤት ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለማጣራት ተብሎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን የሥር ከሳሽ ሕጋዊ ወራሾች ቀርበው ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

በሰ/መ/ቁጥር 120709 የቀረበው የተጠሪዎች የሰበር አቤቱታ ሲሆን የተጠሪዎች ጠበቃ ህዳር 30 ቀን 2008 ዓ/ም 3 (ሦስት) ገጽ የሰበር አቤቱታ በታች ፍርድ ቤቶች በተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የንግድ ሕጉ ከሚደነግገው ውጪ የስር ከሳሽን አክሲዮን በቀድምትነት የመግዛት መብት በመተው አስር አክሲዮኖችን ብቻ እንዲገዙ በማለት የሰጠው ውሳኔ ሕጋዊ ባለመሆኑ ተለውጦ የሥር ፍርድ ቤት የተጠሪዎች እናት ሃያ አክሲዩን ባለቤት ሊሆኑ ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ እንዲፀናላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በመ/ቁጥር 185768 በተሰጠው ውሳኔ መስራች ባለአክሲዮኖች ያሏቸው መብትና ጥቅም እንዲያገኙ ውሳኔ የተሰጠበት ሆኖ ሳላ ከሌሎች ባለአክሲዮኖች ባነሰ የአስር አክሲዩን ድርሻ ብቻ ሊኖራቸው ይገባል የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ የሆነው የስር ተከሳሽም ቀርቦ ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጎአል፡፡ እንዲሁም የስር ፍርድ ቤት መዝገብም እንዲመጣ ተደርጎ የግራ ቀኙ ክርክርና በጉዳዩ ላይ የቀረቡት ማስረጃዎች ይዘት ታይቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ከስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ጉዳዩን ሁለቱም መዝገቦች ያስቀርባል ሲባሉ ከተያዙት ጭብጦች አንጻር በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመርነውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልጋቸው አበይት ነጥቦች፡-

1. የሥር ከሳሽ ኤትርትራዊ/የውጭ አገር/ዜጋ ናቸው ተብሎ ድምዳሜ በተያዘበት አግባብ በአክሲዮን የማህበር አባል ሁነው መቀጠል ይችላሉ ተብሎ በመወሰኑ የተፈጸመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለ? ወይም የለም?፣
2. የስር ከሳሽ በአመልካች ማህበር ሊኖራቸው የሚገባው የአክሲዮን ብዛት አስር ነው ተብሎ የተወሰነው በሕጉ አግባብ ነው? ወይስ አይደለም? የሚሉት ሁነው ተገኝተዋል፡፡

**<u>የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡-</u>** አመልካች የሰበር አቤቱታውን ባቀረበበት የሰበር መዝገብ ቁጥር 118246 በመሰረታዊ ጭብጥነት የተያዘውና በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገው ነጥብ የሥር ተከሳሽ የስር ከሳሽን ዜግነት መሰረት በማድረግ ያቀረበው የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ የስር ፍርድ ቤት ውድቅ የማድረጉን አግባብነት የሚመለከት ነው፡፡ የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ የሥር ከሳሽ የውጭ አገር ዜጋ ስለመሆናቸው በቂ ማስረጃ አልቀረበም በማለት የያዘውን ድምዳሜ በዚህ ረገድ ተመሳሳይ ሥልጣን ያለው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን ማስረጃዎችን በመመዘን የስር ከሳሽን የውጭ አገር ዜጋ መሆናቸውን ድምዳሜ ይዞአል፡፡ በመሆኑም የስር ከሳሽ የውጭ አገር ዜጋ መሆናቸው በክርክሩ ሂደት የተረጋገጠ ሲሆን ከዚሁ ጋር ተያይዞ የተነሳው የሕግ ጥያቄ የውጭ አገር መሆኑ የተረጋገጠበት ሰው በኢትዩጵያ ውስጥ በሚካሄደው ኢንቨስትመንት አክሲዮን ገዝቶ በንግድ ሕጉ አግባብ በሚቋቋመው ማህበር አባል መሆን የሚችል መሆን ያለመሆኑን የሚመለከት ነው፡፡

የስር ከሳሽ በዚህ ረገድ በግልጽ ጠቅሶ የሚከራከረው በአዋጅ ቁጥር 769/2004 አንቀጽ 12(1ሀ))፣ 2(6) እና 38 ድንጋጌዎችን በመጥቀስ ነው፡፡ ተጠቃሹ አዋጅ መስከረም 7 ቀን 2005 ዓ/ም ጀምሮ የጸና ሲሆን በአዋጁ አንቀፅ 12(1(ሀ))ድንጋጌ ሲታይ የውጭ ባለሃብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ የሚያስፈልጋቸው ስለመሆኑ የሚገለጽ ሲሆን አንቀጽ 2(6) ደግሞ የውጭ ባለሀብት ማለት የውጭ ካፒናል ወደኢትዮጵያ በማስገባት ኢንቨስት ያደረገ የውጭ አገር ዜጋ ወይም ሙሉ ለሙሉ በውጭ አገር ዜጋ ባለቤትነት የተያዘ ድርጅት ወይም ከሀገር ውስጥ ባለሀብት ጋር በቅንጅት ኢትዮጵያ ውስጥ በተቋቋመ ድርጅት ኢንቨስት ያደረገ የውጭ አገር ዜጋ ወይም ድርጅት ሲሆን እንደውጭ ባለሀብት መቀፐጠር ፈለገ መደበኛ ነዋሪነቱ በውጭ አገር የሆነ ኢትዮጵያዊን ይጨምራል በሚል የተቀመጠ ነው፡፡እንዲሁም የአዋጁ አንቀፅ 38 ሲታይም ማንኛውም ባለሃብት የአገሪቱን ሕጎች የማክበር ግዴታ ያለበት መሆኑን የሚደነግግ መሆኑን ተመልክተናል፡፡ አዋጁ በአንቀፅ 6 ስር ለመንግስት የተከለሉ ወይም ከመንግስት ጋር በቅንጅት የሚሰሩ የሥራ መስኮች የሚዘርዝር ሲሆን ለአገር ባለሃብቶችና ለውጪ አገር ዜጎች የተከለሉ የስራ መስኮችን ደግሞ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሰረት ሊወሰን እንደሚችል በአንቀጽ 7 እና 8 ድንጋጌዎች ስር አስፍሮአል፡፡ በዚህ መሰረት በደንብ ቁጥር 270/2005 አንቀጽ

3 ስር ለሀገር ውስጥ ባለሃብቶች የተከለሉ የስራ መስኮች ተዘርዝረው የወጡ ሲሆን በእነዚህ ዝርዝሮች ውስጥ አክሲዮንን በመግዛት ለንግድ ስራ ምቹ የሆነ ህንፃ በማሰራት የሥራ መስክ ለአገር ውስጥ ባለሃብቶች ብቻ የተከለሉ ስለመሆኑ የተጠቃሹ ደንብ ዝርዝር አያሳይም፡፡ በመሆኑም የስር ከሳሽ የአክሲዩን አባል የሆኑት በሕጉ ለአገር ውስጥ ባለሃብቶች ወይም በመንግስት በተከለሉ የስራ መስኮች ስር ባልተሸፈነው የስራ መስክ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

የስር ተከሳሽ በዚህ ረገድ አጥብቆ የሚከራከረው የሥራ መስኩ ለአገር ውስጥ ባለሃብቶች ብቻ የተከለለ ነው በሚል ሳይሆን የውጭ አገር ዜጋ በኢንቨስትመንት ላይ ለመሳተፍ በአዋጅ ቁጥር 769/2004 አንቀጽ 12(1(ሀ) ድንጋጌ መሰረት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሊኖራቸው ይገባል በሚል ነው፡፡ በእርግጥ ይህ ድንጋጌ በአዋጁ አንቀጽ 38 አግባብ ሊከበር የሚገባው መሆኑ ይታመናል፡፡ ነገር ግን የሥር ከሳሽ በስር ተከሳሽ ማህበር አባል የሆኑት በ1993 ዓ/ም ሲሆን አዋጅ ቁጥር 769/2004 ስራ ላይ የዋለው ደግሞ መስከረም 07 ቀን 2005 ዓ/ም ሁኖ የሥር ተከሳሽ በዚህ ረገድ ያቀረበውን ክርክር ያነሳው በ29/08/2005 ዓ/ም ክስ ከቀረበበት በኋላ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሳያል፡፡ በመሆኑም አዋጅ ቁጥር 769/2004 ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት የሥር ከሳሽ የማህበሩ አባል ከሆኑ ሕጉ የሚፈቅደውን ቅድመ ሁኔታዎች ሕጉ ከወጣ በኋላም ቢሆን እንዲያሟሉ አዋጅ ቁጥር 769/2004 እና ይህንኑ ተከትለው የወጡትን ደንቦች እንዲያስፈጽም ስልጣን የተሰጠው አካል ተገቢውን የሚያደርግ ከመሆኑ በቀር የሥር ተከሳሽ የስር ከሳሽ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ባለመያዛቸው ብቻ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ያገኙትን መብት ቀሪ እንዲሆን ክርክር የሚያቀርብበትና ዳኝነት የሚጠይቅበትን አግባብ አላገኘንም፡፡ በመሆኑም በሰ/መ/ቁጥር 118246 አመልካች የሆነው የዲሞ ተራ ህንጻ ስራ አክሲዩን ማህበር የሥር ከሳሽ የነበሩት ወ/ሮ አብረኸት ሀብተእዝጊ ተማኑ የውጭ አገር ዜጋ ስለሆኑና የኢንቨትመንት ፈቃድ የሌላቸው በመሆኑ በማህበሩ አባል ሁነው ሊቀጥሉ አይችሉም በማለት የሚቀርበው ክርክር ለክርክሩ መሰረት ያደረጋቸው ሕጎች የወጡበትን ጊዜ እና አከራካሪው የማህበር አባልነት የተመሰረተበትን ጊዜ መሰረት ያላደረገ ከመሆኑም በላይ ሕጉ ከመውጣቱ በፊት በሕጉ ባልተከለከሉ የሥራ መስኮች ላይ ተሰማርቶ የተገኘ የውጪ ባለሃብት ሕጎቹ ከወጡ በኋላ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያላያያዘ ከሆነ ከማህበሩ አባልነት እንዲሰረዝ ማህበሩ ወይም የማህበሩ አባላት ዳኝነት ሊጠይቁ የሚችሉበትን አግባብ በህግ አውጪው ያለመቀመጡን ሁሉ ያላገናዘበ ሁኖ ስለአገኘነው በዚህ ረገድ የቀረበውን የሰበር አቤቱታ ባለመቀበል በዚህ ረገድ የተሰጠው የበታች ፍርድ ቤቶች መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት ሁኖ አግኝተናል፡፡

<u>**ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡**</u>- የሥር ከሳሽ ለክሱ ዳኝነት የጠየቁት ተጨማሪ 14 አክሲዮኖችን እንዲገዙ እንዲወሰንላቸው ሲሆን በ1993 ዓ/ም የማህበሩ አባል ሁነው ብር 200,000.00 ከፍለው የአራት አክሲዩን ባለቤት ከመሆናቸውም በላይ ብር 100,000.00 ገቢ አድርገውም የተጨማሪ ሁለት አክሲዮኖች ባለቤት መሆናቸው በታች ፍርድ ቤቶች ፍሬ ነገሩ

ተጣርቶና ማስረጃው ተመዝኖ ድምዳሜ የተያዘበት ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች የማህበሩ መስራች አባላት ቁጥር በ1992 ዓ/ም ሶስት የነበረ መሆኑን፣ በ1993 ዓ/ም ደግሞ 27 ደርሶ በፍርድ ቤት ውሳኔና በአስተዳደሩ አካሉ ውሳኔ መነሻ ከሕጉ ጋር ለማጣጣም ሲባል ኃላፊነቱ ከተወሰነው የግል ማህበር ወደ አክሲዮን ማህበርነት ሲለወጥ የማህበሩ አባላት ቁጥርና የማህበሩ ካፒታል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተለወጠ መጥቶ የአባላቱ ቁጥር 81 ሲደርስ መጋቢት 2005 ዓ/ም በተያዘውና ሚያዚያ 30 ቀን 2005 ዓ/ም በጸደቀው ቃለ ጉባኤ መነሻ የአክሲዮን ድልድል መደረጉን፣ በዚህም መሰረት የሥር ተከሳሽ ማህበር የማህበሩን ዋና ገንዘብ ለመጨመር በመወሰን ይህንኑ ለማሳካት ለነባር አባላት የአክሲዮን ማሳደግ እርምጃ መውሰዱን፣ በዚህም 5 አባላት እያንዳንዳቸው ከነበራቸው አንድ አክሲዮን ወደ 8 አክሲዮኖች፣ 3 አባላት እያንዳንዳቸው ከነበራቸው ሁለት አክሲዮኖች ወደ አስር አክሲዮኖች፣ ሁለት አባላት እያንዳንዳቸው ከነበራቸው ሁለት አክሲዮኖች ወደ ስምንት አክሲዮኖች እንዲሁም አንድ አባል ከነበረው ሶስት አክሲዮኖች ወደ 20 አክሲዮን እንዲሁም አንድ አባል ከነበረው አራት አክሲዮን ወደ 20 አክሲዮኖች እንዲያድጉ የተወሰነ መሆኑን ተጠቃሹ ቃለ ጉባኤ የሚያሳይ መሆኑን በሰነድ ማስረጃዎች የተረጋገጡ ነጥቦች መሆናቸውን ከይግባኝ ሰሚው ፍርድ የውሳኔ ግልባጭና እና ከስር ፍርድ ቤት ዋና መዝገብ ተመልክተናል፡፡ ይህ ድልድል ህንጻው በነበረው ቦታ ላይ የነበራቸውን የይዞታ መጠንና ለማህበሩ መቋቋምም የነበራቸውን አስተዋጽኦ መሰረት አድርጎ የተደረገ መሆኑንና በጠቅላላ ጉባኤውም ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን የሥር ተከሳሽ ገልጾ የሚከራከር ሲሆን የሥር ከሳሽ ግን እነዚህ መስፈርቶች ሕጋዊ አይደሉም፣ በቃለ ጉባኤውም በተጽእኖ ፈርመው ቆይተው ፊርማቸውን የሰረዙ በመሆኑ ሊገደዱበት የማይገባ መሆኑን በመጥቀስ የሚከራከሩ መሆኑን ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡

እንግዲህ የሥር ከሳሽ መጋቢት ወር 2005 ዓ/ም የተያዘውንና ሚያዚያ 30 ቀን 2005 ዓ/ም 94.12% የሆነ የአክሲዮን ድርሻ ባላቸው አባላት በተደረገው የጠቅላላ ጉባኤ የተሰጠው የተደለደለውን የአክሲዮን የሕግ መሰረት በሌላቸው መስፈርቶች የተደረጉ ከመሆናቸውም በላይ መብቴን የጎዳ ውሳኔ ነው በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም የጠቅላላ ጉባኤው የጠራውን አካል ስልጣን፣በጠቅላላ ጉባኤ አካሄድ ማለትም በምልዓተ ጉባኤውና ውሳኔው በአብላጫ ስለመሰጠቱ ላይ፣ በጉባኤው ቃለ ጉባኤ አጻጻፍ ላይ በግልጽ ያቀረቡት ክርክር የሌለ መሆኑን የክርክሩ ሂደት የሚያሳይ መሆኑን ተረድተናል፡፡ አንድ የባለአክሲዮኖቹ ጉባኤ በሕጉ ጥበቃ የሚያገኘው በሕጉ የተመለከቱት ሁኔዎች ሲሟሉ ስለመሆኑ ከን/ሕ/ቁጥር 416(1) ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ሕግን፣ መመስረቻ ፅሑፍንና መተዳደሪያ ደንብን በመከተል የተደረገ የጉባኤው ውሳኔዎች በጉባኤው ያልተገኙትን ወይም በሃሳብ ያልተስማሙትን (ማህበርተኞች) ሁሉ ያስገድዳል በሚል በኃይለ ቃል አስቀምጧል፡፡

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመጣም አከራካሪውን የአክሲዮን ድልድል ያደረገው ጠቅላላ ጉባኤ ሕግን፣ መመስረቻ ጽሑፍንና መተዳደሪያ ደንብን ባለመከተል የተደረገ ነው ለማለት የሚያስችሉ

ፍሬ ነገሮች የሌሉ መሆኑን ከማህበሩ አመሰራረት መነሻና አብዛኞቹ አባላት ወደ ማህበሩ እንዲገቡ የተደረጉት ሕንጻው በሚሰራው ቦታ ላይ ነባር ባለይዞታዎች በመሆናቸው ምክንያት ስለመሆኑ ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ የሥር ከሳሽ የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ለማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ የነባር ባለይዞታነትንና የልዩ አስተዋጽኦ መሰፈርቶችን መሰረት አድርጎ አክሲዮን መደልደል አይችልም በማለት ክርክር ያቀረቡ ቢሆንም ለጉዳዩ ተፈፃሚነት ያለው የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 13.2.1 ግን የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ማናቸውንም አይነት የማህበሩን ፖሊሲ ጉዳዮች ላይ እንደሚወስን፣ በደንቡ አንቀጽ 13.2.4 ደግሞ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ለማህበሩ ዘላቂ የካፒታል እድገት ተጨማሪ የአክሲዮን መዋጮ መጠን እንደሚወሰን የተደነገገ ከመሆኑም በላይ ይህ የደንቡ ድንጋጌ ከን/ሕ/ቁጥር 536(2) ድንጋጌ ጋር ተዳምሮ ሲታይ የማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ለክሱ መነሻ የሆነውን ተጨማሪ አክሲዮን መወሰኑ ሕጋዊ የማይሆንበት ምክንያት የለም፡፡ ጠቅላላ ጉባኤው በማናቸውም አይነት የማህበሩ ፖሊሲ ጉዳዮች ላይ እንደሚወሰን በመተዳደሪያ ድንቡ የተቀመጠው ድንጋጌ በይዘቱ ሰፊ መሆኑን ለመረዳት የማያዳግት ሲሆን አሁን ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የአክሲዮን ድልድል መሰፈርቶችን መሰረት አድርጎ አክሲዮን እስከመደልደል የሚያደርስ ውሳኔ ማሳለፍን ሊያካትት የማይችልበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ አከራካሪ መስፈርቶች አብላጫ ድምጽ ባላቸው የማህበሩ አባላት ተቀባይነት ያገኙ ሲሆን አብዛኞቹ የማህበሩ አባላትም ከመነሻው ከነበራቸው የአክሲዮን ብዛት በተወሰነ መልኩ የተጨመረላቸው ከመሆኑ ውጪ ሁሉም እንደአመልካች የዳኘነት ጥያቄ ሃያ አክሲዮን እንዲኖራቸው የተደረገ ያለመሆኑን በጉዳዩ ላይ የቀረቡት ማስረጃዎች ያሳያሉ፡፡

የሥር ከሳሽ የማህበሩ መስራች አባል ሳይሆኑ በ1993 ዓ/ም አባል የሆኑና ህንጻው በሚገነባባት ቦታ ላይ ይዞታ የሌላቸው፣ በማህበሩ ምስረታ ላይም የተለየ አስተዋጽኦ ያላደረጉ መሆኑ የበታች ፍርድ ቤቶች በፍሬ ነገር ደረጃ ያረጋገጧቸው ነጥቦች ናቸው፡፡ እነዚህ መሰፍርቶችን መሰረት አድርጎ የአክሲዱን ድልድል ማድረግ እንዲቻል አብዛኞቹ የማህበሩ አባላት ፍላጎት ስለመሆኑ በጠቅላላ ጉባኤ ላይ ውሳኔ ላይ የተገኙት የአባላት ቁጥር ገላጭ ነው፡፡ በመሆኑም የሥር ከሳሽ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 185768 በተሰጠው ውሳኔ መሰረት መስራች ባለአክሲዮኖች ያሏቸው መብትና ጥቅም እንዲያገኙ ውሳኔ በተሰጠበት አግባብ ከሌሎች ባለአክሲዩኖች ባነሰ የአስር አክሲዩን ድርሻ ብቻ ሊኖራቸው ይገባል ተብሎ ውሳኔ መሰጠቱን በዚህ ሰበር ደረጃ ማንሳታቸውና አጣሪ ችሎቱም በዚህ ረገድ ጭብጥ ለይቶ መያዙ በስር ፍርድ ቤት ያልነበረን የክርክር ነጥብ መሰረት ያደረገና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 32((1) ድንጋጌ መሰረት ተቀባይነት ሊሰጠው የማይገባ ከመሆኑም በላይ የሥር ከሳሽ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 185768 ተከራካሪ ከነበሩትና ይህ መብት ከተጠበቀላቸው ሰዎች መካከል ያልሆኑና በ1992 ዓ/ም ማህበሩ ሲመሰረት ወይም ከዚህ በኂላ ወደ አክሲዮንነት ሲለወጥም በመስራች አባልነት የሚታወቁ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ በስር ፍርድ ቤቶች

ያልቀረበ፣ በመስራችነት ደግሞ የአክሲዮን ቁጥር ከፍ እንዲል ተብሎ በጠቅላላ ጉባኤም የተወሰነ ባለመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበውን ክርክር የምንቀበልበትን የሕግ አግባብ አላገኘንም፡፡

የሥር ከሳሽ በማህበሩ አባልነታቸው በእኩልነት መርህ መስተናገድ ያለባቸው ስለመሆኑ በንግድ ሕጉ ስር ያሉትን ድንጋጌዎች በማየት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን የስር ከሳሾች በእኩልነት መርህ የመስተናገድ አግባብ ተጥሷል ለማለት የሚቻልበትን ህጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡ ምክንያቱም በአከራካሪው ጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሰረት አክሲዩን የመግዛት የመጨመር መብት የተጠበቀላቸው የማህበሩ አባላት አብዛኞቹ አመልካች የሚጠይቁትን ያህል አክሲዩን እንዲኖራቸው ያልተደረጉ ሲሆን ሁለት አባላት በተለዩ መልኩ አክሲዮኖቹ ሃያ እንዲሆን የተደረገው በቦታው ላይ የነበራቸው የቦታ ስፋትና በማህበሩ ምስረታ ላይ የነበራቸው ተሳትፎ ታይቶ ነውና፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔም የስር ከሳሽ ሕንጻው በተገነባበት ቦታ ላይ ነባር ይዞታ ያልነበራቸው ከመሆኑም በላይ ለማህበሩ ምስረታ ያደረጉት አስተዋጽኦ ያልነበራቸው ቢሆንም ተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ የነበሩ የማህበሩ አባላት ከተደረገላቸው የአክሲዮን ጭማሪ አንጻር በማየት የአክሲዩን ቁጥሩ ወደ አስር ከፍ እንዲል መወሰኑም የስር ከሳሽን በእኩል የመስተናገድ መብታቸውን ያስከበረ ነው ከሚባል በስተቀር የሕግ መሰረት የለውም ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለልም ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ በመመርመር እና የማህበሩ አባላት አክሲዮናቸውን እንዲጨምሩ ከተደረገበት አግባብ አይቶ ለስር ከሳሽ ተጨማሪ አራት አክሲዮኖችን በመግዛት በማህበሩ አባላትነት እንዲቀጥሉ ሲል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ ስላልተገኘ ተከታዩን ወስናነል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የሥር ተከሳሽን በተመለከተ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁጥር 140942 በ23/10/2007 ዓ/ም የተሰጠው ውሳኔ፣ የስር ከሳሽን ደግሞ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 140942 በ23/10/2007 ዓ/ም ተሰጥቶ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 117601 በ30/02/2008 ዓ/ም በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1)መሰረት ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ብ/ይ

የሰ/መ/ቁ. 139932

ሐምሌ 20 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

ጳውሎስ ኦርሺሶ

ሠናይት አድነው

አመልካች ፡- አስማማው በየነ -ጠበቃ አዲሱ ወርቁ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- አሰፋ ነጋሽ -የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ ሊቀርብ የቻለው አመልካች መጋቢት 26 ቀን 2009 ዓ/ም በተጻፈ ማመልከቻ በሰሜን ጎንደር መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 01-31103 ታህሳስ 21 ቀን 2009 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት 01-00874 የካቲት 28 ቀን 2009 ዓ/ም የጸናው ብይን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ሲባል ነው፡፡

ክርክሩ ሲጀመር የአሁኑ አመልካች ከሳሽ፣የአሁኑ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ አመልካች ያቀረቡት ክስም ጥቅምት 04 ቀን 2009 ዓ/ም ባቀረቡት ክስ ተጠሪ ቁጥሩ 5938779 የሆነና በላዩ ላይ ብር 500,000.00(አምስት መቶ ሺህ ብር) የያዘ ቼክ የሰጧቸውና ይህንን ቼክ ይዘው ገንዘቡን ወጪ ለማድረግ መስከረም27 ቀን 2009 ዓ/ም ደባርቅ ከተማ ወደሚገኘው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ ሲሄዱ ባንኩ በተጠሪ ተቀማጭ ሂሳብ ውስጥ በቂ ገንዘብ ስለሌለ በቼኩ ላይ የታዘዘው ገንዘብ ሊከፍል እንደማይችል የገለፀላቸው መሆኑን ዘርዝረው ተጠሪው ገንዘቡን ከወለድ፣ ከወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

የሥር ተከሣሹም መከላከያ መልስ እንዲያቀርቡ ተፈቅዶላቸው ህዳር 08 ቀን 2009 ዓ/ም በሰጡት መከላከያ መልስ ክሱ በይርጋ የሚታገድ ነው በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አንስተዋል፡፡ በዚሁ ነጥብ ላይም ግራ ቀኙ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትም በይርጋ

መቃወሚያ ላይ ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ክርክር መርምሮ አመልካች በንግድ ህግ ቁጥር 855 በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ቼኩን ባንክ ያላቀረቡ መሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጠ መሆኑን በመያዝና በስድስት ወር ቼክ ለባንክ አቅርቦ ገንዘቡ ያልተከፈለው ቼክ አምጪ በን/ህ/ቁጥር 881 ስር በተመለከተው የይርጋ ጊዜ መብቱን ለማስከበር የሚችለው ከመጀመሪያውኑ በመብቱ ለመጠቀም እንዲችል ቼኩን ማቅረብ ካለበት የስድስት ወር ጊዜ ሳያበቃ ከአቀረበ ነው በሚል ምክንያት የአንድ አመት የይርጋ ጊዜ ለጉዳዩ ተፈፃሚነት የሌለው መሆኑን በመገንዘብ አመልካችን ቼኩን መሰረት በማድረግ ያቀረቡት ክስ በይርጋ የታገደ ነው በማለት ብይን ሰጥቶአል፡፡ አመልካች ይህንኑ ብይን በመቃወም ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው የይርጋ ጊዜ በን/ሕ/ቁጥር 881 ስር የተመለከተው የአንድ አመት ጊዜ ሁኖ እያለ የበታች ፍርድ ቤቶች ቼኩ ባንክ የቀረበው ስድስት ወር ካለፈ በኂላ ነው በማለት ክሱን በይርጋ ውድቅ ማድረጋቸው የን/ሕ/ቁጥር 885 እና 881 ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ ነው የሚል ነው፡፡ አቤቱታው ተመርምሮም በዚህ ችሎት እንዲታይ የተደረገ ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በፅሑፍ እንዲከራከሩ አድርጎአል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ብይንና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ በዚህም መሰረት አመልካች በተጠሪው ላይ በሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ በመወሰኑ የፈጸመው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለ? ወይስ የለም? የሚለውን ጭብጥ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መረዳት የታቻለው አመልካች ለክሱ መሰረት ያደረጉት ቼክ ቁጥር 5938779 ህዳር 14 ቀን 2008 ዓ/ም የተጻፈ ሁኖ ባንክ መስከረም 27 ቀን 2009 ዓ/ም ቀርቦ ተጠሪ በቂ ስንቅ የላቸውም በሚል ምክንያት አመልካች ገንዘቡ ሳይከፈላቸው ከተመለሰ በኌላ አመልካቹ በተጠሪ ላይ ክስ የመሰረቱት ጥቅምት 04 ቀን 2009 ዓ/ም ስለመሆኑ በፍሬ ነገር ደረጃ የተረጋገጡ ነጥቦች መሆናቸውን ነው፡፡

በመሰረቱ ቼክ የንግድ ወረቀት ከሚባሉ አንዱ ሲሆን እንደቀረበ የሚከፈል፣በባንክ ተቀማጭ ሂሳብ ያለው ሰው ገንዘቡ ለራሱ ወይም ለሌላ ወገን እንዲከፈል ሐተታ የሌለው ትዕዛዝ የሚሠጥበት፣ገንዘብን ተክቶ ክፍያን የሚያቀላጥፍ የንግድ ወረቀት ወይም ሰነድ ስለመሆኑ ከን/ሕ/ቁጥር 732፣ 827፣828 እና 854 ድንጋጌዎች ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ስለሆነም ቼክ እንደቀረበ የሚከፈል የገንዘብ ሰነድ በመሆኑ በቼክ ገንዘብ ለመክፈል አውጭው በባንክ ተንቀሳቃሽ ሂሳብ የተቀመጠ የቼኩን ዋጋ አጣርቶ የሚከፍል፣በቂ ስንቅ (ገንዘብ) ሊኖረው የሚገባ ስለመሆኑም እርግጠኛ መሆን እንዳለበት የን/ሕ/ቁጥር 830 (2) ድንጋጌ ያስቀምጣል፡፡ይህንኑ በሕግ የተጣለበትን

ግዴታ ሳይወጣ የቀረ አውጪ በቼኩ ላይ የተፃፈውን ገንዘብ (እዳ) ለአምጪው እንዲከፍል የሚገደድ ስለመሆኑ የሕጉ ይዘትና መንፈስ የሚያስገነዝበን ጉዳይ ነው፡፡ዕዳ ከፋዩ (አውጪው) ግዴታውን እንዲወጣ የማይገደደው በሕጉ የተቀመጡትን መቃወሚያዎች (መከራከሪያ ነጥቦችን) በአግባቡ ሲያስረዳ ነው፡፡በሕጉ እዳ ከፋዩ በአምጪው ላይ ሊያቀርብ ይችላል ተብለው የተቀመጡት መቃወሚያዎች በን/ሕ/ቁጥር 717 ስር የተመለከቱት ናቸው፡፡ እነዚህም፡-በሁለቱ የግል ግንኙነቶች ላይ የተመሰረቱ፣በሰነድ አጻጻፍ ፎርምና በሠነዱ ላይ በተጻፉ ቃሎች፣እንዲሁም ፊርማን በማስመሰል የተሠራ፣ ችሎታ ወይም ሰነዱ ሲወጣ የውክልና ሰልጣን ባለመኖሩ ወይም ክስ ለማቅረብ አስፈላጊ የሆኑት ሁኔታዎች ባለመሟላታቸው የሚነሱ መቃወሚያዎችና አምጭው ይህን ሰነድ ባገኘበት ጊዜ እዳ ከፋዩን ለመጉዳት እያወቀ ያደረገው መሆን ስለመሆናቸው የሚያሳዩ እንደሆነ ሕጉ አስቀምጧል፡፡

እንግዲህ ቼክ እንደቀረበ የሚከፈል እንደመሆኑ መጠን አውጪው ለቼኩ መውጣት ምክንያት የሆነውን ነገር የማስረዳት እና የማስተባበል ሸክም ያለበት ስለመሆኑ ከሕጉ ቅርፅ፣ይዘትና መንፈስ በቀላሉ የምንገነዘበው ጉዳይ ሲሆን በቼኩ የተጻፈውን ገንዘብ ለመክፈል አልገደድም የሚለው አውጪው ከላይ በን/ሕ/ቁጥር 717 ስር የተመለከቱትን ሁኔታዎች በበቂ እና አሳማኝ መንገድ ማስረዳት ግዴታውን ሲወጣ ስለመሆኑ ግልጽ ነው፡፡ እነዚህ በሕጉ የተመለከቱት ሁኔታዎች ቼኩን በቼክነቱ መሰረታዊ የሆኑ መብቶችን ማስገኘትና ግዴታዎችን ደግሞ ለማስከትል የሚያስችሉ መሆናቸውን የሚያስገነዝቡ ነው፡፡ በመሆኑም ቼክ በቼክነቱ የሚያስገኘውን መብት ለመጠቀም በህጉ የተመለከቱ ሁኔታዎች ተሟልተው መገኘት አለባቸው፡፡ ቼክ በቼክነቱ የሚያስገኛቸው መብቶች ቀሪ ከሚሆንባቸው ምክንያቶች አንዱ የይርጋ ጉዳይ ነው፡፡

ከይርጋ አንፃር ጉዳዩ ሲታይም አንድ ቼክ ከተፃፈበት ቀን ጀምሮ ባሉት 6 ወራት ጊዜያት ውስጥ ወደ ባንክ ለክፍያ መቅረብ ያለበት ስለመሆኑ የን/ሕ/ቁጥር 855 አስገዳጅነት ባለው መልኩ የሚደነገግ ሲሆን በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ለባንክ ቀርቦ ክፍያው ካልተፈፀመም ቼክ አምጪው ቼኩ ለባንክ የቀረበበት ጊዜ ካለፈ ጀምሮ ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ ፍርድ ቤት ክስ በማቅረብ መብቱን ማስከበር የሚችል መሆኑን በን/ሕ/ቁጥር 881(1) ስር በግልጽ ተመልክቶአል፡፡ የን/ሕ/ቁጥር 855 እና 881(1) አንድ ላይ ሲነበቡ የክስ ማቅረቢያ ጊዜ በቼኩ ላይ ከተፃፈበት ጊዜ ጀምሮ በሚቆጠር አንድ አመት ጊዜ መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ጊዜ መያዝ ያለበት ቼኩ በን/ሕ/ቁጥር 855 ስር ሕግ አውጪው በአስገዳጅነት በደነገገው አግባብ ቼኩ ከተፃፈበት ጊዜ ጀምሮ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ባንክ መቅረቡ ሲረጋገጥ ነው፡፡ በመሆኑም በን/ሕ/ቁጥር 855 ስር በተመለከተው የስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ባንክ ሳያቀርብ ይህንኑ ጊዜ አሳልፎ አንድ አመት ሳያልፍ ባንክ አቅርቦ በቼክ አውጪው ስም በቂ ስንቅ የሌለው መሆኑን ያረጋገጠ ቼክ አምጪ ቼኩን መሰረት አድርጎ የሚያቀርበው ክስ አንድ አመት አላለፈበትም በሚል ክሱ ተቀባይነት የሚያገኝበት አግባብ ሊኖር አይችልም፡፡ አመልካች በን/ሕ/ቁጥር 881(1) ስር በተመለከተው

የአንድ አመት የጊዜ ገደብ ክስ የማቅረብ መብታቸው በሕግ ፊት ተቀባይነት ሊኖር የሚችለው በን/ሕ/ቁጥር 855 ስር ቼኩን በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ለባንክ የማቅረብ ቅድመ ሁኔታ ሲያሟሉ ነው፡፡ ይህ ቅድመ ሁኔታ ሳይሟላ ቼኩን መሰረት አድርገው የሚያቀርቡት ክስ በን/ሕ/ቁጥር 855 እና 881(1) ድንጋጌ አግባብ ይርጋው የሚቆጠርበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡ በእነዚ ሁሉ ምክንያቶች ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. በሰሜን ጎንደር መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 01-31103 ታህሳስ 21 ቀን 2009 ዓ/ም ተሰጥቶ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት 01-00874 የካቲት 28 ቀን 2009 ዓ/ም የጸናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
2. የአመልካች የቼክ ክስ በይርጋ የታገደ ነው ተብሎ ክሱ ውድቅ በመደረጉ የተፈፀመ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣ ወጪና ኪሳራ ግራ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

   መዝገቡ ዘግቷል፤ ወደ መዝገብ በት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ይ

# ወንጀል

የሰ/መ/ቁ. 104637

ታህሳስ 24 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዳኜ መላኩ

ተኽሊት ይመሰል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ ኦርሺሶ

አመልካች፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ ራቢያ በድሩ ቀርባለች

ተጠሪ፡- ሙዑዝ ደስታ ገ/እግዚአበሔር ከጠበቃቸዉ አቶ መኮንን በዛብህ ጋር ቀርበዋል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በቀን 12/12/2006 ዓ/ም በተጻፈ አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት በወ/ይ/መ/ ቁጥር 96602 በቀን 29/09/2006 ዓ/ም በሰጠው ውሳኔ ተጠሪን በነፃ መልቀቁን በመቃወም ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን አመልካች በአሁኑ ተጠሪ ላይ ያቀረበው ክስ መሠረታዊ ይዘቱ ሲታይ ተጠሪን ሁለት የወንጀል ህግ ድንጋጌዎችን በመጣስ ወንጀል የከሰሰው ሲሆን የመጀመሪያው ክስ ወላጅ እናቱ ወ/ሮ አወጣሽ አብርሃ ሆና እያለ የማይመለከተውንና በሥጋ ዝምድና ግንኙነት የሌላቸውን የአቶ ግርማ ወ/ጊዮርጊስ 1,7000.00 (አንድ ሚሊየን ሰባት መቶ ሺህ ብር ) የሚገመት ንብረት ያለአግባብ ለመውረስ ሲል ከላይ የተመለከተውን የወላጅ እናቱን ስም በመለወጥ የእናቱ ስም ወ/ሮ አወጣሽ ወ/ጊዮርጊስ እንደሚባሉና የሟች ግርማ ወ/ጊዮርጊስ እህት እንደሆኑ በማስመሰል የወራሽነት ማስረጃ ከፍርድ ቤት ያወጣ በመሆኑ የወንጀል ህግ ቁጥር 696 (ሐ) መሠረት በከባድ የማታለል ወንጀል እንደተከሰሰ የሚገልጽ ሲሆን ሁለተኛው ክስ ተጠሪ በ1996 ዓ/ም የወጣውን የወንጀል ህግ ቁጥር 378 ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ በ1ኛ ክስ ላይ እንደተገለጸው ምንም ዓይነት የሥጋ ዝምድና የሌላቸውንና አጎቱ ያልሆኑትን ሟች አቶ ግርማ ወ/ጊዮርጊስን የእናቱን ወንድም እና አጎቱ

እንደሆኑ እና አጎቱ ለማስመሰል ሀሰተኛ የሆነ የአቤቱታና የቃለ መሃላ ሰነድ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፍትሐብሔር ችሎት በማቅረቡና እንደዚሁም በድሬዳዋ ማዘጋጃ ቤት በ20/02/2002 ዓ/ም የተሰጠው የጋብቻ ምስክር ወረቀት ላይ የእናቱ ስም የሚለው ቦታ ላይ አወጣሽ አብርሃ ተብሎ የተሰጠውን በተመሳሳይ ማስረጃ ለመውረስ እንዲያመቸው አስቦ ለድሬዳዋ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቤቱታ ፅፎ በማቅረብ የጋብቻ ሰርቲፊኬት ላይ የእናቱ አባት ስም ወ/ጊዮርጊስ ሆኖ እያለ በስህተት አብርሃ ተብሏልና ወ/ሮ አወጣሽ አብርሃ መባሉ ቀርቶ ወ/ሮ አወጣሽ ወ/ጊዮርጊስ ተብሎ ተስተካክሎ ይሰጠኝ ብሎ ለፍርድ ቤት አቅርቦ ፍርድ ቤቱም የቀረበውን አቤቱታ እውነተኛ እንደሆነ አድርጎ ቀይሮ የእናቱን አባት ስም አብርሃ መባሉ ቀርቶ ወ/ጊዮርጊስ ይባል ብሎ ውሳኔ በመስጠቱና ፍርድ ቤቱን አታሎ ማስረጃውን ከወሰደ በኃላ ድሬዳዋ ማዘጋጃ ቤት አቅርቦ የጋብቻው ሰርቲፊኬት ላይ ቀደም ሲል የእናቱ ስም ወ/ሮ አወጣሽ አብርሃ ይባል የነበረው ተቀይሮ ወ/ሮ አወጣሽ ወ/ጊዮርጊስ ተብሎ ሌላ ሀሰተኛ የሆነ የጋብቻ ሰርቲፊኬት አውጥቶ ይህንኑ ሰርቲፊኬት የሟች ንብረትን ለመውረስ በሚደርግ የፍትሐብሔር ክርክር ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት አቅርቦ የተጠቀመበት በመሆኑ ተጠሪ በፈጸመው በሀሰተኛ ሰነድ መገልገል ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

ተጠሪ ወንጀል ያለመፈጸሙን ክዶ የተከራከረ ሲሆን ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወንጀል ችሎት የግራ ቀኝ ማስረጃዎችን ተመልክቶ ተጠሪን በተከሰሰባቸው ሁለቱም ክሶች ጥፋተኛ በማድረግ በ3 ዓመት ከ7 ወር ጽኑ እስራትና በ 1000.00 ብር (አንድ ሺህ ብር) የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ሲል ወስኗል፡፡

ተጠሪ በውሳኔው ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርቧል፡፡ የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኙን ተቀብሎ የግራ ቀኙን አከራክሮና ተጨማሪ ማስረጃዎችን ሰምቶ ተጠሪ ወንጀሎቹን ስለመፈጸሙ ስላልተረጋገጠበት በነፃ ሊሰናበት ይገባል በማለት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሯል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የጠቅላይ ፍርድ ቤት ወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪን በነፃ በመልቀቅ የወሰነውን ውሳኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ ይዘትም በአጭሩ፡- ተጠሪ ለፈጸመባቸው ወንጀሎች ከመንግሥታዊ አካል የተሰጡ ሰነዶች እያሉ ይህንን ሳይመለከት ተጠሪ ብቻ ያለውን ሰምቶ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ መስጠቱ ከማስረጃ አመዛዘንና አቀራረብ አንጻር በአንድ ወገን ያለውን ብቻ በመስማት የተሰጠ ውሳኔ አግባብ አይደለም፣ በተጨማሪ ማስረጃነት የሰማውን የተጠሪን አባት ምስክርነት በተመለከተ በሃሰት መስክረው ከሆነ ክስ የሚመሰረት ሆኖ በማለት የሥር ፍርድ ቤት ጠቅሶ ነገር ግን ለአሁን ጉዳይ የሰጡት ቃል

አመኔታ የሚጣልበት ነው ማለቱ አግባብነት የሌለውና እርስ በእርሱ የሚጋጭ ነው፣ የተጠሪ እናት ነኝ ብለው የቀረቡት ወ/ሮ አወጣሽ አብርሃ የዲኤንኤ (DNA) ምርመራ እንዲያደርጉ በሥር ፍርድ ቤት ቢጠየቁም ቆራቢ በመሆናቸው በሚል ምርመራውን ለማድረግ አለመፈለጋቸው በተቃራኒው ሊተረጎም ሲገባው ተጠሪን በሚደግፍ ሁኔታ አለመመርመራቸው ጥያቄ ውስጥ ሳይገባና ቆራቢ ናቸው ተብሎ መታለፍ ያለአግባብ ነው፣ በሥር ፍርድ ቤት እንዲመጣ ያልታዘዘ ሰነድ ተጠሪ በራሱ መነሻነት ያቀረበውን በአንድ የፖሊስ አባል የተጻፈን ሰነድ ብቻ ተቀብሎ ታማኝነት ያለው ሰነድ ነው በማለት ውሳኔ መስጠቱ አግባብነት የሌለው ሲሆን የሥር ፍርድ ቤት በተጠሪ በኩል የቀረበው ማስረጃ በፖሊስ ኮሚሽኑ በምን መነሻነት ሰነዱን ሊሰጥ እንደቻለ ማጣራት ሳያደርግ ተጠሪን በነፃ ማሰናበቱ አግባብነት የሌለውና ምክንያታዊ ያልሆነ በመሆኑ የጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ ተሽሮ የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ እንዲጸናልን የሚል ነው፡፡

አመልካች ያቀረበው አቤቱታ ተመርምሮ ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ ያስተናገደው ፍርድ ቤት ተጠሪ ያለአግባብ ለመውረስ አስቦ ከዘጠኝ ዓመት በፊት ባስመዘገበው የጋብቻ ሰርቲፊኬት ላይ የትክክለኛ የወላጅ እናቱ ስም ወ/ሮ አወጣሽ አብርሃ ሆኖ እያለ በ2002 ዓ/ም ያረፉት የወ/ሮ አወጣሽ ወ/ጊዮርጊስ እናቱ እንደሆኑ አሳስቶ ባገኘው ማስረጃ ስለመገልገሉ በዐቃቤ ህግ ምስክሮችና የሰነድ ማስረጃዎች ተረጋግጧል በማለት የወሰነውን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ከፖሊስ ቀደም ብሎ የተጻፈው ዳብዳቤ በኃላ በተጻፈው ተሽሯል በማለት በተለይ የሥር ፍርድ ቤት የቀበሌ ማኅደር ጭምር አስቀርቤያለሁ በማለት በወሰነው ላይ ምንም ሳይል ማለፉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል አቤቱታ ለሰበር ቸሎት ይቅረብ ተብሎ ታዟል፡፡

የሰበር አቤቱታው ለተጠሪ ደርሶት ሟች ወ/ሮ አወጣሽ ወ/ጊዮርጊስ የተጠሪ እናት ስለመሆናቸው በማያመነታ መንገድ በሰውም ሆነ በጽሁፍ ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ወ/ሮ አወጣሽ አብርሃ የተጠሪ እንጀራ እናት እንጂ ወላጅ እናቴ ወ/ሮ አወጣሽ ወ/ጊዮርጊስ መሆናቸውን ወላጅ አባቴ ጭምር በምስክርነት ያረጋገጡት ጉዳይ ከመሆኑ በተጨማሪ የአፅቢ ወንበርታ ፖሊስ ጽ/ቤት ሚያዝያ 29 ቀን 2006 ዓ/ም በጻፈው ዳብዳቤ ቀደም ሲል ወ/ሮ አወጣሽ አብርሃ የተጠሪ እናት እንደሆኑ አድርጎ የጻፈው በተጠናከረ ማስረጃ ተመስርቶ አለመሆኑን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማረጋገጡ እውነታውን ይበልጥ የሚያሳይ ስለሆነ ተጠሪ ከወንጀል ህግ ቁጥር 23 አኳያ ጥፋተኛ ልባል የሚቻልበት ህጋዊ ምክንያት የለም በማለት ግንቦት 24 ቀን 2007 ዓ/ም የተጻፈ መልስ አቅርቦ ተከራክሯል፡፡ አመልካችም ቅሬታውን በማጠናከር በቀን 10/10/2007 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የክርክሩ ሂደት አጠር ባለ መልኩ ከላይ እንደተገለጸው ሲሆን ጉዳዩን ከስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ፣የግራ ቀኙ በዚህ ችሎት ካደረጉት ክርክር እንዲሁም ለሰበር ያስቀርባል ተብሎ ከተያዘው ጭብጥ አንጻር መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነውም የጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪን በነፃ መልቀቁ በአግባቡ ነው ወይ? በሚለው ጭብጥ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም ግራቀኝ ወገኖች ይህን ጭብጥ መሠረት በማድረግ ያሰሙትን ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሳኔ እና ከህጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከላይ በዝርዝር እንደተመለከትነው በዐቃቤ ሕግ ክስ የተመለከተውን ድርጊት አልፈጸምኩም በማለት ተጠሪ ቢከራከርም፤ ክሱን የሰማው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግን ድርጊቱን ስለመፈጸሙ በማስረጃ አረጋግጦአል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የሰማው ፍ/ቤት ግን የራሱን ተጨማሪ ማስረጃ በመስማት የስር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሯል፡፡ እንደሚታየው ድርጊቱ ተፈጽሞአል ወይስ አልተፈጸመም የሚለው የፍሬ ነገር ጭበጥ በመሆኑ የሚነጥረው (የሚጣራው) በማስረጃ ነው፡፡ የፍሬ ነገር ጭብጥን በማስረጃ የማጣራት እና የተሰማውን ማስረጃ የመመዘን ሥልጣን ያላቸው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ክርክሩን ተመልክተው የተለያየ መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል፡፡ በዐቃቤ ህግ ክስ የተመለከተው ድርጊት በተጠሪ መፈጸሙን ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ በማረጋገጡም ድርጊቱን ከተጠቀሰው የወንጀል ሕጉ ድንጋጌ ጋር አገናዝቦ የጥፋተኛነት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት ደግሞ በሰማው ተጨማሪ ማስረጃ ተጠሪ ወንጀል ስላለመፈጸሙ ተረጋግጧል በማለት ተጠሪን በነፃ እንዲሰናበት ወስኗል፡፡

በበኩላችንም እንደምናየው ተጠሪ በዐቃቤ ህግ ክስ የተመለከተውን ድርጊት ፈጽሞአል ወይስ አልፈጸመም የሚለውን የፍሬ ነገር ጭብጥ የማጣራት ሥልጣን ለሰበር ችሎቱ የተሰጠ ባለመሆኑ በዚህ ደረጃ የምንመረምረው አይደለም፡፡ በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠው እውነታ በክሱ በተጠቀሰው ድንጋጌ የተመለከተውን ወንጀል ያቋቁማል ወይ? የሚለው ነጥብ ግን የህግ ጭብጥ በመሆኑ ተመልክተነዋል፡፡

ተጠሪ የተከሰሰው የመጀመሪያው ክስ በወንጀል ህጉ በአንቀጽ 696 (ሐ) የተመለከተውን ድንጋጌ ተላልፎ ወንጀል ፈጽሞአል ተብሎ እንደሆነ ከላይ ተመልክተናል፡፡ ድንጋጌው የሚለው "ወንጀሉ የተፈጸመው በህዝብ አስተዳደር ወይም በህዝብ አገልግሎት ላይ እንደሆነ ነው፡፡" በዚህ ድንጋጌ ሥር ጥፋተኛ ሲባል ከአስራ አምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራትና እስከ ብር ሃምሳ ሺህ በማይበልጥ መቀጮ ያስቀጣል፡፡

በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው የተጠሪ ወላጅ እናቱ ወ/ሮ አወጣሽ አብርሃ ሆና እያለ የማይመለከተውንና በሥጋ ዝምድና ግንኙነት የሌላቸውን የአቶ ግርማ ወ/ጊዮርጊስ 1,7000.00 (አንድ ሚሊየን ሰባት መቶ ሺህ ብር ) የሚገመት ንብረት ያለአግባብ ለመውረስ ሲል ከላይ

የተመለከተውን የወላጅ እናቱን ስም በመለወጥ የእናቱ ስም ወ/ሮ አወጣሽ ወ/ጊዮርጊስ እንደሚባሉና የሚች ግርማ ወ/ጊዮርጊስ እህት እንደሆኑ በማስመሰል የወራሽነት ማስረጃ ከፍርድ ቤት አውጥቷል፡፡ለፍርድ ቤቱ ወራሽ መሆኑ እንዲረጋገጥለት አቤቱታውን በቃለ መኀላ አረጋግጦ አቀርቧል፡፡ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ህግ ቁጥር 92 እንዲሁም ቁጥር 205 መሠረት አንድን አቤቱታ በቃለ መሃላ እንዲቀርብ ህግ አውጪው የፈለገበት በሁለት ምክንያቶች ነው፡፡ የመጀመሪያው ሀሰተኛ አቤቱታዎች በፍትህ ሥርዓቱ ውስጥ የሚያስከትሉትን የፍትህን መጓደል ለመከላከል ሲሆን ሁለተኛው ምክንያት ሀሰተኛ አቤቱታ የሚያቀርቡ ተከራካሪዎች በህግ እንዲጠየቁ ለማድረግ ነው፡፡ ተጠሪ ሀሰተኛ አቤቱታ በማቅረብ ፍትህ እንዲዛባ ከማድረጉም ባሻገር በህግ በተቋቋመ የተከራካሪዎችን መብትና ጥቅም በሚያስከበር አካል ፊት እንደዚህ ያለውን ሀሰተኛ የሆነ አቤቱታ አቅርቦ ማስወሰኑ በወንጀል ህግ ቁጥር 696 (ሐ) የተደነገገውን ድንጋጌ የጣሰ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡በመሆኑም በተያዘው ጉዳይ በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠው እውነታ በክሱ በተጠቀሰው ድንጋጌ የተመለከተውን ወንጀል የሚያቋቁም ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የወንጀል ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይህንን እውነታ በአግባቡ ሳያጤን አልፎ ተጠሪን በነፃ እንዲሰናበት በማለት መወሰኑ የማስረጃ ህግ መርህን ጭምር የሚጥስ ውሳኔ በመሆኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሁለተኛውን ክስ በተመለከተ በ1ኛው ክስ ሥር ሊጠቃለል የሚችል ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ከተጠሪ ድርጊት አንጻር መርምረናል፡፡ የተጠሪ ሀሳብና ፍላጎት የሚች ግርማ ወ/ጊዮርጊስን ንብረት ለማግኘት ነው፡፡ ለዚህ ግብ ያስችለው ዘንድ እናቱን የሚች እህት አድረጎ ማስወሰን ስላለበት በ1989 ዓ/ም ጋብቻ ሲመሰርት የእናቱን ስም አወጣሽ አብርሃ በማለት በጋብቻ ሰርቲፊኬት የመዘገበውን ወ/ሮ አወጣሽ ወ/ጊዮርጊስ ተብሎ እንዲቀየር በድሬዳዋ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አቅርቦ ካስወሰነ በኃላ ለማዘጋጃ ቤት በማቅረብ የጋብቻ ሰርቲፊኬቱ እንዲቀየር አድርጓል፡፡ይህንን ማስረጃ ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በማቅረብ የሚች ወራሽ መሆኑን አስወስኗል፡፡ይህን ሰነድ የተጠቀመውም ዋናው ግብ የሆነውን የሚች ንብረት የማግኘት ዓላማውን ከግቡ ለማድረስ ስለሆነ ሊታይ የሚገባው ከወንጀል ህግ አንቀጽ 61 (3) አንጻር ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ወንጀል ህግ አንቀጽ 378 ድንጋጌን በመተላለፍ የተከሰሰበት ወንጀል በወንጀል ህግ ቁጥር 61 (3) መሰረት በወንጀል ህግ ቁጥር 696 (ሐ) የሚጠቃለል ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በወንጀል ህግ ቁጥር 378 መሠረት የጥፋተኝነትም ሆነ የቅጣት ውሳኔ ሊወሰንበት አይገባም ብለናል፡፡

በመጨረሻም ከላይ በዝርዝር እንደተገለጸው ተጠሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 696 (ሐ) በመተላለፍ ጥፋተኛ ሆኖ ስለተገኘ ሊወሰን የሚገባውን ቅጣት ከወንጀል ህግ እንዲሁም ወንጀሉ በተፈጸመበት ጊዜ በሥራ ላይ ከነበረው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 አንጻር ተመልክተናል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪን በወንጀል ህግ ቁጥር 696 (ሐ) መሠረት ጥፋተኛ ነው

ካለ በኃላ የወንጀል ደረጃውን መካከለኛ ሲል ይዟል፡፡ በእኛም በኩል ይህ ተገቢ እንደሆነ ተመልክተናል፡፡ ይህም እርከን 19 ሥር የሚያርፍ በመሆኑ በዚህ እርከን ያለው ፍቅደ ሥልጣን ከ4 ዓመት እስከ 4 ዓመት ከ10 ወር በመሆኑ መነሻ ቅጣት 4 (አራት) ዓመት ተይዟል፡፡ በከፍተኛ ፍርድ ቤት ለተጠሪ የተያዙለት ሁለት የቅጣት ማቅለያዎች እያንዳንዳቸው ሁለት እርከን የሚያስቀንሱ በመሆናቸው 4 (አራት) እርከን ተቀንሶ መጨረሻ ቅጣት ሊወሰን የሚገባው እርከን 15 ሥር በመሆኑ ተጠሪ በ2 ዓመት ከ9 ወር ጽኑ እስራት እንዲቀጣ ብለናል፡፡ ሲጠቃለልም የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በወ/ይ/መ/ቁ. 96602 በቀን 29/09/2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 195 (2) (ለ) (2) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የከ/መ/ቁ 109227 ህዳር 3 ቀን 2006 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 195 (2) (ለ) (2) መሠረት ተሸሽሏል፡፡
3. ተጠሪ ጥፋተኛ በተደረገበት የወንጀል ህግ ቁጥር 696 (ሐ) መሰረት ቀደም ሲል የታሰረው ካለ ታሳቢ ተደርጎ በሁለት ዓመት ከዘጠኝ ወር ጽኑ እስራትና በብር 1000.00 (አንድ ሺህ ብር) መቀጮ እንዲቀጣ ተወስኗል፡፡
4. በተጠሪ ላይ የተወሰነውን የ2 ዓመት ከ9 ወር ጽኑ እስራትን ቀደም ሲል የታሰረ ካለ ታሳቢ ተደርጎ የተወሰነበትን ቅጣት ተከታትሎ እንዲያስፈጽም ለአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት የመሰሪያ ወራንት ይጻፍ፡፡የብር 1000.00 (አንድ ሺህ) መቀጮ ለመንግሥት ገቢ ይደረግ፡የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ልማት ሚንስቴር ያስፈጽም፡ይጻፍ፡፡
5. የውሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍርድ ቤቶች ይድረስ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ፍ

ሰ/መ/ቁ 132266

ታህሳስ 26 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች ፡- ዓሊ መሀመድ

ተኽሊት ይመሰል

ቀነአ ቂጣታ

ሰናይት አድነዉ

ጳዉሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- ወ/ሮ አልማዝ አሰፋዉ ልጅ መስፍን አስፋዉ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጲያ ሱማሌ ክልል የዐቃቤ ህግ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለዉን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበዉ አመልካች የወንጀል ህግ አንቀጽ 574(2) የተመለከተዉን በመተላለፍ ወንጀል ፈጽማለች በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ ህጋዊ መሰረት ያለዉ ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉን ምላሽ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነዉ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየዉ በፋፈን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነዉ፡፡ ከዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጠሪ ባቀረበዉ የወንጀል ክስ አንደኛ ተከሳሽ የሆነችዉ የአሁን አመልካች የአስራ ሁለት ዓመት ህጻን የሆነችዉ ሚች ኤደን ሃጂ ሽርቅያ ሚያዝያ 3 ቀን 2006 ዓ.ም ከቀኑ አስራ አንድ ሰአት ተኩል ከተከሳሽዋ ሻወር ቤት ዉስጥ በአሰቃቂ ሁኔታ ስትገደል ተከሳሻዋ ግቢ ዉስጥ እያለች ምንም እርደታ ያላደረገች በመሆኑ ወንጀል ፈጽማለች በማለት ተከሳሽ የወንጀል ህግ ቁጥር 448 በመተላለፍ ለፍትህ እገዛ በማድረግ ፈቃደኛ ባለመሆን ወንጀል ፈጽማለች በማለት ሁለት የወንጀል ክሶችን አቅርቦባታል፡፡

2.አመልካች በተከሳሽነት ቀርባ የወንጀሉን ድርጊት አልፈጸምኩም ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ክዳ ተከራክራለች ፡፡ ተጠሪ ክሱን ያስረዱልኛል በማለት አምስት ምስክሮች አቅርቦ አሰምቷል፡፡ አመልካች መከላከያ ማስረጃ እንድታቀርብ የስር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሰጥቶ አመልካች የሰዉና የሰነድ ማስረጃ በመከላከያ ማስረጃነት አቅርባለች፡፧ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች

በወንጀል ሕግ አንቀጽ 574(2) እና አንቀጽ 448 የተመለከተዉን በመተላለፍ የወንጀል ድርጊት የፈጸመች ናት በማለት ወንጀሉ አንደኛ ደረጃ ላይ የሚወድቅ መሆኑን ገልጾ አመልካች በአምስት ዓመት ጽኑ እስራት እንድትቀጣ ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርባለች፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት አቅርባ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የባታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበትም በማለት አጽንቶታል፡፡

3. አመልካች ነሐሴ 19 ቀን 2008 ዓ/ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ከሟች ህፃን ኤደን ወላጆች ጋር በአበልጅነት ተሳስረው የቀረበ ወዳጅነት የነበራቸው በመሆኑ ሟችና የእሷ ወንድም በትምህርት ቤታቸው ቅርብ ከሆነው በአመልካች ቤት የምሳ እቃቸውን በማስቀመጥ በምሳ ሰዓት እየመጡ ምሳቸውን ይበሉ ነበር፡፡ ሚያዚያ 1 ቀን 2006 ዓ/ም ሟችና ወንድሟ በተለመደው ሁኔታ ምሳ አስቀምጠው በምሳ ሠዓት በተለመደው ሁኔታ ከአመልካች ቤት መጥተው ምሳቸውን ከበሉ በኃላ ወደ ትምህርት ቤት ተመልሰው ሄደዋል፡፡ ነገ ግን ህጻን ኤደን የትምህርት ቤት ደንብ ስለጣሰሽ ወላጅ ይዘሽ እንዲትቀርቢ በማለት ትምህርት ቤቱ ይህንን ለወለጆቿ ደውሎ በመናገሩ በዚህ ተደናግጣ፣ ከአመልካች ቤት ውስጥ ተደብቃ በመግባት ከአመልካች ንግድ ቤት ራቅ ብሎ የተሰራው ሻወር ቤት ውስጥ ገብታ ከውስጥ በሩን ቆልፋ ራሷን በጨርቅ አንቀ በጓሮ በኩል ያለው ጎረቤት የጣር ጽምፅ በመስማቱ በሩን ሰብሮ ጨርቁን በመበጠስ ሕይወቷን ለመታደግ ሞክሯል፡፡ ከዚህ በኂላ እኔም ሟችን በባጃጅ ወደ ሀኪም ቤት ስወሰድ ህይወቷ አልፏል፡፡ እውነታው ይህ ሆኖ እያለ ተጠሪ አንድ ጊዜ ሟችን ከሞት ለመታደግ የሞከሩትን ሰዎች በግፍ ገድላችኂታል በማለት ክስ አቅርቦ ሰዎቹን በይግባኝ በነፃ ተሰናብተዋል፡፡ እኔን ደግሞ ከህግ አግባብ ውጭ አግባብነት የሌለው የህግ ድንጋጌ ጠቅሶ ያቀረበውንና ተጠሪ በማስረጃ ያላረጋገጠውን ክስ በመቀበል የበታች ፍረድ ቤቶች የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በስበር ታይቶ እንዲታራምልኝ በማለት አመልክታለች፡፡

4. ተጠሪ ጥቅምት 16 ቀን 2009 ዓ/ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ ባቀረበው መልስ እድሜዋ ለአቅመ ሄዋን ያልደረሰች በአመልካች ቤት ስታድግና ጤናማ አዕምሮ ያልነበራት ልጅ ለአደጋ ስትጋለጥ ማዳን እያቻለች ለማዳን ያልሞከረች መሆኑ ተጠሪ ባቀረበው ማስረጃ ተረጋግጦ ውሳኔ የተሰጠበት በመሆኑ አመልካች ያቀረበችው የሰበር አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች ጥቅምት 23 ቀን 2009 ዓ/ም የተጻፈ የመልስ መልስ አቅርባለች፡፡

5. ከስር የክርክሩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ተገቢነት መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ጥፋተኛ የተባለችው የወንጀል ህግ አንቀጽ 574(2) ተላልፋለች ተብሎ ነው፡፡ የወንጀል ህግ አንቀጽ 574 የወንጀል ህጉ የሰውን ህይወት አካል ወይም ጤንነት ለአደጋ በማጋለጥ የሚፈጸመው ወንጀሎች በማለት በምእራፍ አራት ስር ከወንጀል ህጉ አንቀጽ 571 እስከ አንቀጽ 579 በዘረዘረቸው ወንጀሎች ውስጥ ተካትቶ የሚገኝ ድንጋጌ ነው፡፡ በወንጀል ህግ አንቀጽ 57/2/ የተደነጋገውን ወንጀል ፈጽሟል ተብሎ አንድ ሰው በኃላፊነትን የሚጠየቀው በወንጀል ህግ አንቀጽ 574 ንዑስ አንቀጽ 1 የተዘረዘሩትን ወንጀሉን የሚያቋቋሙ መሠረታዊ ፍሬ ነገሮች በአንቀጽ 574 ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከቱት የማክበጃ ምክንያት መኖራቸው በማስረጃ ሲረጋገጥ ነው፡፡

6. የወንጀል ህግ አንቀጽ 574 “ሰውን ለአደጋ ማጋለጥ ወይም መተው” በእንግሊዘኛው ቅጅ Exposure or Abandonment of Another የሚል ርእስ ያለው ሲሆን የአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ 1 ቃል በቃል ሲነበብ” በጤናው በእድሜው በሁኔታው ወይም በማናቸውም ሌላ ምክንያት ራሱን ለመጠበቅ የማይችለውን ሌላ ሰው የማናቸውም ምክንያት ይሁን በጠባቂነት ወይም በኃላፊነት ለማኖር የተቀበለ ማንም ሰው የተባለውን ሰው አስቦ (ሀ) በሕይወቱ ወይም በጤናው ላይ በቅርብ መድረሱ ለማይቀር አደጋ ያገለጠው እንደሆነ ወይም (ለ) ይህን በመሰለ ሁኔታ ላይ በሚገኝበት ጊዜ ጥሎት የሄደ እንደሆነ ወንጀሉን እንደፈጸመ ተቆጥሮ ቅጣት የሚጣልበት መሆኑን የሚደነግግ ሲሆን የአንቀጽ 574 ንዑስ አንቀጽ 2 ወንጀሉ የተፈጸመው በህጻን ልጅ ላይ የሆነ እንደሆነ ቅጣቱ ከሰባት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት ይሆናል፡፡ በማለት ይደነግጋል፡፡

7. የአንቀጽ 574 የእንግሊዘኛው ቅጅ ይዘት ሲታይም “የአንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1“ who ever Having the custody or charge, on no matter what grounds of a person in capable of protecting

Himself= whether on account of his health, his age, his situtation any other circumstances intentionally

(a) Exposes him there by putting him imminent danger of life or heath or
(b) Abandons him when in like situation የሚል ይዘት ያለው ሲሆን ንዑስ አንቀጽ 2 ‹‹where the crime is committed against infant, the punishment shall be rigorous imprisonment not exceeding seven years›› የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

8. ከላይ ከጠቀስነው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 574 ድንጋጌ የምንረዳው፣ በመጀመሪያ ደረጃ ሰውን ለአደጋ የማጋለጥ ወይም የመተው ወንጀል ሆነ ተብሎ የሚፈጸም ወንጀል መሆኑን ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ ተጠያቂ የሚሆን ሰው፣ ሰውየውን ለአደጋ ያጋለጠው ወይም ህይወቱ በአደጋ ላይ እንደሚወድቅ እያወቀ የተወው፣ ተጎጅው በአደጋው ህይወቱን እንዲያዳጣ ሆነ ብሎ አስቦበት የፈጸመው ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ወንጀሉን የፈጸመው ሰው ከአደጋ ካልጠበቀው በስተቀር የተጎጅውን ህይወት ከአደጋ ውስጥ የሚጥል እርግጠኛና በፍጥነት ሊደርስ የሚችል አደጋ መኖሩን እያወቀ ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ በሶስተኛ ደረጃ የሌላውን ህይወት ከአደጋ የመጠበቅ ሃላፊነት ያለበት ሰው፣ ህይወቱ ለአደጋ የተጋለጠውን ሰው በማናቸውም ምክንያት ለመጠበቅና በእሱ ቁጥጥርና ክትትል ስር ለማኖር ሃላፊነቱን የተቀበለ ሰው መሆን ያለበት መሆኑ ሲሆን፣ በአራተኛ ደረጃ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 574 ንዑስ አንቀጽ 2 የአማረኛው ቅጅ "ህጻን" የሚለውን አነጋገር፣ ማናቸውም አስራ ስምንት ዓመት ያልሞላው ሰው ማለት እንዳልሆነ ከእንግሊዘኛው ቅጅ "where the crime is committed against infant" በማለት በደነገገው አገላለጽ ግልጽ ያደረገው መሆኑን የሚያሳይ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

9. ከላይ የተደነገገውን የሕጉን ይዘት ተጠሪ በአመልካች ላይ ካቀረበው ክስና ማስረጃ ጋር ስናገናዝበው በመጀመሪያ ደረጃ ተጠሪ አመልካች የአስራ ሁለት አመት ህጻን የሆነችው ኤደን፣ በሌሎች ሰዎች በአሰቃቂ ሁኔታ ስትገደል አመልካች ምንም እርዳታ አላደረገችም በማለት ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረበው የወንጀል ክስ የገለጸ ሲሆን፣ ሟች ህጻን ኤደን በሰዎች ያልተገደለች መሆኑና አመልካች መታጠቢያ ክፍል ውስጥ ገብታ ራሷን በጨርቅ በመስቀሏ ምክንያት የሞት አደጋ የደረሰባት መሆኑን ተጠሪ ባቀረበው የወንጀል ክስ ሁለተኛው ፓራግራፍ እና በበታች ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ይህ የሚያሳየው ተጠሪ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 574 ይዘት በአግባቡ ሳይረዳና የወንጀል ክሱን የወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 111 እና የወንጀል ሕግ ቁጥር 112 በሚደነግገው መሰረት አዘጋጅቶ ያላቀረበ ፣ ተጠሪ ያቀረበው የወንጀል ክስ ይዘት ተቃራኒ ይዘት ያለው መሆኑን ነው፡፡

10. ተጠሪ አመልካች የወንጀል ሕግ ቁጥር 574 ንዑስ አንቀጽ 2 በመጣስ ሟች ኤደንን ለአደጋ አጋልጣለች ወይም ትታለች በማለት ባቀረበው የወንጀል ክስ ውስጥ ሟች የሞተችው በአመልካች የገላ መታጠቢያ ክፍል ውስጥ ራሷን በጨርቅ በመስቀል መሆኑን፣ አመልካች በወቅቱ ከዚያው ግቢ ውስጥ ስለነበረች ሟች የታነቀችበትን ጨርቅ በጥሳ ከሞት ልታድናት እየቻለች ይህን ያላደረገች መሆኑን ገልጿል፡፡ ተጠሪ ይህንን ክስ ለማስረዳት ያቀረባቸው ምስክሮች ሚያዚያ 1 ቀን 2006 ዓ.ም ኤደን የተባለች ልጅ ታንቃ፣ ሰዎች የታነቀችበትን ጨርቅ በጥሰው አመልካችና ሌሎች ሰዎች ወተት ለማጠጣት ሲሞክሩና በኋላም በባጃጅ ሟችን ይዘው ወደ ሃኪም ቤት ሲወስዱ ያዩ መሆናቸውን እንደመሰከሩ ከበታች ፍ/ቤቶች ውሳኔ ይዘት ለመረዳት ችለናል፡፡

11. ተጠሪ ያቀረበው የወንጀል ክስ፣ ሟች ህጻን ኤደን ራሷን በራሷ ለማጥፋት እንደምትሞክርና በዚህም ምክንያት የሟች ኤደን ህይወት አደጋ ላይ ሊወድቅ እንደሚችል አመልካች እያወቀች፣ አመልካች ሆንብላና ህጻን ኤደን ራሷን በማነቅ እንድታጠፋ በማሰብ ተገቢውን ጥንቃቄ ሳታደርግ የተወቻት መሆኑን የሚገልጽ አይደለም፡፡ አመልካች ህጻን ኤደን ህይወቷን በገዛ እጇ ለማጥፋት በሚያስችላት በእርግጠኝነት ሊደርስ በሚችል አደጋ ውስጥ የነበረች መሆኑን እንደምታውቅ የተጠሪ ምስክሮች አላስረዱም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ህጻን ኤደን ትምህርቷን አቋርጣ ወደ እሷ ቤት የመጣች መሆኑን ያየችና የምታውቅ መሆኑን ተጠሪ ያቀረባቸው ማስረጃዎች የሚገልጹ እንዳልሆኑ ተረድተናል፡፡ ተጠሪ ህጻኗ ከንግድ ቤቱ ራቅ ብሎ ከተሰራው መጸዳጃ ቤት ውስጥ ገብታ በጨርቅ ራሷን ስታንቅ፣ አመልካች በዚያው ግቢ ውስጥ ሆና ሳለ ቀድማ አልደረሰችም በማለት የሚያቀርበው ክርክር በወንጀል ህግ አንቀፅ 574 የተደነገገው ወንጀል የሚፈፀመው ሆን ተብሎ እንደሆነ ከሚገልፀው ጋር አብሮ የሚሄድ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ተጠሪ አመልካች ሆነብላ እና አስባ ህፃን ኤደን ራስዋን በራስዋ እንድታጠፋ ለአደጋ ያጋለጠቻት ወይም ትታት የሄደች መሆኑን የማስረዳት ግዴታውን የህገ-መንግስቱ አንቀፅ 20 ንኡስ አንቀፅ 3 በሚደነግገው መሰረት አልተወጣም፡፡በሌላ በኩል አንድ ወንጀል ወንጀሉን በቸልተኝነት የሚያስጠይቀው በህጉ በተለየ ክፍል ያስቀጣል ተብሎ በግልፅ በተደነገገ ግዜ እንደሆነ የወንጀል ህጉ አንቀፅ 59 ንኡስ አንቀፅ 2 የተደነገገ በመሆኑ አመልካች ሟች ራሷን ባነቀችበት ቤት ግቢ ውስጥ እያለች የሟችን የሲቅና የጣር ድምፅ ባለመስማቷ ምክንያት በወንጀል ህግ ቁጥር 574 ንኡስ አንቀፅ 2 ተጠያቂ የምትሆንበትን የህግ ምክንያት አላገኘንም፡፡

12. ከላይ በዝርዝር በገለፅናቸው ምክንያቶች ተጠሪ አመልካች የወንጀል ህግ 574 የተዘረዘረውን ወንጀል የፈፀመች ስለመሆኑ በህጉ አነጋገር እና የድርጊቱን አፈጻፀም የሚገልፅ |የወንጀል ክስ በወ/መ/ስ/ስ/ሕግ ቁጥር 111 እና በወንጀል ህግ ቁጥር 112 መሰረት አላቀረበም፡፡የበታች ፍ/ቤቶች ተጠሪ የወንጀል ክሱን በማሻሻል አመልካች የወንጀል ሕግ አንቀፅ 574 (2) የተገለፀውን የወንጀል ድርጊት የፈጸመች መሆኑን የሚያሳይ የአመልካችን የሀሳብ ክፍል ሆን ብላ ወንጀሉን የፈፀመች በመሆኗ የአመልካችን ግዙፍ ድርጊትና ተሳትፎ ግልፅ አድረጎና ዘርዝሮ እንዲያቀርብ በወ/መ/ስ/ስ/ህ/ቁ 119(1) መሰረት ትእዛዝ ሳይሰጡ የወንጀል ክሱን ማየታቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ሟች ህፃን ኤደን ከመፀዳጃ ቤት ታንቃ ሌሎች ሰዎች የታነቀችበትን ጨርቅ በጥሳው ከወጣች በኃላ ፈፅማዋለች በማለት በተጣራ ምስክሮች የተዘረዘረው ግዙፍ ተግባር አመልካች የሟችን ሂወት ለመታድገ የቻለችውን ጥረት ማድረጓንና በወንጀል የሚያስጠይቅ የወንጀል ተግባር ያልፈፀመች መሆኑን የሚያረጋግጥ ሆኖ እያለ የበታች ፍ/ቤት አመልካች የወንጀል ሕግ ቁጥር 574(2) በመተላለፍ ወንጀል ፈፅማለች

በማለት የሰጡት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ ከላይ በዝርዝር የጠቀስናቸውን የህግ ድንጋጌዎች የሚጥስና መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

13. የስር ፍርድ ቤት አመልካች በወንጀል ህግ አንቀጽ 448 በመተላለፍ ጥፋት፣ፈጽማለች በማለት የጥፋተኝነት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ሆኖም ተጠሪ አመልካች በወንጀል ህግ አንቀጽ 448 የተዘረዘሩትን ድርጊቶች ስለመፈጸሙ በግልጽና የወ/መ/ስ/ስ/ህግ/ቁ/111/ እና የወ/መ/ስ/ስ/ህግ/ቁ/ 112 በሚደነግገበት መሰረት አላቀረቡም፡፡ ተጠሪ ያቀረበችው ምስክሮቹም አመልካች በወንጀል ህግ አንቀጽ 448 የተመለከተውን ወንጀል ስለመፈጸሟ የሰጡት የምስክርነት ቃል የሌለ መሆኑን ተረድተናል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ተጠሪ በአግባቡ የወንጀል ክሱን ባላቀረበበትና ክሱን የሚያስረዳ ማስረጃ ባላቀረበበት ሁኔታ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በወንጀል ህግ አንቀጽ 448 በመተላለፍ ወንጀል ፈጽማለች በማለት የሰጠውን ውሳኔ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት ማፅናታቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

14. በአጠቃላይ ሲታይ አመልካች የወንጀል ህግ አንቀጽ 574/2/ እና አንቀጽ 448 የተደነገጉትን በመተላለፍ የወንጀል ተግባር የፈጸመች መሆኑን በተሟላ ሁኔታ የሚያሳይ የወንጀል ክስ ተጠሪ ያላቀረበበት ሆኖ እያለና ተጠሪ ያቀረበውን የወንጀል ክስ የማስረዳት ግዴታውን በአግባቡ ባልተወጣበት ሁኔታ አመልካች በወንጀል ህግ አንቀጽ 574/2/ እና አንቀጽ 448 የተመለከተውን በመተላለፍ ወንጀል ፈጽማለች በማለት በአምስት ዓመት ጽኑ እስራት እንድትቀጣ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ስርዓት ህግ ቁጥር 195 ንዑስ አንቀጽ 2/ለ/1 መሰረት በመሻር አመልካች በነፃ ልትሰናበት ይገባል በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የኢትዮጲያ ሱማሌ ክልል የፋፉን ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 711/06 ሰኔ 10 ቀን 2005 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔና ፍርድ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 05/1/201/06 መጋቢት 1 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 05/01/125/07 ሰኔ 15 ቀን 2008 ዓ/ም የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ስ/ስ/ህግ/ቁ/ 195 ንዑስ አንቀጽ 2/ለ/1/ መሰረት ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የወንጀል ህግ አንቀጽ 574/2/ እና የወንጀል ህግ 448 በመተላለፍ ወንጀል የፈጸመች ስለመሆኑ ተጠሪ የማስረዳት ግዴታውን ያልተወጣ በመሆኑ አመልካችዋ ከቀረቡባት ሁለት የወንጀል ክሶች በነፃ እንድትሰናበት በማለት ወስነናል፡፡

3. በአመልካች ላይ ተወስኖ የነበረው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ሙሉ በሙሉ ተሽሮ አመልካች በነፃ እንድትሰናበት ከዚህ ሰበር ችሎት የተወሰነ መሆኑን አውቆ አመልካችን በዛሬው ዕለት ከእስር እንዲለቃት ለክፍሉ ማ/ቤት የመፍቻ ትዕዛዝ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ፍ

የሰ/መ/ቁ.123046

የካቲት 29 ቀን 2009ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተፈሪ ገብሩ

ቀነዓ ቂጣታ

አይሸሽም መለሰ

ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- አቶ  አዲሱ ገመቹ ተከታታይ ዘመድ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ዐ/ሕግ ሞገስ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ የቀረበዉ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች በቸልተኝነት ሲያሽከረክር በወንጀል ሕግ አንቀጽ 559 ንኡስ አንቀጽ 2 በመተላለፍ ገንዘብ አስከፍሎ አሳፍሯቸዉ በነበሩት በሰባት ሰዎች ላይ ሰባት በቸልተኝነት በሰዉ አካል ላይ ጉዳት የማድረስ ወንጀሎችን የፈጸመ ጥፋተኛ ነዉ በማለት የሰጡት የሕግ ትርጉም የጥፋተኝነትና የቅጣት ዉሳኔ ተገቢ ነዉ ወይስ አይደለም? የሚለዉን ጭብጥ በሰበር አይቶ ለመወሰን ነዉ፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የታየዉ በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ መስተዳደር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነዉ፡፡ በስር ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ፣ አመልካች ተከሳሽ ሆነዉ ተከራክረዋል፡፡
2. ክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበዉ ክስ ነዉ፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ሥምንት የወንጀል ክሶችን አቅርቦበታል፡፡ ተጠሪ ባመልካች ላይ ባቀረበዉ የመጀመሪያዉ ወንጀል ክስ ተከሳሽ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 543/3/ በመተላለፍ የሰዉን ሕይወትና ጤንነት የመጠበቅ ሙያዊ ግዴታ እያለበት ሆኖ እያለ ይህንን ግዴታዉን በአግባቡና በጥንቃቄ ባለመወጣት ነሐሴ 15 ቀን 2006 ዓ.ም ከጠዋቱ በግምት 1፡00 ሰዓት ሲሆን የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-29507 ኦ.ሮ የሆነ የሕዝብ ማመላለሻ ሚኒባስ እያሽከረከረ ይዞ ከሰንቦ ወደ ሸኖ አቅጣጫ ሲጓዝ ሕግ እንዲጭን ከተፈቀደለት አስራ ሁለት ሰዎች በላይ ሥድስት ሰዎችን በትርፍነት በመጫን በአንለላና ጠራ ወረዳ ፌጠናአላመስኖ ቀበሌ ጨለቅለቃ ከተባለዉ ልዩ ሥፍራ ሲደርስ ከአስፓልት መንገድ

11 ሜትር 40 ሳንቲሜትር ወጥቶ መኪናዉ በመገልበጡ በአደጋዉ ሟች መሰረት በደኑና ሟች ሳህለ ማርያም ከፍተኛ ጉዳት ደርሶባቸዉ፣ በሕክምና ሲረዱ ቆይተዉ ሀምሌ 16 ቀን 2006 ዓ.ም ሕይወታቸዉ ያለፈ በመሆኑ በከባድ ቸልተኝነት የሰዉ መግደል ወንጀል ፈጽሟል፡፡

3. እንደዚሁም ተጠሪ ከላይ በተገለጸዉ ሥፍራና ጊዜ በመኪናዉ ዉስጥ ተሳፋሪ የነበሩት 1ኛ ሞገስ መገርሳ 2ኛ ደሉ ወልዴ 3ኛ በሻህ ጌታነህ 4ኛ ቤዛ ሞገስ 5ኛ እሸቱ ሉቤን 6ኛ ዘዉድነሽ አለሙና እና 7ኛ አለነሽ ጋሸን በተለያየ የሰዉነት ክፍላቸዉ ላይ ጉዳት የደረሰባቸዉ በመሆኑ ተከሳሽ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 559/2/ በመተላለፍ ሰባት በሰዉ አካል በቸልተኝት ጉዳት የማድረስ ወንጀሎችን ፈጽሟል በማለት በእያንዳንዱ ተጎጅ ሥም አንድ ወንጀል ክስ በጥቅል ሰባት ወንጀል ክሶችን አቅርቧል፡፡

4. ተከሳሽ በሥር ፍርድ ቤት ቀርቦ ክሱ ተነቦለት ከተረዳ በኃላ በሰጠዉ የእምነት ክህደት ቃል የወንጀል ድርጊት የፈጸመ ቢሆንም እንደ ክሱ አይደለም የሞት አደጋም ሆነ የአካል ጉዳት የደረሰባቸዉ ግለሰቦች ጉዳት የደረሰባቸዉ በድንገት የኃላ ጎማ በመፈዳቱና ሚዛኑ ወደ አንድ በኩል በማጋደሉ ነዉ፡፡ አደጋ የደረሰዉ በድንገት በመኪናዉ ላይ በደረሰ ችግር ስለሆነ ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ተከራክሯል፡፡

5. ተጠሪ በወቅቱ መኪናዉ ዉስጥ በነበሩ ምስክሮች አቅርቦ አሰምቷል፣ትራፊክ አደጋ ፕላን መግለጫ ሰነድና ፕላኑን ያነሳዉን ባለሙያ በማስረጃነት አቅርቧል፡፡ አመልካች የመከላከያ ማስረጃ እንዲያቀርብ የሥር ፍርድ ቤት ብይን ሰጥቷል፡፡ አመልካች የመከላከያ ማስረጃ የሌለዉ መሆኑን በጽሁፍ አረጋግጧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የተጠሪን ተደራራቢ ወንጀል ክስና ማስረጃ ከመረመረ አመልካች በወንጀል ሕግ ቁጥር 543/3/ የተመለከተዉን በመተላለፍ በከባድ ቸልተኝት ሰዉ መግደል ወንጀል የፈጸመ ጥፋተኛ ነዉ፡፡ እንደዚሁም አመልካች በወንጀል ሕግ ቁጥር 559/2/ በመተላለፍ ከሳሽ ባቀረባቸዉ ሰባት ወንጀል ክሶች የተገለጹትን ሰባት በቸልተኝት አካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል የፈጸመ ጥፋተኛ ነዉ በማለት የጥፋተኝነት ዉሳኔ ሰጥቷል፡፡

6. የቅጣት ዉሳኔዉን በተመለከተ የቅጣት አስተያየት ከተቀበለ በኃላ አመልካች በወንጀል ሕግ ቁጥር 543/3/ በመተላለፍ ጥፋተኛ ሆኖ ለተገኘበት አንደኛዉ ክስ የእስራት ቅጣቱ እርከን ሃያ አምስት የገንዘብ መቀጮ እርከን ሰባት ላይ ይወድቃል፡፡ አመልካች በወንጀል ሕግ ቁጥር 559/2/ በመተላለፍ ጥፋተኛ ለተባለባቸዉ ሰባት ወንጀል ክሶች በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 አንቀጽ 22 መሰረት ለእያንዳንዱ ተደራራቢ ወንጀል ሁለት እርከን ለሰባት ወንጀሎች አስራ አራት በእርከን ሃያ አምስት ላይ ሲጨመር እርከን 39 ላይ ያርፋል፡፡ ሆኖም በወንጀል ሕግ ቁጥር 187 (ለ) (2) እና በወንጀል ሕግ ቁጥር 66 ንዑስ አንቀጽ 1(ሐ) ቅጣቱ በሕግ ልዩ ክፍል ከተደነገገዉ በላይ መብለጥ የሌለበት በመሆኑ የእስራት ቅጣቱ

እርከን 32 የገንዘብ መቀጮ እርከን ሰባት ሥር ለመመደብ በህግ ተገድደናል፡፡ ተከሳሽ መልካም ፀባይ የነበረዉ መሆኑ ለጎጆዎች ካሳ መክፈሉና ቤተሰብ አስተዳዳሪ በመሁኑ ሶስት ማቅለያ በመያዝ በእርከን 29 ከተቀመጠዉ ቅጣት በአስር ዓመት ፅኑ እስራ እና በብር 5000(አምስት ሺ ብር) ገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ በማለት ወስኗል፡፡

7. የሥር ተከሳሽ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የቀረበ ሲሆን ችሎቱም ግራ ቀኛቸዉን  በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የሥር ፍ/ቤት የሰጠዉን የጥፋተኝነት ዉሳኔ በማጽናት ቅጣትን በተመለከተ አመልካች ያልተማረ መሀይም መሆኑ አንድ የቅጣት ማቅለያ ሆኖ ሊያዝለት ይገባል በማለት ግን የቅጣት አወሳሰን መመሪያን መሰረት አድርጎ በማስላት ተከሳሽ ከዚህ ቀደም የታሰረዉ ታስቦ በዘጠኝ ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጣ በማሻሻል ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አመልካች የቀረበዉን የሰበር አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ ይግባኝ ሰሚዉ ችሎት ሰጠዉን ዉሳኔ አጽንቷል፡፡

8. አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡ አመልካች ጥር 25 ቀን 2008 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታ የዐቃቤ ህግ ምስክሮች በድንገት የመኪናዉ ላይ በደረሰ የቴክኒክ ብልሽት አደጋዉ የደረሰ መሆኑ ገልጸዉ እያለ ጥፋተኛ መባሌ የህግ ስህተት ነዉ፡፡ አመልካች መጠየቅ አለበት ከተባለ እንኳን በሰባት አካል ማጉደል ወንጀል ጥፋተኛ መባል የለብኝም በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በ 30/04/2008ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ የመልሱም ይዘት የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ፍርድና ዉሳኔ በማስረጃ ምዘና መርህ እና በሕግ አተረጓጎም ረገድ የሚነቀፍበት ምክንያት ስለሌለ አመልካች ያቀረበዉ አቤቱታ የሕግ ድጋፍ ስለሌለዉ ዉድቅ ተደርጎ የሥር ፍርድና ዉሳኔ እንዲጸና በማለት ተከራክሯል፡፡ የአሁን አመልካች የሰበር አቤቱታዉን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

9. የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኛቸውን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም በአመልካች ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔም ሆነ የቅጣት ውሳኔ በህግ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን እንደጭብጥ በመያዝ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የአሁን አመልካች በዐ/ህግ ክስ ላይ በተመለከተው ጊዜ እና ቦታ የሰሌዳ ቁጥሩ የተጠቀሰውን ሚኒባስ የህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ እያሽከርከረ እያለ፤ መኪናዋ ለመጫን ከተፈቀደላት በላይ ትርፍ ሰው በመጫኑ አደጋው የደረሰና ከመንገድ ወጥታ በመገልበጧ በሁለት ሰዎች ላይ የሞት እና በሌሎች ሰባት ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት አደጋ እንደደረሰባቸው የዐ/ህግ ማስረጃ ያረጋገጠ ፍሬ ነገር መሆኑን የስር

ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ያመለክታል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ይህን የዐ/ህግ ምስክሮች ቃል እና የቀረበውን የሰነድ ማስረጃ በመመዘን የአሁን አመልካች ባለው የማሽከርከር ሙያ ተሳፋሪዎች በተሽከርካሪው አሳፍሯቸው ሲጓዝ ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን ደንብ በመጣስ፣ ከአቅም በላይ ሰው በማሳፈር የሙያውን ግዴታ እና የስራ ልምድ በሚጠይቀው መጠን ላሳፈራቸው የሰዎቹን ህይወት፣ ደህንነት የመጠበቅ ግዴታ በአግባቡ ባለመወጣቱ አደጋው የደረሰ መሆኑ ፍሬ ጉዳይና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርደ ፍ/ቤቶች ያረጋገጡት ፍሬ ነገር ነው፡፡ ይህን ተከትሎ ፍ/ቤቱ አመልካች የቀረበበትን ክስ እንዲከላከል በሰጠው ትዕዛዝ የመከላከያ ምስክሮች የሌለው መሆኑን በመግልጽ ያልተከላከለ መሆኑን ከስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ተረድተናል፡፡

10. ስለዚህ የስር ፍ/ቤት ፍሬ ነገርን የማጣራት እና ማስረጃን መዝኖ የመወሰን ስልጣኑን መሰረት በማድረግ የአሁን ተጠሪ ያቀረበውን ክስ በበቂ ማስረጃ፣ አመልካች ሙያዊ ግዴታውን ባለመወጣት እና በቸልተኛነት በፈጸመው ድርጊት የሁለት ሰዎችን ህይወት እንዳጠፋ እና በሰባት ሰዎች አካል ላይ ጉዳት እንዳደረሰ በወንጀል ህግ አንቀጽ 543(3) እና 559(2) ስር የጥፋተኝነት በውሳኔ መስጠቱን ከውሳኔ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም ይህ ችሎት ደግሞ ከተሰጠው ስልጣን አንጻር ሲታይ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ፍሬ ነገርን በማጣራትና ማስረጃን በመመዘን በአመልካች ላይ የሰጠው የጥፋተኛነት ውሳኔ በህጉ አግባብ የተሰጠ ነው በማለት ከሚቀበል በስተቀር በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የማይቻል በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበውን ቅሬታ አልተቀበልነውም፡፡

11. "በእኛ በኩል በዚህ ሰበር ችሎት መታየት ያለበት አመልካች ጥፋተኛ ነው የተባለባቸው ሰባት በቸልተኝነት በሰው የአካል ላይ ጉዳት የማድረስ የወንጀል ድርጊቶች በወንጀል ህጉ ከተመለከተው በአንድ የወንጀል ሀሳብና በአንድ የወንጀል ድርጊት በተለያዩ ሰዎች ላይ ከደረሰ ጉዳትና ተደራራቢ ወንጀሎች ተከሳሽ ተጠያቂ ከሚሆንባቸው ሌሎች ሁኔታዎች አንጻር እንዴት ይታያል? የሚለው ነጥብ ነው፡፡ ተደራራቢ ወንጀሎችን በተመለከተ በወንጀል ህጉ አንቀጽ 60 እና ተከታዮች ድንጋጌዎች ተመለክቶ እናገኛለን፡፡ የወንጀል ህግ አንቀጽ 60(ሐ) እንደሚያመለክተው "ማንም ሰው ተደራራቢ ወንጀሎችን አድርጓል የሚባለው በአንድ የወንጀል የማድረግ አሳብ ወይም ቸልተኛነት ያደረገው ወንጀል አንድን የህግ ድንጋጌ የሚጥስ ሆኖ ቁጥራቸው ከአንድ በላይ በሆነ ሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ አንድ ዓይነት ጉዳት ያስከተለ እንደሆነ ነው" በማለት ይደነግጋል፡፡ የዚህ ድንጋጌ የእንግሊዘኛው ቅጅ "In the case of criminal act which, though flowing from the same criminal intention or negligence and violating the same criminal

provision, causes the same harm against the rights or interests of more than one person." በማለት ይደነግጋል፡፡ በዚህ ድንጋጌ የተመለከተው የተደራራቢ ወንጀሎች መርህ ከላይ በተገለጸው መንገድ የተቀረጸ መሆኑ የህጉን ድንጋጌ ከሌሎች የህግ ድንጋጌዎች ጋር አጣጥሞ ተግባራዊ በማድረግና በመተግበር በኩል ግልጽና ከችግር የጸዳ የሚያደርገው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

12. በተለየም ከላይ የተገለጸው የድንጋጌው ይዘትና ተግባራዊ ተፈጻሚነት በወንጀል ህግ ለአንድ ጥፋት አንድ ቅጣት መርህን ከሚደነግገው የወንጀል ህግ አንቀጽ 61 ድንጋጌዎች ጋር አጣጥሞ ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር ጥያቄዎችን የሚያስነሳ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር በጭብጥነት ከተያዘው ነጥብ አንጻር አንድ ሰው በቸልተኝነት በሚፈጸመው አንድ ድርጊት፣ በአጋጣሚ ቁጥራቸው ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች ተጎጅዎች ሆነው ቢገኙ፣ ተከሳሹ መከሰሰና መቀጣት ያለበት በእያንዳንዱ ተጎጅ ላይ አንድ ራሱን የቻለ የወንጀል ድርጊት እንደፈጸመ ተቆጥሮና ጥፋተኛ ተብሎ ነው ወይስ አንድ ወንጀል እንደፈጸመ ተቆጥሮ ነው የሚለው ነጥብ የህግ ትርጉም የሚያስፈልገው፡፡ ከላይ የተነሳውን ጥያቄ ለመመለስ በተለይም በአንድ የቸልተኝንት ወንጀል ድርጊት ቁጥራቸው ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎች ተጎጅ ቢሆኑ ውጤቱ ምንድንነው የሚለውን ለመተርጎምና ለመረዳት ህግ አውጭው የወንጀል ህግ አንቀጽ 543 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ የተደራራቢ ወንጀሎችና ቅጣት መርህ ተፈጻሚ መደረጉ ሕግ አውጭው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 61 እና ንዑስ አንቀጽ 3 ከሚያራምዳቸው ሃሳቦች ጋር የሚሄድና የሕጉን አላማ የሚያሳካ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የቀረፀበትን አግባብና የድንጋጌውን አውደንባብና መሰረታዊ ዓላማ ማገናዘብ የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

13. የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543 ንዓስ አንቀፅ 3 መሰረቱ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 1 በተመለከተው መሰረት በተከሳሹ ቸልተኝነት የሰው ሕይዎት የሕልፈት የተዳረገ መሆኑ ነው፡፡ በተከሳሹ ቸልተኝነት የሰው ሕይወት ለሕልፈት የተዳረገ መሆኑ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 3 የተጠቀሰው የወንጀል ድርጊት ማቋቋሚያ አንዱ መሰረታዊ ሁኔታ እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 2 እና ንዑስ አንቀፅ 3 የማክበጃ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ አንድ አሽከርካሪ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 3 በመተላለፍ የወንጀል ተጠያቂነት አለበት የሚባለው ጥፋተኛው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎችን የገደለ እንደሆነ መሆኑን በግልፅ ተደንግጓል፡፡

14. "ጥፋተኛው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎችን የገደለ ወይም ወንጀሉን የፈፀመው ግልፅ የሆነ ደንብ ወይም መመሪያ ተላላፎ ቅጣቱ ከአምስት እስከ አስራ አምስት አመት

ፅኑ እስራት እስከ አስራ አምስት ሺህ ብር የሚደርስ መቀጮ ይሆናል" ከሚለው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 3 አቀራረፅ፣ ይዘትና አውደንባብ ለመገንዘብ እንደሚቻለው፣ አሽከርካሪ በአንድ የቸልተኝነት ተግባር ሁለት ወይም ከዛ በላይ የሆኑትን ሰዎች በሕይወት የመኖር መብት በመጣስ በቸልተኝነት በመግደሉ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 60/ሐ/ በደነግገው መሰረት እያንዳንዱ ሟች ለመገደል አንድ ራሱን የቻለ በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል እነደፈፀመ ተቆጥሮ ተደራራቢ የወንጀል ክስና ቅጣት ማይወሰንበት መሆኑና በአንፃሩ አንድ ከባድ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀል እንደፈፀመ ተቆጥሮ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 3 በመተላለፉ ጥፋተኛ ተብሎ እንደሚቀጣ ከሚለው ድንጋጌው አውደንባብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

15. በዚህ ድንጋጌ መሰረት ጥፋተኛው በእያንዳንዱ ሰው ሕይወት አንፃር የሚጠየቅ ባይሆንም ጥፋተኛው ሁለት እና ከዛ በላይ ሰዎችን መግደሉ ሊወሰንበት የሚገባውን ቅጣት ከፍ እንደሚያደርግበት የማያመለክት ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ድንጋጌ አግባብ በቸልተኝነት ሰውን መገደል ምንም እንኳን የሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ላይ የሞት አደጋ ያስከተለ ቢሆንም ቅጣቱን ከፍ ከሚየደርግበት በስተቀር፣ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 60/ሐ/ በሚደነግገው መሰረት እያንዳንዱ ሟች ለመገደል አንድ ራሱን የቻለ በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል እንደፈፀመ ተቆጥሮ በተደራራቢ ወንጀሎች ጥፌተኛ የሚያሰኘውና የሚያስቀጣው ሳይሆን በድንጋጌው በተመለከተው ልዩ ማክበጃ ሁኔታ ባለበት አንድ ከባድ በቸልተኝነት ሰው መግደል ወንጀል እንደፈፀመ ተቆጥሮ ጥፋተኛ የሚባልና ቅጣት የሚወሰንበት መሆኑን ሕግ አውጭው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 3 በመደንገግ በግልፅ አስቀምጧል፡፡

16. እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ አሽከርካሪው በፈፀመው በአንድ ቸልተኝነት ተግባር በዚህ መዝገብ አከራካሪ ጭብጥ በሆነው መንገድ ሰባት ሰዎች የአካል ጉዳት ቢደርስባቸው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 60/ሐ/ ስር በተመለከተው መሰረት ሰባት በቸልተኝነት በሰው አካል ላይ ጉዳት የማድረስ ተደራራቢ ወንጀሎች እንደፈፀመ ተቆጥሮ ጥፋተኛ ሊባልና ሊቀጣ ይገባዋል ወይስ አንድ ወንጀል እንደፈፀመ ተቆጠሮ ጥፋተኛ ሊባልና ሊቀጣ ይገባዋል? የሚለው ነው፡፡ ከላይ እንደተመለከተው በተሽከርካሪ በቸልተኝነት ቁጥራቸው ሁለት ወይም ከዚያ በለይ ሆኑ ሰዎችን የገደለ ጥፋተኛ ሕግ አውጭው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 543 ንዑስ አንቀፅ 3 ቅጣቱን ከፍ የሚያደርግበት በስተቀር፣ ተደራራቢ በቸልተኝነት የሰው መግደል ወንጀሎችን ፈፅማል ተብሎ ተደራራቢ ወንጀል ክሶች እንደማይቀርቡበትና በተደራራቢ ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ እንደማይቀጣ በግልፅ አስቀምጧል፡፡

17. ይህ ከሆነ አሽከርካሪው በአንድ ቸልተኝነት ተግባር በተለያዩ ሰዎች አካል ላይ ጉዳት ሲያደርስ በቸልተኝነት ተደራራቢ አካል ማጉደል ወንጀል እንደፈፀመ ተቆጥሮ ተደራራቢ ወንጀል ክስ ሊቀርብበትና በተደራራቢ ወንጀል በመፈፀም ጥፋተኛ ተብሎ ሊቀጣ ይገባዋል የሚለው የተጠሪ ክርክርና በታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ሰባት በቸልተኝነት በሰው አካል ላይ ጉዳት የማድረስ ወንጀል የፈፀመ ነው በማለት የሰጡት የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ለአንድ ጥፋት አንድ ቅጣት መርህን ከሚደነግገው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 61 መሰረታዊ መርህ ጋር የማጣረስና የሕጉን ድንጋጌዎች ከፍትሐዊ፣ ወጥነት እና ተገማች የሆነ የሕግ ትርጉም ከመስጠት አንፃር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም የአሁኑ አመልካች ምንም እንኳን በክሱ እንደተመለከተው የሰውን አካል ደህንነት ለመጠበቅ ያለበት ግዴታ ወደ ጎን በመተው ከመኪናዋ አቅም በላይ ተርፍ ሰዎች በመጫን መኪናዋ መገልበጥ አደጋ እንድደርባት በማድረግ በሰባት ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ቢሆንም፣ በቸልተኝነት በፈፀመው አንድ ተግባር ሰባት ሰዎች አካል ደህንነት መብት በመጣሱ ብቻ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 60/ሐ/ ተመለከተው የተደራራቢ የወንጀሎችና ቅጣት መርህ ተፈጻሚ መደረጉን ህግ አዉጭዉ የወንጀል ህግ አንቀጽ 61 እና የወንጀል ህግ አንቀጽ 543 ንዑስ አንቀጽ 3 የሚያራምዳቸዉን አሳቦች ጋር የሚሄድና የህጉን አላማ የሚያሳካ ሆኖ አላገኘነዉም፡፡

18. የአሁን አመልካች ምንም እንኳን በሰባት ሰዎች ላይ በተሽከርካሪው የአካል ጉዳት ያደረሰ ቢሆንም እንደ አንድ የወንጀል ድርጊት እንደፈጸመ እንጅ በአንድ ቸልተኝነት ተግባር ምክንያት በደረሰው መኪና መገልበጥ በአደጋ በአጋጣሚ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ቁጥር ሰባት በመሆናቸው ሰባት ተደራራቢ በቸልተኝነት አካል ጉዳት የማድረስ ወንጀሎች እደተፈጸሙ ተደርጎ የወንጀል ክስ ሊቀርብበትም ሆነ ጥፋተኛ ተብሎ ቅጣት ሊወሰንበት አይገባም፡፡ በሌላ በኩል አመልካች በሰባት ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት በማድረሱ በአንድ ሰው ላይ አካል ማጉደል ካደረሰው አሽከርካሪ ጋር ወንጀሉ ክብደት በእኩል አይን የሚያየው የወንጀሉን ደረጃ በእኩል የሚሳየው አይሆንም፡፡ ከዚህ አንጻር አሁን ስራ ላይ ያለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ በተከሳሹ የቸልተኝነት ተግባር የአካል ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች ቁጥር መሰረት በማድረግ ወንጀሉን ደረጃ እና እርከን የሚደነግግ አለመሆኑ በመመሪያው መሰረት ቅጣት በመወሰን ሂደት በግልጽ የሚታይ ክፍተኛ ያለበት በመሆኑ መመሪያው ሲሻሻል በተከሳሹ የቸልተኝነት ተግባር የአካል ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች ቁጥር መሰረት በማድረግ ወንጀሉን ደረጃ እና እርከን ከፍ ሊያደርግ የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

19. ይህ ማለት በተሽከርካሪ በቸልተኝነት ድርጊት በአንድ ሰው አካል ላይ ጉዳት ያደረሰ አሽከርካሪ እና በሁለት እና ከዛ በላይ በሆኑ ሰዎች **የአካል** ላይ ጉዳት ያደረሰ አሽከርካሪ እኩል ሊቀጡ ይገባል ማለት አይቻልም፡፡ ስለሆነም የአሁን አመልካች በሚያሽከረክረው ተሽከርካሪ በቸልተኛነት በሶስቱ ሰዎች ላይ ላደረሰባቸው የአካል ጉዳት እንደ አንድ የወንጀል ድርጊት ተወስዶ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 559/2/ ስር ጥፋተኛነት ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል ብለናል፡፡ በዚህ አግባብ የቅጣት ስሌቱ ሲታይ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው የቅጣት ውሳኔ መሰረት በመደረግ አመልካች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 543/3/ ጥፋተኛ የተባለ በመሆኑ በዚህ ድንጋጌ ስር በደረጃ 1 እርከን 25 ስር ስምንት አመት መነሻ ቅጣት ተወስዷል፡፡

20. በቸልተኛነት በሰባት ሰዎች አካል ላይ ጉዳት ማድረስን በተመለከተ እንደ አንድ የወንጀል ድርጊት በመውሰድ በወንጀል ሕግ አንቀጽ 559/2/ ስር ጥፋተኝነት ውሳኔ የተሰጠ በመሆኑ አመልካች በሰባት ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት ያደረሰ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት ይህ ድንጋጌ ደረጃ የወጣለት ሲሆን ከደረጃ 1 እስከ ደረጃ 7 ድረስ ተደንግጎ ይገኛል፡፡ በዚህ መሰረት ደረጃ 1 ሲታይ ቀላል የአካል ወይም የጤና ጉዳት አድራሹ የሌላ ሰውን አካል ወይም ጤንነት የመጠበቅ ሙያ ወይም ሌላ ግዴታ ያለበት እንደ ህክምና ባለሙያ ወይም አሽከርካሪ ያለ ሰው እንደሆነመ የእስራት ቅጣት መነሻ እርከን 7 የገንዘብ ቅጣት እርከን 1 ስር እንደሚያስቀጣ ያመለክታል፡፡ ነገር ግን ከደረጃ 2 እስከ ደረጃ 7 ባሉት ስር በሁለት ወይም ከዛ በላይ በሆኑ ሰዎች ቀላል የአካል ጉዳት ያደረሰባቸው እንደሆነ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ በተዘረዘሩት ደረጃዎች የሚሸፈን ሆኖ አይገኝም፡፡ ይህ በሆነ ጊዜ ደግሞ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 አንቀጽ 27/1/ መሰረት ከዚህ ቅጣት መመሪያ ወጥቶ ተገቢ ቅጣት ሊወሰን ይገባል፡፡

21. በዚህ አግባብ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት የወ/ሕ/ቁ. 559/2/ ቅጣቱ ከስድስት ወር የማያንስ ቀላል እስራትና አንድ ሺህ ብር የማያንስ መቀጮ እንደሚያስቀጣ ይደነግጋል፡፡ በዚህ መሰረት አመልካች እንደ አንድ አሽከርካሪ ያለበትን ግዴታ መወጣት ሲገባው የሆነው ይሁን በማለት የሚያሽከረክረውን ተሽከርካሪውን ተሽከርካሪ ጥሎ በመውረድ በሰባት ሰዎች ላይ ቀላል የአካል ጉዳት የደረሰባቸው በመሆኑ በዚህ ድንጋጌ ስር አመልካች ሊቀጣ ይገባል በማለት ችሎት ያመነበት ሁለት /2/ አመት ቀላል እስራት ሲሆን፣ ይህ ደግሞ ወደ ጽኑ እስራት ሲቀየር 1 ዓመት /አንድ አመት/ ጽኑ እስራት ይሆናል፡፡ በመሆኑም ከላይ የወ/ሕ/ቁ. 543 ንዑስ አንቀጽ 3 ስር ከተያዘው መነሻ ቅጣት ጋር ተደምሮ 8 ዓመት ጽኑ እስራት ጋር ተደምሮ ዘጠኝ ዓመት እንደቅጣት መነሻ የሚወሰድ ሲሆን ይህ ደግሞ እርከን

26 ስር የሚወድቅ ይሆናል፡፡ በስር ፍ/ቤት ሶስት የቅጣት ማቅለያ ይግባኝ ሰሚው ችሎት አንድ ማቅለያ በድምሩ አራት ማቅለያዎች ይዘውለታል፡፡

22. ይህም ችሎት እነዚህን ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን በመውሰድ ቅጣቱ ከእርከን 26 ወደ እርከን 22 ዝቅ እንደሚል ተገንዝቧል፡፡ እርከን 22 ስር ከአምስት ዓመት ከስድስት ወር እስከ ስድስት አመት ከሰባት ወር የሚያስቀጣ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡ በዚህ መሰረት ይህ ችሎት አመልካችን ያስተምራል፣ ሌሎችን ያስጠነቅቃል በማለት ያመነበት ቅጣት አመልካች በዚህ ጉዳይ ከታሰረበት ጊዜ ጀምሮ በሚታሰብ በስድስት ዓመት ከሥድስት ወር ጽኑ እስራት በብር 5000(አምስት ሺ ብር ሊቀጣ) ይገባል ብለናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.0235878 የካቲት 16 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳ እና ይህንን ዉሳ በማሻሻል የአማራ ክል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችት በመ.ቁ 02-15930 በ 10/09/2007ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.50596 ህዳ 8 ቀን 2008ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በከፊል መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በወ.መ.ሥ.ሥ.ሕ.ቁ.195 ንዑስ አንቀጽ 2(ለ)2 መሰረት ተሻሽሏል፡፡
2. የአሁን አመልካች በዚህ ጉዳይ እጁ ከተያዘበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ በበስድስት ዓመት ከስድስት ወር ጽኑ እስራትና በብር 5000(አምስ ሺብር) መቀጮ እንዲቀጣ ተወስኗል፡፡ የክልሉ ማረሚያ ቤት በዚህ ዉሳ መሰረት እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡ ይጻፍ፡፡
3. የዚህ ዉሳ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች እና ለአመልካች ይድረስ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ 131705

ሚያዚያ 16 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሀይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካቾች፡- 1ኛ.አብርሃም ሰለሞን
2ኛ. የሺመቤት ጓዴ
3ኛ. ዳንኤል ሰለሞን
ከማረሚያ ቤት አልቀረቡም

ተጠሪ፡- የፌዴራል አ/ህግ - ዐ/ህግ መሰረት ሙላቱ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታ የቀረበው አመልካቾች በተከሰሱበት ከባድ ስርቆት ወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ በተሰጠ የቅጣት ውሳኔ ላይ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በሚል እንዲታረም አቤቱታ ስላቀረበነው፡፡

አመልካቾች የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ሀ/ እና 669/3/ለ ተላልፈው ከግል ተበዳይ ቤት ግምቱ 843,000 ብር የሚያወጣ ልዩ ልዩ ንብረት ሚያዚያ 29 ቀን 2006 ዓ/ም በመውሰዳቸው ከባድ የስርቆት ወንጀል ፈጽሟል በሚል ዐ/ህግ ክስ መስርቶባቸው ፍርድ ቤቱም የዐ/ህግ እና የተከሳሾችን መከራከሪያ ከመረመረና ማስረጃ ከሰማ በኃላ በተከሰሱበት አንቀጽ የጥፋተኝነት ውሳኔ እና የቅጣት ውሳኔ አስተላልፎባቸዋል፡፡

አመልካቾች ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ ይግባኝ ቅሬታቸውን ባለመቀበል የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አጽንቷል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል ሲሉ 1ኛ እና 2ኛ አመልካቾች በሰበር መ/ቁ/ 131705 ሐምሌወር 2008 ዓ/ም የተፃፈ አቤቱታ ያቀረቡ ሲሆን 3ኛ አመልካች በበኩሉ በሰበር መ/ቁ/ 131706 ሐምሌ 30 ቀን 2008 ዓ/ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡

መዝገቦች ከስር በአንድ ክስ የቀረበባቸው መሆኑ ታይቶ ተጣምሮ እንዲመረመር ተደርጓል፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካቾች ጥፋተኛ ከተባሉበት አንቀጽ 669/3/ለ/ አንፃር ወንጀሉ በቡድን የተፈጸመ ነው ተብሎ የቅጣት ማክበጃ መወሰዱ የወንጀል ህጉን 84/1/መ/ እና 84/2/ አንፃር አግባብነቱን ለመመርመር ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ ተደርጓል፡፡ ዐ/ህግ በሰጠው መልስ በቡድን ወንጀል መስራታቸው መረጋገጡን ጠቅሶ ነገር ግን የአንቀጽ ማቋቋሚያ ከተደረገ በኃላ የቅጣት ማክበጃ ተደርጎ በተጨማሪነት ሊወሰድ እንደማይገባ አስተያየት ሰጥቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ ባጭሩ የተገለጸ ሲሆን ይህ ችሎት የቅጣት አወሳሰን በተመለከተ የቀረበውን የክርክር ነጥብ ከህጉ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡ ከመዝገቡ መገንዘብ እንደተቻለው አመልካቾች በግብረአበርነት የወንጀል ህግ አንቀጽ 32/1/ሀ እና 669/3/ለ/ ተላልፈው ከባድ የስርቆት ወንጀል የፈጸሙ መሆናቸው ማስረጃ የማጣራት ስልጣን በተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ለዚህ ድንጋጌ ማቋቋሚያ ናቸው ብሎ ዐ/ህግ በክሱ የጠቀሳቸው ፍሬ ነገሮች ሲታዩ የወንጀሉ አፈፃጸም በረቀቀ ዘዴ አደገኛነታቸውን የሚያሳይ መሆኑ፣ 2ኛ አመልካች የቤት ሰራተኛ ሆኖ እንድትገባ ማድረጋቸው እና ይህንን የቅጥር ግንኙነት አጋጣሚ በመጠቀም እንዲሁም በስምምነት በቡድን የተፈጸመ የወንጀል ድርጊት መሆኑ ተመልክቷል፡፡

እንግዲህ ቅጣት አወሳሰን አስመልክቶ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ባወጣው የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 የሚሸፍን መሆኑ አከራካሪ ባለመሆኑ በዚህ መመሪያ በአንቀጽ በተቀመጠው ደረጃ መሰረት ሲታይ ክስ የቀረበበት የገንዘብ መጠን ከ100,000 /መቶ ሺህ ብር/ በላይ መሆኑና ሶስት የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች መሟላታቸው ጋር ሲዛመድ እርከን 30 ደረጃ 9 ላይ እንደሚመደብ መገንዘብ ይቻላል፡፡ የስር ፍርድ ቤት ግን የገንዘብ መጠኑን ታሳቢ አድርጎ ቅጣት ማክበጃ ሁለት እንደተረጋገጠ ግምት አስገብቶ መነሻ ቅጣት ደረጃ 8 እርከን 26 መያዙን መገንዘብ ተችሏል፡፡

በመሆኑም በቀረበው ክስ ከተረጋገጠው ሶስት በአንቀጽ ማቋቋምያ ማክበጃ ምክንያቶች ውስጥ የስር ፍርድ ቤት ሁለቱን ብቻ መውሰዱ ሲታይ በመሰረታዊነት ተከሳሾች /አመልካቾችን/ የጠቀመ ነው ከሚባል በስተቀር የጎዳቸው ነው ሊባል አይችልም፡፡ በእርግጥ የአንቀጽ ማቋቋሚያ የሆነ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ዳግም የቅጣት ማክበጃ ተደርጎ ሊወሰድ እንደማይገባ በወንጀል ህግ አንቀጽ 84/2/ በግልጽ የተመለከተ ስለሆነ ይህ በጥብቅ ሊከበር እንደሚገባ የምንስማማበት

መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ በውጤቱ ሲታይ አመልካቾች ተጠቃሚ እንጂ ተጎጂ ባለመሆናቸው ከአመልካቾች ጥያቄ አንፃር መሰረታዊ ለውጥ የሚያመጣ ሆኖ አላገኘነም፡፡ በሌላ በኩል የቀረበው ቅሬታ የቤተሰብ አስተዳዳሪነት፣ የቀደመ የወንጀል ሪከርድ ሳይኖር የወንጀል ሪከርድ አለመኖር እንደቅጣት ማቅለያ አለመያዙ ስህተት ነው በሚል የቀረበውን ከህጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

በዚህ ረገድ የስር መዝገብ መርምረን እንደተገነዘብነው 1ኛ እና 3ኛ አመልካቾች በተደጋጋሚ በወንጀል ተጠርጥረው የጣት አሻራ የሰጡ ስለሆነ የዘውትር ጸባይ መልካም ነው ተብሎ የቅጣት ማቅሊያ በወ/ህግ 82/1/ሀ/ ሳይያዝላቸው ታልፏል፡፡ አመልካቾች ይህንን በጥብቅ ተቃውሞ ተከራክረዋል፡፡ በመሰረቱ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህግ መንግስት አንቀጽ 20/3/ እንደተደነገገው በወንጀል ጥፋት እስካልተፈረደ ድረስ እንደጥፋተኛ ያለመቆጠር መብት የተጠበቀነው፡፡ ስለሆነም አመልካቾች በወንጀል ተጠርጥሮ የጣት አሻራ ሰጥቷል በመባላቸው ብቻ እንደ ጥፋተኛ ተቆጥሮ የወንጀል ጥፋት ሪከርድ እንዳለባቸው ተደርጎ በስር ፍርድ ቤቶች ግምት መውሰዱ በህገመንግስቱ የተከሰሱ ሰዎች መብት አስመልክቶ ከተደነገገው መሰረት ሀሳብ ጋር የሚጣረስስ ለሆነ በዚህ ረገድ የስር ፍርድ ቤቶች አቋም መሰረታዊ የህግ መንግስት መርህ የሚጣረስ ሆኖ አግኝተናል፡፡ በዚሁአግባብ 1ኛ እና 3ኛ አመልካቾች የመልካም ባህርይ የቅጣት ማቅሊያ ተደርጎ ሊያዝ አይገባም ሲሉ የስር ፍርድ ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ ሲታረም የሚገባ ሆኖ አግኝተናል፡፡ ከዚህ ሌላ በአመልካቾች በኩል የቀረበው የቅጣት ማቅሊያ የቤተሰብ አስተዳዳሪነት ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ረገድ አመልካቾች በስር ፍርድ ቤት በተሰጣቸው ቀጠሮ ማስረጃ ማቅረብ እንዳልቻሉ ፍርድ ቤቱ በመዝገቡ መመዝገቡን ማየት ችለናል፡፡ ይህ ፍሬ ነገር ደግሞ በማስረጃ የሚረጋገጥ ጉዳይ ከመሆኑ አኳያ ማስረጃ የሚረጋገጥ ጉዳይ የመመርመር እና ፍሬ ነገር የማጣራት ስልጣን በተሰጠው ፍርድ ቤት ዘንድ ማስረጃ አቅርቧል ያላረጋገጡትን ፍሬ ነገር መሰረት አድርገው አመልካቾች ያቀረቡት አቤቱታ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80 /3/ሀ/ አንፃር የዚህ ሰበር ችሎት ስልጣን ወሰን ወጪ ስለሆነ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ሲጠቃለል በቅጣት አወሳሰን ረገድ አመልካቾች ካቀረቡት የቅሬታ ነጥቦች ተቀባይነት ያገኘው 1ኛ እና 3ኛ አመልካቾች የቀደመ የወንጀል ሪከርድ ስለመኖሩ በፍርድ የተረጋገጠ ባለመቅረቡ በወ/ህግ አንቀጽ 82/1/ሀ መሰረት አንድ የቅጣት ማቅሊያ ምክንያት እንዲያዝላቸው ብለናል፡፡

በዚሁመሰረት 1ኛ አመልካች በስር ፍርድ ቤት የቅጣት ውሳኔ ከተሰጠበት እርከን 27 3ኛ አመልካችም በተመሳሳይ ከእርከን 27 ላይ አንድማቅሊያ ሲያዝላቸው በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 አንቀጽ 23/4/መሰረት አንድ እርከን ሲቀንስ ቅጣቱ እርከን 26 ላይ ያርፋል፡፡ እርከን 26 ላይ የተመለከተው የእስራት ቅጣት ፍቅደ ስልጣን ከ7 አመት ከ8 ወርእስከ 9 አመት

ከ2 ወር ጽኑ እስራት መሆኑ ከአባሪ አንድ ማየት ይቻላል፡፡ ስለሆነም 1ኛእና 3ኛ አመልካቾች በዚህ ጉዳይ ከዚህ ቀደም የታሰሩት ታሳቢ ተደርጎ በስምንት /8/ አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ተብሎ በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ቁ/ 195/2/ለ/2/ መሰረት ቅጣቱ ተሻሽሎ ተወስኗል፡፡

በ2ኛ አመልካች በኩል የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመ/ደረጃ ፍርድ ቤት በወ/መ/ቁጥር 120047 በ17/09/07 ዓ/ም የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ ጸንቷል፡፡ ቅጣት አስመልክቶ ግን የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይህንኑ ማሻሻል ሲገባው ማለፉ ስህተት መሆኑ ታይቶ 1ኛ እና 3ኛ አመልካች ላይ የተላለፈው የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ህ/ስ/ስ/ህግ/ቁ/195/2/ለ/2/ መሰረት በማሻሻል በዚህ ጉዳይ እጃቸው የተያዘበት ጊዜ ጀምሮ የታሰሩት ታሳቢ ተደርጎ በስምንት /8/ አመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ተወስኗል፡፡
2. 2ኛ አመልካች ላይ በስር ፍርድ ቤት የተላለፈው የቅጣት ውሳኔ ጸንቷል፡፡
3. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመ/ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ በመ/ቁ/000962 30/09/08 ያጸናው በዚህ ችሎት በቅጣት ረገድ ብቻ የተሻሻለለ መሆኑ እንዲታወቅ ይፃፍ፡፡
4. 1ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ላይ በስር ፍርድ ቤት የተወሰነው ዘጠኝ አመት ከስድስት ወር /9፡6 ወር /ጽኑ እስራት ወደ ስምንት /8/ዓመት ጽኑ እስራት የተሻሻለ መሆኑን አውቆ ማረሚያ ቤቱ በዚሁ መሰረት እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ትዕዛዝ

ይህ መዝገብ ከሰበር መ/ቁ/ 131706 ጋር ተጣምሮ የተወሰነ ስለሆነ የዚህ መዝገብ ውሳኔ ግልባጭ ከመዘገበ ቁጥር 131706 ጋር ይያያዙ ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ተ

የሰ/መ/ቁ.126017

ሚያዚያ 26 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሃመድ

ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ

ቀነአ ቂጣታ

ፀሃይ መንክር

አመልካች - የአርሲ ነገሌ ከተማ ፖሊስ ጽ/ቤት ተወካይ ገለቶ አኖታ ቀረቡ

ተጠሪ - አቶ ተስፋአለም ገ/ሚካኤል- ቀርቧል

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች የተሰጠው ውሣኔና ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረበውን የሰበር አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ሲሆንጉዳዩ የተጀመረው በምዕራን አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡

የክሱ ይዘት የሰሌዳ ቁጥሩ 03 - 0188468 አ/አ የሆነ ኤፍ ኤስ አር አይሱዚ መኪናዬን በ28/03/2007 ዓ.ም የይለፍና የማጓጓዝ ፈቃድ ሳይዝ ስኳር ሲያጓጉዝ ይዣለሁ በሚል ሰበብ የፌደራል የንግድ ውድድር እና የሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁር 813/2006 አንቀፅ 27(1) የተደነገገውን በመተላለፍ ስልጣን ሳይኖረው በቁጥጥር ስር በማድረግ ይዞት ስለሚገኝ እንዲለቅልኝ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን መኪና የያዝኩት ምክንያት ከሳሽ ህጋዊ የይለፍ እና የማጓጓዣ ፈቃድ ሳይኖረው በራሱ መኪና 100 (መቶ) ኩንታል ስኳር በመጫን እራሱ እያሽከረከረ እያለ በአርሲ ነገሌ ከተማ ውስጥ እጅ ከፍንጅ በመያዙ በተደረገው የፖሊስ ምርመራ የጫነው ስኳርም ህገወጥ ሆኖ ስለተገኘ ሹፌሩም እራሱ የመኪናው ባለቤት በመሆኑ ስኳሩና መኪናው የወንጀል ኤግዚቢት ሆኖ የምርመራ መዝገቡ ለፍትህ ጽ/ቤት ከተላለፈ በኋላ በአቃቤ ህግ ክስ አቅራቢነት ተጠሪ በሸማቾች ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 813/2006 አንቀፅ 43(5) የተደነገገውን በመተላለፍ ህገ ወጥ ስኳር ያጓጓዘ በመሆኑ የወንጀል ክስ በ07/08/2007 ዓ.ም በፍርድ ቤት መዝገብ ቁጥር 27876/07ቀርቦበትመኪናው እንደ ዓቃቤ ህግ ማስረጃ ኤግዚቪት ሆኖ እያለ ይህ የወንጀል ተከሳሽ በዋስትና ምክንያት ወጥቶ ስለታጣ መዝገቡ ለጊዜው ተዘግቷል፡፡ ስለሆነም ከሳሽ በወንጀል ተከሶ መኪናውም እንደ ኤግዚቪት ማስረጃ ሆኖ ውሳኔ ለማግኘት

የሚጠብቅ እንጂ ከሳሽ እንደሚለው በህገወጥ መንገድ ያለስልጣኔ መኪናውን የያዝኩ ስላልሆነ ክሱ ውድቅ ይሁንልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

ክርክሩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተከሳሹ ጽ/ቤት የተመረመረው የወንጀልመዝገብና በፍርድ ቤት የሚገኘው መዝገብ እንዲቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶ በማስቀረብ መርምሮ ከሳሽ በተጠረጠረበት ወንጀል በተጣራበት የምርመራ መዝገብ መኪናው እግዚቢት ሆኖ ተይዞ የሚገኝ መሆኑን እና የፖሊስ መዝገቡ ለፍትህ ጽ/ቤት ተልኮ ክስ ተከፍቶበት በወረዳው ፍርድ ቤት የወንጀል ተከሳሹ (የፍትሃብሔር ክስ የመሰረተው) ባለመቅረቡ የወንጀሉ መዝገብ ለጊዜው መዘጋቱን ማረጋገጡን፤ የፖሊስ ተግባር ወንጀል መከላከልና ወንጀል ከተፈፀመ ደግሞ ጉዳዩን አጣርቶ ለሚመለከተው ስልጣን ላለው የህግ አካል በማቅረብ ፍትሃዊ ውሳኔ ማስጠት መሆኑን፤ በተያዘው ጉዳይም ተከሳሽ ጽ/ቤት በከሳሽ ላይ መዝገቡን አጣርቶ ይመለከተዋል ለሚለው አካል ጉዳዩን ማቅረቡን፤ ይህ ጉዳይ የቀረበለት ፍትህ ጽ/ቤትም መኪናውን እና የተያዘውን ስኳር እንደ ማስረጃና ኤግዚቢት በማድረግ ክሱን ዓቃቤ ህግ በከሳሽ ላይ መስርቶ ለፍርድ ቤት አቅርቦ ከሳሽ ባለመገኘቱ ምክንያት የመጨረሻ ውሳኔ ሳያገኝ መዝገቡ ለጊዜው መዘጋቱን ማረጋገጡን፤ ስለሆነም ከሳሽ ስለተያዘው መኪና በወንጀሉ መዝገብ ላይ መከራከር የሚችል እና መፍትሄ ሊያገኝበት የሚችል እንጂ ይህ የወንጀል ጉዳይ ውሳኔ ሳያገኝ እግዚቢት ሆኖ እንደማስረጃ ተይዞ ስላለው መኪና ከወንጀሉ ውሳኔ በፊት በፍትሃብሄር መመልከቱ የህግ ድጋፍ ያለው ሆኖ እንዳላገኘው በመግለፅ ተከሳሽ መኪናውን በህገወጥነት የያዘው ስላልሆነና መኪናውን የተመለከተ ዝርዝር ክርክርም በወንጀሉ መዝገብ መፍትሄ የሚያገኝ ስለሆነ በፍትሃብሄር መልክ የቀረበው ክስ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪ ይህን ውሳኔ በመቃወም ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱ መኪናው ያለመፍትሄ ተይዞ የመቀመጡን ተገቢነት ለማጣራት በሚል የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የወንጀል ክሱ የቀረበለት ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 813/2006 መሰረት የቀረበለትን ጉዳይ ለማየት ስልጣን የሌለው በመሆኑ የተጠሪ መኪና ጉዳይ ስልጣን ባለው አካል ታይቶ ውሳኔ ማግኘት ሲገባው ተይዞ መቆየቱ ህጋዊ ስላልሆነ በከፍተኛው ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አለበት በማለት ውሳኔውን ሽሮ መኪናው ለተጠሪ እንዲለቀቅ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ላይ ቅሬታውን ለክልሉ ሰበር ችሎት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው በዚህ ነው፡፡ አመልካች በ28/07/2008 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻተፈፀመ የሚለውን የህግ ስህተት በመዘርዘር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች ለክርክሩ መነሻ የሆነው መኪና ለተጠሪ እንዲመለስ የሰጡት ውሳኔ ተሽሮ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲፀና ጠይቋል፡፡ተጠሪመልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ በ22/09/2008 ዓ.ምበተፃፈ መልስ ውሳኔው ስህተት የለበትም ተብሎ እንዲፀና ተከራክረዋል፡፡

ከፍ ሲል ባጭሩ የገለፅነው የክርክሩንአመጣጥ ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ በበኩላችን የወንጀል ክሱን ለማየት ሥልጣኑ በሌለው ፍርድ ቤት ክሱ መቅረቡን ምክንያት በማድረግ ከወንጀሉ ክስ ጋር በተያያዘ አግዚቪት ነው የተባለ ንብረት እንዲመለስ የፍትሃብሄር ክስ መቅረቡ እና ንብረቱ እንዲመለስ በፍትሃብሄር ክርክሩ ውሳኔ መሰጠቱ በአግባቡ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች ወንጀል ተፈፅሟል በሚል በተጠሪ ላይ የወንጀል ምርመራ አድርጎ በህገወጥ መንገድ ሲጓጓዝ ነበር ያለውን 100 (መቶ) ኩንታል ስኳር እና የተጓጓዘበትን ተሽከርካሪ የወንጀል ኤግዚቪት አድርጎ በመመዝገብ የምርመራ መዝገቡን ለፍትህ ጽ/ቤት አስተላልፎ በአቃቤ ህግ በኩል በተጠሪ ላይ በወረዳው ፍርድ ቤት የወንጀል ክስ መቅረቡን ከክርክሩ ተገንዝበናል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ቅሬታ የቀረበበትን ውሳኔ ያሳለፈው የወንጀል ክሱ ጉዳዩን ለማየት ስልጣን ለሌለው ፍርድ ቤት ቀርቧል፤ የተጠሪ መኪና ስልጣን ባለው አካል ታይቶ ውሳኔ ማግኘት ሲገባው ተይዞ መቆየቱ ህጋዊ አይደለም በማለት ነው፡፡ የወንጀል ክሱ ጉዳዩን ለማየት በህግ ስልጣን በተሰጠው ዳኝነት ሰጭ አካል መታየት አለበት መባሉ እንዲሁም የወንጀል ክሱ በአፋጣኝ ታይቶ ውሳኔ ሊያገኝ ይገባል መባሉ ህጉን የተከተለ በመሆኑ በዚህ ረገድ የተሰጠው ምክንያት የሚነቀፍ አይደለም፡፡ ነገር ግን ክርክሩ የሚመራው በህግ የተዘረጋውን ስርዓት ተከትሎ በመሆኑ በህግ ከተዘረጋው ስርዓት ውጭ የሚቀርብ ክርክር እና የሚሰጥ ውሳኔ በህጉ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

የወንጀል ጉዳይን ተቀብሎ ለመወሰን ስልጣን ለሌለው ፍርድ ቤት ጉዳዩ ቢቀርብ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹን ሳይጠራ ስልጣን የለኝም በማለት መመለስ የሚጠበቅበት ሲሆን ይህ ታልፎ ተከሳሽ እንዲቀርብ ከተደረገምበወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 130 ሥር እንደተመለከተው ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ስልጣን እንደሌለው በሚቀርብ መቃወሚያ መነሻነት የሥልጣን ክርክሩ እልባት እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡ በሌላም በኩል በአግዚቢትነት የተመለከተ ከወንጀል ክሱ ጋር የተያያዘ ንብረት በመንግስት ሊወረስ የሚገባ ስለመሆኑ ወይም ለባለንብረቱ ሊመለስ የሚገባ ስለመሆኑ ውሳኔ የሚሰጠው የወንጀል ክሱን ተፈጥሮ እና ለጉዳዩ ተገቢነት ያላቸውን የወንጀል ህጉን እና የወንጀል ሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎችን መሰረት በማድረግ የወንጀል ክሱን በሚመለከተው አካል ነው፡፡ ከዚህ ውጭ የወንጀል ክሱን ለማየት ስልጣን ለሌለው ፍርድ ቤት ክስ ቀርቧል በሚል ከወንጀል ክሱ ጋር በተያያዘ በወንጀል ችሎቱ ዳኝነት ታይቶ ውሳኔ ሊያርፍበት የሚገባ ንብረት በፍትሃብሄር ክስ ለማስመለስ የክስ ምክንያት ማድረግ የሚያስችል የህግ አግባብ የለም፡፡ከዚህም በተጨማሪ በወንጀል የሚደረገው ክርክርና በፍትሃብሄር በሚደረገው ክርክር፣ የሚያዘው ጭብጥና የሚቀርቡ ማስረጃዎች እንደዚሁም የማስረጃ አመዛዘን ሥርዓቱ ሁሉ የተለያየ ነው፡፡

ስለሆነም የክልሉጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ችሎቶች ከወንጀል ክስ ጋር በተያያዘ በወንጀል ክርክሩ ውሳኔ ሊያገኝ የሚገባ በኤግዚቢትበት ተመዝግቦ ለፍርድ የቀረበ ንብረት

እንዲመለስ ተጠሪ ያቀረቡት የፍትሐብሄር ክስ ተቀባይነት ሊያገኝ ይገባል በማለት የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ በመሻር ንብረቱ እንዲመለስ ያሳለፉት ውሳኔ የወንጀልና የፍትሃብሄር ክርክሩ የሚመራበትን የሕግ ሥርዓት የሚጥስ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነምተከታዩንወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 237427 በ19/06/2008 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔ እንዲሁም የክልሉጠቅላይፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 241263 በ14/07/2008 ዓ.ም ያሳለፈው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የምዕራብ አርሲ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 23948 በ03/05/2008 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡
3. በወንጀል ጉዳይ በኤግዚቪትነት የተያዘ ንብረት በፍርድ ውሳኔ የሚያገኘው በወንጀሉ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ሲሰጥ ለባለንብረቱ ይመለስ ወይም ለመንግስት ገቢ ይሁን ተብሎ ሲወሰን ወይም ተገቢውን የህግ ስርዓት ተከትሎ ሥልጣን ባለው አካል ትዕዛዝ ሲተላለፍ እንጂ በወንጀል ክስ ውሳኔ እየተጠባበቀ ባለው መዝገብ ላይ የተያዘውን እግዚቢት የፍትሐብሄር ክስ እንዲቀርብ ተደርጎ በዚሁ ክስ መነሻነት ንብረቱ ይለቀቅ በማለት ውሳኔ የሚሰጥበት የህግ አግባብ የለም ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውንይቻሉ፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

መ/ተ

የሰ/መ/ቁ.131088

ሚያዝያ 30 ቀን 2009 ዓ.ም

**ዳኞች**፡-ብርሃኑ አመነው

በእውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አቶ ጎይትኦም ግደይ - ጠበቃ ወይንሸት ከበደ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

ጉዳዩ የቀረበዉ አመልካች የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 212810 የሰጠዉ የጥፋተኝነት እና የቅጣት ዉሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ መዝገብ ቁጥር 178772 የሥር ፍ/ቤት የሰጠዉ የጥፋተኝነት ዉሳኔ በማጽናት እና የቅጣት ዉሳኔ በማሻሻል የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ያቀረበዉን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ፡፡በሥር መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ ከሳሽ፣ አመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክሯል፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበዉ የወንጀል ክስ ነዉ፡፡የክሱ ዝርዝርም ሲታይ ተከሳሽ አዋጅ ቁጥር 622/2001 ዓንቀፅ 91(1) በመተላለፍ በግምት ከምሽቱ 3፡00 ሰአት ከማሊ(ባማኮ) በረራ በማድረግ አዲስ አበባ ቦሌ አለም አቀፍ ኤርፖርት ሲደርስ በአየር መንገዱ የመንገደኞች ማስተናገጃ ተርሚናል ሁለት ላይ ሲደርስ ይዞት የገባውን ሻንጣ የጓዝና የአካላዊ ፍተሻ ማድረግ ፣ማስደረግ ሲገባው ሳያስፈትሽ መንገድ በመቀየር ጉዞውን በአየር መንገዱ የቀረጥ ነፃ ሱቅ በማድረግ ዋጋ በሚተመንበት በኩል ሊያመልጥ ሲል በቁጥጥር በመዋሉ በያዘው ፎለውሚ ሻንጣ በተደረገበት ፍተሻ ተገቢውን የጉምሩክ ስነስርአት ያልተፈፀመባቸው የቀረጥ ታክስ መጠናቸው 23411.52 (ሃያ ሶስት ሺህ አራት መቶ አስራ አንድ ከ 52/100) የሆኑ መጠናቸው 47600 (አርባ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ) ብር የሆኑ አርቴፊሻል ጥንድ የጆሮ ጌጣጌጦች ይዞ ወደ ሃገር ውስጥ ሲያሥገባ በመያዙ በፈፀመው የኮንትሮባንድ ተግባር ፈጽመዋል በማለት ወንጀል ክስ አቅርቦበታል፡፡

አመልካች በዓቃቤ ሕግ የቀረበበትን ክስ ክደው በመከራከራቸው ማስረጃዎች ቀርበው ከተሰሙ በኃላ እንዲከላከሉ ታዘው አመልካች መከላከያ ምስክሮቻቸው አስቀርበው አሰምተዋል ። ፍ/ቤቱ ተከሳሽ ባቀረቡዋቸው የመከላከያ ማስረጃ  የዓቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃ ማስተባበል ያልቻሉ በመሆናቸው በተከሰሰበት የሕግ አንቀጽ ሥር ጥፋተኛ ተብለዋል። በቅጣት ረገድም የግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየት እና የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት በማድረግ የወንጀሉ ደረጃ እና መነሻ የእስራት እና የገንዘብ ቅጣት እርከን በመለየት ተከሳሽ  በሦስት ዓመት ጽኑ እስራት በተጨማሪም 5000(አምስት ሺህ ብር )የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ውሳኔ ሰጥቷል።

የሥር ተከሳሽ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኛቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ የጥፋተኛነት ዉሳኔ በማጽናት ቅጣትን በተመለከተ በተሻሻለው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት ደረጃና እርከን የወጣለት ስለሆነ በስር ፍ/ቤት ከተያዙት የቅጣት ማቅለያዎች በተጨማሪ ሁለት ማቅለያዎች በመያዝ በስር ፍርድ ቤት ካረፈበት እርከን 17 ሁለት ማቅለያ ምክንያት ሲቀነስ የእስራት ቅጣት እርከን 15 የሚያርፍ ይሆናል ።የገንዘብ መቀጮም ከእርከን 7 ሁለት ማቅለያ ሲቀነስ እርከን 5 ላይ ያርፋል ስለሆነም አመልካች ከዚህ በፊት የታሰረበት ካለ የሚታሰብለት ሆኖ በ2 አመት ከዘጠኝ ወር ፅኑ እስራት እና 7000 (ሰባት ሺህ ብር) የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ውሳኔ ሰጥቷል።አሁን የቀረበው ቅሬታ በዚሁ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ሲሆን  የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ይግባኝ በጠየቁበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤት የተወሰነው የገንዘብ መቀጮ በማሻሻል ከፍ ተደርጎ የመወሰኑ አግባብነት ለመመርመር ሲባል በሰበር ችሎት ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው የጽሁፍ ክርክራቸው ተለዋውጠዋል።

የጉዳዩ አመጣጥና የግራ ቀኙ ክርክር ከፍ ሲል የተመለከተው ሲሆን እኛም ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል ከክርክሩ ሂደት ለመረዳት የተቻለው አመልካች በስር ፍ/ቤት የቀረበባቸው ክስ የወንጀል ህግ ድንጋጌ አዋጅ ቁ/ 622/2001 አንቀጽ 91/1/ በመተላለፍ ነው።

ቅጣትን በተመለከተ አመልካች ሊቀጡ የሚገባው ጥፋተኛ በተባሉባቸው የሕግ ድንጋጌዎች መሰረት ነው። አመልካች በተከሰሱበት የኮንትሮባንድ ወንጀል መፈፀማቸው በሚገባ ተረጋግጧል። በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀፅ 91(1) ጥፋተኛ የተባለ አጥፊ ሊቀጣ የሚገባው ከአስራ አምስት አመት በማይበልጥ ጽኑ እስራትና እስከ ብር ሃምሳ ሺህ በማይበልጥ መቀጮ ነው።

በመሠረቱ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ የወንጀል ህግ የአገሪቱን የወንጀል ህግ ግብ በአዋጅ ቁጥር 414/1996 አንቀጽ 1 ስር ሲደነግግ “የወንጀል ህግ ግብ ወንጀል እንዳይፈፀም

መከላከል ሲሆን ይህንን የሚያደርገው ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፣ ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰዱባቸው በማድረግ ነው" በማለት ያስቀምጣል፡፡ ህጉ በአንቀጽ 87 ላይ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች ህጉ ሊደርስበት ያሠበውን ዓላማ ለማረጋገጥ በሚቻልበት ሁኔታ በህጉ መንፈስ መሠረት መፈፀም እንዳለባቸው በመርህ ደረጃ ይደነግጋል፡፡ ይኸው አንቀጽ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎቹ ምን ጊዜም ሠብዓዊ ክብርን በሚጠብቅ መንገድ መፈፀም እንደሚኖርባቸው ያስገነዝባል፡፡ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 88 ሲታይም የቅጣቶች እና የጥንቃቄ እርምጃዎች አወሣሠንን በተመለከተ ዘርዘር ያሉ ንዑስ ድንጋጌዎችን አካቶ ይዟል፡፡ በዚህ አንቀጽ ስር ያሉ ንዑስ አንቀጾች የሚያሣዩት ፍርድ ቤቱ ቅጣቶችንና የጥንቃቄ እርምጃዎችን የሚወስነው የወንጀል ህጉን ጠቅላላ ክፍል ድንጋጌዎችን እንዲሁም ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው የሚደነግጉትን የልዩ ክፍሉ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ መሆኑን፣ ቅጣት ሊወሰን የሚገባው የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን ያለፈ የህይወት ታሪኩን ወንጀል ለማድረግ ያነሣሡትን ምክንያቶችና የሀሣቡን ዓላማ የግል ኑሮውን ሁኔታ፣ የትምህርቱን ደረጃ፣ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈፃፀሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን መሆኑን፣ የወንጀል ህግ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ፍርድ ቤቱ እጅግ ቀላል ከሆነው ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በጥንቃቄ በመመርመር ለእያንዳንዱ ጉዳይ ተገቢ የሆነውን ቅጣት እንደሚወስን የቅጣት አወሳሳን ደንቡ በግልፅ ያሳያል፡፡ ከላይ እንደተገለጸው የወንጀል ቅጣት የሚወሰነው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 88(2) ስር የተመለከቱትን ሁኔታዎችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ይህ ችሎትም እነዚህ ሁኔታዎችን ተመልክቷል፤ አመዛዝኗልም፡፡

በያዝነው ጉዳይ በስር ፍርድ ቤት አመልካች ጥፋተኛ በተባሉበት የህግ ድንጋጌ ቅጣት ሲወስን የግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየት እና የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት በማድረግ የወንጀሉ ደረጃ እና መነሻ የእስራት እና የገንዘብ ቅጣት እርከን በመለየት ተከሳሽ በሦስት ዓመት ጽኑ እስራት በተጨማሪም 5000 (አምስት ሺህ ብር ) የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ፍርድ ቤቱ የግራ ቀኙን የቅጣት አስተያየት በመቀበል ቅጣቱን በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 መሰረት አስልቶ ወንጀሎች በዝቅተኛ ደረጃ በመመደብ፣ለወንጀሉ መነሻ ተደርጎ የተያዘው ዝቅተኛው የቅጣት መጠን 5 ዓመት መሆኑን እና ይህም በአባሪ አንድ በእርከን 20 ስር የሚወድቅ መሆኑን በመግለጽ፣በተጠሪ በኩል የቀረበ ማክበጃ ምክንያት ስለሌለ በአመልካች በኩል የቀረቡትን ሦስት የማቅለያ ምክንያቶች ተገቢ አድርጎ በመቀበል እርከኑን ወደ 17 ዝቅ ካደረገ በኃላ በእርከን 17 በተመለከተው ፍቅድ ስልጣን መሰረት አመልካቹ በሦስት

ዓመት ጽኑ እስራት እንዲቀጡ ውሳኔ መስጠቱን፣አመልካች ጥፋተኛ የተባሉበት የህግ ድንጋጌ ከእስራት ቅጣት በተጨማሪ የገንዘብ መቀጮ የሚያስቀጣ በመሆኑ የገንዘብ መቀጮው በተመለከተም የህግ ድንጋጌው የሚያስቀጣው ከ50,000 እስከ 150,000 ብር የገንዘብ መቀጮ ስለሆነ በመመሪያው መሰረት ደረጃ በማውጣት ወንጀሉ ዝቅተኛ የተያዘ በመሆኑ የገንዘብ ቅጣት መነሻ 50,000 በመያዝ በአባሪ ሁለት እርከን 10 መነሻ እርከን በመያዝ ሶስት የቅጣት ማቅለያ መሠረት ወደ እርከን 7 ዝቅ እንዲል ካደረገ በኂላ አመልካች በ5000 ብር እንዲቀጣ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ቅጣት ውሳኔ መሰረት አድርጎ ግራቀኙ ካከራከረ በኂላ በአመልካች ቀርበው በስር ፍርድ ቤት ያልተያዙት ተጨማሪ ሁለት የቅጣት ማቅለያዎች በመያዝ የእስራት ቅጣት እርከኑ ወደ እርከን 15 ዝቅ በማድረግ በዚሁ እርከን ባለው ፍቅድ ስልጣን ቅጣቱ በማሻሻል አመልካች ሁለት አመት ከዘጠኝ ወር ፅኑ እስራት እንዲቀጡ የወሰነ ሲሆን የገንዘብ መቀጮ በተመለከተ ግን በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 2/2006 ላይ ባለው አባሪ ሁለት በተጨማሪነት ለአመልካች ከተያዙለት ሁለት የቅጣት ማቅለያዎች መሰረት ከእርከን 7 ወደ እርከን 5 ዝቅ ካደረገ በኂላ የስር ፍርድ ቤት ከወሰነው ቅጣት 5,000 (አምስት ሺህ) የገንዘብ ቅጣት በላይ 7000 (ሰባት ሺህ) ብር እንዲቀጣ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡በሰበር አጣሪ ችሎት ለክርክር የተያዘው ጭብጥም አመልካች ባቀረቡት ይግባኝ መነሻነት ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የገንዘብ ቅጣቱን የመጨመሩ አግባብነት የሚመለከት ነው፡፡ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር የወንጀለኛ መቅጫ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 196(2) ስር እንደተደነገገው ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ቅጣቱን ያፀናል ፣ይጨምራል፣ወይም ይቀንሳል በማለት ተደንግጓል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ለመረዳት የሚቻለው ተከሳሽ ይግባኝ የሚለው ቅጣቱ ለመለወጥ ወይም ለማሻሻል እንደሆነ አከራካሪ አይሆንም ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የስር ፍርድ ቤት አመልካች (ተከሳሽ )ባቀረቡት ይግባኝ ቅሬታ መነሻነት የገንዘብ ቅጣት መጨመሩ የወንጀል ህጉ አላማ አይደለም፡፡ ስለሆነም አመልካች ባቀረቡት ቅሬታ መነሻነት በስር ፍርድ ቤት ያልተያዘላቸው ሁለት የቅጣት ማቅለያዎች በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተያዘላቸው ስለሆነ ይህንን ይግባኝ ተብሎ ያልተሻረ ስለሆነ በእርከን 5 ስር ካለው ፍቅድ ስልጣን በወንጀል ህግ ቁጥር 90 መሠረት በማስላት መወሰን ሲገባው አመልካች ባቀረቡት ይግባኝ መነሻነት የገንዘብ ቅጣት በማክበድ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው ብለናል፡፡ ስለሆነም አመልካች ጥፋተኛ በተባሉበት የህግ ድንጋጌ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሰረት በማስላት የእስራት ቅጣቱ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ሆኖ የገንዘብ ቅጣት በተመለከተ ግን ሊወሰን የሚገባው ቅጣት በእርከን 5 ስር ካለው ፍቅድ ስልጣን በወንጀል ህግ ቁጥር 90 መሠረት መሰላት ስላለበት አመልካች 2000 (ሁለት ሺህ) ብር የገንዘብ መቀጮ ሊቀጣ ይገባል ብለናል፡፡

ሲጠቃለል በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የጸናው የጥፋተኝነት ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ ስላልተገኘ እና በቅጣት ውሳኔው ላይ ግን ከላይ በተገለጸው ምክንያት ተገቢው ማስተካከያ ሊደረግበት የሚገባ ሆኖ በመገኘቱ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቶአል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በአመልካቹ ላይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 212810 በ03/09/2008 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 178772 በ05/11/2008 ዓ.ም. የጸናው የጥፋተኝነት ውሳኔ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 195(2)(ለ)(2) መሰረት ፀንቶአል፡፡
2. በአመልካቹ ላይ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የተወሰነው የሁለት አመት ከዘጠኝ ወር ፅኑ እስራት ቅጣት እንዳለ ተቀብለን ፣ተጥሎ የነበረውን የብር 7,000 (ሰባት ሺ.ህ) መቀጮ የቅጣት ውሳኔ በማሻሻል አመልካቹ ከፅኑ እስራቱ በተጨማሪ 2000 (ሁለት ሺ.ህ ) ብር መቀጮ እንዲቀጡ ወስነናል፡፡
3. ይህንኑ ተገንዝቦ የተሻሻለውን የገንዘብ ቅጣት መሠረት እንዲያስፈጽም ለሚመለከተው አካል የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ከመሸኛ ትዕዛዝ ጋር ይላክ፡፡
   ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፡፡

መ/ተ

የሰ/መ/ቁ. 127312

ግንቦት 23 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በእውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡-የአ.ብ.ክ.መ. ፍትህ ቢሮ ዐቃቤ ህግ - ዳግማዊ አገኘሁ

ተጠሪዎች፡-1ኛ አቶ እሸቱ ሉሌ ንጉሴ - ቀርበዋል፡፡

2ኛ አቶ ደግዋለ ልክነህ ደርሰህ

3ኛ ወ/ሮ ጥሩዬ ደግዋለ } አልቀረቡም

4ኛ ወ/ሮ ይሳለሙ ደመቀ

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የእነማይ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 0202415 በቀን 02/04/07 ዓ.ም የሰጠውን ፍርድና የቅጣት ውሳኔ የምስራቅ ጐጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 0213319 በቀን 21/07/2007 ዓ.ም በመሻሩ እና የአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 02-13131 በቀን ህዳር 29 ቀን 2009 ዓ.ም ይህንኑ በማጽናቱ እና የአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት መሠረታዊ የህግ ግድፈት አልተፈፀመም ሲል በሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የወንጀል ክስ እንዲሻሻል የተሰጠ ትእዛዝ ውጤትን ይመለከታል፡፡ አመልካች በተጠሪዎች ላይ በስር ፍ/ቤት ባቀረበው ክስ 1ኛ፣ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የወንጀል ህግ ቁጥር 32/1/ /ሀ/ 555 /ለ/ የተመለከተውን ተላልፈው በሌላ ሰው አካል ላይ ጉዳት ለማድረስ አስበው ነሐሴ 9 ቀን

2006 ዓ.ም በ12፡00 ሰዓት የግል ተበዳይ ላቃቸው ሞገስን ብቸና ከተማ 01 ቀበሌ ኪዳነምህረት ቤተክርስቲያን 1ኛ ተከሳሽ በጅንፋ ሽመል እየደጋገመ ሲመታው 2ኛ ተከሳሽ በድንጋይ መሐል ራሱን 3ኛ ተከሳሽ ድንጋይ በመወርወር ግንባሩን በመምታታቸው በአካል ላይ ጉዳት አድርሰዋል 4ኛ ተከሳሽ የወ/ህ/ቁ 27/1/ 556/2/ /ሀ/ የተመለከተውን ተላልፈው በተመሳሳይ ቀንና ቦታ ከ1-3 ያሉት ሲመቱት እሷ በድንጋይ ወርውራ የሳተችው በመሆኑ በአካል ላይ ጉዳት ለማድረስ ሞክራለች የሚል ሲሆን ተጠሪዎች በክሱ ላይ በሌላ መዝገብ ታይቶ የተወሰነ ስለመሆኑ መቃወሚያ ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ በ01/03/2007 ብይን ተሰጥቶበታል በማለት አልፎ የግል ተበዳይን ጨምሮ የአመልካችን ሁለት ምስክሮች እና የሰነድ ማስረጃዎች ከሰማ በኋላ 1ኛ ተጠሪ የወ/ህ/ቁ 556/2//ሀ/፣ 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች የወ/ሕ/ቁ. 555/ለ/ እና 4ኛ ተጠሪ በቀረበበት ክስ እንዲከላከሉ ብይን የሰጠ ቢሆንም የተጠሪዎች ጠበቃ ባለመቅረቡ ማስረጃዎቻቸውንም በተከታታይ ቀጠሮዎች አለማቅረባቸውንና ራሳቸውም መሆናቸውን በመግለጽ ጠበቃቸው ሲቀርብ እንዲሰሙ እንዲታዘዝላቸው ተለዋጭ ቀጠሮ የጠየቁ ቢሆንም ፍ/ቤቱ ህዳር 19፣ ህዳር 29 እና ታህሳስ 1/2007 ተሟልተው አልቀረቡም ጠበቃቸውም አልቀረበም በማለት የመከላከያ ማስረጃ የማሰማት መብታቸውን በማለፍ ተከላከሉ በማለት በሰጠው ብይን መሠረት 1ኛ ተጠሪ የወንጀል ህግ ቁጥር 556/2/ /ሀ/ ጥፋተኛ በማለት 4ወር ቀላል እስራት፣ 2ኛ ተጠሪ እና 3ኛ ተጠሪ የወንጀል ህግ ቁጥር 555 /ለ/ ጥፋተኛ በማለት 2 ዓመት ከ4 ወር እና 2ዓመት ከ3ወር እንደቅደም ተከተላቸው እንዲሁም 4ኛ ተጠሪን በ1 ወር ቀላል እስራት እንዲቀጡ በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች በዚህ ፍርድ እና የቅጣት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለምስራቅ ጉጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱም አመልካች የወ/ህ/ቁ 556/2/ /ሀ/ ወደ 555 /ለ/ ለማሻሻል ያቀረበው በብይን ውድቅ ተደርጐ ሳለ በሌላ መዝገብ ክስ ማቅረቡን፣ ይህንኑ መሰረት አድርጎ ተጠሪዎች በቀረበባቸው ክስ ተከላከሉ የተባሉበትን አግባብ እና የመከላከያ ማስረጃ ሳያሰሙ የተሰጠው ፍርድ እንዲሻርልን በማለት ያቀረቡትን ቅሬታ ፍርድ ቤቱ በመመርመር አስቀድሞ ክስ ቀርቦበት ነበር የተባለውን የእነማይ ወረዳ ፍርድ ቤት መ/ቁ 0202368 እንዲቀርብ በማድረግ መርምሮ አመልካች በተጠሪዎች ላይ አስቀድሞ በመ/ቁ 0202368 በቀላል አካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ክስ አቅርቦ ምስክር ከተሰማ እና እንዲከላከሉ ብይን ከተሰጠ በኋላ አመልካች ክሱን በከባድ የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ለማቅረብ አሻሽሎ እንዲያቀርብ ጠይቆ ፍርድ ቤቱ ምክንያቱን ባለመቀበል ውድቅ በማድረግ የአመልካቾች የመከላከያ ማስረጃ እንዲሰማ ያዘዘ ቢሆንም አመልካች ክሱን አንስቶ በሌላ መዝገብ ቁጥር 0202415 አዲስ ክስ አቅርቧል፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይህንን ጭብጥ በመመርመር ክስ ማንሳትና ማሻሻል ለአመልካች በህግ የተሰጠው ቢሆንም ክሱን መቀጠል ያለበት ግን በተዘጋው መዝገብ ላይ እንዲቀጥል እንጂ አዲስ ክስ መዝገብ ተከፍቶበት የሚቀርብ አይደለም፡፡ የስር ፍ/ቤት የተጠሪዎችን ተቃውሞ ያለፈበት ምክንያት የህግ መሠረት የለውም፣ የተጠሪዎች የመከላከያ ምስክሮች መጥሪያ ደርሷቸው ያልቀረቡና በፖሊስ አማካኝነት እንዲቀርቡ ታዞም ካለመቅረባቸውም በላይ ጠበቃቸው ባለመቅረቡ ተለዋጭ ቀጠሮ ተጠይቆ ከወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 94 አንፃር ማየት ሲገባው ፍ/ቤቱ የመከላከያ ማስረጃ የማሰማት መብታቸውን ማለፋ ተገቢነት የለውም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሽሮ አመልካች በቀድሞው መዝገብ እንዲቀጥል አዟል፡፡

አመልካች በዚህ ፍርድ ቅር በመሰኘት ያቀረበው ይግባኝ የተመለከተው የአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በማጽናቱ መሠረታዊ ስህተተ ተፈጽሟል በማለት ለአብክመ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ያቀረቡትን አቤቱታ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ለዚህ ችሎት የቀረበውም በዚሁ ምክንያት ሲሆን ይዘቱም ዐቃቤ ህግ ከውሳኔ በፊት በማናቸውም ጊዜ ክሱን አሻሽሎ ለማቅረብ የሚከለክለው ህግ ባለመኖሩ ከቀረበው ማስረጃ አንጻር ተመጣጣኝ ድንጋጌ ጠቅሶ ማቅረቡ ተገቢ ነው በሰበር መ/ቁ 57632 ተመላክቷል፡ የወረዳ ዐቃቤ ህግ የህክምና የመጨረሻ ውጤት ሳይጠበቅ ተቀራራቢነት በሌለው አነስተኛ ድንጋጌ ክስ ማቅረቡ ፍትህን ስለሚያዛባ ድንጋጌው ተሻሽሎ ክስ መቅረቡ የተጣሰ ህግ የለም ስለመሆኑም የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሳኔ ተሽሮ የወረዳው ይጽናልኝ የሚል ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪዎች ቀርበው መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሠረት 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ መልስ የሰጡ ሲሆን 3ኛ እና 4ኛ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡ የመልሳቸው ይዘትም ዓቃቤ ህግ ክሱን ከውሳኔ በፊት በማንኛውም ጊዜ የማንሳት መብት ቢኖረውም ይህንን መብት ግን ያለአግባብ ሊጠቀምበት አይገባም፣ በሰበር መ/ቁ 57632 በሌለበት የተሰጠ ውሳኔን እንጂ ከዚህ ጉዳት ጋር አይያያዝም፡፡ ከፍተኛው ፍ/ቤት ወረዳው የሻረው የወንጀል ህግ አንቀጽ 556 ወደ 555 ለምን ተቀየረ በሚል ሳይሆን በተለየ መዝገብ ክስ መቅረቡን መሰረት በማድረግ ነው ስለሆነም የአመልካች አቤቱታ የህግ መሠረት የሌለው በመሆኑ ይሻርልኝ የሚል ነው፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ፍርድ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረነዋል እንደመረመርነውም በዋናነት ምላሽ የሚሻው የክርክሩ ጭብጥ ዐቃቤ ህግ አመልካች በተጠሪዎች ላይ አቅርቦት የነበረው ክስ የተጠሪዎች የመከላከያ ማስረጃ ከመሰማቱ በፊት ክሱን እንዲያሻሽል የቀረበው አቤቱታ በፍርድ ቤቱ ተቀባይነት በማጣቱ ክሱን ካነሳ በኋላ በሌላ መዝገብ ለማሻሻል

ባቀረበው ምክንያት ውጤት መሠረት አዲስ ክስ ማቅረብ የሚችልበት አግባብ ከወንጀል ሥነ ሥርዓት ህግ ድንጋጌዎች ዓላማ አንጻር መርምረናል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የሚቻለው አመልካች በተጠሪዎች ላይ በስር ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 0202368 የወ/ህ/ቁ 556 ተላልፈው ቀላል የአካል ጉዳት አድረሰዋል በማለትበቀረበው ክስ ማስረጃዎቹን አሰምቶ እንዲከላከሉ ብይን ከተሰጠ በኋላ አመልካች ክሱን ለማሻሻል ያቀረበውን አቤቱታ ፍርድ ቤቱ ባለመቀበሉ የመከላከያ ምስክሮች ከመሰማቱ በፊት ክሱን በማንሳቱ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን ዘግቷል፡፡ አመልካች በሌላ መዝገብ በስር ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 0202415 በተጠሪዎች ላይ የወ/ህ/ቁ555 እና 27/1/ /ሀ/ 556 የተመለከተውን ተላልፈዋል በማለት አዲስ ክስ አቅርባል፡፡ ተጠሪዎቹ መቃወሚያ ቢያቀርቡም ውድቅ ሆኖ ለዚህ ሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው ውሳኔ በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤት ተሠጥቷል፡፡

በመሠረቱ በተከሳሽ ላይ በቀረበ የወንጀል ክስ ዋና ስህተት ወይም ያልተጠቀሰ ነገር ሲኖር ይህም ክሱ የቀረበበትን ተከሳሽን የሚያሳስት ወይም ያሳሳተ በመሰለ ጊዜ /የወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 118/ በክሱ መሠማት ወቅት ፍርድ ከመስጠቱ በፊት በማናቸውም ጊዜ ፍርድ ቤቱ በራሱ ጊዜ ወይም ከተከራካሪ ወገኖች በሚነሳ አስተያየት ቀርቦ የነበረው የወንጀል ክስ እንዲለወጥ ወይም እንዲጨመር ወይም አዲስ ክስ እንዲዘጋጅ ፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ለመስጠት እንደሚችል በወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 119/1/ ተመልክቷል፣፣ ከዚህ ድንጋጌ መረዳት እንደሚቻለው ፍርድ ቤቱ በራሱ ወይም ከተከራካሪ ወገኖች በአንዱ በሚያቀርበው ማመልከቻ መሠረት እንደነገሩ ሁኔታ ክሱ እንዲለወጥ እንዲጨመር ወይም አዲስ ክስ እንዲዘጋጅ ትእዛዝ የሚሰጥ ስለመሆኑ ነው፡፡ ይህ ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ትእዛዝ የማሻሻል ጥያቄውን ውድቅ በማድረግ የተሰጠ ከሆነ ደግሞ የመጨረሻ በመሆኑ ይግባኝ ሊባልበት የሚገባ ስለመሆኑ በሰበር መ/ቁ 93234 አስገዳጅ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡

በዚህ በያዝነው ጉዳይ አመልካች በተጠሪዎች ላይ በቅድሚያ በመ/ቁ 0202368 በወረዳው ፍርድ ቤት በቀረበው ክስ ላይ ክሱን ለማሻሻል ያቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት ሲያጣ አመልካች ይግባኝ በማለት በበላይ ፍርድ ቤት ሊያሳርም አልሞከረም፡፡ በይግባኝ በበላይ ፍርድ ከማሳረም የቀረበውን ክስ በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 122/ለ/ መሠረት ክሱን የማንሳት እና ለዚያው ፍርድ ቤት በሌላ መዝገብ በመ/ቁ 0202415 አዲስ ክስ በማቅረብ ለማሻሻል ለፍርድ ቤቱ አቅርቦ ያጣውን መብት ክሱን በማንሳት አዲስ ክስ በማቅረብ ክርክሩ እንዲቀጥል የሆነ መሆኑን ነው መዝገቡ የሚያስረዳው፡፡

የወንጀል ሥነ ሥርዓት ህግ ዋነኛ ዓላማ የወንጀል ህጉ በተግባር የሚተረጐምበትን ሥርዓት በመዘርጋት በህጉ ላይ የተመለከቱ ወንጀሎች ተፈጽመው በሚገኙ ጊዜ እውነት በማውጣት ውጤታማ፣ ቀልጣፋና ፍትሐዊ የወንጀል ፍትህ ሥርዓት እንዲኖር ማስቻል ነው፡፡ ከሥነ-

ሥርዓት ሕጉ ውጪ በሆነ አካኂን ተመርምሮና ክርክር ተካሂዶ የሚሰጥ ፍርድ በህገ-መንግስታችን አንቀጽ 20 የተረጋገጠውን በተገቢ አጭር ጊዜ ፍትህ የማግኘት መብት ያጓደለ ነው የሚሆነው፡፡

አመልካች ክሱን ለማሻሻልም ሆነ ለማንሳት ብሎም በሌላ መዝገብ አዲስ ክስ ለመቅረብ ምክንያት የሚያደርገው የወረዳው ዐቃቤ ህግ የህክምና የመጨረሻ ውጤት ሳይቀርብ ክሱን በማቅረቡ በቀላል አካል ጉዳት ክስ የቀረበ ቢሆንም አሁን የህክምና ማስረጃ የደረሰ በመሆኑ ነው ክሴን ላሻሽል የሚል ነው፣ ይህ ሁኔታ አይኖርም ባይባልም መፈጸም ያለበት ግን በሕግ በተዘረጋ ሥርዓት ነው፣ በመሰረታዊነት ያላለቀ ምርመራ ላይ ክስ አይቀርብም.፣ ከወ/መ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 40/1/ ዐቃቤ ሕግ በተከሳሹ ላይ ክስ ለማቅረብ በቂ ምክንያት መኖሩን ከተረዳ ክስ የሚያቀረብና ከዚህ በፊት ግን ተመሳሳይ ሁኔታዎች እንዳያጋጥሙ በወ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 38፣ 41 እና ተከታዮቹ መሰረት መፈጸም የሚገባው ነው፡፡

ስለሆነም አመልካች በቅድሚያ ያቀረበው ክስ ላይ ማስረጃዎቹን ካሰማና እንዲከላከሉ ታዞ የክሱ መሰማት በቀጠለበት ሂደት ላይያቀረበው ክስ ማሻሻል አቤቱታ ተቀባይነት ሲያጣ ይህንን በህጉ አግባብ በይግባኝ ከማሳረም ክሱን በማንሳት በሌላ መዝገብ አዲስ ክስ ማቅረቡ ምክንያቱ ምንም ይሁን ምንም የሥነ-ሥርዓት ህጉን ዓላማ ያልጠበቀ እና የፍርድ ቤቱን ትእዛዝ ያላከበረ በመሆኑ ተገቢውን ፍትህ ሊያስጥ የሚችል ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም የምስራቅ ጉጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውና በበላይ ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ያገኘው ውሳኔ መሠታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ያላገኘነው በመሆኑ ተከታዩን ውሳኔ ሠጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1/ የእነማይ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 0202415 በቀን 02/04/07 ዓ.ም የሰጠውን ፍርድ በመሻር የምስራቅ ጉጃም አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 0213319 በቀን 21/07/2007 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የአብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 02-13131 ህዳር 29 ቀን 2008 ዓ.ም እና አብክመ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት መ/ቁ 55406 መጋቢት 5 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጡት ትእዛዝ በወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 195/ለ/ /2/ መሠረት ፀንቷል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ግ

ሰ/መ/ቁ. 110736

ሠኔ 23 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻውአዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡-አብዲ ኡመር ሰዒድ

ተጠሪ፡-የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

መዝገቡ ከተዘጋ በኂላ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ጥር 22 ቀን 2009 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው አቤቱታ ተጠሪ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ድሬዳዋ ምድብ ችሎት በመ.ቁ 07770 እና 08155 በመሠረተበት ክስ መነሻነት በድምሩ የ16 ዓመት ጽኑ እሥራት ቅጣት የተላለፈበት መሆኑን፤በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 104839 እና 105180 ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም በሁለቱም መዝገቦች ውሳኔው የጸናበት መሆኑን፤በመቀጠልም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትበመ.ቁ 110735 እና 110736 አቤቱታ ያቀረበ መሆኑን፤በመ.ቁ 110735 ያቀረበው አቤቱታ ተመርምሮ የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ የጸና መሆኑን፤በመ.ቁ 110736 ያቀረቡት አቤቱታ ተመርመሮ በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጠው የቅጣት ውሳኔ ተሻሽሎ አመልካች በአምስት ዓመት ከሥድሥት ወር ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ እና በበታች ፍ/ቤቶች የተላለፈበት የብር 3,000 / ሦስት ሺህ ብር/ የገንዘብ መቀጮ አልተነካም በማለት ውሳኔ የተሰጠ መሆኑን በመግለጽ በመዝገቦቹ የተሰጠው የቅጣት ውሳኔ በአንድ ጊዜ ቢወሰንበት ኖሮ ሊወሰን ይችል ከነበረው ከፍተኛ ቅጣት ሳያልፍ ይጣመርለት ዘንድ ዳኝነት ጠይቋል፡፡

ይህ ፍ/ቤት አመልካች ባቀረበው አቤቱታ ላይ ተጠሪ አስተያየት እንዲሰጥበት በፖስታ ቤት መጥሪያ የላከለት ቢሆንም ተጠሪ ቀርቦ የሰጠው አስተያየት የለም፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ድሬዳዋ ምድብ ችሎት በመ.ቁ08155 በተመሰረተበት የካናቢስ ዕጽ ማከማቸት እና ለሽያጭ ማቅረብ ወንጀል ክስ የተላለፈባበት የዘጠኝ ዓመት ጽኑ እሥራት እና የብር 20,000 /ሐያሺ ህ ብር / የገንዘብ መቀጮ ላይ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 105180፤በመቀጠልም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 110735 አቤቱታ አቅርቦ የሥር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ የጸና መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በሌላ በኩል አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ድሬዳዋ ምድብ ችሎት በመ.ቁ. 07770 በተመሰረተበት የካናቢስ ዕጽ ማከማቸት እና ለሽያጭ ማቅረብ ወንጀል ክስ በሰባት ዓመት ጽኑ እሥራት እና በብር 3,000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ በማለት ውሳኔ የተሰጠ መሆኑን፤አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ104839 ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አከራክሮ ውሳኔውን ያጸናው መሆኑን፤አመልካች በመቀጠል ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ መዝገብ /የመ.ቁ 110736 / አቤቱታ አቅርቦ ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኂላ ሕዳር 20 ቀን 2008 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን የቅጣት ውሳኔ በማሻሻል አመልካች በአምሥት ዓመት ከሥድስት ውር ጽኑ እሥራት እንዲቀጣ እና በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው የብር 3,000 /ሦስት ሺ ብር / የገንዘብ መቀጮ አልተነካም በማለት ውሳኔ የሰጠ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 96505 የወንጀል ሕግ አንቀጽ 186(3) በአንድነት ተጣምረው መታየት የነበረባቸው የወንጀል ክሶች በተለያዩ ፍርድ ቤቶች ወይም ችሎቶች በተናጠል ታይተው የተለያዩ ቅጣቶች በተወሰኑ ጊዜ እንደገና በአዲስ መልክ እያንዳንዱ ቅጣት ተሰልቶና የቅጣት ማቅለያዎች ሁሉ ታይተው የሚወሰን ሳይሆን ሕጉ ጥፋተኛው በፈፀማቸው ተደራራቢ ወንጀሎች በአንድ ጊዜ ቢፈረድበት ኖሮ ሊወሰንበት ይችል ከነበረው ከፍተኛ ቅጣት ሳያልፍ እንደሚወሰን የሚያስረዳ መሆኑን፤ ስለተደራራቢ ወንጀሎች ቅጣት አወሳሰን የሚመለከተው የወንጀል ሕግ አንቀጽ 184(1)(ለ)"ም" ሲታይም ጥፋተኛው ተደራራቢ ወንጀሎች ፈፅሞ በተገኘ ጊዜ በተደራራቢነት ለተፈፀሙ ለእያንዳንዱ ወንጀል በተናጠል ተገቢው የቅጣት መጠን ተወስኖ የሁሉም እንደሚደመር እና ቅጣቶችም ተደምረው ለወንጀሉ አይነት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ከተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት መብለጥ እንደማይችል በመግለጽ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/1 መሠረት በየትኛውም እርከን ላይ ለሚገኙ ፍ/ቤቶች አስገዳጅ የሆነ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ አመልካች በተለያዩ መዝገቦች ላይ ቅጣት የተላፈለበት በመሆኑ የሰበር ሰሚ ችሎቱ በሰጠው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም መሠረት ቅጣቶቹ ተጣምረው ሊወሰኑ የሚገባ

በመሆኑ የመጨረሻ ፍርድ በተሰጠባቸው የመ.ቁ 08155እና 110736 በሆኑት መዝገቦች በሁለቱም የተሰጠው የቅጣት ውሳኔ ተደምሮ መወሰን የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም አመልካችየመ.ቁ 08155 በሆነው መዝገብ የተላለፈበት የዘጠኝ ዓመት ጽኑ እሥራት እና የብር 20,000 /ሐያ ሺህ ብር / የገንዘብ መቀጮ እና በዚህ መዝገብ / የመ.ቁ 110736 / በሆነው መዝገብ የተላለፈበት የአምሥት ዓመት ከሥድስት ወር ጽኑ እሥራት እና የብር 3,000 / ሦስት ሺህብር / የገንዘብ መቀጮ ተደምሮ አመልካች በአሥራ አራት ዓመት ከሥድሥት ወር ጽኑ እሥራት እና በብር 23,000 / ሐያ ሦስት ሺህ ብር / ሊቀጣ ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ትዕዛዝ</u>

የድሬዳዋ ማረሚያ ቤት በዚህ መዝገብ ተደምሮ በተሰጠው የቅጣት ውሳኔ መሠረት የእሥራት ቅጣቱን እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ሰ/መ/ቁ 134834

ሠኔ 29 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዳኜ መላኩ

ብርሃኑ አመነው

ሸምሱ ሲርጋጋ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡- የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤሕግ - ዐ/ሕግ ውብሸት ይመኑ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1. ሸዋነሽ መንግሥቱ ቀረቡ

2. ወንድአፍራሽ ፍቅሩ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የይግባኝ ማስፈቀጃን የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች በተጠሪዎች ላይ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦት የነበረውን ክስ በሚመለከት ፍ/ቤቱ 1ኛ ተጠሪን ከ2ኛ ክስ፤ 2ኛ ተጠሪን ከ2ኛ እና ከ6ኛ ክስ በወ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 141 መሠረት በነጻ እንዲሰናበቱ በማለት ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም ብይን ሰጥቷል፡፡ በሌላ በኩል በመዝገቡ ላይ የቀረቡትን ሌሎች ክሶች በተመለከተ ክርክሩ ቀጥሎ ታሕሳስ 13 ቀን 2007 ዓ.ም ፍርድ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የሥር ፍ/ቤት ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም በሰጠው ብይን እና በዋናው ጉዳይ ላይ በሰጠው ፍርድ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ጥር 19 ቀን 2007 ዓ.ም ይግባኝ አቅርቧል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤት ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም ብይን ከሰጠ በኂላ አመልካች ይግባኝ ለማቅረብ እንዲችል ሐምሌ 25 ቀን 2006 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ ግልባጭ እንዲሰጠው የጠየቀ ሲሆን ለተጠሪዎች የብይኑ ግልባጭ የተሰጣቸው ሐምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም በመሆኑ አመልካች የመዝገብ ግልባጭ የተሰጠን ታሕሳስ 22 ቀን 2007 ዓ.ም ነው በማለት ያቀረበው ምክንያት የሚታመን አይደለም፤ አመልካች ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም በተሰጠው ብይን ላይ ጊዜው ሳያልፍ የይግባኝ ቅሬታ ማቅረብ ሲገባው ያለበቂ ምክንያት ዘግይቶ ጥር 19 ቀን 2007 ዓ.ም

ይግባኙን ያቀረበ በመሆኑ አመልካች በተጠሪዎች ላይ ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም በተሰጠው ብይን ላይ ያቀረበው ይግባኝ ጊዜው ያለፈበት ነው በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡- የሥር ፍ/ቤት ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም የሰጠው ብይን እና በመዝገቡ የተደረገው ሙሉ ክርክር ግልባጭ የተሰጠን ታሕሳስ 22 ቀን 2006 ዓ.ም ነው፤ በዚሁ መሠረት የይግባኝ ቅሬታችንን አዘጋጅተን ጥር 15 ቀን 2007 ዓ.ም ባቀረብንበት ሁኔታ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የብይኑ ግልባጭ ለተጠሪዎች የደረሰው ሐምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም በመሆኑ አመልካች ያቀረበው ምክንያት የሚታመን አይደለም በማለት አመልካች ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም በተሰጠው ብይን ላይ ያቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ጊዜ ያለፈበት ነው በማለት የሰጠው ብይን መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ችሎት መታየት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎ ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከረከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ እኛም የግራቀኙን ክርክር ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

የወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 187/1 ድንጋጌ ይግባኝ ማለቱን ለማስታወቅ የሚጽፈውን ማመልከቻ ይግባኝ ባዩ ወይም ጠበቃው ይግባኝ የሚልበት ፍርድ በተሰጠ በአሥራ አምሥት ቀን ውስጥ ማቅረብ አለበት፤ ይግባኝ ማለቱን ለማስታወቅ የጻፈው ማመልከቻ ለፍርድ ቤት መዝገብ ሹም ሲደርሰው ይግባኝ የተባለበትን ፍርድ አስገልብጦ ለይግባኝ ባዩ ወይም ለጠበቃው ይሰጣል፤ ይግባኝ ባዩ በእሥር ቤት ያለ እንደሆነ ይግባኝ የተባለበትን ፍርድ ግልባጭ የፍርድ ቤት መዝገብ ሹም ለይግባኝ ባይ እንዲሰጥ ለወህኒ ቤቱ ሹም ይልካል፤ ፍርዱ ተገልብጦ ያለቀበትን ቀን እና ኋላም ለይግባኝ ባዩ ወይም ለጠበቃው ወይም ለወህኒ ቤቱ ሹም የደረሰበትን ቀን የፍርድ ቤት መዝገብ ሹም በፊርማው ያረጋግጣል በማለት ይደነግጋል፡፡ የዚሁ ሕግ ንኡስ ቁጥር 2 ድንጋጌ ይግባኝ ማለት የሚፈልገው ወገን ይግባኙን የፍርዱ ግልባጭ በደረሰው በ30 ቀን ውስጥ ፍርዱን ለሰጠው ፍ/ቤት መዝገብ ቤት ማቅረብ እንዳለበት ይደረግጋል፡፡ ከድንጋጌዎቹ ይዘት መገንዘብ የሚቻለው ይግባኝ መጠየቅ የሚፈልገው ወገን ይግባኝ የሚልበት ፍርድ በተሰጠ በአሥራ አምሥት ቀን ውስጥ ይግባኝ የሚጠይቅ መሆኑን በመግለጽ ማመልከቻ ማቅረብ ያለበት መሆኑን፤ የፍርድ ቤቱ መዝገብ ሹም ይግባኝ መጠየቅ የሚፈልገው ወገን ያቀረበው ማመልከቻ ሲደርሰው ይግባኝ የተባለበትን ፍርድ አስገልብጦ ይግባኝ መጠየቅ ለሚፈልገው ወገን ማድረስ ያለበት መሆኑን፤ ይግባኝ ማለት የሚፈልገው ወገን የፍርዱ ግልባጭ በደረሰው በ30 ቀን ውስጥ ይግባኙን ማቅረብ ያለበት መሆኑን ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች የሥር ፍ/ቤት ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም በተሰጠው ብይን ላይ ይግባኝ ማቅረብ እንደሚፈልግ በመግለጽ በሕጉ የተገለጸው የአሥራ አምሥት ቀን ጊዜ ሳያልፍ ሐምሌ 25 ቀን 2006 ዓ.ም ይግባኝ መጠየቅ እንደሚፈልግ ገልጾ ግልባጭ የጠየቀ ለመሆኑ በሥር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬነገር ነው፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሬጅስትራር ጽ/ቤት መጋቢት 26 ቀን 2008 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም የተሰጠው ብይን ለአመልካች የደረሰው በመዝገቡ ላይ ጠቅላላ ውሳኔ ከተሰጠ በኂላ ታሕሳስ 22 ቀን 2007 ዓ.ም መሆኑን አረጋግጧል፡፡ የሥር ፍ/ቤት አመልካች ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም በተሰጠው ብይን ላይ ያቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ጊዜው ያለፈበት ነው ከሚል መደሚደሚያ ላይ ሊደርስ የቻለው ተጠሪዎች የብይን ግልባጭ የደረሳቸው ሐምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም በመሆኑ አመልካች የብይኑ ግልባጭ የተሰጠኝ ታሕሳስ 22 ቀን 2007 ዓ.ም ነው በማለት ያቀረበው ክርክር የሚታመን አይደለም በማለት ነው፡፡ አመልካች በሕጉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ይግባኝ መጠየቅ እንደሚፈልግ በመግለጽ ግልባጭ እንዲሰጠው በጠየቀበት ሁኔታ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሬጅስትራር ጽ/ቤት ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም የተሰጠው ብይን ለአመልካች የደረሰው በመዝገቡ ላይ ጠቅላላ ውሳኔ ከተሰጠ በኂላ ታሕሳስ 22 ቀን 2007 ዓ.ም ነው በማለት ባረጋገጠበት ሁኔታ፤ አመልካች የክርክሩን ሙሉ ይዘት የሚያሳይ የመዝገብ ግልባጭ ሳይደርሰው ይግባኝ መጠየቅ በማይችልበት ሁኔታ፤ አመልካች ግልባጭ እንዲሰጠው በጠየቀበት ቀን እና የመዝገቡ ግልባጭ ለአመልካች በደረሰበት ቀን መካከል ያሉት የባከኑ ቀናት በአመልካች ጥፋት ምክንያት ባልባከኑበት ሁኔታ፤ አመልካች የመዝገቡ ግልባጭ ታሕሳስ 22 ቀን 2007 ዓ.ም ደርሶት በሕጉ የተቀመጠው የሠላሳ ቀን የጊዜ ገደብ ሳያልፍ ጥር 19 ቀን 2007 ዓ.ም ይግባኙን አዘጋጅቶ ባቀረበበት ሁኔታ የሥር ፍ/ቤት የብይኑ ግልባጭ ለተጠሪዎች የደረሰው ሐምሌ 17 ቀን 2006 ዓ.ም ነው በሚል ምክንያት አመልካች ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም በተሰጠው ብይን ላይ ያቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ጊዜው ያለፈበት ነው በማለት የሰጠው ብይን በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕጉ የይግባኝ አቀራረብን አስመልክቶ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ያላገናዘበ እና መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡"በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 109183 ሕዳር 05 ቀን 2009 ዓ.ም አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም በተጠሪዎች ላይ በሰጠው ብይን ላይ ያቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ጊዜው ያለፈበት ነው በማለት የሰጠው ብይን ተሽሯል፡፡

2. አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሐምሌ 14 ቀን 2006 ዓ.ም በተጠሪዎች ላይ በሰጠው ብይን ላይ ያቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ጊዜው ያላላፈበት ነው በማለት በወንጀል ሥነ-ሥርዓት 191/4 መሠረት ወስነናል፡፡
3. አመልካች ያቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ጊዜው ያላላፈበት በመሆኑ ይህ ውሳኔ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በሚቆጠር አሥር ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለሚመለከተው ፍ/ቤት ያቅርብ ብለናል፡፡

መዝገበ ተዘግቷል፡፡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ብ/ይ

የሰ/መ/ቁ. 122766

ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡-ብርሃኑ አመነው

በእውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አቶ ሄኖክ ብሩክ አረጋ ጠበቃ እንዳለ ክፍሌ

ተጠሪ፡-ፌዴራል ዓ/ህግ  መሰረት ሙላቱ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ወንጀል ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ የመሠረተው የወንጀል ክስ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወ/ህ/አንቀጽ 539(1(ሐ)) ስር የተመለከተውን በመተላለፍ ተከሳሽ የፈፀመው የአስገድዶመድፈር ሙከራ ወንጀል እንዳይገለፅበት ለማድረግ አስቦ ጥር 14 ቀን 2005 ዓ/ም በግምት ከጠዋቱ 2፡50 ሲሆን በን/ላ/ክ/ከ/ቀበሌ 12/13 ልዩ ቦታው ሽገር ማህበር ተብሎ ከሚጠራው አካባቢ ከሚገኘው የመኖሪያ ቤት ውስጥ ሟች መዝገበ ክበበው ወይም አባቷ ባወጣላት ስሟ አለምፀሃይ ብሩክ የተባለችው እድሜዋ 13 አመት የሆነችውን ህፃን አስገድዶ መድፈር ሙከራ ወንጀል ከፈፀመባት በኋላ ሟች የፈፀመባትን ድርጊት ለአባትህ እነግርልሃለሁ ስትለው በመጀመሪያ አንገቷን ካነቃት በኋላእጀታው እንጨት በሆነ ቢላዋጨካኝነቱን በሚያሳይ ሁኔታ አንገቷን አርዶ በመግደሉ ክስ የቀረበበት ሲሆን ሁለተኛው ክስየወንጀል ህግ አንቀፅ 27/620(2(ሀ))የተመለከተውን ተላልፎ በአንደኛው ክስ በተጠቀሰው ጊዜና ቦታ ከግል ተበዳይ ጋር የግብረስጋ ግንኙነት ለመፈፀም አስቦየግል ተበዳይ እድሜዋ 13አመት የሆነችውን ህፃን በእጁ አፍኗት ወለል ላይ ወድቃ ራሷን እንድትስት ካደረጋት በኋላ ለብሳው የነበረው ቱታና ፓንት አንድ ላይ በማውለቅ የግብረስጋ ግንኙነት ሊፈፅምባት ሲል  ቆሞ የነበረው ብልቱ በመቀዝቀዙ ፣አመልካች በቀኝ እጁ  ጣት

ብልቷን በመነካካት የግብረስጋ ግንኙነት ለመፈፀም የሞከረ በመሆኑ 18 አመት ባልሞላት ህፃን ላይ አስገድዶ መድፈር ሙከራ ፈፅሟል በሚል ክስ ቀርቦበታል፡፡ ሶስተኛው ክስ የወንጀል ህግ አንቀፅ 654 የተመለከተው በመተላለፍ በአንደኛው ክስ በተገለፀው ጊዜና ስፍራ የአጉቱ ልጅ ለሆነችውየግል ተበዳይ ጋር የግብረስጋ ግንኙነት ለማድረግ መሞከርወንጀል ተከሷል በማለት ክስ አቅርቧል፡፡

አመልካች በዓቃቤ ሕግ የቀረበበትን ሶስት ክሶች በጠበቃው እየታገዘ ተቃውሞ አቅርቦበብይን ከታለፈ በኂላ ስለድርጊቱ ሲጠየቅ ድርጊቱን እንደፈፀመ አምኖ ድርጊቱን ሲፈፅም ራሴን ስቼ ስለነበር ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት በመከራከሩ ማስረጃዎች ቀረበው ከተሰሙ በኂላ ሶስተኛው ክስ በተመለከተአመልካችና የግል ተበዳይ (ሟች) የስጋ ዝምድና ያላቸው ስለመሆኑ ዓ/ህግ አላስረዳም በማለት አመልካች በአንደኛና ሁለተኛው ክሶች ፍርድቤቱ እንዲከላከሉ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡መከለከያ ምስክር አቅርቦም አሰምቷል፡፡ፍ/ቤቱ የተከሳሽ መከላከያ ማስረጃ የዓ/ቃቤ ሕግ ክስና ማስረጃ ማስተባበል ያለቻሉ በመሆናቸው አመልካች በተከሰሰበት ሁለቱም የሕግ አንቀፆች ሥር ጥፋተኛ ተብሎዋል፡፡ በቅጣት ረገድም የግራ ቀኙ የቅጣት አስተያየት እና የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 መሰረት በማድረግ የወንጀሉ ደረጃ እና መነሻ ቅጣት እርከን በመለየት ተከሳሹ ሁለት የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ቀርቦበት፣ሁለት ቅጣት ማቅለያ ምክንያት የተያዙለት በመሆኑ፣ ምክንቶቹ እርስበርሳቸው የሚዋዋጡ በመሆኑ ከተያዘው መነሻ ቅጣት ከፍ ወይም ዝቅ የሚልበት ምክንያት አልተገኘም በማለት አመልካችን በእድሚ ልክ ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይህን ዉሳኔ በመቃወም ይግባኝ ቅሬታው ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ቢሆንም ቅሬታው ባለመቀበል ሰርዞታል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበው የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት የጥፋተኝነት እና የቅጣት ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረበው ቅሬታ መሰረታዊ ይዘት ወንጀሉ የተፈፀው በነበረኝ የመንፈስ ጭንቀት በድንገተኛ አጋጣሚ አእምሮየን ስቼ እያለሁ የተፈፀመ እንጂ ቂም በቀልበመያዝ ወይም ወንጀል ለመፈፀም አስቤና ተዘጋጅቼ በጨካኝነት የፈፀምኩት ባለመሆኑ ዓ/ህግ ክስ ሲያቀርብ ተገድጄ በሰጠሁት እምነት ቃል ተመስርቶ እንጂ በሌላ ማስረጃ የተደገፈ ባለመሆኑ የተጠቀሰብኝ የህግ አንቀፅና የወንጀል ዝርዝሩ ተጣጥሞ ክሱ በወንጀል ህግ አንቀፅ 540(1)ማቅረብ ነበረበት፡፡ ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ የነበረውእድሜዬ 16 አመት እንጂ 19 አመት አልነበረም፡፡የወንጀል ድርጊቱን ከመፈፀሜ በፊት የመንፈስ ጭንቀት በፈጠረብኝ ምክንያት የአእምሮ ችግር ያለብኝ መሆኑ በስርፍርድ ቤት አመልክቼ ሳይታይ ታልፎየተሰጠው ውሳኔ ነው በማለት እንዲታረምለት ጠይቀዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በሰጠው መልስ አመልካች የአእምሮ በሽተኛ

መሆኑ ያቀረበው ማስረጃ የለም ፡፡ አመልካች ድርጊቱ በተፈፀመበት ጊዜ እድሜው 19 አመት ስለመሆኑ በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የቀረበው ማስረጃ ተረጋግጧል፡፡ ቅጣት በተመለከተ የቅጣት መነሻው እርከን 39 ከተያዘ በኋላ በማንዋሉ መሰረት ለእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ሶስት እርከን ቢቀነስ ተቃውሞ የለንም በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመከለተው ሲሆን እኛም በክርክሩ እልባት ማግኘት የሚገባው፡-

1. በአመልካቹ ላይ የተሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አለ ወይስ የለም?

2. በአመልካች ላይ በበታች ፍርድ ቤቶች የተሰጠው የቅጣት ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት አለበት? ወይስ የለበትም?

የሚሉ ነጥቦች መሆናቸውን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከእነዚሁ ነጥቦች አንፃር መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ፡- አመልካች የእምነት ክደት ቃል ሲጠየቅድርጊቱን እንደፈፀመ አምኖ ድርጊቱን ሲፈፅም ራሴን ስቼ ስለነበር ጥፋተኛ አይደለሁም በማለት ቃሉን ያስመዘገበ ቢሆንም በወቅቱ በስር ተከሳሽ የሚያቋቋም ነው ተብሎ ጥፋተኛ የተባለበት በቀረቡት የዓ/ህግ ማስረጃ አመልካች ሟችን በግፍ የገደላት ስለመሆኑ እንዲሁም አስገድዶ ለመድፈር የሞከረ ስለመሆኑ፣የአመልካች እድሜ በሚመለከትምየቀረበው የሃኪም ማስረጃ ወንጀሉ በተፈፀመበት ጊዜ አመልካች እድሜ 19 አመት የነበረ ስለመሆኑ፣በወቅቱ የአእምሮ ችግርነበረኝ በማለት የተከራከረ ቢሆንም ወንጀሉ ሲፈፅም የአእምሮ ችግር የነበረበት ስለመሆኑ በህግ አግባብ ተደግፎ የቀረበ ምንም አይነት ማስረጃ አለመኖሩ ተረጋግጦና የአመልካች የመከላከያ ማስረጃዎችአመልካች ድርጊቱን ስላለመፈፀሙየምስክሮቹ ቃል ያረጋገጣል ሊያስብል የሚችል አለመሆኑን ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡

እንግዲህ የበታች ፍርድ ቤቶች አመልካች ድርጊቱን ፈፀመ በማለት ድምዳሜ የደረሱትየአመልካች ድርጊቱን ስለመፈፀሙ የአቃቤሕግ ምስክሮች በሚገባ ተረጋግጧል፣አመልካች በመከላከያ ማስረጃው አልተደገፉም በሚል ምክንያት ነው፡፡አመልካች ከሚከራከርባቸው ነጥቦች ውስጥ የአመልካችን የድርጊት ፈጻሚነት በተገቢው መንገድ አቃቤ ሕግ በማስረጃ ያለማስደገፉንና የአቃቤ ሕግ ማስረጃዎችን አመልካች በመከላከያ ምስክሮች የማስተባበላቸው ሁኔታን የሚመለከቱ ነጥቦች የሚገኙ ሲሆን የበታች ፍርድ ቤቶች በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 141 ስር የተመለከተውን የማስረጃ

ምዘና መርህ ተከትለው አመልካችን ጥፋተኛ ያደረጉ ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት የሚያሳየን ሁኖ አግኝተነዋል፡፡በመሆኑም ከዚሁ የበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መገንዘብ የሚቻለው አመልካች ጥፋተኛ የተባለው በጉዳዩ ላይ የቀረቡት ማስረጃዎቸ ተመዝነው መሆኑን ነው፡፡እንደሚታወቀው ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት አንድ የመጨረሻ ፍርድ ያገኘን ጉዳይ ማረም የሚችለው በውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት መኖሩ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3(ሀ)) እና አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ተመልክቷል፡፡ከእነዚህ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው ደግሞ ይህ ሰበር ችሎት ፍሬ ነገርን የማጣራት ወይም ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የሌለው መሆኑን ነው፡፡በተያዘው ጉዳይም አመልካች አጥብቆየሚከራከርባቸው ነጥቦች የመሰረታዊ ሕግ ስህተት መመዘኛን መሰረት ያደረጉ ሳይሆን የፍሬ ነገርንና የማስረጃ ምዘናን መሰረት ያደረጉ በመሆናቸው በዚህ ችሎት ሊታዩ የሚችሉ ሁነው አላገኘናቸውም፡፡

በመሆኑም አመልካች የአቃቤ ሕግማስረጃዎች በመከላከያ ማሰረጃቸው ባላስተባበሉበት ሁኔታ ወንጀል ለመፈፀሜ አልተረጋገጠም በማለት የሚያቀርበው ቅሬታና ክርክር የሕግ መሰረት ያለው ሁኖ አልተገኘም፡፡አመልካች ለድርጊቱ ኃላፊነት አለበት ተብሎ የተወሰነው ወንጀሉ መሰራቱ ወይም መፈጸሙና ተሰራ ወይም ተፈጸመ የተባለው ወንጀል ደግሞ በአመልካች መፈጸሙ በበቂና በአሳማኝ ሁኔታ ፍሬ ነገርን የማጣራትና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች በተረጋገጠበት ሁኔታ በመሆኑና ይህም በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 23(4)፣27(1(ሀ)፣620(2(ሀ))፣58 እና 539(1(ሐ)) ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ የሚያሟላ በመሆኑ በዚህ ረገድ የቀረበውን ክርክር የምንቀበለው ሁኖ አላገኘነውም፡፡

ሁለተኛው ነጥብ፡- ቅጣትን መሰረት አድርጎ ወደቀረበውና በአቢይ ጭብጥነት ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም የአመልካች መሠረታዊ ክርክር የበታች ፍርድ ቤቶች ያስተላለፉት የእድሜ ልክ ፅኑ እስራት ቅጣት ውሳኔ የቅጣት አወሣሠን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ያስቀመጣቸውን መርሆዎች ያላገናዘበ ነው የሚል ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ቅጣት ሲወስኑ አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት ሁለት ድንጋጌዎች ውስጥ ለወንጀል ህግ ዓንቀፅ 539(1(ሐ))ከባድ የግፍ መግደል ወንጀል የእድሜልክ ፅኑ እስራት በመውሰድ ፣ ለሁለተኛው ክስ አስገድዶ መድፈር ወንጀል ሙከራ በ15 አመት ፅኑ እስራት የመነሻ ቅጣት እንዲቀጣ ከወሰነ በኂላ በተከሳሽ ላይ ሁለቱም ክሶች የተወሰነበት ቅጣት በወንጀል ህግ አንቀፅ 184(1(ለ)) ሲደመሩ በህጉ ከተወሰነው ከፍተኛ ቅጣት የሚበልጥ ሆኖ ስላገኘው በአንደኛው ክስ የተወሰነው እድሜ ልክ ፅኑ እስራት የሚጠቃለል በመሆኑ ለሁለቱም የህግ ድንጋጌዎች ይህንኑ መነሻ ቅጣት መወሰኑ መዝገቡ ያመለክታል፡፡ ፍርድ ቤቱ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት ቅጣት የወሰነ መሆኑ በመግለፅ የመጨረሻ ቅጣት ሲያስቀምጥም በከሳሽ ዓ/ህግ በኩል የቀረበ ሁለት ቅጣት ማክበጃዎች እንዲሁም በአመልካች

በኩል የቀረበና ፍርድ ቤቱ የተቀበላቸው ሁለት የቅጣት ማቅለያዎች እንደተቀበለ በመግለፅ የእድሜ ልክ ፅኑ እስራትአመልካች እንዲቀጣውሳኔ ሰጥቷል፡፡ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች ያቀረበው ይግባኝ ሲያፀና የስር ፍርድ ቤት ቅጣቱን ከመመሪያው በመውጣት መወሰን የነበረበት መሆኑ በመግለፅ ያፀና መሆኑ ከቀረበው የመዝገብ ግልባጭ ለመረዳት ችለናል፡፡

በመሠረቱ የወንጀል ህግ አንቀጽ 187 ድንጋጌ የሚወሰነው ቅጣት ከወንጀል ሕጉ አላማና ግብ ጋር በተጣጣመ መልኩ የጥፋቱን ከባድነት በማመዛዘን በድንጋጌዉ ከተወሰነዉ የቅጣት ጣራ ሳያልፍ ቅጣት ሊወስን እንደሚገባ ተደንግጓል፡፡እንዲሁም መመሪያው በወንጀል ሕጉ ስለቅጣት አወሳሰን ከተደገጉት ድንጋጌዎች ጋር ተጣጥሞ መተርጎም እንደሚገባው በአንቀጽ 4(9) ስር ተመልክቷል፡፡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፓብሊክ የወንጀል ህግ የአገሪቱን የወንጀል ህግ ግብ በአዋጅ ቁጥር 414/1996 አንቀጽ 1 ስር ሲደነግግ “የወንጀል ህግ ግብ ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን ይህንን የሚያደርገው ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት፣ ማስጠንቀቂያነቱ በቂ ባልሆነበት ጊዜ ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ሌላ ወንጀል ከመፈፀም እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰዱባቸው በማድረግ ነው” በማለት ያስቀምጣል፡፡ ህጉ በአንቀጽ 87 ላይ ቅጣቶችና የጥንቃቄ እርምጃዎች ህጉ ሊደርስበት ያሠበውን ዓላማ ለማረጋገጥ በሚቻልበት ሁኔታ በህጉ መንፈስ መሠረት መፈፀም እንዳለባቸው በመርህ ደረጃ ይደነግጋል፡፡ የወንጀል ህጉ አንቀጽ 88 ሲታይም የቅጣቶች እና የጥንቃቄ እርምጃዎች አወሣሠንን በተመለከተ ዘርዘር ያሉ ንዑስ ድንጋጌዎችን አካቶ ይዟል፡፡ በዚህ አንቀጽ ስር ያሉ ንዑስ አንቀጾች የሚያሣዩት ፍርድ ቤቱ ቅጣቶችንና የጥንቃቄ እርምጃዎችን የሚወስነው የወንጀል ህጉን ጠቅላላ ክፍል ድንጋጌዎችን እንዲሁም ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው የሚደነግጉትን የልዩ ክፍሉ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ መሆኑን፣ ቅጣት ሊወሰን የሚገባው የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኛነት መጠን ያለፈ የህይወት ታሪኩን ወንጀል ለማድረግ ያነሣሡትን ምክንያቶችና የአሣቡን ዓላማ የግል ኑሮውን ሁኔታ፣ የትምህርቱን ደረጃ፣ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነትና የአፈፃፀሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን መሆኑን፣ የወንጀል ህግ ልዩ ክፍል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ፍርድ ቤቱ እጅግ ቀላል ከሆነው ቅጣት አንስቶ እስከ ከባዱ ድረስ ያለውን በጥንቃቄ በመመርመር ለእያንዳንዱ ጉዳይ ተገቢ የሆነውን ቅጣት እንደሚወስን የቅጣት አወሳሳን ደንቡ በግልፅ ያሳያል፡፡ከላይ እንደተገለጸው ቅጣት የሚወሰነው በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 88(2) ስር የተመለከቱትን ሁኔታዎችን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው፡፡

የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ደረጃ ላልወጣላቸው የወንጀል ድንጋጌዎች ደረጃ የሚወጣበትን አግባብ በመመሪያው በአንቀጽ 13 ከማስቀመጡ በተጨማሪ በ አንቀጽ 21/1/ መሠረት የወንጀል አፈጻጸሙ ሆነ ባህሪዉ በቅጣት አወሳሰን መመሪያዉ መሠረት ለመወሰን የማያስችል ሆኖ ሲገኝ ወይም ቅጣቱ ፍትሕን የሚያዛባ ነዉ ብሎ ፍ/ቤቱ ካመነ መመሪያዉን ተግባራዊ ለማድረግ ያልቻለበትን ምክንያት በዝርዝር በማስቀመጥ በመመሪያዉ ላይ ከተቀመጠዉ በተለየ መልኩ ቅጣት ሊወስን ይችላል በማለት አስቀምጧል፡፡ ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ አመልካች በስር ፍርድ ቤት ጥፋተኛ የተባለበት ሁለት የህግ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ እነሱም የወንጀል ህግ ዓንቀፅ 539(1(ሐ)) ተከሳሽ የራሱ ክፉ ስራ እንዳይገለፅ በማሰብ እድሜዋ 13 አመት የሆነችውን ህፃን አሰቃቂ በሆነ ሁኔታ አንገትዋን አርዶ መግደሉ ለዚሁ ወንጀል መነሻ ቅጣቱ እድሜ ልክ ፅኑ እስራት ወይም ሞት ቅጣት መሆኑ፣ የወንጀል ህግ ዓንቀፅ 620(2(ሀ))ደግሞ እድሜዋ አስራ ሶስት አመት በሆናት ህፃን ልጅ ላይ የተፈፀመ በመሆኑ ቅጣቱ ከአምስት አመት እስከ ሃያ አመት ለመድረስ በሚችል ፅኑ እስራት የሚያስቀጣ በመሆኑ እነዚህ ሁለት የተለያዩ ወንጀሎች የፈፀመው አመልካች ላይ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 መሰረት ቅጣት ለመወሰን በወንጀል ህግ አንቀፅ 184(1(ለ)) መደመር የግድ ይላል፡፡

የስር ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ቅጣት ሲወስን አመልካች ጥፋተኛ የተባለበት ሁለት ድንጋጌዎች ለወንጀል ህግ ዓንቀፅ 539(1(ሐ))ከባድ የግፍ መግደል ወንጀል የእድሜ ልክ ፅኑ እስራት በመውሰድ ለሁለተኛው ክስ አስገድዶ መድፈር ወንጀል ሙከራ በ15 አመት ፅኑ እስራት የመነሻ ቅጣት እንዲቀጣ ከወሰነ በኋላ በተከሳሽ ላይ ሁለቱም ክሶች የተወሰነበት ቅጣት በወንጀል ህግ አንቀፅ 184(1(ለ))ሲደመር በህጉ ከተወሰነው ከፍተኛ ቅጣት የሚበልጥ ሆኖ ስላገኘው በአንደኛው ክስ የተወሰነው እድሜ ልክ ፅኑ እስራት የሚጠቃለል በመሆኑ ለሁለቱም የህግ ድንጋጌዎች ይህንኑ መነሻ ቅጣት ይዟል፡፡በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 መሰረት የቅጣቱን ለማስላት የተያዘው የመነሻቅጣት በመመሪያው አባሪ አንድ ላይእርከን 38 ላይ የሚያርፍ ሲሆን ፍርድ ቤቱ በተቀበላቸው ሁለት ማክበጃ ምክንያቶት ሁለት እርከን ስለሚጨምር እና መመሪያው አባሪ አንድ እስከ እርከን 39 ብቻ እንጂ ከዚህ በላይ እርከን አርባ አልተቀመጠም፡፡

ስለሆነምአመልካች ጥፋተኛ የተባለበት ሁለት ድንጋጌዎች በወንጀል ህግ አንቀፅ 184(1(ለ)) ሲደመር በህጉ ከተወሰነው ከፍተኛ ቅጣት የሚበልጥ ሆኖ በመገኘቱ ፣ በአንደኛው ክስ የተወሰነው እድሜ ልክ ፅኑ እስራት የተጠቃለለ ከመሆኑ በተጨማሪ ቅጣቱ ሲሰላ በቀረቡት ሁለት የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች በመመሪያው ከተቀመጠው እርከን በላይ ስለሚሆን ይህንን ጉዳይ የወንጀል አፈጻጸሙ ሆነ ባህሪዉ እንዲሁም ከተፈፀመው ወንጀል ክብደት አንፃር ፍትሃዊ ውሳኔ ለመስጠት በቅጣት አወሳሰን መመሪያዉ መሠረት ለመወሰን የማያስችል በመሆኑ ከላይ በተገለፁት

ምክንያቶች መነሻነት የያዝነው ጉዳይ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሰረት ሲወሰን ለተፈፀመው ወንጀል ተመጣጣኝ ቅጣት ለመወሰን ስለማይቻል፤የሚሠጠው ቅጣትአመልካች የፈፀማቸው ሁለት ከባድ ወንጀሎች በመሆናቸው፣ፍትህን ስለሚያዛባእንዲሁም ስለወንጀል ህጉ ግብና አላማ የማያሳካ ስለሚሆን በቅጣት አወሳሰን መመሪያ አንቀጽ 21/1/ መሠረት ከቅጣት አወሳሰን መመሪያው ውጪ ሊወሰን የሚገባ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ በተገለፀው ምክንያት መነሻነትየስር ፍርድ ቤት የቀረበለት ጉዳይ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ መሠረት ሊሰላ የማይቻል ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ ውጪ በመውጣት የቅጣት ውሳኔው መወሰን ሲገባው የሰጠው የቅጣት ውሳኔ በመሆኑ ሊስተካከል የሚገባው ነው ብለናል፡፡ስለሆነም አመልካች ጥፋተኛ ለተባለበትየህግ ድንጋጌዎች፡-የአስገድዶ መድፈር ሙከራ ተግባር የተፈፀመው እድሜዋ አስራ ሶስት አመት በሆናት ህፃን ልጅ ላይ በመሆኑ ፣ እንዲሁም አመልካች የራሱ ክፉ ስራ እንዳይገለፅ በማሰብ እድሜዋ 13 አመት የሆነችውን ህፃን አሰቃቂ በሆነ ሁኔታ አንገትዋንካነቃት በኋላ እጀታው እንጨት በሆነ ቢላ አንገትዋን አርዶ መግደሉጨካኝነት እና ነውረኝነቱን የሚያሳይ ተግባር ነው፡፡ አንድ ሰው በወንጀል ጥፋተኛ ሁኖ ከተገኘ ተገቢውን ቅጣት ማግኘት ያለበት ስለሆነ የሚጣለው ቅጣት የወንጀሉን ከባድነትና የአፈፃፀሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን መሆኑን የወንጀል ህጉ አላማ የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡አመልካች ባቀረባቸው ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 አንቀፅ 16(8) መሰረት ለእያንዳንዳቸው ሶስት እርከን ጠቅላላ ስድስት እርከን እንዲቀንስለት ቅሬታ አቅርቧል፡፡ይሁን እንጂ የተፈፀሙት ሁለት ወንጀሎች ፤የወንጀል አፈጻጸማቸው ሆነ ባህሪዉ እንዲሁም ከተፈፀመው የወንጀል ክብደት አንፃር ፍትሃዊ ውሳኔ ለመስጠት በቅጣት አወሳሰን መመሪያዉ መሠረት ለመወሰን የማያስችል በመሆኑ ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ ውጪ ቅጣቱ እንዲወሰን ድምዳሜ ላይ የተደረሰ ስለሆነ የአመልካች አቤቱታ አልተቀበልነውም፡፡ ስለሆነም በቅጣት ማክበጃነትና ማቅለያነት በማስረጃና በሕግ የተደገፉና በችሎት ተቀባይነት ያገኙትን ግንዛቤ ዉስጥ በማስገባትና በማመዛዘን ፍትሐዊ ቅጣት ሊወሰን ስለሚገባ የስር ፍርድ ቤት አመልካች ላይ የወሰነው የእድሜ ልክ ፅኑ እስራት ቅጣት አመልካች እንዲቀጣ መወሰኑን አመልካች ለፈፀማቸው ወንጀሎት ተመጣጣኝ ቅጣት ስለሚሆን ሌላው ህብረተሰብም የሚያስተምር በመሆኑ በአመልካች ላይ የተወሰነው ቅጣት በውጤት ደረጃ የወንጀል ህጉ መሰረታዊ መርሆዎችን ያልተከተለ ነው ለማለት የሚቻል ሁኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም ፍርድ ቤቶች በተከሳሽ ላይ የሚጣለው ቅጣት የወንጀል አፈጻጸሙ ሆነ ባህሪዉ እንዲሁም ከተፈፀመው ወንጀል ክብደት አንፃር ፍትሃዊ ውሳኔ ለመስጠት በቅጣት አወሳሰን መመሪያዉ መሠረት ለመወሰን የማያስችል ሆኖ በተገኘ ጊዜ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሰረት ምክንያቱ በማስቀመጥ በመመሪያው ከተቀመጠው በተለየ መልኩ ቅጣት ሊወስኑ ይችላሉ፡፡

ሲጠቃለልም በአመልካች ላይ የተሠጠው የጥፋተኝነትና የተጣለው የእድሜልክ ፅኑ እስራት ቅጣት ውሳኔ የወንጀል ሕጉን መሰረታዊ ግብ እንዲሁም የቅጣት አወሳሳን መርሆዎች ከድርጊቱ አፈጻፀም ጋር ያገናዘበ በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ስላልተቻለ ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 131521 ግንቦት 24 ቀን 2007 ዓ/ም የሰጠው የጥፋተኝነት ውሳኔ እንዲሁም ሰኔ05ቀን 2007 ዓ/ምየሰጠውየቅጣት ውሳኔ ፣ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 115002 ታህሳስ 13 ቀን 2008 ዓ.ም የጸናው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 195(2)(ለ-2) መሠረት በአብላጫ ድምፅ ጸንቷል፡፡

2. አመልካች በእድሜ ልክፅኑ እስራት እንዲቀጣ ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡

3. የበታች ፍርድ ቤቶች የተሠጠው ውሳኔ የፀና መሆኑን እንዲያውቀው ለክፍሉ ማረሚያ ቤት ይፃፍ ብለናል፡፡

4. ይህ ውሳኔ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 አንቀፅ 21(1) መሰረት መመሪው ከሚያስቀምጠው በተለየ ከመመርያው በመውጣት የቅጣት ውሳኔ የተሰጠ በመሆኑ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ አንቀፅ 21(2) መሰረት ለሚመለከተው አካል እንዲያውቀው ይደረግ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሩ/ለ

## የልዩነት ሐሳብ

ስሜ በተ.ቁ 5 የተሰየመው ዳኛ አብላጫው ድምጽ በአመልካች ላይ የተላለፈውን የቅጣት ውሳኔ አስመልክቶ በሰጠው የሕግ ትርጉም እና በደረሰበት መደምደሚያ ስላልተስማማሁ በሐሳብ ተለይቻለሁ፡፡አብላጫው ድምጽ አመልካች ለፈጸመው የወንጀል ድርጊት ፍትሐዊ የቅጣት ውሳኔ ለመስጠት ቅጣቱን በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሠረት ለመወሰን የማያስችል በመሆኑ

ቅጣቱን ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ ውጪ እንዲወሰን ድምዳሜ ላይ የተደረሰ በመሆኑ የአመልካች አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ከሚል መደምደሚያ ላይ ሊደርስ የቻለው ፍ/ቤቱ ከወንጀል አፈጻጸሙም ሆነ ባሕርይው በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሠረት ለመወሰን የማያስችል ሆኖ ሲገኘው ወይም ቅጣቱ ፍትሕን የሚያዛባ ነው ብሎ ካመነ መመሪያውን ተግባራዊ ያላደረገበትን ምክንያት በዝርዝር በማስቀመጥ ከመመሪያው ወጥቶ ቅጣት ሊወስን እንደሚችል የሚደነግግ በመሆኑ፣አመልካች ለፈጸማቸው ሁለት ከባድ ወንጀሎች ቅጣት ለመወሰን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184/1/ለ ድንጋጌ መሠረት መደመር የሚያስፈልግ እና የሁለቱም ወንጀሎች መነሻ ቅጣት ሲደመር በሕጉ ከተወሰነው ከፍተኛ ቅጣት የሚበልጥ ሆኖ በመገኘቱ የሥር ፍ/ቤት መነሻ ቅጣቱን በአንደኛው ክስ የተወሰነውን የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት የያዘ በመሆኑ፣በአመልካች ላይ ተቀባይነት ያገኙ ሁለት የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች ያሉ ቢሆንም በመመሪያው ላይ እርከን 40 የሌለ በመሆኑ፣ቅጣቱ ሲሰላ በመመሪያው ከተቀመጠው እርከን በላይ የሚሆን በመሆኑ፣አመልካች አሰቃቂ ወንጀል የፈጸመ በመሆኑ እና ድርጊቱም የተፈጸመው ዕድሜዋ 13 ዓመት በሆናት ሕጻን ላይ ነው በማለት ነው፡፡

በመሠረቱ አንድ አቤቱታ አቅራቢ የይግባኝ ወይም የሰበር አቤቱታ የሚያቀርበው በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ሕግን መሠረት በማድረግ ያልተሰጠ ውሳኔ ስለሆነ ሊታረም ይገባል ከሚል መነሻ እንደሆነ የይግባኝ ወይም የሰበር ሥርዓት ከተዘረጋበት ዓላማ መገንዘብ ይቻላል፡፡በዚሁ አግባብ የቀረበውን አቤቱታ የሚመረምረው የበላይ የሆነው ፍ/ቤት የአቤት ባዩን አቤቱታ ከተገቢው ሕግ ጋር በማገናዘብ በአቤት ባዩ ላይ የተሰጠውን ፍርድ ሊያጸና፣ሊያሻሽል ወይም ሊሽር ከሚችል በቀር አቤት ባዩ ባስከፈተው የይግባኝ ወይም የሰበር መዝገብ  ላይ በአቤት ባዩ ላይ የተሰጠውን ፍርድ ሊያከብድ የሚችል የፍርድ ትችት መስጠት አይጠበቅበትም፡፡በተያዘው ጉዳይ የሥር ፍ/ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 01/2002 አመልካችን የሚጠቅም በመሆኑ በዚሁ መመሪያ መሠረት ቅጣቱ ተሰልቷል በማለት በቅጣት ውሳኔው ላይ የገለጸ ቢሆንም አመልካች ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ያሉኝ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት መመሪያው በሚፈቅደው መሠረት ለእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ሦስት ሦስት እርከን መቀነስ ሲገባው አንድ አንድ እርከን ብቻ በመቀነስ የሰጠው ውሳኔ መመሪያውን ያላገናዘበ ነው በማለት የይግባኝ አቤቱታ ባቀረበበት ሁኔታ፣ተጠሪ በሰጠው መልስ አመልካች ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ያሉት በመሆኑ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሠረት ለእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ሦስት እርከን ለሁለቱም የቅጣት ማቅለያዎች ሥድሥት እርከን ተቀንሶ ቅጣቱ ቢወሰን ተቃውሞ የለኝም በማለት መልስ በሰጠበት ሁኔታ አብላጫው ድምጽ አመልካች ባስከፈተው የሰበር አቤቱታ / በአመልካች መዝገብ / ላይ በአመልካች የወንጀል አፈጻጸም እና በግል ተበዳይ ዕድሜ ምክንያት

በመመሪያው መሠረት ቅጣቱ ቢወሰን ፍትሕ የሚዛባ በመሆኑ ቅጣቱ ከመመሪያው ውጪ ሊወሰን ይገባል በማለት በደረሰበት መደምደሚያ አልተስማማሁም፡፡

አብላጫው ድምጽ ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ ውጪ ቅጣቱ እንዲወሰን ድምዳሜ ላይ ተደርሷል ለማለት አመልካች ድርጊቱን የፈጸመው ዕድሜዋ 13 ዓመት በሆናት ሕጻን ላይ ነው፤የወንጀል አፈጻጸሙ እና ባሕርይው ከባድ ነው በማለት ምክንያት ሰጥቷል፡፡በእርግጥ አመልካች የፈጸመው ወንጀል አሰቃቂ ወንጀል ለመሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ሆኖም የተበዳይን ዕድሜ መሠረት በማድረግ አመልካች ከመነሻውም ቢሆን በከባድ ወንጀል /aggravated crime/ የተከሰሰ ሆኖ ሳለ አብላጫው ድምጽ በግል ተበዳይ ዕድሜ እና በድርጊት አፈጻጸሙ ምክንያት ቅጣቱ ከመመሪያው ውጪ ሊወሰን ይገባል በማለት በደረሰበት መደምደሚያ አልተስማማሁም፡፡

አብላጫው ድምጽ ከቅጣት አወሳሰን መመሪያ ውጪ ቅጣቱ እንዲወሰን ድምዳሜ ላይ ተደርሷል ለማለት የሰጠው ሌላ ምክንያት አመልካች ለፈጸማቸው ሁለት ከባድ ወንጀሎች ቅጣት ለመወሰን በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184/1/ለ ድንጋጌ መሠረት መደመር የሚያስፈልግ እና የሁለቱም ወንጀሎች መነሻ ቅጣት ሲደመር በሕጉ ከተወሰነው ከፍተኛ ቅጣት የሚበልጥ ሆኖ በመገኘቱ በአንደኛው ክስ የተወሰነውን የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት መነሻ ሆኖ የተያዘ ቢሆንም ፍ/ቤቱ የተቀበላቸውን ሁለት  የቅጣት ማክበጃ ምክንያቶች መሠረት በማድረግ ቅጣቱን ለማክበድ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው ላይ እርከን 40 ስለሌለ አመልካች ከፈጸመው ድርጊት አኳያ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሠረት መወሰን ፍትሕን ያዛባል የሚል ነው፡፡ሆኖም የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 184/1(ሀ)እና(ለ) ድንጋጌ ተደራራቢ ወንጀሎች በአንደኛው ምክንያት የሞት ወይም የዕድሜ ልክ እሥራት ወይም ወንጀሎቹ ተመሣሣይ ዓይነት የእሥራት ቅጣት የሚያስቀጡ ሆኖ በአንደኛው ምክንያት በሕጉ ጠቅላላ ክፍል የተቀመጠው ከፍተኛ ቅጣት ሲወሰን ይህ ውሳኔ ለሌሎቹም ተደራራቢ ወንጀሎች የሚወሰነውን ቅጣት ሁሉ አጠቃሎ እንደሚይዝ፤ተደራራቢ ወንጀሎች ተፈጽመው በተገኙ ጊዜ በተደራራቢነት ለተፈጸመው ወንጀል ተገቢ የሆነ ቅጣት ተወስኖ የሚደመር እና ቅጣቱ በሕጉ ጠቅላላ ክፍል ከተቀመጠው ቅጣት መብለጥ እንደማይችል ይደነግጋል፡፡በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 01/2002 ተደራራቢ ወንጀሎችን በተመለከተ የተቀመጠው የቅጣት አሰላል በወንጀል ሕጉ ተደራራቢ ወንጀሎችን አስመልክቶ በተቀመጡት ድንጋጌዎች መሠረት የተቀመጠ ሆኖ ሳለ፤መመሪያው ከባድ የሚባሉትን የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት እና የሞት ቅጣት የያዙ እርከኖች ያሉት ሆኖ ሳለ አብላጫው ድምጽ በመመሪያው መሰረት ቅጣቱ ቢወሰን ቅጣቱ የሚደመር እና በመመሪያው ላይ እርከን 40 ያልተቀመጠ በመሆኑ ቅጣቱ ከመመሪያው ውጪ ሊወሰን ይገባል በማለት በደረሰበት መደምደሚያ አልተስማማሁም፡፡

የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 01/2002 ተፈጻሚ ሲሆን በአተገባበር ባጋጠሙ ችግሮች ምክንያት መመሪያውን ማሻሻል በማስፈለጉ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 88/4 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 02/2006 አውጥቷል፡፡የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተቋቋመው በአገሪቱ ውስጥ ወጥ የሆነ የሕግ አተረጓጎም እንዲኖር ለማደረግ እንደሆነ ችሎቱ ከሰጣቸው በርካታ ውሳኔውች እና በተግባር ከሚታየው አሰራር መገንዘብ ይቻላል፡፡በዚሁ መሠረት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የቅጣት አወሳሰን መመሪያን በሚመለከት በሰበር መዝገብ ቁጥር 95438 እና በሌሎች በርካታ መዛግብት የሕገ መንግስቱን አንቀጽ 22 እና የወንጀል ሕጉን አንቀጽ 6 መሠረት በማድረግ ወንጀል ፈጻሚው ድርጊቱን የፈጸመው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ተግባራዊ በነበረበት ጊዜ ከሆነ ቅጣቱ በዚሁ መመሪያ መሠረት ሊወሰን የሚገባ መሆኑን፤አዲሱ የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ተግባራዊ በማድረግ ቅጣት ሊወሰን የሚችለው አዲሱ መመሪያ ተከሳሽን የሚጠቅም በሆነ ጊዜ ብቻ መሆኑን በመግለጽ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/1 መሠረት በየትኛውም እርከን ላይ ለሚገኙ ፍ/ቤቶች አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ይህን የሕግ ትርጉም መሠረት በማድረግም ቀላል፤መካከለኛ እና ከባድ በሆኑ የወንጀል አፈጻጸሞች ላይ በቅጣት አወሳሰን መመሪያ አተገባር ላይ የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ በበርካታ መዝገቦች ላይ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩ በቀጥታ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 01/2002 አመልካችን የሚጠቅም በመሆኑ ቅጣቱ በዚሁ መመሪያ መሠረት ተሰልቷል በማለት በውሳኔው ላይ የገለጸ ቢሆንም ለእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ አንድ እርከን ብቻ በመቀነስ ቅጣቱን ያሰላ በመሆኑ የቅጠት ማቅለያ እርከኖች አሰላል ላይ ቅጣት አወሳሳን መመሪያ ቁጥር 02/2006 መሠረት በማድረግ ውሳኔ እንደሰጠ የሚገመት ነው፡፡አመልካች ድርጊቱን የፈጸመው የቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 ተግባራዊ በነበረበት ጊዜ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት የመመሪያውን ሙሉ ይዘት ተፈጻሚ በማድረግ መወሰን የሚገባው ሆኖ ለአንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት አንድ እርከን ብቻ በመቀነስ ውሳኔ መስጠቱ የቅጣት አወሳሰን መመሪያውን እና ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት በቅጣት አወሳሰን መመሪያ ተግባራዊ በነበረበት ጊዜ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት የመመሪያው ሙሉ ይዘት ተፈጻሚ በማድረግ መወሰን የሚገባው ሆኖ ለአንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት አንድ እርከን ብቻ በመቀነስ ውሳኔ መስጠቱ የቅጣት አወሳሰን መመሪያውን እና ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት በቅጣት አወሳሰን መመሪያ አተገባበር ላይ የሰጠውን አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የሚጥስ በመሆኑ ሊታረም የሚገባው ሆኖ ሳለ አብላጫው ድምጽ ከአመልካች የድርጊት አፈጻጸም፤ከወንጀሉ ባሕርይ እና ከተበዳይ ዕድሜ አኳያ በመመሪያው መሠረት ቢወሰን ፍትሕን ያዛባል በማለት በደረሰበት መደምደሚያ አልተስማማሁም፡፡

በሌላ በኩል የአመልካች ግላዊ ሁኔታ በቅጣት ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ታሳቢ ሊደረግ ስለሚችልበት ሁኔታ በተለያዩ ሕጎች ላይ የተቀመጡትን ድንጋጌዎች መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግሥት አንቀጽ 36/2 ሕጻናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግሥታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጎት ተቋሞች፤በፍ/ቤቶች በአሥተዳደር ባለሥልጣኖች ወይም በሕግ አውጪው አካላት የሕጻናት ደህንነት በቀደምትነት መታሠብ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ኢትዮጲያ የተቀበለችው የሕጻናት መብቶች ሥምምነት አንቀጽ 1 ድንጋጌ ሕጻን ማለት ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆነ ማንኛውም ሰው ነው በማለት ይደነግጋል፤የዚሁ ሥምምነት አንቀጽ 3 በመንግሥት ወይም በግል ማሕበራዊ ደህንነት ተቋሞች በፍርድ ቤቶች በአሥተዳደር ባለሥልጣኖች ወይም በሕግ አውጪ አካላት ሕጻናትን የሚመለከት ማንኛውም እርምጃ ሲወሰድ የሕጻናቱ ጥቅም የሚጠበቅበት ሁኔታ ከሁሉ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ እንደሆነ ይደነግጋል፡፡

ሕገመንግሥቱን መሠረት በማድረግ የወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የወንጀል ሕግ በመግቢያው ላይ አዋጁ እንዲወጣ አስፈላጊ ከሆነባቸው ምክንያቶች ውስጥ በአገሪቱ ሥር ነቀል የሆኑ ለውጦች የተካሔዱ በመሆኑ፤ከእነዚህም ውስጥ የህጻናት እና የሴቶች መብቶች ኢትዮጲያ በተቀበለቻቸው ዓለምዓቀፍ ሥምምነቶች እና በሕገመንግስቱ እውቅና ያገኙ በመሆኑ፤ፍርድ ቤቶች በተመሣሣይ ጉዳዮች ላይ ተመሣሣይ ቅጣት የሚወስኑበትን መንገድ ማመቻቸት አስፈላጊ በመሆኑ፤ወንጀል አድራጊዎችን በመቅጣት ወንጀል እንዳይፈጸም በመከላከል ሕብረተሰቡን መጠበቅ እና ወንጀል ለሚፈጽሙ ሰዎች ማሥጠንቀቂያ መሥጠት እና ትክክለኛ የፍትሕ ሥርዓትን ማስፈን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 176 ከአሥራ አምስት ዓመት በላይ ፤ከአሥራ ሥምንት ዓመት በታች የሆነ ወጣት ወንጀል አድራጊ ወንጀል በሠራ ጊዜ ፍ/ቤቱ በመደበኛው የሕግ ድንጋጌ መሠረት ሲወስን የነገሩ አካባቢ ሁኔታ በቂ ምክንያት የሚያስገኝ መሆኑን የገመተ እንደሆነ በአንቀጽ 179 በተመለከተው ድንጋጌ መሠረት ቅጣት ሊያቀልለት እንደሚችል፤አሥራ ሥምንት ዓመት ሳይሞላው በፈጸመው ማናቸውም ወንጀል ምክንያት የሞት ቅጣት ሊወሰንበት እንደማይችል ይደነግጋል፡፡የወንጀል ሕጉ አንቀጽ 87 ዳኞች ቅጣትን ሲወስኑ ሕጉ ሊደርስበት ያሰበውን ዓላማ ለማረጋገጥ በሚቻልበት ሁኔታ በሕጉ መንፈስ መሠረት መፈጸም ያለባቸው መሆኑን እና ቅጣቶቹ እና የጥንቃቄ እርምጃዎቹ ምንጊዜም ሰብዓዊ ክብርን በሚጠብቅ መንገድ እንዲሆን ማድረግ ሊከተሉት የሚገባ መርህ ስለመሆኑ ይደነግጋል፡፡የዚሁ ሕግ አንቀጽ 88 ድንጋጌም ፍ/ቤቱ ቅጣትን ሲወስን የወንጀል አድራጊውን ግላዊ የአደገኝነት መጠን ያለፈ የሕይወት ታሪኩን፤ወንጀል ለማድረግ ያነሳሱትን ምክንያቶች እና የአሳቡን ዓላማ የግል ኑሮውን ሁኔታ

የትምህርቱን ደረጃ እንዲሁም የወንጀሉን ከባድነት እና የአፈጻጸሙን ሁኔታዎች በማመዛዘን መሆን እንዳለበት ይደነግጋል፡፡

ከላይ ከተገለጹት ድንጋጌዎች አጠቃላይ ይዘት ሕግ አውጪው ዕድሜው ከአሥራ አምሥት ዓመት በላይ፤ከአሥራ ሥምንት ዓመት በታች የሆነ ወጣት ወንጀል አድራጊ ወንጀል በሠራ ጊዜ በሕጉ የተቀመጡት ከባድ የሚባሉ ቅጣቶች እንዲወሰኑበት ፍላጎት የሌለው መሆኑን እና ፍ/ቤቶች በሚሰጡት  የቅጣት ውሳኔ ላይም ጥንቃቄ ሊያደረግ የሚገባቸው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡በተያዘው ጉዳይ አመልካች እድሜዋ 13 ዓመት በሆናት ሕጻን ላይ ወንጀል የፈጸመ ለመሆኑ፤ ድርጊቱንም የፈጸመው አሰቃቂ በሆነ ሁኔታ ለመሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ሆኖም በሥር ፍ/ቤት በማስረጃነት የቀረበው አመልካች በወንጀል ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 27/2 መሠረት ለፖሊስ የሰጠው ቃል አመልካች ድርጊቱን በፈጸመበት ጊዜ የ16 ዓመት ልጅ እና የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ የነበረ መሆኑ ያሳያል፤አመልካች ድርጊቱን ሲፈጽም ዕድሜው 16 ዓመት እንደነበረ የሚያሳይ የልደት ሰርተፍኬት ያቀረበ ሆኖ ሳለ ፤አመልካች ለፖሊስ የሰጠውን ቃል በማስረጃነት የሚወሰደው በአመልካች ላይ የጥፋተኝነት ውሳኔ ለመወሰን ብቻ ሳይሆን ማስረጃው ከነሙሉ ይዘቱ  በማስረጃነት የሚወሰድ ሆኖ ሳለ አብላጫው ድምጽ አመልካች ድርጊቱን ሲፈጽም ዕድሜው 19 ዓመት እንደነበረ በራድዮሎጂ ምርመራ ውጤት የተረጋገጠ መሆኑ ተጠቅሶ በበታች ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ ፍሬነገር ነው በማለት በደረሰበት መደምደሚያ አልተስማማሁም፡፡አመልካች ድርጊቱን ሲፈጽም ዕድሜው 16 ዓመት እንደነበረ ለፖሊስ በሰጠው ቃል ላይ እና ባቀረበው የልደት ሰርተፊኬት የተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች ድርጊቱን ሲፈጽም ዕድሜው 16 ዓመት ነበር፡፡አመልካች ድርጊቱን ሲፈጽም የ16 ዓመት ልጅ እና የዘጠነኛ ክፍል ተማሪ የነበረ በመሆኑ ድርጊቱ የሚያመጣበትን ውጤት ያመዛዝናል ተብሎ የማይጠበቅ በመሆኑ በአመልካች ላይ የተላለፈው የዕድሜልክ ጽኑ እሥራት አመልካች  በሕገመንግሥቱ፤አገሪቱ በተቀበለችው የሕጻናት መብት ሥምምነት እና በወንጀል ሕጉ የተጠበቀለትን መብት መሠረት ያላደረገ ነው በማለት በሐሳብ ተለይቻለሁ፡፡

በአጠቃላይ የሥር ፍ/ቤት ቅጣቱን በመመሪያ ቁጥር 01/2002 መሠረት ያሰላ መሆኑን ገልጾ ተቀባይነት ባገኙ ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች በመመሪያው መሠረት ሦስት ሦስት እርከን በመቀነስ መወሰን ሲገባው ይህን ሳያደርግ በመቅረቱ አመልካች የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲታረም አቤቱታ ባቀረበበት ሁኔታ የሥር ፍ/ቤት የቅጣት ማቅለያ አቀናነስ ላይ የፈጸመው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት ሊታረም ሲገባለው አብላጫው ድምጽ በአመልካች መዝገብ ላይ ከወንጀሉ ባሕርይ፤ከድርጊቱ አፈጻጸም እና ከተበዳይ ዕድሜ አኳያ ከላይ ቅጣቱ ከመመሪያ ውጪ ሊወሰን ይገባል በማለት በደረሰበት መደምደሚያ ከላይ በገለጽኳቸው ምክንያቶች ያልተስማማሁበት

በመሆኑ በሥር ፍ/ቤት ተቀባይነት ባገኙ ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች በመመሪያው መሠረት ለእያንዳንዱ የቅጣት ማቅለያ ሦስት እርከን ለሁለቱም የቅጣት ማቅለያ ስድሥት እርከን ተቀንሶ ቅጣቱ  ሊሰላ ይገባ ነበር በማለት በሐሳብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛፊርማ አለበት፡፡

ሩ/ለ

# አፈፃፀም

የሰ/መ/ቁ. 124618

ሕዳር 22 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

አብዩ ካሳሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡-

1. ወ/ሮ ድባካ መሰለ - ቀረቡ
2. ሀብቱ ሞገስ - ሞግዚት ወ/ሮ ድባካ መሰለ - ቀረቡ
3. የሽወርቅ ሞገስ - ሞግዚት ወ/ሮ ድባካ መሰለ- ቀረቡ

ተጠሪ፡-ሳጅን ኃይሉ ሞገስ - የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍርድ አፈጻጸምን የሚመለከት ክርክር ሲሆን አመልካቾች አቤቱታቸውን ለዚህ ችሎት ያቀረቡትም ለፍርድ አፈጻጸሙ ምክንያት የሆነው መኖሪያ ቤት ክፍፍል መፈጸም የሚገባው በሀራጅ ተሸጦ ነው በሚል በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠውን የአፈጻጸም ትዕዛዝ በፍርድ በማጽናት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 0311349 በ16/06/2008 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ነው፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ በተመለከተ፡-የ1ኛ አመልካች ባለቤት የነበሩት አቶ ሞገስ ጌታሁን በሞት መለየታቸውን ተከትሎ በተነሳው የውርስ እና የጋራ ንብረት ክፍያ ክርክር በዋግኽምራ ዞን በሰቆጣ ከተማ በቀበሌ 02 ክልል በሟች ስም ተመዝግቦ ይታወቅ ከነበረው ቤት ውስጥ ግማሹ የአሁኗ 1ኛ አመልካች ድርሻ ሆኖ ቀሪው ግማሽ ደግሞ ከሟች ለሚወለዱት ሰባት ልጆች እንዲከፋፈል ውሳኔ የተሰጠ መሆኑን፣ይህንን የስረ ነገር ፍርድ ለማስፈጸም 1ኛ አመልካች

በፍርድ ባለመብትነት ተሰይመው ባደረጉት እንቅስቃሴ በከተማው አስተዳደር በቀረበው የዋጋ ግምት መሰረት የቀሪዎቹን ወራሾች ድርሻ 1ኛ አመልካች ከፍለው እና ከወራሾቹ መካከል የአሁኑ ተጠሪ ቤቱ በጨረታ መሸጥ ከሚገባው በቀር ግምቱን ለመቀበል አልስማማም በማለታቸው ድርሻቸው በሞዴል 85 እንዲያዝ ተደርጎ የቤቱ ስመሀብት አፈጻጸሙን በያዘው የሰቆጣ ወረዳ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወደ 1ኛ አመልካች የተዛወረ መሆኑን፣1ኛ ተጠሪ በዚህ ትዕዛዝ ባለመስማማት በየደረጃው ያቀረቡት ክርክር በመጨረሻ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኃላ የስርፍርድ ቤቶችን የአፈጻጸም ትዕዛዝ ሽሮቤቱ ከተቻለ በዓይነት፣ካልተቻለ ግራ ቀኙ እርስ በእርስ በሚያደርጉት ጨረታ፣ይህም ካልተቻለ ለ3ኛ ወገን በጨረታ እንዲሸጥ በመዝገብ ቁጥር 03-08523 በ26/04/2007 ዓ.ም ውሳኔ የሰጠ መሆኑን፣የወረዳው ፍርድ ቤትም በዚሁ አግባብ ቤቱ በጨረታ እንዲሸጥ ለማስቻል የጨረታ ማስታወቂያ እንዲወጣ ትዕዛዝ የሰጠ መሆኑን፣በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት 1ኛ አመልካች ያቀረቡት ይግባኝ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 010913 በ02/10/2007 ዓ.ም. በትዕዛዝ የተዘጋ እና አቤቱታቸውም በክልሉ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር0311349 በ16/06/2008 ዓ.ምበተሰጠ በፍርድ ተቀባይነት ያጣ መሆኑን የመዝገቡ ግልባጭያመለክታል፡፡

አመልካቾች ለዚህ ችሎት ያቀረቡት አቤቱታ ተመርምሮ አመልካቾቹ በአከራካሪው ቤት ላይ ያላቸው የጋራ ድርሻ በጣም ብዙ ሆኖ እያለ እና የተጠሪው ድርሻ ግን በድርሻቸው ብቻ የታጠረ ሆኖ እያለ፣ይህንኑ ከግምት በማስገባትም 1ኛ አመልካች ከአሁኑ ተጠሪ በቀር ለቀሪው እያንዳንዱ ወራሽ ግምቱን ከፍለው ቤቱን በስማቸው አዛውረው እያለ የአሁኑ ተጠሪ ግምቱን ለመቀበል ባለመስማማታቸው ብቻቤቱ በሀራጅ እንዲሸጥ የመታዘዙን አግባብነት ተጠሪው ባሉበት ለማጣራት ይቻል ዘንድ ጉዳዩ ለሰበር ክርክር እንዲቀርብ በመደረጉ ግራ ቀኙ የጽሁፍ ክርክር ተለዋውጠዋል፡፡የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም በጉዳዩ እልባት ማግኘት የሚገባቸው፡-

1. በስረ ነገሩ ፍርድ መሰረት ለማስፈጸም ይቻል ዘንድ በቤቱ ላይ የሀራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ እንዲወጣ በወረዳው ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ያገኘው የአፈጻጸም ትዕዛዝ የሚነቀፍበት ሕጋዊ ምክንያት አለ ወይስ የለም?
2. አመልካቾቹ ከአከራካሪው ቤት ላይ አለን የሚሉትን አብላጫ ድርሻ መሰረት በማድረግ ቤቱን ማስቀረት የሚችሉበት የሕግ አግባብ አለ ወይስ የለም?

የሚሉ ነጥቦች መሆናቸውን በመገንዘብ አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ከእነዚሁ ነጥቦች አንጻር መርምረናል፡፡

የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ 1ኛ አመልካች አጥብቀው የሚከራከሩት ከአከራካሪው ቤት በሚስትነታቸው ያላቸው ድርሻ ግማሽ ሆኖ እያለ እና የሰባት ወራሾች ድርሻ ከሆነው የቤቱ አጋማሽ ውስጥ ደግሞ 1ኛ አመልካች ሞግዚት የሆኗቸው 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾችእያንዳንዳቸው አንድ ሰባተኛ ድርሻ ያላቸው ሆኖ እያለ እንዲሁም ከተጠሪው ውጪ ላሉት ቀሪ ወራሾች 1ኛ አመልካች ድርሻቸውን ከፍለው እያለ ከቤቱ አጋማሽ ውስጥ አንድ ሰባተኛ ድርሻ ብቻ ላላቸው የአሁኑ ተጠሪ ጥቅም ብቻ ሲባል ወደ 1ኛ አመልካች ስም ተዛውሮ የነበረው ቤት በሀራጅ እንዲሸጥ የተሰጠው ትዕዛዝ ፍትሐዊ አይደለም የሚል መሆኑን የአቤቱታቸው ይዘት ያመለክታል፡፡ይሁን እንጂ የክልሉ ሰበር ችሎት የአፈጻጸም ሂደቱን አስመልክቶ ቀደም ሲል ቤቱ ከተቻለ በዓይነት፣ካልተቻለ ግራ ቀኙ በመካከላቸው በሚያደርጉት ጨረታ፣ይህም ካልተቻለ ደግሞ ለ3ኛ ወገን በጨረታ እንዲሸጥ በመዝገብ ቁጥር 03-08523 በ26/04/2007 ዓ.ም. ውሳኔ የሰጠው 1ኛ አመልካች ከአሁኑ ተጠሪ ውጪ ላሉት ሌሎች ወራሾች ድርሻቸውን ሰጥተው ቤቱን በስማቸው ካዛወሩ በኃላ በመሆኑ የተጠሪው ድርሻ ከቤቱ አጋማሽ ውስጥ አንድ ሰባተኛ ብቻ ሆኖ እያለ ቤቱ በሐራጅ ይሸጥ መባሉ ተገቢ አይደለም የሚሉ ከሆነ የሰበር አቤቱታቸውን በወቅቱ በስርዓቱ መሰረት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አቅርበው ተገቢውን ውሳኔ ማስጠት ይገባቸው የነበረ ከመሆኑ በቀር በክልሉ ሰበር ችሎት ውሳኔ መሰረት ጉዳዩ ወደ ወረዳው ፍርድ ቤት ተመልሶ የአፈጻጸም ሂደቱ ከቀጠለ በኃላ ወደኃላ ተመልሰው ቤቱ በሀራጅ እንዲሸጥ የተሰጠው የአፈጻጸም ትዕዛዝ ፍትሀዊ አይደለም በማለት አሁን እያቀረቡ ያሉት ክርክር ስነ ስርዓታዊ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡በመሆኑም አፈጻጸሙን የያዘው የሰቆጣ ወረዳ ፍርድ ቤት ቀደም ሲል በክልሉ ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 03-08523 በ26/04/2007 ዓ.ም. የሰጠውን ውሳኔ ተከትሎ በስረ ነገሩ ፍርድ መሰረት ለማስፈጸም ይቻል ዘንድ በቤቱ ላይ የሀራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ እንዲወጣየሰጠው እና በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ያገኘው የአፈጻጸም ትዕዛዝ የሚነቀፍበትን ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡

ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ ከአከራካሪው ቤት 1ኛ አመልካች ግማሽ ድርሻ፣2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ደግሞ ከቤቱ አጋማሽ ውስጥ እያንዳንዳቸው አንድ ሰባተኛ ድርሻ ያላቸው መሆኑ አላከራከረም፡፡ይህም 1ኛ አመልካችም ሆኑ 2ኛ እና 3ኛ አመልካቾች ከቀሪዎቹ ወራሾች ጋር የአከራካሪው ቤት የጋራ ባለሀብቶች መሆናቸውን መገንዘብ የሚያስችል ነው፡፡በፍርድ አፈጻጸም ምክንያት ተይዞ የሚሸጠው የማይንቀሳቀስ ንብረት ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች በሕብረት የያዙት እና ያልተከፋፈሉት በሆነ ጊዜ ከተካፋዮቹ አንዱ ንብረቱን ለመግዛት በጨረታ ተወዳዳሪ ሆኖ የቀረበ እንደሆነ የፍርድ ባለዕዳው እንደቀረበ ተቆጥሮ የተቀዳሚነት መብት የሚሰጠው ስለመሆኑ የፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 443 ይደነግጋል፡፡ከስነ ስርዓት ሕጉ በተጨማሪም የጋራ ባለሀብቶች የሆኑ ሰዎች ያልተከፋፈለውን የጋራ ንብረት ከማንኛውም ሶስተኛ

ወገን በፊት ቀዳሚ ሆነው በግዥ የማስቀረት ሕጋዊ መብት ያላቸው ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1261 (1) የተደነገገ ሲሆን ይህ መብት ተግባራዊ የሚደረግበት ስርዓትም በዚሁ ሕግ ከቁጥር 1386 እስከ 1409 ተደንግጎ ይገኛል፡፡በመሆኑም አመልካቾቹ አከራካሪውን ቤት ለማስቀረት የሚችሉት በቤቱ ላይ በሚከናወነው ጨረታ መሰረት ከፍተኛ ዋጋ በማቅረብ አሸናፊ የሆነው ተጫራች ጨረታውን ያሸነፈበትን ዋጋ መሰረት በማድረግ ከላይ በተጠቀሱት ድንጋጌዎች በተጠበቀላቸው የቀዳሚነት መብት በመገልገል ነው፡፡በቀጣይ የአፈጻጸሙ ሂደት አመልካቾቹ ከፍተኛ ዋጋ በማቅረብ አሸናፊ የሆነው ተጫራች ጨረታውን ያሸነፈበትን ዋጋ መሰረት በማድረግ የቀዳሚነት መብታቸውን ተግባራዊ የሚያደርጉ ከሆነ በሰበር አቤቱታቸው እንደሚከራከሩት ከአሁኑ ተጠሪ ውጪ ላሉት ሌሎች ወራሾች ድርሻቸውን ከፍለው በቤቱ ላይ ያላቸውን ድርሻ ከፍ ያደረጉ መሆን አለመሆኑ፣ጨረታውን ካሸነፉበት የዋጋ መጠን ውስጥ የራሳቸው ድርሻ ተቀንሶ ገቢ ማድረግ የሚገባቸው የገንዘብ መጠን ምን ያህል እንደሆነ እና መሰል የአፈጻጸም ጉዳዮች ፍርዱን በሚያስፈጽመው ፍርድ ቤት ተስተናግደው ተገቢው ትዕዛዝ የሚሰጥባቸው ይሆናል፡፡

ሲጠቃለል አመልካቾቹ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 443 እንዲሁምበፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1261 (1)፣1386 እስከ 1409 በተደነገገው የቀዳሚነት መብታቸው የመገልገል መብታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ አከራካሪው ቤት በሀራጅ እንዲሸጥ በወረዳው ፍርድ ቤት የተሰጠው እና በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ያገኘው ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ስላልተቻለ የሚከተለው ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በሰቆጣ ወረዳ ፍርድ ቤት ተሰጥቶ በዋግኽምራ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 0101913 በ02/10/2007 ዓ.ም. በትዕዛዝ የጸናውን የአፈጻጸም ትዕዛዝ በፍርድ በማጽናት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 0311349 በ16/06/2008 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 348 (1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. የስረ ነገሩ ፍርድ ያረፈበት ቤት በሀራጅ ይሸጥ መባሉ በአግባቡ ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. አከራካሪው ቤት በሀራጅ በሚሸጥበት ጊዜ አመልካቾቹ በፍትሐብሔር ስነ ስርዓት ሕግ ቁጥር 443፣እንዲሁም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1261 (1)፣1386 እስከ 1409 በተደነገገው የቀዳሚነት መብት የመገልገል መብት አላቸው በማለት ወስነናል፡፡

4. እንዲያውቁት የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለሰቆጣ ወረዳ ፍርድ ቤት፣ለዋግኽምራ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ይላክ፡፡
5. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 0311349 በ16/06/2008 ዓ.ም. የተሰጠው ውሳኔ አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ በዚህ መዝገብ በ06/07/2008 ዓ.ም. ተሰጥቶ የነበረው ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡
6. የሰበር ክርክሩ ያስከተለውን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
7. ውሳኔ ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሃ/ወ

የሰ/መ/ቁ. 121565

ሚያዚያ 20 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡-ዳኜ መላኩ

ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንደሻው አዳነ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- ወ/ሮ ፍረወይኒ አብርሃ

ተጠሪ፡- አቶ ገ/ጊዮርግስ ፀጋይ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የፍርድ አፈፃፀም የተመለከተ ክርክር ነው፡፡ የአመልካች አፈፃፀም ከሳሽ ተጠሪ የአፈፃፀም ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የአፈፃፀም ክርክሩ መነሻ በግራ ቀኙ መካከል የነበረ ጋብቻ ውሣኔ መፍረስን ተከትሎ የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ላይ የተሰጠ ውሣኔ ለማስፈፀም ነው፡፡

አሁን አከራካሪ ሆኖ ለዚህ ሰበር ችሎት አቤቱታ ምክንያት የሆነው በመቀሌ ከተማ በሐነድነት ክ/ከተማ በደብሪ ቀበሌ የሚገኝ 400 ካ.ሜ ቦታ ላይ ያረፈ ቤት ክፍፍል ላይ የሥር ፍርድ ቤቶች የተለያየ አቋሞ በመያዛቸው ነው፡፡ ከመዝገቡ መገንዘብ እንደተቻለው የመቀሌ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይህ ቤት የባለቤትነት ማረጋገጫ ስላልወጣለት ወይም ገና ህጋዊ መሆኑ ስላልተረጋገጠ የባለቤትነት ማረጋገጫ እስኪወጣለት ድረስ የሚፈፀም አይደለም ሲል የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ አድጓል፡፡

ይግባኝ የቀረበለት የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ግራቀ ኙን ካከራከር በኋላ ለግራ ቀኙ በአማራጭማስፈፀም የሚቻልበት ሁኔታ የለም በማለት በአብላጫ ድምፅ የሥር ፍርድ ቤት ትእዛዝ አፅንቷል፡፡ አናሳው ድምፅ ቤቱ የጋራ ነው እስከተባለ ድረስ አስተዳደር አካል ተገቢውን

ውሣኔ እስኪሰጥበት ድረስ በጋራ የሚጠቀሙበት አማራጭ ሊታይ ይገባል ሲል ልዩነት ሀሳብ አስፍሯል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ላይ ሲሆን የአመልካች የቅሬታ ነጥብ በአጭሩ ሲታይ ተጠቃሹ 8 ክፍል ቪላ ቤት አመልካችናተጠሪ በጋራ በትዳር ላይ እያሉ ያፈሩት መሆኑ ተረጋግጦ የሚከፈል ከሆነ በዐይነት እንዲከፋፈሉ ማካፈል ካልተቻለም ደግሞ በጨረታ ወይም በስምምነት ተሸጦ እንዲካፈሉ በመ/ቁጥር 149270 ውሣኔ መስጠቱን፤በዚሁ መሠረት እንዲፈፀም አቤቱታ ማቅረቧን፤የሐድነት ክ/ከተማ መሬት አስተዳደርም ተጠይቆ ይህ ቦታና ቤት ካርታ ያልወጣለት ስለሆነ መፈፀም እንዳልተቻለ ምላሽ መስጠቱን ይህ የማይቻል ከሆነ ለጊዜው በጋራ እያስተዳደሩ እንዲጠቀሙበት መደረግ ሲገባ ተጠሪ ብቻ እንዲጠቀም መደረጉ ስህተት ስለሆነ እንዲታረም የሚል ነው፡፡

ይህችሎትም ይህንኑ ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲሰጥ አዟል፡፡ የተጠሪ ጠበቃም በሰጡት መልስ ፍርድ ሊፈፀም የሚገባው እንደፍርዱ ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 378(1) ጠቅሰው የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ትእዛዝ ተገቢ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥና የግራ ቀኙን ክርክር ከላይ ባጭሩ የተመለከተ ሲሆን እኛም አግባብነት ካለው ህግ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

ከመዝገቡ መገንዘብ እንደተቻለው በሐድነት ክ/ከተማ በ400 ካ.ሜ ይዞታ ላይ ያረፈው ቤት የአመልካችና የተጠሪ የጋራ ሀብት ነው ተብሎ ውሣኔ ያረፈበት መሆኑ በሥር ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪ በዋናው ውሣኔ ለዚህ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁጥር 122453 አቤቱታ አቅርቤያለሁ ቢሉም የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለውም ተብሎ ህዳር 19 ቀን 2009 ዓ.ም መወሰኑን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡

ይህ የጋራ ንብረት የተባለው ቤት በፍርድ አፈፃፀም ለጊዜው ሊፈፀም አይችልም የተባለው ይዞታው ህጋዊ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር አላገኘውም በሚል ነው፡፡

ስለሆነም የሚመለከተው አስተዳደር አካል ስለህጋዊነቱ ተገቢውን ውሣኔ እስሲጥበት ጊዜ ድረስ በጋራ በማስተዳደር የምንጠቀምበት አግባብ እንዲታዘዝሲሉ አመልካች በአማራጭ ጥያቄ አቅርባል፡፡

በመሠረቱ በጋብቻ ወቅት የተፈራ የጋራ ንብረት ነው እስከተባለ ድረስ በዚህ ንብረት ሕጋዊነት ላይ አስተዳደር አካል አግባብ ያለው ውሣኔ እስኪሰጥ ድረስ መሸጥ መለወጥ ባይችልም ባለበት ሁኔታ ሁለቱም ወገኖች እኩል ተጠቃሚ የሚሆንበት ሥርዓት ሊበጅለት ይገባል፡፡

ይህ ካልሆነ አንደኛው ወገን ብቻ ተጠቃሚ ማድረግ በሕገመንግስቱ እና በሌሎች የቤተሰብ ሕጉ ድንጋጌዎች የተመለከተውን የእኩልነት መርህ ያላከበረ አካሄድ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከዚህ ባሻገር በአፈፃፀም ሂደት እንደ ፍርዱ ለመፈፀም የማይቻልበትህጋዊ ምክንያት ሲገኝ አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤት ተገቢውን አማራጭ ተመርኩዞ አግባብ ያለው ትእዛዝ መስጠት እንደሚቻል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ 386/2/ ድንጋጌ ይዘታ ያስገነዝባል፡፡ በተመሣሣይ የሥነ ሥርት ሕጉ አተገባበር ላይ የፌዴራል ጠቅለላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትውሣኔ የሰጠባቸውን መዝገቦች ይዘትም ማየት ይቻላል፡፡ የሰበር መ/ቁጥር 38041፣62804፣101345 እና ሌሎች ተዛማች መዝገቦችን ማየት ይቻላል፡፡

ከዚህ አንፃር ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ይህ የጋራ ነው የተባለው ቤት በሕጉ አግባብ ለክፍፍል የሚያመች ሕጋዊ ሁኔታእስኪሟላ ጊዜ ድረስ የግራ ቀኙን እኩል ተጠቃሚነት በሚያረጋግጥ አግባብ በጋራ የሚያስተዳድሩበት ወይም ተከፋፍለው የሚጠቀሙበት ወይም አከራይተው ጥቅሙን እኩል የሚከፋፈሉት ሁኔታ ማመቻቸት ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኛ አናሳ ድምፅ ያስቀመጠው አማራጭ ከግራ ቀኙ አስተያየት ተጠይቆ ተገቢ ትእዛዝ ሊሰጥበት እየተገባ ተጠሪ ብቻ ይዞ እንዲጠቀም በሚያደርግ መልኩ መወሰኑየጋራ ባለንብረት የሆነችውን የአመልካችን የእኩልነት መብት ያጣበበ በመሆኑ ውሣኔው ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. አከራካሪውን በሐድነት ክ/ከተማ ቀበሌ ደብሪ የሚገኘው ቤት አስመልክቶ የመቀሌ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አብላጫ ድምፅ እንደቅደም ተከተላቸው በመ/ቁጥር 17034 እና 76406 የሰጡት ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ስለሆነም ይህ ቤት ሕጋዊነቱ በሚመለከተው እኩል ውሣኔ እስኪሰጥበት ጊዜ ድረስ ባለበት ሁኔታ ግራ ቀኙ በጋራ የሚያስተዳድርበት ወይም አከራይተው የሚጠቀሙበት አማራጭ ሁኔታዎች ላይ የግራ ቀኙን አስተያየት ተቀብሎ ተገቢውንና ተስማሚውን ውሣኔ እንዲሰጥበት ብለን ጉዳዩን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 343/1/ መሠረት ለመቀሌ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መልሰናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡ ብ/ግ

የሰ/መ/ቁ. 118808

ሚያዚያ 30 ቀን 2009ዓ.ም

ዳኞች:- ዳኜ መላኩ

ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

እትመት አሰፋ

አመልካች:- አቶ ደስታ ንጉሴ አልቀረቡም

ተጠሪ:- አቶ ሐየሎም በላይ አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍ ር ድ

ጉዳዩ አፈጻጸምን የሚመለከት ሆኖ የተጀመረዉ የሓድነት ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች በአቶ ሕንጻ በላይ እና በአሁኑ ተጠሪ ላይ በአንድነትና በተናጠል እንዲከፍሉ ካስወሰነዉ ገንዘብ ዉስጥ የአሁኑ ተጠሪ ግማሹን መክፈሉን ገልጾ ቀሪዉን ግማሽ ብር 22,165 የመክፈል ግዴታ ያለበት በመሆኑ ተጠሪ እንዲከፍለዉ ሲጠይቅ፤ ተጠሪ በበኩሉ በአንድነትና በተናጠል እንድንከፍል ተወስኖ የነበረዉን አቶ ሕንጻ በላይ ይግባኝ ጠይቀዉ ተጠያቂ ሊሆኑ አይገባም ተብሎ የተወሰነና ከአፈጻጸም ክሱም የተሰናበቱ በመሆናቸዉ በዋናዉ ፍርድ መሠረት ተጠሪ ሙሉ ገንዘቡን ብከፍል በአንድነትና በነጣላ ተጠያቂ ነዉ ተብሎ ከነበነረዉ ሰዉ ግማሹን የማስመለስ መብቴ ስለተነካ የአቶ ህንጻ በላይ ድርሻ የምከፍልበት አግባብ የለም ሲል ተከራክሯል።

የወረዳዉ ፍ/ቤት የአፈጻጸም ክርክሩን መርምሮ ተጠሪ ከአቶ ሕንጻ በላይ ጋር በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ተወስኖ የነበረዉን አቶ ሕንጻ በላይ ይግባኝ ጠይቀዉ ኃላፊነታቸዉን በተመለከተ ዉሳኔዉን አሽረዋል። ተጠሪ የአቶ ሕንጻ በላይን ድርሻ ለመክፈል ይገደዱ የነበረዉ አቶ ሕንጻ በላይ ባለዕዳ ሆነዉ ለመክፈል ፍቃደኛ ባይሆኑ ነበር። አሁን ግን አቶ ሕንጻ በላይ የተወሰነባቸዉን ያሻሩ ስለሆነ ተጠሪ ገንዘቡን ጠቅልለዉ ከፍለዉ ከአቶ ሕንጻ በላይ መልሰዉ ድርሻቸዉን የሚያስከፍሉበት የሕግ አግባብ በሌለበት ተጠሪ ድርሻዉ ከሆነዉ ግማሽ ገንዘብ በላይ እንዲከፍል ሊገደድ አይገባም በማለት ብይን ሰጥቷል። ይህን ብይን በመቃወም አመልካች

ያቀረቡትን ይግባኝ የተመለከተዉ የመቀሌ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት ይግባኙን አሰናብቷል፡፡ እንዲሁም አመልካች የሰበር አቤቱታ ለትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኃላ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈጸመም በማለት የስር ፍ/ቤቶችን ዉሳኔ አጽንቶታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነዉ፡፡

አመልካች ያቀረበዉ የሰበር አቤቱታ ይዘት፡- ዋናዉ ፍርድ በግልጽ የሚያመለክተዉ ተጠሪና አቶ ሕንጻ በላይ በአንድነትና በነጠላ የኮንስትራክሽን ዕቃዎች ዋጋ እና ኪራይ እንዲከፍሉኝ ነዉ፡፡ ስለዚህ ዉሳኔዉ ተጠሪና አቶ ሕንጻ በላይ ድርሻ ሳይነጣጠል በጋራ እንዲከፍሉኝ የተወሰነ ነዉ፡፡ በዋናዉ ፍርድ ሁለቱም ለከፍተኛ ፍ/ቤት ለየብቻቸዉ ይግባኝ አቅርበዉ በወረዳ ፍ/ቤት የተሰጠዉን ዉሳኔ ቢያሽሩም በተጠሪ መዝገብ በተሰጠዉ ዉሳኔ ስላልተስማማሁ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቤ የከፍተኛዉ ፍ/ቤት ዉሳኔ ተሽሮ የወረዳዉ ፍ/ቤት ዉሳኔ ሙሉ በሙሉ ጸንቷል፡፡ የወረዳዉ ፍርድ ቤት በአፈጻጸም በሰጠዉ ብይን ራሱ የሰጠዉን ዉሳኔ ብቻ ሳይሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ ጭምር ሽሯል፡፡ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ይህን ብይን ማጽናቱ ስህተት ነዉ፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤቶች የአፈጻጸም ትዕዛዝ ተሽሮ ተጠሪ ዕዳዉን በሙሉ እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ የሚል ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ ለዚህ አፈጻጸም መሠረት የሆነዉ ፍርድ መነሻ የሆነዉ የክስ ምክንያት ከተጠሪ ጋር ተከሶ የነበረዉን ግለሰብ ጭምር ሳይሆን ተጠሪን ብቻ በግሉ የሚመለከት ነዉ ተብሎ ግለሰቡ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ከኃላፊነት ነጻ እስከተባለ ድረስ ተጠሪ ፍርዱን በሙሉ እንዲፈጽም ሊገደድ አይገባም ወይ የሚለዉን ነጥብ ለመመርመር ሲባል ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራ ቀኙ መልስ እና የመልስ መልስ በጽሁፍ በማቀባበል እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በሰበር መልሳቸዉ ያቀረቡት ክርክር ይዘት፡- አቶ ሕንጻ በላይ ተጠያቂ አይደለም የተባለዉ በድርሻዉ ላለዉ ተጠያቂነት ነዉ፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የወረዳዉን ፍ/ቤት ዉሳኔ አጽንቻለሁ ማለቱ ሁለቱም በአንድነትና በነጠላ ተጠያቂዎች መሆናቸዉን የሚያሳይ ነዉ፡፡ ይህም የአሁኑ ተጠሪ አጠቃላዩን ለመክፈል የሚጠየቅበት አግባብ የለም፡፡ ተጠሪ በዉሳኔዉ መሠረት ግማሽ ድርሻዬን የከፍልኩኝ ሲሆን አቶ ሕንጻ በላይ መክፈል ያለባቸዉን ገንዘብ መክፈል አለብህ የሚለዉ ቅሬታ አቶ ሕንጻ በላይ በነጻ ከመሠናበቱ አንጻር የሕግ መሠረት የለዉም፡፡ ክፈል ተብዬ ተገድጄ ብከፍል መጨረሻ ላይ ከአቶ ሕንጻ ገንዘቡን ማስመለስ አልችልም፡፡ አመልካች በራሳቸዉ ቸልተኝነት በአቶ ሕንጻ በላይ ይግባኝ ሳያቀርቡ ለቀረባቸዉ ግማሽ ክፍያ ተጠያቂ ራሳቸዉ እንጂ ተጠሪ አይደለም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ድርሻዉን ግማሹን ገንዘብ ስለከፈልኩ አመልካች ከተጠሪ የሚጠይቁት ተጨማሪ ክፍያ የለም ተብሎ የስር ፍ/ቤቶች ዉሳኔ ይጽናልኝ የሚል ነዉ፡፡ አመልካች አቤቱታቸዉን በሚያጠናክር መልኩ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ባጭሩ ከላይ የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካለዉ የሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡

የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ ለአፈጻጸሙ መሠረት የሆነዉን ፍርድ በቅድሚያ የሰጠዉ የመቀሌ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት ተጠሪን እና የስር 1ኛ ተከሳሽ የነበረዉን አቶ ሕንጻ በላይን በአንድነትና በነጣል ዕዳዉን እንዲከፍሉ የወሰነባቸዉ ሲሆን ሁለቱም ባለዕዳዎች በተናጠል ለመቀሌ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበዉ በተለያዩ መዝገብ ዉሳኔዉን አሽረዋል፡፡ የአሁኑ አመልካች ተጠሪን በተመለከተ ብቻ ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ግራቀኙን ካከራከረ በኃላ ተጠሪ ነጻ የተባለበትን ዉሳኔ በመሻር የወረዳዉ ፍ/ቤት የሰጠዉን ዉሳኔ አጽንቶታል፡፡ አመልካች ፍርዱን ሙሉ በሙሉ ተጠሪ እንዲፈጽምለት የጠየቀ ሲሆን የስር ፍ/ቤቶች በተመሳሳይ ተጠሪ የፍርዱን ግማሽ ገንዘብ በመክፈል ድርሻዉን የተወጣ በመሆኑና በዋናዉ ጉዳይ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቶ ሕንጻ በላይን አስመልክቶ በነጻ እንዲሰናበት በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ የአሁኑ አመልካች ይግባኝ ጠይቆ ባለማሻሩ ምክንያት የአሁኑ ተጠሪ ሙሉ ገንዘቡን ቢከፍል በድርሻዉ አቶ ሕንጻ በላይን ጠይቆ የማስመለስ መብቱን የሚያሳጣዉ በመሆኑ ተጠሪ ከግማሽ ዕዳ ወይም ከድርሻዉ በላይ እንዲከፍል ሊገደድ አይገባም በማለት ወስነዋል፡፡ የአሁኑ አመልካች አጥብቆ የሚከራከረዉ ተጠሪ ለሙሉ ዕዳዉ በአንድነትና በተናጠል ኃላፊ ነዉ እስከተባለ ድረስ ተጠሪ ሙሉ ገንዘቡን የመክፈል ግዴታ አለበት በሚል ነዉ፡፡

በመሠረቱ የአንድነትና የነጣላ ኃላፊነት ምን ማለት እንደሆነ በሕጋችን ተካትቶ የምናገኘዉ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1896፣ 1897 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ላይ ነዉ፡፡ እነዚህ ድንጋጌዎች የሚገኙት ግዴታዎችን በተመለከተዉ የፍትሐብሔር ሕጉ መጽሐፍ በተለይም ስለ ዉሎች በጠቅላለዉ በሚለዉ አንቀጽ 12 ስር ቢሆንም መርሁ ግዴታዉ ከዉል፣ ከሕግም ሆነ ከፍርድ የመነጨ ቢሆንም ይህንኑ የሚመለከት የተለዩ የሕግ ድንጋጌ እስካልኖረ ድረስ በተጠቀሱት ድንጋጌዎች የተቀመጠዉ የአንድነትና የነጠላ ኃላፊነት መርህ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 1896፣ 1897 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻለዉ ሁለት ባለዕዳዎች በአንድነትና በነጣላ አንድን ዕዳ እንዲከፍሉ ከተፈረደባቸዉ ባለገንዘቡ ገንዘቡ እንዲከፈለዉ ሁለቱን ባለዕዳዎች በአንድነት ወይም አንደኛዉ ባለዕዳ ሙሉ ገንዘቡን እንዲከፍል ሊጠይቅ ይችላል፡፡ እንዲሁም አንዱ የፍርድ ባለዕዳ በዋናዉ ፍርድ ይግባኝ ጠይቆ የራሱን ኃላፊነት አስመልክቶ ፍርዱን አሽሮት ከሆነ ሙሉ እዳዉን ለመክፈል ኃላፊነት የሚኖርበት ይግባኝ ሳይጠይቅ በመቅረቱ ዋናዉን ፍርድ ባልተሻረለት ወይም ይግባኝ ጠይቆ ፍርዱ በጸናበት ሰዉ ላይ ይሆናል፡፡ ፍርድ ያላሻረዉ ወይም የጸናበት ባለዕዳ ዕዳዉን የምከፍለዉ በድርሻዬ ልክ ወይም ግማሹን ነዉ ለማለት አይችልም፡፡ ምክንያቱም ሁለት ሰዎች በአንድነትና በነጠላ ኃላፊ ናቸዉ ሲባሉ ለእዳዉ

አከፋፈል አንዳቸዉ ወይም ሁለቱም በጋራ ለባለገንዘቡ ግዴታ አለባቸዉ ማለት እንጂ ሁለቱ በመካከላቸዉ ዕዳዉን እኩል ለመካፈል ኃላፊነት አለባቸዉ ማለት አይደለም፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1907 መሠረት የተቀመጠዉ የሕግ ግምት እንደተጠበቀ ሆኖ በሁለቱ ባለዕዳዎች መካከል ያለዉ የኃላፊነት መጠን የሚወሰነዉ እርስ በርሳቸዉ ሲጠያየቁ በሚኖረዉ ኃላፊነት መሠረት አንዱ ለሙሉ ወይም ለከፊሉ ዕዳ ኃላፊ ነዉ ተብሎ ተለይቶ ሲወሰን ነዉ፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ አመልካች የስር ተከሳሾች በአንድነትና በተናጠል ኃላፊነት የሚያስከትልባቸዉ የሕግ ተጠያቂነት አለባቸዉ ብሎ ቢያምንም ሲፈልግ ሁለቱን ሳይፈልግ አንዱን መርጦ የመክሰስ መብት አለዉ፡፡ እንዲሁም በይግባኝ ደረጃም ቢሆን በአንዱ ላይ ይግባኝ ጠይቆ በሌላኛዉ ላይ ይግባኝ ያለመጠየቅ መብት አለዉ፡፡ ምክንያቱም አንዱን ነጥሎ መክሰሱ ወይም በአንዱ ላይ ብቻ ይግባኝ መጠየቁ ብቻ ገንዘቡን የሚያስከፍለዉ መሆኑን እስካረጋገጠለት ድረስ ሁለቱን በአንድነት የመክሰስ ወይም ይግባኝ የመጠየቅ ግዴታ አይኖርበትም፡፡ አመልካች ያቀረበዉ ክስም ሆነ ይግባኝ የስር ተከሳሾች ለአመልካች የሚኖራቸዉን ግዴታ ወይም ኃላፊነት የሚወስን እንጂ በቀጥታ በሁለቱ ተከሳሾች የዕዳ መከፋፈልን ወይም አንዱ ሙሉ እዳ ከፍሎ ከሌላዉ የሚጠይቅበት ፍርድ ወይም የዳኝነት ጥያቄ አይደለም፡፡ ተጠሪ ለሙሉ እዳዉ በአንድነትና በተናጠል ኃላፊ ነዉ ተብሎ የተወሰነበትን በይግባኝ ወይም የሰበር አቤቱታ አቅርቦ እስካላሻረ ድረስ ወይም ኃላፊነቱ በድርሻዉ እንዲቀንስ እስካላደረገ ድረስ ሙሉ እዳዉን ለአመልካች ለመክፈል ይገደዳል፡፡ አመልካች የመቀሌ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቶ ሕንጻ በላይን በነጻ ሲያሰናብት ይግባኝ አለመጠየቁ ወይም ይግባኝ ተይቆ የጸናበት መሆኑ ተጠሪ ዕዳዉን በሙሉ ለመክፈል ባለዉ ኃላፊነት ላይ ለዉጥ አያመጣም፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤቶች አመልካች የመቀሌ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቶ ሕንጻ በላይን በነጻ ሲያሰናብት ይግባኝ ጠይቆ ባለማሻሩ ተጠሪ ሙሉ ክፍያ ከፍሎ ግማሹን ከአቶ ሕንጻ በላይ የማስመለስ መብቱን የሚነካ በመሆኑ ተጠሪ ድርሻዉን ወይም ግማሹን ፍርድ እንጂ ግማሹን ለመክፈል አይገደድም በማለት የሰጡት የአፈጻጸም ዉሳኔ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፡፡

ሲጠቃለል በዋናዉ ፍርድ በወረዳዉ ፍ/ቤት ከተጠሪ ጋር በአንድነትና በተናጠል ለሙሉ ዕዳዉ ኃላፊ ተደርጎ የነበረዉ አቶ ሕንጻ በላይ ይግባኝ ጠይቆ ራሱን ከኃላፊነት ነጻ ባደረገበትና በተጠሪ ላይ በወረዳዉ ፍ/ቤት የተሰጠዉ ዉሳኔ ባልተሻሻለለት ወይም ባልተሻረለት ሁኔታ፤ የስር ፍ/ቤቶች ተጠሪ ግማሹን እስከከፈለ ድረስ ግማሹን ወይም የአቶ ሕንጻ በላይን ድርሻ ለመክፈል አይገደድም በማለት የሰጡት የአፈጻጸም ዉሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሚከተለዉ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

1. የመቀሌ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት የሓድነት ምድብ ችሎት በመ/ቁ 04593 ሕዳር 22 ቀን 2007 ዓ.ም ተሰጥቶ፤ በመቀሌ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 16754 መጋቢት 11 ቀን 2007 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ እና የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 75025 ነሐሴ 07 ቀን 2007 ዓ.ም በተሰጠ ዉሳኔ የጸናዉ የአፈጻጸም ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. የተጠሪ ኃላፊነት አስመልክቶ የወረዳዉ ፍ/ቤት የሰጠዉ ዋና ፍርድ በይግባኝ የጸና በመሆኑና በይግባኝ የተሻረዉ የአቶ ሕንጻ በላይ ኃላፊነት ብቻ በመሆኑ ተጠሪ የሚከፍለዉን ገንዘብ ግማሽ ከአቶ ሕንጻ ማስመለስ መቻል አለመቻሉ ግምት ዉስጥ ሳይገባ ለአመልካች እንዲከፈል የተወሰነዉን ሙሉ ገንዘብ ተጠሪ የመክፈል ወይም እንደፍርዱ የመፈጸም ኃላፊነት አለበት ተብሎ ተወስኗል፡፡ የመቀሌ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት የሓድነት ምድብ ችሎት መዝገቡን በማንቀሳቀስ ለአመልካች ያልተፈጸመለትን ቀሪ ገንዘብ ተጠሪ እንዲከፍል በማድረግ ፍርዱን እንዲያስፈጽም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343(1) መሠረት ጉዳዩ ይመለስለት ተብሏል፡፡ ይጻፍ፡፡
3. የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ዉሳኔ ያገኘ ስለሆነ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ፍ

ሰ/መ/ቁ. 128776

ግንቦት 16 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

እንዳሻው አዳነ

ሃይሉ ነጋሽ

እትመት አሠፋ

አመልካች፡-አቶ ገ/ኢየሱስ ሃይሉ አልቀረቡም

ተጠሪ፡-ዳዊት ልዑል አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ አፈጻጸምን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በሽሬ እንዳስላሴ ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር አመልካች የአፈጻጸም ከሳሽ ተጠሪ ደግሞ አፈጻጸም ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡አመልካች ለአፈጻጸም ችሎቱ ባቀረቡት አቤቱታ ተጠሪ በፍርድ ለአመልካች እንዲከፍሉ የተወሰነባቸውን ገንዘብ ለማስከፈል ተጠሪ ከአመልካች የገዟት የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 03-46545 የሆነች መኪና በባለሙያ በተገመተው ብር 731426.05 / ሠባት መቶ ሠላሳ አንድ ሺህ አራት መቶ ሐያ ሥድሥት ብር ከዜሮ አምሥት ሣንቲም / በሐራጅ ተሸጣ የተጠሪ ዕዳ እንዲከፈል በማለት ለሁለት ተከታታይ ጊዜ ጨረታ የወጣ ቢሆንም መኪናዋ በጨረታ ያልተሸጠች መሆኑን፤የመኪናዋ ግምት ከፍ ያለ እና የማይመጥናት ስለሆነ ልትጫረት ያልቻለች መሆኑን፤ተጠሪ በመሠለው ዋጋ መኪናዋን ሸጦ እንዲሰጣቸው የጠየቁት ቢሆንም መኪናዋን ሸጦ ገንዘቡን ሊሰጣቸው ያልቻለ መሆኑን በመግለጽ በውሳኔው መሠረት በብር 430,000 / አራት መቶ ሠላሳ ሺህ / ሒሳብ የመኪናው ሥመሐብት ወደ ሥማቸው እንዲዛወርላቸው ወይም 3ኛ ጨረታ ከታዘዘ በጨረታው እንዲሳተፉ እንዲታዘዝላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ በሰጡት መልስ መኪናዋ እስካሁን የምትታወቀው በአመልካች ሥም መሆኑን፤አመልካች መኪናዋን እንዳትሸጣት በማለት ማስጠንቀቂያ የሰጣቸው መሆኑን ፤መኪናዋ በመንገድ ትራንስፖርት ግምት የወጣላት በመሆኑ አመልካች መኪናውን ወስደው ቀሪ ገንዘቡን እንዲመልሱልኝ ይታዘዝልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ፍ/ቤቱም የግራቀኙን ክርክር መርምሮ መኪናዋ ለሁለት ጊዜ ጨረታ ወጥቶ ልትሸጥ አልቻለችም፤የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 428/2 ሁለተኛ ጨረታ ወጥቶ ተጫራች ካልቀረበ የፍርድ ባለመብት ንብረቱን እንዲረከብ ትዕዛዝ የሚሰጥ መሆኑ ይደነግጋል፤ለአመልካች ሊከፈል የሚገባው ጠቅላላ ገንዘብ ብር 446,098.57 / አራት መቶ አርባ ሥድሥት ሺህ ዘጠና ሥምንት ብር ከሐምሳ ሠባት ሣንቲም / በመሆኑ እና መኪናዋ የተገመተችው ብር 731,426.05 / ሠባት መቶ ሠላሳ አንድ ሺህ አራት መቶ ሐያ ሥድሥት ብር ከዜሮ አምሥት ሣንቲም / በመሆኑ አመልካች ልዩነቱን ብር 285,327.48 /ሁለት መቶ ሠማንያ አምሥት ሺህ ሦስት መቶ ሐያ ሠባት ብር ከአርባ ሥምንት ሣንቲም / ለተጠሪ ከከፈለ በኋላ መኪናዋን ይረከብ በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡አመልካች በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት አቤቱታቸው ውድቅ ተደርጓል፡፡የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡-አንድ ንብረት ለፍርድ አፈጻጸም ተብሎ ለሐራጅ ሲቀርብ መነሻ ዋጋው ወቅታዊ የንብረቱ ዋጋ መሆን ይኖርበታል፤ወቅታዊ የገበያ ግምቱንም በትራንስፖርት ቢሮ በሚገኝ ባለሙያ ማስገመት ይገባል፤የሸሬ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህን የባለሙያ ግምት ሳያገኝ መኪናው ወደ ሐገር ውስጥ ሲገባ ለግብር አከፋፈል ተብሎ በኢትዮጲያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን የተቀመጠውን ግምት በመነሻነት መውሰዱ ተጫራች እንዳይቀርብ ከማድረጉም በተጨማሪ ከአፈጻጸም ሕግ ድንጋጌዎች ጋር የሚጻረር ነው፤ንብረቱ ለሁለተኛ ጨረታ ቀርቦ ገዢ ከታጣ የፍርድ ባለመብት ንብረቱን እንዲረከብ ተደርጎ ፍርዱ በሙሉ ወይም በከፊል እንደተፈጸመ ይቆጠራል እንጂ የፍርድ ባለመብት ገዢ ያጣውን ንብረት ከግምቱ በላይ ለፍርድ ባለዕዳው ገንዘብ በመመለስ የፍርድ ባለዕዳው ያለአግባብ እንዲበለጽግ የሚደረግበት የሕግ አግባብ የለም፤በመሆኑም የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ችሎት መታየት ያለበት ሆኖ ስለተገኘ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎ ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡እኛም የግራቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ፡-

1. አመልካች ከጨረታው ቀን በኋላ ያቀረቡት የመኪና ግምት መቃወሚያ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም?
2. የአፈጻጸም ችሎቱ በሁለተኛው ጨረታ ተጫራች ስላልቀረበ አመልካች በመኪናዋ ግምት እና ለአመልካች ሊከፈል በሚገባው የገንዘብ መጠን መካከል ያለውን ልዩነት ከፍለው መኪናዋን ሊረከቡ ይገባል በማለት የሰጠው ትዕዛዝ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም?የሚሉ ጭብጦችን በመያዝ እንደሚከተለው መርምረነዋል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ

አመልካች ለሐራጅ የቀረበችው መኪና ዋጋ ወቅታዊ የገበያ ዋጋ አይደለም፤መኪናው ሐገር ውስጥ ሲገባ ለግብር አከፋፈል ተብሎ በኢትዮጲያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን የተቀመጠለትን ግምት በመነሻነት መወሰዱ ተጫራች እንዳይቀርብ ከማድረጉም በተጨማሪ ከአፈጻጸም ሕግ ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረን ነው በማለት የሚከራከሩ ቢሆንም የመኪናውን ግምት በተመለከተ መኪናው ጨረታ ከመውጣቱ በፊት የተቃወሙ ለመሆኑ የክርክሩ ሒደት አያሳይም፡፡

በፍርድ አፈጻጸም ጉዳይ ማናቸውም ንብረት በሐራጅ እንዲሸጥ በሚወሰንበት ጊዜ የሚሸጠው ንብረት ከትክክለኛው የዋጋ ግምት አላግባብ ከፍ ወይም ዝቅ ተደርጎ እንዳይገመት ለማድረግ እና በንብረቱ ግምት ምክንያት በፍርድ ባለገንዘቡም ሆነ በፍርድ ባለዕዳው ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት መከላከል እንዲቻል ፍርድ ቤቱ የሐራጁን ሥርዓት አፈጻጸም ለሕዝብ ማስታወቅ እንዳለበት፤የሚሸጠው ንብረት ዓይነት እና ግምት በሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያው ውስጥ ከሚገለጹት ነገሮች ውስጥ አንዱ እንደሆነ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 423/1እና2 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡አመልካች የመኪናው ግምት ተጋኗል የሚሉ ከሆነ የጨረታው ቀን ከመድረሱ በፊት የጨረታውን ትዕዛዝ ለሰጠው ፍ/ቤት ግምቱ ተጋኗል በማለት መቃወሚያ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

አመልካች የጨረታው ቀን ከመድረሱ በፊት ግምቱ ተጋኗል በማለት ያቀረቡት መቃወሚያ ሳይኖር በጨረታው ቀን በቀረበው ግምት መሠረት ተጫራች ስላልቀረበ አስቀድሞ የተያዘው ግምት የገበያን ዋጋ መሠረት አላደረገም በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ተገቢ አይደለም፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 428/2 በሁለተኛው የጨረታ ማስታወቂያ በተወሰነው ቀን ተጫራች ያልቀረበ እንደሆነ ማናቸውም ተቃራኒ ድንጋጌ ቢኖርም እንኳን ለጨረታ የቀረበውን ንብረት የፍርድ ባለገንዘቡ ተረክቦ እንዲይዝ ትዕዛዝ ሊሰጥ እንደሚችል፤ይህም በሆነ ጊዜ ፍርዱ በሙሉ ወይም በከፊል እንደተፈጸመ እንደሚቆጠር ይደነግጋል፡፡ከድንጋጌው ይዘት መገንዘብ የሚቻለው የፍርድ ባለገንዘቡ ለጨረታ የቀረበውን ንብረት እንዲረከብ ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችለው የፍርድ ባለገንዘቡ

ንብረቱን ለመረከብ ፈቃደኛ ከሆነ እንጂ ከፈቃዱ ውጪ ንብሩቱን እንዲረከብ የማይደረግ መሆኑን ነው፡፡የፍርድ ባለመብት ንብረቱን ለመረከብ ፍቃደኛ ከሆነ ምላሽ ሊሰጠው የሚገበው ቁልፍ ነጥብ ለጨረታ የቀረበው ንብረት ግምት ለፍርድ ባለገንዘቡ ሊከፈለው ከሚገባው የገንዘብ መጠን የሚበልጥ ከሆነ የፍርድ ባለመብት ልዩነቱን የመክፈል ሀላፊነት አለበት? ወይስ የለበትም? የሚለው ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ለጨረታ የቀረበችው መኪና ግምት ብር 731,426.05 / ሠባት መቶ ሠላሳ አንድ ሺህ አራት መቶ ሐያ ሥድስት ብር ከዜሮ አምሥት ሣንቲም / በመሆኑ እና ለአመልካች ሊከፈል የሚገባ አጠቃላይ የገንዘብ መጠን ብር 446,098.57 / አራት መቶ አርባ ሥድሥት ሺህ ዘጠና ሥምንት ብር ከሐምሳ ሠባት ሣንቲም / በመሆኑ ለጨረታ በቀረበችው መኪና ዋጋ ግምት እና ለአመልካች ሊከፈል በሚገባው የገንዘብ መጠን መካከል የብር 285,327.48 /ሁለት መቶ ሠማንያ አምሥት ሺህ ሦስት መቶ ሐያ ሠባት ብር ከአርባ ሥምንት ሣንቲም / ልዩነት አለ፡፡

ከላይ በአንደኛው ጭብጥ እንደተገለጸው ንብረት በሐራጅ እንዲሸጥ በሚወሰንበት ጊዜ የሚሸጠው ንብረት ከትክክለኛው የዋጋ ግምት አላግባብ ከፍ ወይም ዝቅ ተደርጎ እንዳይገመት ለማድረግ እና በንብረቱ ግምት ምክንያት በፍርድ ባለገንዘቡም ሆነ በፍርድ ባለዕዳው ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት መከላከል እንዲቻል የሚሸጠው ንብረት ዓይነት እና ግምት በሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያው ውስጥ የሚገለጽ በመሆኑ እና አመልካች የጨረታው ቀን ከመድረሱ በፊት ግምቱን በሚመለከት ያቀረቡት መቃወሚያ የሌለ በመሆኑ አስቀድሞ የቀረበውን የዋጋ ግምት እንደተቀበሉት ግምት የሚወሰድበት ነው፡፡

አመልካች ለጨረታ የቀረበውን የመኪናዋን ዋጋ ግምት ከጨረታው ቀን በፊት ባልተቃወሙበት ሁኔታ በሁለተኛው ጨረታ ተጫራች ስላልቀረበ ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍለው በሚገባው የገንዘብ መጠን ልክ መኪናዋን ልረከብ ይገባል በማለት የሚያቀርቡት ክርክር ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 423 እና 428 ድንጋጌዎች ዓላማ ውጪ በመሆኑ በዚህ አግባብ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

የክልሉ ፍ/ቤቶች በሁለተኛው ጨረታ ተጫራች ስላልቀረበ በመኪናዋ ዋጋ እና ለአመልካች ሊከፈለው በሚገባ የገንዘብ መጠን መካከል ያለውን ልዩነት አመልካች ሊከፍሉ ይገባል በማለት የደረሱበት መደምደሚያ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 423 እና 428 ድንጋጌዎች ዓላማ አኳያ ተቀባይነት ያለው ቢሆንም በሁለተኛው ጨረታ ተጫራች ባለመቅረቡ ምክንያት የፍርድ ባለመብቱ ለጨረታ የቀረበውን ንብረት እንዲረከቡ ትዕዛዝ ሊሰጥ የሚችለው የፍርድ ባለመብቱ ለጨረታ በቀረበው የገንዘብ መጠን መሠረት ንብረቱን ለመረከብ ፈቃደኛ መሆኑ በቅድሚያ ከተረጋገጠ በኋላ ነው፡፡የክልሉ ፍ/ቤቶች አመልካች ንብረቱን ለጨረታ በቀረበው የገንዘብ መጠን መሠረት ለመረከብ ፈቃደኛ መሆናቸውን በቅድሚያ ሳያረጋግጡ አመልካች በመኪናዋ ዋጋ እና ለአመልካች ሊከፈል

በሚገባው የገንዘብ መጠን  መካከል ያለውን ልዩነት ከፍለው መኪናዋን ይረከቡ በማለት የሰጠው ትዕዛዝ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 428/2 ድንጋጌን ያላገናዘበ እና መሠረታዊ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በሽሬ እንዳስላሴ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 20344 ሕዳር 09 ቀን 2008 ዓ.ም ተሰጥቶ፤በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 81864 የካቲት 30 ቀን 2008 ዓ.ም በትዕዛዝ የጸናው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. የክልሉ ፍ/ቤቶች አመልካች ለጨረታ በቀረበው የዋጋ መጠን እና ሊከፈላቸው በሚገባው የገንዘብ መጠን መካከል ያለውን ልዩነት ከፍለው መኪናዋን ለመረከብ ፈቃደኛ መሆናቸውን በቅድሚያ ሳያረጋግጡ አመልካች ልዩነቱን ከፍለው መኪናዋን እንዲረከቡ በማለት የሰጡት ውሳኔ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 428/2 ድንጋጌን ያላገናዘበ ነው ብለናል፡፡
3. በሁለተኛው ጨረታ ተጫራች ባለመቅረቡ ምክንያት አመልካች ለጨረታ በቀረበው የዋጋ መጠን እና ሊከፈላቸው በሚገባው የገንዘብ መጠን መካከል ያለውን ልዩነት ከፍለው መኪናዋን እንዲረከቡ ሊገደዱ አይገባም በማለት ወስነናል፡፡
4. የሽሬ እንዳስላሴ ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች በጨረታ መነሻ ዋጋ ተሽከርካሪውን ለመረከብ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው አፈጻጸሙ በፍርድ ባለዕዳው ሌላ ንብረት ላይ እንዲቀጥል በማድረግ ወይም ለጨረታ በቀረበው ተሽከርካሪ ላይ አፈጻጸሙ የሚቀጥልበት አግባብ ካለም ተገቢውን በመፈጸም አፈጻጸሙን እንዲቀጥል ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1 መሠረት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
5. በዚህ ፍ/ቤት  ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡
6. ሚያዝያ 19 ቀን 2009 ዓ.ም በመዝገቡ የተሠጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ይጻፍ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ፍ

# አምራዊ ንብረት

የሰ/መ/ቁ. 104755

ሕዳር 16 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሐመድ

ተኽሊት ይመሰል

ቀነዓ ቂጣታ

ሰናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- ዱራታ ባትሪ ካምፓኒ የቀረበ የለም

ተጠሪ፡- የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ፅ/ቤት የቀረበ የለም

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ከንግድ ምልክት ምዝገባ ጋር የተያያዘ ክርክር ሲሆን የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ለተጠሪ ፅ/ቤት ያቀረበው የምዝገባ ጥያቄ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ የአመልካች የንግድ ምልክት ይመዝገብልኝ ጥያቄ በተጠሪ ፅ/ቤት ውድቅ ከተደረገ በኋላ ይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ ያቀረበውም በተጠሪ ፅ/ቤት እና በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተፈፀመ የተባለውን የሕግ ስህተት አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡

ከስር የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ አመልካች ለተጠሪ ፅ/ቤት ሚያዝያ 21 ቀን 2005 ዓ.ም ባቀረበው ማመልከቻ “DURA SUN” የሚል የንግድ ምልክት እንዲመዘገብለት የጠየቀ ሲሆን የአመልካች ጥያቄ ያስተናገደው በተጠሪ ፅ/ቤት ስር የተደራጀው ኢንዱስትራዊ ንድፍ ጥበቃና ልማት ዋና የስራ ሂደት አመልካች እንዲመዘገብለት ያቀረበው “DURA SUN” የንግድ ምልክት በፅ/ቤቱ “DURA CELL” በሚል መጥሪያ ሰርተፍኬት ቁጥር 1987 ከተመዘገበ የንግድ ምልክት ጋር በአዋጅ ቁጥር 501/1998 አንቀፅ 7/1/ መሰረት ተመሳሳይ በመሆኑ የንግድ ምልክት ምዝገባ ጥያቄው ውድቅ ተደርጓአል፡፡

አመልካች በስራ ሂደቱ ውሳኔ ቅር በመሰኘት በፅ/ቤቱ ለተቋቋመው ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታው አቅርበዋል፡፡ አመልካች ባቀረበው አቤቱታ ምንም እንኳ ሁለቱ የንግድ ምልክቶች “ዱራ” በሚለው ቃል አንድ አይነት ቢሆኑም “DURA SUN” የሚለው የንግድ ምልክት

በአነጋገር፣ በትርጉም እና በአቋሙ ጠቅላላ ሲታይ “DURA CELL” ከሚለው የንግድ ምልክትና ምርቶቹን በተመለከተ ጥሩ ስምና እምነት ያገኘበት በመሆኑ የንግድ ምልክቱ እንዲመዘገብለት ጠይቋል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴው አጠቃላይ የክርክሩን ይዘት ካሰፈረ በኋላ “DURA CELL” ሎጎ ያለበት የንግድ ምልክት እ.ኤ.አ በ1996 ዓ.ም በፅ/ቤቱ የተቀማጭነት የምስክር ወረቀት በማግኘት በንግድ ምልክቱ ላይ የቀዳሚነት መብት /priority Right/ ያገኘ መሆኑን፣ የንግድ ምልክት ጥበቃ የሚደረግበት ዋነኛ ምክንያት ዕቃ በማምረት፣ በማከፋፈል ወይም አገልግሎት በመስጠት የንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ሰዎችን መልካም ስምና ዝና ለመጠበቅ እንዲሁም በተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች መካከል መሳከርን ለማሶገድ ስለመሆኑ፣ በፅ/ቤቱ በቀዳሚነት ከተመዘገቡ የንግድ ምልክቶች ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው እና መሳከርን የሚያስከትሉ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ሊመዘገቡ እንደማይገባ፤ ሁለቱም የንግድ ምልክቶች በዕይታ፣ በንባብ፣ በድምጸት ተመሳሳይነት ያላቸውና በህብረተሰቡ ዘንድ መሳከርን ሊፈጥሩ የሚችሉ መሆናቸውን ኮሚቴ መገንዘቡን፣ በተመሳሳይ ሁለቱ የንግድ ምልክቶችን ለባትሪ ምርት የሚያገለግሉ በመሆኑና ይህንንም ምርት የሚጠቀሙ ሸማቾች ወይም አግባብነት ያላቸው የሕ/ሰቡ ክፍሎች በአንፃራዊነት ከሌሎች ምርቶች አኳያ ሲታይ ኢኮኖሚያዊ አቅማቸው እና የትምህርት ደረጃቸው ዝቅተኛ የሆኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚጠቀሟቸው ምርቶች በመሆናቸው ሁለቱም የንግድ ምልክቶች በአግባቡ ለይተው ይገዛሉ ብሎ መናገር አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ በመሆኑም አመልካች “DURA SUN” በሚል መጥሪያ እንዲመዘገብለት የጠየቀው የንግድ ምልክት ጋር ከዚህ በፊት በፅ/ቤቱ ከተመዘገበው “DURA CELL” ሎጎ የንግድ ምልክት ጋር ተመሳሳይና በሕብረተሰቡ ዘንድ መሳከርን ሊያስከትል የሚችል በመሆኑ የንግድ ምልክትና ኢንዱስትሪያል ንድፍ ጥበቃና ልማት ዋና የስራ ሂደት የሰጠው ውሳኔ ኮሚቴው ተቀብሎ አፅንቶታል በማለት ወስኗል፡፡

የፅ/ቤቱ የበላይ ኃላፊም በይግባኝ ሰሚ ኮሚቴ የተሰጠው ውሳኔ በማፅደቅ ለአመልካች አሳውቀዋል፡፡ አመልካች በፅ/ቤቱ የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረበው ይግባኝ አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ ያቀረበውም በተጠሪ ፅ/ቤት እና ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔና ትዕዛዝ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች ሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘትም ሁለቱም የንግድ ምልክቶች በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ እንደሆኑ፣ የመጀመሪያ ሶስት ፊደሎች ተመሳሳይ በመሆናቸው ብቻ የንግድ ምልክቶቹ መሳከር ይፈጥራሉ ተብሎ መወሰኑ በአዋጅ ከተቀመጠው ትርጉም ውጭ ስለመሆኑ፣ በንባብ፣ በአተረጓጎምና ድምጸት አንድ ናቸው የተባለውም በአግባቡ አለመሆኑን፣ ፅ/ቤቱ አንድ የህብረተሰብ ክፍል ብቻ መሰረት በማድረግ ምዝገባ መከልከሉ የአመልካች መብት በእጅጉ የጣሰ በመሆኑ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ የአሁኑ አመልካች ለተጠሪ ባቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ላይ እንደገለፀው “ዱራታ” የሚለውን ምልክት አስቀድሞ

ያስመዘገበውና በብዙ ሀገሮች አስመዝግቦ እየተገለገለ የሚገኝበት ከሆነ "DURA SUN" የሚለው "DURA CELL" ከሚለው የንግድ ምልክት ጋር የተመሳሰለ ነው ወይስ አይደለም? ለማለት "DURA" የሚለውን ቃል ለምን ተጠቀመ የሚለውን ምክንያት ለፍርድ ሐተታው እና መነሻ ማድረጉና በዚህም የተነሳ ያሳክራል ከሚል መደምደማያ የደረሰበትን አግባብነት ተጠሪን ባለበት ይጣራ ዘንድ ያስቀርባል ተብሏል፡፡ ተጠሪም ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ የበኩሉን መልስ የሰጠ ሲሆን ዋናው ፍሬ ጉዳይ የአመልካች የንግድ ምልክት ይመዝገብልኝ ጥያቄ ውድቅ የተደረገው በፅ/ቤቱ ቀደም ከተመዘገበው የንግድ ምልክት ተመሳሳይነት ያለውና መሳከርን የሚፈጥር መሆኑን ተረጋግጦ በመሆኑ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግ አመልክቷል፡፡ የመልስ መልስም ቀርበዋል፡፡

ጉዳዩ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በፅሁፍ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ተጠሪ እና የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጡት ውሳኔና ትዕዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀም አለመፈፀሙን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

እንደመረመርነውም፡- አመልካች እንዲመዘገብለት ያቀረበው የንግድ ምልክት /trade mark/ "DURA SUN" የሚል ነው፡፡ ተጠሪ የአመልካች ጥያቄ ውድቅ ያደረገው በፅ/ቤቱ አስቀድሞ የተመዘገበ "DURA CELL" የሚል የንግድ ምልክት እንዳለና አሁን ለምዝገባ የቀረበው "DURASUN" በዕይታ፣ በንባብ እና በድምጸት ተመሳሳይነት ያለው በመሆኑ በህብረተሰቡ ዘንድ መሳከርን ይፈጥራል በሚል መነሻ ነው፡፡ የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ፅ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 320/1995 አንቀፅ 6 ከተሰጡት ስልጣንና ተግባራት አንዱ የንግድ ምልክት መመዝገብ ስለመሆኑ መገንዘብ ተችሏል፡፡ የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/1998 የሰጠበት መሰረታዊ ዓላማ "ዕቃ በማምረት እና በማከፋፈል ወይም አግለግሎት በመስጠት የንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ሰዎችን መልካም ስም እና ዝና ለመጠበቅ እንዲሁም በተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች መካከል መሳከርን ለማሰወገድ የንግድ ምልክት ጥበቃ ማድረግ በማስፈለጉ" እንደሆነ በአዋጅ መግቢያ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ በዚህ አዋጅ መሰረት ከቀዳሚ የንግድ ምልክት ጋር አንድ ዓይነት የሆነ ወይም መሳከርን ሊያስከትል የሚችል ተመሳሳይነት ያለው የንግድ ምልክት መመዝገብ እንደማይቻል በአንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 1 ተደንግጓአል፡፡ በተያዘው ጉዳይ በተጠሪ ፅ/ቤት እ.ኤ.አ በ1996 ዓ.ም ተመዝግቦ የተቀማጭነት የምስክር ወረቀት ያገኘ፣ "DURA CELL" ተ ሎጎ ያለበት የንግድ ምልክት መኖሩን ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ አመልካች እንዲመዘገብለት ያቀረበው የንግድ ምልክት "DURA SUN" የሚል መሆኑን አልተካደም፡፡ እነዚህ ሁለት ምልክቶች የጋራ የሆነ "ዱራ" የሚል መነሻ ቃል ያላቸው ከመሆኑ በተጨማሪ በዕይታ፣ በንባብ፣ በድምጸት ተመሳሳይነት ያላቸው ስለመሆኑ የተጠሪ ፅ/ቤት ባደረገው ማጣራት

አረጋግጧል፡፡ ምዝገባ የተጠየቀበት የንግድ ምልክት አስቀድሞ ከተመዘገበው የንግድ ምልክት በአብዛኛው የሕብረተሰብ ክፍል ወይም ተገልጋዮችና ሸማቾች መሳከርን የሚፈጥር መሆኑን ግንዛቤ ከተወሰደበት ሊመዘገብ እንደማይገባ ከአዋጅ ቁጥር 501/1998 አንቀፅ 7 ድንጋጌ መሰረታዊ ይዘት የምንገነዘበው ነው፡፡ አመልካች እንዲመዘገብለት ያቀረበው የንግድ ምልክት "DURA SUN" አስቀድሞ ከተመዘገበው "DURA CELL" ባትሪ ተመሳሳይነት ያለው በመሆኑ በአብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል መሳከርን የሚፈጥር ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች ያቀረበው የምዝገባ ጥያቄ በተጠሪ ውድቅ መደረጉ ከላይ የተመለከተውን አዋጅ ዓላማና ግብ በአግባቡ ተፈፃሚ አድርጎአል ከሚባል በስተቀር በጉዳዩ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀሙን አያሳይም፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 57179 የካቲት 22 ቀን 2003 ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ በንግድ ምልክት መመሳሰል በአንድ ምርት ወይም አገልግሎት ጋር በተገናኘ ሁኔታ የሕዝብ ግንዛቤ ያዛባ ወይም ሊያዛባ የሚችል፤ በሁለት ድርጅቶች መካከል መሳከርን የሚፈጥር ከሆነ ሕ/ሰቡ ሊያገኝ የሚገባው ሕጋዊ ጥበቃና ዋስትና በተሟላ ሁኔታ ተፈፃሚ ለማድረግ የሚያስችል በመሆኑ በተመሳሳይ የንግድ ምልክት ላይ ምዝገባ እንዲደረግ የሚቀርበው ጥያቄ ተቀባይነት እንደሌለው አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ ይህ ችሎትም የሰጠው ገዥ የሕግ ትርጉም ደግሞ በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ በሁሉም ደረጃ ባሉ ፍርድ ቤቶች ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀፅ 2/1/ ስር ተደንግጓል፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የአመልካች የንግድ ምልክት ምዝገባ ጥያቄ በተጠሪ ውድቅ መደረጉ እና የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤትም በአመልካች ያቀረበው ይግባኝ ቅሬታ መሰረዙ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ፅ/ቤት የሰጠው ውሳኔ፤ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 148038 በ3/10/2006 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ፀንቷል፡፡
2. በዚህ ፍርድ ቤት በተደረገው ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልስናል፡፡የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

# ልዩ ልዩ

የሰ/መ/ቁ. 120355

ሕዳር 06 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

አብዬ ካሳሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- ወ/ሪት ሐናን እስማኤል አብዱልዋሂድ ጠበቃ ወርቁ መንገሻ ቀረቡ፡፡

ተጠሪ፡- የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለጉዳዩ መቅረብ ምክንያት የሆነው አዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 24125 መስከረም 14 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ዳኝነት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ታይቶ ሊታረምልኝ ይገባል በማለት አመልካች በጠበቃቸው አማካኝነት ህዳር 13 ቀን 2008 ዓ.ም የተፃፈ 04 ገጽ የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የአመልካች የሥር አቤቱታ ይዘት በአጭሩ፡-ታህሳስ 10 ቀን 1987 ዓ.ም ከአባታቸው ከአቶ እስማኤል አብዱልዋህድና ከእናታቸው ከወ/ሮ ሳባ አልታሰብ አርባ ምንጭ ከተማ ውስጥ ተወልደው ስማቸው ሐናን እስማኤል አብዱልዋሂድ በሚል ተፅፎ የምስክር ወረቀት ማግኘታቸውን፤ በኋላም የእናታቸው ወንድም ሚስት የሆኑት ወ/ሮ መአዛ አዳነ አሻሜ ሮሆቦት አካዳሚ በተባለው ት/ቤት ሲያስመዘግቡ ሀና አዳነ አሻሜ በሚል ስም ያስመዘገቧቸውና በሂደትም በዚህ ስም የልደት የምስክር ወረቀት የወጣላቸው መሆኑን፤ ከዚያም ወደ ወላጆቻቸው አካባቢ በመመለስ አስቀድሞ በወጣላቸው ሐናን እስማኤል አብዱልዋሂድ በተባለው ስማቸው እየተጠሩ የቀበሌ አስተዳደር መታወቂያ ወጥቶላቸውና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም ተመዝግበው እየተማሩ እንደሚገኙ ገልፀው የስማቸው መጠሪያ በተለያየ አጋጣሚ በተለያየ ስም የተመዘገበ በመሆኑ

ችግር ያስከተለባቸው መሆኑን በመጥቀስ ሐናን እስማኤል አብዱልዋሂድ ተብለው እንዲጠሩ እንዲወሰንላቸው አቤቱታ አቅርበው ነበር፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች በትክክለኛው ወላጅ አባታቸው በአቶ እስማኤል አብዱልዋሂድ ስም ልጠራ ያሉ በመሆናቸው ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ልጅነትን አረጋግጠው ይቅረቡ በማለት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የይግባኝ ቅሬታ በኂላም የሰበር አቤቱታ አቅርበው የነበሩ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኙም፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ የቀረበው የሥር ፍርድ ቤቶች ዳኝነት መሠረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል በሚል ሲሆን አቤቱታቸው በአጭሩ፡ የአመልካች አቤቱታ የማንንም ጥቅምና መብት የማይነካ፤ በአሳማኝ ማስረጃም ተደግፎ የቀረበ ሆኖ እያለ የሥር ፍርድ ቤቶች ከውልደቴ ጀምሮ በወጣልኝ ስም ለመጠራት ያቀረብኩትን አቤቱታ ውድቅ ያደረጉት ያላግባብ በመሆኑ ሊታረምልኝ ይገባል  በሚል ያቀረቡት ነው፡፡

ሰበር አጣሪው ችሎቱም መዝገቡን መርምሮ የሥር ፍርድ ቤቶችን ዳኝነት ተገቢነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ በመወሰኑ በጉዳዩ ላይ ተጠሪ የሆነ ተከራካሪ ባለመኖሩ መዝገቡ ለምርመራ የቀረበ ነው፡፡

ክርክሩ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ተጠናቋል፡፡ እኛም አቤቱታው ለሰበር ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አንጻር ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመረነው ምላሽ ማግኘት ያለበት ነጥብ አመልካች በወላጅ አባታቸው እስማኤል አብዱልዋሂድ ስም መጠሪያቸው እንዲሆን የአቀረቡትን አቤቱታ የሥር ፍርድ ቤቶች ውድቅ ያደረጉበት አግባብ ተገቢ ነውን? የሚለው ጭብጥ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በፍትሐብሔር ህግ አንቀጽ 32(1) ሥር በመርህ ደረጃ እንደተመለከተው አንድ ሰው የቤተዘመድ ስም፤ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የግል ስሞች እና የአባት ስም እንደሚኖረው ተደንግጓል፡፡ ለልጁ አባት ስም የሚሆነውም የአባቱ የግል ስም ለመሆኑ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 36 ሥር ተመልክቷል፡፡ ስለ ልጅ መወለድ መግለጫ ሊሰጥ የሚገባው ሰው ልጁ ከተወለደበት ቀን አንስቶ በዘጠና ቀናት ውስጥ ለልጁ የተሰጠውን የግል ስም ልጁ በተወለደበት ቀበሌ ለሚገኘው የክብር የመዝገብ ጽ/ቤት መግለጫ የማቅረብ ግዴታ የተጣለበት ለመሆኑም ከፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 37 መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡ በዚህ ረገድ አመልካች ተወልድኩ በሚሉበት በ1987 ዓ.ም በአገራችን ልደት ጋብቻና ሞት የሚመዘገብ የክብር መዝገብ ሹም በህግ አግባብ ተቋቁሞ በተደራጀ መልኩ ሥራ ላይ ያልነበረ በመሆኑ የአንድ ሰው ስምን በተመለከተ ተደራጅቶ የተጻፈ ማስረጃ

ማግኘት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ በመሆኑም አመልካች በተወለዱበት ወቅት ልደትን፣ሞትንና ጋብቻን ባግባቡ መዝግቦ ለመያዝ የሚችል የተደራጀ አካል ባለመኖሩ በወላጆች የወጣላቸው ስም በአጎታቸው ሚስት አማካኝነት ተለውጦ በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ ስሞች መጠራታቸውንና የአባታቸውም ስም በተወለዱበት ጊዜ በሆስፒታሉ የምስክር ወረቀት የሰፈረውና በአሁኑ ጊዜ በቀበሌ መታወቂያቸውና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተመዝግበው የሚገኘው ለመሆኑ በፍርድ ቤት እንዲነገርላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሥር መዝገቡ ያስረዳል፡፡

አመልካች አሳዳጊያቸው የነበሩት የአጎታቸው ሚስት ባስመዘገቢቸው ሀና አዳነ አሻሜ በሚል ስም ሮሆቦት አካዳሚ ተመዝግበው መማራቸው፣ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም የልደት ምስክር ወረቀት ማውጣታቸውን ገልፀዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ወደ ተወለዱበት አካባቢ ተመልሰው ሐናን እስማኤል አብዱልዋሂድ በሚል ስም የቀበሌ መታወቂያ በማውጣት እስከ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተመዝግበው እየተማሩ እንደሚገኙና ይህ ስማቸው አስቀድሞ በተወለዱበት ጊዜ የወጣላቸውና በሆስፒታሉ ምስክር ወረቀት የተመዘገበ ለመሆኑ እየተከራከሩ ይገኛሉ፡፡

አንድ ሰው የቤተዘመድ ስም እንዲለወጥ የመጠየቅ መብት ያለው መሆኑን በዚህ ረገድ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ፍርድ ቤቶች በሶስተኛ ወገኖች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ በጥንቃቄ በመመርመር ስሙን ለመለወጥ በቂ ምክንያት ሲኖር መለወጥ እንደሚችሉ በፍትሐብሔር ህጉ አንቀጽ 42 ሥር የተደነገገ ሲሆን በዚሁ ህግ አንቀጽ 43 ሥር ደግሞ አንድ ሰው የግል ስሙ እንዲለወጥ ወይም ከብዙዎች የግል ስሞች አንዱ እንዲሰረዝ፣ ወይም ሌላ ግል ስም እንዲጨመርለት ባለጥቅሙ ጥያቄ ባቀረበ ጊዜ ሊፈቀድለት እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ በዚህ ረገድ የሚቀረቡ ጥቄዎችን ፍርድ ቤቶች የአመልካቾችን ስም በማስተካከል ሊወስኑ እንደሚገባቸው የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 87420 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ያደረጉበት ምክንያት ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ልጅነት ሳይረጋገጥ የአባትን ስም መለወጥ አይገባንም በሚል መነሻ ለመሆኑ ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ አመልካች የጠየቁት ዳኝነት ስሜ ሐናን እስማኤል አብዱልዋሂድ ለመሆኑ የሚያመለክቱ ማስረጃዎች ያሏቸው መሆኑን በመግለፅ በተወለዱበት ጊዜ በዚህ ስም ተጠርተው እንደነበርና በሂደት የአጎታቸው ሚስት በአሳዳጊነት ዘመናቸው ስማቸውን የለወጡባቸው መሆኑንና በኋላም ሲወለዱ ወደ ወጣላቸው ስም ተለውጦ እየተጠሩበት እንደሚገኝ ይህንን የሚያስረዱ ማስረጃዎች መኖራቸውን በማጣቀስ እየተከራከሩ ይገኛሉ፡፡ ስለሆነም ዋናውና መጣራት ያለበት ነጥብ አመልካች በፍሬ ጉዳይነት የሚያነሱት በየጊዜው በተለያዩ ስሞች የመጠራት ወይም ያለመጠራት ጉዳይ ሊሆን ይገባል እንጂ የአመልካች ወላጅ አባት ማን ነው የሚል ጭብጥ ሊሆን አይችልም፡፡ ክርክሩ ያስነሳውን ጭብጥ ፍርድ ቤቶች ምላሽ በሚሰጡበት

ጊዜ የሶስተኛ ወገኖችን ጥቅም እንዳይጎዳ ተገቢ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ የሌላን ሰው ስም ያላግባብ የሚጠቀም ወገን ካለም ህጉ ኃላፊነትን የሚያስከትል ለመሆኑ የደነገገው በመሆኑ ስም ይለወጥልኝ በሚል ጥያቄ የሚያቀርብም ወገን ጥንቃቄ ማድረግ የሚገባው ነው፡፡ በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች ጉዳይን ከቀረበው የዳኝነት ጥያቄ አንፃር በመመልከትና በአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41(1)(ሰ) መሠረት በመቀበል የአመልካችን ስም መለወጥ አስፈላጊ የሚያደርጉ ሁኔታዎች መኖር አለመኖራቸውን በማስረጃ አጣርተውና የሶስተኛ ወገን ጥቅም የማይጎዳ ለመሆኑ ጭምር ካረጋገጡ በኂላ ተገቢውን መወሰን ሲገባቸው ጉዳዩን ከልጅነት ይረጋገጥልኝ ጥያቄ አንፃር በመመልከት ውድቅ ማድረጋቸው አግባብነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም የሚከተለውን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 4332/07 ሐምሌ 01 ቀን 2007 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ፣የአዲስ አበባ ከተማ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 24075 ነሐሴ 11 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 24125 መስከረም 14 ቀን 2008 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች ጥያቄ የሥም ለውጥ ስለሆነ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41(1)(ሰ) መሠረት ስልጣን አለው ብለናል፡፡ ጉዳዩን የማየት ሥልጣን አለው ብለናል፡፡
3. በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች ስማቸው እንዲለወጥላቸው ያቀረቡትን አቤቱታና ማስረጃ አስቀርቦ በመመርመር የአመልካች ስም መለወጥ በሶስተኛ ወገኖች መብት የሚያስከትለው ጉዳት መኖር አለመኖሩን ጭምር ካጣራ በኂላ ተገቢውን እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 341(1) መሠረት መልሰናል፡፡ ይፃፍ፡፡
4. በዚህ ችሎት ክርክር የወጣ ወጭና ኪሳራ አመልካች የራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ት/ጌ

የሰ/መ/ቁ 110507

ሕዳር 30 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡-አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሠለ

አብዬ ካሣሁን

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አቶ ጉታ ጫካ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡-1.የኦሮሚያ ፍትሕ ቢሮ አልቀረቡም

2. አቶ አብዱልወሃብ ተካ አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ በጥብቅና አገልግሎት ላይ በተፈጸመ የሥነምግባር ጥሰት ምክንያት የተሰጠ የዲስፐሊን ውሳኔን የሚመለከት ነው፡፡ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠበቆች የሥነምግባር ጉዳይ ጉባኤ የአሁን አመልካች የጥብቅና አገልግሎት ሲሰጡ ፈጽመውታል በተባለው የሥነምግባር ጥሰት ምክንያት የቀረበባቸውን የዲሲፐሊን ክስ ተመልከቶ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡በአመልካች ላይ የቀረበው የዲስፐሊን ክስ በአጭሩ፡-

1. ሁለተኛ ተጠሪ ንብረትነቱ የወ/ሮ ላቀች ጎሳዬ በሆነ አይሱዙ ተሽከርካሪ እየተጓዙ የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 3-00972 ኢት የሆነ እና አቶ መሐመድ ይመር የተባለ ግለሰብ ሲነዳው ከነበረ ተሽከርካሪ ጋር በመጋጨት እሳቸውን ጨምሮ በአይሱዙ መኪናው ውስጥ በነበሩ ግለሰቦች ላይ ጉዳት የደረሰባቸው በመሆኑ ጉዳቱን አድርሷል በተባለው አቶ መሐመድ ይመር ላይ የወንጀል ክስ ቀርቦበት የነበረ ቢሆንም አመልካች ለግለሰቡ ጥብቅና በመቆም ከወንጀል ክሱ በነጻ እንዲሰናበት በማድረጋቸው፤

2. ሁለተኛ ተጠሪ ለደረሰባቸው ጉዳት ካሳ እንዲከፈላቸው በማለት ሲጓዙበት የነበረው አይሱዙ ተሽከርካሪ ባለቤት ወ/ሮ ላቀችጎሳዬ ላይ ባቀረቡት ክስ አመልካች ተከሳሽዋን ወክለው የጥብቅና አገልግሎት በመስጠታቸው፤
3. ሁለተኛ ተጠሪ ካሣ እንዲከፈላቸው ባቀረቡት ክስ ላይ ጣልቃ ገብ ሆኖ ለሚከራከረው የመድን ድርጅት አመልካች ጠበቃ በመሆን በመከራከራቸው ምክንያት አመልካች ሁሉንም ወገኖች በመወከል መከራከር አይችሉም የሚል መቃወሚያ 2ኛ ተጠሪ ያቀረቡ መሆኑን፤ክርክሩን ሲመራ የነበረው ፍ/ቤት አመልካች ተከሳሽን እና ጣልቃገብን በመወከል ክርክሩ እንዲቀጥል ቢደረግ የጥቅም ግጭት ሊኖር አይችልም ለማለት ስለማይቻል እና የጥቅም ግጭቱ ካለ ደግሞ የክርክሩን ሂደት የሚያዛባ በመሆኑ አመልካች ተከሳሽ / የጉዳት አድራሹን መኪና ባለቤት / እና ጣልቃ ገብን / መድን ድርጅትን / ወክሎ መከራከር አይችልም ተከሳሽ ሌላ ሰው በመወከል ወይም በራሷ እንድትከራከር በማለት ብይን የሰጠ መሆኑን፤በዚህ ብይን ላይ በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች ክርክር ተደርጎበት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 90540 የተሰጠውን ብይን ያጸናው መሆኑን በመግለጽ አመልካች የጥብቅና ሙያ የሥነ ምግባር ጥሰት የፈጸሙ በመሆናቸው ቅጣት እንዲተላለፍባቸው የሚል ነው፡፡

አመልካች ለቀረበባቸው የዲሲፒሊን ክስ በሰጡት መልስ አመልካች ተከሳሽ እና ጣልቃ ገብን ወክሎ መከራከር አይችልም በማለት ብይን የተሰጠው ግንቦት 23 ቀን 2004 ዓ.ም በመሆኑ ጉዳዩ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን፤ጉዳዩ መታየት ያለበት በአዋጅ ቁጥር 86/96 እንጂ በአዋጅ ቁጥር 182/2005 ሊታይ የማይገባ መሆኑን፤ተከሳሽን በመወከል እንዳይከራከሩ የሚያግዳቸው ሕግ የሌለ መሆኑን፤ተከሳሽ በፍትሐብሔር ጉዳይ ጥፋት የሌለባቸው መሆኑን፤ተከሳሽን ወክለው መከራከራቸው በአመልካች ላይ የሚደርስ ጉዳት የሌለ መሆኑን፤ተከሳሽ ለተሽከርካሪዋ መድን ሽፋን ያላቸው በመሆኑ እና ለመድን ድርጅቱ ጠበቃ በመሆናቸው መድን ድርጅቱን ወክለው መልስ መስጠታቸው ጥፋት አለመሆኑን፤በተከራካሪዎች ላይ ሊፈጠር የሚችል የጥቅም ግጭት የሌለ መሆኑን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የሥነ ምግባር ጉዳይ ጉባኤ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠው ጥር 29 ቀን 2006 ዓ.ም በመሆኑ አመልካች ጉዳዩ በአዋጅ ቁጥር 182/2005 መሠረት መታየት የለበትም በማለት ያቀረቡት መቃወሚያ አመልካች ተከሳሽን እና ጣልቃገብን በመወከል ሊከራከር አይገባም በማለት ታሕሳስ 23 ቀን 2004 ዓ.ም የተሰጠው ብይን በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች ክርክር ሲደረግበት ቆይቶ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠው ጥር 29 ቀን 2006 ዓ.ም በመሆኑ እና የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠውም አዋጅ ቁጥር 182/2005 ከታወጀ በኋላ በመሆኑ ጉዳዩ በቀድሞ አዋጅ መሠረት መታየት አለበት

በማለት የቀረበው ቅሬታ የሕግ መሠረት የለውም፤የይርጋ መቃወሚያውን በተመለከተ የቀረበው ክርክር በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠው ጥር 29 ቀን 2006 ዓ.ም በመሆኑ እና 2ኛ ተጠሪ ለጉባኤው አቤቱታ ያቀረቡት ነሐሴ 13 ቀን 2006 ዓ.ም በመሆኑ የይርጋ መቃወሚያው ተቀባይነት የለውም በማለት የአመልካችን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ አድርጓል፡፡ በዋናው ጉዳይ ላይም አመልካች የአደጋ አድራሹ መኪና አሽከርካሪ በሆነው ግለሰብ ላይ የቀረበበትን የወንጀል ክስ በጥብቅና በመከራከር በነጻ እንዲሰናበት አድርጓል፤2ኛ ተጠሪ ባቀረበው የፍትሐብሔር ክስ ላይ ተከሳሽ ለሆኑት የመኪናው ባለቤት እና ጣልቃገብቶ ለተከራከረው መድን ድርጅት በጥብቅና በመወከል የጥቅም ግጭት ባለው ጉዳይ ላይ በመከራከሩ በ2ኛ ተጠሪ ተቃውሞ ቀርቦበት ጉዳዩን ሲያይ የነበረው ፍ/ቤት አመልካች ተከሳሽን እና ጠልቃገብን በመወከል ክርክሩ እንዲቀጥል ቢደረግ የጥቅም ግጭት ሊኖር አይችልም ለማለት ስለማይቻል እና የጥቅም ግጭቱ ካለ ደግሞ የክርክሩን ሂደት የሚያዛባ በመሆኑ አመልካች ተከሳሽ እና ጣልቃ ገብን ወክሎ መከራከር አይችልም በማለት ብይን ሰጥቶበታል፤ይህ ብይን እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ክርክር ተደርጎበት ጸንቷል፤አመልካች በተሰጠው ብይን ላይ የሕግ ሥሕተት ተፈጽሟል በማለት በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች ቅሬታ በማቅረብ ክርክሩን አሳግዶ የ2ኛ ተጠሪ ጉዳይ በወቅቱ ውሳኔ እንዳይሰጥበት በማድረግ ላልተገባ ወጪ የዳረገው እና ከፍተኛ መጉላላት እንዲደርስበት ያደረገው በመሆኑ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጠበቆች እና ሕግ ጉዳይ ጸሐፊዎች እና የፈቃድ አሠጣጥ አዋጅ ቁጥር 182/2005 አንቀጽ 36/3/15 መሠረት ከባድ የሥነምግባር ጥፋት ፈጽመዋል በማለት አመልካች ብር 10000 / አሥር ሺህ ብር / የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ እና የጥብቅና ፈቃዳቸው ለ6 ወር ታግዶ እንዲቆይ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የሥነ ምግባር ጉባኤው የሰጠውን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡በመቀጠል አመልካች ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም አቤቱታቸው ተቀባይነት አላገኘም፡፡የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሠረታዊ ይዘትም፡-ጉባኤው አመልካች ተከሳሽን እና ጣልቃገብን በመወከል መከራከር አትችልም በማለት ግንቦት 23 ቀን 2004 ዓ.ም በተሰጠው ብይን ላይ ይግባኝ መጠየቅ አልነበረብህም፤ክርክሩንም ማሳገድ አልነበረብህም በማለት ቅጣት የጣለብኝ ቢሆንም ለቅጣቱ መነሻ ያደረገው ምክንያት በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 37 ላይ የተደነገገውን ፍትሕ የማግኘት መብት የሚቃረን ነው፤በጉባኤው እና በበታች ፍ/ቤቶች ያቀረብኩት የይርጋ መቃወሚያ መታለፉም ተገቢ አይደለም፤ጉዳዩ መታየት የነበረበት ቅጣቱን በሚያከብደው አዋጅ ቁጥር 182/2005 ሳይሆን በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 22 መሠረት በአዋጅ ቁጥር 86/96 መሆን

ነበረበት፤2ኛ ተጠሪ ለ3ኛ ወገን ጥቅም የሥነ ምግባር ክስ ማቅረብ ይችላል መባሉ የሰዎችን የመዋዋል ነጻነት የሚነካ ነው፤በሥነምግባር ጉባኤውም ሆነ በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል የሚል ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች ጉዳት አድርሷል ተብሎ በወንጀል የተከሰሰውን ግለሰብ በጥብቅና ወክሎ ተከራክሮ በነጻ እንዲሰናበት ካስወሰነ በኋላ በተሽከርካሪው ባለቤት ላይ የጉዳት ካሣን ማስከፈል በቀረበው ክስ ተከሳሽን እና የመድን ድርጅቱን በመወከል መከራከሩ የጥቅም ግጭት ያስነሳል በማለት መወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎ 2ኛ ተጠሪ መጥሪያ ደሷቸው ባለመቅረባቸው መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል፡፡አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ይህ ችሎትም እንዲጣራ የተያዘውን ነጥብ ብቻ ለጉዳዩ መነሻ ምክንያት ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ ሒደት መገንዘብ የተቻለው በአመልካች ላይ ጉዳት ሊደረስ የቻለው አመልካች ሲጓዙበት የነበረው መኪና እና የወ/ሮ ዘይነባ መሐመድ መኪና በመጋጨታቸው ምክንያት መሆኑን፤አመልካች የጉዳት ካሣ እንዲከፈላቸው ክስ የመሠረቱት ሲጓዙበት በነበረው መኪና ባለቤት ላይ መሆኑን፤የኢትዮጲያ መድን ድርጅት 1ኛ ጣልቃገብ መሆኑን፤ወ/ሮ ዘይነባ መሐመድ 2ኛ ጣልቃገብ መሆናቸውን እና አመልካች የወ/ሮ ዘይነባ መሐመድ መኪናአሽከርካሪ ነው በማለት በወንጀል ተከሶ ለነበረው ግለሰብ፤ለተከሳሽ እና ለ1ኛ ጣልቃገብ ጠበቃ በመሆን መከራከራቸውን ነው፡፡የሥነምግባር ጉባኤው አመልካች የጥብቅና ሙያ ሥነምግባር ጥሰት ፈጽመዋል በማለት የቅጣት ውሳኔ ሊያስተላልፍ የቻለው አመልካች ጉዳት አድርሷል የተባለውን ተሽከርካሪ ሲያሽከረክር በነበረው ግለሰብ ላይ የቀረበውን የወንጀል ክስ ለግለሰቡ ጠበቃ ሆነው በመከራከር በነጻ እንዲሰናበት አድርገዋል፤ተጠሪ ለደረሰባቸው ጉዳት ካሣ እንዲከፈላቸው ተሳፍረው ሲጓዙበት በነበረው ተሽከርካሪ ባለቤት ላይ ባቀረቡት ክስ አመልካች ተከሳሽዋን በመወከል ተከራክረዋል፤በክርክሩ ጣልቃገብ ሆኖ ለሚከራከረው መድን ድርጅትንም በመወከል ተከራክረዋል፤ተጠሪ ጠበቃው ለተከሳሽ እና ለጣልቃገብ በጥብቅና በመወከል መከራከር አይችሉም በማለት ባቀረቡት ተቃውሞ ጉዳዩን ሲመራ የነበረው ፍ/ቤት የጥቅም ግጭት ሊፈጠር ስለሚችል አመልካች ተከሳሽን እና ጣልቃገብን በመወከል መከራከር አይችሉም ተከሳሽ ራሳቸው ወይም ሌላ ጠበቃ በመወከል ይከራከሩ በማለት ብይን ሰጥቷል፤አመልካች በዚህ ብይን ላይ እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ተከራክረውበት ብይኑ ጸንቷል፤አመልካች ክርክሩን በማሳገድ እና በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች በተሰጠው ብይን ላይ ይግባኝ በማቅረብ 2ኛ ተጠሪን ላልተገባ ወጪ ዳርገውታል ከፍተኛ መጉላላትም አድርሰውበታል በሚል ነው፡፡ጉባኤው

ውሳኔ ለመስጠት  በዋነኝነት የሰጠው ምክንያት አመልካች የጥቅም ግጭት በሚፈጥር ሁኔታ ጉዳዩን በአግባቡ የሚያውቁ ሆኖ ሳላ በጉዳዩ በወንጀል ተከሳሽ ለነበረ እና የፍ/ብሔር ክስ ለቀረበባቸው ተከራካሪ ወገኖች ጥብቅና በመቆም ተከራክረዋል፡፡ይህም የጥቅም ግጭት የሚፈጥር መሆኑ ተረጋግጦባቸው እስከ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ ተወስኖባቸዋል የሚል ምክንያት ነው፡፡ጉባኤው አመልካች ለተከሳሽ እና ለጣልቃገብ መከራከር አትችልም በማለት በሰጠው ብይን ላይ በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች ይግባኝ በመጠየቅ እና ክርክሩን በማሳገድ ጉዳዩ በጊዜ እንዳይወሰን በማድረግ 2ኛ ተጠሪን ለአላስፈላጊ ወጪ ዳርገዋል በማለት የሰጠው ምክንያት በአመልካች ላይ ለተጣለው የዲስፕሊን ቅጣት ብቸኛ ምክንያት ሳይሆን ተጨማሪ ምክንያት በመሆኑ አመልካች ጉባኤው ለውሳኔው መሠረት ያደረገው ምክንያት ለተጣለባቸው የዲስፕሊን ቅጣት ብቸኛ ምክንያት እንደሆነ በመውሰድ በጉባኤው የተሰጠው የዉሳኔ ምክንያት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገመንግስት አንቀጽ 37 ላይ የተሰጠውን ፍትሕ የማግኘት መብት የሚጻረር ነው በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ተገቢ አይደለም፡፡

አመልካች በ2ኛ ተጠሪ የጉዳት ካሣን በተመለከተ የፍ/ብሔር ክስ በቀረበባቸው ተከሳሽ እና ጣልቃገብን በመወከል መከራከር አይችሉም፤ተከሳሽ ራሳቸው ወይም ሌላ ጠበቃ በመወከል ይከራከሩ ተብሎ በተሰጠው ብይን ላይ ባቀረቡት ቅሬታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 90540 የኢትዮጵያ መድን ድርጅት የመድን ውሉን መነሻ በማድረግ በስር ተከሳሿ ላይ ጭምር ክርክር ሊያቀርብ የሚችልበት አጋጣሚ ሊኖር ስለሚችል የስር ተከሳሿ እና የኢትዮጵያ መድን ኢንሹራንስ ጥቅም ሊጻረር የሚችልበት አጋጣሚም ሊኖር የሚችል መሆኑን፤በ2ኛ ተጠሪ ላይ ለደረሰው አደጋ ምክንያት የሆኑት 2ኛ ተጠሪ ሲጓዙበት የነበረው መኪና ባለቤት እና ከዚህ መኪና ጋር የተጋጨው መኪና ባለቤት የሆኑት ወ/ሮ ዘይነባ መሐመድ ጉዳቱ በሌላው መኪና አሽከርካሪ ጥፋት ምክንያት የደረሰ ስለሆነ ኃላፊነቱ እኔን አይመለከተኝም በሚል አንዱ የሌላውን ጥቅም በሚፃረር መልኩ አንዳቸው በሌላኛው ላይ ክርክር ሊያቀርቡ የሚችሉበት አጋጣሚም ያለ መሆኑን፤አመልካች ወ/ሮ ዘይነባ መሐመድን መኪና አሽከርካሪ ነው ተብሎ ተከሶ የነበረውን ግለሰብ ወክሎ በወንጀል ሲከራከር በነበረበት ጊዜ በወ/ሮ ዘይነባ መሐመድ በኩል ሊነሱ የሚችሉትን ክርክሮች እና እንዲሁም ከሙያው ጋር ተያይዞ ሊያገኛቸው የሚችሉትን ሌሎች መረጃዎችንም አጋጣሚውን በመጠቀም ማወቁ ወይም ማግኘቱ የማይቀር መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ከወ/ሮ ዘይነባ መሐመድ ጋር ተፃራሪ ጥቅም ሊኖራቸው ከሚችሉት 2ኛ ተጠሪ ተሳፍረው ሲጓዙበት የነበረው መኪና ባለቤት እና ለመኪናዋ የመድን ሽፋን የሰጠውን መድን ድርጅት ወክሎ መከራከሩ እና በተከሳሽዋ እና በመድን ድርጅቱ መካከል የጥቅም ግጭት ሊኖር የሚችልበት አጋጣሚ እያለ ሁለቱን ወክሎ መከራከሩን የሙያውን ስነ-ምግባር መርሆዎችን የሚጥስ ከመሆኑም ባሻገር የጠበቆች ስነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ

10፣11፣12 እና 13 ድንጋጌዎች ይዘት ፣አላማ እና መንፈስ ጋርም የተጣጣመ አይደለም በማለት አመልካች ተከሳሽን እና ጣልቃገብን ወክሎ መከራከር አይችልም በማለት የተሰጠውን ብይን አጽንቶታል፡፡

የሥነምግባር ጉባኤው ከላይ የተገለጸውን የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ መሠረት በማድረግ አመልካች የጥቅም ግጭት ሊፈጠር በሚችልበት ሁኔታ የተለያዩ ተከራካሪዎችን በመወከል መከራከራቸው በፍ/ቤት ውሳኔ የተረጋገጠባቸው መሆኑን፤ይህ ድርጊታቸውም በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጠበቆች እና ሕግ ጉዳይ ጸሐፊዎች እና የፈቃድ አሠጣጥ አዋጅ ቁጥር 182/2005 አንቀጽ 36/3/15 ድንጋጌን የሚጥስ እና ከባድ የሥነምግባር ጥሰት መሆኑን በማረጋገጥ ውሳኔ የሰጠ በመሆኑ የጉባኤው ውሳኔ አመልካች ባቀረቡት ቅሬታ ላይ ይህ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ መሠረት ያደረገ እና የአመልካች ድርጊትም የጥብቅና ሙያ አገልግሎት የሥነምግባር ደንብ የሚጥስ በመሆኑ ጉባኤው በሰጠው ውሳኔም ሆነ በየደረጃው ባሉ ፍ/ቤቶች በሰጡት ውሳኔ ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የሕግ ሥሕተት አላገኘንበትም፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠበቆች የሥነምግባር ጉዳይ ጉባኤ በ16/06/07 ዓ.ም ተሠጥቶ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 201729 ሚያዚያ 01 ቀን 2007 ዓ.ም በውሳኔ፤በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 204457 ሚያዚያ 13 ቀን 2007 ዓ.ም በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

የሰ/መ/ቁ.108692

ታህሳስ 24 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሀመድ

ተኽሊት ይመስል

ቀነዓ ቂጣታ

ሡናይት አድነው

ጳውሎስ አርሺሶ

አመልካች፡- የትግራይ ክልል ዐቃቤ ህግ

ተጠሪ፡-አቶ ገብረአርዕያ አሰፋ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

<u>ፍ ር ድ</u>

1. ጉዳዩ የቀረበው አመልካት በሥልጣን አላግባብ የመገልገል የደንብ መተላለፍ ጥፋት አልፈፀመም በማለት የትግራይ ክልል ሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? ሚለውን ጭብጥ በሰበር አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ የታየው በሐውዜን ወረዳ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪና ሌሎች በዚህ ክርክር ተሣታፊ ያልሆኑ ሰዎች በወንጀል ሕግ አንቀጽ 796 የተመለከተውን በመተላለፍ፤ ሐውዜን ከተማ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ሆነው ሲሰሩ መጣራት የሚገባውን ነገር ሣያጣሩና አቶ ሃይላይ ገራስና ወ/ደብረብርሃን አረጋዊ እህታቸው እንደፈረሙ በማሰብ ፈርመናል ብለውናል በማለት ግንቦት 7 ቀን 2009 ዓ.ም ዕርቅ በማፅደቅና የአቶ ሃይላይ ገራስ ጋብቻ ፈርሷል የሚል ማስረጃ ለመቀሌ ማዘጋጃ ቤት በመላካቸው በሥልጣን አላግባብ ወንጀልፈፅመዋል የሚል ክስ አቅርቧል፡፡
2. ተጠሪ በአመልካች የቀረበበትን የወንጀል ክስ ክዶ ተከራክሯል፡፡ አመልካች ሶስት ምስክሮች በማቅረብ፤ ከተጠሪ ፊት ያልቀረቡት አቶ ሀይላ ገራስና ወ/ደብርሃን አረጋዊ ለማህበራዊ ዳኞች ፊት ቀርበው ሣይፈርሙ፤ የፈረሙ በማስመሰልና የዕርቅ ሰነድ በማፅደቅ ለመቀሌ ማዘጋጃ ቤት ማስረጃ ልኳል በማለት የመሰከሩ ሲሆን፤ የፅሑፍ ማስረጃም አመልካች አቅርቧል፡፡ ተጠሪ የመከላከያ ማስረጃ አቅርቧል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪ የተጠቀሰበትን

የወንጀል ህግ አንቀጽ 796 በመተላለፍ ጥፋት የፈፀመ ነው በማለት በሁለት ወር እስራት ተጠሪ እንዲቀጣና ቅጣቱ በሁለት ዓመት የሙከራ ጊዜ እንዲገደብ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠውን የጥፋተኝነት ውሣኔ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አፅንቶታል፡፡

3. ተጠሪ የበታች ፍርድ ቤቶች በሰጡት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ሰበር ችሎት የሰበር አቤተታ አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ተጠሪ በህግ የተሰጠውን ሥልጣን አላግባብ ስለመገልገሉ፣ የአመልካች ተጠሪ ፈፅሞታል በማለት የሚዘረዝረው የተረጋገጠው ፍሬ ነገር አያሳይም፡፡ የተጠሪ ተግባር ወንጀል የሚያቋቁም አይደለም በማለት ተጠሪ ከተሰሰበት ወንጀል በነፃ እንዲሰናበት በማለት ውሣኔ ተስቷል፡፡ አመልካች የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ታህሳስ 21 ቀን 2007 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበሲሆን፣ ተጠሪ የወ/ሮ ምፅላል ወላጆች ያልፈረሙበትን ሰነድ እንደፈርሙበት በማስመሰልና በችሎት ሣይቀርቡ ቀርበዋል በማለት ማስረጃ መስጠቱ፤ በግል ተበዳይ ላይ ጉዳት ማድረሥ በተረጋገጠበት ሁኔታ ተጠሪ የወንጀል ተጠያቂነት የለበትም መባሉ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ መምህር የማነብርሃን እና ወ/ሮ ምፅላል ሃይላይ የሥጋ ዝምድና ያላቸው መሆኑን በፖሊስ ጣቢያ ከተካሰሱ በኋላ ቤተዘመድ የተራቁ መሆኑን በመግለፅ የሰጠሁት ማስረጃ ስህተት የለበትም በወንጀልም አያስጠይቀኝም በማለት ግንቦት 17 ቀን 2007 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡

   አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

4. ከሥር የጉዳዩ አመጣጥና ግራ ቀኙ ለዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪ አመልካች የወንጀል ህግ አንቀጽ 796 የተመለከተውን በመተላለፍ ጥፋት ፈፅሟል በማለት ክስ የቀረበበት፣ ተጠሪ ከሌሎች ሁለት ሰዎች ጋር ሆኖ የሀውዜን ከተማ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኛ ሆኖ ሲሰራ፣ መምህር የማነብርሃን ከወ/ሮ ምፅላል ሃይላይ ጋር ጋብቻ የሚከለክል የሥጋ ዝምድና ያላቸው መሆኑን የሚገልፅ ግንቦት 17 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ የዕርቅ ሰነድ በማፅደቅ መጋቢት 2 ቀን 2002 ዓ.ም ከተፃፈ ከመሸኛ ደብዳቤጋር ለመቀሌ ማዘጋጃ ቤት ልከዋል በማለት ነው፡፡

   ተጠሪና ሌሎች የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች አፀደቁት የተባለው የዕርቅ ሰነድ መነሻው በሐውዜን ከተማ ፖሊስ ጣቢያ ያቀረበን የወንጀል ክስ ቀሪ ለማድረግ፤ የወንድና የሴት ቤተዘመዶች ሶስት ሽማግሌዎች ባሉበት የታረቁ መሆኑን የሚገልፅናከአንደኛ እስከ አምስተኛ ስማቸው የተገለፀው ሰዎች የፈረሙ መሆኑን የሚገልፅና 6ኛ ምፅላል ሃይላይ አልፈረመችም የሚልና የአስታረቁትን ሶስት ሰዎች ስም የያዘ መሆኑንና ተጠሪ

ከሌሎች የማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ጋር በመሆን የምስክሮችን ቃል ሰምቶ፤ ማስረጃ የሰጠ መሆኑ ተረጋግጧል።

5. አመልካች የሚከራከረው ተጠሪ ከሌሎች ማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ጋር ሆኖ ማጣራት የሚገባውንና ፍሬ ነገር ሣያጣራ በወቅቱ የዕርቅ ሰነዱን ለማፅደቅ በማህበራዊ ፍርድ ቤት ያልቀረቡ የወ/ሮ ምፅላል ሃይላይ ወላጆች፣ ችሎት የቀረቡ መሆኑን በአግባቡ ሣያረጋግጥ፣ በችሎት እንዲቀርቡ በማስመሰል ማስረጃ ሰጥቷል በማለት ነው። ተጠሪ ከሌሎች የሀውዜን ከተማ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ጋር በመሆን፣ ምስክሮችን በመስማት መምህር የማነብርሃን ወ/ሮ ምፅላል ሀይላይ በትግራይ ክልል የቤተሰብ ህግ መሠረት ጋብቻ እንዳይፈፅሙ የሚከለክል የሥጋ ዝምድና ያላቸው መሆኑን በመግለፅ፣ የዕርቅ ሰነዱን የምስክሮች ቃል ያረጋገጡ መሆኑን ገልፀው ለመቀሌ ማዘጋጀ ቤት ማስረጃ መስጠታቸው ተረጋግጧል።

6. ተጠሪ ማስረጃውን አጣርቶ የሰጠው ከሌሎች የሀውዜን ማህበራዊ ፍርድ ቤት ዳኞች ጋር በመሆንና በችሎት በመሰየም እንደሆነ በመከላከያ ማስረጃ ተረጋግጧል። የሀውዜን ከተማማህበራዋ ፍርድ ቤት ዳኞች /ተጠሪን ጨምሮ /ይህንን ማስረጃ የሰጡት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 37 ንዑስአንቀጽ 1 1985 በወጣው የትግራይ ክልል ሕገ መንግስት 89 እንደተሻሻለ እና በትግራይ ክልል ምክር ቤት ባወጣው የቤተሰብ ሕግ መሠረት በተሰጣቸው የዳኝነት ነክ ሥልጣን መሠረት በማድረግ ነው። ይህ ከሆነ፣ ተጠሪ በሕግ የተሰጠውን የዳኝነት ነክ ተግባሩን ከሌሎች ዳኞች ጋር በሚወጣበት ወቅት፤ የፍርድ ሥራ ስህተት በይግባኝ፤ በሰበር ወይም በሌላ በሕግ በተዘረጋ የፍርድ ሥራ ስህተት ማረሚያ መንገዶች የሚመለከታቸው ግለሰቦች አቅርበው እንዲያሳርሙ ከሚደረግ በስተቀር፣ ተጠሪ በተናጠል የወንጀል ህግ አንቀጽ 796 በመተላለፍ በሥልጣን አላግባብ የመገልገል ወንጀል ፈፅሟል በማለት የወንጀል ክስ የሚቀርብበትና ኃላፊ የሚሆንበት ህጋዊ ምክንያት የለም። ከዚህ አንፃር የትግራይ ክልል ሰበር ችሎት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡትን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በመሻር ተጠሪ በነፃ እንዲሰናበት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሌለበት ነው በማለት ወስነናል።

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 67011 ጥቅምት 14 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል።

መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ። የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ሰ/መ/ቁ. 128466

ሰኔ 29 ቀን 2009ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አቶ እንዳልካቸዉ ይላቅ ቀረቡ

ተጠሪ፡- የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር ዐ/ሕግ ሙዕዝ ገ/ሉዑል ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው የአሁኑ ተጠሪ መ/ቤት የዲስፕሊን ኮሚቴ የሰጠው የዲስፕሊን ውሣኔ ለተጠሪ መ/ቤት የበላይ ሀላፊ ቀርቦ በመጽደቁ አመልካች ይግባኛቸውን በአዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀጽ 29 መሰረት ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ከፍተኛው ፍ/ቤትም መልስ ሰጪውን መጥራት ሳያስፈልግ በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሠረት የይግባኙን መዝገብ በመዝጋቱ አመልካች የተሠጠዉ ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት የሰበር አቤቱታቸውን ስላቀረቡ ነው፡፡

ለዲስፕሊን ኮሚቴ ውሣኔ መነሻ ወ/ሮ አበባየሁ አያሌዉ መጋቢት 25 ቀን 2006 ዓ/ም በተፃፈ ማመልከቻ ያቀረቡት አቤቱታ ሲሆን ይዘቱ፡- ከአሁኑ አመልካች ጋር ሐምሌ 25 ቀን 2003 ዓ.ም በተጻፈ የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ዉል ባላቸዉ የቤት ክርክር ጉዳይ ክስ መስርተዉ እንዲከራከሩ ለጊዜዉ ቅድመ ክፍያ ብር 25,000 እና ለመዝገብ ማስከፈቻ ብር 2,000 ከፍለዉ ወደ ዉጭ አገር መሄዳቸዉን ገልጸዉ ከ3 ዓመት በኃላ ወደ አገር ሲመለሱ አመልካች ክስ ሳይመሰርቱ በመቆየታቸዉ ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸዉ መሆኑን ገልጸዉ ተገቢዉ እርምጃ እንዲወሰድላቸዉ ጠይቀዋል፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስም ከዲስፒሊን ክስ አቅራቢ ጋር የጥብቅና አገልግሎት ዉል ማድረጋቸዉን አምነዉ ብር 25,000 ሳይቀበሉ ዉጪ አገር ከሄዱ በኃላ እንዲልኩ ተስማምተዉ እንደተቀበሉ አድርገዉ የፈረሙ መሆኑን፤ የፋይል ማስከፈቻ ብር 2,000 ያልተቀበሉ መሆኑን፤ ክስ ሳይመሰርቱ የቀሩበት ምክንያት ለክሱ የሚያስፈልጉ ምስክሮችንና መረጃ ደንበኛቸዉ ሳትሰጥ ወደ ዉጭ አገር በመሄዷ እንደ ሕግ ባለሙያ ማስረጃ ሳይያያዝ ክስ መመስረት ስለማይቻል እንጂ በጥፋት ባለመሆኑ ክሱ ዉድቅ እንዲደረግለት በመጠየቅ ተከራክሯል፡፡ የዲስፒሊን ክስ አቅራቢ በበኩላቸዉ በሰጡት መልስ ለአሁኑ አመልካች አስፈላጊዉን የወራሽነትና ሌሎች የሰነድ ማስረጃዎችን እንዳስረከቡትና የሰዉ ምስክሮችንም ዝርዝር ሰጥተዉ ወደ ዉጭ አገር እንደሄዱ ከገለጹ በኃላ የግራቀኙን ምስክሮች ለመስማት በተቀጠረበት ዕለት ግራቀኙ ታሕሳስ 16 ቀን 2007 ዓ.ም በተጻፈ ስምምነት የአሁኑ አመልካች የተቀበሉትን ገንዘብ በመክፈል የተፈራረሙትን አያይዘዋል፡፡ የዲስፒሊን ኮሚቴዉ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች በጠበቆች የስነ ምግባር ደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 4 መሰረት ዉል ከመፈጸማቸዉ በፊት ስለሚይዙት ጉዳይ ህጋዊነትና በማስረጃ የተደገፈ ስለመሆኑ እና ማስረጃዎችና ምስክሮች ተሟልተዉ የቀረቡ መሆኑን ማረጋገጥ ሲገባቸዉ ዉል ከመፈጸማቸዉ በፊት ምስክሮችና ማስረጃዎች መሟላቱን አለማረጋገጣቸዉ የአመልካች ጉድለት እንጂ የደንበኛቸዉ ችግር አይደለም፤ ደንበኛቸዉ ከአገር ዉስጥ የሌሉ መሆኑን እያወቁ ከ3 ዓመት በላይ ክስ ሳይመሰርቱ በመቆየታቸዉ ጥፋተኛ ናቸዉ በማለት በብር 5,000 እንዲቀጡ የወሳኔ ሀሳብ ለተጠሪ መስሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ አቅርቦ በማስጸደቅ አስወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የሰበር አቤቱታዉ የቀረበዉ ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነዉ፡፡አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት፡- የስር አቤቱታ አቅራቢ ታህሳስ 16 ቀን 2004 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ ለጉባኤዉ ያቀረብኩት ክስ ስህተት ነዉ፤ ጠበቃዉ የፈጸመዉ ምንም ዓይነት ጥፋት የለም፤ ክስ ሳይመሰርት የቆየዉ እኔ ማስረጃዎችን ለጠበቃዉ ባለመስጠቴ እና አሟልቼ ባለማስረከቤ ነዉ በማለት የራሷ ጥፋት መሆኑን አረጋግጣለች፡፡ በነጻ እንድሰናበትም አመልክታ እያለ ምንም ዓይነት ጥፋት ሳይኖር ጥፋተኛ ተብዬ ብር 5,000 መቀጣቴ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነዉ፡፡ ሁለቱ የጉባኤ አባላት በዉሳኔ ሀሳቡ ያልፈረሙበት በመሆኑ ባልተሟላ ጉባኤ የተሰጠዉ ዉሳኔ ስህተት ነዉ፡፡ ክሱ ከቀረበ 1 ዓመት ከ12 ቀን በኃላ የተሰጠ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 119/92 መሰረት በ9 ወር ይርጋ ቀሪ ነዉ፡፡ በመሆኑም ዉሳኔዉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ ይሻርልኝ የሚል ነዉ፡፡

የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ የስር አቤቱታ አቅራቢ ጥፋተኛ እኔ ነኝ፤ አማልካች አይደለም በማለት በጽሁፍ ለጉባኤዉ አመልክተዉ ሳለ እንዲሁም የስር አቤቱታ አቅራቢ የሚኖሩት በዉጭ አገር በመሆኑ ክሱን ለመመስረት የሰዉ ማስረጃ ስም ዝርዝር ባልሰጡበት ሁኔታ አመልካች

ጥፋተኛ ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለማጣራት ሲባል ለሰበር ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራቀኙ መልስ እና የመልስ መልስ በጽሁፍ በማቀባበል ክርክር ተደርጓል፡፡

የተጠሪ መልስ ይዘት፡- አመልካች በደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 4 መሠረት ጉዳዩን ተቀብሎ የጉዳዩን ፍሬ ነገር እና ማስረጃዎች ሳይመረምሩ በጥብቅና አገልግሎት ስም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ማስረጃዎች ሳይሟሉ ዉል ተዋዉለዉ ጉዳዩን መያዙ በራሱ የስነ-ምግባር ጥሰት በመሆኑ የግል ተበዳይ ጥፋተኛ እኔ ነኝ በማለት በጽሁፍ ለጉባኤዉ ማመልከታቸዉ የተፈጸመዉን የዲስፒሊን ጉድለት የሚያስቀር አይደለም፡፡ የጉባኤዉ አባላት አብዛኛዎቹ እስከተገኙ ድረስ ጉባኤዉ ዉሳኔ መስጠት ስለሚችል የተፈጸመ ስህተት የለም፡፡ በአዋጅ ቁጥር 119/92 አንቀጽ 24(8) መሠረት በ6 ወር የዉሳኔ ሀሳቡን ማቅረብ ካልቻለ በጽሁፍ ተጨማሪ ጊዜ መጠየቅ ስለሚችል በይርጋ አልታገደም ሲል ተከራክሯል፡፡ አመልካችም አቤቱታቸዉን በሚያጠናክር መልኩ ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተገለጸዉን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካለዉ የሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡ የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ አመልካች ከስር አቤቱታ አቅራቢ ጋር ቤት ክርክርን አስመልክቶ ክስ እንዲመሰርቱ የጥብቅና አገልግሎት ዉል ካደረጉ እና ቅድመ ክፍያ ከተቀበሉ በኃላ አቤቱታ አቅራቢ ዉጭ አገር ከሄዱበት ከ3 ዓመት በኃላ ሲመለሱ ክስ ሳይመሠርቱ ቆይተዋል፡፡ አመልካች ክስ ላለመመስረታቸዉ የሰጡት ምክንያት የስር አቤቱታ አቅራቢ ወይም ደንበኛቸዉ የምስክር ዝርዝር ሳይሰጡ ዉጭ አገር በመሄዳቸዉ ያለማስረጃ ክስ መመስረት ስለማይችሉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ የስር አቤቱታ አቅራቢ ለጉባኤዉ በሰጡት መልስ የምስክር ዝርዝርና የወራሽነት ማስረጃ ሰጥተዉ እንደሄዱ ቢከራከሩም የግራቀኙን ምስክሮች ለመስማት በተቀጠረበት ዕለት ግራቀኙ ታርቀዉ አመልካች ቅድመ ክፍያዉን መልሰዉ ደንበኛቸዉ ደግሞ የምስክር ዝርዝር ሳይሰጡ በመሄዳቸዉ ምክንያት ክስ ያለመመስረቱና አሁን በሌላ ጠበቃ በጉዳዩ ክስ ተመስርቶ በክርክር ሂደት ላይ የሚገኝ በመሆኑ አመልካች ጥፋት የሌለባቸዉ መሆኑን ገልጸዉ የተስማሙበትንና የተፈራረሙበትን ታሕሳስ 16 ቀን 2007 ዓ.ም የተዘጋጀ ሰነድ አቅርበዋል፡፡ ጉባኤዉ የስር አቤቱታ አቅራቢ የምስክር ዝርዝር ሳይሰጡ መሄዳቸዉ ለክሱ አለመመስረት ምክንያት ሊሆን ቢችል እንኳ ከጅምሩ ምስክሮችና ማስረጃ መሟላቱን ሳያረጋግጥ የጥብቅና አገልግሎት ዉል ፈርመዉና ዉክልና ተቀብለዉ ቅድመ ክፍያ መቀበላቸዉ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ጠበቆች የሥነ ምግባር ደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 4 መሠረት አንድ ጠበቃ የጉዳዩን ፍሬ ነገርና ማስረጃዎች ከመረመረ በኃላ ክርክሩ ሕጋዊ መሠረት የሌለዉ ከሆነ ጉዳዩን መያዝ የለበትም የሚለዉን ክልከላ ተላልፏል በማለት አመልካችን ጥፋተኛ ብሏቸዋል፡፡ ከዚህ መገንዘብ የሚቻለዉ የክርክሩ አብይ ጭብጥ የደንቡ አንቀጽ 4 የምስክርን ዝርዝር ሳይቀበሉ

የጥብቅና አገልግሎት ዉል መዋዋልን ይከለክላል ወይስ አይከለክልም የሚለዉ በመሆኑ የድንጋጌዉን ይዘትና ትርጉም መመልከቱ ተቃሚ ነዉ፡፡

በመሠረቱ የደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 4 ማንኛዉም ጠበቃ የሕግ አገልግሎት ለማግኘት የመጣ ደንበኛን ጉዳይ ተቀብሎ የጉዳዩን ፍሬ ነገርና ማስረጃዎች ከመረመረ በኃላ ክርክሩ ሕጋዊ መሠረት የሌለዉ ከሆነ ጉዳዩን መያዝ የለበትም፡፡ ሆኖም ለሰጠዉ የሕግ ምክር አገልግሎት ተገቢዉን ክፍያ ተቀብሎ ደንበኛዉን ያሰናብታል በማለት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ ይዘት መገንዘብ የሚቻለዉ አንድ ጠበቃ ከጅምሩ የሕግ መሠረት የሌለዉና አዋጭ አለመሆኑ የተረጋገጠን ወይም ተከራክሮ የመርታት ዕድል የሌለዉ መሆኑን እያወቀ ደንበኛዉን አላስፈላጊ ለሆነ ክርክርና ወጪ መጋበዝ የሌለበት መሆኑን የሚያስገነዝብ ነዉ፡፡ ሆኖም ይህ ድንጋጌ ጠበቃዉ የጥብቅና አገልግሎት ዉል ከመዋዋሉ በፊት ማስረጃ ሰብስቦ ማጠናቀቅ ይገባዋል ወይም ምስክሮችን አስቀርቦ መጠየቅና የሚያዉቁትን አስቀድሞ ማወቅ አለበት ማለት አይደለም፡፡ ይልቁንም ደንበኛዉን ሲቀበል የጉዳዩን ይዘት ደንበኛዉን በማነጋገር መረዳት፣ ደንበኛዉ በእጁ የያዘዉ ሰነድ ካለ ተቀብሎ የማስረጃዉን ይዘት መመልከት እና ክሱ የሕግ መሠረት ያለዉ መሆን አለመሆኑን መገንዘብ ያለበት መሆኑን በቅድመ ሁኔታ የሚያስቀምጥ እንጂ ከጥብቅና አገልግሎቱ በፊት ማስረጃ አሰባስቦ እንዲጨርስ የሚያስገድድ አይደለም፡፡ ክሱን ማዘጋጀትና በደንበኛዉ እንዳሉ የተገለጹ ማስረጃዎችን ማሰባሰብ እና ማደራጀት የግድ ከዉሉ በፊት አስቀድሞ መጠናቀቅ ያለበት አይደለም፡፡ ጠበቃዉ ዉል ካደረገና በማስረጃ መሰበሰብ ሂደት ላይ ወሳኝ የሆነ ማስረጃ እንደሚያስፈልግ ቢገነዘብ እና ደንበኛዉን በማነጋገር ማስረጃዉን ማግኘት የደንበኛዉን ጥቅም የበለጠ የሚያስጠብቅ ሆኖ ሲያገኘዉ ክስ መመስረቱን አቁሞ ደንበኛዉን ማነጋገርና ማስረጃዉን ማግኘት ከጠበቃዉ የሚጠበቅ ተግባር እንጂ በቅድሚያ መሟላቱን ሳታረጋግጥ ዉል ያዝክ የሚያስብል አይደለም፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ በአመልካችና በደንበኞቸዉ መካከል ታሕሳስ 16 ቀን 2007 ዓ.ም በተደረገዉ የስምምነት ሰነድ ሰፍሮ እንደሚገኘዉ በአሁኑ ወቅት ጉዳዩ በሌላ ጠበቃ አማካይነት ክስ ተመስርቶ በክርክር ሂደት ላይ የሚገኝ መሆኑ መገለጹ ከጅምሩ አመልካች የሕግ መሠረት የሌለዉ መሆኑን እያወቀ የጥብቅና አገልግሎት ዉል ገብቷል የሚያስብል አይደለም፡፡ እንዲያዉም አመልካች ከደንበኛዉ የተሰጡትን ሰነዶችን ብቻ መሠረት በማድረግ ደንበኞቸዉ ዉጭ አገር በመሆናቸዉና ሊያገኛቸዉ ስላልቻለ ብቻ የምስክሮችን ዝርዝር ለፍ/ቤት ሳያቀርብ ወይም ዝርዝራቸዉን አቅርቦ ያሉበትን አድራሻ ሳያዉቅና ሳያገኛቸዉ ክስ ቢመሰርት የደንበኛዉን ጥቅም የሚጎዳ ሊሆን ስለሚችል የስነ-ምግባር ጥሰት ሊሆን በቻለ ነበር፡፡ አመልካች ክስ ሳይመሰርቱ ለመቆየታቸዉ ደንበኞቸዉ ዉጭ አገር መገኘታቸዉ እና የምስክሮች ዝርዝር ያለማቅረባቸዉ መሆኑን ምንም እንኳ ክሱ ከቀረበ በኃላ ቢሆንም የስር አቤቱታ አቅራቢ ከላይ በተጠቀሰዉ ሰነድ

ላይ ፊርመዉ ባረጋገጡበት፣ ይህ ላለመሆኑና የምስክሮች ዝርዝር ለአመልካች ተሰጥቶት የነበረ ስለመሆኑ በማስረጃ ባልተረጋገጠበት እንዲሁም የስር አቤቱታ አቅራቢ ወጭ አገር የነበሩ በመሆናቸዉ ከአመልካች ጋር የነበራቸዉ ግንኙነት ተቋረጦ የነበረ መሆኑ ክስ ላለመመስርቱ የራሱ አሉታዊ አስተዋጽኦ የነበረዉ መሆኑ መረጋገጡ፣ ደንበኞቸዉ አገር ዉስጥ ቢሆኑ ኖሮ ችግሩ ሊከሰት የማይችል መሆኑን ግምት የሚወሰድበት ነዉ፡፡ ከዚህ አንጻር ጉባኤዉ የስነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 4ን በተሳሳተ መንገድ በመገንዘብና በመተርጎም አመልካችን የስነ-ምግባር ጥሰት ፈጽሟል በማለት ጥፋተኛ ማድረጉም ሆነ በብር 5,000 መቅጣቱ ተገቢ አይደለም፡፡

ሲጠቃለል አመልካች በገባዉ የጥብቅና አገልግሎት ዉል መሠረት ክሱን ሳይመሠርት የቆየዉ ደንበኞቸዉ የምስክሮችን ዝርዝርና አድራሻ ሳይሰጡ ዉጭ አገር በመሄዳቸዉ መሆኑ ታሕሳስ 16 ቀን 2007 ዓ.ም በተደረገዉ የእርቅ ስምምነት ደንበኞቸዉ ባረጋገጡበት፣ ስምምነቱ በተደረገበት ወቅት ክሱ ተሟልቶ ቀርቦ በፍርድ ቤት ክርክር ሂደት ላይ የሚገኝ መሆኑ በተገለጸበት እና ጉዳዩ የሕግ መሠረት የሌለዉ መሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ጉባኤዉ የፌዴራል ፍ/ቤቶች ጠበቆች የስነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 57/92 አንቀጽ 4 መሰረት የጥብቅና አገልግሎት ዉል ከመገባቱ በፊት ማስረጃ ተሰብስቦና ተመርምሮ መጠናቀቅ እንደሚገባዉ ድንጋጌን በተሳሳተ መንገድ በመገንዘብና በመተርጎም አመልካችን ጥፋተኛ በማድረግ በብር 5,000 እንዲቀጣ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የጠበቆች የዲሲፕሊን ጉባኤ መጋቢት 03 ቀን 2007 ዓ/ም ተሰጥቶ በፍትህ ሚኒስትሩ መጋቢት 14 ቀን 2007 ዓ/ም ጸድቆ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 173828 የካቲት 24 ቀን 2008 ዓ/ም በትዕዛዝ የጸናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የፌዴራል ፍ/ቤቶች ጠበቆች የስነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 52/92 አንቀጽ 4 የተመለከተዉን ተላልፈዋል ተብለዉ በስር ጥፋተኛ መባላቸዉም ሆነ የብር 5,000 የገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ የተሰጠዉ ዉሳኔ በአግባቡ ሆኖ ባለመገኘቱ ተሽሯል፡፡ አመልካች በነጻ ይሰናበታሉ ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ሰ/መ/ቁ.135094

ግንቦት 21 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- ብርሃኑ አመነዉ

በዕዉቀት በላይ

እንዳሻዉ አዳነ

ኃይሉ ነጋሽ

እትመት አሰፋ

አመልካች፡- አቶ ዳዊት በላይ -- አልቀረቡም

ተጠሪዎች፡- 1. አቶ ደነቀ አበበ -- ጠበቃ መኮንን ኃ/ስላሴ ጋር ቀረቡ

2. ዶ/ር ዉብሸት ዝቅአለ አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ የግልግል ጉባኤ ዳኛ ሆኖ የተሰየመ ሰዉ ጉዳዩን ከማየት እንዲነሳ የቀረበ አቤቱታን የሚመለከት ሆኖ የተጀመረዉ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነዉ፡፡ በአሁኑ 1ኛ ተጠሪ አቤቱታ አቅራቢነት አመልካችና 1ኛ ተጠሪ በመካከላቸዉ የተፈጠረዉ አለመግባባት በግልግል ዳኞች ዉሳኔ እንዲሰጥበት ለማድረግ በአመልካች በኩል አቶ ሚካኤል ጉንታ በ1ኛ ተጠሪ በኩል የአሁኑ 2ኛ ተጠሪ በመሰየማቸዉ ሁለቱ የግልግል ዳኞች ሠብሳቢ ዳኛዉን እንዲመርጡ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ሆኖም ሰብሰቢዉ ዳኛ ከመመረጡ በፊት የአሁኑ አመልካች 2ኛ ተጠሪ ጉዳዩን በገለልተኝነት ሊያዩት አይችሉም በሚል ከግልግል ዳኝነት ጉባኤ አባልነት ይነሱልኝ ሲሉ አቤቱታ ለፍ/ቤቱ አቅርበዋል፡፡ የአቤቱታዉ ይዘት፡- 2ኛ ተጠሪ በነጻነትና በገለልተኝነት የመሥራት ኃላፊነት እያለባቸዉ የ1ኛ ተጠሪን ዓላማ ለማሳካት የታሰበ በሚመስል መልኩ የአቶ ሚካኤል ጉንታ ከሳሽ እና በእርሳቸዉ ላይ ያለአግባብ መስካሪ ሆነዉ ተገኝተዋል፡፡ አቶ ሚካኤል እና 2ኛ ተጠሪ ሰብሳቢ ዳኛ ለመምረጥ ሞክረዉ አንዱ ሌላኛዉ ባቀረበዉ ጥቆማ ላይ ባለመስማማታቸዉ 2ኛ ተጠሪ ትልቅ ሥራ ስላገኘሁ የግልግል ዳኝነት ጉባኤ አባል ሆኜ አልሠራም፤ ይህንኑ

ለመረጠኝ ድርጅት አሳዉቂያለሁ ማለታቸዉ እና ሐምሌ 21 ቀን 2007 ዓ.ም ለአመልካች በጻፉት ደብዳቤ የገለጹት አቋም የገለልተኝነት መርህን የሚቃረን ስለሆነ ከግልግል ዳኝነት ጉባኤ አባልነት ይነሱልኝ የሚል ነዉ፡፡

1ኛ ተጠሪ በበኩላቸዉ የቀረበዉ አቤቱታ 2ኛ ተጠሪ ባላቸዉ የትምህርት ደረጃና የሥራ ልምድ እንዲሁም በግልግል ድርጅቶች ዉስጥ ስለሚያበርክቱት አስተዋጽኦ ወቀሳ እንደማይገባቸዉና ግምታዊ በሆነ ሀሳብ ከግልግል ዳኝነት ጉባኤ አባልነት ሊነሱ እንደማይገባ በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ 2ኛ ተጠሪ በቀረበባቸዉ መቃወሚያ ላይ መልስ እንዲሰጡ የተደረገ ሲሆን ተናግረዋል የተባለዉን ነገር እንዳልተናገሩና ባልተጨበጠ ማስረጃ የቀረበባቸዉ ተቃዉሞ የሥራ ብቃትና ሀላፊነታቸዉን የማይለዉጥ መሆኑን በመግለጽ ዉድቅ እንዲደረግላቸዉ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተዉ የስር ፍ/ቤት የግራቀኙን ክርክር ሰምቶና መርምሮ 2ኛ ተጠሪ ገለልተኛ አለመሆናቸዉንና የተጠሪን ዓላማ ለማሳካት በሚመስል ሁኔታ አቋማቸዉን አሳይተዋል የተባለዉ በማስረጃ ያልተደገፈና በግልግል ዳኝነት ጉባኤ አባልነት እንዳይቀጥሉ የሚያደርግ አይደለም በማለት የአመልካችን አቤቱታ ዉድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ አመልካች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት ሠርዞታል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡት ይህን ዉሳኔ በመቃወም ለማስቀየር ነዉ፡፡

አመልካች 2ኛ ተጠሪ ገለልተኛ ባለመሆናቸዉ ከግልግል ዳኝነት ጉባኤ አባልነት ሊነሱ ይገባል ያሉባቸዉን ምክንያቶች በሰበር አቤቱታቸዉ በዝርዝር አቅርበዋል፡፡ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች 2ኛ ተጠሪ ከግልግል ዳኝነት እንዲነሱላቸዉ ከገለጽዋቸዉ ምክንያቶች ገለልተኛ አይደሉም የሚያስብል አይደለም በማለት እንዲቀጥሉ መወሰኑ ሰበር ሰሚ ችሎት ከዚህ በፊት በመ/ቁጥር 99679 ከሰጠዉ ዉሳኔ አንጻር አግባብነቱን ለመመርመር ሲባል ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ግራቀኙ መልስ እና የመ/መልስ በማቀባበል እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

1ኛ ተጠሪ ለአቤቱታዉ በሰጡት መልስ የተመረጡት ገላጋይ ዳኛ ወይም 2ኛ ተጠሪ ገለልተኛ አለመሆኑን የሚያሳይ ምክንያትና ማስረጃ በሌለበት ከግልግል ዳኝነት ጉባኤ አባልነት ሊነሱ አይገባም፡፡ በሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 99679 የተሰጠዉ የሕግ ትርጉም ለጉዳዩ አግባብነት የለዉም እንዲሁም አመልካች የጠቀሳቸዉ ምክንያቶች የፈጠራ፣ የሀሰትና በማስረጃ ያልተረጋገጡ በመሆናቸዉ 2ኛ ተጠሪ በጉባኤዉ በዳኝነት ሊያገለግሉ ይገባል ተብሎ እንዲወሰን በመጠየቅ በዝርዝር ክርክራቸዉን አቅርበዋል፡፡

2ኛ ተጠሪ በበኩላቸዉ በሰጡት መልስ በስር ፍ/ቤት በነበረዉ ክርክር ተከራካሪዎች አመልካችና 1ኛ ተጠሪ ናቸዉ፡፡ የስር ፍ/ቤት በመቃወሚያዉ ላይ አስተያየት እንድሰጥበት ብቻ ነዉ ያደረገዉ፡፡ ስለሆነም የክርክሩ ቀጥተኛ ተሳታፊ ባለመሆኔ በሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 99679 በተሰጠዉ ትርጉም መሠረት ከክርክሩ እንድወጣ እንዲደረግ እና ለተከራካሪ ወገኖች ፍትህ

የማግኘት የወደፊት ጉዞ የተቃና እንዲሆን ተገቢዉ ዉሳኔ ይሰጥበት ብለዋል፡፡ አመልካች አቤቱታቸዉን በሚያጠናክር መልኩ የመልስ መልስ አቅርባል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ባጭሩ ከላይ የተመለከተዉን የሚመስል ሲሆን እኛም አቤቱታ ከቀረበበት ዉሳኔ እና አግባብነት ካለዉ የሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ መዝገቡን መርምረናል፡፡ የሰበር አቤቱታዉ ያስቀርባል ሲባል ከተያዘዉ ጭብጥ አንጻር መርምረን እንደተረዳነዉ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተዉ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች 2ኛ ተጠሪ የግልግል ዳኝነት ጉባኤዉ አባልነታቸዉ እንዲነሱ ያቀረቡትን አቤቱታ ዉድቅ ያደረገዉ የአመልካች አቤቱታ በማስረጃ የተደገፈ አይደለም በማለት ነዉ፡፡ የስር ፍ/ቤት በርግጥ 2ኛ ተጠሪ አቋማቸዉን አሳይተዉበታል ያለዉን ሐምሌ 21 ቀን 2007 ዓ.ም ተጻፈ የተባለዉን ደብዳቤ አስቀርቦ እንደተመለከተዉና የደብዳቤዉ ይዘት 2ኛ ተጠሪ የገለልተኝነት መርህን የሚቃረን ሀሳብ ወይም አቋም አንጸባርቋል የሚያስብል አለመሆኑን በፍርዱ ገልፅዋል፡፡ ሆኖም ሌሎች ነጥቦችና አቋማቸዉን አንጸባርቀዋል የተባሉትን ንግግሮች 2ኛ ተጠሪ ተናግረዋል የተባሉት ለአቶ ሚካኤል ጉንታ ከመሆኑ አንጻር ለምን ቀርበዉ እንዳልተሰሙና እንዳልተጣራ ግልጽ አይደለም፡፡

በሌላ በኩል አቤቱታዉ ለሠበር ያስቀርባል ሲባል ወደ ተያዘዉ ጭብጥ ስንመለስ 2ኛ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ክርክር ከነበረዉ ሚና እና በሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 99679 ከተሰጠዉ አስገዳጅ ትርጉም አንጻር በግልግል ጉባኤ አባልነት ይቀጥሉ መባሉ በአግባቡ ነዉ? ወይስ አይደለም? የሚለዉን እንመልከት፡፡ ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ከዚህን ቀደም በተጠቀሰዉ መዝገብ የሰጠዉ ትርጉም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 3342 መሠረት በአንድ የግልግል ዳኛ ላይ መቃወሚያ ሲቀርብበት ተከራካሪ ሆኖ መቅረብ ያለበት ማን እንደሆነ? ከጉባኤዉ እንዲነሳ ጥያቄ የቀረበበት ዳኛ ጥያቄዉን ካነሳዉ ተከራካሪ ወገን ጋር መልስ ሰጭ ወይም ተጠሪ ሆኖ ቀርቦ ዝርዝር ክርክር ካቀረበ በኃላ፤ ፍርድ ቤት ተከራካሪ ሆኖ በቀረበበት ጉዳይና በተከራካሪነት ቀርቦ ሲሞግተዉ የነበረዉን ተከራካሪ ወገን ለግልግል ዳኞች የሚያቀርበዉን ክርክርና ማስረጃ በገለልተኝነት ሰምቶ ሊወስን ይችላል ተብሎ በግልግል ዳኝነት እንዲሰየም ማድረግ በመርህ ደረጃ የግልግል ዳኝነቱን ዓላማ የማያሳካ መሆኑን፤ የግልግል ዳኛዉ ጉዳዩን ለማስረዳት ከሚቀርብ በቀር ዳኛዉን ከዳኝነቱ የሚያስነሳዉ በቂ ምክንያት አለ ወይስ የለም በሚለዉ ጭብጥ ዙሪያ ተከራካሪ ሆኖ መሰለፉንና ዝርዝር ክርክር የሚቀርብበት ሁኔታ መኖር የሌለበት መሆኑን ግልጽና አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ ምንም እንኳ 2ኛ ተጠሪ ለሰበር አቤቱታዉ በሰጡት መልስ የክርክሩ አካል ሆኖ መቀጠል ስለማይገባቸዉ ከክርክሩ ዉጭ እንዲደረጉ የጠየቁ ቢሆንም በስር ፍ/ቤቶች የነበራቸዉን ተሳትፎ ምን እንደነበረ መመልከቱ ተገቢ ነዉ፡፡ አመልካች ለስር ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ 2ኛ ተጠሪን በተከራካሪነት የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆኑ በአቤቱታቸዉ አልጠቀሱም፡፡ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በራሱ ተነሳሽነት 2ኛ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ትዕዛዝ የሰጠ ሲሆን 2ኛ ተጠሪም ዝርዝር ክርክር አቅርበዋል፡፡ በርግጥ የዚህ ዓይነት አቤቱታ የቀረበበት የግልግል ዳኛ

የበኩሉን አጭር አስተያይት እንዲያቀርብ ማድረግ የተለመደ አሠራር ቢሆንም እንደአንድ ተከራካሪ ወገን ተወስዶ በመልስ ሰጭነት ተሰይሞ የክርክሩ ሙሉ ተካፋይ መደረጉ ተገቢ አይደለም፡፡ የስር ፍ/ቤት በፍርዱ ላይ 2ኛ ተጠሪን በተከራካሪነት ወይም በመልስ ሰጪነት ከመሰየሙም በላይ 2ኛ ተጠሪ ያቀረበዉን አስተያየት በመደበኛ ተከራከሪ እንደቀረበ ክርክር አድርጎ መዝግቦታል፡፡ ይህም በመጀመሪያዉ ክርክር ብቻ ሳይሆን በይግባኝ ሰሚ እና በሰበር ሰሚ ችሎት ደረጃ 2ኛ ተጠሪ በመዝገቦቹ በመልስ ሰጭነት ወይም በተጠሪነት የክርክሩ ተሳታፊ እንዲደረግ ምክንያት ሆኗል፡፡

የፍ/ብ/ሕ/ቁ 3340(2) መሠረት እና በሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ 99679 ከተሰጠዉ አስገዳጅ ትርጉም አንጻር ዳኛዉን ገለልተኛ ወይም ነጻ ላይሆን ይችላል በማለት ከግልግል ዳኝነቱ ለማስነሳት የግድ ዳኛዉ ከአንደኛዉ ተከራካሪ ወገን ጋር ያለዉን ጠንካራ ግንኙነት በጠንካራ ማስረጃ ማረጋገጥ አይጠበቅም፡፡ ዳኛዉ ገለልተኛ ወይም ነጻ ላይሆን የሚችልበት ግምት ለመዉሰድ የሚያስችል ወይም ጥርጣሬን የሚፈጥር አካባቢያዊ ምክንያት መኖሩ ብቻ በቂ ነዉ፡፡ ስለሆነም 2ኛ ተጠሪ መ/ሰጪ ወይም ተጠሪ እንዲሆንና ዝርዝር ክርክር እንዲያቀርብ በማድረግ የክርክሩ ተካፋይ በተደረገበት ሁኔታ በአመልካችና በ1ኛ ተጠሪ መካከል ያለዉን ክርክር የግልግል ዳኛ ሆኖ በገለልተኝነትና በነጻነት መመልከት ስለመቻሉ ጥርጣሬ የሚፈጥር በመሆኑ 2ኛ ተጠሪ ከግልግል ጉባኤ አባልነቱ እንዲነሱ ማድረግ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ዉሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ዉ ሳ ኔ

በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 234067 ሚያዚያ 08 ቀን 2008 ዓ.ም ተሰጥቶ፣ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 180400 ሕዳር 14 ቀን 2009 ዓ.ም በተሰጠ ትዕዛዝ የጸናዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡

2ኛ ተጠሪ በአመልካች በቀረበዉ አቤቱታ ላይ አስተያየት ከመስጠት ባለፈ ዝርዝር ክርክር እንዲያቀርበና በመ/ሰጪነት ተሰይሞ የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን በስር ፍ/ቤት የተደረገ በመሆኑ ከዚህ በኃላ ገለልተኛና ነጻ ሆኖ ጉዳዩን ያየዋል የሚል ግምት ባለመኖሩ ከግልግል ዳኝነት አባልነት እንዲነሳ ተወስኗል፡፡ 1ኛ ተጠሪ በ2ኛ ተጠሪ ምትክ ሌላ የግልግል ዳኛ መምረጥ እንዲችል ተገቢዉ ይፈጸም ተብሏል፡፡

የሰበር ክርክሩ ያስከተለዉን ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡

ሰበር/መ/ቁ 117151

ሕዳር 21 ቀን 2009 ዓ.ም

ዳኞች፡- አልማው ወሌ

ሙስጠፋ አህመድ

አብርሃ መሰለ

አብዬ ካሣሁን

እትመት አሠፋ

አመልካች፡-የመንግሥት ሠራተኞች ማሕበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ...ነ/ፈጅ ሄኖክ መሳው ቀረቡ

ተጠሪ፡-ወ/ር ቸኮል ሙሉጌታ ..... ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል።

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 113138 ሐምሌ 27 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት ባቀረበው አቤቱታ መነሻነት ነው።ተጠሪ ከነሐሴ 01 ቀን 1990 ዓ.ም እስከ ሚያዝያ 30 ቀን 2001 ዓ.ም ድረስ በወንጀል ጥፋተኛ ተብለው በእስር ላይ የቆዩ መሆናቸውን በመጥቀስ ተቋርጦ የቆየው የጡረታ አበል ይከፈላቸው ዘንድ ለአመልካች አቤቱታ አቅርበዋል፤አመልካች በጉዳዩ ላይ የሕግ አስተያየት እንዲሰጥበት አድርጓል፤የአመልካች መሥሪያ ቤት የሕግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ተጠሪ የጡረታ አበል በመቀበል ላይ ያሉት በአስገድዶ መድፈር ወንጀል ጥፋተኛ ተብለው 12 ዓመት ከተቀጡ በኋላ በመሆኑ እየተከፈላቸው የነበረው የጡረታ አበል አግባብ አይደለም፤ለወደፊትም መቋረጥ አለበት የሚል አስተያየት በመስጠቱ አመልካች የተጠሪን የጡረታ አበል ክፍያ አቋርጧል፡፡

ተጠሪ በአመልካች መሥሪያ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለማሕበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ይግባኝ አቅርበዋል።ይግባኝ ሰሚው ጉባኤ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ ተጠሪ በወንጀል ጥፋተኛ ተብለው 12 ዓመት ጽኑ እሥራት የተፈረደባቸው በመሆኑ እና የቀድሞ የጡረታ አዋጅ ቁጥር 5/1967 አንቀጽ 34 የመንግሥት ሠራተኛ በወንጀል ተከሶ ጥፋተኛ መሆኑ በሕግ በተቋቋመ

ፍ/ቤት ከተረጋገጠበት እና ቢያንስ የሦስት ዓመት ጽኑ እሥራት ቅጣት ከተወሰነበት የጡረታ መብቱን ያጣል ወይም በመከፈል ላይ ያለው የጡረታ አበል ይቋረጥበታል የሚል በመሆኑ አመልካች የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው በማለት አጽንቶታል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ይግባኙ የቀረበለት ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካች እና የማሕበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የተጠሪን የጡረታ አበል ለማቋረጥ መሠረት ያደረጉት የአዋጅ ቁጥር 5/1967 አንቀጽ 34 ድንጋጌን ነው፤ሆኖም ይህ አዋጅ በአዋጅ ቁጥር 424/97 እና 714/2003 ተሽሯል፤አዋጅ ቁጥር 714/2003 በወንጀል የተቀጣ ሰው የጡረታ መብት እንደሚያጣ አይደነግግም፤የዚህ አዋጅ አንቀጽ 49/1 ውዝፍ ክፍያ በሦስት ዓመት ይርጋ እንደሚቋረጥ የሚደነግግ በመሆኑ ውዝፍ ክፍያ ለመክፈል አዋጁ ይከለክላል በማለት የተሠጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ሆኖም ተጠሪ የጠየቀው ውዝፍ ክፍያ እንዲከፈለው ሆኖ ሳለ አመልካች የተሻረን አዋጅ በመጥቀስ ተጠሪ ባልጠየቀው ዳኝነት ላይ እየተከፈለ ያለው የጡረታ አበል እንዲቋረጥ በማለት መወሰኑ ተገቢ አይለም በማለት አመልካች እና የማሕበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሰጡትን ውሳኔ በመሻር የተጠሪ የጡረታ አበል ሊቋረጥ አይገባም፤የተጠሪ የጡረታ አበል ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ ይከፈላቸው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ዋና ይዘት፡-ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የአመልካች ውሳኔ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ውሳኔ መስጠት ሲገባው ተጠሪ በጠየቁት የውዝፍ የጡረታ አበል ይከፈለኝ መነሻነት በመከፈል ላይ ያለው የጡረታ አበል እንዲቋረጥ መደረጉ ተገቢ ነው? ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ መስርቶ ውሳኔ መሰጠቱ ተገቢ አይደለም፤በአዋጅ ቁጥር 714/2003 አመልካች *መሥሪያ* ቤት ተጠየቀም አልተጠየቀም በራሱ ተነሳሽነት ምርመራ ካደረገ በኋላ አላግባብ ሲከፈል የተገኘን የጡረታ አበል ሊያስቆም ይችላል፤በጽኑ እሥራት ምክንያት ተከልክሎ የነበረው የጡረታ መብት የተፈቀደው በአዋጅ 907/2007 ነው፤ሆኖም ይህ አዋጅ ውዝፍ የጡረታ አበልን ሳይጨምር ለወደፊት የጡረታ አበል የማግኘት መብት ይኖረዋል በሚል የሚደነግግ እንጂ ውዝፍ ክፍያን የሚፈቅድ አይደለም፤አመልካች የተጠሪን የጡረታ አበል በማቋረጥ ውሳኔ የሰጠው ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ነው፤ተጠሪ የጡረታ አበል መቀበል የሚችሉት አዋጁ በሥራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተጠሪ የጡረታ አበል ተቋርጦ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ እንዲከፈላቸው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ነው፡፡በሌላ በኩል አዋጅ ቁጥር 345/95 እና አዋጅ ቁጥር 714/2003 አዋጆቹ ከመውጣታቸው በፊት የነበሩት ሕጋዊ ሁኔታዎች ተፈጻሚነታቸው እንደሚቀጥል የሚደነግጉ በመሆኑ አመልካች እና ይግባኝ ሰሚው ጉባኤ

የሰጡት ውሳኔ የሕግ መሠረት አለው የሚል ነው፡፡የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለተጠሪው እንዲከፈላቸው የተወሰነው የጡረታ አበል ክፍያ ከአዋጅ ቁጥር 907/2007 አንጻር ለመመርመር ሲባል ጉዳዩ በዚህ ችሎት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎም ግራቀኙ በጽሑፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ  በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው፡፡ይህ ችሎትም እንዲጣራ የተያዘውን ነጥብ በጭብጥነት  በመያዝ የግራቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

አመልካችም ሆነ የማሕበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው የተጠሪ የጡረታ አበል ሊቋረጥ ይገባል ከሚል መደምደሚያ ላይ ሊደርሱ የቻሉት የጡረታ ሕግን አስመልክቶ በወቅቱ ሥራ ላይ የነበሩትን የሕግ ማእቀፎች መሠረት በማድረግ በመሆኑ ተጠሪ በወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ ተብለው ከሦስት ዓመት በላይ ጽኑ እሥራት ቅጣት የተወሰነባቸው በመሆኑ የጡረታ መብታቸው ሊቋረጥ ይገባል በማለት መወሰናቸው ተገቢ ነው፡፡በሌላ በኩል የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አዋጅ ቁጥር 907/2007 ከመውጣቱ በፊት አሥቀድመው ሥራ ላይ የነበሩት የጡረታ ሕግ ማዕቀፎች በወንጀል ጥፋተኛ የተባለ እና ከሦስት ዓመት በላይ ጽኑ እስራት የተፈረደበት  ሰው የጡረታ መብቱን እንደሚያጣ የሚደነግጉ ሆነው ሳላ በሥራ ላይ የነበሩት አዋጆች ከሦስት ዓመት በላይ በጽኑ እስራት የተቀጣ ሰው የጡረታ መብቱን እንዲያጣ አይደነግጉም በማለት የደረሰበት መደምደሚያ ተገቢ ኖኖ አላገኘነውም፡፡

አመልካች እና የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤው ውሳኔ ከሰጡ በኋላ አዋጅ ቁጥር 907/2007 ወጥቶ ሥራ ላይ ውሏል፡፡ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 11/9 የጡረታ አበል ተጠቃሚ ሆኖ በወንጀል ጥፋት ምክንያት ከሦስት ዓመት ያላነሰ ጽኑ እስራት ቅጣት ተፈርዶበት የዘለቄታ የጡረታ አበል መብቱን ያጣ ባለመብት ማሻሻያ አዋጁ ከጸናበት ጊዜ ጀምሮ ውዝፍ አበል ሳይጨምር የጡረታ አበል የማግኘት መብት እንደሚኖረው የሚደነግግ በመሆኑ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ለነበሩ የማሕበራዊ ዋስትና ጉዳዮች ተፈጻሚነት ያለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች ለዚህ ችሎት  ባቀረበው ክርክርም አዋጅ ቁጥር 907/2007 ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው ሕግ መሆኑን አምኖ የተከራከረ በመሆኑ ተጠሪ በወንጀል ጥፋተኛ ተብለው ከሦስት ዓመት በላይ ጽኑ እስራት ተፈርዶባቸው የነበረ እና አስቀድመው በሥራ ላይ በነበሩት ሕጎች የጡረታ መብታቸው የተቋረጠ ቢሆንም በአዋጅ ቁጥር 907/2007 መሠረት የጡረታ ክፍያ የማግኘት መብት አላቸው፡፡ሆኖም የአዋጅ አንቀጽ 11/ 9 የጡረታ ባለመብቱ የጡረታ ክፍያ የማግኘት መብት የሚኖረው ማሻሻያ አዋጁ ከጸናበት ጊዜ ጀምሮ ውዝፍ አበል ሳይጨምር እንደሆነ የሚደነግግ በመሆኑ የተጠሪ የጡረታ ክፍያ ከተቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ እንዲከፈላቸው በማለት

የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ሥሕተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 113138 ሐምሌ 27 ቀን 2007 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተጠሪ የጡረታ አበል በተጠሪ የቋረጠበት ጊዜ በሥራ ላይ የነበሩት የጡረታ ሕግ ማዕቀፎች በወንጀል ጥፋተኛ ተብሎ ከሦስት ዓመት በላይ ጽኑ እስራት የተፈረደበት ሰው የጡረታ መብቱን እንደሚያጣ አይደነግጉም በማለት የሰጠው የውሳኔ ክፍል እና የተጠሪ የጡረታ አበል ክፍያ ከተቋረጠበት ቀን ጀምሮ እንዲከፈላቸው በማለት የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡
3. የተጠሪ የጡረታ አበል ሊቋረጥ አይገባም በማለት የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ጸንቷል፡፡
4. ተጠሪ የጡረታ አበል ክፍያ የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅን ለማሻሻል የወጣው አዋጅ ቁጥር 907/2007 ከጸናበት ከሐምሌ 01 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ይከፈላቸው ብለናል፡፡
5. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሩ/ለ

የሰ/መ/ቁ.122258

ሚያዚያ 30 ቀን 2009 ዓ/ም

ዳኞች፡- ዓሊ መሀመድ

ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ

ቀነአ ቂጣታ

ፀሀይ መንክር

አመልካች፡- አቢሲንያ ባንክ አክሲዮን ማህበር የቀረበ የለም

ተጠሪ፡-የኤ.ፌ.ድ.ሪ የግል ድርጅት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ የደቡብ ሪጅን ፅ/ቤት - ነገረፈጅ ወንድወሰን ፀጋዬ- ቀረቡ

መዝገቡ መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል ፡፡

ፍ ር ድ

1. ጉዳዩ በዕዳ አከፋፈል ሂደት አከፋፈል ሂደት የቀደምነት መብት አከባበር ላይ የተመሰረተ ክርክር ሲሆን የጀመረው በደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል የሐዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በስር ተጠሪ ከሳሽአመልካች ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ባቀረበው ክስም በአዋጅ ቁጥር 715/2003 አንቀጽ 9(1)መሰረት ውዙፍ የጡረታ መዋጮ ያላቸው ድርጅቶች ንብረት ከፍርድ ቤት ወጪ በሆነ መንገድ በመሸጥ ገቢ የማስድረግ ስልጣን እንደተሰጠው፤ ብሉናይል የተባለው ሆቴል ንብረትነቱ የአቶ ታምራት ሙሉ ምትኩ የሆነ ድርጅት ህንፃ በአሁኑ አመልካች አማካኝነት በአዋጅ ቁጥር 97/1990 ከፍርድ ቤት ውጪ በ29/07/2007 ዓ/ም የሽያጭ ጨረታ ተከናውኖበታል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ድርጅት ከ 82 ሠራተኞች ተሰብስቦ ያልተከፈለ ብር 443,519.57 የጡረታ መዋጮ ዕዳ አለበት፡፡ በአዋጅ ቁጥር 715/2003 አንቀፅ 11(12)የጡረታ ዕዳ ከማንኛውም ዕዳ ቅድሚያ የሚሰጠው በመሆኑ የድርጅቱ ህንፃ ሽያጭ እንደፀደቀ ተጠሪ ከሽያጭ ገንዘቡ አስቀድሞ የጡረታ ዕዳውን ለአመልካች ገቢ እንዲያደርግ ትዕዛዝ ይሰጥልን ሲል ዳኝነት ጠይቋል፡፡
2. የአሁኑ አመልካች በቀረበው የመከላኪያ መልስ በአዋጅ ቁጥር 97/1990 በተሰጠው ሥልጣን መሰረት የመያዣ ንብረት የመሸጥ መብት እንዳለው፤ የፍ/ሕ/ቁ/3054 የቀድምትነት መብት

እንደሚሰጠው፤ አመልካች የመያዝ መብቱ በ2000ዓ.ም ያቋቋመ በመሆኑ እና አዋጅ ቁጥር 715/2003 አንቀፅ 57(1) ቀደም ሲል ሲሰራባቸው የነበሩ እንደመሆናቸውን ስለሚያመለክት፤ ገንዘቡም ከህዝብ የተሰበሰበ ከመሆኑ አንፃር የማይመለስ ከሆነ ከፍተኛ ተጽዕኖየሚያሳድር ስለመሆኑ፤ የገንዘብ መጠኑም በገለልተኛ ባለሙያ ያልተጣራ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም የሚል ክርክር ያቀረበ ሲሆን የድርጅቱ ባለቤት የተባሉት ግለሰብ በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረት በ20/12/2007 ዓ/ም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/40(2) መሰረት ወደ ክርክሩ እንዲገቡ አዞ በማረሚያ ቤት በኩልመጥሪያ የደረሣቸው ቢሆንም ወደ ክርክሩ መግባት እንደማይፈልጉ የገለጹ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ አልፎታል፡፡

3. የስር ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር ከመረመረ በኋላ የአሁኑ ተጠሪ የሚጠይቀው የጡረታ መዋጮ ምን ያህል ነው? የሚለው በክሱ 443,519.57 መሆኑን መግለጹን፤ የድርጅቱ ባለቤት ወደ ክርክሩ እንዲገቡ መጥሪያ የተላከ ቢሆንም ወደ ክርክሩ አልገባም ያሉ በመሆኑ ተጠሪ ያቀረበው ውዝፍ የጡረታ መዋጮ አልተስተባበለም፡፡ የቀደምትነትመብት ያለው ማንነው? የሚለው ነጥብ በተመለከተም የሁለቱም አዋጆች ይዘት እንደመረመረ፤ የጡረታ ዕዳ ከማንኛውም ዕዳ ቅድሚያ ሊከፈል የሚገባ መሆኑን አዋጅ ቁጥር 715/2003 የሚገልጽ ስለመሆኑ ይህ አዋጅም ከአዋጅ ቁጥር 97/1990 ዓ.ም በኋላ የወጣ ህግ ከመሆኑ አንፃር ተጠሪ በተያዘው ንብረት ላይየቀዳሚነት መብት ያለው መሆኑ የሚያሳይ በመሆኑ የቀደምትነት መብት አለው ሲል ፍርድ ሰጥቷል፡፡ የአሁኑ አመልካች በስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘትለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ቅሬታውን ያቀረበ ቢሆንም ተቀባይነት አላገኘም ፡፡

4. የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔበመቃወም ለማሳረም ነው፡፡አመልካች በሰበር አቤቱታው የተጠሪ ክስ ጨረታው ከተካሄደና ገንዘቡ ለዕዳ መክፈያ ከዋለ በኋላ የቀረበ ነው፡፡በአዋጅ ቁጥር 97/1990፣ ፍ/ሕ/ቁ/3059 መሰረት ቀደምትነት መብት እንዳለው፤ የደቡብ ክልል ፍርድ ቤት ውክልና ሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 322/2005 እንደተነሳ፣ የጡረታ መዋጮ መጠኑም ሊጣራ ይገባ ነበር የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡ የአመልካች አቤቱታ ከተመረመረ በኋላ በዚህ ጉዳይ በግራ ቀኙ እያከራከረ ያለው የቅድሚያ መብት ጥያቄ ሊታይ የሚገባው በአዋጅ ቁጥር 97/1990 ነው፡፡ ወይስ አዋጅ ቁጥር 715/2003? የሚለውን ነጥብ ተጠሪ ባለበት ይጣራ ዘንድ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ያስቀርባል የተባለ ሲሆን ተጠሪም በሕጉ አግባብ ጥሪ ተደርጎለት ቀርቦ ጨረታ ከተካሄደና ለዕዳ መክፈያ ከዋለ በኋላ የቀረበ ክስ ነው የሚለው በስር ፍርድ ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር ስለመሆኑ፤ የጡረታ መዋጮ ከማንኛውም ዕዳ ቅድሚያ እንደሚሰጠው፤ዕዳው አልተካደም ተከፍሏል የሚል ማስረጃ ብቻ በማስቀረብ የሚሰተባበል ከመሆኑ አንፃር የአመልካች

ክርክር ተገቢነት እንደሌለው፤ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የውክልና ስልጣንም እንዳልተነሳ በመግለጽ አቤቱታው ውድቅ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡ የመልስ መልስም ቀርበዋል፡፡

5. ከሥር የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በጽሑፍ ያደረጉት ክርክር ለሰበር አቤቱታ መነሻ ከሆነው ውሳኔና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ እንዲሁም ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ሊቀርብ ከተያዘው ጭብጥ አንፃርበስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስሕተት መፈጸም አለመፈጸሙን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው የቀደምትነት መብት ባደረገው የመያዣ ውል ያረጋገጠ በመሆኑየአሁኑ ተጠሪ የጡረታ መዋጮ ዕዳ የመሰብሰብ የቅድሚያ መብት አለው ተብሎ የተሰጠው ፍርድ ተገቢ አይደለም በሚል ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አዋጅ ቁጥር 715/2003 ዓ.ም የጡረታ ዕዳ ከማንኛውም ዕዳ ቅድሚያ እንደሚሰጠው በግልፅ የተደነገገ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ የሚነቀፍ አይደለም በማለት መከራከሩን ተገንዝበናል፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታው የተጠሪ ክስ ጨሪታው ተከናውኖ ዕዳው ከተከፈለ በኋላ የቀረበ ነው በማለት ያቀረበው ክርክር ተጠሪ በሰጠው መልስ ክርክሩ በስር ፍ/ቤት ያልተነሳ አዲስ ክርክር ነው ውድቅ ሊደረግ ይገባል ብሏል፡፡ ከመዝገቡ እንደተረዳነው አመልካች በሥር ፍርድ ቤት በዋናነት ያቀረበው ክርክር በአዋጅ ቁጥር 97/1990 የቀደምትነት መብት እንዳለው፤ የአዋጅ ቁጥር 715/2003አንቀጽ 57/(1)ቀደም ሲል ሲሰራባቸው የነበሩ ተፈፃሚ ናቸው ስለሚል የተጠሪ የቀደምነት መብት አግባብነት የለውም በሚል ነው፡፡ ከዚህ አንፃር አመልካች በስር ፍርድ ቤት የክርክር አካል ያላደረገው ጉዳይ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት በአዲስ መልክ ሊያነሳ እንደማይችል የፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ/329/1/ በግልጽ ደንግጓል፡፡ የፍርድ ቤት ስልጣንም በተመለከተም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ የሚመለከተው /originaljurisdiction/ ስልጣኑ የተነሳ መሆኑ ግልጽ ቢሆንም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመወከል የሚመለከተው ጉዳይ የውክልና ስልጣን ያልተነሳ በመሆኑ ክርክሩ የህግ መሰረት የለውም ብለናል፡፡

6. አመልካች ከስር ፍርድ ቤት ጀምሮ ባነሳው ክርክር በአዋጅ ቁጥር 97/1990 የቀደምነት መብት ያቋቋመ በመሆኑ የተጠሪ ጥያቄ ውድቅ ሊያደርግ ይገባል ብሏል፡፡ ተጠሪም የአዋጅ ቁጥር 715/2003 አንቀጽ 11/12/ የቀደምትነት መብት እንደሚሰጠው ተከራክሯል፡፡ አመልካች በውል የቀደምትነት መብት ማቋቋሙ ያከራከረ ጉዳይ አይደለም፡፡ ተጠሪም ብሉናይል ከተባለው ሆቴል ያልተሰበሰበ የሰራተኞች የጡረታ መዋጮ እዳ እንዳለው አረጋግጧል፡፡ አመልካች እና ተጠሪ ብሉ ናይል በተባለው ሆቴል ላይ የፍርድ ባለመብት መሆናቸው ያከራከረ ነጥብ አይደለም፡፡ አከራካሪ የሆነውን መሰረታዊ ነጥብ የዕዳው አከፋፈል ቅደም ተከተል ነው፡፡ አመልካች ከውል የመነጨ የመያዣ መብት ያለው ሲሆን

ተጠሪም በህግ የተረጋገጠ የቀደምትነት መብት አለው፡፡ የስር ፍርድ ቤት አዋጅ ቁጥር 715/2003 ከአዋጅ ቁጥር 97/1990 በኋላ የወጣ መሆኑን የተጠሪ ቀደምትነት መብት ለመወሰን እንደአንድ መነሻ የወሰደው ቢሆንም ጉዳዩ መታየት ያለበት ህጎች ከወጡበት ጊዜ አንፃር ሳይሆን በክርክሩ ለተያዘው ጉዳይ ልዩ ህግ /special law/ የትኛው ነው? በሚል መሆን ይገባው ነበር፡፡ የስር ፍርድ ቤት በዚህ ረገድ የደረሰበት መደምደሚያ ተገቢነት ያለው አይደለም፡፡ ወደ አከራካሪው ነጥብ ስንመለስ አዋጁ ቁጥር 97/1990 ባንኮች በመያዝ የተያዠ የተያዙ ንብረቶች የሚሸጡበት ስርዓት የሚደነግግ ነው፡፡ አዋጅ ቁጥር 715/2003 የግል ድርጅትሰራተኞች ጡረታ አዋጅ የሚመለከት ሲሆን በአዋጅ አንቀጽ 11/12/" የጡረታ መዋጮ ክፍያ ከማንኛዉም እዳ ክፍያ ቅድሚያ ይኖርዋል፡፡ በማለት የደነገገ ሲሆን የእንግሊዘኛ ትርጉም the payment of contribution shall have priority over any debt``በማለት ተገልጸዋል፡፡ ከዚህ የምንረዳው የተጠሪ የቀደሞትነት መብት በግልጽ በልዩ ህግ የተመለከተ መሆኑ ነው፡፡ አመልካች የአዋጅ ቁጥር 715/2003 አንቀጽ 57/1/ በመንቀስ የተከራከረ ቢሆንም አቋቋምኩት የሚለው የቀድምትነት መያዣ መብት የሚደግፍ ድንጋጌ ሆኖ አልተገኝም፡፡ ስለሆነም የአሁኑ ተጠሪ በልዩ ህጉ የጡረታ መዋጮ ክፍያ ከማንኛውም እዳ ቅድሚያ እንደሚሰጠው መሰረት በማድረግ ያቀረበው ክርክር የህግ መሰረት ያለው ነው ብለናል፡፡ የአሁኑ አመልካች በመያዣ ውል አቋቆምኩት ከሚለው የቀደምትነት መብት ይልቅ በልዩ ህግ የተቋቋመው የቀደምትነት መብት ለተጠሪ ቅድሚያ የሚሰጠው ነው፡፡ በዚህ ሁሉ ምክንያት የስር ፍርድ ቤቶች የአሁኑ ተጠሪ ብር 443,519.57 የጡረታ መዋጮ እዳ በቅድሚያ እንዲከፈለው የሰጡት ፍርድ ህጉን በአግባቡ ተፈጻሚነት አድርጓል ከሚባል በስተቀር መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በደ/ብ/ብ/ህ/ክልል የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 17653 በ11/02/2008 ዓ/ም የሰጠው ፍርድ፤ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁ/67034 በ19/04/2008 ዓ/ም የሰጠው ውሳኔ ጸንቷል፡፡
2. የዚህ ፍርድ ቤት ክርክር ያስከተለው ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ የየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡
3. የዚህ ፍርድ ቤት ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይተላለፍ ብለናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት በ16/05/2008 ዓ/ም የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ዘግተን ወደ መ/ቤት መልሰናል፡፡ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡